A74-1
10.00
5.11.99

# የጽሑፍ ጥበብ መመሪያ

ከዳኛቸው ወርቁ

ኩራዝ አሳታሚ ድርጅት
የመጀመሪያ እትም ፲፱፻፹፯
KURAZ PUBLISHING AGENCY
1995

- ማራቶን ........ 73
- ቃላት ያጥሩኛል ........ 78
- ሰበካ ........ 79
- መመፃደቅ ........ 80
- ጥቅልና ረቂቅ ........ 81
- የዓነ ሰውኛ ........ 88
- የባእድ ቋንቋ ፈሊጥ ........ 89
- ፀያፍ ........ 90
- ማጠቃለያ ........ 90

**ምእራፍ ሶስት ፤ አረፍተ ነገር** ........ 98
- የአረፍተ ነገር ክፍሎች ........ 98
- የአገባብ ስልቶች ........ 100
  - በአገልግሎታቸው ........ 100
  - በሰዋሰዋዊ ቅርፃቸው ........ 102
  - በኪነ-ፅሁፋዊ ቅርፃቸው ........ 103
  - በልጨኛ ቅርፃቸው ........ 104
  - በቅርፅ ውዴታቸው ........ 111
- ማጠቃለያ ........ 116

**ክፍል ሁለት ፤ አንቀፅና ድርሰት**

**ምእራፍ አራት ፤ አንቀፅ** ........ 121
- ማቀናበሪያ ስልቶች ........ 122
  - የአንድነት ስልት ........ 123
  - የዝምድና ስልት ........ 126
  - የደልዳላነት ስልት ........ 140
  - የቅርፅ ልክኛነት ስልት ........ 142
  - የማሳደጊያ ስልት ........ 142
    - የትረካ አንቀፅ ፤ በጊዜ ተከታታይነት ........ 143
    - ሁለገብ አንቀፆች ........ 144
    - በስፍራ ወሳኝነት ........ 144
    - በምክንያታዊ (ሎጂካዊ) ተዛምዶ ........ 144
    - በምሳሌ ወይም በማስረጃ ........ 150
    - በምስል መከሰቻ ........ 151
    - በበርካታ ምክንያት ........ 152
    - በምክንያትና ውጤት ........ 155
    - እንዳለ ወይም ለዋውጦ ከመደጋገም ........ 157
    - በማወዳደር ........ 164
    - ምርጫን በማጥበብ ........ 164
    - ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር ........ 166
    - ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ ........ 168
  - የርዝማኔ ስልት ........ 169

**ምእራፍ አምስት ፤ አበይት የአደራረስ አይነቶች** ........ 171
- ተራኪ ድርሰት ........ 171
  - እውናዊ ተራኪ ........ 173
  - ልቦለዳዊ ተራኪ ........ 178
- ስእላዊ (መስተዋታዊ) ድርሰት ........ 183
- ገላጭ ድርሰት ........ 194
  - ትርጓሜ ውሳኔና የገደብ ስልት ........ 195
  - የድልድላ ስልት ........ 201
  - የአብነት ስልት ........ 206
  - የማመሳሰልና የማነፃፀር ስልት ........ 212
  - የትንተና ስልት ........ 224
- አመዛዛኝ ድርሰት ........ 228
- የሞውውት ድርሰት ........ 239

**ክፍል ሶስት ፤ ትረካ — ጥንታዊ ፤ ዘመናዊ**

**ምእራፍ ስድስት ፤ ጥንታዊ ትረካ** ........ 249

**ምእራፍ ሰባት ፤ ዘመናዊ ትረካ** ........ 267
- ትልም ........ 247
  - የጊዜ ገደብ ........ 267
  - ነባር መጻረጊያዎችና ሁነቶች ........ 268
  - የድርጊት ፤ የሁነታዎችና የመጻረጊያዎች አመራረጥ ...279
- ትልምና ሂደቱ ........ 284
- ትልም ከባለታሪኮች ጋር ያለው ዝምድና ........ 287
- የትልም ጥድፊያና ዘገምታ ........ 288
- ትልም ለስሜት ፍንጠቃ ፤ ለሰበካ ፤ ለፕሮፓጋንዳ ፤ ለስሜትና ለመልእክት ፤ ........ 292
- የልዓንጠልጣልነትና የግርምታ ስልቶች ........ 293

. ተራኪ ........ 295
. የተራኪ አኳያዎች ........ 296
. በአይን ከማየት አኳያ ........ 296
. ከአእምሮ ልምድ አኳያ ........ 297
. ከፍላጎት ሂደት አኳያ ........ 298
. የተራኪ አይነቶች ........ 300
. የተራኪ ተግባራት ........ 301
. የተራኪ ሀተታና ትርጓሜ ማቅረቢያ ዘዴዎች ........ 304
. የተራኪ ድምፅ ........ 321
. የተራኪ መልእክት ........ 322
. ባለታሪኮች (ገፀ-ባህርያት) ........ 324
. የባለታሪክ አይነቶች ........ 325
. ነጠላ ባለታሪክ ........ 325
. ውስብስብ ባለታሪክ ........ 328
. ባለታሪክ የማቅረቢያ ዘዴዎች ........ 331
. አካላዊ አቀራረብ ........ 331
. ድብልቅ አቀራረብ ........ 332
. ባህርያዊ አቀራረብ ........ 334
. ባለታሪክና አቋሙ ........ 338
. የባለታሪክ ጥምርነት ........ 339
. የትረካ ሜዳ(ዳጀን) ........ 344
. የዳጀን አጠቃቀም ........ 345
. የዳጀን ማቅረቢያ ስል ቶች ........ 345
. አዳራሽ ዳጀን ........ 245
. መነሻ ዳጀን ........ 346
. ስሜት ፈንጣቂ ዳጀን ........ 347
. ሬዛዊ ዳጀን ........ 348
. አእምሯዊና ልቦናዊ ዳጀን ........ 349
. እውነታ ፈንጣቂ ዳጀን ........ 350
. ቅርፅ ........ 351
. ውጫዊ ቅርፅ ........ 353
. ውስጣዊ ቅርፅ ........ 354
. የአፃፃፍ ዘዬ ........ 360
መውጫ ........ 363


# መቅድም

የፅሁፍን ፣ መባያውን፣ የሚለውንና በመጨረሻ ሰዎችን (እንባቢዎችን ወይም አድማጮችን) የሚያስኘውን ነጣጥሎ ፣ እንዲህ እንዲህ እንዲህ ነው ማለቱ ተገቢ ያለ መሆኑን ብዙ ሊቃውንት ያስተምራሉ ። እስከዛሬ ግን ሌላ አማራጭና የተሻለ ዘዴ አላገኙልንም ። ፅሁፍን ስነ ፅሁፍ የሚያሰኘው ዋሀድነቱ ፣ የማይነጣጠል ወጥነቱ መሆኑን እየተረዳንም ሳለ ፣ ለመማር ያህል ፣ መነጣጠላችን አል ቀረም ።

በዚህ መመሪያ ውስጥ በመጀመሪያው ክፍል ፣

(ሀ) አንድ ፀሀፊ በምንድነው ለማለት የሚፈልገውን የሚለው ?

(ለ) በእንዴት ያለ መንገድ ነው ለማለት የሚፈልገው የሚባልለት ?

(ሐ) ለማለት የሚፈልገውን እያለ እንዴት ነው ስሜት ለመፍጠር የሚችለው ? በማለቱ መባያውን በማስመልከት ራሳችንን ጠይቀናል ።

በሁለተኛው ክፍል ደግሞ ፣

(ሀ) መባያው እንዴት ነው ከሚላቸው ጋር ደረጃ በደረጃ የሚዋደደው ?

(ለ) ደረጃ በደረጃ ማዋደጃስ እንዴት እንዴት ያሉ ዘዴዎች አሉ ?

(ሐ) ዘዴዎቹስ እንዴት እንዴት ያሉ ውጤቶች ያስገኛሉ ? በማለት ራሳችንን ጠይቀናል— ውህደትንና እድገትን በማስመልከት ።

በሶስተኛው ክፍል በተለይ በኪነ ፅሁፍ (ስሜት ኮርኳሪ ፅሁፍ) ረገድ ፣ ቋንቋ በመልእክት ማስተላለፊያነቱ ብቻ ሳይሆን በስሜት ኮርኳሪነቱ የሚጠቀምባቸውን ስልቶች በማስመልከት የሚከተሉትን ጠይቀናል ፤

(ሀ) <u>ትረካ ምንድነው ?</u>

የትረካ ዋናዎቹና ደጋፊ አባሎቹ ምንድናቸው ? እንዴትስ ነው እየተዛመዱ የሚጎናጎኑት ?

.ሁነቶች ምንድናቸው ? እንዴትስ ነው አንድነት የሚኖራቸው ?

.ትረካ ከማን ወይም ከነማን ግምባር ነው የሚነገረው ?

.በእንዴት ያለ ትልም ነው ትረካ የሚሰለፈው ? በጊዜ ቅደም ተከተል ወይስ በሌላ ስልት ?

(ለ) <u>ትልም ምንድነው ?</u>

.ትልምን ነጠላ ወይም ውስብስብ የሚያሰኘውስ ?

.ትልምን በያኝ ወይም ብየናውን ለአንባቢ (የሚተው) ቁቁ (ማለትም ደንቾችን የሚከስ አጥፊዎችን የሚቀጣ ወዘተ...) የሚያሰኘው ምንድነው ?

.ትልምን የሰንሰለታዊ ሁነቶች ወይም የተከታታይ ትእይንቶች ውጤት ነው የሚያሰኙት ምንድናቸው ?

.ትልም ሙሉ በሙሉ እየተማዘዘና እየበለፀገ የሚሄደው እንዴት ነው ፣ በከፊል የማይንቀሳቀስ የሚሆነውስ ?



.ትልም ከባለታሪኮች ጋር እንዴት ነው የሚዛመደው ?

(መ) ምን አይነት አቢይና ንኡስ ባለታሪኮች ናቸው በትረካ ውስጥ የሚካፈሉት ?

(ሠ) ባለታሪኮችን የሚያሳስባቸው ማእከላዊ ቅራኔ አላቸው ፣ የላቸውም ?

ካላቸውስ ቅራኔው የሚመሰረተው ፥

.ሰዎች ከተፈጥሮ ሀይል ጋር ባላቸው ቅራኔ ላይ ነው ? ወይስ

.ሰዎች ከሰዎች ጋር ባላቸው ቅራኔ፣ ወይስ

.ሰዎች ከህብረተሰብ ጋር ባላቸው ቅራኔ፣ ወይስ

.በሰው ውስጥ ሁለት ሀይሎች በሚኖራቸው ቅራኔ እና ወይስ

.ከዚህ በላይ የተዘረዘሩት ቅራኔዎች አብሮ አብሮ በመሆን በተገኙበት ቅራኔዎች ላይ ?

(ረ) የባለታሪኮች ባህርያት * እንዴት ነው የሚከሰቱት ?

.በድርጊያ

.በምስል

* ሌላ ማብራሪያ ካልተሰጠ በስተቀር ፣ ባህርያት ስንል የነገሮችን ፣ የሁ ኔታዎችንና የተግባሮችን ምንነት ማለታችን ነው ። ባህርያቱ ጊዜያዊ ልምዶች ፣ በታሪካዊ ወቅት የተከሰቱ ጠባያት ወይም የበለፀገና የደረጁ የ'ነገሩ' የተፈጥሮ ባህርያት ሊሆኑ ይችላሉ ።

.በጭውውት

.በመግለጫ ? እና ወይስ

.በሁሉም ?

(ሸ) የታሪክ ደጃፎች እንዴት ያሉ ናቸው ?

.ተፈጥሯዊ ?

.ታሪካዊ ?

.ማህበራዊ ? ወይስ

.ሶስቱንም ያቀፉ ?

(ቀ) የቱን ያህል ነው የአካባቢው ሁናቴ ወይም ደጃፍ በድርጊያና በባለታሪኮች ላይ ተፅእኖ ያለው ?

(በ) የአፃፃፍ ዘዬና የተራኪ ድምፅ የቱን ያህል ነው የተራኪን ስብእናና አላማ የሚገልፁት ?

(ተ) ትረካ ምን ያስተምረናል ?

.ከደራሲ አዲስ የሆነ አለምን አመለካከት አኳያ

.ከእውነታ አኳያ (ስለ እውነታ)

(ቸ) የኪነ-ፅሁፍ ርባና ምንድነው ? ሰፊው መልእክቱና ሁለንታዊነቱስ ?

ባጠቃላይ በሶስቱ ተደጋጋፊ ክፍሎች የፅሁፍ ጥበባትን አካል አበይት አባሎች በማስመልከት ፣ ጠቋሚና አመልካች ጥያቄዎች ቀርበዋል ። ከሀገራችን ተጨባጭ ሁኔታ ፣ ባህላዊና ታሪካዊ የአፃፃፍ ስልቶች አንፃር እየታዩና እየተዋሃዱ የሚቀርቡትን ኪነ-ፅሁፋዊ መልሶች በመጠባበቅ ።



# መግቢያ

ስእል ይሳላል ። ኪነ-ስእል (ተንቀሳቃሽ ስእልን ጨምሮ) ይነሳል ። ቅርፃቅርፅ ይቀረፃል ። ሀንፃ ይታነፃል ። ስነ-ፅሁፍ ይፃፋል ። ሙዚቃ ይደረሳል ። የመጀመሪያውና ሁለተኛው በቀለም ፣ ሶስተኛውና አራተኛው በልዩ ልዩ ማእደን (እብነበረድ ፣ ድንጋይ ፣ ብረታብረት ወዘተ) ፣ አምስተኛው በቃላት ፣ ስድስተኛው በድምፅ ይጠቀማሉ ። አንዱ በድምፅ ፣ ሌላው በቃላት ስለሚሰራ ፣ ሙዚቃና ስነ-ፅሁፍ ዝምድና የላቸውም አይባልም ። ወይም አንዱ በእብነበረድ ሌላው በቀለም ስለሚሰራ ። የእያንዳንዳቸው ይዘት ፣ ቅርፅ እና መባያ (እንደ ቋንቋና ቀለም አይነቱ ማለት ነው) ይለያይ እንጂ ውስጣዊ ዘዴዎቻቸውና ግቦቻቸው የተመሳሰሉ ናቸው ። ሁሉም ታሪክ ፣ መልእክት እና ቅርፅ አላቸው ። ሁሉም ፣ ይብዛም ይነስ ፣ ቀለም ፣ ድምፅ ፣ ንቅናቄና የመሳሰሉት ማቅረቢያ ዘዴዎች አሏቸው ። ሁሉም አባሎቻቸውን ማሰባሰቢያ ፣ ማነፃፀሪያ ፣ ማመዛዘኛ ፣ ማዛመጃና ለአንድ ግብ ማሰለፊያ ስልቶች አሏቸው ። በነዚህ ስልቶች አማካይነትም ሁሉም በሰዎች አእምሮ ውስጥ ምስል በመፍጠር የተመልካችንም ሆነ የሰሚን ሀሳብና ስሜት ይቀሰቅሳሉ ። በልምዱ ፣ በአሳቢነቱ ፣ በእውቀቱና በአስተዋይነቱ መጠን ። እርካታም ያስገኛሉ ።

እንዲያም ሆኖ ታዲያ ፣ ሁሉም የየራሳቸው ጥንካሬና ድክመትም አላቸው ። የቅርፃቅርፅ ፣ የስእል ፣ የፎቶግራፍ ቅርፅ በግልፅ ይታያል ። ለአእምሮ ባንዴ ለመያዝም ያመቻል ። ባንዴ ከተያዘም እንደየሰዉ እውቀትና ልምድ የሆነውን አይነት ሀሳብ እና/ወይም ስሜት ወዲያው ያስገኛል ። በቃላት የሚገለፀው ቅርፅ ግን ወዲያው አይታይም ። ሰዎ

ቹም ፣ ሁነታዎቹም ፣ ምስሎቹም ቀስ በቀስ ነው የሚከሰቱት ። ቅርፅ የሚያበጁት ። የሚፈጥሩትም ምስልና የሚቀስቅሱትም ስሜት እንደዚያው ። ቀስ እያለ እየተደመረ ሄዶ ነው እግቡ የሚደርሰው ። ለምሳሌ ከኪነ ፎቶ ውስጥ ፊልም ብንወስድ የታሪኩ ተዋንያን ባንዴ ነው የሚከሰቱት ። መልካቸው ፣ ቁመናቸው ፣ ልብሳቸው እና የመሳሰለው ። በፅሁፍ ግን የትየለሌ መግለጫ ያስፈልጋል ። ያውም ቢሆን ላያጠግብ ይችላል ። በዚያ ላይ በፊልም ረገድ ቀጥታ የጀሯችንም ተሳታፊነት አለ ። የተዋንያኑን ድምፅ እንሰማለን ፣ ሙዚቃና የተለያዩ ድምፆች እናዳምጣለን ። በተዋንያኑ የጭውውት ድምፅ አጣጣል ደራሲው ሊያስተላልፈው የፈለገውን መልእክት እናገኛለን ፣ እና እነዚህ ሁሉ ተባብረው ነው የተፈለገውን ሀሳብ እና ስሜት የሚከሰቱት። በፅሁፍ ግን እነዚህን መሳይ ድጋፎች የሉም ። ሁሉም በቃላት ነው የሚገለፁት ። ቃላቱ ደግሞ ቦታ ይፈጃሉ ፣ ጊዜ ያራዝማሉ ። በመከያውም የታሪኩን ሂደት ይጎትታሉ ።

በለሆነም ፣ ፅሁፍም ቢሆን የራሱ የሆነ ጥንካሬ አለው ። ደብዛም ይነስ ፣ በፅሁፍ ውስጥ ፣ ለሌሎቹ ስነ ጥበቦች ብቸኛ መገናኛቸው በሆኑት ዘዴዎች ሁሉ ለመጠቀም ይቻላል ። ቅርፅ በቃላት ይገለፃል ። ቀለምና መጠን በቃላት ይቀረፃል ። ድምፅ በቃላት ይፈጠራል ። እንቅስቃሴ በቃላት ይከሰታል ። እነዚህ — ቅርፅ ፣ ቀለም ፣ መጠን ፣ ድምፅ እና እንቅስቃሴ — ደግሞ ህይወት ያለው ምስል በሰው ውስጥ ይቀሰቅሳሉ ። እና ፣ በጥበብ ከተሰራበት በሚገባ ያወሳዳል ማለት ነው — ቋንቋ ።

እንደ መግቢያ ያህል የሚከተለውን ፅሁፍ እንመልከት — ኪናዊ አፃፃፍ መባያውንና የሚለውን በሚያዋውድ ባዋው ስልቶች ለመጠቀም ያህል ።



« ብን ያለ ዝናብ ያነበንባል ።

የዲሬክተሩን መኖሪያ ቤት በአይኑ እየቃኘ ፣ ዘበኛው ፣ ተማሪዎቹን (አትጎትቱ ፣ ፈጠን ፈጠን በሉ !)እያለ ፣ ትምህርት ቤቱ በረንዳ ላይ ቆሞ ደወሉን ይደውላል ። ተማሪዎች በአራት ረድፍ መሰለፍ ጀምረዋል ። ረድፎቹ እየተሟሉ ሄደው ዲሬክተሩ ቀስ እያለ መጥቶ ከተማሪዎቹ ኋላ እንደ ቆመ ፣ ተማሪዎቹ ወደ ክፍል መግባት ይጀምራሉ ።

«በመጀመሪያው ረድፍ ፊት ለፊት የቆመው ተማሪ ፀጉሩን ያሳደገ ፣ ጠይም ፊቱ ቅጭም ባለ ቁጥር ወደ ጥቁርነት የሚያዘነብል ፣ የግምባሩ በስተቀኝ ጠባሳ ያለበት ነው ። ትራስ አድርጎት ያደረ ይመስል አሮጌ ኮቱ ተጨረማምቷል ። ከእርጅናው ብዛትም ከጥቁርነት ወደ ቡላነት ተለውጧል ። ከኮሌታው እስከ እጅጌው ነትቧል ። ቁልፎቹ ተበጣጥሰዋል ። የክርኖቹ አካባቢ ተቀደው በጥቁር ካኪ እራፊ ተጥፈዋል ። ኪሶቹም (ምናልባት ቆሎ ለመዝገን እኪሱ በሚገቡት የጓደኞቹ እጆች ሊሆን ይችላል) ዳርዳራቸው ተጎልጉሏል ። ውስጣቸውም ተሸነቋቁሯል ። አንዳንዴ ከዶረቱ ቀና ይልና ፣ በመጀነን ፣ ወገቡን በኪሱ እስር በማድረግ ሁኔታ ፣ የሁለት እጅ ጣቶቹን በቀዳዳዎቹ አሾልኮ ታቹን ብቅ ሲያደርጋቸው ይታያል ። የጥቁር ካኪ ቁምጣው ወደላይ እስኪሸበሸብ ። በግራ ብብቱ ጥቂት ደብተሮችና መፅሀፍ ይዟል ። የሚለጥቀው ልጅ ቀላ ያለ ነው ። ረዘም ያለ ሪዛም ፊትና አፍንጫማ ። ቡና መሳይ ካኪና ቦላሌ ለብሷል ። ወደል የቆዳ ቦርሳ አንጠልጥሏል ። ቀጥሎ ያለው ደግሞ ሳቂታ መሳይ ልጅ ቅጠልያ ጃኬትና ቁምጣ ለብሷል ። ጨዋታ ወዳድ ይመስላል ። ፊትና ኋላ የነበሩትን ይጐነታትላል ። ከሱ ኋላ ደግሞ ጥቁር መሳይ የሀዘን ልብስ የለበሰች ልጅ ። ከሙቹ ገብቼ በሚል አስተያየት በረንዳውን የምትመለከት ። ከሷም ኋላ ሌላ

ሴት ። እንደገና ደግሞ ሌሎች ወንዶችና ሴቶች በረድም
ከትትል ።

(አትንተቱ !) እያለ ይጮሃል ዘበኛው ።

«ሁለተኛው ረድፍ ከመጀመሪያው ይለጥቃል ። የመ
ጀመሪያዋ ሴት ናት ። ነጭ ኩታና ቀሚስ የለበሰች ። በወይን
ጠጅ መታጠቂያ ወገቧን ሸብ ያደረገች ። ዘለል ያለ ደል
ዳላ ሰውነት ያላት ። አይኖቿ በተለይ የመንተግተግ ሀይል
ያላቸው ። ቀስ እያለች በትራመድ ወገቧ የሚዘምር የሚመ
ስል — ሳብ ረገብ ቅንጥስ እንደማለት አይነት ። ሁለተኛ
ዋም ሴት ናት ። ቀይና አረንጓዴ ራስ ማሰሪያ አንገቷ ዙሪያ
የጠመጠመች ። ነጭ ሸሚዝ ለብሳ ፣ ቡናማ ሱሪ የታጠ
ቀች ። እየተቻኮለች ተከተለች — ፊቷ የነበረችውን ለመ
ያዝ ወይም ለመቅደም የምትጣደፍ አይነት ። የበረንዳውን
ደረጃ ስትወጣ የሚሳብ መሳሪያዋ ወድቆ ሜዳ ሙሉ አስኪ
ቅጨለጨል ። ከሷ ቀጥሎ ደግሞ ቁመቱ ለግላጋ ፣ ጃኬትና
ቁምጣ የለበሰ ። እልፍ እልፍ ፣ ኋላው ከነበረው ልጅ ጋር
የሚነጋገር ። አረማመዱ ደፋ ደፋ አይነት ። ትክሻ ቀላል
መሳይ ። ከሱ ኋላ ደግሞ አንድ ቦታ እርፍ የማይቆም ።
እኋላው የነበረችውን ልጅ በጉልበቱ ለመጉሸም የሚሞ
ክከረው ። እንደመዝፈንም እንደ ማፏጨትም የሚከጃጀ
ለው ። ከሱም ኋላ እንዲሁ በተከታታይ — በረድም ።

(ፈጠን ፈጠን በሉ !) እያለ ይጮሃል ዘበኛው ።

«ሶስተኛው ረድፍ ትንንሽ ልጆች ። የመጀመሪያው
ልጅ ኮስታራ መሳይ ፣ ቀይና ሰማያዊ ፣ እትከሻው ላይ ነጭ
የሀምሳ አለቅነት ምልክት ያለበት ጃኬት የለበሰ ፤ እጆቻ
ምቹና አንገትጌው በጥቁርና በነጭ ቀለም ክር የተጠለፉ ።
እፍንጫው ደፍጠጥ ያለና አይኑ የጭንቁር የሚያይ — ተን
ኮል የማያጣ የሚመስል ። የሚቁነጠነጥና ባልደረቦቹን



ለማዝዝና ለመገፋፋት የሚሻ ። ከሱ ኋላ ፣ የተቀዳደደ ዥጉ
ርጉር ኮትና ቁምጣ የለበሰ ። ፊቱን የከፋው ። እንባው ፊቱ
ላይ የደረቀ ። ቶሎ ቶሎ ራመድ ይልና ሀምሳ አለቃውን
ሊቀድም ሲችል ፣ ፈራ ብሎ ራሱን ገታ የሚያደርግ ።
ከሱ ቀጥሎ ደግሞ ወይን ጠጅ ቀሚስ የለበሰች ። ባለ ብዙ
አበባ — ቀይና ሀምራዊ ፣ ብጫ ። ፈሪ መሳይና የልብሷ
ፍቅር ያላለቀላት የምትመስል ። ከሷም ኋላ ሌሎች ሴቶችና
ወንዶች በተከታታይ ።

(ፈጠን ፈጠን በሉ !) እያለ ይጮሃል ዘበኛው ።

አራተኛው ረድፍ ውጫጮች ። ቀይ ፣ አረንጓዴ ፣
ሰማያዊ ፣ ጥቁር ፣ ነጭ ፣ ዥጉርጉር የለበሱ ፤ አንዱን ከሌ
ላው ለመለየት የማይቻል ። ጫጫታቸው የማያቋርጥ
የጨረባ ሰርግ ይመስል ።

---

አምስተኛው የትምህርት ቤቱ ዲሬክተር ። የአፈርማ
ካፖርቱን ኮሌታ እጀረ ግንዱ ድረስ አጥፎና በሁለት እጆቹ
ይዞ ፤ ጥቁር ቦት ጫማውን እስከ ጉልበቱ አጋማሽ ድረስ
እጥልቆ ሲጥ ሲጥ እያደረገና ጐንበስ ጐንበስ እያለ በመ
ራመድ (በየክፍላችሁ ፣ በየክፍላችሁ) እያለ በማዘዝ ።

በመጨረሻም ዘበኛውና ደወሉ ።»

ይህ እንግዲህ ኪነ ፅሁፍን ለማሳየት የተጻፈ ነው ።
በይበልጥ እንዲያመለክት የታሰበው ታሪኩን አይደለም ።
ምስልነቱን ነው።በቃላት የተሳለ ምስል መሆኑን ።

በመጀመሪያ ዘበኛውን እናያለን ። በረንዳው ላይ
ቆሟል ። ደወል ይደውላል ። ከዚያ የመጀመሪያውን ረድፍ
ተማሪዎች ሲገቡ እናያለን ። በጥቁር ፣ ደብዛዛና ኮርፋዳ
ቀለም የተሳሉ ናቸው ። ከሳቂታውና ቅጠልያ ከለበሰው
ሶስተኛው ልጅ በስተቀር ቀለምና ብሩህነት አይታይባ
ቸውም ። ሁለተኛው ረድፍ ውስጥ በርከት ያለ ቀለምና

ትርግርግታ ይታያል — «ነጭ ኩታና ቀሚስ ፣ ወይን ጠጅ
መታጠቂያ ፤ የሚንቀገተት አይኖች ፤ ሳብ ረገብ ፣ ቅንጥብ
የሚል ወገብ ፤ ቀይና አረንጓዴ የተሰበጣጠረበት ራስ
ማሰሪያ» ። በዚህ ላይ ፈጣን እንቅስቃሴ ይታይበታል —
«እየተቻኮለች ተከተለች» ፤ «አንድ ቦታ አርፎ የማይ
ቆም» ። ድምፅ ይሰማበታል — «የሂሳብ መሳሪያዋ ወድቆ
ሜዳ ሙሉ እስኪቅጨለጨል ፤ አልፎ አልፎ እኋላ ከነበ
ረው ልጅ ጋር የሚነጋገር ፤ እንደ መዝፈንም እንደ ማፏ
ጨትም የሚከጃጅለው» ።

ሶስተኛው ረድፍ ፣ ከመጀመሪያው ሁለቱ የጐላና የደ
መቀ መሆኑን መዘርዘር አያስፈልግም — በርከት ያሉ
ቀለሞችን የያዘ ፣ የንቅናቄውን ሁኔታ በዝርዝር የሚገል
ፅና በጉልህ የሚታይ የባህሪ አቀራረብ ያለበት ነው ።

አራተኛው ላይ ስንደርስ ግን ፀሀፊው ፅሁፉን ፣ በጣም
በጐላ ቀለም ፣ ጥቃቅን የንቅናቄን ሁኔታ በሰፊው በሚ
ያሳይ ተግባር ፣ ባህሪንም ሙሉ በሙሉ በሚስል መንገድ
ያቀርባል ብለን ስንጠባበቅ ፣ ባላሰብነው ሁኔታ ጨርሶ
ጥቃቅን ነጥቦችን ያሶገደ ፣ መሸጋገሪያ ብቻ የሆነ አንቀፅ
ሆኖ እናገኘዋለን ። ይሆናል ብለን ያሰብነው ሁኔት አልሆ
ነም ። ላልሆነበትም ምክንያት አለው ።

(ሀ) ያላሰብነው አቀራረብ ሲገጥመን ምክንያቱን
ወደ መጠየቅ እናመራለን ።

(ለ) ምክንያቱን ስንጠይቅ ፀሀፊው ያልተለመደ
የመሰለን ነገር በመፍጠር ተግታ ሰጥቶ ፣ ለማስገንዘብ የፈ
ለገውን መንደርደሪያ ሀሳብ እናገኛለን ።

(መ) መንደርደሪያውን ስናገኝ ቀዝቃዛው አገላለፅ
ከበፊቱ የነበሩትን ጉልህ ሁነቶች የበለጠ እንዳጐላቸው
እንገነዘባለን (እንደ ጳመና ግላጭ አይነት ማለት ነው) ።



አምስተኛው ረድፍ ብቻውን የምናየው ጠልጠሉው
ካምርት ነው ። ፊትየለሽ ፣ ደብዛዛ ፣ ከባድ ሸክም የሚመ
ስለው ዲሬክተር ። (በተለይ አስቀድሞ ከተገለፁት ጋር
ሲወዳደር) ድምፁ ማዘዙን እንጂ ትእዛዙ ስራ ላይ
ቢውል ባይውል ግዴለሽ የሚመስለው ።

በመጨረሻም ዘበኛውና ደወሉ ።

እንግዲህ አይኖቻችን ከዘበኛው ጀምረው ፣ ተማሪዎ
ቹን ቃኝተው ፣ ዲሬክተሩን አሳልፈው ፣ ተመልሰው እዘ
በኛው ላይ አረፉ ማለት ነው — ኪናዊ ፅሁፍ ።

ይህን ፅሁፍ ኪናዊ የሚያደርጉት ገፅታዎች አሉት ፤

(ሀ) ቅርፅ አለው ፤ እያንዳንዱ አንቀፅ እንዳለ ከህ
ይወት የተወሰደ ሳይሆን በእቅድ ነው የተዘጋጀው ። አጠ
ቃላይ ፅሁፉም እንዲሁ በእቅድ ፤ ዘበኛውና ዲሬክተሩ
ፊትና ኋላ ፣ ተማሪዎቹ በአራት ረድፍ ፣ በመካከል ።

(ለ) የቀለምና የድምፅ ውህደት አለው ።

(መ) ንቅናቄ አለው — እንደ ልብ ምት አይነት
ህያውነትን በሚያሳይ ድግግሞሽ የተገለፀ ፤ መጀመሪያ
ላይ ፣ ዘበኛው 'አትንተቱ ፈጠን በሉ' ይላል ። ሁለተኛው
ላይ 'አትንተቱ' ብቻ ነው የሚለው ። ሶስተኛው ላይ 'ፈጠን
ፈጠን በሉ' ። አራተኛው ላይ ያልተጠቀሰው 'አትንተቱ'
የሚለው ቃል ከ'ፈጠን በሉ' ጋር መጀመሪያው ላይ ተጠ
ቅሶ ስለነበር ፣ በመጨረሻዎቹ ላይ ባይጠቀስም ፣ በእእ
ምሯችን አብሮ ነው የሚከሰተው — ተለያይተው ከማያ
ውቁ ጓደኞች አንዱን ባየን ጊዜ ሌላውን እንደምናስ
ታውስ አይነት ።

(ሰ) ንፅፅር አለው ፤ በየአንዳንዱ አንቀፅ የተገለ
ፁት አባባሎች ከበፊታቸው ለሚገኘው ወይም ወደኋላ

ቸው ለሚመጣው ወይም ለሁለቱም ተነፃፃሪ በመሆን በማጉያነት ወይም በማቀዝቀዣነት ነው የተሰለፉት ።

(ረ) ታሪክ አለው ፤ በጊዜ ተከታታይነት ትልም የቀረበ — 'ብን ያለ ዝናብ ይዘንባል ። የትምህርት ቤቱ ዘበኛ በረንዳ ላይ ቆሞ ደወሉን ይደውላል ። ተማሪዎቹም ከየቦታው በመምጣት በአራት ረድፍ መሰለፍ ጀምረዋል ፤ ቀስ እያሉ ። በዘገምተኝነታቸው ዘበኛው አልፎ አልፎ እየገሰፃቸው ። ከዚያም ዲሬክተሩ እንደ መጣ ተማሪዎች በየክፍሉ መግባት ይጀምራሉ' ።

(ሸ) ባለታሪክ አለው ፤ በሶስተኛው አንቀፅ ውጫዊ መልክን ብቻ ሳይሆን ባህሪንም የሚያመለክቱ ጥቆማዎች ስላሉት ።

(ቀ) ደጀንም አለው ፤ የትምህርት ቤቱ ግቢ ፡ ዲሬክተሩ ፥ ዘበኛውና ተማሪዎቹ ።

ባጠቃላይም ፅሁፉ ኪናዊ አቀራረብ አለው ማለት ነው ።

ኪናዊ አቀራረብ ስንል ግን ምን ማለት ነው ? ከዚህ በላይ የተመለከቱትና ሌሎችም የአቀራረብ ቴክኒኮች ያሉበት ፅሁፍ ኪናዊ ስለሚያሰኝ እነሱን ማስገባቱ ፥ ወይም በነሱ መጠቀሙ የፅሁፍን ጥሩነት ያረጋግጣል ማለት ነው ? ሙዚቃ ፥ ስእል ፥ ቅርፃቅርፅ እና የመሳሰሉት በሚጠቀሙባቸው ስልቶች መጠቀሙስ ? ብዙ ደራሲያን በኪናዊ አፃፃፍ በመጠቀም ነው የታወቁ ድርሰቶች ያቀረቡት ? ካልሆነ ለምን እንደክማለን ?

እዚህ ላይ ለጊዜው ጥያቄዎቹን በጥያቄነታቸው እጠነን እናልፋቸዋለን ፤ መመሪያውን ተከታትላችሁ ስትጨርሱ መልሶቹን ከራሳችሁ እንደምታገኙ በመተማመን ።



# ክፍል አንድ

## ሀሳብ ፡ ስሜትና ልምድ

## ቃላትና አረፍተ ነገሮች

ምዕራፍ አንድ

# ሀሳብ ስሜትና ልምድ

## 1.1 ሀሳብ ይዞኛል

ብዙ ጊዜ ስንጫዋወት 'ሀሳብ ይዞኛል' የሚለውን ሀረግ ስንጠቀምበት ይሰማል ፤

'ስለ ስራዬ ሀሳብ ይዞኛል . . .
ስለ ጤንነቴ ሀሳብ ይዞኛል . . .
ስለ ፈተናዬ ሀሳብ ይዞኛል . . .
ስለ እጮኛዬ ሀሳብ ይዞኛል . . . ' ወዘተርፈ . . .

ጠያቂ የለም እንጂ ፣ እንደዚህ ያለው አባባል ሲሰነዘር 'አንተስ ሀሳቡን ይዘኸዋሎይ?' ተብሎ መጠየቅ ነበረበት ፣

'ስለ ስራህ ሀሳብ የሆነብህ ምንድነው ?
ስለ ጤንነትህ የያዘህ ሀሳብ ምንድነው ?
ስለ ፈተናህ ፣ ስለ እጮኛህስ ፣ የያዙህን ሀሳቦች አውቀ ሃቸዋሎይ ?'

ሀሳቡ እሱን የያዘውን ያህል እሱም ሀሳቡን ከያዘው ወዲያው ይነግራችኋል ፣ የሚከተለውን በሚመስል አይነት ፤

'የመኪናዬን ሞተር ማደስ እፈልጋለሁ ፣

ሞተሯን ካወረድሁ በኋላ መለወጫው ባይገኝስ ??'

ወይም

'ውሃ አዘወትሮ ይጠማኛል

ደምና ሽንቴን ካስመረመርኩ ምናልባት ስኳር በሽታ ሆኖ ቢገኝስ ?'

እዚህ ላይ እንግዲህ ሀሳብ የሆነበት ስራው ሳይሆን 'የመለዋወጫ' አለመገኘቱ ፤ ጤንነቱ ሳይሆን ፣ የጤንነት ምርመራ ውጤቱ 'የስኳር በሽታ' ቢሆንስ የሚለው ፍራቻ ነው ።

ሀሳቡ እሱን የያዘውን ያህል እሱ ሀሳቡን አልያዘውስ እንደሁ ? የሚከተለውን በሚመስል አይነት ይገልፀዋል ፤

'እስ አይደለም ፣ ስራ ለመስራት ስትጀምር ፣ ሞተር ደሞ ቀላል ነገር አይደለም ፤ ጋራዥ ስትወስድ ዋጋ ቸው የትየለሌ ? በዚያ ላይ ደግሞ ደህና እቃህን ነው የሚለውጡብህ . . .'

ወይም

'ምን ትላለህ ? ቢያምህስ የትኛው ሀኪም ቤት ነው የምትሄደው ?

ተራ ጠብቀህ ፣ ለዚያውም ደግሞ በሽታህን ቢያውቀልህ . . . አየሩ እንደሁ ከቶኛ ተለዋውጧል ፤ ባንድ ፊት ሙቀቱ ባንድ ፊት ቅዝቃዜው . . ደግሞ ውሃ ማስጠማቱ . . .'

## 1.2 ስሜት ይዞኛል

ስሜት ይዞትስ እንደሆን ? የያዘውን ስሜት በእርግጥ ያውቀዋል ? ለምሳሌ ፣ 'ስሜት ይዞኛል' ይበላችሁ ። የያዘውን ስሜት እሱም ይዞት እንደሆን ለማወቅ ፣



'ምን አይነት ስሜት ነው የያዘህ?' ብላችሁ ትጠይቁት ይሆናል ። በዚህን ጊዜ እሱ ፣ 'ደስ የሚል ወይም የሚረብሽ ስሜት ወይም የሚያስጨንቅ ስሜት . . .' ከማለት ሌላ በእርግጥ ሳያውቀው ይችላል ። እነዚህ መልሶች ግን የያዘውን ስሜት ማወቁን አይገልፁም ።

'ደስ የሚል ስሜት' ነው የያዘው እንበል ለምሳሌ ። ነገር ግን ፣ የትኛው አይነት ደስ የሚል ስሜት !

ጥሩ ምሳ መብላት ደስ የሚል ስሜት ይሰጣል ። ጠላትን መበቀል ደስ የሚል ስሜት ይሰጣል ። ፍቅር ሲይዝ ደስ የሚል ስሜት ይሰጣል ። ስራን ማገባደድ ደስ የሚል ስሜት ይሰጣል ። ጆርባን ሲበላ እከክ እከክ ማድረግ ደስ የሚል ስሜት ይሰጣል ። 'ቆንጆ' ነገር ማየት ደስ የሚል ስሜት ይሰጣል ።

ይኸም ብቻ አይደለም ፤ 'ስላፈቀርሁ ደስ የሚል ስሜት ይዞኛል' ቢልስ ምን ያህል ሊጠቅም ። ያፈቀረው ነገር ምንድነው? ሴት ከሆነች ምንድነው ፍቅር የጣለው ? ምኗን ነው የወደደው ? ምንድነው የሚፈልገው ? ወዘተርፈ . . .

አንዳንዴ ከላይ በተጠየቁት ጥያቄዎች መሰረት ቢብራራም ጠቀሜታ ላይኖረው ይችላል ። ለምሳሌ 'ፍቅር ያስያዘኝ ቁንጅናዋ ነው' ብሎ 'ምን ትመስላለች ?' ተብሎ ሲጠየቅ ፣ 'አይኗ የብር ጉልላት ፣ ሽንጧ የነብር ጅራት ፣ ጥርሷ የበረዶ እምብርት' ወዘተርፈ በማለት ፣ ባልተቀናጁና ምስል በማይከስቱ ንፅፅሮች ሊገልፃት ቢሞክርም እምብዛም አይረዳም ።

በእርግጥ እውቃት እንደሆን ግን ፣ በሚመስል አይነት አገላለፅ ነው የሚጀምረው ፤ 'ረጅም ነች . . . ስትራመድ አከላቷ የሚውረገረግ የሚመስል ፣ ስትጠጋት ጎላ ጎላ ያሉት አይኖቿ ወጥረው የሚይዙህ . . .'

ከማስረጃዎቹ እንደምንመለከተው ፣ ሀሳብ ወይም
ስሜት የያዘው ሰው ሀሳቡን ወይም ስሜቱን ሲይዘው ፣
ሀሳቡ ወይም ስሜቱ ግልፅትና ተጨባጭነት አለው ። ካል
ያዘው ግን የተጠቃለለና የተዝረከረከ ነው የሚሆነው ።

በዚህ አይነት አካሄድ አሳብና ስሜት ምንድነው ?

አሳብና ስሜት ከስራ ፣ ከህብረተሰብ የምርት ግንኙ
ነትና በአጠቃላይ ከሰው ልጅ የእድገት ግስጋሴ ውጤት
እንየር ፣ ከሰው ውስጥም ሆነ ከሰው ውጪ ካለው አለም
የሚመነጭ ባንድ በተወሰነ ቅፅበት የሚጤን አጠቃላይ
ወይም ዝርዝር ክስተት ነው ። ግልፅትና ተጨባጭነት
ሊኖረው ላይኖረውም ይችላል ።

(ለትንተናው ያህል ሀሳብና ስሜትን የለያየናቸው ቢመስ
ልም ፣ አንዳንድ ሀሳቦች እምነቶች ሲሆኑ ስሜታችንን እንደ
ሚነኩና ፣ በሌላው በኩል ደግሞ ስሜቶቻችን ለከቶም ሆነ
ለበጎ ሀሳቦቻችንን እንደሚገዙ ማጤን ይኖርብናል ።)

## 1.3 ልምድስ ምንድነው ?

ልምድ፣ሀሳብና ስሜት በተግባር የሚፈተኑበት መድ
ረክ ነው ። በመሆኑም ልዩ ልዩ ሀሳቦችንና ስሜቶችን
በእያንዳንዱ ሰው የተወሰነ እድሜ ውስጥ ማዳረስ
ያዳግታል ። የስሜት ልምዶችን እንደ ምሳሌ አድርገን
ብንወስድ ፣ የተለያዩ ስሜቶችን — የመበቀል ስሜትን ፣
የማፍቀር ስሜትን ፣ የቅንአት ስሜትንና የመሳሰሉ
ትን — ከሰውነቱ አዋህዶ የሚያውቃቸው በእርግጥ
የደረሰበት ነው — በሀሳብ ደረጃ ሲነገርላቸውና ሲቀ
ረከላቸው የነበሩት ስሜቶች በልምድ ደረጃ ሲገለጡ
ለት ። ሆኖም የእያንዳንዱ ሰው እድሜ አጭር በመሆኑ ፣



አካላዊና ስነልቦናዊ አፈጣጠሩም የተለያየ ፣ ለየልምዱም
አስፈላጊ የሚሆኑት አጋጣሚዎች እስከዚህም ተሟል
ተውለት ሊገኙ ባለመቻላቸው ፣ እያንዳንዱ ሰው በእውናዊው
አለም የሚከሰቱትን ስሜቶች ሁሉ በልምዱ ሊደርስባቸው
ያዳግተዋል ። ከስነ ጥበባት ስራዎች የሚገኘው ልምድ በእው
ናዊው አለም የሚገኘውን በመምሰል ተመሳሳይ ስሜቶች
ሊፈጥርለት (ማለትም ፣ አንድ ግለሰብ ፣ ስለ ቀናተኛ ሰው
በሚያነብበት ወቅት ከተራኪው ኪናዊ አቀራረብ የተነሳ ፣
እስከ ታሪኩ ፍፃሜ ድረስ የቀናተኛውን ህይወት ራሱ እን
ባቢውም እንዲኖረው ሊያደርገው) ቢችልም ፣ ከዚህ መስ
ረተ ሀሳብ በመነሳትም ፣ አንድ ደራሲ አንድ ስሜትን ወይም
ጥቂት ስሜቶችን ለድርሰቱ ማስባሰቢያ አድርጎ በሚፅፍ
በት ወቅት ፣ ደራሲው በተወሰኑ ገፆች ውስጥ ያን ወይም
እነዚያን ስሜቶች እንደሚሰሙ አድርጎ አቀረባቸው እንጂ
በእርግጥ እንደዚያ እንዲሰሙ ለማድረግ የቻለው በእውና
ዊው ህይወት ራሱ ስለ ደረሱበት እንዳልሆነ ለማጤን አያ
ዳግትም ፣ ሊደርሱበትም ላይደርሱበትም ይችላሉ ። እን
ባቢውም ቢሆን በእውናዊው አለም ሊደርሱበት የሚችሉ
ትን አይነት ስሜቶች ተሰሙት እንጂ በሱነቱ በእውናዊው
አለም የሚቀሰቀሱበት ስሜቶች ናቸው አይባሉም — የእ
ውናዊውና የልቦለዳዊው አለም አካላዊና ስነልቦናዊ አካ
ባቢዎች እንዳሉ ተመሳስለው ስለማይገኙለት ። ስለዚህ
በልቦለድ አለም ውስጥ የሚከሰቱ ስሜቶች ሁሉ ከራስ
ልምድ የመነጩ እንዲሆኑ መሻት የሚያዋጣ አይመስ
ልም (ግድያን በታመነ መንገድ ለማቅረብ ገዳይ ሆኖ
መገኘት ስለሚሆን) ። ዋናው ጉዳይ ራስን ባለታሪኩ ባለበት
ኢኮኖሚያዊና ባህላዊ ኑሮ ውስጥ አሸጋግሮ በማጤን ፣
ከዚያ ሁኔታ የሚመነጨውን ድርጊያና የሚከሰትውን

ስሜት ተአማኒነት ባለው መንገድ እማቅረቡ ላይ ነው ። ስለዚሀ በተወሰኑ ገፆች ውስጥ የታቀፈውን በኪነ ፅሁፍ ውስጥ የሚገኘውን ልምድ በእውናዊው አለም ከሚከሰተው ልምድ ለይቶ ማወቅ ተገቢ ሲሆን ፤ ለድርሰት ዋናው ቁምነገር ደግሞ ፣ ሀሳቦችንና ስሜቶችን ከእውናዊው አለም አንፃር ታማኝነት እንዲኖራቸው እማድረጉ ላይ መሆኑን መገንዘብ ያሻል ።

## 1.4 የአሳብ (እሳቤ) እና የስሜት ዝርያዎች

አሳብና ስሜት ሶስት አበይት ዝርያዎች አሏቸው ።

1.4.1 አንድ አሳብ ወይም አንድ ስሜት — በብቸኛነት ፤

1.4.2 አያሌ አሳቦች ወይም አያሌ ስሜቶች — በወል ወይም በውስብስብነት ፤

1.4.3 ከሁለት ወይም ከሁለት በላይ ከሆኑ የተለያዩ አሳቦች ወይም ስሜቶች የተገኘ ግንኙ-አሳብ ወይም ስሜት ፤ እንዲህ አይነቱ አሳብ ወይም ስሜት አንዳንዴ በአለማችን ከታወቁትና ከተለመዱት ነገሮች ውጪ ሊሆን ይችላል — ከእውነታ ውጪ ።

### 1.4.1 ብቸኛ አሳብ (እሳቤ) ወይም ስሜት

(በዚህ ፅሁፍ ውስጥ አጠቃላይ ሀሳብን ባጭሩ ሀሳብ ብለን የምንጠራው መሆናችንንና ዝርዝርና ግልፅ



ሀሳብን ግን 'አሳብ' ወይም 'እሳቤ' እንደምንለው ማጤን ያስፈልጋል ። )

ከላይ እንደተመለከተው ብቸኛ አሳብ ወይም ስሜት አንድ ብቸኛ ነገርን ወይም ባህሪን ፣ ወይም ስሜትን ወይም ድርጊትን ወይም ሁኔታንና ተዛምዶን የሚገልፅ አእምሯዊ ተወካይ ነው ።

(ሀ) የ'ነገሮች' ተወካይ ሲሆን (በስም) ይገለፃል ። (ፋጢማ ፣ ዴሬሳ ፣ ወይራ ፣ ግመል ፣ መብረቅ) ።

(ለ) 'የድርጊት' ተወካይ ሲሆን በግስ ወይም በስም ይገለፃል ።(ስራ ፣ አመረተ ፣ አመራረት ፣ ትግል)።

(መ) 'የስሜት' ተወካይ ሲሆን በስም ወይም በቅፅል ወይም በግስ ይገለፃል ።(የልጅ ፍቅር ፣ ደጦርነት ፍርሃት ፣ የወዳጅ ምቀኛ ፣ የእናት ማልቀስ ፣ የልሀ መንቀጥቀጥ) ።

(ሰ) 'የባህርያት' ተወካይ ሲሆን በቅፅል ወይም በስም ይገለፃል ።(ረጅም ፣ እንጨታም ፣ ድፍን ፣ ሸንትርማ ፣ ቀለማም ፣ ቅርንጫፋም ፣ ዘራም — ከዛፍ ባህርያት ጥቂቶቹ) ።

(ረ) 'የሁኔታና የተዛምዶ' ተወካይ ሲሆን ፣ በተውሳከ ግስ ፣ በመስተዋድድ ፣ በመስተፃምር ወይም በስም ይገለፃል ።(እየፈጠነ ፣ በመሬት ፣ ወደላይ)

### 1.4.2 በተለያዩ ነገሮች ውስጥ የሚገኝ ተመሳሳይ አሳብ ወይም ስሜት በወል ወይም በውስብስብነት

የወል እሳቤ ወይም ስሜት ፣ የጋራ የሆነ አሳብ ወይም ስሜት ከያዙ የተለያዩ ነገሮች ወይም

ስሜቶች ወይም ባህርያት ወይም ድርጊቶች ወይም ሁኔታዎችና ተዛምዶዎች ውስጥ የሚገኘውን አሳቤና ስሜት የሚገልፅ አእምሯዊ ወካይ ነው ። (ወንበር ፣ ፍቅር ፣ እንስሳ ፣ ወጣት ወዘተ ... )

### 1.4.3 ከሁለት ወይም ከሁለት በላይ ከሆኑ የተለያዩ አሳቦች ወይም ስሜቶች የሚገኝ ግንኙ - አሳቤ ወይም ስሜት

እምብዛም ለእውነታ ሳይቸገር ፣ ሌሎች አሳቤዎችን ወይም ስሜቶችን በማጣመድ (በማገናኘት) የሚፈጠር ፣ ከተለያዩ ነገሮች ወይም ባህርያት ወይም ድርጊቶች ወይም ሁኔታዎችና ተዛምዶዎች ውስጥ የተቀናጀውን አሳቤ ወይም ስሜት የሚገልፅ ፣ አእምሯዊ ተወካይ ነው ። (የበረዶ እምብርት ፣ የሀር ነዶ ፣ ቀንዳም አህያ ፣ አገም ጠቀም ወዘተ... )

## 1.5 አሳቤና ስሜት

ስለአሳቤና ስለስሜት ስናወሳ አሳቤው ወይም ስሜቱ የምን አሳብ ወይም ስሜት እንደሆነ ለይተን ማወቅ አለ ብን። በአሳቤውና በሚወክለው ተተኳሪ (ተጨባጭ ማመሳ ሰያ) መካከል ያለውን አንድነትና ልዩነት ማጤን አለብን።


አንድን ነገር ስናይ ፣ በእርግጥ ካጤንነው ፣ ከነተጨ ባጭ ዝርዝሩ እናየዋለን ። አንድ ስሜት ሲሰማን ወይም ሀሳብ ስናስብ ፣ ምንጊዜም ቢሆን ያንን በዚያ ቅፅበት የተሰማንን ልዩ ስሜት ፣ ወይም ያንን በዚያ ቅፅበት የተ ከሰተልንን ልዩ ሀሳብ ፣ ነው የምናጤነው ። ነገር ግን ስለተ ሰማን ስሜት ፣ ስለተገለፀልን ሀሳብ ስናስብ ወይም ስን ናገር ፣ የምንገልፀው በጥቅል ቃላት ነው ፤ (ለምሳሌ —



ልብስ ፣ ደስታ ፣ ውሳኔ ወዘተ ...) ማለትም ፤ አጠቃላይ በሆነ አሳቤ ነው የምንጠቀመው ።

በዚህ ረገድ ስንመለከተው ፣ አንድ አሳቤ ለአያሌ ተተኳሪዎች (ነገር ፣ ባህሪ ፣ ድርጊት ወዘተ...) ቆሞ እናገኘዋለን ።

ለምሳሌ ፣ ‘ልብስ’ የሚለውን አሳቤ ብንወስድ ፣ በአንድ አውቶቡስ ውስጥ ለሚታዩት ፣ በተለያዩ ሰዎች ለተለበሱት የተለያዩ ልብሶች (ተተኳሪዎች) ሁሉ ይቆማል ። በሌላ በኩል ደግሞ ፣ አንድ ተተኳሪም ለአያሌ አሳቤዎች ይቆማል ፤ ለምሳሌ አንድ የብር ማንኪያ እንደ መብያ ፣ እንደ ቅርስ ፣ እንደ ውድ እቃ ፣ እንደ ውብ ነገር ሊታይ ይችላል ። በተጨማሪም ይኸው ቁሳቁስ ጠንካራነትን ፣ ነጭነትን እንዲሁም ከሌሎች እቃዎች ጋር ካለው ተዛምዶ አንፃር የተለያዩ አሳቤዎች ይሰጠናል ። አሳቤ ከተተኳሪውና ከወካዩ ጋር ያለውን ዝምድና በሚከተለው ንድፍ * እንደሚታየው ማስቀመጥ ይቻላል ።




ወካዩ በፅሁፈት እና ወይም በድምፅ የሚገለፀው ቃል ነው ።
(ስለ ወካይና ስለ ተወካዩ ምእራፍ 2 ተመልከት ።)

* ‘የቋንቋ ጎን - ሶስት’ — ከጎምፔርዝ (1908) ።

## ምዕራፍ ሁለት

# ቃላትና የቃላት አጠቃቀም

## 2.1 መግለጫ

### 2.1.1 ቃል (ስያሜ) ምንድነው ?

ቀደም ብሎ እንደ ፣ ተገለፀው ፣ ቃል በአንደበት ወይም በፊደል ምልክትነት የሚገለፅ የሀሳብ ወይም የስሜት ወካይ ነው ።

### 2.1.2 ቃል ወካይ ነው ስንል ምን ማለታችን ነው ?

ቃል ወካይ ነው ስንል ፣ ቃሉ ራሱን ሳልሆኑ ሌላ ነገር ይቆማል ማለታችን ነው ። ለምሳሌ 'ወንበር' የሚለው ቃል መቀመጫ ፣ መደገፊያና አራት እግሮች ላሉት ነገር ይቆማል ። 'ወንበር' የሚለው ቃል ግን በቃልነቱ መቀመጫ ፣ መደገፊያና አራት እግሮች የሉትም ። 'ወንበር' የሚለው ቃል ዋና ተግባሩ ለወንበሩ መቆም ነው ። በዚህ አይነት ወንበር የሚለውን ቃል ወካይ እንለዋለን ። መቀመጫ ፣ መደገፊያና አራት እግሮች ያሉትን ነገር ተወካይ እንለዋለን ። በቃሉና በነገሩ መካከል ያለውን ግንኙነት ውክልና እንለዋለን ።

## 2.2 የቃላት (የስያሜ) አይነቶች

ቃላት በስነ ፅሁፍ ውስጥ ካላቸው ጠቀሜታ አንፃር በአምስት አበይት አይነቶች ይከፈላሉ ፤

2.2.1 ረቂቅ መጠሪያ
2.2.2 ጥቅል (ወል) መጠሪያ
2.2.3 ብቸኛ መጠሪያ
2.2.4 ከቻርጌ (ከተፎ) መጠሪያ እና
2.2.5 የተናጠል (እየቅል) መጠሪያ

## 2.2.1 ረቂቅ መጠሪያ

አያሌ ልዩ ልዩ ነገሮች ፣ አንዱ ከሌላው የሚለዩበቸው ባህርያት እንዳሏቸው ሁሉ ፣ የሚመሳሰሉባቸው ባህርያትም አሉ ። ላባና የጥጥ ንድፍ ባጠቃላይ ሲታዩ የተለያዩ ነገሮች ናቸው ። ግን ዝርዝር ባህርያቸውን ስንመረምር የሚመሳሰሉባቸውም አሉ ። ሁለቱም የ'ቀላልነት' ባህርይ አላቸው ። አበባና ሀርን ብንወስድ ፣ የተለያዩ ነገሮች ናቸው ፤ ሆኖም በ'ልስላሴ' ይመሳሰላሉ ። ዱቄትና አመድም እንዲሁ በብዙ ነገሮች ቢለያዩም ፣ በ'ድቀት' በ'ነጭነት'ና በ'በናኝነት' ይመሳሰላሉ ። እነዚህን ነገሮች በርከት አድርገን አበባን ፣ ሀርን ፣ ላባን ፣ ንድፍን ፣ ዱቄትን ብንወስድም ፣ በርግጥ በብዙ ነገሮች ይለያያሉ ፤ በ'ልስላሴ'ግን ይመሳሰላሉ ። በአጠቃላይ አንድ ነገር በውስጥም ሆነ በውጪ ባህርያቱ ከሌላ ነገር ጋር ሲወዳደር የሚመሳሰልበትና የሚለይበት ባህርያት አሉት ።

እነዚህም ልዩ ልዩ ባህርያት (ቀላልነት ፣ ልስላሴ ፣ ድቀት ፣ ነጭነት) ረቂቅ መጠሪያዎች በመባል ይታወቃሉ ።

ረቂቅ መጠሪያዎች አጠቃላይ ቃላት ናቸው ። 'ቀላል' የሚለውን ቃል ስናስብ አንድ ብቸኛ የሆነ ቀላል ነገር አይታወሰንም ።

ከላይ እንዳየነው ፣
ንድፍ ቀላል ነው ፤
ላባ ቀላል ነው ፤



በተጨማሪም ፣
ፊኛ ቀላል ነው ፤
ባሉን ቀላል ነው ፤
ወረቀት ቀላል ነው ፤
ሌሎችም ብዙ ብዙ ቀላል ነገሮች አሉ ።

ከአያሌ የተለያዩና የማይመሳሰሉ ከሚመስሉ ነገሮች ውስጥ የሚመሳሰሉበትን ፈልፍሎ ማግኘት ቀላል አይደለም ። ባህርያትን መልመድና አዛምዶ ማየትን ይጠይቃል ። ባህርያትን መለየትና አነፃፅሮ ማየትን ይጠይቃል ። ንድፍ ቀላል መሆኑን የሚያውቅ ሰው ፣ ባሉን ቀላል መሆኑን ለማወቅ ሁለቱን ነገሮች በአእምሮው ውስጥ ሊያይቶ ፣ አነፃፅሮና አዛምዶ ማየት አለበት ። የሚመሳሰሉበትን ምክንያት ተረድቶ የማዛመድን (ፈረንጆች ሎጂክ የሚሉትን) ችሎታ ይጠይቃል ።

ረቂቅ መጠሪያዎች የእነዚህ ባህርያት ስሞች ናቸው ብለናል ። ስም ያለው ነገር ደግሞ ሲጠሩት የሚሰማ መሆን ይኖርበታል ። 'ባህርዛፍ' የሚለውን ስም ብጠራ በአእምሮዬ ውስጥ ባህርዛፍ የሆነ ነገር ይታየኛል ። ብቸኛ የሆነ እየቅሉ የታወቀ ነገር ይታወሰኛል ። ነገር ግን ፣ 'ቀላል' ብል ምን ይታወሰኛል ? 'ቀላል' የሚለው ቃል ብዙ ነገሮች ውስጥ የሚገኝ ባህርይ መሆኑን አውቃለሁ ። ይሁንና ፣ በተለይ ራሱ የሆነ አንድ ብቸኛ ነገር አያስታውሰኝም ።

እላይ ከተዘረዘሩት ባህርያት ውስጥ ፣ ለምሳሌ ፣ 'ልስላሴ' የሚለውን መጠሪያ ብንወስድም ይኸንኑ ነው የሚያስገነዝበው ። አበባው ፣ ሀሩ ፣ ላባው ወዘተ... ወዲያው ይከሰቱልናል ማለት አይደለም ። እያንዳንዳቸው ውስጥ ከልስላሴያቸው ይልቅ ሌላው ባህርያቸው አመዝኖ ሊታይ

ይችላል፤ (ለምሳሌ፣ ከአበባ፣ ሽታው፤ ከወር፣ ብልጭልጭነቱ፤ ከላባ ቀላልነቱ ወዘተ...) እንዲያውም እላይ የጠቀስናቸው ቀርተው፣ ያልተጠቀሰ የአንድ የምናፈቅራት ሴት ሰውነት እፊታችን ይደቀን ይሆናል። ወይም ደግሞ፣ እንዳመለካከታችን፣ አምስቱም ነገሮች ከሚመሳሰሉበት ይልቅ የማይመሳሰሉበት እጅግ ጎልቶ ከመታየቱ የተነሳ፣ ጭራሹንም በአእምሯችን ላይመጡ ይችላሉ።

ስለዚህ፣ ረቂቅ መጠሪያዎች ትርጉማቸውን እውን የሚያደርግ አንድ ልዩና ብቸኛ የሆነ ነገር ወይም ተተኳሪ የላቸውም። በአእምሯችን ምስል የመስራት ሀይላቸው ደካማ ነው። ወሰነ ሰፊ የሆኑ ስሜታዊ ቃላት (ሰላም፣ ፍቅር፣ ቁንጅና፣ ፍርሃት ወዘተ...) የሚገኙት እነሱ ውስጥ ቢሆንም፣ የእነዚህ አይነቶቹ ባህርያት ስሜት ቀስቃሽነት የሚከሰተው ከብቸኛ መጠሪያዎች ጋር ሲጣመዱ ነው — ማለትም የእናት አገር ፍቅር፤ የጣይቱ ቁንጅና ወዘተ...

ረቂቅ መጠሪያዎች፣ አንድ አይነት (ተመሳሳይ) ባህርያት፣ አስቀድሞ ከነበሩባቸው እየቅል ከሆኑ (የተለያዩ) ተተኳሪ ነገሮች በምክንያታዊ ተዛምዶ (ሎጂክ) አማካይነት እየተለዩ በመውጣት፣ የጠቅላላ ባህርያት መጠሪያ ስለሆኑ፣ በይበልጥ የሳይንስና ፍልስፍና ቃላት ናቸው።

## 2.2.2 ጥቅል መጠሪያ

ነገሮች (የውስጣችንም ሆኑ የውጭው አለማችን) መጠሪያቸው የሚወጣላቸው እንደ ተገኘ ሳይሆን፣ ስርአትን ተከትሎ መሆኑን፣ እስካሁን ባየናቸው ማስረጃዎች ተመልክተናል። እዚህም የምናየው የተለየ አይደለም። ጥቅል መጠሪያዎች በባህርይ ስም አወጣጥ ስርአታቸው፣ የረቂቅ መጠሪያዎችን ይመስላሉ፤ የቅርብ ዝምድናም አላቸው።



በአብዛኛው የረቂቅም ሆኑ የጥቅል መጠሪያዎች፣ ሁለት አይነት የስም አወጣጥ ስርአት አላቸው። አንደኛው፣ ክፍልፋዩን ከሙሉው አንፃር በመመልከት የሚወጣው ሲሆን፣ ሌላው ደግሞ፣ ዋናውን ዝርያ ወስዶ በወገን፣ በቤተኛ፣ በወላጅ፣ በተዋላጅ፣ በዝምድና የሚወጣ ነው።

ክፍልፋዩን በዋናው አንፃር በመመልከት ለሚደረገው የስም አወጣጥ የሰውን አካል እንደ ምሳሌ ለመውሰድ ይቻላል። የሰው አካል ብዙ ትላልቅ ክፍልፋዮች (አባላት) አሉት። ትላልቅ ክፍልፋዮቹ በውስጣቸው ሌሎች ትናንሽ ክፍልፋዮች አሏቸው። ትናንሽ ክፍልፋዮቹም እንዲሁ በተዋረድ አናሳ ክፍልፋዮች ሊኖሯቸው ይችላል። በዚህ አይነት፣ አንዱን ትልቅ ክፍል ‘ራስን’ ብንወስድ፣ በውስጡ አገጭ፣ አፍ፣ አይን፣ አፍንጫ፣ ጆሮና ሌሎችም አሉ። ቀጥለን ደግሞ ከአነስተኛ አባላቱ አይንን ብንወስድ፣ በውስጡ፣ ብሌን፣ ብሬት፣ ሽፋል፣ ሽፋሽፍት ሌሎችም አሉ።

ዝርያን ወስዶ በወገን፣ በቤተኛ፣ በወላጅ፣ በተዋላጅና በዝምድና አንፃር ለሚደረገው የስም አወጣጥ ደግሞ ተሽከርካሪን በመውሰድ ለማየት ይቻላል። ተሽከርካሪ ብዙ ወገኖች አሉት። በየወገናቸውም እያሌ ቤተኞች አሉ። በየቤተኞቹም ውስጥ እንዲሁ ወላጆችና ተዋላጆች አሉ። በዚህ አያያዝ፣ ተሽከርካሪን ራሱን እንደ ትልቅ ዝርያ ብንወስድ፣ በውስጡ የመሬት ተሽከርካሪ፣ የባህር ተሽከርካሪ፣ የአየር ተሽከርካሪ፣ የህዋ ተሽከርካሪና ሌሎችም ወገኖች አሉ። ቀጥለን ደግሞ፣ ከወገኖቹ ውስጥ የአየር ተሽከርካሪን ብንወስድ፣ ካየር ቀላል ተንሳፋፊ፣ ካየር ከባድ ተሽከርካሪና ሌሎችም ቤተኞች አሉ። ከቤተኞቹ ውስጥ ደግሞ፣ ካየር ቀላል ተንሳፋፊዎቹ ውስጥ እንደ ባሉን አይነቶቹ፣ ከአየር ከባድ ተሽከርካሪዎቹ እንደ አይሮፕላን አይነቶቹ አሉ።

እስቲደመን ጥቅል መጠሪያዎች ከረቂቅ መጠሪያዎች ጋር እንደሚዛመዱ አንስተናል ። በርግጥ አንዳንዶቹ ጠቅላላ ባህርያትን መጠሪያ በመሆናቸው ይዛመዳሉ ። ሆኖም ፣ ጥቅል መጠሪያ የውልደት ተዛምዶ ውጤት እንጂ ፣ በረቂቅ መጠሪያዎች ውስጥ እንዳየነው ፣ የምክንያታዊ ተዛምዶ ውጤት አይደለም ። ተዛምዶቻቸው በመወላለድ በመሆኑም ፣ በአብዛኛው እንደ ረቂቅ መጠሪያዎች ስፋትና ጥልቀት የላቸውም ። ለምሳሌ ፣ እላይ ከጠቀስናቸው ካየር ቀበል ተንሳፋፊዎች ውስጥ ፣ ለጊዜው ከባሉንና ከአየር መርከብ ሌላ የለም ። እንዲሁም በሰው ቤተኛ (ቤተሰብ) ውስጥ ልጃገረድ የሚለውን መጠሪያ ብንወስድ ፣ የከብት ልጃገረድ የአንበሳ ልጃገረድ ስለማንል ውሱንነቱን እንረዳለን ። አጠቃላይም ቢሆን እንደ ረቂቅ መጠሪያ ብዙና ሰፊ ተጠሪዎችን ያቀፈ አይደለም ።

በረቂቅ ባህርያት ፣ በድርጊት ፣ በሁኔታና በተዛምዶ ስም አጠራር ረገድም ስርአቱ ያው ነው ።

ከረቂቅ ባህርያት ፣ ጉብዝና የሚለውን ስያሜ እንደ ዝርያ ምሳሌ ብንወስድ ፣

'የትምህርት ጉብዝና
የስራ ጉብዝና
የነገር ጉብዝና' በማለት ፣ ዝርያው ወደየወገኑ ይዘረዘራል ፤ ሌሎችም እንዲሁ በተዋረድ ።

ከድርጊት በላ የሚለውን ስያሜ እንደ ዝርያ ምሳሌ ብንወስድ ፣

'ቅማል የበላው
አሲድ የበላው
ጥይት የበላው



ነገር የበላው' በማለት ፣ ዝርያው ወደየወገኑ ይዘረዘራል ፤ ሌሎችም እንዲሁ በተዋረድ ።

ከሁኔታና ከተዛምዶ ስያሜዎች እያሌ ፣ ከፍታ ፣ እንደ ዘመድ ፣ የተባሉትን ቃላት እንደ ዝርያ ምሳሌዎች ብንወስድ ፣

'እያሌ ሰው መጣ' ከማለት ፣ 'አምስት (አስር ፣ አምሳ ወዘተ ...) ሰው መጣ' ፤

'ከፍታ አለው' ከማለት ፣ 'አምስት (ሃያ ፣ ሰላሳ ፣ መቶ) ሜትር ቁመት አለው' ፤

'እንደ ዘመድ ነው' ከማለት ፣ 'እንደ ወንድም ፣ እኅት ፣ አባት ወዘተ...' ነው እየተባለ በየወገኑ ይዘረዘራል ።

ስለዚህ ፣ ጥቅል መጠሪያዎችን እውን የሚያደርግ ብቸኛ ተተኳሪ ባይኖራቸውም ፣ በተወሰኑ የነገሮች ፣ የባህርያት ፣ የድርጊት ፣ የሁኔታና የተዛምዶ ዝርያዎችና ክፍልፋዮች መካከል የሚያገለግሉ መጠሪያዎች በመሆናቸው ፣ በአእምሮችን ፣ በተናጠልም ባይሆን ምስል የመከሰት ሀይላቸው ከረቂቅ መጠሪያዎች እጅግ የተሻለ ነው ። ስሜትንም ይነካካሉ ።

ጥቅል መጠሪያዎችም በይበልጥ የፍልስፍና ቃላት ናቸው ።

### 2.2.3 ብቸኛ መጠሪያ

ስለ ጥቅል መጠሪያ ስናብራራ ፣ ከረቂቅ መጠሪያ ጋር ያለውን አንድነትና ልዩነት ለማገናዘብ ሞክረናል ። አሁን ደግሞ ፣ ከብቸኛ መጠሪያ ጋር የሚኖረውን ተዛምዶ እንመረምራለን ።

---

('ለረቂቅና ጥቅል መጠሪያ' የምንባብ ምሳሌ ፣ ከገጽ 81—87 ተመልከት)

### በቅድሚያ ብቸኛ መጠሪያ ምንድነው ?

ብቸኛ መጠሪያ የነገሮች ፣ የባህርያት ፣ የድርጊትና የሁኔታ ተዋላጆች ወይም ሙሉና ክፍልፋዮች በመደብ ፣ በአይነትና እንዲሁም በየእራስ ተለይተው በሚገለፁበት ጊዜ የሚሰጣቸው ስም ነው ።

ለምሳሌ ፣ የተሽከርካሪውን ተዋላጆች በዘረዘርንበት ጊዜ ፣ በተሽከርካሪ ወገኖች ውስጥ የአየር-ተሽከርካሪን ተመልክተናል ። ታዲያንን እነዚህን በመውሰድ ፣ ከብቸኛ መጠሪያዎች አንፃር ስንተነትናቸው ፣ የአየር-ተሽከርካሪ ከዝርያው ከተሽከርካሪው አንፃር ሲታይ ፣ ብቸኛ መጠሪያ ነው ማለት ነው ። ወይም ቤተኛው የሆነውን ፣ ከአየር-ቀላል ተሽከርካሪን ከአየር ተሽከርካሪ ጋር ስናወዳድረው ፣ ከአየር ቀላል ተሽከርካሪ ብቸኛ መጠሪያ ይሆናል ። እንዲሁም ከአየር ቀላል ተሽከርካሪን ፣ ተዋላጁ ከሆነው ከባሉን ጋር ስናነፃፅረው ፣ ባሉን ብቸኛ መጠሪያ ይሆናል ማለት ነው ።

### ከአየር ከባድ ተሽከርካሪዎችንስ ብንወስድ ?

በእነዚህ ረገድም ያው ነው ። አየር ከባድ ተሽከርካሪን ተዋላጁ ከሆነው ከአይሮፕላን ጋር ስናወዳድረው ፣ አይሮፕላን ብቸኛ መጠሪያ ይሆናል ። ሌሎች ማስረጃዎችንም እንውሰድ ፣

እንስሳ ዋና የሆነ የዝርያ መጠሪያ ነው ። የእንስሳ ወገን መጠሪያ የሆነውን ፣ ውሻ የሚለውን ቃል ወስደን እንስሳ ከሚለው ቃል ስናነፃፅረው ፣ ውሻ ብቸኛ መጠሪያ ነው ። ወይም የውሻ ቤተኛ የሆነውን ሶለግን ወስደን ከውሻ ጋር ስናነፃፅረው ፣ ሶለግ ብቸኛ መጠሪያ ይሆናል ። ባይከዳኝ የሚባል ፣ አንድ በራሱ የታወቀን የተለየ ውሻ ወስደን



ከሶለግ ጋር ብናነፃፅረውስ ? አዎ ፣ ባይከዳኝ ብቸኛ መጠሪያ ይሆናል ማለት ነው ። በሌላ አነጋገር ፣ ውሻ ከእንስሳ ሲነፃፀር ብቸኛ መጠሪያ ሲሆን ከሶለግ ጋር ሲነፃፀር የጥቅል መጠሪያ ነው ። ሶለግ ደግሞ ፣ እንዲሁ ከውሻ ጋር ሲነፃፀር ብቸኛ መጠሪያ ሲሆን ፣ ባይከዳኝ (ከሚለው የአንድ ሶለግ ውሻ መጠሪያ) ጋር ሲነፃፀር የጥቅል መጠሪያ ይሆናል ። ባጠቃላይ በጥቅል መጠሪያና በብቸኛ መጠሪያ መካከል ያለው ልዩነት አንፃራዊ ነው ።

ስለዚህ ፣ ብቸኛ መጠሪያዎች ፣ ከጥቅል መጠሪያዎች ጋር አንፃራዊ በሚሆኑበት ወቅት የሚያስገኙት ምስል አጠቃላይ ቢሆንም ፣ ብቸኛ ተተኳሪ በሚያስገኙበት ጊዜ ግልፅ ምስል (ለምሳሌ ባሉን ፣ ባይከዳኝ) ስለሚከስቱ የስሜት አውታሮችን የመነካካት ሀይል አላቸው ።

ብቸኛ መጠሪያዎች የኪነ-ፅሁፍ ቃላት ናቸው ።

## 2.2.4 ከቻርጌ (ምስል ከሳች) መጠሪያ

ከቻርጌ (ከች አድርጌ) መጠሪያ ፣ ከዝርያዎችና ከተዋላጆቻቸው ወይም ከሙሉ ነገሮችና ከክፍልፋዮቻቸው ብቸኛ ለሆኑና ፣ በየእራሳቸው ስም ለታወቁ ነገሮች ፣ ባህሪዎች ፣ ድርጊቶች እና ዝምድናዎች የሚሰጥ መጠሪያ ነው ። ምንም እንኳ ከብቸኛ መጠሪያና ለየእራስ (ለየቅል) ከሚሰጥ ስያሜ ጋር የተቃረበ ቢሆንም ፣ ከቻርጌ የሚለው ስያሜ በእውን ላለ ፣ በመዳሰስ ለሚገኝ ወይም በስሜት ለታወቀ ወይም በልምድ ለተከሰተ ነገር የሚሰጥ አጠቃላይ መጥሪያ ነው ።

ለምሳሌ ፣ ጆሮ ደግፍ ፣ ቀስተደመና ፣ መብረቅ ፣ የምጥ ውጋት ፣ ግሳት ፣ ወዘተ...

ከቻርጌ መጠሪያዎች መኖራቸው የታወቁ ነገሮችን ፣ በእርግጥ የታሰቡ ሀሳቦችን ፣ በእርግጥ በልምድ የተደረሰ

ባቸው ሌሎችንም የታዩና የተገለጡ ባህርያትንና ዝምድ ናዎችን ይይዛሉ ።

ከቻርጌ መጠሪያዎች ተጨባጭ ኑረት ያላቸውን ነገ ሮችን ምስል ይከስታሉ ።

ከቻርጌ መጠሪያዎች ረቂቁን ነገር ግላዊ እንዲሆንና በስሜት አውታሮች እንዲደረስበት ያደርጋሉ ። ደብዛዛን ምስል እውን የማድረግ ሀይል አላቸው ።

ከቻርጌ መጠሪያዎች የኪን-ፅሁፍ ቃላት ናቸው ።

('ለብቸኛና ከቻርጌ መጠሪያ' የምንባብ ምሳሌ ፣ ለልውጤንት የተመቻቹ ባለታሪኮች የሚለውን ከገፅ 340—344 ተመልከት ።)

## 2.2.5 <u>የተናጠል (እየቅል) መጠሪያ ፤</u>

የተናጠል መጠሪያ አንድ ነገር፣ አንድ ሀሳብ ፣ አንድ ባህሪ ፣ ድርጊት ፣ ሁኔታና ዝምድና ፣ ለየእራሱና ለየብቻው የሚታወቅበት መጠሪያው ነው ።

ምኒልክ — የነበረ ፣ ህያው ሰው ፤

ይህ ዛፍ — እትምህርት ቤታችን መግቢያ ላይ በስተቀኝ ያለው ፤

ይህ ቁር — በዚሁ ዛፍ ሁለት ሜትር ላይ የሚገኘው ፤

የዚሁ ዛፍ አወዳደቅ — ኮረንቲ ስለነካ የተቆረጠ እለት ፤

ይህ የልብ ውጋት (አካላዊ) — በተወሰነ ቅፅበት የሚሰማኝ ፤

ይህ የመንፈስ ሁከት (ህሊናዊ) — በተወሰነ ቅፅበት የሚሰማኝ ፤

ይህ እይታ — ከስሜት ህዋሶቼ በአንደኛው የተከሰተልኝ ፤



ይህ እእምሯዊ ምስል — በተወሰነ ቅፅበት የተገለፀልኝ ፤

የተናጠል መጠሪያ ፣ በውስጥም ሆነ በውጪው አለ ማችን ፣ ባንድ በተወሰነ ቅፅበት ያጤንነው ወይም የምናጤነው ማንኛውም ክስተት ነው ። ምንጊዜም ቢሆን መጠሪያው እራሱን (ብቻውን) የሚያደርገው (ያረገው) ወሰን አለው ። ይህ በተጤነበት (በሚጤንበት) ክልል ውስጥ ያለው እሱነቱ ነው እየቅል መጠሪያውን የሚያስገኝለት ።

የተናጠል መጠሪያ የኪን-ፅሁፍ ቋንቋ ነው ።

(በ'ተናጠል መጠሪያ' ለተሰፈ ምንባብ ገፅ 124 ተመልከት ።)

## 2.3 <u>ቃላትና ውክልናቸው</u>

ቃላት አበይት የሆኑ ሶስት የውክልና አሰጣጥ ስልቶች አሏቸው ፤ እነሱም ፥

2.3.1 የግል ትርጉም ውክልና
2.3.2 የአዛማጅ ትርጉም ውክልና
2.3.3 የዘመድ አዝማድ ትርጉም ውክልና ናቸው ።

### 2.3.1 <u>የግል ትርጉም ውክልና</u>

የግል ትርጉም ውክልና የተሰኘው አቢይ ስልት ነጠላ ትርጉም ውክልና እና ድርብርብ ትርጉም ውክልና ያላቸው ሁለት ቅርንጫፎች አሉት ።

#### (ሀ) <u>ግላዊ ነጠላ ትርጉም ውክልና</u>

ግላዊ ነጠላ ትርጉም ውክልና የሚባለው ፣ በቃሉና በተወከለው 'ነገር' መካከል ብቸኛ የሆነ ተተኳሪ ሲኖር ነው ። ቃሉ ወይም ወካዩ የሚቆመው በግልፅ ለተተረጎመና ለተ

ወሰነ እንደ ተወካይ ነው ። ራሱ ቃሉ ፣ ከተወካዩ ጋር
በአንድ አይነት መንገድ ግንኙነት ያላቸውን ወይም የተ
ዛመዱ ሌሎች ነገሮችን እያሳሰብም ወይም እያመለክትም ።
'ወንበር' የሚለው ቃል ድጋፍ ፣ መቀመጫና አራት እግሮች
ያሉትን ነገር ነው የሚወክለው ፤ በተለመደ አገባቡ ቃሉ
የሚቆመው ለዚህ ትርጉም ብቻ ነው ። በወኪልነቱም ለአ
እምሯችን የሚከሰተው ምስል ይኸንኑ ተወካይ ብቻ መሆን
አለበት ።

በቀላል የቃላት አጠቃቀም ደረጃ ፣ በአብዛኛው
ሲታይ ፣ ሳይንስና ፍልስፍና የነጠላ ትርጉም ውክልና
ባላቸው ቃላት የመጠቀም ጥረት ያደርጋሉ ።

ሳይንስ በዝርያና በወገን ወይም በሙሉና በክፍልፋይ
የአሰያየም ስርአት የወጡ ብዙ ስያሜዎች(ቃላትና ሀረግ)
አሉት ። ስያሜዎቹ የሚመሳሰሉ ጥቅል ባህርያትን የሚ
ገልፁ ናቸው ። ጥቅል ባህርያቱ ተጨባጭ ማረጋገጫ
አላቸው ። ተጨባጭ ማረጋገጫዎቹም በሰው ውስጥና ከሰው
ውጪ ባለው አለም ይገኛሉ ። እነዚህን ስያሜዎች
ማወቁ በአለማችን ውስጥ ያሉትን ጭብጦች የማወቅ
ፍላጎታችንን ያሟላልናል ።

<u>እስረጅ ፤</u>

'ዳምትራ ፤ የሚናደፍ ፣ መርዘኛ ፣ ጥቁር ከሰ
ልማ ፣ ባለጠጉር ሸረሪት ።' [1]

'ዳነ ፤ ጤና አገኘ ።' [2]

1,2 ደስታ ተክለ ወልድ ፣ 'ዐዲስ ያማርኛ መዝገበ ቃላት'፥(አ.ኢ. 1962) ፣
ገፅ 362 ።



ፍልስፍና ጽምድን ወደ አሳቤዎች ወይም ስሜት በመ
ለውጥ የተገኙ ብዙ ስያሜዎች (ቃላትና ሀረግ) አሉት ። ስያሜ
ዎቹ የሚመሳሰሉ ረቂቅ ባህርያትን የሚገልፁ ናቸው ። ረቂቅ
ባህርያቱ ምክንያታዊ ተዛምዶ ካላቸው ነገሮች የወጡ ተመ
ሳሳይ ባህርያት የሚታወቁበት አሳቤዎች ናቸው ፤ በአብዛ
ኛው ትርጉማቸውን እውን የሚያደርግ ብቸኛ የሆነ ተተኳሪ
የላቸውም ። ተዋህደዋቸው ከነበሩት የተለያዩ ብቸኛ ተተ
ኳሪዎች ተለይተዋል ። እነዚህን ረቂቅ ስያሜዎች ማወቁ
በአለማችን ውስጥ ለሚኖሩን ልምዶች ርእዮተአለማዊ
አመለካከታችንን የማሳደግ ፍላጎታችንን ያሟላልናል ፤

<u>እስረጅ ፤</u>

'ርእዮተዓለም ፤ በአንድ መደብ ጥቅምና ፍላ
ጎት ላይ የተመሠረተ ኑሮን (ሕይወትን) ትርጉም
መስጫ ፣ መመሪያ ነው ።'

'ንቃተ ህሊና ፤ ከሥራና ከህብረተሰብ የምርት
ግንኙነት የሚመነጭ የነባራዊ እውነታ ነፀ
ብራቅ ነው ።'

'ዝግንነት ፤ ዝግና መኾን ፣ ጉብዝና ፣ ሐርበ
ኝነት ።' [3]

በሌላ አቀራረብ ፣ የነጠላ ትርጉም ውክልና ሲባል ፣
ወካዩ ከአንድ በላይ የትርጉም ውክልና አይኖረውም
ማለት ነው ። ያው አንዱ ውክልና ግን ትክክል ፣ ቀጥታ ፣
ብቸኛና ልክ የሆነ ትርጉም እንዲሆን ያስፈልጋል ።

3 ከላይ ከተጠቀሰው ፣ ገፅ 516 ።

## (ለ) ግላዊ [illegible] ትርጉም ውክልና

በቃላት ውክልና ስልት አንድ ቃል ለተለያዩ አያሌ ተወካዮች ሊቆም ይችላል ። 'አፍ'[4] የሚለው ቃል ለምሳሌ ፤

(1) ከአገጭ በላይ የሚገኝ የሰውነት አባልን
(2) ስለትን
(3) ቋንቋን
(4) ትርጁማንን
(5) ጠበቃን
(6) የሸማ ፈርጅን
(7) ቃልን
(8) ነገርን
(9) ቀዳዳን

ይወክላል ። ይኸም ሆኖ ፤ ቃሉ በአንድ ጊዜ ለአንዱ ተወካይ ብቻ ነው የሚቆመው ። በሚው ወይም አንባቢው የትኛውን ትርጉሙን እንደሚወክል የሚያውቀው ከአገባቡ ነው ፤ አፍ ከሚለው ቃል ጋር ተሳክተው ከቀረቡት ቃላት ።

ቃሉ የሚወክለውን ትርጉም ለመረዳት የሚከተሉትን አረፍተ ነገሮች መመልከት ይቻላል ፤

- በአፉ የሚገባውን መመጠን አለበት ፤ አለዚያ ይታነቃል ።
- የሰይፉ አፍ ቂርቂሩን ቀረደደው ።
- በምን አፍ ነው ያነጋገርከው ፤ በኢጣልያንኛ ነው በእስፓንኛ ?

4 ከላይ ከተጠቀሰው ፤ ገፅ 129 ።



- በቀኑ ቀጠሮህ አፍህን ይዘህ እንድትመጣ ፤ የሚያስተረጉምልህን ።
- በቀን ቀጠሮው አፉን አላቀረበም ፤ ጠበቃውን ።
- የልብሱን አንድ አፍ ብቻ ነው የቋጨሁት ።
- ምን አፍ ትችላለህ ፤ ከውጭ አገር ቋንቋዎች ?
- አንድ አፍ ሳይወጣው ሄደ ።

ስለዚህ አንድ ቃል በአንድ ጊዜ ለአንድ ነገር እስከ ቆመ ፤ ሌሎች ትርጉሞቹን ሳያጎትት ወይም ሳያሳስብ ፤ ከእያንዳንዳቸው ተወካዮች ጋር የሚፈጥረው ግንኙነት ያው ነጠላ ውክልና ነው ። እንደ 'አፍ' ያለው አይነት ቃል እንግዲህ አያሌ የተለያዩ ነጠላ ተወካዮች ናቸው ማለት ነው ያሉት ።

እስካሁን በግል ትርጉም ውክልና ስልት እንደ ተመለከትነው ፤ አንድ ቃል ወይም ወካይ በአንድ ጊዜ ለአንድ ነገር ወይም ተወካይ ብቻ ነው የሚቆመው ። ታዲያ ያው አንድ ነገር የሚቆምለት ትርጉም ጠባብ ወይም ሰፊ መስኮችን ወይም በየውስጡ የሚገኙ ትናንሽ የትርጉም ቀጠናዎችን የሚሸፍን ሊሆን ይችላል ። 'ሚስቱ' የሚለው ቃል ለምሳሌ ፤ በአብዛኛው ለአንድ ተወካይ ብቻ — ማለትም ለአንድ ሰው ነው የሚቆመው ። በሌላ በኩል ደግሞ ፤ ሰው የሚለው ቃልም ለአንድ 'ተወካይ' ነው የሚቆመው ። ነገር ግን ፤ ይህ ቃል ከብዙ ሰዎች ውስጥ ለማንኛውም አንድ ሰው ነው የሚቆመው ፤ ወይም ፤ እንዲያውም 'ሰው ቆሞ አይኖርም' በሚለው አነጋገር ውስጥ እንዳለው አይነት ለሰዎች ሁሉ ይቆማል ። በዚህ አይነት 'ሰው' የሚለው ቃል 'ሚስቱ' ከሚለው ቃል የበለጠ የትርጉም ስፋት አለው እንላለን ፤ የወል ለሆኑ አንድ አይነት ባህርያት ላሏቸው ነገሮች በሙሉ ስለ ቆመ ። ሌሎች

ችም 'ሰው' ከሚለው ቃል ይበልጥ ስፋት ያላቸው ቃላት አሉ ፤ 'እንስሳ' የሚለው ቃል ለምሳሌ በውንና ሌሎች አያሌ የተለያዩ አባላትን ይጨምራል ። 'እንስሳ' ከሚለው ቃል በላይም ሊኖር ይችላል ። ስለዚህ ፣ በግል የትርጉም ውክልና ጊዜ ፣ አንድ ቃል ለአንድ ተወካይ ይቆማል ስንል ፣ ይህ አንድ ተወካይ አንድ ሙሉ ቤተኛን የሚወክል ሰፊ ወይም ጠባብ መስከን የሚያቅፍ ፣ ወይም የቤተኛን ማንኛውንም ወላጅና ተወላላጅ አባል የሚወክል ፣ ሊሆን እንደሚችል ማስታወስ ይኖርብናል ።

## 2.3.2 የአዛማጅ ትርጉም ውክልና

እንዳንዴ በቃሉና በተወካዩ መካከል ያለው ግንኙነት ውስብስብ ይሆናል ። ራሱ ቃሉ ከዋናው ተወካይ ጋር ቤተኛነት ያላቸውን ሌሎች ነገሮችን ለማሳሰብ ፣ እንዲያም ብሎ ለመወከል ይችላል። ቃሉ አሁንም ለአንድ ተወካይ ሊቆም ይችላል ። ጭሰኛ የሚለው ቃል በሰው መሬት ላይ ቤት ሰርቶ የሚኖር ሰውን የሚወክል ነው ። ይህ አንድ የግል ትርጉም ውክልና ነው ማለት ነው ። ሆኖም በዚህ አያበቃም ። በጭሰኛው ላይ ይደርስ የነበረውን ስድብና ግልምጫ ፣ በተፈለገ ጊዜ እንደ እርጎ እቃ መወርወሩን ፣ ልቡ እርፎ የሚኖርበት መጠለያ ያልነበረው መሆኑንና የመሳሰሉትን ሁሉ ያስስባል ። በዚህ አይነት 'ጭሰኛ' የሚለው ቃል ከሚኖረው የግል ትርጉም ውጪ ፣ እንደየሰዉ ልምድ ፣ ቃሉ የሚያሳስበው ወይም የሚያስታውሰው ጠቅላላ የትርጉም አካባቢ የአዛማጅ ትርጉም ውክልና ይባላል ።

በቃላት አጠቃቀም ደረጃ ፣ በአብዛኛው ሲታይ ፣ ኪነ-ፅሁፍ በአዛማጅ ትርጉም ውክልና የመጠቀም ጥረት ያደርጋል ።



የአዛማጅ ትርጉም ውክልና የተለያዩ መልኮች አሉት ፤ ውሱን አዛማጅ ትርጉም ፣ ሰፊ አዛማጅ ትርጉም እና ሁለንታዊ አዛማጅ ትርጉም ይባላሉ ።

### (ሀ) ውሱን አዛማጅ ትርጉም

(1) እየራስ በገጠመን ልምድ መሰረት የምንፈጥረው የግለሰባዊ ልምድ ውጤት ሊሆን ይችላል ፤

አስረጅ 1

'ሊሾ' የሚለው ውርስ ቃል ነጠላ ትርጉሙ የኃማ ጥርስ ማለቅ ነው ። ቃሉን ለሚሰማው ወይም ለሚጠቀምበት ሰው ግን ፣ የአእምሮ ጥርስ ማለቅን ሊያሳስበው ይችላል ። ኃማው በመንገድ ብዛት እንደሚጨረስ አእምሮው በአልኮል የተጨረሰ አይነት ።

(2) በዚሁ አይነት እንዳንዴ በቡድን ፣ እንዳንዴ በቤተሰብ ፣ እንዳንዴ በጎሳ አካባቢ ብቻ የሚሰራባቸውም አሉ ። ለምሳሌ ፣ በቡድን አካባቢ ፓስቴ ፣ አንዱን አባል ፣ ገረሱን ያስታወስ እንደሁ ፣ ገረሱ ፓስቴ ስለሚወድና ስለሚበላ ፤ ወይም በቤቶሰብ አካባቢ ስምቡልጥ የሚለው ቃል አንድ በሬን ያስታውስ እንደሁ ፣ የቤተሰቡ አባት በሚያርስበት ጊዜ በየጊዜው 'ተው ተው ስምቡልጥ — አትለማም ሳብ' ሲል ስለሚሰማ ፤ ወይም በጎሳ አካባቢ በፍርሃት አውጪኝ እግሬ ያለ ሁሉ ፋደት ይባል እንደሁ ፣ ከዚያ በፊት ከጎሳው ውስጥ ይሆን ያደረገ ሰው ፋደት ተብሎ ተጠርቶ ስለነበረ ። የተጠቀሙባቸው ቃላት ፣ 'ፓስቴ ፣ ስምቡልጥ ፣ ፋደት' ፣ የሚያሳስቧቸው 'ነገሮች' ከዚያ ቡድን ፣ ቤተሰብ ወይም ጎሳ ውጪ የተባሉትን 'ነገሮች' ስለማያሳስቡ የመ

ግባቢያነት ሀይላቸው ጠባብ ነው ፤ በሰፊው የጋራ መግባቢያ አይደሉም ።

ይህም ሆኖ ፣ በኪነ-ፅሁፍ ውስጥ አይሰራባቸውም ማለት አይደለም ። ቃላት በአንድ በተወሰነ መፅሀፍ ውስጥ ብቻ የተወሰኑ 'ነገሮችን' እንደሚያስታውሱ ሆነው ይቀርባሉ ፤ ከደራሲው ግምባር ወይም ከአንድ ገፀ ባህሪ ግምባር ። ለምሳሌ ፣ ዝናብ የሚለው ቃል ለአብዛኛው ሰው ልምላሜን ፣ ቡቃያን ፣ የጥጋብ ጊዜን ሲያስታውሰው ፣ አንድ ደራሲ ባለው ያቀራረብ ሀይል አማካይነት ፣ በአንድ መፅሀፍ ውስጥ የጥፋት ፣ የተስፋ መቁረጥ ፣ የጨለማ ህይወት አስታዋሽ አድርጎ ሊያቀርበው ይችላል ። አንባቢም በዚያን ወቅት አጠቃላይ ትውስታውን እረስቶ ውሱን ትርጉሙን ሲከታተል ይገኛል ማለት ነው ።

## (ለ) ሰፊ አዛማጅ ትርጉም

ብዙዎች አዛማጆች ከቋንቋ እድገት ጋር አብረው የበለፀጉ ናቸው ። በዚህ አይነት አንድ ብሄራዊ ቋንቋ በሚናገር አገር ውስጥ ዳብረው ይገኛሉ ። ሌሎች ደግሞ ፣ በጋራ ወይም በህዝባዊ ልምድ ላይ የተመሰረቱ በመሆናቸው በአብዛኛው ሰው የታወቁ ፣ ለአብዛኛው ሰው የሚገቡና ተቀባይነት ያላቸው አሉ ። በእርግጥ የየሰዉ አዛማጅ ትርጉሞች ሙሉ ለሙሉ ተመሳሳይነት ላይኖራቸው ይችላል ። እንዱን ፣ 'ጭሰኛ' የሚለው ቃል የሚያስታውሰው ወይም የሚያሳስበው በባለመሬት መዋረድን ፣ በየጊዜው ከቤት መባረርን ሲሆን ፣ ሌላዉን ከሚያርሰው መሬት መነቀልን ፣ የቤተሰብ መደፈርን ፣ ተገቢ ያልሆነ ኪራይ መክፈልን ፣ ሌላዉን ደግሞ ፣ ያሳደገውን ሙክት መቀማትን ፣ ልጁን ለጭንገረድነት መስጠትን እና የመሳሰሉትን ሊሆን ይችላል ። ሆኖም በያንዳንዱ ሰው ልምድ ውስጥ አዛ



ማጅ ትርጉሙን የጋራ የሚያደርግ በቂ ተመሳሳይነት ስለሚኖር የመግባባት ችግር አይኖርም ።

## (መ) ሁለንታዊ አዛማጅ ትርጉም

የአብዛኛው ሰው ወይም የሰዎች ሁሉ ልምድ ውጤት የሆኑ ጥቅል ወይም ሁለንታዊ አዛማጆችም አሉ ፤ ወሰን የማያግዳቸው ፣ ቋንቋ የማይወስናቸው አዛማጆች ፤

አስረጅ ፤

- 'ባሕር — የውሃ ቦታ ፣ መቆሚያ ፣ መከማቻ ፣ ሰፊ ፣ ጥልቅ ፣ ውሃው የማያልቅ ፣ የማይደርቅ ፤ ስፋቱ ከየብስ የሚበልጥ . . . ።'[5]
- 'ነገደ — ሩቅ አገር ሄደ ፣ ወጣ ወረደ ፣ ገዛ ፣ ሸጠ ፣ ለወጠ ፣ ሸቀጠ ለማትረፍ ።'[6]

ከዚህ በላይ የተሰጡት የባህርና የመነገድ ትርጉሞች ነጠላ ትርጉም ሲሆኑ ፣ በሁለንታዊ አዛማጅ ትርጉማቸው ዘለአለማዊነትንና እድሜን ያመለክታሉ ።

ባጠቃላይ ፣ የአዛማጅ ትርጉም ውክልና ፣ አንድ ቃል ወይም ሀረግ ከመደበኛ ነጠላ ትርጉሙ ውጪ የጎድን በመሄድ ፣ ጥልቅ ስሜትን ለመፍጠር የሚኖረው ስብስብ የአካባቢ ትርጉምና ስሜትን ፈንጣቂነት ነው ።

## 2.3.3 የዘመድ አዝማድ ትርጉም ውክልና

የዘመድ አዝማድ ትርጉም ውክልና የአንድን ቃል የግል ተወካይ ለሌላ ነገር እንዲቆም አድርጎ ማቅረብ ነው ።

---

5,6 ከላይ የተጠቀሰው ፣ ገፅ 161 እና 837 ።

ወንበር የሚለው ቃል መደገፊያ ፣ መቀመጫና አራት እግሮች ላለው ነገር ወካይ ነው ብለናል ። አሁን ደግሞ ፣ ይኸው መደገፊያ ፣ መቀመጫና አራት እግሮች ያለው ነገር ፣ ለአንድ ለሌላ ነገር ወካይ ይሆናል ማለት ነው ። በዚህ ረገድ ፣ ለዳኛ። በዚህ አይነትም ፣ ቃላት ከነጠላ ትርጉማቸው ውጪ የተሳሳበ ትርጉም ኖሯቸው ሲገኝ ፣ የተሳሳበው ትርጉም መጠሪያ የዘመድ አዝማድ ትርጉም ውክልና ይባላል ።

የዘመድ አዝማድ ትርጉም ውክልና ሶስት አበይት መደቦች አሉት ። እነሱም ፣ አወዳዳሪ ፈሊጦች ፣ አነፃፃሪ ፈሊጦችና አጓዳኝ ፈሊጦች ናቸው ።

(ሀ) አወዳዳሪ ፈሊጦች

አወዳዳሪ ፈሊጦች በሶስት ይከፈላሉ ። አንፃር ፣ ተምሳሊት እና ሰውኛ ተብለው ።

(1) አንፃር

አንፃር የሚባለው ማወዳደሪያው በቀጥታ ሲጠቀስ ነው ። ለምሳሌ ፣ 'ፀጉሯ እንደ ሀር ነዶ ነው ።' በዚህ ፈሊጥ ውስጥ የተሳሳበ ውክልና የለበትም ። 'የሀር ነዶው' አሁንም 'የሀር ነዶ ነው' ፤ የገባን ተጨማሪ ነገር ቢኖር ፣ ፀጉሯ ባንዳንድ ነገር የሀር ነዶዉን መምሰሉ ነው ። በልስላሴዉ ፣ በማማሩ ፣ በጥራቱና በመሳሰሉት ።

(2) ተምሳሊት (አምሳያ)

በተምሳሊት ግን አወዳዳሪው በቀጥታ አይገለፅም ። በውስጠ ታዋቂነት ነው የሚታለፈው ። ለምሳሌ ፣ 'ፀጉሯ የሀር ነዶ ነው' ብንል ቀጥታ



ውድድር አይታይበትም ። ውድድሩ ከአገባቡ ቢታወቅም ። በተምሳሊት ፈሊጥ ውስጥ የተሳሳበ ውክልና አለ ። ፀጉሯ የሀር ነዶ አይደለም ። 'የሀር ነዶ' የሚለው ቃል በሚታወቅበት ቀጥታ ትርጉሙ አይደለም እዚህ የገባው ። እርግጥ በዚህ አይነት አነጋገር ውስጥ 'የሀር ነዶ' በአንድ በኩል ለደንበኛ ተወካዩ ሊቆም ይችላል ። ስለሆነም ፣ በሌላ በኩል አሁን 'የሀር ነዶዉ' የቆመው 'ልስላሴው ፣ ማማሩና ጥራቱ' እንደ ሀር ነዶ ለሆነ 'ነገር' ነው ።

(3) ሰውኛ

በዚህ ፈሊጥ ፣ ሰው ያልሆነ ነገር በውስጠ ታዋቂነት ከሰው ጋር ይወዳደራል ። ለምሳሌ 'አበባዎቹ በመስከረም ፀሀይ ፈነደቁ' ቢል ፣ አበቦችን እንደ ህፃናት በመመልከት የተደረገ ውድድር አለ ማለት ነው ።

(ለ) አነፃፃሪ ፈሊጦች

አነፃፃሪ ፈሊጦች በሶስት ይከፈላሉ ። ምፀት ፣ አንስቶ መጣል እና ጥሎ ማንሳት በመባል።

(1) ምፀት (ነገረ ግልባጭ)

በምፀት ውስጥ ቃላቱ የተሳሳበ ትርጉም የላቸውም ። ለውጡ የሚመነጨው ለቃሉ ትርጉም ተቃራኒ የሆነውን ትርጉም ከመውሰዱ ላይ ነው ። ምሳሌ ፣ የስራ ባልደረባችን ፊቱን ጭንንት አስመስሎ ቢጠብቀን ፣ 'ዛሬስ ፊትህ በደስታ ያበራል ፣ ምን አግኝተሃል ?' ብንል ፣

‘በደስታ ያበራል’ ለ‘ጭንንቅ መብሏል — ከፍ ቶሃል’ ፤ ‘ምን አገኘተሃል’ — ‘ምን ደረሰብሀ ? ምን አጣህ ?’ ለማለት ነው የቆሙት ።

### (2) <u>እንስቶ መጣል</u>

እንስቶ መጣል ማለት ፥ በቦታው ለማለት ከተፈለገው ሀሳብ ወይም ስሜት በላይ ቃላቱ አቅፈው የመገኘታቸው ባህሪ ነው ። ማጋነን ቢኖርበትም እምብዛም ማኪያኪያስ ላይኖርበት ይችላል ፤ ‘በንትርክ ልቤን አወለቀኝ’ ቢል ለምሳሌ ፥ ‘ልብ መውለቅ’ የጭቅጭቁን አሰልችነትና ችኮነት አጠናክሮ አቀረበው እንጂ ቀጥታ ትርጉሙን አይመለከትም ፥ ወይም

‘. . . ጥሬ ስጋዬን ትበላዋለች . . .’

‘. . . ጥንቢራችን እስኪዞር ጋበዘን . . .’

‘. . .ልጁን በአልጋ ላይ እንዳለ ገማመ

ጡት . . . , ሳሙት ለማለት ።

### (3) <u>ጥሎ ማንሳት</u>

ጥሎ ማንሳት ማለት ደግሞ ቃላቱ ፥ በቦታው ለማለት ከታሰበው ሀሳብ ወይም ስሜት በታች ያላቸው መስለው መቅረባቸው ነው ፤

ለምሳሌ ፥ ደብረ ብርሃንን የሚያውቅ ሰው ፥ ‘ትንሽ ቅንሽ ንፋስ አለበት’ ቢል ፥ ለማለት ከፈለገው እንዳልደረሰ ይሰማል ።



ባጠቃላይ ፥ በአነጋገሬ ፈሊጦች የመጠቀም ልምድ ፥ በቦታው ለማለት የተፈለገውን መሰረታዊ ሀሳብ ወይም እንዲሰማ የተፈለገውን መሰረታዊ ስሜት ፥ አጠናክሮና የማስማት ሀይሉን አሳድጎ ለማቅረብ ያስችላል ፤ የተባለውንና ለማለት የተፈለገውን ከማገናዘብና ከማጤን የሚደርስበት ትርጉም ስለሆነ ።

### (መ) <u>አጓዳኝ ፈሊጦች</u>

የቃሉ ትርጉም ከግል ተወካዩ ትርጉም ውጪ ፥ ከተወካዩ ጋር ግንኙነት ወዳለው ‘ነገር’ ይዘምታል ።

አጓዳኝ ፈሊጦች በሁለት ይከፈላሉ ፤ ዘማች እና ሙሉ-ከፊል በመባል ።

### (1) <u>ዘማች</u>

ዘማች የሚባለው የቃሉ ትርጉም ከተተኳሪው ጋር ዝምድና ወዳለው ነገር ወይም እሳቤ ሲፈዘም ነው ። ምሳሌ ፥ ‘አልጋው ተገለበጠ’ ፤ ‘መንግስቱ ተገለበጠ’ ለማለት ፥ ወይም ‘በላቡ ነው የሚያድረው’ ፤ ‘በጉልበቱ ስራ’ ለማለት ፤

### (2) <u>ሙሉ - በከፊል</u>

በዚህ ረገድ የአንድ ‘ነገር ’ አባል ለአካሉ እንዲቆም ሲደረግ ነው ።

ምሳሌ ፤ ቤቱ አሸለበ — የቤቱ አውራ ሲሞት ። <u>መሳሪያው</u> ሳተ — ጥይቱ ሳይመታ ቀረ ።

(3) ክፊል በሙሉ

በዚህ ደግሞ ፣ የአንድ 'ነገር' አካል ፣ ለአባሉ እንዲቆም ሲደረግ ነው ።

ምሳሌ — አንድ ሺ እግረኛ አሰለፈ ።

አምሳ ድምፅ አገኘ ።

ድርቅ አመት ።

### (ለ) የዘመድ አዝማድ ትርጉም ውክልና ጥቅሶች

«ነፋሱ ባሕሩን ከተኛበት ቀስቅሶ እንደ ሕፃን በደረቱ ላይ አድርጎ ሲያስጨፍረውና ሲያስቦርቀው ፣ እንቡር እንቡር እያሰኘና እሽሩሩ እያለ ሲያስፈነጥዘውና ሲያቃብጠው ለተፈጥሮ ምን ያህል የቀበጠ ጠባይ እንዳለው የተመልካችን አሳብ በምርመራ ላይ ያውለዋል.........»[7]

«አንዳንድም ጊዜ ማዕበሉ ወደላይ ደንገላሳ እየተነሣ ፣ በመርከቦቹ ላይ ሲቸለስና መርከቦቹ በማዕበሉ ዳልጋ ተሸፍነው ወደ ጥልቁ ሲወርዱ ወይም ሰጥመው ቀሩ ሲባል ተመልሰው በባሕሩ ጀርባ ላይ እንደገና ሲታዩሉ ግሩም ኃይለ እግዚአብሔር ያሰኛል.........»

«አባቶቻችን በደም በለቀለቁት ውድማ ጠላትን በዐይን ቅጽበት ፍጥነት እንደ ማሽላ ርችት ወቁት ... »[9]

«በየዘመኑ የሚገጥማቸውን የጦር ማዕበል እንደ ውሃ ዋናተኛ እየቀደዱ በመሻገር ገናና ታሪካቸውን አድሰዋል ...»[10]

---

7 ወ/ጊዮርጊስ ወ/ዮሐንስ ፣ 'አግዐዚ' አ.አ. (ገፅ) 12 እና 8 ።
9,10 አዲስ ዘመን ፣ ቁጥር 411 (ሚያዝያ 30 1954) ።



## 2.4 ቃላትና ጥብቅናቸው (በስሜት ፈንቅልነት)

እስካሁን ስለ ቃላት የተሰጠው ትችት ኪናዊ ባል ሆኑ ፅሁፎችም ለሚውሉ ቃላት ጭምር መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል ። ለምሳሌ ፣ ከሳይንስ መስክ ፣ ቴክኒካዊ ገላጭ ፅሁፎች እንዲሁም አንዳንድ የፍልስፍና ፅሁፎች በአብዛኛው በጥቅል ፣ በብቸኛና በከቻርጌ ቃላት ይጠቀማሉ ፤ ኪነ-ፅሁፎች የሚጠቀሙበትን ያህል ባይሆንም ።

ከዚህ ቀጥሎ ቃላት በኪነ-ፅሁፍ ውስጥ በስሜት ፈንቅልነት ሲሰራባቸው እንዴት ስሜትን ለመቀስቀስና ለመማረክ እንደሚውሉ እንመለከታለን ።

ቃላት ስሜትን የሚፈነቅሉባቸው ባህርያት ሁለት ሲሆኑ ፣ እነሱም ፣

2.4.1 በአምስቱ የስሜት አውታሮች (የማየት ፣ የመስማት ፣ የጣእም ፣ የሽታና የዳሰሳ) አማካይነት ምስል እየከሰቱ ስሜት የመፍጠር ባህርያቸው ፣ እና

2.4.2 ቃላቱ በቀጥታ ባላቸው ስዋዊ ቅርበት አማካይነት በሚኖራቸው ስሜት የመቀስቀስ ጠባያት ናቸው ።

### 2.4.1 በስሜት አውታሮች አማካይነት

በስሜት አውታሮች አማካይነት በሚከሰቱ ምስሎች ስሜትን ለመፈንቀል የሚጠቀሙ ኪነ-ፅሁፎች ብቻ ሳይሆን ፣ የማስታወቂያና የመቀስቀሻ ፅሁፎች ፣ የፖለቲካ

ዲስኩሮች ፣ ጋዜጣዊ ርእስ አንቀፆች እና የመሳሰሉት ሁሉ ናቸው ። ለእነዚህ አገልግሎት የሚውሉት ቃላትም ከዚህ ቀደም በምስል ከሳችነታቸው የተመለከትናቸው (ጥቅል ፣ ብቸኛ ፣ ከቻርጌና የተናጠል መጠሪያዎች) ቃላት አይነቶች ስለሆኑ ፣ ማንኛውንም ኪነ-ፅሁፍ በምናዘጋጅበት ወቅት ፣ የስሜት አውታሮችን አገልግሎት ባለመርሳት ፣ ምስሎቹ በሚቀሰቀሱባቸው የተተኳሪዎች መጠሪያ ቃላት መጠቀም ያስፈልጋል ።

ባጠቃላይ ፣ የስሜት አውታሮች (ህዋሶች) በተተኳሪዎቹ ተቀስቅሰው ምስል የሚከስቱባቸው ቃላት አይነቶች ፣ ከዚህ በታች የተመለከቱትን ይይዛሉ ፤

(ሀ) <u>የማያ አውታር</u>

በማያ አውታራችን (በአይናችን) አማካይነት የሚከሰቱ ምስሎች ፤

- <u>ቀለም</u> ፤ ምሳሌ (1) በቀለምነቱ — አረንጓዴ ፣ ሀምራዊ ፣ ብጫ ፣ ግራጫ ፣ ቀይና የመሳሰሉት ፤ (2) በተዘዋዋሪ ቀለምነቱ — ደም ፣ ጦርነት ፣ ትኩስ ቅጠል ፣ ደረቅ ቅጠል ፣ የጎመራ ፍሬ እና የመሳሰሉት ፤

- <u>ቅርፅ</u> ፤ ምሳሌ (1) በቀጥታ ቅርፅነቱ — ክብ ፣ ሾጣጣ ፣ ውርግርግ ፣ አራትዮ ፣ ማእዘን እና የመሳሰሉት ፤

  (2) በተዘዋዋሪ ቅርፅነቱ — ወፍጮ (ወፍጮ አፍ) ፣ ጦር (ጦር አፍ) ፣ መሳል (መሳል እራስ) ፣ እምቦ ብርሌ ፣ ቀጨሞ (ቀጨሞ እግር) ፣ አለንጋ (አለንጋ ጣት) ፣ መጅ (መጅ እግር) ፣ ዶጋን (ዶጋን እግር) የመሳሰሉት ፤



- <u>አቀማመጥ</u> ፤ ምሳሌ (ሀ) በቀጥታ መጠንነቱ — ትልቅ ፣ ትንሽ ፣ ሰፊ ፣ ጠባብ ፤ አጭር ፣ ረጅም ፣ ብዙ ፣ ጥቂት እና የመሳሰሉት ፤

  (2) በተዘዋዋሪ መጠንነቱ — አውሳላ (አውሳላ ሜዳ) ፣ ሰማይ ጠቀስ ፣ እርም ፣ የመርፌ ቀዳዳ ፣ ጉቶ ፣ የሰማይ ከዋክብት ፣ የባህር አሸዋ ፣ የጋሸበ ጤፍ (ለፀጉር) ፤

  <u>የማሰማት ሀይል</u> (ደማቅነት) ፤ ምሳሌ (1) በቀጥታ ማሰማቱ — ጥቁርቁር ፣ ጥቁር ፣ ብሩህ ፣ ክፍት ፣ ዝግ ፣ ደብዛዛ ፣ እንትግትግ ፣ ብልጭታ እና የመሳሰሉት ፣ (2) በተዘዋዋሪ ማሰማቱ — ውሃ (ውሃ ሰማያዊ) ወይን ጠጅ ፣ ከሰሌ ፣ በረዶ (ጥርስ በረዶ) እና የመሳሰሉት ።

(ለ) <u>የመስሚያ አውታር</u>

በመስሚያ አውታራችን (በጆሮአችን) አማካይነት የሚከሰቱ ምስሎች ፤

- ድምፃቸው የድምፁን አይነት የሆኑ ቃላት ፤ ምሳሌ — ኳኳ ፣ ቋቋ ፣ ወለልታ ፣ በርቸስቸስ እና የመሳሰሉት ፤

- ድምፅ የሚያስታውሱ ቃላት ፣ ምሳሌ — ማሲንቆ ፣ ክራር ፣ ፏፏቴ ፣ ዝምታ ፣ ፀጥታ ፣ ክላሽንኮቭ ፣ የእሳት አደጋ መኪና እና የመሳሰሉት ።

(መ) <u>የማሽተቻ አውታር</u>

በማሽተቻ አውታራችን (በአፍንጫችን) አማ ካይነት የሚከሰቱ ምስሎች ፤

- ቀጥታ ሽታ ፤ ምሳሌ — ሽቶ ፣ ግም ፤
- ተዘዋዋሪ ሽታ ፣ ምሳሌ — ሎሚ ፣ አዛባ ፣ ባርሶነት ፣ ወይራ ፣ ብርጉድ ፣ እጣን ፣ እንጨት ፣ ኩበት ፣ ፋንድያ ፣ ሳር ፣ ድርቆሽ እና የመሳሰሉት።

(ሰ) <u>የማጣጣሚያ አውታር</u>

በማጣጣሚያ አውታራችን (በአፋችን) አማካ ይነት የሚከሰቱ ምስሎች ፤

- ቀጥታ ጣእም ፤ ምሳሌ — ጣፋጭነት ፣ መራር ነት ፣ ጎምዛዛነት ፣ አሲድነት ፤
- ተዘዋዋሪ ጣእም ፤ ምሳሌ — ሎሚ ፣ ማር ፣ በር በሬ ፣ ጨው እና የመሳሰሉት ።

(ረ) <u>የመዳሰሻ አውታር</u>

በመዳሰሻ አውታር (በጣቶች) አማካይነት የሚ ከሰቱ ምስሎች ፤

- በቀጥታ ዳሰሳ ፤ ምሳሌ — ሻካራ ፣ ግርድፍ ፣ ድቁስ ፣ ሙቅ ፣ ቀዝቃዛ ፣ እሳት ፣ ልስልስ እና የመሳሰሉት ፤

በተዘዋዋሪ ዳሰሳ ፤ ምሳሌ ጭንጎት — (ጭን ጎት እራስ) ፣ ሞረድ (ሞረድ እግር) ፣ ጭቃ (ጭቃ አነጋገር) ፣ ምድጃ (ምድጃ አፍ) ፣ በረዶ (በረዶ ሰውነት) ፣ አበባ እና የመሳሰሉት



## 2.4.2 <u>በሰዋዊ ትርበታቸው አማካይነት</u>

የዚህ አይነቶቹ ቃላት ባጠቃላይ ፣ ከማንኛውም የሰው ልጅ ከፍተኛ ግምት ከሚሰጣቸውና እርባና (ፋይዳ) አላቸው ብሎ ከተቀበላቸው ተቋሞች እየመነጩ ፣ እንደ ዘመኑ ህይወትን መተርጎሚያ በመሆን የሚያገለግሉ ናቸው ። አብዛኞቹ ከቤተሰብ ፣ ከሀገር ፍቅርና ከሃይማኖት ጋር ይዘመዳሉ ፤ ምሳሌ — ወንድም ፣ እናት ፣ አባት ፣ እህት ፣ ልጅ ፣ ቀዬ ፣ የትውልድ አገር ፣ መንደር ፣ እና የመሳሰሉት ።

## 2.5 የቃላት ጥርቅሞች[1]

ሀሳብ፣ በቃል፣ በድርብ ቃላት፣ በሀረግና ከዚያም በላይ በሆኑ ክፍሎቶች፣ በሚገለፅበት ወቅት፣ በየፅሁፉ፣ ልት ርጉምም ሆነ ለስሜት እምብዛም ፋይዳ የሌላቸው የቃላት ጥርቅሞች ይታያሉ። በእንደነዚህ አይነት ጥርቅሞች ከመጠቀም እንድንቆጠብ፣ ምን እንደሚመስሉ የሚያመለክቱ ምሳሌዎችን፣ ከዚህ በታች አለፍ አለፍ ብለን እንጠቅሳለን።

### (1) ድረታ

ድረታ ሀሳብን ለመግለፅ ተመሳሳይ ነጠላ ትርጉም ባላቸው ቃላትና ሀረግ የመጠቀም ልምድ ነው።

**አስረጅ 1**

- በአእምሮ ማሰብ
- በልብ ማፍቀር
- በጆሮ መስማት
- አጉል ውሸት
- መናጢ ድሃ
- ሲጋዊ ሰውነት
- ወደ ከርሰ መቃብር ገብተው በይበልጥ እስካል ወረዱ ድረስ ...

[1] ስለ ተገቢዎቹ የሰነ ፅሁፍ ቃላት አመራረጥ፣ ከገፅ 31—59፣ ስለ አገባበቻው ደግሞ፣ ከገፅ 98—117 ተመልከት።



### (2) የመሸነኔ ክሊሼ[2]

የአባቤ ቅንጅቱ እውን ካልሆነ ነገር በሚመነጭ አእምሯዊ ምስል የመጠቀም ልምድ ነው።

**አስረጅ 1**

- አይኗ የብር ጉልላት፣ ጥርሷ የበረዶ እምብርት አንገቷ እም ብርሌ፣ ሽንጧ የነብር ጅራት የሚመስል ወጣት ...
- ከተሰያየንበት ቀንና ሰአት ጀምሮ፣ የሰማይ አድቀቱን፣ የኮከብ ብዛቱን፣ የጣና ጥልቀቱን ያህል እንደምን ሰንብተሃል። እኔ ብሆን፣ ሰማይን ያለውታር፣ ምድርን ያለዋልታ የፈጠረ፣ ለቸርነቱ ወሰን የሌለው ጌታ ይመስገን ደህና ነኝ...

### (3) የተምሳሌት ግንኙ (ያገነነው)

ለሀሳቡ ከሚመጥነው ቃላት በላይ በማስጨን አሳብን በማጉላት ፈንታ የማስልሰያ ልምድ ነው።

**አስረጅ 1**

- በድሎት ላሸቀ
- የሀብት ፈሳ ሆነ
- ከኑሮ ማህደር፣ ከሰውነት ቅፅና ከመታወሻ ገፅ ተፋቀ።

[2] ስለሉ ግልፅ ሆና ለሚታይ የመሸነኔ አገላለፅ፣ ከገፅ 167 - 169 (ሀ)(2)ን እና 'ሐ' ን ተመልከት።

### (መ) የማሽተቻ አውታር

በማሽተቻ አውታራችን (በአፍንጫችን) አማካይነት የሚከሰቱ ምስሎች ፤

- ቀጥታ ሽታ ፤ ምሳሌ — ሽቶ ፣ ግም ፤
- ተዘዋዋሪ ሽታ ፣ ምሳሌ — ሎሚ ፣ አዛባ ፣ ባርሶንት ፣ ወይራ ፣ ብርጉድ ፣ እጣን ፣ እንጨት ፣ ኩበት ፣ ፋንድያ ፣ ሳር ፣ ድርቆሽ እና የመሳሰሉት።

### (ለ) የማጣጣሚያ አውታር

በማጣጣሚያ አውታራችን (በአፋችን) አማካይነት የሚከሰቱ ምስሎች ፤

- ቀጥታ ጣእም ፤ ምሳሌ — ጣፋጭነት ፣ መራርነት ፣ ጎምዛዛነት ፣ አሲድነት ፤
- ተዘዋዋሪ ጣእም ፤ ምሳሌ — ሎሚ ፣ ማር ፣ በርበሬ ፣ ጨው እና የመሳሰሉት ።

### (ረ) የመዳሰሻ አውታር

በመዳሰሻ አውታር (በጣቶች) አማካይነት የሚከሰቱ ምስሎች ፤

- በቀጥታ ዳሰሳ ፤ ምሳሌ — ሻካራ ፣ ግርድፍ ፣ ድቁስ ፣ ሙቅ ፣ ቀዝቃዛ ፣ እሳት ፣ ልስልስ እና የመሳሰሉት ፤

በተዘዋዋሪ ዳሰሳ ፤ ምሳሌ ጭንጎት — (ጭንጎት እራስ) ፣ ሞረድ (ሞረድ እግር) ፣ ጭቃ (ጭቃ እነጋገር) ፣ ምድጃ (ምድጃ እፍ) ፣ በረዶ (በረዶ ሰውነት) ፣ አበባ እና የመሳሰሉት



## 2.4.2 በሰዋዊ ቅርበታቸው አማካይነት

የዚህ አይነቶቹ ቃላት ባጠቃላይ ፣ ከማንኛዎቹም የሰው ልጅ ከፍተኛ ግምት ከሚሰጣቸውና አርባና (ፋይዳ) አላቸው ብሎ ከተቀበላቸው ተቋሞች እየመነጩ ፣ እንደ ዘመኑ ሁኔታ መተርጎሚያ በመሆን የሚያገለግሉ ናቸው ። አብዛኞቹ ከቤተሰብ ፣ ከሀገር ፍቅርና ከሃይማኖት ጋር ይዛመዳሉ ፤ ምሳሌ — ወንድም ፣ እናት ፣ አባት ፣ እህት ፣ ልጅ ፣ ቀዬ ፣ የትውልድ አገር ፣ መንደር ፣ እና የመሳሰሉት ።

## 2.5 የቃላት ጥርቅሞች [1]

ሀሳብ፣ በቃል ፣ በድርብ ቃላት ፣ በሀረግና ከዚያም በላይ በሆኑ ክፍልፋዮች፣ በሚገለፅበት ወቅት ፣ በየፅሁፉ ፣ ልቅ ርቱዕም ሆነ ለስሜት እምብዛም ፋይዳ የሌላቸው የቃላት ጥርቅሞች ይታያሉ ። በእንደነዚህ አይነት ጥርቅሞች ከመጠቀም እንድንቆጠብ ፣ ምን እንደሚመስሉ የሚያመለክቱ ምሳሌዎችን ፣ ከዚህ በታች አለፍ አለፍ ብለን እንጠቅሳለን።

### (1) ድረታ

ድረታ ሀሳብን ለመግለፅ ተመሳሳይ ነጠላ ትርጉም ባላቸው ቃላትና ሀረግ የመጠቀም ልምድ ነው ።

**እስረጅ ፤**

- በአእምሮ ማሰብ
- በልብ ማፍቀር
- በጆሮ መስማት
- አጉል ውሸት
- መናጢ ድሃ
- ሲጋዊ ሰውነት
- ወደ ከርሰ መቃብር ገብተው በይበልጥ እስካል ወረዱ ድረስ ...

[1] ስለ ተገቢዎቹ የስነ ፅሁፍ ቃላት አመራረጥ ፣ ከገፅ 31—59 ፣ ስለ አገባባቸው ደግሞ ፣ ከገፅ 98—117 ተመልከት ።



### (2) የመሸነኔ ክሊሼ [2]

የአሳቤ ቅንጅቱ እውን ከልሆነ ነገር በሚመነጭ አእምሮዊ ምስል የመጠቀም ልምድ ነው ።

**እስረጅ ፤**

- አይኗ የብር ጉልላት ፣ ጥርሷ የበረዶ እምብርት አንገቷ እዋ ብርሌ ፣ ሽንጧ የነብር ጅራት የሚመስል ወጣት ...
- ከተለያየንበት ቀንና ሰአት ጀምሮ ፣ የሰማይ እርቀቱን ፣ የኮከብ ብዛቱን ፣ የጣና ጥልቀቱን ያህል እንደምን ሰንብተሃል ። እኔ ብሆን ፣ ሰማይን ያለውታር ፣ ምድርን ያለዋልታ የፈጠረ ፣ ለቸርነቱ ወሰን የሌለው ጌታ ይመስገን ደህና ነኝ...

### (3) የተምሳሌት ግንኝ (ያገነነው)

ለሀሳቡ ከሚመጥነው ቃላት በላይ በማስጫን እሳቡን በማጉላት ፈንታ የማሰልሰያ ልምድ ነው ።

**እስረጅ ፤**

- በድሎት ባሸቀ
- የሀብት ፊሳ ሆነ
- ከኑሮ ማህደር ፣ ከሰውነት ቅፅና ከመታወቂያ ገፅ ተፋቀ ።

[2] ስለሉ ግለፅ ሆኖ ለሚታይ የመሸንኔ አገላለፅ ፣ ከገፅ 167-169(ለ)(2)ን እና 'ተ' ን ተመልከት ።

- ስለ ገበሬው ፈለግ ያወጡ እጆች ለምን እሰባለሁ ፤ በውስጤ ብዙ እጆች ፈለግ እያወጡ ባሉ...
- ያጠናቀረውን የሀሳብ ቅርጣት በሰሌዳ እንቅብ ሰፍሮ አቀረበ ።

(ስለ ተምሳሌት ተገቢ አገባብን በሚመለከት ፤ ከገፅ 50—51 '(ሀ) (2)' እና ገፅ 54 '(ለ)'፣የዘመድ አዝማድ ትርጉም ወከልና ቀቅሶች የሚለውን ተመልከት)

(4) ትርጉም - የለሽ ፀተር በንጠቃ ፤

ሀሳቡ አለመጠን ከመወጠሩ (ከመለጠጡ) የተነሳ ፤ በመጨረሻ አሳቤው የሚጠፋበት የአፃፃፍ ልምድ ነው ።

አስረጅ ፤

«ትምህርት ምስጢሩ ናላን የሚአዞር ፣ ብርዱ በቤትና በልብስ የማይተገን ፤ ሀሳብን ከትልቅ ከተማ እንደገባ ሰው የሚአንቀዋልል ፣ አካላትን እንደንዳድ የሚአንቀጠቅጥ ፣ ሰውዘዋሪት ተቀን ሳይል በሰው ጭንቀላት የሚጋልብ ፣ ለውዝዋዜው ወሰን የሌለው የቁርጥማት በሽታ ነው እላለሁ . . . »

«. . . ትልቁ እይን እይኑ ልቡና ነው ። እይኑ ልቡና ከፊቱ የቀረበለትን ብቻ አይደለም የሚአየው ፤ ተራራና ጫካ የማይጋርደው ፤ እድማስ የማይመልሰው ፤ ያለፉትን ያሉትንና ወደፊት የሚመጡትን ለማስተዋሉ ወሰን ሳይኖረው የሚመለከት ፣ በእይን ቀርቶ በቃል ሊገለፅ የማይችለውን ሀሳብን መርምሮ የሚገልፅ ትልቁ እይን ነው . . »

(5) የጓኑ ተነፃፃሪ

ተነፃፃሪዎቹ ከመብዛታቸው የተነሳ ስለማይጣጣሙ ፤ አሳቤው የሚጠፋበት የአፃፃፍ ልምድ ነው ፤ ኪናዊ የማ ሆንበትን አቀራረብ ወደፊት እናሳያለን ፤



አስረጅ ፤

- 'እንደ ሰንፍና ሰልቹ እገሌጋይ ፊቱን አግዘርቦ የቆየው ክረምት ፣ ሀገን ልጅዋን ከእቅፏ እንደ መነጨቋት እናት እንባው ይጎርፍ የነበረው ሰማይ ፣ እንደላሊበላ ማለዳና ማታ የሚያጓራውም ነጎድጓድ ሁሉም ተግባራቸውን እረሱት ። ምን ነካቸው ፣ ያለወትሯቸው ፀጥታን ፣ መደሰትንና መሳቅን ፣ ፈገግ ፈገግ ማለትን አመጡ ። እንደ ዘመኑ ሰው መለዋወጡ ምኑ አምሯቸው ይሆን ?'
- 'ከተቀመጠችበት ወርዳ ፣ እየተሳጋ እንደሚወርድ የአረሀ 'ላይ ፏፏቴ ሽንጧን ማስቀዳት በጀመረችማ ጊዜ ፣ እግዚአብሄር ፀኪኑ ጥበቡ የደገፈው ሽንጧ እንደ ገመገም የተንሰራፋውን ዳሌዋን ተሸከሞ ውሃ እንደሚያማታው የወፍጮ ሰሌዳ ሲሽከረከር ባየሁ ጊዜ ግርምኝና ደንቆኝ ሰይጣንም ይሆንን እይቶ በፍቅር ጊዜ 'በስመአብ ይቅር' እስከ እያልኩ መንገዴን ቀጠልኩ . . .'
- 'እንደ ጥይት ተወርዋሪ ፣ እንደ አንበሳ ግርማዊ ፣ እንደ ነበር ግልፍተኛ የሆነ ፣ የወንድነት ሀሞቱ የፈሳበት ፣ ያርበኝነት መንፈሱ የገነፈለበት ፣ የድፍረት ገፊት ያስከረው ፣ ገንጋኙ የሀገሬ ጀግና እገሩን እያስደፍርም . . .'[23]

« ባውስጡ ያለበት የመርዶ ቃል እንጀቱ ይበላል።
ልቦና ይከፋፍላል ። እንደ ፍላፃ ውስጥ እንጀት
ይወጋል ። ለማንበብም ስሞክረው የስሜቱ ሹል
ጦር ትክል ብሎ ሰውነቴን ሽንቆረው ። እም ሽክ
አድርጎ እንደ ሰይፍ አረደኝ ፤ ሸንተፈኝ ። »

« በመጀመሪያ እኔ ቁሜ የሄድኩት በአራት
አመቴ ነው ። በምቾት ሰውነቴ እንደ ኳስ እያበጠ
ደረጃ አውጥቶ የተከመረው ስጋዬ የማይገባኝን
ክብደት ስለ ጨመረብኝ ቶሎ ቶሎ ቆሜ ልሄድ በሁ
ለት ዓመቴ ለመዳህ እንኳ አልቻልኩም ። ካለ
ሁበት ቤታ እንደ ገዘፈ በልፈሰፈሰ የቤት ቁሳቁስ
ተመርኩዤ ለመቆም እተነፍሰው የነበረው ሜን
ጫን ትንፋሽ ከባድ ጭነት የተሸከመ ተሸከርካሪ
ከሚአስወጣው ጢስ የማያንስ ነበር ። ሰው ካልቸ
ገረው ሊሰራና እድገት ለማግኘት እንደማይሻ
ከዚህ ነው ለመረዳት የቻልኩት ። እኔን ምግብ
ቢቸግረኝ ኖሮ ሲርበኝ . . . ከወለል የፈሰሰውን
ጥሬ ከዶሮች ጋር ለመናጠቅ ስታገል ያን በሶስትና
በአራት አመት ያልሆነልኝን መቆም በአንድ አ
መት ውስጥ በሞከርኩት ነበር ። ምቾት ነው ፤ ያን
ከመጠን በላይ የተሸከምኩት ሲጋ ነው ፤ ያን
ያህል ጊዜ እንደ ቅንቡርስ ከወለል እንድንከባ
ለል ያደረገኝ ። » *

---

ምረት በላለው ተንፃፃሪ ገፅ 54 በሀዳግ ማስታወሻ ቁጥር 9 እና 10 የተ
ቀሱትን ተመልከት ። *

(6) የተንዛዛ

እሳቤው የሚገልፀውን ጉዳይ ካለማወቅ ወይም
ለሁኔታው ግርማ ለማስገኘት ሲባል ግልፀት



ሳይኖረው ፤ የሚበራከትና ማንም ሰው ሊያው
ቀው የሚችለውን በማፍታታት ብቻ ፤ እኔ
ነኝ የማውቀው ፤ የሚል አይነት የአፃፃፍ
ልምድ ነው ።

አስረጅ ፤

'በድሎት ላሽቆ ሳይሞት የሞተ የሀብት እሬሣ
ለመጨረሻ ጊዜ ዘለዓለማዊ ዕረፍቱን ሲያገኝ
ከመሬት በታች ይውላል ። ምድራዊ ሀብቱ
ግፍ ቢል በዓመት ውስጥ ፤ ሥጋዊ ሰውነቱ
በዐሥራ አምስት ቀናት ውስጥ ድራሻቸው ይጠ
ፋል ፤ ማለት ምድራዊ ሀብቱን እእምሮው
ያደገለት ፤ ጥርሱን በዘመን ብዛት በከንፈሩ
የሰበሰበ ፤ ጥፍሩን በመዛሪያ የሚቀረቅፍ
ፍጡር ፤ ሥጋዊ ሰውነቱን ደግሞ በመሬት ውስጥ
የሚርመሰመሱ የጥቃቅን ፍጡራን ሠራዊት
ድራሹን ያጠፉታል . . .'

(7) አንስቶ መጣል

አስረጅ ፤

« . . . ነገር ግን እያንዳንዱ ሰው ፤ ሁኔታው አላግ
ባብ መሆኑን ሲዐውቀው ፤ በማዘንና በማሰብ ፈን
ንታ በበኩሉ እንዳይፈጸም ለማድረግ ቢጥር ፤ ጉድ
ለቱ ሁሉ ከመቶ ሃምሳ ተቀንሶ አንቺንም አሁን
ባላሳዘነሽ ነበር ። የሆነው ሆኖ ፤ በማንም መንፈስ
ቅር አይበልሽ እንጂ በጊዜአችን ያሉት ልጃገረ
ዶች ቀርተው ባለትዳሮች የዐይናቸው ተግገሮች
ናቸው ። በሩቅ ሲመለከቱት አሸዋም ውሃ ይመስ

ላል ። በዚህ ሁኔታ መርጠው የኑሮ አሳት ይፈጥራሉ ። ወንዶችም ከዚህ የተሻለ ሕስተያየት የለንም ። ለአንድ ሰው አንድ ይበቃዋል ። ዘጠኝ ዳቦ ከመላስ አንዱን አጥብቆ መጉረስ ይሻላል ይላሉ አባቶች ። የሚጎረሰው ጣፋጭና ለሆድ ተስማሚ መሆኑን መምረጥ ያለበት ባለቤቱ ነው ። ጥሩ ቢሆን ሰውነት ፥ መጥፎ ቢሆን ትውከት መፍጠሩን መራጭ ዐውቆ መጠንቀቅ አለበት ። »

«...ከዚህም አያይዘው ፥ 'የኢትዮጵያ ሕዝብ ባለፈው ረጅም ታሪክ ስሙን በአስተዋይነትና በጨዋነት ያስመዘገበበት ብዙ የጠሩ ምዕራፎች አሉ ፤ ይኸውም የጀግንነትና የሃይማኖት ጽናት ብቻ ሳይሆን ፥ አርቆ ማስተዋልና ለጋራ ጥቅም መሥዋትን ፥ መብትና ክብርን ዐውቆ ማስከበርን ከቀደምት ጊዜ ጀምሮ ያለን ሙያ መሆኑን የብዙ ሺህ ዘመን ታሪካችን ይመሰክራል' በማለት . . . ታሪካችንን እንድንመረምር በማስታወስ ፥ '. . . ያለፈ ታሪክ ለመጭው ጊዜ ማረጋገጫ ዋስትና እንዲሆን ዋጋውን ማስከበርና ጠብቆ ማኖር የትውልድ ፈንታ ስለሚሆን ፥ በዚህ አንጻር መመራትና ትግሉን መቀጠል ይኖርብናል እንጂ ፥ ባባቶች ሙያ በታሪክ ዝና እየተመካን ተከናንበን ብንተኛ ወይም ራሳችንን በከንቱ ውዳሴ እየደለልን ስንፍና ማጥ ብንጠልቅ ፥ ያለፈው ታሪካችን ለትዝብትና ለትምህርት እንጂ ለሌላ ጉዳይ ይጠቅመናል ለማለት አይቻልም' ሲሉ በጥልቅ ማስተዋል አስገንዝበዋል ። » [4]

---

ሰንደቅ ዓላማችን » ፤ ቁጥር 23 ፤ መስከረም 7/56 ።



(8) <u>እውነታ ቢስ</u>

በእውን ከሚታየው ልምድ ውጪ የሆነ ፋይዳቢስ የሀረጎች አዝልዝል ነው ።

<u>አስረጅ ፤</u>

« በሽታዬ ሁሉ ለቀቀኝ ። ማቅ ተከልክሎ የነበረው ጥርሴ ፍልቅቅ ፍልቅቅ ይል ጀመር ። ያረረው ከንፈሬ ወዛ ። ጥጊው የወጣው ወዘናዬ ተመለሰ ። የተቃጠለው አንጀቴ ራሰ ። የደረቀው ደሜ ተላወሰ ። ከሞት አፋፍ የደረሰው ሕይወቴ ተመለሰ ። የደረቁት አጥንቶቼ ለመለመ ያለቀው ሥጋዬ ባጥንቶቼ ሞላ ። የተነቃቀሉት ጡጉሮቼ እንደገና በቀሉ ። እንባው ከማለቁ የተነጣ እንደዋሻ ጎድጉዶ የነበረው ዐይኔ ቡጢ አካከለ ። ተሸራምጦ የነበረው አፍንጫዬ የሰንደዶነቱን አቀማመጥ ያዘ ። ፋጫ የመሰለው መልኬ መልአከ እግዚአብሔር መሰለ ። እንባ የገመሰውና ቦይ ያበጀው ፊቴና ጉንጫጉንጩ ድንቡሎነቱን አገኘ ። .......... ከእንግዲህ ወዲያ ........ ሙሉ ቆራጥነት አይደረብኝ ። »

«... በጦርነት ጊዜ ማረሻቸውን ሰይፍ ፥ ጎራዴ ፥ ማጭዳቸውን ጦር ፥ ቢላዋቸውን ካራ ፥ ጩቤ አድርገው እየሠሩ ወደ ጦርነት ሜዳ መውጣትን ፥ በሰላም ጊዜ ሰይፋቸውን ፥ ጎራዴያቸውን ማረሻ ፥ ጦራቸውን ማጭድ ፥ ካራቸውን ፥ ጩቤያቸውን ዶማ ፥ መጥረቢያቸውን ቢላዋ አድርገው እየሠሩ ወደ ሰላማዊ ሥራ መሠማራትን ዐውቀውበት ኖረዋል ... »

(9) <u>የሰለቸ ክሊሼ *</u>

ተናጋሪም ሆነ ፀሐፊ በየጊዜው በሰሚያጋገመው ፣ ጨርቶ ጨርቶ አላቂው የቀረ አባባል ነው ።

<u>አስረጅ ፥</u>

- እንደ ሰም አቅልጦ ፥ እንደ ብረት አዝብጦ
- የረቀቀውን አጉልቶው ፥ የተሰወረውን ገልጠው
- እንደ ገል ቀጥቅጦ ፥ እንደ ጭቃ ረግጦ
- ባልጋ ቁራኛ ፥ በደዌ ዳኛ
- ከረጅሙ ባጭሩ ፥ ከብዙ በጥቂቱ
- ከባቶቻችን ሲወርድ ፥ ሲዋረድ
- ሁላችንም እንደምናውቀው ሁሉ
- እንደ መሆኑ መጠን
- ከዱር የሚገባው ፥ ከገበያ የሚገዛው
- ለአፍ ጉርስ ፥ ለአካል ልብስ
- በሰማይ በራሪ ፥ በምድር ተሽከርካሪ
- የዱር ወንበዴ ፥ የከተማ ዱንዬ
- የስልጣን አሰናካይ ፥ የስራ አስተጓጓይ
- የመንደር ሰላይ ፥ የገበያ አታላይ
- የዳኛ አድላይ ፥ የምስክር አባይ
- ሴት አስኰብላይ ፥ አጥር ዘላይ
- ግንብ ሰርሳሪ ፥ ሳንቃ ሰባሪ
- ነገር ቀባጣሪ ፥ ሀሰት ተናጋሪ
- ቤት ሰርተው ፥ ንብረት ገዝተው
- ጎጆ ቀልሰው ፥ ከቤት አርብተው

* ክሊሼ ምስል ከሳች ስለሆነ ፥ በተለይ በኪነ-ፅሁፍ ውስጥ ሲቀር አይከ
ፋም ። ቢሆንም የተቻለውን ያህል አዳዲስ ምሳሌዎች ፥ ተምሳሌቶች ፥ ንፅ
ፅሮች ቢኖሩ ይመረጣል ፤ ከጊዜዉ አስተሳሰብ ጋር የሚስማሙ ።



- ልጅ ወልደው ፥ አርሰው ቆፍረው
- ትእግስቱ ተደንቆ ፥ እውቀቱ ታውቆ
- ማእረጉ ምጡቅ ፥ ጥበቡ ረቂቅ
- ፍጥረት እንዲያውቀው ፥ ፀሀይ እንዲሞቀው ፥
- በብርሃን ልባቸው ፥ በሰፊ እውቀታቸው
- አንዱ ላሽ አንዱ ቀማሽ
- ጌትነት አይናቸውን ሸፍኖ ፥ ራሳቸውን አዞሮ ፥ አእምሯቸውን ሸውጦ
- ሰይፋቸውን ቀንተው ፥ ጠመንጃቸውን ሰጉመው

(10) የተጋነነ የአወዳደሪ ፥ የአነፃፃሪ ፥ የአንዳንድ ፈሊ ጦች እና የመሳሰሉት ስብስብ

<u>አስረጅ ፤</u>

- «... ፍቅር ታጋሽ ናት ፥ በጎም ናት ። ፍቅር አትቀናም ። አትመካም ፤ አትነፋም ፥ ፊቷን አታጠቁርም ፤ ገንዘብን አትሻም ፤ ቶሎ አት ቆጣም ፤ በክፉ አታስብም ፤ በኃጢአት ደስ አይላትም ፥ በውነት ደስ ይላታል እንጂ ። ሁሉን ትችላለች ፥ ሁሉን ታምናለች ። ሁሉን ተስፋ ታደርጋለች ፤ በሁሉ ትታገሳለች ። ፍቅር ከቶ አትወድቅም . . .» [5]

- «... ትምህርትን ተላይ ተላዩ ኩረፌውን ማንግ ትና ካናት ካናቱ ገፈታውን መጨለፍ ብቻ ሳይ ሆን ከሥር ጉብተህ ጥለቀው ፤ ደንብቀው ፤ አንቅ ረው ፤ አሟጠው ፤ ምጠጠው ፤ ጨልጠው ...»

5 «አእምሮ» ፤ 'በማልባኔ አስተዳደግ' ፥ እ.ኢ. ሐምሌ 25/1916 ።

«ወይ ሰው! ወይ አንተ ብሎ ፍጡር! ፍቅርን ያህል ነበልባል ተፈጥሮብህ፥ ሕይወትህ የጋመ፥ የተሟሟቀ ወይም የገመነና የተቃጠለ ሲሆን ብህ ይኖራል. . .»

«ይህች ቀበሌ፥ የአበባ ድሪ በአንገትዋ አጥልቃ በተፈጥሮ እንዲህ ትሽለምለም እንጂ፥ ልማድ ሁለት እግሩን በተራራ በተራራው፥ በአምባ በአምባው እንፈራጠ ዘርግቶ፥ ደመናውን በውሃው ላይ ጥሎ፥ ግድግዳውን በስንፍና ጋርዶ እየተሞላቀቀ፥ የዕውቀት ጮራ አላሳልፍም እያለ ይታገላል ... »

«. . . ድርጊቱ የሆነበትን ቦታ በትክክል ባላውቀውም ቅሉ፥ በዚች የሰው ደም እንደ ጅረት በሚፈስባት ጣእመ አልባ የእንጀራ እናት ዓለም መሬት መሆኑን እርግጠኛ ነኝ ... »

«...በዚች በምታስገርም ዓለም፥ በአስገራሚነቷ ላይ አስገራሚ ነገር ሲደረግ ከመኖሩ የተነሣ፥ ከመንገድ ላይ ቆሞ ፍጥረትን በሚያስተላልፈው በዓለም ፖሊስነት የሚዘዋወረውን የደቂቀ አዳምን መንገድ ሲመረምሩት፥ ደንና ጥሻ፥ ገደልና ዋሻ፥ ወጣ ገባና ስርጉጥጉ ጣም ሆኖ ይገኛል... »

«...ዓለምም የቀድሞውን እድፋምነት ትታ፥ መኳኳልና መዋዋብ፥ ራሷን መሠራረትና መታሸም፥ ጠጉሯንም ማሳመርና በሚያንፀባርቅ መልክ መታየት ፈቀደች። ከዚህ የተነሣ፥



ልምድን ዘወር በል ብላ አፍንጫውን ለማለት በትር ብትመዝበት፥ ካንቺ ጋር ምን አታገለኝ በማለት እልም ብሎ ጠፋ ...»

«...የጥበብ ተወላጅ፥ የሥልጣኔ ተዛማጅ እንድሆንና የዕውቀት ባላባት እንድባል፥ ተምሮ ለማወቅ ወደ ውጭ አገር ጉርፍ ወሰደኝ። እንዲህ ነው ውሀ አወሳሰድ ...»

«...ነፋሱ ጸጥ (ዲብ) ሲል ባሕሩ እንደ ጸሎተ ሐሲና አድራሽ ድምጹን ጥፍት ያደርጋል። ኮሽ አይልበትም። ከተውንም ሁሉንም ይተውና ይዝላል። ሥርዓት ሞት እንደ ደረሰለት ምውት አሳቡን ጥሎ ፏ ብሎ ይዘረጋል ...»

«...ያልተማረ ሕዝብ ባሕሩ ...... የኢኮኖሚ መተንፈሻ ሳንባ መሆኑን አያውቅም ...»

«...መርከቦቹ የውሀ እናት አበባዎች መስለው ከባሕሩ ማዕበል ጋር እየተፈካከሩና እየተገረመሙ እየተጣለቁና እየተዳፈቁ በትግል ላይ ሆነው ሲታዩ ያስገርማሉ...»

«...አእሮፕላኖች የአየር ዋናተኞች ሆነው የነፋሱን ማዕበል እየቀዘፉና እንደ ሰንጋ ፈረስ ከፍንጫቸው በሚወጣው የአየር ቡልቅታ፥ ኃይለ ነፋሳትን እያራገቡ ሲበሩ........»

«...ነፋሱስ ቢሆን በተፈጥሮ ሕጉ ውስጥ የሌለ ሸክም በጀርባው ላይ ተጭኖ የጥበብ አጋሰስ ሆኖ፥ ለኩራቱ መርገጫ በሌለው በአየር ላይ

እየታገለ ሰማይ ለሰማይ ሲንጋፈፍ እንዴት ይደንቀው ...»

- «... 1921 ዓ. ም. ገና ሰላም ሳይታመም ፤ በመካከለኛ ሕይወት ሳለ ፤ ራሴንና ወገቤን እያለ ሲንቆላበስና ብርድ ብርድ ሲለው ወይም ሲያተኩሰውና እንደማሳል ሲለው... »

- «...የልማድ ጉም የሸፈነውና የስንፍና ዳመና የጋረደው ጊዜ መቼም ቢሆን ለፀሐይ አይመቻትም ። ዘለዓለም ከስንፍና ምድጃ ተወዝቶ ይኖር ዘንድ... የተፈጠረ ፍጥረት እንዲህ ያለው ተግባር የሞት ሞቱ ነው ...»

- «ሰውነቴ በእሳት ሀዘን ተቃጠለ ። በሀዘን ንፍር ውሀ ተቀቀለ ። አንጀቴ ተበጣጠሰ ። ልቤ ነበዘ ። አእምሮዬ ናወዘ ። ዐይኔ ቦዘ ...»

- «... በእንደዚህ ያለ ማዳከም ፤ የወጣቶችን አሳብ የተሰበረ መቃ ለማድረግ በፍቅራዊ መንፈስ ወይም በመንፈሳዊ ፍቅር ልቡናን ማሸት ፤ በአእምሮ የተቀረፀውን የዕውቀት ማህፀን ያሟሽሽዋል ...»

- «... ትኩስ ስሜት በሰውነቴ ውስጥ ካውያውን አሙቆ ልቤን ያሸው ፤ ይዳምጠው ጀመር... »

«... ከዚህ የትምህ የሀገሬ አኳኋን ትዝ አለኝ ። ትዝታዋም እሳቱን ለኮሰብኝ ። ከቶውንም ረመጡን ጭሮ በተነብኝ ። ጭራሮውን ብው አድርጎ አነደደው ። ሰውነቴን አቃጠለው ። እን



ዥቴን አሳረረው ። የናፍቆቷ ሽል በሆዴ ተላወሰ ። የሡራ አካላቴን አፈራረሰው ። ፍቅሯ በጥልቅ ሰውነቴ ገብቶ በረበረኝ...»

- «... መምህሬም ትጋቴንና እያያዜን በማየት ትምህርት ወተትን አብዝተው በዋንጫ ራቤ ሞሉልኝ ...»

- «... ልብ ብለው ሲመለከቱት ሀዘን በሜዳ ልቡ ላይ አዳራሹን የገጠገጠበት ይመስላል...»

## (11) ማራቶን ፤

ማራቶን (ረፍት የለሽ) አረፍተ ነገር ፤ ከመርዘሙ የተነሳ ሀሳቡ በየፈርጁ ያልተቋጨ ወይም ቢቋጭም አሰልችነት የሚኖረው አፃፃፍ ነው ። አንዳንዴ ስርአቱን ተከትሎ ከተቀናበረና እንዳይሰለች ሆኖ ከተቋጨ ፤ ከአጫጭር አረፍተ ነገሮችም ይበልጥ የሚያመረቃበት አገባብ አለው ።

### አስረጅ ፤

«... እዚህ ላይ በእቀረብኩት አስተያየት መኪናዎች ከውጭ አገር እንዳይመጡና አገር ውስጥ ገብተው እንዳይሸጡ መከልከል አለባቸው የማለትና ፤ ገዥዎችንም የመንቀፍ ሳይሆን ፤ ሁላችንም እንደምናውቀው በአለንበት ዘመን በሥልጣኔ ገስግሰው እንዲሰትረያቸውን የእስፋፉ አገሮች ፤ በየጊዜው የመኪናዎችን ሞዴል እየለዋወጡ የሚአቀርቡልንን መኪና ለመግዛት የሀብታቸው መጠን የማይ

---

የሰመረ አገባብን በሚመለከት ፤ ስለ ፈሊጥ ገፅ 53 '(መ) (1)—(3)' ፤ ስለ ሰውኛ ገፅ 166 '(0) (1)'ን ተመልከት ።

ፈቅድላቸው ሁሉ በዱቤም ሆነ ዋጋውን እርስት በመሸጥ ከፍለው የመኪና ባለንብረት የሆኑ ሰዎች ብዙ ስለሆኑና በአዲስ አበባ ውስጥ መኪናዎች ካለመጠን በዝተውና ከመንገዱ ተትረፍርፍው ሲታዩ ከሀገራችን ውስጥ እየተሠሩ የሚወጡ እንጂ ከውጭ አገር ተሰርተው መጥተው በውድ ዋጋ የተገዙ ስሊማይመስልና አገራችን ወጣት ልጆቿን እያስተማረች የፍጡር ጓደኞቻችን ከሚገኙበት ሥልጣኔ ለመድረስና ሰፊ ዕውቀትን ለመጨበጥ በምትገሰግስበት ጊዜ ይህ ጉዳይ ከግቡ እንዲደርስ መርዳት የሁላችን ተገቢ ሥራችን መሆኑን ዐውቀን፥ ከባዕድ አገር እየተላኩ የሚቀርቡልንን መኪናዎች በውድ ዋጋ በመግዛትና ገንዘባችን ከሀገራችን እየወጣ የውጭ አገር ኩባንያዎችን ካፒታል ከማዳበር እንድንታገሥና እራሳችንንም ሆነ ወገኖቻችንንና በጠቅላላ ሀገራችንን ለመርዳት ለሚችል ድርጅት እንድናውለው በማለት ለማሳሰብ ነው . . .'[6]

በራሱ ቋንቋ ሲስተካከል ፤

ብዙ ሰዎች ፥ የሀብታቸው መጠን መኪና ለመግዛት የማይፈቅድላቸው ሁሉ ፥ በዱቤም ሆነ ዋጋውን እርስት በመሸጥ ከፍለው የመኪና ባለንብረት ስለሆኑ በ(የሆኑ ሰዎች ብዙ ስለሆኑ) አዲስ አበባ ውስጥ መኪናዎች ካለመጠን በዝተውና ከመንገዱ ተትረፍርፈው (ሲታዩ) ይታያሉ ። ከሀገራችን ውስጥ እየተሠሩ የሚወጡ እንጂ እውነትስ ከውጭ አገር ተሠርተው መጥተው በውድ ዋጋ የተገዙ (ስለማይመስልና) አይመስልም። (እዚህ ላይ በአቀረብኩት አስተያየት) አስተያየቴ መኪናዎች ከውጭ አገር እንዳይ

6 የዛሬይቱ ኢትዮጵያ ፥ 'የኢኮኖሚያችን መቅሠፍት' ፥ (አ.አ. 1945)።



መጡ ወይም (አገር ውስጥ ገብተው) ከመጡ በኋላ እንዳይሸጡ (መከልከል አለባቸው) የማለትና ፡ ገዥዎችንም (ሳይሆን) የመንቀፍ አይደለም ። አገራችን ወጣት ልጆቿን እያስተማረች የፍጡር (ጓደኞቻችን) ጓደኞቿ ከሚገኙበት ሥልጣኔ ለመድረስና ሰፊ ዕውቀትን ለመጨበጥ በምትገሰግስበት ጊዜ (ይህ ጉዳይ ከግቡ እንዲደርስ) ከግቧ እንድትደርስ መርዳት የሁላችን ተገቢ ስራችን መሆኑን አውቀን ፥ (ሁላችንም እንደምናውቀው ፤ በአለንበት ዘመን) በስልጣኔ ገስግሰው ኢንዱስትሪያቸውን ያስፋፉ አገሮች በየጊዜው የመኪናዎችን ሞዴል እየለዋወጡ የሚያቀርቡልንን (ከባእድ አገር እየተላኩ የሚቀርቡልንን) መኪናዎች በውድ ዋጋ (በመግዛት) ከመግዛት በመቆጠብ ፥ ገንዘባችንን (ከአገራችን እየወጣ) የውጭ አገር ኩባንያዎችን ካፒታል (ከማዳበር) ማዳበሪያ ከማድረግ እንድንታገስና ፥ እራሳችንንም ሆነ ወገናችንንና በጠቅላላ ሀገራችንን ለመርዳት ለሚችል ድርጅት እንድናውለው በማለት ለማሳሰብ ነው . . . »

(ነጠብጣቦቹ የሚያመለክቱት መውጣት ያለባቸውን ቃላትና ሀረጎች ነው ።)

አሁንም ቢሆን የመጨረሻዉ አረፍተ ነገር ረጅም ነው ። ቢሆንም ሀሳቡን እንደሚገባ አድርጎ ያቀርባል ። በማራቶን አረፍተ ነገር ለመጠቀም ከፍተኛ ችሎታን ይጠይቃል ፥ እለዚያ ከላይ እንደ ተመለከትነው ፥

(ሀ) ባለቤትና ተሳቢ ከመጠን በላይ ከመራራቃቸው የተነሳ ፥ አንባቢው የተነሳበትን ነጥብ ይዘነጋል ። ባይዘነጋም ፥ ትርጉሙን ለማግኘት የመጀመሪያው

ባለቤት የት እንደሚያበቃና ሌላው የት እንደሚጀ ምር ማጤን ይኖርበታል ።

(1) ‘. . . እዚህ ላይ በአቀረብኩት አስተያየት ፣ መኪናዎች ከውጭ አገር እንዳይመጡና አገር ውስጥ ገብተው እንዳይሸጡ መከልከል አለባ ቸው የማለትና ገኸሮዎችንም የመንቀፍ ሳይ ሆን . . . . .

. . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . .

. . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . .

የሚቀርቡልንን መኪናዎች . . . . በመግዛት . . የውጭ አገር ኩባንያዎችን ካፒታል ከማዳበር እንድንታገስ . . . .’

<u>ወይም</u>

(2) ‘. . . . እዚህ ላይ በአቀረብኩት አስተያየት መኪናዎች . . . . . ገኸሮዎችንም የመንቀፍ ሳይሆን . . . .

. . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . .

<u>ገንዘባችንን</u> ጉልበታችንንም ሆነ ወገናችንንና በጠቅላላ ሀገራችንን ለመርዳት ለሚችል ድር ጅት እንድናውለው በማለት ለማሳሰብ ነው . . .’ አንቀፁ ትርጉም እንዲሰጥ «ገንዘባችንን» የሚ ለው ቃል መጨመሩን አስተውል ።



(ለ) <u>ድግግሞሽ ይኖርበታል ።</u>

. መከልከል አለባቸው (ባካባቢው ካለው ሀሳብ ጋር ሲተያይ)...
. የሆኑ ሰዎች ብዙ ስለሆኑ ...
. በሥልጣኔ ገስግሰው እንዱስትሪያቸውን ያስ ፋፉ ...
. ከውጭ አገር እንዳይመጡና አገር ውስጥ ገብ ተው ...

(መ) <u>የተግፌበት ግምባር ያለምክንያት ስለሚለዋወጥ አንድነት ያጣል ።</u>

. ሞዴል እየለዋወጡ የሚያቀርቡልንን ...
. ከባዕድ እየተላኩ የሚቀርቡልንን ...

(ሰ) <u>ድረታ ይበዛበታል</u> ።

. እዚህ ላይ በአቀረብኩት ...
. ሁላችንም እንደምናውቀው ...
. በአለንበት ዘመን ...

(ረ) <u>ባለቤትን ከመለዋወጥ የሚፈጠር ስህተት ይበ ረክታል ።</u>

. ጓደኞቻችን — ጓደኞቿ
. ከግቡ እንዲደርስ — ከግቧ እንድትደርስ
. የውጭ ካፒታል ከማዳበር — የውጭ ካፒታል ልን ማዳበሪያ ከማድረግ

(ሸ) የመደብ ፣ የፆታና የቁጥር ስርአት ፣ የማድረግና የመደረግ ጠባይ ፣ የቃላት አሰካክ ህግ ይፋለሳል ።

(ቀ) ስለተንዛዛ የሀሳብ ቅደም ተከተልና ውህደት ይጠፋል ። ሀሳቦችን አብሮ አብሮ በማሰለፍ ታቅዶ የተፃፈ ሳይሆን ፣ እንደ መጣ የተደረተ ስለሚመስል ትርጉምም ሆነ ስሜት የመስጠት ሀይሉ ይቀንሳል ።

(በ) ከሁሉም በላይ የአረፍተ ነገሩ ርዝመት ካስከተለው ችግር የተነሳ ፣ ደራሲው ያሰበው ሀሳብ በሚገባ ስላልተላለፈለት ድካሙ ሁሉ ከንቱ ይቀራል ማለት ነው ።

(በአግባቡ ስለ ተቀናበረ ማራቶን አረፍተ ነገር፣በመዘርዘር ቅንብር የተዛመደ ፣ ገፅ 331—2 ፣ በሚደራረብና በማስተዛዘል የተዛመደ ፣ ገፅ 137—8 እና ገፅ 139 ቁጥር (7) ን ተመልከት ።)

(12) 'ቃላት ያጥሩኛል'

አላዋቂነትን በግልፅ ስለሚያሳይ የፅሁፍን ተነባቢነት የሚያረክስ አፃፃፍ ወይም አባባል ነው ። የተነሱበትን ሀሳብም ሆነ ሌላ ነገር መግለፅ ሲያቅት እና/ወይም የሚባለው ሳይኖር ሲቀር ማብቃቱ ይመረጣል ።

አስረጅ 1

- ያሳለፍናቸውን የደስታ ጊዜያት ዘርዝሬ ለመግለፅ በእውነቱ ቃላት ያጥሩኛል ።



- ኧረ የዚያን ጊዜ ነገር ስንቱ ተወርቶ !
- ባህሩን ቀለም ሰማዩን ብራና ባረገውም ስላንች ያለኝን ስሜት ፅፌ አልጨርሰውም ።
- በዚህ ጊዜ የነበርኩበትን ደስታ ምን ብዬ ልናገረው ! እንዲያው ዝም ነው ።

(13) ሰበካ

ፀሀፊዉ ለማስተማር ከሚኖረው ፍላጎት አንፃር ፣ ያለ ቦታው ተደንቅሮ የሚገኝ አጠቃላይና የግል አስተሳሰብ የሞላበት ማብራሪያ ነው ። ኪንነት የለውም ፣ ውሸት ውሸት ስለሚል . . . 'ምክርህን ራስህ ተጠቀምበት' ያሰኛል ።

አስረጅ 1

«. . . ታዛቢዎች ፣ 'ሊሆን የማይችል ነው ! ከሆነም ትክክል አይደለም ! መዋደድ መጣላትም ለእሷ ብቻ የመጣ አይደለም ። ደማሞስ ሌላ ማፍቀር አትችልም እንዴ ? እሷስ እንደሱ መሆን አትችልም እንዴ ?' ማለታችሁ የማያጠራጥር ነው ። የእኔ መልስ ግን ፣ 'እንዲህ ማለት አይገባም' የሚል ነው ። በሞት የተለያየ ሰው አልቅሶም ጨፍሮም ከጊዜ በኋላ መርሳት አይቀርም ። በቁም የተለያየ ሰው ግን በተለያየ ቁጥር መንደዱ ፣ መቃጠሉ ፣ የማይቀር ነው ። ሊጠፋ በደረሰ እሳት ላይ እንደገና በየጊዜው ክብሪት መጫር ማለት ነው ። 'በቁም ካሉ ፍቅርን እንደገና ሊመሰርቱ አይችሉም?' የሚል ጥያቄ ሊቀርብ ይችላል ። በምን መንገድ ቢመሰረት የቀድሞውን በሽታ ይሸፍናል ፣ እንደ ቀድሞው ይሆናል ማለት ከንቱ ነገር ነው ። ለማንኛውም

ነገር ቀዳሚ መፍትሔ የሚሆነው ምንንም ነገር ከመጠን በላይ አለ መውደዱ ነው . . .»

(14) <u>በመመፃደቅ</u>

አንድን ነገር ፣ ሁኔታ ወይም ባህሪ ማስረጃና ተጨባጭነት በሌለው አኳኋን ማመስገን ሲሆን ፣ ከንቱ ውዳሴና ግብዝነት ይበዛበታል ። በአብዛኛው በጥቅልና በረቂቅ ቃላት ስለሚጠቀም ኪናዊ ፅሁፍነት አይኖረውም ።

<u>አስረጅ ፩</u>

«... ባልንጀራህን እንደ ራስህ አድርገህ ውደድ የተባለው ቃል በጥብቅ የሚታሰብበት ነው ። ባልንጀራ የምስጢር ተካፋይ የልብ ወዳጅ ነው ። ባልንጀራ ስለ ጓደኛው ሕይወቱን የሚሠዋ ፣ ዓላማውን የማይለውጥ በእርግጥ የሚታመን ነው ። ማንም ሰው ቢሆን ከሚስቱ ካባቱ ፣ ከእናቱና እንዲሁም ከልጁ በፊት የደረሰበትን ወይም የሚደርስበትን ሁኔታ ለጓደኛው ለመግለጽ ይገደዳል ። በዚህ መሠረት የጓደኛነት ቃል ኪዳንና ከልብ የሠረፀ ወዳጅነት ለዘለዓለም ጸንቶ የሚኖርበት ቦታና ቤት ለማኅበራዊ ኑሮ አጠባበቅ አንድ ምስክር መሆኑ አይካድም ። ግን ፣ አንድ ጉድለት አለ ፤ ይኸውም ፍቅር በረከሰበት በአሁኑ ጊዜ የሽንገላና የክህደት መንፈሶች እየበረከቱ በመታየታቸው ነው ። አንዳንድ ጓደኛ ውለታውን አፍርሶ ሕግን ጥሶ ባልንጀራውን ይከዳል ፣ ያማዋል ፣ ወይም ለክፉ ፍርድ አሳልፎ ይሰጠዋል ። መተማመንንም ከሕሊናው ላይ ፍቆ የገዛ ጓደኛውን በጥላቻ ዐይን ይመለከታል ። ከቶውንም በደሙ ለመታጠብ በሕይወቱ ለመጫወት የሚቦዝን አይደለም ። ይህም ዓይነቱ ጓደኛ ከዲያቢሎስ ክህደት ጋር የተያያዘ የተጠላ



ምግባር በስሜቱ ላይ የበቀለበት ነው ። ጓደኛ ፣ የሚለውጥ ባህርይ ወደኋላ የሚሸሽ ተግባር ሊታበት አይገባም ። እስከ መጨረሻው በፍቅር ሰንሰለት ከባልንጀራው ጋር መያያዝ አለበት ። በጓደኛው የሚቀና ባልሠራውም ሥራ ጓደኛውን ወደ ተንኮል ማጥ ለማግባት የሚሞክር ፣ የዕዳና የመከራ ቀንበር ለመሸከም በመንፈሱም በግብሩም የሚጥር ጓደኛ የጠቅላላው ማኅበራዊ ሕይወት ጠላት መሆኑ የተሰወረ አይደለም ። እንደዚህ ዓይነቱም ጓደኛ እንደ ይሁዳ ፈገግታ በመስጠት ጻድቁን ከነሕይወቱ ለመቅበር እያሌ ጊዜ የሚፈጅበት አይደለም ። ይህም የተጠላ ተግባር በብዙዎች ላይ የደረሰ መሆኑን የያንዳንዱ ቤተሰብ ነዋሪ ደህና አድርጎ የሚያውቀው በመሆኑ እምብዛም ሊያስደንቀን አይችልም ። ግን የስሜቱ ወላፈን የአድራጎቱ አፈጻጸም የመንፈስን መልክ በንዴት ሸፍኖት እንደሚኖር አይጠረጠርም . . . »[7]

(15) <u>ጥቅልና ረቂቅ ፅሁፍ</u>

<u>አስረጅ ፩</u>

«... ዐልፈዋል የተባሉትን ዘመናት መለስ ብለን ብንመለከታቸውና ተመልክቲንም ምን ያህል የመኖር ትግል እንደ ተደረገባቸው ፣ ምን ያህል አበው ስለ ነፃነት እንደ ተሰዉባቸው ስናስተውል ፣ እንዳላለፉ ሆነው ለመገኘት የሚያስችል መልክ እናይባቸዋለን ...

---

7 የዛሬይቱ ኢትዮጵያ ፣ 'የተጠላ ተግባር' (ኢ.አ. 1954) ።

«...ይህንም ስል ባለፈው ጊዜ በቂ ተግባር ተፈፅሟልና እሱ ስለሚበቃን አሁን ዝም እንበል ማለቴ አይደለም ። ነፋስና ህይወት ዘወትር መንቀሳቀስ አለበት ...

«...አባቶች እንደዛሬው በመጫሚያ እርዳታ ሳይሆን በሌጣ ተረከዝ እየገሰገሱ ያቀኑት ፣ ያጠኑት አገር ያለው ትውልድ ፣ ምን ማሰብ እንደሚኖርበት ከህሊናው ጋር እሀ ? ብሎ መጠየቅ አለበት ።

«በጊዜው የሆነውን ያየውን ያህል እሀ ? ብሎ የሰማው የአባቶች ገድልና ተጋድሎ ቢኖር እውቀቱም ሆነ የባለታ ሪኮች ዘርነቱ ሊጸድቅለት ይችላል ።

«እነዚያ በስም ህያዋን ፣ በሥጋ ምውታን ፣ በነፍስ ጻድቃን ሁነው በመንፈስ የሚታዩን አባቶቻችን እንደ ረመጥ የሚፋጀውን ረሞጫ እየረገጡ ነው ጠረፋን ጠብ ቀው ያቆዩን ፤ ጦርነታቸውም ከሰብአዊ ጠላት ብቻ ጋር ሳይሆን ፣ ከጥይት ከሚቀድመው ከጦር ይልቅ ጠልቆ ከሚ ወጋው ከበረሃው ወባና ናላ ከሚበሳው ከሀሩሩ ትኩሳት ጋር ነበር ። ከዚህም ራቡና ጥሙ ፣ የመጓጓዣ እጦትና የመገናኛ ችግሩ ምን ያህል አዋኪ እንደ ነበር ለማወቅ አያ ዳግትም ።

«በዚያን ጊዜ ይፈለግ የነበረው አገርን ብቻ ከጠላት ተከላክሎ ማስቀረትና ስንዝር መሬት እንኳ ቢሆን ተቆርሶ እንዳይሄድ ተከላክሎ ማኖን ነበር ። ይህም አልቀረም ። ተደርጓል ። ኢትዮጵያ ለሲሳያቸው ትሆናቸው ዘንድ ጓጉ ተው ለመጡት ወራሪዎች ለመቃብራቸው እስከትሆን ድረስ ብዙ ገድል ፈጽመዋል ።



«ይህን የመሰለው የከባድ ትግል ኑሮ ካለፈ በኋላ የተወ ለደው ትውልድ የዛሬውን ብቻ ሲከታተልና የአሁኑን ብቻ ያዝሁህ ፣ ያዝሁህ ሲል ያለፈው እንዳያመልጠው ዐይኑን ወደ ዘመናት ማዶ መወርወር አለበት ...

«...በአሁኑም በምቾትና በተድላ ዘመን የሚገኝ ትው ልድ ፣ የጊዜው ምቾትና ደስታ የዱሮውን ያባቶቹን መከ ራና ሥቃይ ያስዘነጋዋል ተብሎ አይታሰብም ።

«የታሪክ እባቱን የረሳ ሕዝብ መሠረት የሌለው ሕንፃ ማለት ነው ። የትምህርት መጀመሪያ ፊደል እንደሆነ ሁሉ ለማናቸውም ዕውቀትና ጥበብ ወይም ኑሮና ደረጃ ፣ ታች ኛው መነሻ የተፈጠረባትን አገር እንደ አውታር ወጥሮ ይዞ ፣ ነጻነቷ እንዳይረግብ ፣ በሯ እንዳይንገረበብ ፣ ጋሻዋን ጨብጦ አቆይቶ ለትውልድ ማስተላለፍ የጊዜውን ብቻ ለሚከታተል ትውልድ ዘበት ይመስለው ይሆናል ።

«ለአንድ ክፍል ዓለም ሕዝብ ዋና ችግሩና የቆዳ በሽ ታው ከኃይል በታች በመውደቅ የሚደርስበት የተገዥ ነት ቀንበር ነው ።

«ይህም ከባድና አስጨናቂ ቀንበር በብዛት ወድቆ የነበረው በነማን ጫንቃና በነማን ትከሻ እንደ ነበር ስናስብ ፣ የዛሬው ዓለመኛ የጥንቱ መከረኛ አፍሪካ ትዝ ይለናል ...

«...አፍሪካ በተፈጥሮ ሕያዋንና አግአዝያን የሆኑ ህዝ ቦች የሰፈሩበት ከላይ አየርና ሰማይ ጨረቃና ፀሐይ ከታ ችም ምድርና ቀላይ ያሉበት ፣ አዝማናትና ዓመታት ያል ተከፈሉበት ... ራሱን የቻለ ዓለም መሆኑን የተፈጥሮ አመዳደቡ ይመሰክርለታል ።

«በቀለም ልዩነትም ቢሆን የሌሎች ነጭነትና የእሱ ጠይምነት ከአዳም የደም ጋን የተቀዳና ማእሰ አካሉም (የሥጋውም ቆዳ) ከዚያው ከአዳም ማእሰ ሥጋ የተወሰደ እንጂ ከሌላ የታፈፈና የታረፈ ገላ አይደለም ።

«የመጀመሪያው ሰው የመልኩ ቀለም ነጭ ወይም ጥቁር ወይም ቢጫ መሆኑ በምን ሊታወቅ ይቻላልና ነው ፣ የቀለም ተመፃዳቂዎች የሚኩራሩት?»[8]

ፅሑፉ 550 ያህል ጥቅል ቃላት ይዟል ። ጥቅል ቃላት ረቂቅ እሳቤዎች ናቸው ፤በይበልጥም የሳይንስና ፍልስፍና ሀሳቦችን መግለጫ በመሆናቸው ፣ ይህን ፅሁፍ ደብዛዛና ዝብዝብ የበዛበት አድርገውታል ። ባጠቃላይ ፅሁፉን ከዳ ከሙት ውስጥ የሚከተሉት ነጥቦች ይገኙበታል ፣

### (ሀ) ድግግሞሽ

#### (1) ዘመኑን ካለ መወሰን እንግር

- ያለፈው ዘመን ...
- አልፈዋል የተባሉት ዘመናት ...
- ባለፈው ጊዜ ...

ፀሀፊው የሚፅፍበትን ዘመን እስኪወስን ድግግሞሽ አብዝቷል ። ጊዜውን ከወሰነ እንኳ በኋላ በነዚሁ አመታት ውስጥ ስለ ተደረገው በሚውሳት ፋንታ ሲዋዥቅ ይታያል ።

8 የዛሬይቱ ኢትዮጵያ ፣ 'ህያውነት ያለው የጀግኖች አባቶቻችን ታሪክ' ፣ (እ. እ. 1954) ።



#### (2) ሀሳቡን ካለመጨበጥ እንግር

- የዛሬውን ብቻ ሲከታተል ...
- የአሁኑን ብቻ ያዝሁህ ያዝሁህ ሲል ...
- የመኖር ትግል እንደ ተደረገባቸው ...
- መለስ ብለን ብንመለከታቸው
- ያለፈው እንዳያመልጠው ዐይኑን ወደዘመናት ማዶ መወርወር አለበት
- የጊዜው ምቾትና ደስታ
- በአሁኑ በምቾትና በተድላ ዘመን የሚገኝ ትውልድ

### (ለ) ክሊሼና ምሳሌ

- የዛሬው ዓለመኛ የጥንቱ መክረኛ

### (መ) አግባብ የሌለውና በፅሁፉ በተጨባጭ ያልተደገፈ ጥላቻ

- ይህን የመሰለው የከባድ ትግል ኑሮ ካለፈ በኋላ የተወለደው ትውልድ (የትግል ኑሮው አልተገለፀም)
- የዛሬውን ብቻ ሲከታተልና የአሁኑን ብቻ ያዝ ሁህ ያዝሁህ ሲል
- እህ ? ብሎ የሰማው የአባቶች ገድልና ተጋድሎ ሲኖር እውቀቱም ሆነ የባለታሪኮች ዘርነቱ ሊፀድቅለት ይችላል

- አባቶች . . . እየገሰገሱ ያቀኑት ፥ ያጠኑት አገር ያለው ትውልድ ምን ማሰብ እንደሚኖርበት ከህሊናው ጋር እህ ? ብሎ መጠያየቅ አለበት
- የጊዜውን ብቻ ለሚከታተል ትውልድ ዘበት ይመስለው ይሆናል

### (ለ) ደብዛዛ ዘይቤ

- የተፈጠረባትን አገር እንደ አውታር ወጥሮ ይዞ
- ጋማዋን ጨብጦ
- በስም ህያዋን በሥጋ ምውታን በነፍስ ጻድቃን
- በመንፈስ የሚታዩን አባቶቻችን
- የሌሎች ነጭነትና የእሱ ጠይምነት ከአዳም የደም ጋን የተቀዳ

### (ሬ) የተደረተ ተራ ሀሳብ

- አፍሪካ በተፈጥሮ ህያዋንና እግእዝያን የሆኑ ህዝቦች የሰፈሩበት
- አፍሪካ . . . ከላይ አየርና ሰማይ ፥ ጨረቃና ፀሀይ ፥ ከታች ምድርና ቀላይ ያሉበት
- አፍሪካ . . . አዝማናትና አመታት ያልተከፈሉበት

### በራሱ ቋንቋ ሲስተካከል

ይህንም ስል በቂ ተግባር ተፈፅሟልና እሱ ስለሚበቃን አሁን ዝም እንበል ማለቴ አይደለም ። ነፍስና ህይወት ዘወትር መንቀሳቀስ አለበት ...



... የታሪክ አባቱን የረሳ ህዝብ መሰረት የሌለው ህንፃ ማለት ነው ።

የትምህርት መጀመሪያ ፊደል እንደሆነ ፥ ለማናቸውም ዕውቀትና ጥበብ ወይም የኑሮ ደረጃ ፥ ታችኛው መነሻ የተፈጠሩባትን አገር ነፃነቷ እንዳይረግብና በሯ እንዳይንገረበብ ... ጠብቆ አቆይቶ ለትውልድ ማስተላለፍ ዘበት ይመስለው ይሆናል ። ይህም አልቀረም ተደርጓል ። ኢትዮጵያ ለሲሳያቸው ትሆናቸው ዘንድ ጓጉተው ለመጡት ወራሪዎች ለመቃብራቸው እስክትሆን ድረስ አባቶቻችን ብዙ ገድል ፈጽመዋል ።

ገድሉንም የፈጸሙት እንደዛሬው በመጫሚያ እየሄዱ ሳይሆን በሌጣ ተረከዝ ፥ እንደ ረመጥ የሚፋጀውን ረምጫ እየረገጡ ነው... ። ጦርነታቸውም ከሰብአዊ ጠላት ብቻ ጋር ሳይሆን ከጥይት ከሚቀድመው ከጦር ይልቅ ጠልቆ ከሚወጋው ከበረሃው ወባና ናላ ከሚበሳው ከሀሩሩ ትኩሳት ጋር ነበር ። ከዚህም ራቡና ጥሙ ፥ የመጓጓዣ እጦትና የመገናኛ ችግሩ ምን ያህል አዋኪ እንደ ነበር ለማወቅ አያዳግትም . . . .

ለአንድ ክፍለ አለም ህዝብ ዋና ችግሩና የቆዳ በሽታው ከሀይል በታች በመውደቅ የሚደርስበት የተገዥነት ቀንበር ነው ። ይህም ከባድና አስጨናቂ ቀንበር በብዛት ወድቆ የነበረው በነማን ጫንቃና በነማን ትከሻ እንደነበረ ስናስብ... አፍሪካ ትዝ ይለናል ።

አፍሪካ አንድ ሙሉና ሰፊ ክፍለ ዓለም ነው ። ሌሎች ከተደረገላቸው ተፈጥሮ የጎደለበት ነገር የለም።በቀለም ልዩነትም ቢሆን ፥ በሌሎች ነጭነትና በእሱ ጠይምነት ረገድ ደሙ ከአዳም የደም ጋን የተቀዳና ማእሰ አካሉም (የሥጋው ቆዳ) ከዚያው ከአዳም ማእሰ ሥጋ የተወሰደ እንጂ ከሌላ የታረፈና የታረፈ ገላ አይደለም ። የመጀመሪያው ሰው የመልኩ

ቅለም ነጭ ወይም ጥቁር ወይም ብጫ መሆኑ በምን ሊታወቅ ይቻላልና ነው የቀለም ተመፃዳቂዎች የሚኩራሩት ?...»

## (16) የዓይነ ሰውኛ

### አስረጅ 1

. «መጠጥ በጠጪው አካል ላይ ጉዳት ከማድረሱ በፊት ፥ በቃናው ጣፋጭነት እያታለለ ቀስ ብሎ ይገባና በአንጎል ላይ የማዘዝ ሥልጣኑን ሲቀዳጅ ፥ መላውን የሰውነት ክፍል በፈለገው ዓይነት ሊዳኝ የሚችል የዲክታተሮች ጥሩ ምሳሌ ነው ። የግዛቱም ክልል ከጣሳ በር ጀምሮ እስከ ሻምፓኝ ዳርቻ ስለሆነ ፤ ከትንሽ እስከ ትልቅ ያሉትን ለይቶ ያውቃቸዋል ። የአገዛዙም ፈሊጥና ጥበብ አንዱን በማስለቀስ ፥ ሌላውን በማሣቅ ፥ የሚመራበት ሕግና ደንብ ሲኖረው ትንሹን ሳይንቅ ፥ ትልቁን ሳይፈራ በስነ ሥርአት ያስተዳድራል ። በተለይ የሕይወታችን መቅረዝ ብልጭ ድርግም እያለች « መቆየት ደግ ነው » የምንለው እኔና ቢጤዎች ፥ ያችኑ የመነመነች የሕይወት አውታር በዚያ ስለታም የመጋዝ ጥርሴ በጥሶ እስኪጥላት ፥ ያለንን ፍቅር ሳናጓድል አሜን ብለን እንገዛለታለን . : . »

. «ባሕሮች አስጨፋሪያቸውና አስቦራቂያቸው ከሆነው ከነፋሱ የሚያገኙት ውዝዋዜና ንቅናቄ ለተፈጥሮዋቸው የሚመች የጤና አጠባበቅ ዘዴ ሳያስገኝላቸው አለመቅረቱን ለመረዳት ማዕበሉ ከነፋሱ ጋር ያለው ትግል ናልፊያ ሊያስረዳን ይችላል »

. «በኢትዮጵያ ታላቅ ታሪክ ታየ ። ምድር እልል አለች ። ተራሮች አሸበሸቡ ፤ ኮረብቶች አጨበጨቡ ።



ኢትዮጵያ ደስታዋን እንኳን ለምድርና ለሰማይ አካፈለችው... »

## (17) የባእድ ቋንቋ ፈሊጥ

### አስረጅ 1

- ‘ያልተወጠረ ጊዜ ስላገኘ መታጠቢያ ክፍል ገብቶ ሶስት የአለም አቀፍ የኮሚኒስት ጋዜጦች እያነበበ . .’
- ‘ከቀሚሶቻቸው ጥለት ላይ ተቋጥረን ከአንድ ቀላፊ በሽታ ድነናል ... ’ [9]
- ‘ባያቴ ቀሚስ ተጠልዬ የታላቁ የብረት መድፍ አሳታዊ እስትንፋስ ርቆ ሄደ ...’ [10]
- ‘ባለግርማዊ ጧት ወደ ዓለም መጣ ...’ [11]
- ‘ጨለማው የቅጠሎቹን ብዛት አወፍሮት ነበር ...’ [12]
- ‘የስረገላ ጉሽግ መንጎጠጥ የጉድጓድ መንገ ጫገጭ ከኮቴዎች እንቅስቃሴ ተሰማ ...’ [13]
- ‘በመንገድ የምትጓዘው ሠረገላ አቅለሽልሿት የወደቀች ትመስል ነበር ...’ [14]
- ‘ትናካሽ ብርድ ቀሰቀሰኝ ...’ [15]
- ‘የጦርነቱን ተናካሽ ጢስ ምኄዋለሁ ...’[16]

ከ9—16 ኗቶሬ ‘ናጊቡን ፥ ‘የሲጃራ ማጨሻዎቱ’ ።

(18) ፀያፍ

አስረጅ ፤

'... የወንድ ስኳር የሚፈልገው ሀሞቢ ሞቷል...'

'... እስኪያልባቸው ተላላሱ ፣ ምላስ ለምላስ ተቆላለፉ ፣ ጥርስ ለጥርስ ተሞራረዱ ...'
'... ማሪን አትንካ ስትለው ፣ ሲተሻሹ ፣ ሲጋፉ ፣ ሲሟረዱ ፣ ሲቧረሹ ፣ ሲዳሰጡ ትዝ ድንዝዝ አለው ...'

(19) በተጨማሪ በኪነ-ፅሁፍ ውስጥ ፣ ከባድ የአማርኛ ቃላትና ፈሊጥ ፣ የግእዝ ቃላት ፣ እምብዛም ያል ተለመዱ ባእድ የተውሶ ቃላት በብዛት ተገድ ግደው ከተገኙ የሀሳቡን እና/ወይም የስሜቱን ሽግግር እንደሚያጨልሙት መታወቅ አለበት።

## 2.6 ማጠቃለያ

እስካሁን ስለ ቃላትና በቃላት አጠቃቀም ወቅት ስለሚገ ጥሙ ችግሮች በሰፊው ተወያይተናል ። ቢሆንም ፣ ቤት በጡብ እንደሚገነባ ሁሉ እነሱም የሀሳባችንና/ወይም የስሜታችን መገንቢያዎች ስለሆኑ አንዳንድ አበይት ነጥ ቦችን እንደገና ማጤን ይኖርብናል ።

(1) በነጠላ ትርጉም ረገድ

(ሀ) በይበልጥ ነጠላ ትርጉማቸው ቁጭ ቁልጭ ባለ ቃላት መጠቀም ፤ ደብዛዛ ትርጉም ያላቸ ውን ማስወገድ ፤



ለምሳሌ ፣ አንድ ፀሀፊ በድርሰቱ ውስጥ ፣ አንድ አይነተኛ ገፀ ባህሪ ፣ ፖለቲካን በሚመለከት ጉዳይ የሚ ታይበትን አጉል ተከራካሪነት ለመግለፅ ፈልጐ ፣ 'ግርማ ዘብዛባ ነው' ብሎ እንደሆነ ፣ ፅሁፉን መልሶ እያነበበ ሲያ ስተካክል ዘብዛባ የሚለው ቃል ነገር ማብዛትን እንጂ ፣ ለመግለፅ የፈለገውን አጉል የክርክር አያያዝ እንዳልገለፀለት ከተረዳ ፣ ወደ ጠብ የሚያመራ አጉል ክርክር ከሆነ ፣ በአተካ ረኛ ፣ ክርክር ተያዝ የማያበቃ ከሆነ ፣ በጨቅጫቃ (ነዝናዛ) ፣ ክርክር የማያበቃ ብቻ ሳይሆን ተሰላችተው ጥለውት ሲሄ ዱም የማይለቅ ሲሆን በሞዣዣ ፣ መለወጥ ይኖርበታል ማለት ነው ።

'ወይም ፣ ግርማ ልጅ የለውም' የሚል አረፍተ ነገር ቢገጥ መውና ለመግለፅ የሚፈልገው ግርማ ልጅ የሌለው መሆኑን ብቻ ሳይሆን ፣ ጨርሶ ልጅ ሊኖረው የማይችል መሆኑን ከሆነ ፣ አረፍተ ነገሩን ፣ 'ግርማ መካን ነው' ወይም፣ 'ግርማ ፍሬ ሊኖረው የማይችል ነው' ወደሚል መለወጥ ይኖር በታል ። በዚህ ላይ ፍሬ የማይኖረው የተለያየ 'ነገር' ስላለ ምርጫውም ከዚያው አንፃር መሆን ይኖርበታል ፤ ለምሳሌ ፣ መካን ወንድ ፣ መሲና ላም ፣ የማታፈራ ዛፍ ወዘተርፈ...

አንዳንድ ጊዜ የግስና የስም መስማማትና አለመስማማ ትም ሊገጥም ይችላል ፤ ለምሳሌ ፣ 'ቡና ይፈላል' እንጂ 'ቡና አይጠመቅም' ፤ ወይም 'ጠላ ይጠመቃል' እንጂ 'አይ ፈላም' ።

(ለ) ነጠላ ትርጉም ስንል የድርብ ቃላትን ፣ እንደ ቃል የሚያገለግሉ ሀረጎችንና የግንድ ቃላትን እርባታና

ሂደት ጭምር ማለታችን ስለሆነ፣ አንድ ቃሉ ተሳሳቢነት እያዩ ቃላትን ለማወላለድና በየሂደቱ ውስጥ ያሉትን ለመ ዘርዘር መቻል ።

ለምሳሌ የወረደን እርባታና፣ የመዝራትን ሂደት ብን መለከት ።

የ 'መዝራት' ሂደት

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| መዝራት | መዘርዘር | መድረቅ | መነፈስ | መሰለቅ |
| መብቀል | ማሸት | መታጨድ | መመረት | መቦካት |
| መበቅየት | መጐምራት | መሰብሰብ | መሸክሸክ | መቀጠን |
| ማበብ | መገርጣት | መከመር | መፈተግ | መጋገር |
| | | መወቃት | መስጣት | መበላት |
| | | | መገርደፍ | |

የ'ወረደ' እርባታ

| | |
|---|---|
| ውርድ | ውርርድ |
| ውርዶ | ተዋረድ |
| ውራጅ | መወራረጃ |
| ውርደት | ውርጃ እና የመሳሰሉት ናቸው ። |

ይህን አይነት አሰራር፣ ቃላቱን በመሰረቱ ትርጉማቸው ጠቋሚነት፣ በግልፅና በትክክል እንድናጤናቸው ከመጥ ቀሙም በላይ ላንዳንድ፣ የተለመዱ ቃላት ለማይገኙላቸው፣ ሀሳቦቻችን እና/ወይም ስሜቶቻችን፣ ቋንቋው በሚሰራበት ያረባብ ስልት መሰረት ሊለመዱ የሚችሉ ቃላትን ለመፍጠር ያስችለናል ።

ምሳሌ 1

| | | |
|---|---|---|
| ወረደ | ወረሰ | በረደ |
| ውራጅ | ውራሽ | ብራጅ |
| ውርርድ | ውርርስ | ብርርድ |
| ውርጃ | ውርሻ | ብርጃ |
| ውርዶ | ውርሶ | ብርዶ |
| ወራዳ | ወራሳ | በራዳ |
| ወራጅ | ወራሽ | በራድ/ብራጅ |
| ወረዳ | ወረሳ | በረዳ |



እንደ ውርሻ ፣ ውርሶ ፣ ወራሳ ፣ ወረሳ ወይም እንደ ብርጃ ፣ ብርዶ ፣ በራዳ ፣ በረዳ አይነቶቹን ቃላት በወረደ ውስጥ ያሉት የቃላት ቅርፆች ለሚሰጡት ትርጉም አይነት ለማዋል እንችላለን ማለት ነው ።

(መ) ስለ አንድ ሀሳብ እና /ወይም ስሜት ለመፃፍ ከመነሳታችን በፊት፣ በየፈርጁ የሚገኙትን ቃላት ማጤን ። ለምሳሌ፣ ስለ ግብርና ወይም ስለ ሽመና እንፅፍ እንደሆነ፣ ዋና ዋና የተግባር ስሞችንና ግሶችን በቅድሚያ ብናጤ ናቸው ይበጃል ።

| ዋና ዋና የተግባር ስሞች | | ዋና ዋና ግሶች | |
|---|---|---|---|
| ግብርና | ሽመና | ግብርና | ሽመና |
| ሞፈር | መምቻ | አረሰ | አደራ |
| ቀምበር | መጠቅለያ | ተለመ | ቆጠረ |
| ማነቆ | ባላ | ተረተረ | ቋጠረ |
| ወገል | መወጠሪያ | ገለገለ | ዘረዘረ |
| ምራን | መን | ጨፈለቀ | ሸመነ |
| ማረሻ | አርብ | ዘራ እና | ቆረጠ |
| እርፍ | ድውር | የመሳሰሉትን ። | ቋጨ እና የመ |
| ድግር እና | መቂናጥ | | ሳሰሉትን ። |
| የመሳሰሉትን ። | መወርወሪያ ፣ | | |
| | መዘርዘሪያ እና የመሳሰሉትን ። | | |

በዚህ አይነት ቃላትን ካላቤት ስለሚፅፉት ሀሳብ እና/ወይም ስሜት አለማወቅን ስለሚያሳይ በፅሁፉ እም ነትን ያሳጣል ።

ለምሳሌ ፤

'ገበሬዉ ማረሻውን ተሸክሞ አገኘሁት'፣ ወይም፣ 'ሸማ ኔዉ የድሩን መቃ ቶሎ ቶሎ ይጨርሳል' ቢል፣ ፀሀፊው ለማለት የፈለገውን እንዳላስተላለፈ ይታያል ፤ ማረሻ ቢል አፈር መሰንጠቂያውን ብረት ፣ የድር መቃ ቢል ራሱን ድር ማዳወሪያውን መቃ ካልሆነ በስተቀር ፤ ማለትም — ማረሻ ፣ ለምፈር ቀንበር ፣ የድር መቃ ለድውር መተኪያ ሊሆኑ አይችሉም ማለት ነው — አሳቡን አልገለፀም ።

(ለ) ከተመሳሳዮችና ከተቃራኒዎች ውስጥ ማንኛ ውንም ተመሳሳይ ወይም ተቃራኒ ቢሆን ይሰራል ብሎ ከመውሰድ ይልቅ፣ የተፈለገውን ሀሳብ እና/ወይም ስሜት በትክክል የሚገልጠውን መምረጥ ።

ለምሳሌ፣ ጋለበ በሚለው አጠቃላይ ቃል ጥቅል ሀሳ ብን በመግለፅ ፈንታ፣ 'ሸመጠጠ፣ ሰገረ፣ አረተረተ፣ አቦ መሮመና' በመሳሰሉት፣ ወይም 'ሀይለኛ ነፋስ' በሚለው አጠቃላይ ቃል በመግለፅ ፈንታ፣ 'ሽምልምል ነፋስ፣ ጠሮ ነፋስ፣ ሀብላይ ነፋስ፣ ጉደሬ ነፋስ፣ ሾተሌ ነፋስ፣ እምባላይ፣ ውቅንብል፣ አፈር' እና በመሳሰሉት ቃላት መጠቀም ያስፈልጋል ።



(2) <u>በአዛማጅ ትርጉም ረገድ</u>

ቃሉ ከሚኖረው ነጠላ ትርጉም ውጪ፣ ከልዩ ልዩ የኢኮኖሚ፣የፖለቲካና የሶሻል ለውጥ የተነሳ፣የሚሰጠውን አካባቢያዊ ትርጉም (መልካምም ሆነ አጉል) ማወቅና በአግባቡ መጠቀም ።

(አዛማጅ ትርጉም፣በአብዛኛው የእጅ ሙያንና ሌሎች ጥበባትን ለማኪያኪያስና ባለሞያዎቹ በህብረተሰቡ ውስጥ ያላቸውን ሚና ለማሳነስ በሚደረግ የቃላት አጠቃቀም ረገድ የሚታይ ሲሆን፣ በተለይ ለሞያ ስሞች አንጉል ትር ጉም መስጠትን ያጠቃልላል ።)

ምሳሌ ፣

(ሀ) <u>ከተግባር ስሞች</u>

| <u>አጉል አካባቢ ትርጉም ያላቸው</u> | <u>በመጠኑ ተቀባይነት ያላቸው</u> |
|---|---|
| ጠይብ | አንጥረኛ |
| ባለጅ | ወርቅአፍሳሽ |
| ቀጥቃጭ | ብርአፍሳሽ |
| አዝማሪ | ዜመኛ |
| አርሆ | ዘፋኝ |
| | አንጎራጓሪ |

(ለ) <u>ከሌሎች ስሞች</u>

| <u>አካባቢያዊ ትርጉ ማቸው የተበከለ</u> | <u>ያልተበከለ</u> |
|---|---|
| አጋሰስ | ሰንጋ ፈረስ |
| መጋዣ | ሎሌ ፈረስ |

| | |
|---|---|
| ጌኛ | ድግግሳ |
| ወቀሬ | ባዝራ |

እነዚህ ቃላት ፈረስ ለሚለው ቃል ቢቆሙም ፣ 'ሙሽ ራው በወቀሬ ወይም በጌኛ ተቀምጦ መጣ' እንደማንል አስተውል ፤ በተለየ የአካባቢ ትርጉሙ መጠቀም ፈልገን ካልሆነ ።

(3) <u>በተቻለ መጠን ከረቂቅ ቃላት ይልቅ በብቸኛ መጠሪያ (ቃል) ወይም በክቻርጌ ቃል መጠቀም ፤</u>

(ከገፅ 32 እስከ 41 ተመልከት ።)

<u>ምሳሌ ፣</u>

| <u>አንፃራዊ ረቂቅ</u> | <u>አንፃራዊ ብቸኛ</u> |
|---|---|
| በእጁ መፅሀፍ ይዟል ። | በእጁ የሀዲስ አለማየሁን ፣ 'ወንጀለኛው ዳኛ' ይዟል ። |
| ውበትን አድናቂ ነበረች ። | በእንጦጦ ተራራ ላይ የሰፈረውን ቀስተ ደመና አደነቀች ። |

እዚህ ላይ፣አጠቃላይ አስተያየት የምንሰነዝርባቸው ቦታዎች የሉም ፣ ማለት ስላልሆነ ጥንቃቄ ያስፈልጋል ። ለምሳሌ ፣ 'ውበትን ማድነቅ የሰው ልጅ እድገት ውጤት ነው' የሚል አጠቃላይ ሀሳብ የያዘ አረፍተ ነገር ካስፈለገ ፣ በዚህ አይነት አባባል መቅረብ ይኖርበታል ። 'ቀስተ ደመናን ማድነቅ ፣ የአስቴር ኮሌጅን መጨረስ ውጤት ነው' ተብሎ መለወጥ የለበትም ፤ ለማለት የተፈለገው የመጀመሪያውን እንጂ ሁለተኛውን ስላልሆነ ።



(4) <u>ቢቃላት ድግግሞሽ በጥንቃቄ መጠቀም</u>

ቃላትን መደጋገም የሚያስፈልግባቸው ሁኔታዎች ያሉ ቢሆንም ፣ ድግግሞሹን እንዳይሰለች ለማድረግ በተውላጠ ስሞችና በተመሳሳይነታቸው ቅርበት ባላቸው ቃላት መጠቀም ያስፈልጋል ። አለዚያ ፅሁፉ ከይዘቱ ይልቅ ወደ ድግግሞሹ ስለሚስብ ሀሳቡ እና /ወይም ስሜቱ የተጠበቀውን ያህል እርካታ አይሰጥም ።

(5) <u>ክሊሼዎችን ቢቻል ማስወገድ ፣ ካልተቻለም አጠ</u> ቃቀማቸውን በመጠኑ ማድረግ ።

አንድ በአነጋገር እና/ወይም በፅሁፍ ውስጥ በመደጋገም የሚገኝ ንኡስ ሀረግ ወይም ሀረግ (እንደ ሁኔታው እነዚህም እንደ ስያሜ ቃል የሚወሰዱበት ጊዜ ስላለ) የሚደጋገመው አባባሉ ምስላዊነት ፣ ግልፅትና ታዋቂነት ስላለው ነው ። ስለዚህም ፣ በቀላሉ የማይተካ ስለሚሆን በንግግርም ሆነ ፅሁፍ ውስጥ ብቅ ጥልቅ ማለቱ አይቀርም ። በተለይ በኪነ-ፅሁፍ ውስጥ በይበልጥ መገኘቱ አይቀርም ፤ ኪነ-ፅሁፍ ምስላዊነትንና ስሜት ፈንጣቂነትን ስለሚሻ ። ስለዚህ በተለይ በኪነ-ፅሁፍ ረገድ ፣ ቢቻል አዳዲስ ንፅፅር ወይም ተምሳሌት መፈለግ ፣ ካልተቻለ ደግሞ እንዳይበዛ አድርጎ መጠቀም ይመረጣል ።

ምእራፍ ሶስት

# አረፍተ ነገር

## 3.1 መግለጫ

ቃላት ለየብቻቸው ሲሆኑ የሚኖራቸውን ሙያና አገልግሎት ተመልክተናል። አሁን ደግሞ ቃላት ከሌሎች ቃላት ጋር ሆነው አረፍተ ነገር ሲሰሩ እናያለን ።

በዚህ ክፍል አረፍተ ነገር ምን እንደሆነ የሚገልፅ ዝርዝር ውሳኔ አንሰጥም ፣ ትኩረታችን በአገልግሎቱ ላይ ስለሚሆን ። ስለዚህ ለመግቢያ ያህል ቃላት ንኡስ ሀረግ እየሆኑ፣ ንኡስ ሀረጎች ጥገኛ ሀረግ እየሆኑ አድገው የመጨረሻው አረፍተ ነገር መሆኑን ከተገነዘብን ይበቃናል ።

## 3.2 የአረፍተ ነገር ክፍሎች

አንድ አረፍተ ነገር ሁለት ዋና ዋና ክፍሎች ሊኖሩት ይገባል — በመሰረቱ (አንዳንዴ ባይኖረውም እንዳትገረሙ ለማለት ያህል )።

3.2.1 ስም ወይም ስምን የመሰለ ስምን የሚወክል — የአረፍተ ነገር ባለቤት በመሆን የሚታወቅ ፤

3.2.2 ግስ ፣ የአረፍተ ነገር ማሰባሰቢያ ወይም መቋጫ — ማሰሪያ አንቀፅ በመሆን የሚታወቅ ፣



ለምሳሌ ፣ 'መፅሀፉን ሰጠው' የሚል አረፍተ ነገር ቢኖር 'መፅሀፍ' ስም ፣ 'ሰጠው' አንቀፅ ይባላሉ ማለትነው ።

ነገር ግን ፣ አረፍተ ነገር በስምና በአንቀፅ ብቻ ላያበቃም ይችላል ፤ እንደ ሁኔታው የስም ጓዞች (ተጨማሪዎች) እና የግስ ጓዞች ይኖሩታል ። ጓዞቹ የሚያገለግሉት ዋና ዋናዎቹን ሁለት ክፍሎች (ባለቤቱንና አንቀፁን) ለመወሰን ወይም ለማብራራት ነው ።

ለምሳሌ ፣ የሚከተለውን አረፍተ ነገር እንመልከት ፤

'እምብዛም እትምህርት ቤት ገብቶ ሳይማር ፣ ብልህና አስተዋይ መሆኑ የሚነገርለት አስፋው ፣ አምስት ጊዜ ያህል ደጋግሞ ያነበበውን ፣ 'የኢትዮጵያ አብዮት' የሚል በሰማያዊ ጥራዝ ያጌጠ መፅሀፍ ፣ በታታሪነቱና በምርታማነቱ ለታወቀው ወጣት ሰራተኛ ፣ ለገብሬ ፣ አይን አይኑን እየተመለከተ ሰጠው ። '

በዚህ አረፍተ ነገር ውስጥ አስራ ሁለት አረፍተ ነገሮች አሉ ፤

- አስፋው እትምህርት ቤት ገብቶ አልተማረም ።
- አስፋው ብልህ መሆኑ ይነገርለታል ።
- አስፋው አስተዋይ መሆኑ ይነገርለታል ።
- አምስት ጊዜ ያህል ደጋግሞ አንብቧል ።
- መጽሀፉ 'የኢትዮጵያ አብዮት' የሚል ነው ።
- መጽሀፉ በሰማያዊ ጥራዝ ያጌጠ ነው ።
- ገብሬ ወጣት ሰራተኛ ነው ።
- ገብሬ በታታሪነቱ የታወቀ ነው ።
- ገብሬ በምርታማነቱ የታወቀ ነው ።
- በአድናቆት አይን ተመለከተው ።
- በምስጋና አይን ተመለከተው ።
- አስፋው ለገብሬ መፅሀፍ ሰጠው ።

በአረፍተ ነገሩ ውስጥ ዋናውን ሀሳብ የያዘው ዋናው አረፍተ ነገር ፣ 'እስፋው ለገብሬ መፅሀፍ ሰጠው' የሚለው ነው ። የቀሩት የባለቤትና የአንቀፅ ጓዞች ናቸው ። በሌላ አነጋገር ፣ በአረፍተ ነገሩ ውስጥ ያለው አንድ ዋና አሳብ ሲሆን ፣ የቀሩት የዋናዉ ሀሳብ ተገዥዎች ናቸው ።

የባለቤት ጓዝና የአንቀፅ ጓዝ ስንል ደግሞ ፣ ማንኛውም አይነት ጓዝ አይደለም ፤

- የስም ጓዝ ፣ ቅፅልና ቅፅልን የመሳሰሉት ሲሆኑ ፣
- የግስ ጓዝ ደግሞ ፣ ተውሳከ ግስና የተውሳከ ግስን ስራ የሚሰሩ ብቻ ናቸው ።

ባጠቃላይ ከዚህ በላይ በተጠቀሰው አረፍተ ነገር ውስጥ አስራ አንዱ አረፍተ ነገሮች ፣ እንደ ቅፅል የስም ተገዥ ፣ እንደ ተውሳከ ግስ ደግሞ የግስ ተገዥ ሆነዋል ማለት ነው ። (ተገዥነቱን ያመጣባቸው መስተፃምር ተጭ ኗቸው ስለሆነ ለዝርዝሩ የሰዋስው መፅሀፍ ተመልከት ።)

### 3.3. የአረፍተ ነገር አገባብ ስልቶች *

#### 3.3.1. በአገልግሎታቸው

በአገልግሎታቸው የታወቁ አራት የአረፍተ ነገር አይነቶች እንዳሉ ይነገራል ፤ አወንታ ፣ ጥያቄ ፣ ትእዛዝና አጋኖ ።

(ሀ) አወንታ አረፍተ ነገር ፣ ጥያቄ የሚጠይቅ ወይም ትእዛዝ የሚያስተላልፍ ወይም ነገሮችን አግኖ የሚያቀርብ ሳይሆን ፣ ስለ ነገሮች ፣ ጉዳዮች ወይም ስሜቶች ቀጥታ የሆነ አስተሳሰብን ማስተላለፊያ አረፍተ ነገር ነው ።

ምሳሌ ፣

'ወንበር መቀመጫ ነው ።'
'ፍቅር ይዞታል ።'
'መፅሀፍ ማንበብ ይጠቅማል ።'

(ለ) ጥያቄ አረፍተ ነገር — ስለ ማንኛውም ጉዳይ በጥያቄ መልክ የሚቀርብበት አረፍተ ነገር ነው ።

ምሳሌ ፣

'ቤትህ ትሄዳለህ?'
'ማነው የወሰደው?'
'ምን ትፈልጋለህ?'
'ትመጣለህ ወይ ?'
'መጣሽን ?'

(መ) ትእዛዝ አረፍተ ነገር ፣ ስለ ማንኛውም ጉዳይ በትእዛዝ ወይም በፈቃድ መልክ የሚቀርብበት አረፍተ ነገር ነው ።

ምሳሌ ፣

'መፅሀፉን እንድትመልስ ።'
'አዲሳባ ከሄድህ ዘመዶቼን ጠይቅልኝ ።'

(ሰ) አጋኖ አረፍተ ነገር ፣ ስለ ማንኛውም ጉዳይ ድንገተኛና ሀይለኛ ስሜት የሚቀርብበት አረፍተ ነገር ነው ። ባሁኑ ጊዜ የስሜቱ ጠንካራነት ሳይሆን በአረፍተ ነገር መጨረሻ እጅ እንዳመጣ የአጋኖ ምልክት (!) መጨመር ተለምዷል ፤ ስህተት ነው ። ስሜቱ ካለ ግን የአጋኖ ምልክቱ ሊኖርም ላይኖርም ይችላል ።

* የአረፍተ ነገር የአገባብ ስልቶችን የጠቀስነው ለማስታወስ ያህል ነው እንጂ ፣ ዝርዝር ገለፃው የዚህ መመሪያ አካል አይደለም ።

ምሳሌ ፣

'ድንገት ከተፍ ስትይ !'
'ያ ሁሉ ሩጫዬ በከንቱ !'
'አ ! ልቤ እንዴት ስንጥቅ አለ
መሰለሽ ።'

## 3.3.2. በሰዋስዋዊ ቅርፃቸው

አራት በሰዋስዋዊ ቅርፃቸው የታወቁ የአረፍተ ነገ አይነቶች እንዳሉ ይነገራል ፤ ነጠላ ፣ ድርብ ፣ ድብልቅ ድርብ ድብልቅ ።

(ሀ) ነጠላ አረፍተ ነገር — አንድ ባለቤትና አን አንቀፅ ያለው (ጓዝ እንዳስፈላጊነቱ) ፤

ምሳሌ ፣

'ታደሰ መጣ ።'

(ለ) ድርብ አረፍተ ነገር — በአብዛኛው ባዛማጅ መ ተፃምር የተያያዙ ሁለት ወይም ከሁለት በላ እራሳቸውን የቻሉ አረፍተ ነገሮች ያለው (ጓ እንዳስፈላጊነቱ) ፤

ምሳሌ ፣

'ታደሰ መጣና ወደ ቤቱ ሄደ ።'

(መ) ድብልቅ አረፍተ ነገር — አንድ ዋና አረፍ ነገርና በጥገኛ መስተፃምር አማካይነት ተገ የሆነ ሀረግ ወይም ሀረጎች ያሉት (ጓዝ እንዳስ ላጊነቱ) ፤



ምሳሌ ፣

'ታደሰ ስለ መጣ ፣ እኔ ወደ ቤቱ ሄድሁ ።'

(ሰ) ድርብ ድብልቅ አረፍተ ነገር — ድርብርብና ድብልቅ አረፍተ ነገር አብረው የሚገኙበት (ጓዝ እንዳስፈላጊነቱ) ።

ምሳሌ ፣

'ታደሰ ስለመጣ ወደ ቤቱ ሄድሁና ተኛሁ'

ስለ አረፍተ ነገሮች በምንነጋገርበት ወቅት ፣ የዚህ ምእራፍ አላማ ፣ በሰዋስው መፃህፍት ውስጥ በሰፊው ተብ ራርተው ስለሚገኙት ሰዋስዋዊ ያሰካክ ህጎች ፣ (ስሁተት የሌለበት አረፍተ ነገር እንዴት እንደሚፃፍ በማሳየት) ፣ በተጨማሪ ለማቅረብ ሳይሆን ፣ አረፍተ ነገሮች ትክክልና ግልፅ ከመሆንም በላይ ፣ ሀሳብ እና ወይም ስሜትን ያዋዋዱ ደማቅና አመርቂ አረፍተ ነገሮች እንዴት ሊሆኑ እንደሚ ችሉ ለመጠቆም ስለሆነ ፣ ኪነ-ፅሁፋዊ አረፍተ ነገሮችን ከዚህ በታች እንመለከታለን ።

## 3.3.3 በኪነ-ፅሁፋዊ ቅርፃቸው

አረፍተ ነገር — የሰዋስው ስህተት የሌለበት ሆኖ ፣ ያወቃቀር ስልት ስህተትም የሌለበት ሆኖ ፣ እንዲሁም የሀሳብ እና/ወይም ስሜት ስህተት የሌለበት ሆኖ — ጨርሶ አንባቢና ደግመው ሊያነቡት የማያጓጓ አይነት ሊሆን ይች ላል ። ለምን ቢባል ፅሁፍ የብዙ አይነት ሀሳብና ስሜት መግለጫ ዘዴዎችን ስለሚተካ ።

እንድ ሰው ለሌላ ሰው ሀሳቡን በንግግር በሚገልፅበት ወቅት በቃላት ብቻ አይደለም ሀሳብ እና/ወይም ስሜቱን

የሚያስተላልፈው ። ከፊቱ ፣ ላይ ልዩ ልዩ ፍልቅልቅታዎች ይታያሉ ፤ ፍልቅልቅታዎቹ ቃላቱና አሰካካቸው ደከም ያሉባቸውን ነጥቦች ያጠናክራሉ ። ከድምፁ ፣ ልዩ ልዩ የድምፅ ቅላጤዎች (ርግብግብታዎች) ይሰማሉ ፤ ቅላጤዎቹ ተናጋሪው ከሚናገረው ነገር ጋር ያለውን ቅርበትና ተዛምዶ ያመለክታሉ ። ከጁ መወናጨፍ ፣ ልዩ ልዩ እንቅስቃሴዎች ይከሰታሉ ፤ እንቅስቃሴዎቹም የንግግሩን ትኩረቶች አጠናክረው ወይም አኪያኪሰው ያቀርባሉ … አዎ ፣ እነዚህንና እነዚህን በመሳሰሉት ሌሎች መገናኛዎች ጭምር ነው ፣ ሰው ሀሳቡን እና/ወይም ስሜቱን በቃል የሚገልፀው ።

በዚህ አይነት ታዲያ በፅሁፍ ብቻ በሚወሰንበት ጊዜ ፣ ከዚህ በላይ የተመለከቱትን መገናኛዎች አይነቶቹን የሚተኩ ሌሎች ዘዴዎች መኖር ይኖርባቸዋል ። አለዚያ የሚተላለፈው ሀሳብ እና/ወይም ስሜት በሚገባ ወይም በሚጥም ፣ ስሜት በሚሰጥ ፣ በሚያዝናና ፣ በማይሰለችና እንጨት እንጨት በማይል ሁኔታ ይቀርባል ለማለት ያዳግታል ።

ለማንኛውም ዋና ዋናዎቹን ዘዴዎች ከዚህ ለጥቀን እንመለከታለን ።

### (ሀ) በልጨኛ ቅርፃቸው

አንደኛው ፣ ዘዴ በልጨኛ አረፍተ ነገሮች መጠቀም ነው ። ልጨኛ አረፍተ ነገሮች ፣ ለማስተላለፍ ከተፈለገው ሀሳብ እና/ወይም ስሜት አንፃር እየታዩ ልዩ ልዩ ቅርፅና አሰካክ እንዲኖራቸው ሆነው ለመቅረብ የሚችሉ ናቸው ። በአብዛኛው ፣ የየሁኔታውን ስነልቦናዊ አዝማሚያና ስሜታዊ ሁናቴዎች በሚገባ ለመቅረፅ ያስችላሉ ፤ ምንነታቸውንና አቅማቸውን አውቆ በብልሃት ከተጠቀሙባቸው ።



በውስጣቸው አይነታቸው ቢበዛም ፣ ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉትን ያጠቃልላሉ ፤ ልቅ ፣ ዝግና ምጥን አረፍተ ነገሮችን ።

### (1) ‘ልቅ’ አረፍተ ነገሮች

‘ልቅ’ ሲባል ስርአት የሌለውና መረን ወይም ስድ የተለቀቀ አይነት አረፍተ ነገር ሊመስል ይችላል ። ‘ልቅ’ ሲባል ሰፊ ፣ አውላላና የአይን ማረፊያ የሌለበት የሚያሰለች ማራቶን አረፍተ ነገር ሊመስልም ይችላል ። ሁለቱም አመለካከት ያስኬዳል ። ልቅ አረፍተ ነገርም ሆነ ማንኛውም ሌላ አይነት አረፍተ ነገር ፣ ለሀሳቡ እና/ወይም ስሜቱ የሚስማማ ገደብ ካልተበጀለት መረን ይወጣል ። ዝብዝቡ የማያበቃ ፣ ሁሉን በእንጥልጥል የሚተው ፣ አንባው ሲጨርሱት የትነሱበት የሚዘነጋበት አረፍተ ነገር ከሆነ ደግሞ ፣ የሚያሰለች ማራቶን አረፍተ ነገር ሊሆን ይችላል ።

ይሁን እንጂ በዚህ ፅሁፍ ውስጥ ‘ልቅ’ የሚለው ቃል የቆመው ስርአት በያዘ መንገድ ለሚዝናና አረፍተ ነገር ነው — እሰልችነት በማይኖረው መንገድ ለሚፃፍ አረፍተ ነገር ።

‘ልቅ’ አረፍተ ነገር የሚባለው ፣ ዋናውን ሀሳብ የያዘውን አቢይ ሀረግ — የመኪና ሞተር ከተጐታቹ ተለይቶ እንደሚቀድም ሁሉ — አስቀድሞ ፣ ጥገኛ ሀረጐቹን ወይም ጭምርማሪዎቹን የሚያስከትል አረፍተ ነገር ነው ።

ምሳሌዎች ፣

- መፅሀፌን ተቀበልኩ ፣ ከብዙ ድካም በኋላ ።
- አስቴር ከአሜሪካ ተመለሰች ፣ እንዴት ተስማምቷታል ፣ እንዴት አምሮባታል ።

. እይኑን ለማየት አልፈለግሁም ነበር ፣ እንዲያ ያ
ረገኝን ሳስበው ፣ ባላሰብሁት መንገድ ነገሮች
ጠምጥሞ ፣ ባላሰብሁት መንገድ ነገሮችን ተርጉ
በአእምሮዬ እንኳ ካልነበሩ ሰዎች ጋር አላኩሶ . . .

ከዚህ በላይ ከተጠቀሱት ሶስት አረፍተ ነገሮች ውስጥ
አቢይ ሀረጎች ፣ 'መፅሃፌን ተቀበልሁ' ፣ 'እስቴር ከአሜሪ
ተመለሰች' እና 'እይኑን ለማየት አልፈለግሁም ነበር'
የሚሉት ናቸው ። በየአረፍተ ነገሮቹ ውስጥ የተቀሩት
ጥገኛ ሀረጎች ናቸው ።

'ልቅ' አረፍተ ነገር የንግግርን ቋንቋ ስለሚመስል ለ
ንባቢ ቅርበት አለው ። የየወቅቱን ያነጋገር ዘይቤ ይከ
ላል ። ዋናውን ሀሳብ መጀመሪያው ላይ በማቅረቡ ፣ 'ፍሬ
ነገሩ ምን ይሆን' በሚል አይነት ልብን የሚያንጠለጥል
አይነት ባይሆንም ፣ አቢይ ሀሳቦቹን ወዲያው ወዲያው በመ
ደርደሩ ፣ ሀሳቡን በያንዳንዶቹ ሀረጎች አማካይነት ለማብ
ሰልሰልና ለማጣጣም ጊዜ ይሰጣል ። ጥገኛ ሀረጎቹም
እምብዛም የአእምሮን የማሰብ እንቅስቃሴ ስለማይሹ የማ
ዝናናት ባህሪያቸው ከፍተኛ ነው ።

በዘዴና በብልሃት ከተጠቀሙበት 'ልቅ' አረፍተ
ነገር ፣ ጠቃሚ የኪነ-ፅሁፍ ማቅረቢያ ስልት ነው — በተ
ለይ ጥድፊያ ያለው ድርጊት ለማቅረቢያና የባህርያትን
ቀጥታ ንግግሮች ለመመዝገቢያ ።

## (2) 'ዝግ' አረፍተ ነገሮች

ዘጋ 'ዝጎን ፣ ደጁን ከባላ (አጥ) እስከ ደንቆሮዉ... ዘረ
ጋ' ወይም 'ቀስ ብሎ ሄደ'[1] በማለት ይተረጉመዋል ፣

[1] ከሣቴ ብርሃን ተሰማ ፣ የአማርኛ መዝገበ ቃላት ፣ (አ.አ. 1951 ገፅ 1044) ።



መዝገበ ቃላቱ ። በዚህ ፅሁፍ ውስጥ ያለው የቃሉ አገባብም ቢሆን ፣ ከሁለቱ ትርጉሞች እምብዛም አይርቅም ። የሸማኔዉ 'ድር ከባላ እስከ ደንቆሮዉ' ተዘርግቶ ካልተሸመነ ልብስ አይሆንም ። እንዲሁም 'ዝግ' አረፍተ ነገር ከባለቤት እስከ አንቀፅ ያሉት ሀረጎች ተቀነባብረው ባንድነት ካልተወሰዱ ፣ የመጀመሪያው ፣ የመካከሉ ወይም የመጨረሻው ሀረግ ወይም ሀረጎች ብቻቸውን ትርጉም አይሰጡም ። የተጀመረው ሀሳብ በመጨረሻው አንቀፅ መዘጋት ይኖርበታል ፣ በአረፍተ ነገሩ ምን ለማለት እንደታሰበ ለመረዳት ።

'ዝግ' አረፍተ ነገር ለማለት የሚፈለገውን ለማስተላለፍ ስለሚንቆረሰስ (ቀስ ብሎ ስለሚሄድ) ፣ ዋና ዋና ሀሳቡን ቶሎ ቶሎ ለመያዝ አይቻልም ፤ እስከ አረፍተ ነገሩ መጨረሻ ማንበብን ይጠይቃል ። የተጣደፈ አንባቢን እልህ ያስጨርሳል ።

በሌላ መልኩ ደግሞ ፣ 'ዝግ' አረፍተ ነገር አንጊነት አለው ፤ ልብን ያንጠለጥላል ፤ መጨረሻው እስኪደርሱ 'ምን ሊል ይሆን' የሚለውን ስለማይመልስ ።

አንዳንድ 'ዝግ' አረፍተ ነገር ከመርዘሙ የተነሳ ፣ በቅድሚያ በሚገለፁት ጥገኛ ሀረጎች ውስጥ የሚመለከቱትን ሀሳቦች መዘንጋትን ያስከትላል ። ስለዚህም እስከ መጨረሻው ቃል ፣ ሀሳቦቹን ሳይዘነጉ ንቁ ሆኖ መከታተልን ይጠይቃል ።

ምሳሌዎች ፡

- የፈለጉትን ለማግኘት መስራት ያስፈልጋል ።
- ለወገን እድገት ፣ ለሀገር እድገት መስራት ማለት ፣

በየፊናችን የተሰጠንን ስራ አሸንፎ መገኘት ሲሆን በመከያውም ከየእራሳችን ችግር መውጣት ነው

- 'በህግ ሙያ በምሰለጥንበት ጊዜ ፥ ተመርቄም በል
ልዩ መ/ቤቶች ተቀጥሬ ፥ እንዱ ለሌላው ቅን ያለ
ሰብ አዝማሚያ ፥ የየራሱን እንጀራ ለማብሰ
ያደርገው የነበረው ሽኩቻ ፥ ለህሊና እስካልተሰ
ውሸት መናገር የማያሳፍርና ተገቢ መስሎ መ
የቱ ፥ መተማመን የአላማ አንድነት እስካለ ድረ
ብቻ መሆኑ ፥ የኔንም ባህሪ ቀስ በቀስ እየቦረቦ
ስለ ለወጠው ዛሬ ይኸውና እንደምታዩኝ ደንበ
አቃልጣ የወጣኝ ይመስለኛል . . .'

- ከአውራው መንገድ መገንጠያ ላይ ፥ ወደ ቤቱ ሲ
መራ ፥ ያየው ሶስት ሰዎች የተጨፈለቁበት የአቶሞ
ቢልና የትሬንታ ግጭት አሁንም ይሰገጥጠዋል ፥

## (3) 'ምጥን' አረፍተ ነገሮች

'ምጥን' የቃል ድርድሮች አሉ ። ምጥን የንኡስ ሀረግና የሀረግ ድርድሮች አሉ ። ምጥኖቹ ፥ ድርብ አረፍተ ነገር ወይም ድርብ ድብልቅ አረፍተ ነገር ሊሆኑ ይችላሉ ። የማንኛውም አይነት ድርድር ምጥኖች ፥ ማንኛውንም አይነት የአረፍተ ነገር ቅርፅ ይኑራቸው ፥ አንድ የሚመሳሰሉበት አቀራረብ አላቸው ። በምጥን አረፍተ ነገር የሚቀርቡት ሀሳቦች አንድ አላማን የሚያጉለምሱ ፥ የተቀራረቡ ወይም የማይቀራረቡ ፥ ሀሳቦችን የያዙ መሆን አለባቸው ። 'ምጥን' አረፍተ ነገሮች እኩል ሆነው የሚመጡ ተመሳሳይ ቅርፅ ያላቸው የቃል ወይም የሀረግ ድግግሞሽ ስለሆኑ ግጥማዊ መልክ ይታይባቸዋል ።



በግጥም ቤት በአንድ አይነት የመጨረሻ ፊደል እየተደጋገመ እንደሚገጠም ግጥም 'ቾቾቾ ... ... ሸሸሸ ... ' እየሆነ እንዳያሰለች ሆኖ ከተቀናበረ ፥ ለሌሎች አይነት አረፍተ ነገሮች ማጣፈጫ ይሆናል ። ምጥን አረፍተ ነገሮች የተዛዘሉ ሀረጎች በመባልም ይታወቃሉ ።

ምጥን ቃሎቹ ወይም ሀረጐቹ በብዛት ተደጋግመው ከረዘሙ ፥ ፍሬ ሀሳቡንና/ወይም ስሜቱን እስከ መጨረሻ የማቆየትና አንባቢን የማሰልቸት ጠባይ ስለሚኖራቸው ፥ አገልግሎታቸው በብልሃት ሊሆን ይገባል ።

### ልዩ ልዩ ምሳሌዎች

- 'የጣመ ፥ የጣፈጠ ፥ የረቀቀ ፥ የጠለቀ ... '
- ' ... ብቻህን ስትሆን ትፈራ ፥ ወይም ትባባ ወይም ትባንን ወይም ታለቅስ ይሆናል በማለት ነበር ...'[2]
- 'ውሻው ጅራቱን የሸጐበ ፥ ጆሮውን የጣለና ለሀጩን የሚያዝረከርክ ነበር ... '[3]
- 'ሰርቆም ፥ አንቆም ፥ ገድሎም ፥ ጉቦም መንትፎ በቶፋ የቀበረ ፥ ቪላም የገጠገጠ ፥ በባንክም ያስቀመጠ ፥ በመቀነትም የቋጠረ ...'[4]
- አእዋፍ ብርብር ፥ እፀዋት ቀና ቀና ፥ እንስሳት ብቅብቅ ማለት ፥ አራዊትም ፋሲካ ጀምረዋል ።
- ልቤ ትርትር ፥ አይኔ ስልምስልም ፥ እንባዬ ዱብ ዱብ ፥ እግሮቼ መዛልና እጆቼ መንቀጥቀጥ ፥

---

[2],[3] ተክለ ማርያም ፋንታዬ ፥ 'እውነትም የእንጀራ እናት' ።

[4]: ሰይድ አበጋዝ ፥ 'የመቃብሩ ትል' ።

የሚጨብጡትን ማጣት — በጠቅላላው ሰብአዊ ሰውነቱ እንክሽክሽ ፣ ስብርብር የሚልበት ምን ፍጡር ምንስ ነገር ይሆን ?

- ነፋሱ ሽውሽው ፣ ሰማዩ ጠራጠራ ፣ አየሩ ሞቅሞቅ ፣ ደመናው ገለጥ ገለጥ ፣ ፀሀይም ደመቅ ደመቅ ማለት ጀመሩ ።
- '... በዐይንና በጆሮ በአፍና በአፍንጫ ፣ እየገባ እንደ ፌጦና ሰናፍጭ እየሰነፈጠ ፣ በላይና በውስጥ በማቃጠል ዐይንን እያፈረጠ ፣ ጠቅላላ ሰውነትን እየላጠና እየቆራረጠ አንገብግቦ የሚገድል የጋዝ መርዝ ጭስ .....'[5]
- '... በየደኑ በየተረተሩ ፣ በየተራራው በየሸንተረሩ ፣ በየሸጥ በየሸለቆው ፣ በየአሸዋው እየተዘዋወሩ የጠላትን ግንባር በሰይፍ ካልፈለጡትና በጎራዴ ካልከሰከሱት ፣ ሲአፈጥ ደረቱን ፣ መለስ ሲል ባቱን በቀጭኔ ጦርና በድብልብል አንካሴ ካልፈረከሱት ፣ ጋራ ዞሮና ረኸም ሜዳን አቋርጦ በሚመታ ጥይት የጀግንነት ሱሳቸውን አያረኩም ...'[6]

እዝልዝል ሀረጎች በአንድ አረፍተ ነገር ውስጥ ብቻ ሳይሆን በተለያዩ አረፍተ ነገሮች ውስጥም ሊሰራባቸው ይችላል ።

ምሳሌዎች ፤

. አገሬን አገሬን የሚል ሰው ሲደላው ወድዷት ሲቸግረው አይጠላትም ። በጥጋብ ጊዜ ተንቀባርቦባት በችግር ጊዜ አይሸጣትም ። በሰላም ጊዜ ኖሮባት በቀውጢ ጊዜ አይክዳትም . . .

[5] አዲስ ዘመን ፣ ቁ 411 (ሚያዝያ 1954) ።
[6] ከላይ የተጠቀሰው ።



. አባቶቻችን በሰማይ አልበረሩም ። በምድር አልከነፉም ። ብዙ አገር አላቋረጡም ። ብዙ መፅሀፍ አላነበቡም ። መሬት ባለመልቀቃቸው ግን ፣ መሬታቸውን አስከብረዋል ። ቀስ እያሉ በመሄዳቸው ብዙ ተመልክተዋል ። ወረቀት አይሁን እንጂ የተፈጥሮን ገፅ አገላብጠዋል ። ብዙም አይራቁ እንጂ የሚሻላቸውን አገር መርጠዋል ። ለምርጫቸውም መስዋእት ሲሆኑ ኖረዋል. . .

. አገር ቀውጢ ስትሆን ሰዉም ቀውጢ ይሆናል ። ቅሌን ጨርቄን የለም ፣ ማን አስቦት ። ልጄን ከብቴን የለም፣ ማን አጢኖት ። እናት ልጅዋን ረግጣ ፣ አባት ልጁን ደፍጦ የሚከንፍበት ፣ አለቃና ምንዝር ፣ አዛዥና ታዛዥ የማይኖርበት ፣ ሰው ህሊናውን የሚስትበት . . .

በአብዛኛው ተደጋጋሚዎቹ ቃላት ፣ ንኡስ ሀረግ ወይም ሀረጎች ቢያንስ ከሁለት ማነስ የለባቸውም ። ሀረጎቹ የመስተዋድድ ተገዥም ሆኑ (በቤቱ ፣ በወንዙ ፣ በሸንተረሩ) ወይም መስተፃምር የተጫናቸው (የሚከንፍበት ፣ የማይኖርበት ፣ የሚስትበት) ወይም ቃላት (መናገር ፣ መለፍለፍ ፣ መቀባጠር) ።

እነዚህ ከላይ የተብራሩት ሶስት ልጨኛ የአረፍተ ነገር አይነቶች መሰረታዊ ናቸው ። መሰረታዊ በመሆናቸውም ፣ እያንዳንዳቸውን አይነት ሌሎች ብዙ የተለያዩ አረፍተ ነገሮች ለመቅረፅ ይቻላል — ለተፈለገው ሀሳብ እና/ወይም ስሜት እንዳመችነታቸው ።

## (ለ) <u>የሀሳብ/ስሜት እና አረፍተ ነገር ቅርፅ ውዴታ</u>

ኪነ-ፅሁፋዊ አረፍተ ነገሮችን ለመፃፍ ሁለተኛዉ ዘዴ ፣ ሀሳብን እና/ወይም ስሜትን ከአረፍተ ነገሩ ጋር እንዲ

ዋደድ የማድረግ ተግባር ነው ። የአረፍተ ነገሮችን አይነ
ቶች በተለያየ አገልግሎታቸው ወይም በሰዋስዋዊ ቅርፃ
ቻቸው ወይም በልጨኛ አቀራረባቸው ማወቁ ብቻ አመር
ቂና ለዛ ያላቸው አረፍተ ነገሮችን ለመፃፍ አያበቃንም ።
ከማንኛውም አይነት አረፍተ ነገር ጋር ይሁን ሀሳቡ እና/
ወይም ስሜቱ በሚገባ እንዲዋደድ ካስፈለገ ፣ አረፍተ
ነገሩ ውስጣዊ የሀሳብ/የስሜት አንድነትና የቃላት አሰካክና
ዝምድና ያለው እንዲሆን ያስፈልጋል ።

## የሀሳብ/የስሜት አንድነትና የቃላት አሰካክና ዝምድና

(1) አረፍተ ነገሩ ባለቤትና አንቀፅ እንዲኖረው ያስ
ፈልጋል (እንዳይኖረው በማስፈለጉ የሚያስተላ
ልፈው መልእክት እስከ ሌለ) ። ማለትም ፣ ‘ልጅቷ
ብትመጣ ኖሮ … ’ ወይም ‘እየተንገደገደ እቤቱ
ከደረሰ በኋላ …’ ወይም ‘… እየተገነዘብሁት
እያጤንኩት ነው’ የሚል አይነት አረፍተ ነገር
አይፈቀድም ።

(2) የአረፍተ ነገሩ ርዝማኔ ወይም እጥረት ፣ እንደሚ
ገልፀው ሀሳብ እና/ወይም ስሜት ነጠላነትና ውስ
ብስብነት ሊሆን ይገባዋል ። ስለ ረጃጅም አረፍተ
ነገሮች ከገፅ 73 እስከ 78 የተገለፀው ይታወሳል ።
በአጫጭር አረፍተ ነገሮችም ረገድ ቢሆን ፣ የሚ
ከተሉትን አይነት ችግሮች ይፈጠራሉ ፤

- በሀሳብ ወይም በስሜት የሚገናኙት አረፍተ
ነገሮች ተቆራርጠው ለየብቻቸው ስለሚቀ
ርቡ የሀሳብ ዝምድና አያሳዩም ።

- እኩል ክብደት ያላቸው አረፍተ ነገሮች በወ
ደረኛ መስተፃምር ፣ የሚተናነሱት ደግሞ



በአቢይና በጥገኛ ሀረጐች ተዛምደው የሀሳብ
ተዋረድ አያሳዩም ።

- ነጠላ ከመሆናቸው የተነሳ ፣ ለአቢዩም ሆነ
ለጥገኛው ሀሳብ የሚመድቡት ቀንደኛ ቦታም
ሆነ አቢዩ ሀሳብ እንዲብራራበት የሚሰጡት
ቦታ የሚያመቻች አይደለም ። ዋና ዋናዎ
ቹን ሀሳቦች በየአረፍተ ነገሮቹ መጀመሪያ
ወይም መጨረሻ ላይ አጠናክረው አያቀር
ቡም ። የቀረቡትም ቢሆን የሚይዙት ቦታ
ደጋፊ ሀሳቦችን እንዲያቅፉ ሆኖ የሚያብ
ቃቃ አይደለም ።

ምሳሌ ፤

- ወልዴ ሱቅ አለው ።
- በሱቁ የማይገኝ ሸቀጥ የለም ።
- ወደ ሱቁ የማይመጣ ገቢያተኛ የለም ።
- ወልዴ የቤት ሸያጭ ደላላ ነው ።
- የሚሸጥ ቤት ያጠያይቃል ።
- ከቀበሌ ቀበሌ ሲዞር ይውላል ።
- ከሚነገድበት የሚዘጋበት ጊዜ ይበልጣል ።

እነዚህን አረፍተ ነገሮች ለየብቻቸው እንዳሉ ብንመ
ለከታቸው ፣ ከቁርጥርጥነታቸው የተነሳ እኩል ክብደት
ያላቸውን ሀሳቦች እኩል ቦታ በመስጠትና ፣ እንደ ሀሳቡ
ትልቅነትና ትንሽነት በማደላደል የተዘጋጁ አይደሉም ።
የሁለቱ አበይት ሀረጐች የባለቤት ኀዝና የአንቀፅ ኀዝ ፣
ለየብቻቸው ራሳቸውን በቻሉ ቁርጥራጭ አረፍተ ነገሮች
ነው የተገለፁት ፤ የሀሳብ ተዋረድም ሆነ የሀሳብ ዝምድና
አያሳዩም ።

በየዓዛቸው ብናስልፋቸው ግን የሚከተለውን ይመስላል

‘በወልዴ ሱቅ የማይገኝ ሸቀጥ ፣ ወደ ሱቁም የማይ
ጣ ገበያተኛ ባይኖርም ፣ በቤት ሽያጭ ደላላነቱ ደግሞ ፣ የ
ሸጥ ቤት ለማጠያየቅ ከቀበሌ ቀበሌ ሲዞር ስለሚውል
ከሚነገድበት የሚዘጋበት ጊዜ ይበልጣል ።[2]

(ለተጨማሪ መግለጫ ከገፅ 121—170 ተመልከት ።)

(3) አረፍተ ነገሩ አስፈላጊው አይነት ነጥቦች እን
ገቡበት ያስፈልጋል ፤ አለዚያ የአንዱ ጓዝ ከሌላ
ከማይዛመደው ጋር ሲጨፈለቅ ፣ አንድም ጨር
ትርጉም አይሰጥም ፣ አንድም ፣ ቢሰጥም የተፈ
ገውን አይነት አይሆንም ። መግባባት አይኖርም
ማለት ነው ፣ ነጥቦች ተገቢ ቦታቸውን ካልያዙ

ምሳሌ ፣

‘አንዲት ዦሮዋ የማይሰማ ሴት ልጅ ወልዳ ህፃ
ገና ሳያድግ ድንገት ስለ ሞተ ...’[7]

ይህ አረፍተ ነገር በተለያዩ መንገዶች ሊቀርብ ይች
ላል ።

. ‘አንዲት ዦሮዋ የማይሰማ ሴት ፣ ልጅ ወልዳ
ሕፃኑ ገና ሳያድግ ድንገት ስለ ሞተ ...’ ወይም ፣

. ‘አንዲት ዦሮዋ የማይሰማ ፣ ሴት ልጅ ወልዳ
ሕፃኑ ገና ሳያድግ ድንገት ስለሞተ ...’ ወይም ፣

---

7 ማኅተመ ሥላሴ ወ.መ ፣ ‘እንቅልፍ ለምኔ’ ፣
(አ.አ. 1952) ፣ ገፅ 186 ።



. ‘አንዲት ዦሮዋ የማይሰማ ሴት ልጅ ፣ ወልዳ ፣
ሕፃኑ ገና ሳያድግ ድንገት ስለ ሞተ ...’ ወይም ፣

. ‘አንዲት ፣ ጆሮዋ የማይሰማ ሴት ልጅ ወልዳ ፣
ሕፃኑ ገና ሳያድግ ድንገት ስለ ሞተ ...’

እንደምንመለከተው ነጥብ የሌለው አረፍተ ነገር
ብዙ አይነት አነባበብ ስለሚኖረው አግባቢነት የለውም።
ነጥብ ካላቸውም ቢሆን ፣ እንደ ነጥቦቹ አገባብ ልዩነት መና
ሩን ማጤን ያስፈልጋል ። በደራሲው የነጥብ አገባብ መሰ
ረት የቀረበው እንደሚከተለው ነው ፤

‘አንዲት ዦሮዋ የማይሰማ ሴት ፤ ልጅ ወልዳ ሕፃኑ
ገና ሳያድግ ድንገት ስለ ሞተ ...’

(4) አረፍተ ነገሩ ከባለቤት ጓዝና ከአንቀፅ ጓዝ ውጪ ፣
በአረፍተ ነገሩ ውስጥ የሚገኘን አንድ የተወሰነ
ሀረግ ለመግለፅ ሲባል የሚተከል ፣ ማብራሪያ
ሊኖርበት አይገባም ። ተተካዩ ሀሳብ ለማብራራት
የሚረዳ ቢሆንም የጠቀላላውን አረፍተ ነገር ሂደት
ያደናቅፋል (አረፍተ ነገሩን አደናቅፎ ለአንባቢ
ተግታ ለመስጠት ወይም ሌላ ስነልቦናዊ ሁኔታ
ለመፍጠር ተፈልጎ የታቀደ እስካልሆነ ድረስ) ።

ምሳሌ ፤

‘ቁርሴን ልበላ ስሄድ ፣ በአንድ ሰአት ተሩብ ቁርሴን
ማድረግ ልማዴ ስለሆነ ፣ ወመኜው የቤትዬዋን ቦርሳ መን
ጭቆ ሲሮጥ አየሁ ...’

---

ከዚህ በላይ ከተመለከቱት በተጨማሪ ፣ ስለ እንጥልጥል ሀረጐች (ሀረጉ
ያለ ባለቤት ወይም ያለማሰሪያ አንቀፅ ሲገኝ) ገፅ 139 (7) ተመልከት ።

ስለ ባለቤት ግምባር መለዋወጥ (በተለይ ስለ ተውላጠ ስሞች መቀያየር) ፣ የሚዛመድ ሀሳብን በተመሳሳይ አዝል ዝል ሀረግ ካለመግለፅ ስለሚፈጠር መዘላበድ እና ስለ መሳሰሉት ከማንኛውም የሰዋስው መፅሀፍ ለመረዳት ይቻ ላል ።

### 3.3.4. ማጠቃለያ

አረፍተ ነገሮች ሀሳብንና /ወይም ስሜትን በትክክል እንዲገልፁ ጥረት በሚደረግበት ወቅት ፣ በተለይ ኪነ- ፅሁፋዊ አረፍተ ነገሮችን በሚመለከት ፣ ሀይለ ቃላቸውና አመርቂነታቸው ጭምር እንዳይለያቸው የሚከተሉትን ነጥቦች እንደገና ማጤን ያስፈልጋል ፤

(ሀ) በተለያዩ የአረፍተ ነገር አይነቶች * ረገድ

- በአገልግሎት አይነታቸው ከታወቁት ውስጥ በይ በልጥ በአወንታና በጥያቄ አረፍተ ነገሮች ፣

- በሰዋስዋዊ ቅርፅነታቸው ከታወቁት ውስጥ በይ በልጥ በድብልቅ አረፍተ ነገሮች ፣

- በልጨኛነት አይነታቸው የታወቁትን ጨምሮ እያ ሰባጠሩ ፣ መጠቀም ።

* በዚህ ፅሁፍ ውስጥ የተጠቀሱት ማንኛዎቹም የአረፍተ ነገር አይነቶች ፣ መሰረታውያኑ ብቻ ናቸው ። ስለዚህም እያንዳንዳቸው የተለያየ ብዙ አይነት አቀራረብ ይኖራቸዋል ፣ እንደ ፀሀፊው ችሎታና ልምድ ።



(ለ) በአረፍተ ነገር ርዝማኔ ረገድ

የምንጠቀምባቸው አረፍተ ነገሮች ማንኛዎቹም አይነት ቢሆኑ ፣ የተለያየ ርዝማኔ እንዲኖራቸው ማድረግ ።

(መ) በአረፍተ ነገር አባላት ቅደም ተከተል ረገድ

ተጠናክሮ መቅረብ ያለበት ሀሳብ እና/ወይም ስሜት በሚመራው መሰረት ፣ የአረፍተ ነገሮችን ጓዞች (አባላት) እያዘዋወሩ መጠቀም (ባለቤትና አንቀፅ ፣ ተሳቢና ባለቤት ፣ የባለቤት ጓዝና ባለቤት . . . እና በመሳሰሉት) ።

(ሰ) በአረፍተ ነገሮች 'አካል' ረገድ

አረፍተ ነገሮች ፣ እያንዳንዳቸው ራሱን የቻለ 'አካል' ያላቸው መሆናቸውን ተረድቶ ፣ አንድ ነታቸውን ፣ ዝምድናቸውንና ደልዳልነታቸውን የሚያፋልስ ማንኛውንም ጭምርማሪ ማስቀረትና ሊኖር የሚገባውንም ያለ መተው ።

# ክፍል ሁለት

## አንቀፅና

## ድርሰት

## ምእራፍ አራት

# አንቀፅ

### 4.1 <u>መግለጫ</u>

አንቀፅ የረጅምም ሆነ የአጭር ድርሰት 'አካል' መገንቢያ 'ብልት' ነው ። ስለዚህም በብልትነቱ የራሱ የሆነ ቅርፅ አለው ። መጀመሪያ መስመሩ ከምስማክ (ግራ) ህዳግ ገባ ብሎ ይጀምራል ። የመጨረሻው መስመር ደግሞ አለቀበት ያበቃል ፤ ሀሳቡ ከተገታ በኋላ ያልተፃፈበት ቢኖርም ይተዋል እንጂ ሌላ ሀሳብ በዚያው መስመር አይለጥቅም ።

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ፥ በተለይ በደብዳቤ አፃፃፍ ስርአት ፥ አንቀፅን ገባ ብሎ መጀመር መቅረት ጀምሯል ። ይኸም ቢሆን የቆየውን ልምድ ማፍረሱ ሳይሆን ፥ አንድን አንቀፅ ባዲስ መስመር መጀመሩ ብቻ በቂ መስሎ ስለታመነበት ነው ፤ ባዲሱ መስመር ላይ ገባ ብሎ መጀመሩ ልዩነት ስለማያመጣ ። ይሁንና ፥ የአንቀፁ መጨረሻ መስመር እገፅ (እቀኝ) ህዳጉ ዘንድ ደርሶም ሆነ ሳይደርስ ነው የሚያበቃው ፥ አዲስ አሳብ አይለጥቅበትም ፤ አሁንም ልምዱ እንደ ተጠበቀ ነው ።

ማንኛውም ልምድ ጠቃሚ እስካልሆነ ይወገዳል ። ጠቃሚ ከሆነ ደግሞ ይጠበቃል ፥ ይሻሻላልም ። ለምሳሌ ፥ አንቀፅ የራሱ የሆነ 'ብልት' እንዲኖረው ማስፈለጉ ጠቃሚ ነው ። እንዲሁ ሲታይም ቢሆን ለአይን ረፍት ይሰጣል ፤

ፅሁፉ ድፍንና የታመቀ አይመስልም ፣ አይሰለችም ፤ ብርሃን (ያልተፃፈበት ክፍል) ብቅ ጥልቅ የሚልበት ገፅ ስለሚመስል ። እንቅስቃሴንም ያሳያል ፤ የየሀሳቡን ማለቂያ ። በተለይ ስራ ለሚበዛበት ሰው ባጭር ጊዜ ውስጥ ከአንቀፅ ወደ አንቀፅ በመሸጋገር ዋና ዋና ሀሳቦቹን ገረፍ ገረፍ አድርጎ የጠቅላላ ሀሳቡን ፍሬ ነገር ለማግኘት ይችላል ። በዚያ ላይ የአንቀፅ ዋና ተግባሩ እያንዳንዱን ሀሳብ እና/ወይም ስሜት በየፈርጁ ማቅረብ ስለሆነ ፣ ሀሳቡ እና/ወይም ስሜቱ ላለቀበት ወይም ለተቋጨበት ምልክት ይሆናል ። በዚህ አይነት እንግዲህ ፣ የተለየ ሀሳብ ወይም ስሜት ለሌለው አንቀፅ የተለየ 'ብልት' መስጠት ምንን ያስከትላል ማለት ነው ? በሌላ በኩል ደግሞ ፣ የተለየ ሀሳብ ወይም ስሜት ይዞ 'ብልት' ሳይለይለት በዚያው በአንዱ 'ብልት' ውስጥ ቢታጨቅስ ? አዎ ! ፅሁፉ ዘልባዳ ይሆናል ፤ ፅሁፉ ይዘባርቃል ። ዘብራቃ ይሆናል ። ብዙ ያልተገናኙ ሀሳቦች የታመቁበትማ ከሆነ. . አዎ . . . ዝብርቅርቅ ይሆናል ፣ ዝብርቅርቅ ፅሁፍ ደግሞ የተምታታ ስለሚሆን ተነባቢነት የለውም ።

አንቀፅ እንግዲህ በግልፅ የሚታይ 'ብልት' ነው ማለት ነው ። 'ብልት' ከሆነ ደግሞ 'ብልቱ' ተቀናብሮ የተፈጠረ መሆን ይኖርበታል ። ተቀናብሮ የተፈጠረ ከሆነ ደግሞ እያንዳንዱ 'ብልት' የየራሱ የሆነ ህይወት ይኖረዋል። ተቀናብሮ ተፈጥሮም ህይወት ከሌለው በሚገባ አልተቀናበረም ማለት ነው ። እንዲህ ከሆነ በመጀመሪያ አንቀፅ ተቀናበረ የሚባለው እንዴት ሲሆን ነው ?

## 4.2 ማቀናበሪያ ስልቶች

አንቀፅ ተቀናበረ የሚባለው በአንቀፁ የሚገለፀው ሀሳብ ወይም ስሜት ተሟልቶ ሲቀርብ ነው ። ተሟልቶ



የሚቀርበው ደግሞ ፣ በማቀናበሪያ ስልቶች ፣ በሚገባ ሲጠቀሙ ነው ።

ከማቀናበሪያ ስልቶቹ ውስጥ የሚከተሉት ይገኙበታል ፤

4.2.1 የአንድነት ስልት ፣
4.2.2 የዝምድና ስልት ፣
4.2.3 የደልዳላነት ስልት ፣
4.2.4 የቅርፅ ልከኛነት ስልት ፣
4.2.5 የማሳደጊያ ስልት ፣ እና
4.2.6 የርዝማኔ ስልት ።

እያንዳንዳቸውን በሚከተሉት ገፆች እናብራራለን።

### 4.2.1 የአንድነት ስልት

በቅድሚያ አንቀፅ 'ብልት' ነው ብለናል ፤ አንድነት ያለው የድርሰት ክፍል መሆኑን ስንገልፅ ። አንድነት ደግሞ ተመሳሳይነት ያለው ማለት የሚመስላቸው አሉ ። ሊመስል ይችላል ። ግን ምን አይነት ተመሳሳይነት ? አንድ እፍኝ ሽምብራ ተመሳሳይ ነው ፤ አንድ ገበቴ ሙዝ (ካንድ እበዛ የተቆረጠ) ተመሳሳይ ነው ፤ አንድ እፍኝ በሶ ተመሳሳይ ነው ። በዚህ አይነት ከሆነ የገባን ፤ የአንድ አይነት 'ነገር' ተሰባስቦ መገኘት ሊሆን ነው — አንድነት በእርግጥም ። ግን ፣ እኛ የምንፈልገው አንድነት እንዴት እንዲህ አይነቱን ሊሆን ይችላል — ተመሳሳይ ቃላት ፣ ወይም ተመሳሳይ ሀረጎች ፣ ወይም ተመሳሳይ አረፍተ ነገሮች የተሰበሰቡበት? ሊሆን አይችልም ።

እኛ የምንፈልገው 'አንድነት' ፣ ቃላት ወይም አረፍተ ነገሮች ተመሳሳይነት ሊኖራቸው ቢችልም ፣ ልዩ ልዩ ሀሳ

ብና ስሜት እንዲሰጡ ሆነው የተቀናጁበት ነው — አንድነታቸው ከሚገልፁት ሀሳብ ወይም ስሜት ላይ የሆነ ።

ለምሳሌ ፣ የሚከተለውን እንመልከት ።

'ሰው የሆነ ሁሉ ብዙ ምኞትና ፍላጎት አለው ። እንደነ አርስጣጣሊስ ፣ እንደነሶቅራጥስ ፣ እንደነማርክስና እንደ ነኤንጌልስ በፍልስፍና ተራቅቆ አለምን ማወቂያና አስተሳሰብን መለወጫ ለማቅረብ ይፈልጋል ። እንደነማርኮኒ ፣ እንደነጋሊሊዮ ፣ እንደነአንስታይን በሳይንስ ተራምዶ ተፈጥሮን በቁጥጥሩ ስር ለማዋል ይሻል ፣ እንደነ አኒባል ፣ እንደ ናፖሊዮን ፣ እንደነቴዎድሮስ በጦር ሜዳ ጠላትን ድል በማድረግ ጀብዱ ለመስራት ይመኛል ። እንደነ አብርሃም ሊንከን ፣ እንደነጋንዲ ፣ እንደነማርቲን ሉተር ኪንግ ለህዝብ መብትና ለሰላም ፣ እንደነሞዛርት ፣ እንደነ ቤቶቨን ፣ እንደነማይክል አንጀሎ ፣ እንደነሴዛን ፣ እንደነፎክነር እንደነሊዮ ቶልስቶይ ፣ ለሰው ልጅ የመንፈስ ልምድና ደስታን ለማስገኘት ይመኛል ። ይፈልጋልም ...'

(በአብዛኛው በተናጠል (እየቅል) መጠሪያ ቃላት የቀረበ አንቀፅ ።)

ከፅሁፉ እንደምንመለከተው መንደርደሪያው ሀሳብ ፣ 'ሰው የሆነ ሁሉ ብዙ ምኞትና ፍላጎት አለው' የሚለው ነው ። በዚህ አረፍተ ነገር ስር ደግሞ ፣ በአራት አረፍተ ነገሮች የተጠቃለሉ አምስት አበይት ምኞትና ፍላጎቶች ተዘርዝረዋል ። ፈላስፋ ፣ ሊቀ ሳይንስ ፣ የጦር አዛዥ ፣ የሰላም መልክተኛ እና የስነጥበብ ሰው የመሆን ምኞት ። የመጀመሪያዎቹ ሶስት አረፍተ ነገሮች እያንዳንዱን ምኞትና ፍላጎት ለየብቻቸው ሲያቀርቡ፣ አራተኛው አረፍተ ነገር ሁለቱን ምኞት ነው ባንድነት ያቀረበው — እንዲያውም ከሁለቱ አንደኛዉን ከነዘርፎቹ ።



በዚህ አይነት ፣ ሰው የሆነ ሁሉ የሚኖረውን ምኞትና ፍላጎት እስኪሰለች መዘርዘር ይቻላል ። ሆኖም የኛ ፍላጎት የሰውን ልጅ ምኞትና ፍላጎት ሁሉ ለማቅረብ ሳይሆን ፣ ቃላት ፣ ሀረጎችና አረፍተ ነገሮች የተለያዩ መስለው ለአንድ ግብ በሚቆሙበት አሰላለፍ ፣ እንዴት አንድነት እንደሚኖራቸው ለማሳየት ስለሆነ ባጭሩ አብቅተናል ።

በአንቀፁ የተመለከትነው የየአረፍተ ነገሮቹ ተመሳሳይነት ፣ አንዱ የሸምብራ ፍሬ ከሌላዉ ፣ አንዱ ሙዝ ከሌላው ሙዝ ወይም የበሶዉ ቅንጣቶች ከእርስ በርሳቸው እንዳላቸው አይነት አይደለም ። የሸምብራ ፍሬዎቹ እፍኝ ፣ ሙዞቹ አበዛ ፣ ቅንጣቶቹ በሶ ከመሆናቸው አንፃር እንጂ ። አረፍተ ነገሮቹ በሙሉ የሰው ልጅ ምኞትና ፍላጎት የሚለውን መንደርደሪያ ጉዳይ የሚያዳብሩ በመሆናቸው ። እያንዳንዳቸውም የዘረዘሩት ያንኑ ምኞትና ፍላጎትን በመሆኑ ። የተለያዩ ?! አዎ ። የተለያዩ ምኞትና ፍላጎቶችን ። እውነትን እንናገር ካልን ። ስለሽምብራውስ ቢሆን —አንዱ ሽምብራ ከሌላው ሽምብራ ምንም አይነት ልዩነት የለውም ለማለት እንዴት እንችላለን ?

አንድ አንቀፅ አንድነት ያለው እንዲሆን ያስፈልጋል ስንል ፣ እንግዲህ አንቀፁ አንድ አሳብ ወይም አንድ ስሜት ይያዝ ማለታችን ነው ። አንድ አሳብ ወይም ስሜት ስንል ደግሞ ፣ ለአንድ ጉዳይ (ቋም ነገር) የተሰባሰቡ አሳቦች ወይም አንድ አይነት ስሜትን ለመቀስቀስ የተቀናጁ ስሜት ፈንጣቂዎች ማለታችን ነው ። ይህም ሲባል ፣ የፅሁፉን መንደርደሪያ አሳብ ወይም ስሜት የሚያዳብሩ ፣ ተመሳሳይ ወይም ተቃራኒና ተነፃፃሪ ሀሳቦችና ስሜቶችን አይጨምርም ማለት አይደለም ። መንደርደሪያውን ጠብቆ ማዳበ

ሪያ ሀሳቦችንና ውስብስብ ስሜቶችን ሊይዝ ይችላል ። ከመንደርደሪያው ውጪ የሆነ ትርፍራፊ ፣ ጭምርማሪ ወይም እዚህ ግባ የማይባል መደረቻ እስካልሆነ ድረስ ፤ አረፍተ ነገሮቹ እያንዳንዳቸው የአንቀፁን ግብ እስካጠናከሩ ።

ለአንድ አንቀፅ ማበልፀጊያ የሚሆኑትንና የማይሆኑትን አረፍተ ነገሮች በጥንቃቄ ለይቶ ማወቅና መምረጥ ያስፈልጋል — የሚያስፈልጉት እንዲገቡ ፣ እንዳይቀሩ ፣ የማያስፈልጉት እንዲቀሩ ፣ እንዳይገቡ ለማድረግ ።

## 4.2.2. የዝምድና ስልት

አንድ እፍኝ ሽምብራ ቢጉነልቄልና ቢያያዝ ፣ አንድ አበዛ ሙዝ (ከግንዱ ሳይቆራረጥ) እና አንድ ጭብጥ በሶ (በውሃ ተረስርሶ) የሚመሳሰሉበት 'ነገር' አለ ። ሽምብራው በጉንቁሉ ፣ ሙዙ በአበዛው ፣ በሶው በውሃው አማካይነት ተጠጋግተዋል — አብሮነታቸው ይታያል ፤ ተያይዘዋል ።

በዚህ ረገድ ፣ አንቀፅም እንደ ማጉንቈያ ፣ አበዛ እና ማረስረሻ ነው ። እውስጡ የሚሰባሰቡትን አረፍተ ነገሮች የሚያገናኝ፣ የሚያዋድድና የሚያዛምድለት 'ውሃ'ና 'ግንድ' ይፈልጋል ።

አንቀፅ አረፍተ ነገሮቹን የሚያዛምድባቸው በርካታ ዘዴዎች አሉት ፤ ከነሱም ዋና ዋናዎቹን እናብራራለን ፤

(1) አንድ አንቀፅ ውስጥ ሊኖሩ የሚገባቸውን ፣ ለአንድ ሀሳብ እና/ ወይም ለአንድ ስሜት ወይም ለአንድ ጉዳይ ማብራሪያ የሚሆኑትን ሀሳቦች ፣ ስሜቶች ወይም ጉዳዮች መሰብሰብና መምረጥ—ማለትም ፣ ከላይ በ (4.2.1) ውስጥ እተብራራው አንቀፅ ውስጥ በሚገኘው አይነት ፣



በአንድ መንደርደሪያ አረፍተ ነገር (ሰው የሆነ ሁሉ ብዙ ምኞትና ፍላጎት አለው) ውስጥ የሚሰባሰቡትን ።

(2) በአንቀፁ ውስጥ የሚብራራው ጉዳይ ውስጣዊ ባሕሪ ፣ የራሱ የሆነ የአቀራረብ ስልት ይኖረው አይኖረው እንደሆነ መመርመር ። በሌላ አነጋገር ፣ በአንቀፁ የሚገለፀው ጉዳይ የሚዛመደው ፣ እውስጡ የሚጨመሩት ነጥቦች በሚኖራቸው የጊዜ ቅደም ተከተል ወይም የቦታ አንድነት (ባንድ ቦታ ተሰባስበው መገኘታቸው) መሆን አለመሆኑን ማረጋገጥ ። ሆኖ ከተገኘ ፣ የጊዜና የቦታን የአቀራረብ ስልቶች መከተል ። (ከገፅ 143—150 ተመልከት ።)

(3) ለጉዳዩ ባለቤትነት ያላቸውን ዋና ዋና ቃላትና ሀረጎች ቢቻል በተመሳሳያቸው ፣ ካልተቻለም እራሳቸውን መደጋገም — የቃላቱ ወይም የሀረጎቹ መደጋገም የተከታታይ አረፍተ ነገሮቹን ዝምድና ያጠናክራል ። (ከገፅ 157—164 ተመልከት ።)

(4) በቋንቋ አገባብ ስልት መሰረት ፣ በመስተፃምሮች ፣ በልዩ ልዩ ተውሳከ ግሶች መጠቀምና እስከ ተቻለ የሰዋስው ህጎችን መከተል ። እዚህ ላይ ፣ በተለይ መስተፃምሮችና ተውሳከ ግሶችን አለማብዛት ያስፈልጋል ። በአረፍተ ነገርም ውስጥ ሆነ ፣ ከአረፍተ ነገር ወደ አረፍተ ነገር ለመሸጋገሪያነት የሚያገለግሉት (እንደ ፣ ከዚያም ፣ በመጨረሻም ፣ ግን ፣ ቢሆንም ፣ ስለሆነም ፣ ከዚያን ጀምሮ ወዘተርፈ...) እነዚህ ቃላት መግባት ያለባቸው፣አረፍተ ነገሮቹ ያለ እነሱ ተጨማሪነት ዝምድናቸው በግልፅ የማይታይ ሲሆን ብቻ ነው ። እለዚያ ቃላቱ መደረቻ ከመሆናቸውም አልፎ አንባቢን ያሰለቻሉ ።

(5) በአንቀፁ ውስጥ የሚብራራው ጉዳይ፣ ከዝርዝሩ ወደ አጠቃላዩ ቢገነባ ፣ ወይም ከአጠቃላዩ ወደ ዝርዝሩ ቢበተን የሚሻል የማይሻል መሆኑን መወሰን ፤ ተሽሎ

ኩተጊቿ ፣ የመሰብሰቢያን ወይም የመዘርዘሪያን ስልቶች
መከተል ። (ከገፅ 166—169 ተመልከት ።)

(6) በአንቀፁ ውስጥ የሚብራራው ጉዳይ ውስጣዊ
ባህሪ ፣ ባህሪዎችን በማወዳደርና በማነፃፀር ፣ በመዘርዘር ፣
በትርጓሜ (በማብራራትና ክልል በማበጀት) ፣ ዝርዝር ነጥ
ቦችን በማደራረብና በማስተዛዘል ፣ የባህሪዎችን መድረሻ
ከመነሻዎቹ አንፃር በመተንተንና በመሳሰሉት ስልቶች
ለማቅረብ አመችነቱን መመርመርና ፣ ካመቹ በተናጠልም
ሆነ እንደየሁኔታው በሁለትና ሶስት ስልቶች መጠቀም ።

(ከገፅ 144—169 ተመልከት ።)

የዝምድና ስልት ዋና ግቡ ፣ በአንቀፁ ውስጥ የተቀና
ጁት ዝርዝር ነጥቦች ፣ እንዴት የእርስበርስ አግባብ እንዳ
ላቸው ፣ አንባቢዉን ፣ ቀላል በሆነና በግልፅ መንገድ
እንዲያይ ለማድረግ ነው ። የዝርዝር ነጥቦቹ አረፍተ ነገሮች
አንዱ ሌላውን እየጠሻ ካልጎረፉ የጉዳዩ አለመያያዝ ፣
አለመገናዘብና አለመዛመድ በግልፅ ይከሰታል ።

## እስረጅ ፤

## በጊዜ ቅደም ተከተል የተዛመደ

ጤካሳ ዳምጤ ከንማይ ባላባት ፣ ከፊታውራሪ ዳምጤ ብሩና
ከወይዘሮ ጥሩአይነት ታላቅ እህት ፣ ከወይዘሮ እስቴር ተሰማ
የተወለደ ፣ በሁለት እጅ የማይነሳ ፣ ከባድ የጌታ ዘር ነበር ።
በመኩዋንንት ልጆች ወግ የቤተ መንግስት ስራት እያጠ
ናና ደጅ እየጠና ቢያድግ ኖሮ ቢያንስ ቢያንስ ያባቱን ግዛት
ባላጣ ነበር ። ነገር ግን አባቱ በህጻንነቱ ስለሞቱና ምቀ
ኞች ዘመዶቹ እንኩዋን ይህን እድል እንዲያገኝ ሊያደፋፍ
ሩትና ወደፊት ሊገፉት ቀድሞ እሬት ቢያገኙትም ወደ
ውዋላ ለመጎተት የማይመለሱ ስለነበሩ ከቤተ መንግስት



ርቆ ከናቱ ዘንድ አደገ ። ከቤቱ እየተመላለሰ እዚያው አገሩ
ተማሪ ቤት ዳዊት ከደገመ በሁዋላ አሳቡ ወደትምህርት
ተሳበና ካንዱ ተማሪ ቤት ወደሌላው እየተዘዋወረ ዜማም ፣
ቅኔም ተምሮ ሲጨርስ ብዙ አመታት መጣፍ ተማረ ።
በተለይ ሀዲስ አዋቂነቱን የሚያደንቁ ብዞች ነበሩ ።
ባገሩ ትምህርት እውቀቱ የጠለቀ ከመሆኑም በላይ የባ
ላባት ልጅ በመሆኑ የቤተ ክህነት ሹመት ፈላጊ ቢሆን
ኖሮ ከታላላቁ አድባራት ያንዱን አለቅነት ቢያንስ ሊቀ
ጠበብትነት ሊያገኝ እንደሚችል የማይጠረጠር ነበር ። ነገር
ግን አስተያየቱ ከቤተ ክርስቲያን መሪዎችና ከካህናቱ
በጣም የተለዩ ስለነበረና ስራቸውን አጥብቆ ይጠላ ስለ
ነበረ ቤተ ክርስቲያንን በነሱ አይን እያዩ ከቤተ ክርስቲ
ያንም ይርቅ ጀመር ። በሁዋላ እንዲያውም የሚኖርበት
ማህበር የተመሰረተበት ስራት ፣ ልማዱ ፣ ደንቡ ፣ ወጉ ፣ ሆኑ
የማይረባ ከመሆኑም በላይ የሚጎዳ መሆኑን ይሰብክና ይህ
አርጌ ስራት ሳይሻሻል እንደ እግዚአብሄር ቃል ተከብሮ
እንዲኖር የሚጣጣሩትን የልማድ ባሮች ከብቶች ድንጋዮች
እያለ ልዩ ልዩ ስም እዩሰጠ ይዘልፍ ነበር ... »[1]

(ከገፅ 145—147 ተመልከት ። )

## በቦታ አንድነት የተዛመደ

" ... ከዙፋኑ ራቅ ከድልዳሉ ዝቅ እያለ ሲሄድ ግን
የሁሉም አይነቱ ይለወጣል ። ከሁሉ አስቀድሞ ከድልዳሉ
በታች አዳራሹን በወርዱም በቁመቱም ከዳር እስከዳር
የሞላው ህዝብ አንዱ በሌላው ላይ እየተደራረበ ሰፍሮ
የሚተራመስ የንብ ሰራዊት እንጂ በተራ ተቀምጦ የሚበ
ላና የሚጠጣ ሰው አይመስልም ። ስጋውን መልከኞች
ሙዳ ሙዳ አድርገው እየቆራረጡ በሳጠራ ሞልተው

[1] ሀዲስ ዓለማየሁ ፣ 'ፍቅር እስከ መቃብር' ፣ (አ/አ 1975) ፣ ገፅ 121-122 ።

አሸክመው ያመጡና ከሩቅ እየወረወሩ አንዱን ፊቱን ሌላውን ደረቱን ሲሉት ልበኛ ቀልቦ ያስቀረዋል የዘንጋ አምልጦት እመሬት ይወድቅበታል ። ጠጅ አሳላፊዎች ጠላት እንደሚያሳድዳቸው እዬተጣደፉ ጠጁን በኩባያ እዬቀዱ ሲያድሉ በሚጠጡት ሰዎች እጅ እስኪደርስ ግማሹ ያክል በሰውነታቸው በልብሳቸውም ይፈሳል ወዲያው የተረፈውን ቢጨርሱም ባይጨርሱም ላልደረሰው ለማድ ረስ ኩባያውን ከጃቸው ነጥቀው ይወስዱባቸዋል ። ይህ ሲሆን የኩባያውና የቢላዋው ኩዋኩዋታ ያሳላፊውና ያቅ ራቢው ያጋፋሪው ጫጫታ በውነት ራስ ያሳምማል ። አዳ ራሹ ውስጥ የቆሙትን ወጋግራዎች እዬተደገፉ የቆሙ ብዙ አዝማሪዎች አሉ ። ነገር ግን እጃቸው መሰንቆውን ሲገዘ ግዝ ያንገታቸውም የደም ስር ተገትሮ አፋቸው በሙሉና በከፊል ሲከፈት በማየት የሚያዘምሩ መኖራቸውን ከመገ መት በቀር የመሰንቆውም ሆነ የነሱ ድምጽ በጭራሽ አይ ሰማም ። እንዲሁም ጥሩምበኞች እምቢልተኞችና መለከ ተኞች እያደገደጉ ተደርድረው መሳሪያቸውን በያፋቸው ለግበው ጉንጫቸው እንደፊኛ ተነፍቶ አይናቸው ፈጦ የደም ስራቸው በየግንባራቸው ተገትሮ ሲታዩ ሁሉም በዬመሳሪያቸው ሲጫወቱ ፎቶግራፍ የተነሱ ምስሎች እንጂ ያነለት እዚያ ቆመው የሚነፉ ነፍስና ስጋ ያላቸው ሰዎች አይመስሉም ... ” [2]

(ከገፅ 147—150 ተመልከት ።)

<u>በማወዳደር የተዛመደ</u>

<u>አስረጅ ፤</u>

“. . . ለምሳሌ አንድ ገበሬ ስንዴን ይዘራና እየተለባኘ እልክ ሲደርስለት ዐጭዶ ይወቃል ። ከዚህ በኋላ ምርቱን

[2] ከላይ ከተጠቀሰው ፣ ገፅ 448—449 ።



ለብቻው ግርዱንም ለብቻው እንቾቆንም ለብቻው እያ ደረገ በያይነቱ በጎተራው ይከታል ። የደቀቀውን ገለባም ለየብቻው ያስቀምጠዋል ፤ ፣ ወይም ይቀላቅለዋል ፤ የገለባው አሠራር እንደ እህሉ አይደለምና በሰውዬው ሐሳብ የሚወሰን ነገር ነው ። እንደዚሁም ንግግር የሚሰጥ ሰው ገበሬው ምርቱን ግርዱንና እንቾቆን እየለየ በደንበኛው ሥፍራ እንደሚያስቀምጠው በንግግሩ ውስጥ ዋናውን ሐሳብ ካነስተኛው ፣ አነስተኛውንም በጣም ዝቅ ካለው እየለየ በያግባባቸው ይሰጣል ። በተሰጠው ማስረጃ የምና ገኘው ጥቅም ብስልና ጥሬ ነገር እየለየን በየቦታቸው ለማ ስገባት ችሎታን ማግኘት ነው ... ” [3]

<u>በመዘርዝር ቅንብር የተዛመደ</u>

<u>አስረጅ ፤</u>

“የገለልተኞች ንቅናቄ ስድስት አበይት አላማዎች አሉት ። እነሱም ፣ አንደኛ፣ ቀጥተኛም ሆነ የእጅ አዙር ቅኝ አገዛዝን ማስገድ ፣ ሁለተኛ ፣ አንዱ ሀገር በሌላው የውስጥ ጉዳይ ጣልቃ እንዳይገባ መቋቋምና የሀገ ሮች ነፃነትና አንድነት እንዲከበር መታገል ፣ ሶስተኛ፣ ታዳጊ ሀገሮች ከአለም አቀፍ ኢምፔሪያሊዝም ተፅ እኖ ተላቅቀው የፖለቲካና የኢኮኖሚ ነፃነት እንዲ ኖራቸው መደገፍ ፣ አራተኛ ፣ በዴታንትና በአለም ሰላም መረጋገጥ ረገድ የጦር መሳሪያ ምርትና ክም ችት እንዲቀነስ ብሎም እንዲወገድ እሚቻልበት ስምምነት ላይ እንዲደረስ ጥረት ማድረግ ፣ አምስተኛ፣ ታዳጊ አገሮችን ለባሰ ድህነት የሚዳርጋቸው ከበለ ፀጉ አገሮች ጋር ያላቸው የብዝበዛ ግንኙነት ተወግዶ በምትኩ አዲስ አለም አቀፍ የኢኮኖሚ ስርአት እን

[3] ተክለ ማርያም ፋንታዬ፣ ‘ጥንተ ጥበብ ዘሥነ ጽሑፍ’፣ (አ.አ 1964) ገፅ167።

ዲኖር መርዳት ፣ ስድስተኛ ፣ አለም አቀፍ ትብብሮች እንዲዳብሩ ማድረግ ናቸው . . .” [4]

“... እውነተኛንም ታሪክ ለመጻፍ ቀላል ነገር አይደለም ። የሚከተሉትን ሦስት የእግዚአብሔር ስጦታዎች ያስፈልጋልና ፡ መጀመሪያ ተመልካች ልቦና የተደረገውን ለማስተዋል ፣ ሁለተኛ የማያዳላ አእምሮ በተደረገው ለመፍረድ ፣ ሦስተኛ የጠራ የቋንቋ አገባብ ፣ የተመለከቱትንና የፈረዱትን ለማስ ታወቅ ። ያገራችን የታሪክ ጸፎች ግን በነዚህ ነገሮች ላይ ኃጢአት ይሠራሉ ። በትልቁ ነገር ፈንታ ትንሹን ይመለከታሉ ። ለእውነት መፍረድንም ትተው በአድ ልዎ ልባቸውን ያጠባሉ ። አጻጻፋቸውም ድብልቅልቅ እየሆነ ለአንባቢው አይገባም ። ይህም ነገር በቤተ መንግሥትና በየገዳሙ ከሚገኙት ታሪክ ነገሥታት ጥቂት ብራናዎች ብናነብ ወዲያው ይገለጽልናል ። የታሪካችንም ጸፎች ሁለት ዓይነት ሰዎች እንደሆኑ እንረዳለን ። አንዱ ዓይነት የቤተ መንግሥት ሊቃው ንት ይባላሉ ፤ ማለት እንጀራ ሲፈልጉ ከቤተ መንግ ሥት ተጠግተው ንጉሡ ያዘዛቸውን የራሱን ውዳሴ ታሪክ ብለው ጽፈው ለኋላው ትውልድ የሚያቆዩ አቀላማጮች ። ሁለተኛው ዓይነት ግን መነኮሳት ናቸው ። እነሱም የሚጽፉት ታሪክ አድልዎ ይበዛ በታል ፣ የራሳቸውን እንጂ የሕዝቡን ጥቅምና ጉዳት ከቶ አያቋጥሩምና ። ስለዚህ የልባቸውን የሚፈጽም ላቸውን ንጉሥ ቅዱስ ቅዱስ ይሉታል ። ከድንቁር ናቸው ወጥቶ ከፍ ባለ ሕሊና ተመርቶ ስለዜጐች ልማት የሚጥረውን ግን ርኩስ ። አሁን ጐዳናንና ድል ድዮችን ከሚያስበጅ የጥበብንም ማስተማሪያ ቤቶች

ከሚከፍት ንጉሥ ይልቅ የመንግሥቱን ጉዳይ ሁሉ ረስቶ ከናዝሬዊ ከሴላም ዓይነት መነኩሴ የሚውል ፣ ሥራ ፈትተው ለሚኖሩት መነኮሳትም ምግብ ብሎ ብዙዎች አገሮች የሚጐልት ንጉሥ ፣ በነሱ ዘንድ ይመሰገናል ። ያገራችንም የታሪክ ጸፎች ውዳሴ ከን ቱና ስድብ ፣ እውነተኛውን ታሪክ ሳይቶው ፣ የማይ መስለውን ተረት የሚወድ ቢሆን ምንም ባልጐዳንም ነበር።መጽሐፋቸውንም አንበ እውነቱን መርምሮ ለማ ግኘት አእምሮ ላለው ሰው ባላስቸገረም ነበር ...” [5]

## መዘርዝር በተለያዩ አንቀፆች

### አስረጅ ፣

*«የሀብት ዕድል*

የሀብት ዕድል በብዙ ክፍል ይከፈላል ። አንደኛ ፣ የጥበብ ዓይነቱ ብዙ ነውና ይህን ያህላል በማለት ፍጻሜው አይገኝም ... ጥበብ ያለውም ሰው እንጀራ ሲሠሩት እንጂ ሲበሉት አያደክምምና የኋላውን ጥቅም አስቦ የፊቱን ድካም ሳያስተውል ሥራን እርስ በርሱ እያታገለ ማለት ብረትን በብረት ደንጊያን በደንጊያ እንጨትን በእንጨት መሰልን በመሰሉ እያሠራራ፣ መሬትን ከእህል ማናቸውንም ዘር ከተስማሚው ጋር እያገናኘ ፣ ገንዘቡ በጥበቡ ፣ ንብረቱ በብልሃቱ ፣ ስጦታው በሥራው እየተከናወነለት በዚህ ዓይነት የዕድሜውን ቀጠሮ ይጠብቃል ። ይህ በሥራ የተ ገኘ የሀብት ዕድል ይባላል ።

ሁለተኛ ፣ ቀደስኩክ እምክርሠ እምክ እንዴ ተባለ ፣ አን ዳንዱ ከናቱ ማሕፀን በሀብት ጨርቅ ተጠቅልሎ ይወለድና በዚያም ላይ ባላባትነት ይኖረውና በባላባትነቱ አጥንቱ በሀብታምነቱ ንብረቱ እየተመሰገነ አንድ ቀን በችግርና በመ

---

[4] ከአዘጋጁ ።

[5] ገብረ ሕይወት ባይከዳኝ ፣ 'አጼ ምኒልክና ኢትዮጵያ' ፣ ገጽ 1።

ከራ ሳይፈተን ፣ ያዩት ሁሉ ሲመጣ ይነሡለታል ፣ ሲሄድ
ይሸኙታል ፣ ሲናገር እውነት እውነት ፣ ሲጣራ አቤት አቤት ፣
ይባላል ። ከቤቱም ሰንጋው ታርዶ ጠጁ ወርዶ ተነጥፎ
ተጋርዶ ሲቆየው ለአዱኛው ፍጹም ደስታ ያገኛል ። ይህ
እንዲህ ያለው ስጦታ ለሁሉ አይሰጥምና በዚህ መቅናት
አይገባም ። መቅናትስ በመከራ ከተፈተኑ በኋላ በሚገኝና
በሥራ በሚገኝ ሀብት ነው ። መከራ ያልፈተነው ወይም
ትምህርት የጐደለው ሀብታም ረሃብ ምንድር ነው ከማ
ለት ይደርሳል ። ደሃውንም ዐፈር ዘግኖ ጭቃ ለስኖ እንደ
ሠራው ያደርገዋልና አስቀድሞ የፈተና ቀንበር ትከሻውን
ቢያሸውና ከተማሪ ቤት ቢጉላላ መልካም ዕድል ነው ፤
ትምህርት የጥበብ ሁሉ ሙሻዙር ነውና ።

ሦስተኛ ፣ የአፍ ብልጠት የጧት ቁርስ ነው ። አፍ
ያለው ጤፍ ይቆላል እንዲሉ ፣ አፈኛ ካደባባይ በሙግት ፣ ከመ
ጠጥ ቤት በጨዋታ አስመስሎ ሲናገር ከንፈር ያስመጥ
ጣል ። ጥርስ አያስከድንም ፣ አፈ ጮሌ ሳይሾም የተሾመ
ነውና ። ስለዚህ እንደበቱ የእጅ ወረትና መነገጃ ሁኖት
በእውነቱ ሐሰት ፣ በሐሰቱ እውነት እየቀላቀለ ሲጫወት
ሳይከፋበት ከብሮና ታፍሮ ይኖራል ። ነገር ግን የገዳይ ምል
ክቱ ደም በጣቱ እንዲሉ ለጊዜው ለመረመረውና ላወቀበት
የልብ ዕውቀት እንደሌለው ክፉ ምልክት ይገኛል ። አፍ
ከበዛ ዘንድ ወፈፍተኛነት አይቀርምና የአፍ ብልጠት ከልብ
ዕውቀት ጋር ካልተገናኘ እንደ ነጠላ ልብስ ማለት ነው ።

አራተኛ ፣ ያፍ ትእግሥትና የልብ ዕውቀት የማታ
እንጀራ ይሆናሉ ። አፉ ያልተናገረ ሰው እስከ ጊዜው ዕው
ቀቱን ይታወቅልኝ ከማለት ያዘገየዋል ። ስለዚህ ለሰው
ሁሉ አላዋቂ ሞኝ መስሎ ይታያል ። የዕውቀቱ መግለጫ
ሲደርስ ግን አንድ ነገር ተናግሮ ወይም አንድ ሥራ አሳይቶ
ትእግሥቱ ተደንቆ ታውቆ ማዕረጉ ምጡቅ ጥበቡ ረቂቅ
ሆኖ ሳያውቁ ዐወቅን ሳይረዱ ተረዳን በሚሉ መፈራረጃ



ይሆንባቸዋልና ፣ የአፍ ብልጠት የጧት ቁርስ ፣ ዕውቀትና
ትእግሥት የማታ እራት ይሆናሉ ተባለ ። ስለምን የአፍ
ብልጠት ምንጊዜም ሥራ የለበትምና ሀይ ሀይ ብሎ በጧት
ነጥቆ ይበራል ። የልብ ዕውቀት ግን የጧት ጊዜው የሥራ
ስለሆነ ሥራውን ሲሠራ ይቆያልና በጧት አይቀናወም ።

አምስተኛ፥ ጀግንነት የሀገር ኩራትን ያስገኛል ። የሀገሩ
ዐፈር በጠላቱ እጅ እንዳይዘገን ፣ ታግዬ ፣ አልጥልም ተኩሼ
አልገድልም ሳይል ፣ በሱ ሞት የሀገር ሕይወት እንዲ
ጠበቅ እየተመኘ የሚኖር ጀግና ፣ በጠላቱ ዘንድ ከዱር እን
ደወጣ አውሬ ተፈርቶ ፣ እንደሚጥሚጣ በርበሬ ተታኩሶ ፣
አገሩን የሚያረጋጋ ጠላቱን የሚያሠጋ ነውና እንጀራን
እሱ ይብላ ው ። ይህም አንድ ዋና ዕድል ነው ።

ስድስተኛ ፣ ፍርድ ሲጠበቅ ደሃ ይጠበቃል ደሃም ሲጠ
በቅ እግዚአብሔርን ደስ ይለዋል ። ስለዚህም ዳኛ የሆነ
ሰው ለቀይ ለጥቁር ፣ ለረጅም ላጭር ፣ ለወርቅ ለብር
ሳያደላ በውነት ቢፈርድ ከአደባባዩ የጻድቅ ፍሬ ይለቅማል።
- እንዲህ ያለውም ዳኛ ትልቅ ዕድለኛ ይባላል ። ነገር ግን
የዳኛ ዐይን ሲሞት የድሃ ሕይወት አብሮ ይሞታል ...
የደሃ ሕይወቱ የቀና ፍርድ ነውና ። ስንፍና ሳያደርግ እው
ነቱን ከሐሰት አበጥሮ ጽድቅን የሚያስተውል እውነትን
የሚከተል ዳኛ በውነት የእግዚአብሔር ምስሌ ነውና
የደሃ ሕይወት ለምልማ ትኖራለች ፤ ከዚህም የበለጠ እድል
የለም ።

ሰባተኛ ፣ በሥነ ፍጥረት በኩል ደሙ ጠርቶ ሕንጹ
አካሉ ተቃንቶ የመልክ ውበት ያለው በሄደበት ሁሉ ከወ
ንድ መኰንን ከሴት ወይዘሮ ዘንድ መወደድን መደነቅን
መከበርን በውበቱ እየተገበያየ ይኖራል (ማለት) መኰንኑ
ላሽከርነት ፣ ወይዘሮይቱ ለሎሌነት ፣ ሁሉም ለየጥቅማቸው

ይመችታል ። ስለዚህ በሥራው ሳይሆን በመልኩ ውበት ድካም የሌለበት ሀብት ያገኛል ፤ ይህም ስጦታ ነው…”[6]

## በትርጓሜ የተዛመደ

### አስረጅ ፩

“መከር ማለት በመሬት ውስጥ የሚገኙት ማእድኖች ከመራቆታቸው የተነሳ ያረጀን ማሳ በልዩ ልዩ ሰብል እያፈራረቁ በመዝራት ማደስ ነው ። መሬትን ከማሳደር ጋር ግንኙነት አለው ፤ መሬት ሲያድር ፣ ሳይዘራበት ሲቀር አራሙቻ ፣ ሳርና የተለያየ ተክል ስለሚበቅልበትና የደከመው አፈር እንደገና ስለሚጠናከር ። ቢሆንም መከር ማለት መሬትን ያሻውን ያብቅል ብሎ ማሳደር አይደለም ፤ ሰብልን በብልሃትና በጥበብ እያለዋወጡ በመዝራት ማጎልበት ነው እንጂ — አንድ አመት የአገዳ እህል ፣ በሁለተኛዉ አመት ያበባ እህል ፣ በሶስተኛዉ አመት የብርእ እህል በመዝራትና ከዚያም በአራተኛዉ እረፍት እንዲያድርግ በመተውና በአምስተኛዉ በመጨፍለቅ ፤ ወይም በአንዱ አመት አሳድሮ ፣ በሁለተኛዉ ያገዳ እህል ፣ በሶስተኛዉ ያበባ እህል ፣ በአራተኛዉ የብርእ እህልዘርቶ ባምስተኛዉ በማሳደር ወይም በሌሎች እነዚህን በመሳሰሉ ልውውጦች እህሎችን በማዘዋወር ። ሆኖም ሰብሎችን ማዘዋወር ማወቁም በቂ አይሆንም ፤ አንድ አመት ተልባ ዘርቶ በሚቀጥለው አመት ደግሞ ማገጥ ለመዝራት ስለማይቻል ። እነዚህን ተክሎች በአንድ ማሳ ላይ ለመዝራት በተልባውና በማገጡ መካከል አያሌ ሰብሎች መዘራት ይኖርባቸዋል ፤ የመሬቱ የማፍራት ሀይል እንዲመለስ ። ስለዚህ መከር ማለት አንድን ማሳ ከሁለት እስከ አምስት አመት በማደስ ፣ ማሳዉ እደሳዉ ሲጀምር ተዘርቶበት የነበረውን

[6] ብርሃንና ሰላም ፤ ሚያዝያ 5 ቀን 1925 ።



ሰብል መልሶ ለመቀበል እንዲችል የሚያደርግ የሰብል ማፈራረቅ ጥበብ ነው ።”[7]

## ዝርዝር ነጥቦችን በማድራረብና በማስተዛዘል የተዛመደ

### አስረጅ ፩

- “ሰከንድ እንደ ደቂቃ ፣ ደቂቃ እንደ ሰአት የሚገመትባት ፣ ሌሊቱ ሁለት እጅ ቀኑ ሶስት እጅ እረዝሞ የሚታይባት ፣ የአዳም የዘር መግቢያውን የማያምንባት ፣ ፀሀይ እያለች የሌለች የሚመስልባት ፤ የት ልግባ ፣ የት ልሁን ፣ ምን ይዋጠኝ ፣ ተጨነቅሁ የምታሰኝ ፤ ስር ግትርትር እያደረገች ፣ መላ ሰውነት በላብ እያጠመቀች ፣ ሰውን ጓዳና ጉዳንጉዱን ፣ ጫካና ሽንተረሩን አስነክሳ የምትውል ፣ ዘመድን ከዘመዱ ፣ ሚስትን ከባሏ ፣ ልጅን ከናትና ከአባቱ ፣ ከመንጫንጭ ብዛት እያቆራረጠች የምትለያይ ፣ ሴት ፣ ወንድ ፣ ወጣት ፣ ሽማግሌ ሳትል ሁሉን የምታብረከርክ ፤ ደሀውና ሀብታሙ የማይለይባት ፣ ተራ ህዝብና ባለስልጣን በመግባባት እንጂ በሀይል ወይንም በህግ የማይሰሩባት ፤ ይሉኝታን ፣ ፍቅርን ፣ መዋዋልን ፣ ሀዘኔታዊነትን ከሰው አእምሮ የምታጠፋ በጠቅላላው አላማዋ የማይታይ ፣ የምታስፈራ ፣ የምታሰቅቅ ቀን የጭንቀት ቀን ትባላለች ።”[8]

- “አላስሄድ ፣ አላስቀምጥ ፣ አላናግር ፣ አላሰራ የሚል ፤ አይኑ ፣ ጆሮው ፣ እግሩ ፣ እጁ ፣ መቀባጠር ማሰስ ፣ ማንሳት ፣ የለመደ ፤ ያባቱ ፣ የናቱ ፣ ቀያቸው ፣ ውቃቢያቸው የተጣላው ፤ እምባ ገነን ፣ አባይ ገነን ፣ ራስ ቢስ ፣ ነጣላ ትክሻ የሆነ ፤ የሚወደውን ፣ የሚ

[7, 8] ከአዘጋጁ ።

ጠላውን ፣ የሚስቅለትን ፣ የሚስቅበትን የማይለይ ፤ መነሻውን እንጂ መድረሻውን የማያውቅ ፤ ባፉ በምላሱና በጥርሱ ብቻ የሚጠቀም ፤ አእምሮዉ ፣ ልቡ ፣ አብሮ የመስራት ተግባር የማይታይባቸው ወሬኛ ነው ። ወሬኛ ፣ ዘመድ አዝማድን ፣ ወዳጆችን ጓደኞችን ያቆራርጣል ፣ ያጋድላል ፣ ሲያወጋም የሰማው ሁሉ በቁምህ ይለቀስልህ ሲለው ይኖራል ። ወሬኛ ዝቅ ዝቅ እንጂ ከፍ ከፍ የማይል ብኩን ፣ ተስፋ ቢስ ስለሆነ ምስጢር ሊያካፍሉት አይበቃም፤ ምነው ቢሉ ያስለፍልፍ ቅጠል ቀምሿልና ።”[9]

<u>መድረሻዎችን ከመነሻዎች አንፃር በመተንተን የተዛመደ</u>

<u>አስረጅ ፤</u>

“. . . ያው ሌባ ግን ወዲአው ተቁስሉ እንደዳነ ሄዶ ላጤ ቴዎድሮስ እንዲህ ብሎ ጮኸ ። ጃንሆይ ! እግዚአብሔር ያሳይዎ ክርስቶስ ያመልከተዎ ! ልጆቼም ምሽቴም እኔም እራብ ቢአጠቃን እንኳን እህል አሞጭና አሉማ በጋ ሆኖ ቢአጥጠነና ልንሞት ብንሆን እራብ ብዙ ያስመኛል ጥንቱን ሆዳም ሊጋሱን ስስታም ነባዩን አባይ ያደርጋልና ተመሞት ብየ አድርጌው የማላውቀውን ነገር ልሰርቅ በጨለማ ሄድኩ ። ነገር ግን ገና ተበረቱ እንደ ገባሁ ባለቤቱ ነቃና የጠቀርሻ ጦሩን ነጥቆ ተከተለኝ ። እኔም ስሮጥ እሱም እየፎከረ እየተንደቀደቀ ሲከተለኝ ምንም በጠገበ ጉልበቱ ቢውዘገዘግ እንደተቻለኝ ተፈናጥሬ አመለጥሁት ። እንዳመለጥሁት ባየው ጊዜ እሱ ግን በቴዎድሮስ አምላክ በቴዎድሮስ ሞት ቁም አትላወስ አለኝ ። እኔም እሄንስ ብሎ ታቆመኝ መቸም አይወጋኝ ብዬ እንዳ መለጥሁ ማምለጥ ሲቻለኝ እሺ ብየ በስምዎ ተዳኘቸ ቆም

[9] ከአዘጋጁ



ሁለት ። እሱ ግን ሌላ ምንም አላለ እንዲአው ባውራ እጣቱ ቁሞ ሲአበራድደው የነበረውን ጦር በሽንጤ ላይ ወደወደብኝ ። ከዚህ በኋላ በደም አበላ ተነክሬ አእምሮየን ስቼ ወድቄ ባየኝ ጊዜ ጨርሽዋለሁ መስሎት ጥሎኝ ተመለሰ ። እኔም ተዚአው እንደወደቅሁ አድሬ በበነጋው ስለክርስቶስ ያለ መንገደኛ ተወደቅሁበት አንሥቶ ወደቤተ ክርስቲያን እድሞ አስጠግቶኝ መበለቶች እስታመው አዳኑኝ ። አሁን ግን ነገሩን እንዲሰሙት ብየ ከስሼ ይሄው አመጣሁት፤ እግዚአብሔር ያሳይዎ ጃንሆይ አለ. … ”[10]

(7) ጉዳዩ እስካመቸ ድረስ ፣ ተመሳሳይ ክብደትና አስፈላጊነት ያላቸውን ባህርያት ተመሳሳይ ቅርፅ ባላቸው ቃላት፣ ንኡስ ሀረጎች ወይም ሀረጎች ማቅረብ ፤ በተዛዘሉ ሀረጎች መጠቀም ።

<u>አስረጅ ፤</u>

‘መፅሀፍ የተሸከመ ሁሉ አንባቢ ፣ ጠመንጃ ያነገበ ሁሉ ተኳሽ ፣ ዩኒቨርስቲ የጨረሰ ሁሉ እስተዋይ. . . አይደለም’ በማለት ፈንታ ፣ ‘መፅሀፍ የተሸከመ ሁሉ አንባቢ ፣ ጠመንጃ አንግቦ የሚሄድ ሁሉ ይተኩሳል ለማለት ፣ ዩኒቨርስቲ የጨረሰ ሁሉ እስተዋይ ነው. . . አይደለም’ ቢልስ ። በመጀመሪያው እንቀፅ እረፍተ ነገሮቹ ተመሳሳይ ቅርፅ ያላቸው ሲሆን በሁለተኛው እንቀፅ ግን የሶስቱም አረፍተ ነገሮች ቅርፅ የተለያየ ነው ። ስለዚህ አረፍተ ነገሮቹ በሀሳብ ቢገናኙም በአገባብና በአቀራረብ ስለተፋለሱ እንቀፁ በአጠቃላይ አልተዛመደም ።

[10] አፈወርቅ ገ/የሱስ ፣ “የአማርኛ ቋንቋ ሰዋሰው” (በኢጣሊያንኛ የተጻፈ መጽሐፍ ፣ እ. አ. አ. 1905 ) ውስጥ ፣ ‘አጤ ቴዎድሮስ ፣’ ከተሰኘው ፤ ገፅ ፤ 280-1 ።

(8) እምብዛም በኪነ-ፅሁፍ ውስጥ ባይሰራበትም ፣ ጉዳዩን የሚያመለክት ፣ 'ሰው የሆነ ሁሉ ብዙ ምኞትና ፍላጎት አለው' አይነት መንደርደሪያ አረፍተ ነገር በአንቀፁ መጀመሪያ ፣ መካከል ወይም መጨረሻ ላይ ማስገባት — ዝርዝር ባህርያቱን ለማሰባሰቢያነት እንዲረዳ ። አንዳንዴ በፅሁፉም ውስጥ ባይታይ በደራሲው አእምሮ መንደርደሪያ አረፍተ ነገር እንደ ነበረ ለማወቅ ይቻላል — በተለይ የአንቀፁን ጉዳይ ባጭሩ በአንድ አረፍተ ነገር አሳጥሮ ለማቅረብ ከተቻለ ። (ገፅ 131—132 ፣ 133—136 ተመልከት ።)

(9) በአንቀፁ ውስጥ የሚገኙትን አረፍተ ነገሮች እያንዳንዳቸውን ከአንድ ከተወሰነ ግምባር ማቅረብ ፤ ከሶስተኛ መደብ ፣ ከሁለተኛ መደብ ወይም ከአንደኛ መደብ ግምባር ። የአረፍተ ነገሮቹ ባለቤቶችም ለምሳሌ ተውላጠ ስሞች ፣ በቁጥር ረገድ (ከእኔ ወደ እኛ ወዘተርፈ . . .) እና በአይነት ረገድ (ከአንተ ወደ እሱ ወዘተ ... ) ወይም በግስ ጊዜያት (ከሃላፊ ጊዜ ወደአሁን ጊዜ) ያለምክንያት መለዋወጥ የለባቸውም ። ከተለዋወጡ የአንቀፁን አንድነት ያናውጡታል ።

ባጠቃላይ እንግዲህ ፣ ከዚህ በላይ የዘረዘርናቸው ነጥቦች በተናጠልም ሆነ እንደየሁኔታው አብረው አብረው እየተገኙ ፣ በአንቀፁ የሚቀርቡትን የተዛመዱ አረፍተ ነገሮች በመከሰት ፣ ለአንባቢያን የየሀሳቡ ተከታታይነትና ግንኙነት እንዲታይና ጉዳዩ ግልፅ እንዲሆን ያደርጋሉ ማለት ነው ።

### 4.2.3 <u>የደልዳላነት ስልት</u>

አንድ እፍኝ ሽምብራ በተመሳሳይነት አንድነት ፣ በጉንቁልነቱ ተዛምዶ እንዳለው ተመልክተናል ። በቡኮንት



ልዩ ልዩ ቅርፅ ያላቸው ብስኩቶች ቢሰራበትስ ፤ የልብ ቅርፅ ያለው ብስኩት ፣ የወፍ ቅርፅ ያለው ብስኩት ፣ የቢላዋ ቅርፅ ያለው ብስኩት እና የመሳሰሉትን አይነት ። ይህ አሰራር ፣ ቆሎን እንደማፈስ ወይም ባቄላ አረስርሶ እንደ ማጉንቈል በዘፈቀደ ፣ መጠን ሳይበጅለት ፣ የሚደረግ አይደለም ። የልብ ቅርፅ ላለውም ብስኩት ሆነ የወፍ ቅርፅ ላለው ፣ የሚቆነጠረው ሊጥ እንደየአስፈላጊነቱ ነው የሚከፋፈለው — ለልብ ጫፍ ወይም ለወፍ ራስ የሚያስፈልገው ለዋናው አካል ከሚያስፈልገው ጋር ተመጣጥኖ ነው የሚለየው — ምስሉ የተደላደለ እንዲሆን ።

በዚህ ረገድ አረፍተ ነገሮችም ፣ በአንቀፁ ውስጥ ያለውን ቦታ ፣ እንደሚይዙት ሀሳብ ትልቅነትና ትንሽነት ተመጥኖ ነው የሚከፋፈሉት ። ለምሳሌ ፣ በአንድ አንቀፅ ውስጥ አስር አረፍተ ነገሮች ቢኖሩ (ምንም እንኳን በአንድ ልቦለድ ውስጥ የተመለከቱትን አንቀፆች ሁሉ በዚህ አይነት ሂሳብ አቀማመጥ ማስላት የማይመስል ቢሆንም ፣ ስድስቱ ወይም ሰባቱ አረፍተ ነገሮች (ሰባ ከመቶ ያህሉ) የሚውሉት ዋናውን ሃሳብ እና/ ወይም ስሜት ለማበልፀግ ነው ። ሶስቱ ወይም አራቱ አረፍተ ነገሮች (ከሰላሳ እስከ አርባ በመቶ ያህሉ) ብቻ ናቸው ደጋፊ ሀሳቦችን እና/ ወይም ስሜቶችን ለማብራሪያ የሚውሉት ።

ዋናው ሀሳብ ይበልጡን ቦታ የሚይዘው በቀጥታ ድርሻው ብቻ ሳይሆን ፣ ከድርሻውም ውጭ ባሉት አረፍተ ነገሮች ውስጥ (ከሱ ጋር ግንኙነት ያላቸው መሆኑን ለማሳየት) በሚደጋገሙት ባለቤት አመልካች ቃላትና ሀረጎች አማካይነትም ጭምር ነው ፤ ዋናዉ ቃልም ሆነ ዋናዉ ሀረግ በተደጋገመ ቁጥር ፣ ዋናዉ ሀሳብ የሚይዘው ቦታ እየሰፋ ይሄዳል ።

ለማካተቻ ደግሞ ራሱ የየአረፍተ ነገሮቹ አቀማመጥ አለ ። በመጀመሪያ ላይ ዋናዉ ሀሳብ ተጠናክሮ ይቀርባል ። ከዚያ ድጋፍ ሰጭዎቹ ሀሳቦች እንደ ክብደታቸው ፣ ከትልቅ ወደ ትንሽ ወይም ከትንሽ ወደ ትልቅ ይቀርባሉ ። እመደምደሚያው ላይ እንደገና በደጋፊዎቹ ሀሳቦች የበለፀገዉ ዋናዉ ሀሳብ እጅግ ተጠናክሮ ይቀርባል ። በአረፍተ ነገር ውስጥ የተመለከትነው የሀሳብ አቀማመጥ ጉዳይ በአንቀፅ ውስጥም ልዩነት ያመጣል ። ምን ጊዜም የመጀመሪያና የመጨረሻ ቦታዎች ክብደትና ታሳቢነት አላቸው ፤ በይበልጥ ደግሞ የአንቀፅ የመጨረሻ አረፍተ ነገር ፣ በአንቀፁ የተዘረዘረውን የሚያጠቃልል ወይም የተዘረዘረውን አጠቃሎ የሚቀጥለውን ሀሳብ የሚጠቁም ጭምር ስለሚመስል ።

## 4.2.4 የቅርፅ ልከኛነት

ስለ ቅርፅ ልከኛነት ስልት ከገፅ 351 — 354 ፣.በተለይ የሚዛናዊነት ስልት የሚለውን ተመልከት ።

## 4.2.5 የማሳደጊያ ስልት*

ልዩ ልዩ የአንቀፅ ማሳደጊያ ዘዴዎች አሉ ። የብዙ ጊዜ የድርሰት ልምድ ያላቸው ሰዎች የግልና የየራሳቸው የሆነ የአንቀፅ ማሳደጊያ ዘዴዎች ሊኖራቸው ይችላል ። ስለሆነም በአብዛኛው የሚሰራባቸውንና በተለይ ጀማሪ ደራሲያን ሊያጠኗቸው ይገ

* ደራሲ የሆነ ሁሉ በቅድሚያ እንደኛውን ሀሳብ በዚህ ፣ ሌላውን በዚያ ፣ ሌላውን ደግሞ በዚያ ወዘተርፈ ... ማሳደጊያ ስልት እፅፋለሁ ብሎ በውሬ — ጭፍኔ አይነሳም ። ሀሳብ እና/ወይም ስሜቱን ጥርት ባለ ሁኔታና በተሟላ መንገድ ሊገልፅ የሚችልበትን ስልት የሚያገኘው የድርሰቱን ርእስ በሚገባ ከመረመረ በኋላ ነው ።



ባል የምንላቸውን ዋና ዋና ዘዴዎች ከዚህ በታች እናመለክታለን ። ዘዴዎቹ ፣ እንደ ሁኔታው በተናጠልና አብሮ አብሮም እየሆኑ ይሰራባቸዋል ።

## በተናጠል እና አብሮ አብሮም የሚሰራባቸው ዘዴዎች

### ሀ. የትረካ አንቀፅ ፤ በጊዜ ተከታታይነት

እውናዊም ሆነ ልቦለዳዊ ታሪክ የሚተረከው በጊዜ ገደብ ውስጥ የተከታተሉ ሁናቴዎችን ወይም ድርጊያዎችን ከባለታሪኮቹ አንፃር በማቅረብ መሆኑን ጠቁመናል ። ከዚህ ለጥቆ ደግሞ እነዚህ ሁኔታዎች በተግባር እንዴት እንደሚተረጐሙ እናያለን።

ማንኛውም ታሪክ እንደ ሰንሰለት ቀለበቶች የተያያዙ የብዙ ሁናቴዎች ወይም ድርጊቶች ቅንብር ነው ። ሰንሰለቱ ጥንካሬ የሚኖረው እያንዳንዱ ቀለበት ጥንካሬ ሲኖረው እንደ መሆኑ ታሪክም ጥንካሬ የሚኖረው እያንዳንዱ የሀሳብ እና/ወይም ስሜት ቅንብር (አንቀፅ) ጥንካሬ ሲኖረው ነው ።

### የሀሳብ እና/ወይም የስሜት ቅንብር ፤

ከአንድ ታሪክ የሀሳብ እና/ወይም ስሜት ቅንብር ዝቅተኛው (ቀለበት) ቅጥብ አንቀፅ ነው ። አንድ አንቀፅ ተከታታይ የሆኑ ጥቃቅን ሁናቴዎችን ወይም ድርጊያዎችን ከነአስፈላጊ ዝርዝር ማበልፀጊያቸው ጋር ይይዛል ። ወይም አንድ አንቀፅ ራሱን የቻለ አንድ ሀሳብ እና/ ወይም ስሜት ከነአሜሩሬው ይኖረዋል ።

## ለ. ሁለገብ እንቅፆች ፤

(1) በስፍራ ወሳኝነት ፤ በሰዎች ፣ በቦታዎች እና በነገሮች መካከል ያለውን አካላዊ ግንኙነት ለመግለፅ የሚሰራበት ላይን ከታች ፣ መካከልን ከዳር ፣ ይህን ከዚያ ፣ ምስራቅን ከምእራብ ፣ ሰሜንን ከደቡብ ፣ ሰውን ከሰው ፣ ሰውን ከነገር አስተያይቶ የሚያስፍር አንቀፅ ነው ። (ከገፅ 129—130 እና ከገጽ 147—150 ተመልከት ።)

(2) በምክንያታዊ ተዛምዶ (በሎጂካዊ) አቀራረብ ፤ ዝርዝር ነጥቦችን ፣ ምክንያቶችን ፣ ማስረጃዎችን ፣ ምሳሌዎችንና የመሳሰሉትን ለማቅረብ የሚሰራበት ነው ።

(ሀ) ምሳሌን ወይም ማስረጃዎችን በማብራሪያነት በመጨመር የማቅረብ ዘዴ ፤
(ለ) ምስል መከሰቻ ነጥቦችን በማቀናበር ዘዴ ፤
(መ) ለአንድ ጉዳይ በርካታ ምክንያቶችን በማቅረብ ዘዴ ፤
(ሰ) ምክንያትና ውጤትን በማደርጀት ፤
(ረ) እንዳለ እና/ ወይም ለዋውጦ በመደጋገም ፤
(ሸ) በማወዳደርና በማነፃፀር ። (ገፅ 214—223 ።)
(ቀ) ምርጫን በማጣበብ ፤
(በ) ከአጠቃላይ ወደዝርዝር በመተንተን ፤
(ተ) ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ በመተንተን ፤
(ቸ) በመዘርዝር ፤ (ገፅ 131—136 ተመልከት ።)
(ኀ) በትርጓሜ ፤ (ገፅ 136—137 ተመልከት ።)
(ኘ) በዝርዝር ነጥቦች ፤ (ገፅ 137—138 ተመልከት ።)



### አስረጅ ፤

## ሀ. የትረካ አንቀፅ ፣ በጊዜ ተከታታይነት

### (1) በአንድ ራሱን በቻለ ድርጊያ ወይም ሁናቴ

« … ትንሽ ጸጥ ብላ እንደቆዩች አንድ ድምጽ በሩቅ እንደሚሰሙት የብዙ ንብ መዝሙር የሚዝገመገም ድምጽ የሰማች መሰላትና አንገትዋን ወደላይ ሳብ አድርጋ ፣ አንድ ጆሮዋን ድምጹን ወደሰማችበት ወገን ደቅና ብታዳምጥ ጠፋ ። የለም ብላ አንገትዋን ስትሰበስብና ጆሮዋን ከደቀነችበት ስትመልስ ደሞ መጣና ልትይዘው ስትል ደሞ ጠፋ ። እንዲሁ እየሄደ ከሚመለሰው የአየር ማእበል ጋር ድምጹም እየሄደ ሲመጣ ፣ እየሄደ ሲመጣ ፣ እስዋም ጨብጣ ለማስቀረት አንድ ጊዜ ቀኝ አንድ ጊዜ ግራ ጆሮዋን እየደቀነች ሲያመልጣት ቆዩና በሁዋላ መሄዱን ትቶ መምጣቱን ቀጠለ ። ሰብለ ወንጌል ያን ትንኮለኛ ድምጽ ከሚሸሽበት በጆሮዋ አባራ ይዛ እንዳመጣችው ሁሉ በጣም ደስ አላት ። ያ ከትንሽ ጊዜ በፊት ጠልሞ ፣ ከስሎ የነበረ ፊትዋ እንደንጋት ሰማይ ወገግ አለ ። ያዘችው ፤ ማረከችው ፤ ምን እንደ ሆነ እስከታውቅ ቸኮለች ፤ እሱም ትንሽ በትንሽ እየቀረበ እየጎላ መጣና በመጨረሻ እንዲር መሆኑን አወቀች ፤ የገብሬ እንዲር… !”[11]

### (2) በተከታታይ ሁነታዎች ወይም ድርጊያዎች

“እንደመጣሁ አባቶቻችን ሠርተውበት የነበረው ቦታ ላይ እነርሱ ሠርተውት ከነበረው የተሻለ ቤት

[11] ሀዲስ አለማየሁ ፣ ‘ፍቅር እስከ መቃብር’ ፣ ገፅ 95 ።

ሠራሁ ። ቀጥሎም ጥንት ያሳርሱት የነበረውን ምድር አሳረስኩ ። እንደኛው ንብረታቸው ጠፍቶ ካገር ተሰደው የነበሩትን ጭሰኞች ከያሉበት ሰብስቤ ቤትና እርሻቸውን እየተረዳዳን አቋቋምን ። ዛሬ ለኮርቻ የሚሆን በቅሎ ፥ ለግልቢያ የሚሆኑ ፈረሶች ፥ ለጭነት የሚሆኑ አጋሰሶች ፥ ለወተትና ለእርሻ የሚሆኑ የቀንድ ከብቶች ገዝቼ መንደራችን እንደ ጥንቱ ደምቋል ። ላባቶቻችን ነፍስ መታሰቢያም ደማቸው የፈሰሰበት ቦታ ቤተ ክርስቲያን ተተክሎበት ለምለም ሆኖ እንዲኖር ታላላቅ ዛፎች ጸድቀውና ለምተው ላያቸው ደስ ያሰኛሉ ። በእውነት የጠፋውን በቦታው ለመመለስ በማደርገው የመውጣት የመውረድ ድካም አንቺን የማስታውስበት ጊዜ የለኝም ነበር ። የማይቀረው ቀን ዐልፎ ያ የማይቀረው ሌሊት ሲተካ አንዳንድ ጊዜ አካልዐርፎ ነፍስ መድከሟን አታቋርጥም ። የመጀመሪያው የድካሜ እንቅልፍ ሲያልፍ ያንቺ ከኔ መለየት ትዝ እያለኝ ሐዘኔ ይበረክታል ። ከመጣሁ የገዛኋቸው ላሞች ወልደው ፥ ከመጣሁ የተከልኩት ዛፍ ፍሬ አንዠርጎ ሳይ ያለፈውን የቤተሰባችንን ታሪክና የኛን አስተዳደግ አሁን ብቻዬን ከምገኝበት ሁኔታ ጋር ሳስተያየው አንዳንድ ጊዜ ልቤ ገዳምን ይመኛል ። ላሞቼ ጥጆች ወለዱ ፥ እኔ ልጅ የለኝም ። አትክልቴ አፈራ ፥ እኔ አላፈራሁም ። የሰው ምኞት የሚሞላለት ችግሩን የሚወያየው ረዳት ጓደኛ ሲኖረው መሆኑ የታወቀኝ ዛሬ ዕድሜዬ ይበልጥ እየጠና ያለፈውንና ያሁኑን እያስታወስኩ በዚህ አኳኋን ብቻዬን እስከመቼ እኖራለሁ ብዬ ግራ እየገባኝ ነው ። ቀን ከኔ ጋር ሲደክሙ የዋሉ ሰዎችና እንሰሶች ማታ ሲሆን ሁሉም ወደ ማደሪያ



ቤታቸው ሲበታተኑ ፥ በሞተው ሌሊት ውስጥ እኔና ሀሳብ ገላጋይ በሌለበት ቦታ ግንባር ለግንባር ትግል እየገጠምን ከሁለት አንዳችን መጣል እየተሳነን ነጋም ያው በመሆኑ ተቸገርኩ ፤ አንቺስ ውሎሽ ከብዙ ጋር ሆነና ልብሽ ጠና ። ያም ብዙ ክፉና ደግ ያየሽበት ምድር አልናፍቅሽ አለ ...”[12]

ለ. <u>ሁለገብ እንቀዖች</u>

(1) <u>በስፍራ ወሳኝነት</u>

(ሀ) <u>ከሩቅ ወደቅርብ</u>

<u>አስረጅ ፤</u>

‘... የእነርሱ መኖሪያ ቤት ይገኝ የነበረው ሬማፈግግ ወደሆነው ቦታ በሚያመራው መንገድ በኩል አድርጎ ሲሆን ፥ ምንም እንኳን ይኸ ቤታቸው የተሠራው ጉብታማ ቦታ ላይ ባይሆንም ኮራ ብሎ ደረቱን ከነፋ ቦታ ላይ ከሚገኘው ከስፈሩ በስተመጨረሻ አኳያ በስተግርጌ በኩል ነው ። ከቤቱ ስፋት ሩቡን ያህል የማዕድ ቤቱ የያዘው ሲሆን ፥ እናቲቱ የምትተኛበት ክፍልም በስተጥግ በኩል በትንሽ ክፍል ተከፍሎአል ። የተቀረው የቤቱ ሁለት ሦስተኛ ደግሞ ሁለት መስኮቶች ያሉት እና ባለ አራት ማዕዘን ሆኖ የተሠራ ነው ። አንደኛው ጥግ ላይ የፓቬል አልጋ ተዘርግቶበታል ፤ ሌላው ጥግ ደግሞ ጠረጴዛና ሁለት አግዳሚ ወንበሮች ተዘርግተውበታል ። የተቀሩት የቤት ዕቃዎች — ጥቂት ወንበሮች፥ትንሽ መስተዋት እላዩ ላይ ያለበት የልብስ ኮሞዲኖ (ቁምሳጥን) ፥ ልብስ ያለበት ስንዱቅ ፥ ግርግዳ ላይ የግርግዳ ሰአትና በቤቱ በስተጥግ በኩል ደግሞ ሁለት የሚፀለይባቸው የቅዱሳን ሥእሎች... ናቸው ...’[13]

---

[12] አበፋ ገ/ማርያም ፥ ‘እንደ ወጣች ቀረች’ (ኢ.ኢ. 1956 ፥ ገፅ 153-154) ።
[13] ማክሲም ጎርኪይ ፥ ‘እናት’ ፥ ትርጉም ፥ በማዕዘን የማነ (ሞስኮ 1983) ገፅ ፥ 34 ።

(ለ) ከታች ወደላይ

.'ሜዳው ከፊታቸው እየተዘረጋ ሲሔድ የበለጠ ያማረ ሆነ. . . ያንን ወሰን የሌለውን ለጥ ያለ መስክ ምንም ማረሻ ገና አልነካውም ። እንደ ጫካ የሚውጠውን ይህን ረጃጅም ሳር እየጣሱት የሚያልፉት ፈረሶች ብቻ ነበሩ ። እንደዚያ ያለ የተፈጥሮ ውበት በየትም አልነበረም ። የምድርዋን ገጽ በሚሊዮን የሚቆጠሩ አበቦች ጣል ጣል ያሉበት ወርቅማ አረንጓዴ ውቅያኖስ ያለበሰው ይመስል ነበር ። ረጃጅምና ቀጫጭን በሆኑት የሳር ዘለላዎች መካከል ሰማያዊ የወይን ጠጅና ሌላም ልዩ ልዩ ቀለማት ያላቸው አበቦች ብቅ ብቅ ብለዋል ፤ ከየት እንደመጣ እግዚአብሔር ይወቅ አንድ ዘለላ ስንዴ በጓሳው ውስጥ አፍርቶ ይታያል ። አልፎ አልፎ ቆቆች ከሳሩ ሥር አንገታቸውን ብቅ አድርገው ይመለከታሉ ። የሺ አእዋፍ ዜማ ሜዳውን ሞልቶታል . . . ሰማይና መሬት የገጠመ ከሚመስልበት ስፍራ ዝዮች እየጮሁ በአጀብ ሲበሩ ይታያሉ ። ከሳሩ ውስጥ አንዲት አሞራ ተነሥታ በሰማያዊው አየር እየታጠበች በረረች ። ወዲያው ጥቁር ነጥብ እስክትመስል ድረስ ወደአየር ርቃ ተጓዘች ። አሁን ለአጭር ጊዜ ብቻ ክንፍዋ በጸሃይ ብርሃን ብልጭ ሲል ይታያል ... ' [14]

. 'ከድን ያለ ተረከዝ ደብለል ያለ ባት ፣ ሰፋ ያለ ዳሌ ፣ ከሳ ያለ አንጀት ፣ ለቀቅ ያለ ሽንጥ ፣ መለል ያለ አንገት ፣ አስደንጋጭ ፈገግታና የአነጋገር ፈሊጥ የታደላት ሴት ወንድን በፍቅር ለማጥመድ ሆን ብላ የተፈጠረች ናት ቢባል ... ' [15]

---

14 ኒኮላይ ጉጉል ፣ 'ታራስ ቡልባ' ፣ ትርጉም ፣ በባካፋ ኃይለ የሱስ (ሞስኮ 1975) ፣ ገፅ 26—27 ።

15 ገብሬ እድማሱ ፣ 'እያወቁ ማለት' ፣ (አ/አ 1968) ፣ ገፅ 109 ።



(መ) ከላይ ወደታች

'... የቤቶቹ ጣራ ሕዝብ ተከምሮበታል ። ከየመስኮቶቹም የሰው ፊት ብቅ ብቅ ብሎ ይታያል ። በበረንዳዎቹ ላይ የጨዋው ወገኖች ተቀምጠዋል ። የአንድ የምትስቅ ወይዘሮ እንደ ስኳር የነጣ የሚያምር ክንድ በረንዳውን ተደግፎ ይታያል ። በረንዳው ላይ ተቀምጠው የሚመለከቱም መኳንንት ክብር የተሰማቸውና የተጀነኑ ወፈፍራም መኳንንት ነበሩ ። የአማረ ልብስ የለበሰ አሳላፊ ልዩ ልዩ የመደሰቻ ምግብና መጠጥ ይዞ እየዞረ ያሳልፋል ። ብዙ ጊዜ አንዲት ዐይነ መልካም ቀበጥ ወይዘሮ አንድ ብስኩት ወይም ፍሬ ፣ ወተት በመሰሉት ጣቶችዋ ታነሳና ቁል ቁል ወደ ተሰበሰበው ሰው ትጥላለች ። የተራቡት ፈረሰኛ ወታደሮችም ለመያዝ ቆባቸውን አውልቀው ሲዘረጉ ቁመቱ ከፍ የሚለው አንድ ወታደር ቀድሞ ይቀበለውና ስሞ ወደአፉ ይልከዋል ። ክፎቁ በረንዳ ሥር በተንጠለጠለ አንድ የብረት ጎጆ ውስጥ ያለ ንስር አሞራም አንገቱን ወደ አንድ ጐን ዘንበል አድርጐ ከተመልካቾች መካከል አንዱ በመሆን ቁልቁል ያስተውል ነበር ። ወዲያው በሕዝቡ መሃል ጫጫታው በዛና. . . ' [16]

(ሰ) ከዳር ወደማሀል

'ጫካው ፣ በጣም ያረጁ የወፋፍራም ጠየና የወይራ ዛፎች ነበር ። ስራቸው በመሬቱ ላይ ወጥቶ የተወጋገረ ፣ ቅርንጫፎቻቸው የተጠማዘዘ ። በመካከላቸው አጳር ጠን ነበር የምንራመደው — የፀሀይ ብርሃን በልዝብ ዝርጋታ ጥቅጥቅ ያሉ ቅጠላቅጠሎቻቸውን እያለፈ ሲር

---

16 ኒኮላይ ጉጉል ፣ 'ታራስ ቡልባ' ፣ ትርጉም ፣ በባካፋ ኃይለ የሱስ (ሞስኮ ፣ 75) ገጽ 163—164 ።

ገበገብ ፤ የጨሌ ክምክም እንጂ አራሙቻ አልተገማሸረም ፣ በነዚህ በምናልፋቸው እንደ መናፈሻ ቦታ በወግ በወግ የተሰለፉ ከሚመስሉት አፈርማ ትልልቅ ዛፎች ስር. . .' (ከሄሚንግዌ)

(2) በምክንያታዊ ተዛምዶ (በሎጂካዊ) አቀራረብ

(ሀ) ምሳሌ ወይም ማስረጃዎችን በማብራሪያነት በመጨመር

• “በጃን ሜዳ ውስጥ በይበልጥ ሰውን የሚስብና የሚያሰባስበው ቢኖር የየብሄረሰቡ ዘፈንና ጭፈራ ነው ። አንዱ ወገን ከበሮውን ይዞ በለዘብታ “ላልማዬ” እያለ እየተምነሸነሸ ሲሽከረከር ፣ ሌላው ወገን የዝንጀሮ ጐፈሩን አጥልቆ ፣ ቀጭን ዘንጉን ይዞ ፣ “አሸማ አሸማ” እያለ ሰማዩን እየጠቀሰ ያርፋል ። አንዱ “ላላሜቦ ላሌ ኤቦላሌ” እያለ ሸብረክ ብሎ ሶምሶማ ሲረግጥ ፣ ሌላው ደግሞ “እሽከር አበባው” እያለ ጭብጨባውን ያቀልጣል ። በዘፈኑ ቦታ የዘመኑንም ሮክና ጃዝ የሚጫወቱ ጥራዝ ነጠቅ ወጣቶችም አልታጡም ። ትግሮች ከበሯቸውን ይዘው ሲሰለቁ ፣ አማሮች በጭብጨባ ሲውረገረጉ ፣ ወጣቶች በትዊስትና በሮክ ሲምነከነኩ ፣ ኦሮሞች ዘንጋቸውን ይዘው ሲወረወሩ ፣ ጉራጌች ነጠላቸውን አገልደመው ሲያስመሱሙ የሚያይ ሁሉ የአዲስ አበባ ህዝብ የቱን ያህል ዘፈንና ጭፈራ አፍቃሪ እንደሆነ ሊረዳ ይችላል ... ”[17]

---

17 ዳኘቸው ወርቁ ፣ ‘የኪነ-ፅሁፍ ስልት መለማመጃ’ — ያልታተመ ፣ (1963 — አ.አ. ዩኒቨርስቲ) ፣ ገፅ 45 ።



(ለ) ምስል መከሰቻ ነጥቦችን በማቀናበር

• «...እንቅልፏን ጠግባ የተነሳች አይነት ፊቷን ታባብሳለች ፣ እንደ ቡፌ ድመት ። በፊቷ ውስጥ የሚንቀለቀለው የደረሰ ስሜት ሲፈራ ሲቸር ይታያል ፤ አልፎ አልፎ ብርቅ ፍንጥቅ እያለ የዝንኪላ ፍሬ ቀለም በገቡት አይኖቿ እያለፈ ሲውገነገን ። የቀይ ዳማ ገፅታዋን ሲያበራው ሲያጠፋው ። ከንፈሮቿ ደረጃ ደረጃ የወጣለት ደማቅ ጥቁር ተቀብተዋል ፤ ልክ በጊዜው ፋሽን ። ሽፋሽፍቶቿ ተነቅለው በቀጭኑ ተረስሰዋል ፤ በጊዜው ፋሽን ። እንደዚሁም በጊዜው ፋሽን ዘመናዊ ቅንድቦች ሰክታለች ፤ የቂንዳቸው ጮራ ያይኖቿን ውጋጋን እንዲናኝ አይነት ። ሰማያዊ ክፋይ ጉርድ ለብሳለች ፣ በሁለት ጉብታዎች ላይ ከተናደ ነጭ የሀገር ሸሚዝ ጋር ፤ ወገቧን በቀይ ቀበቶ ሸብ አድርጋ ። በመዘዞ እንገቷ ላይ ፣ አጉጠጉጤ መሳይ ትልቅ ዛጐል በወርቅ ሀብል ተሸብቧል ። ረጅምና ጥቁር ፀጉሯ በቀጭን በቀጭኑ ተጐንጉኖ ጫፍጫፉ በትናንሽ ዛጐል ተቆልፏል ። ስትንቀሳቀስ ፊቷን ዙሪያውን እያበሰ እዋት እዋት እያለ ድብብቅ እያጫወተ ። ታዲያ ፀጉሯም ያኮራታል ፤ ሆነ ብላ የምታደርገው አይነት ወደቀኝ ወደግራ በዞረች ቁጥር አብሮ አብሮ እየሆነ ሲያወካ እየሰማች ... ”[18]

---

18 ከአዘጋጁ

- "... እማብቂያው መስመር ላይ የነበርነው ገና
ገብተን አልጨረስንም ። በየዴስኩ መካከል
እየተሽሎከለክን መታወቂያ ቁጥራችን በየነ
በረበት ቦታ በመድረስ መቀመጫችንን እየ
ያዝን ነው ። በአዳራሹ ውስጥ ፈንጠር ፈን
ጠር ብለው ቆመው ስነ ስርአቱን ያስከብራሉ ፣
አምስት ያህል ፈታኞች ። ዋናው ፈታኝ በአ
ዳራሹ ፊለፊት በነበረው መድረክ ላይ ቆሞ
ዙሪያውን ይማትራል ፣ ይመለካከታል —
አንዱ ራሱን ሲያካክክ ፣ ሌላዋ የጭቃ ቀለም
መክደኛዋን ስትነካክስ ፣ ሌላው ጉልበቶቹን
ሲያወዛውዝ ፣ ሌላዋ ተስተካክሎ የተሰራ
ፀጉሯን ስትገላጉል ፣ ሌላው የአፍንጫውን
ጫፍ በሁለት ጣቶቹ ደጋግሞ ሲያረማምድ. . .
ከኮቴ እንቅስቃሴ ድምድምታ ፣ ከእርሳስ ፣
ስክሪፕቶ ፣ ብእርና ማስመሪያ ድውድውታና
ቅውቅውታ ፣ በስሜት ከተወጠረ የሰው ትን
ፋሽ እምምታ በስተቀር ፀጥ ወደማለቱ እየ
ተቃረበ ነው ። የመጨረሻው ተማሪ ገብቶ
ቦታውን እንደያዘ ዋናው ፈታኝ ትክ ብሎ
ሰአቱን መመልከት ጀምሯል ... " [19]

(መ) በበርካታ ምክንያቶች

- "... ነፋስ ለሰው ልጅ ለእንስሳትና ላትክልት
ይጠቅማል ። ባንድ ዐይነት አስተያየት እነዚህ
የተጠቀሱት ፍጥረቶች ያለዝናም ወይም ያለ
ውኃ ለመኖር አይችሉም ።
ነፋስ በሙቀት ኀይል ካየሩ ላይ የሚነሣ

19 ዳኛቸው ወርቁ ፣ 'የኪነ-ጽሁፍ ስልት መለማመጃ' ፣ ያልታተመ (1963—አ.አ.አ. ፣ አ.አ. ዩኒቨርስቲ) ገፅ 60 ።



ውኃ ውኃ ባየሩ ላይ እየነዳና እየወሰደ እን
ዲዘንምላቸው ያደርገዋል ። በዚህ አኳኋን
ነፋስ በርጥበት አብቅለውና በሙቀት ኀይል
እንዲያበስሉ ይደግፋቸዋል ። ለሰው ልጅ
በተለይ የሥራ ረዳቱ ነው ። አዝርዕት እንዲ
ያድጉለትና በደረሱም ጊዜ በውቂያ ላይ ምርቱ
ከገለባው እንዲለይለት ያደርግለታል ። ያላ
ንዳች ሥጋትም አይሮፕላን ባየር ውስጥ እን
ዲበር ይረዳል ። ላትክልትም ፣ አንደኛ ሴቴ
ንና ወንዴን አበቦች እያጋባ እንዲራቡ ያደ
ርጋቸዋል ። ሁለተኛ ፣ ጥቅጥቅ ባለ ጫካ ውስጥ
የፀሐይን ብርሃን ለማግኘት የማይችሉትን አት
ክልት ፣ ባጠገባቸው የሚገኙትን ወዲያና ወዲህ
እያላጋ የፀሐይን ሙቀት ከነጨረሯ እንዲያ
ገኙ ያግዛቸዋል ። በዚያውም ላይ ይህን በሚ
ያደርግበት ጊዜ በጠቅላላ ለዕፅዋት ብርታትን
ይሰጣቸዋል ። ለደማውያን እንስሶች ፣ ሸማ
በየፈርጁ ይለበሳል እንደሚባለው ፣ በልዩ
ልዩ ስልት ይጠቅማቸዋል ። አንዳንዶቹ እን
ስሶች በተለይ የማሽተት ስጦታ ስላላቸው
ከሩቅ ምን ነገር እንደ መጣባቸው ወይም ምን
እንደ መጣላቸው ይነግራቸዋል ... " [20]

- የወደፊቱ የኢትዮጵያ ተስፋዎች ገና በመወለድ
ላይ ሳሉ በአጭር እንዳይቀጩ ፣ እናቶች ታዳጊ
ልጆቻቸውን አፍስሰው እንዳይቀጠፉ ፣ ነዋ

20 ተክለ ማርያም ፋንታዬ ፣ 'ኖኅተ ጥበብ ዘሥነ ጽሑፍ' ፣ አ.አ. (1964 ፣) ገፅ 171—172 ።

ሪዎች በቀላሉ በሚፈወስ በሽታ ተለክፈው
የመንፈስ ወይም የአካል ስንኩላን ሆነው
ሽክም እንዳይሆኑ በአቅራቢያቸው የጤና ጣቢያ
ያስፈልጋቸዋል ። ከበሰበሰ ኩሬ የገማ ውሃ
ቀድቶ ከመጠጣት ፣ እድሜ ልካቸውን እንስራ
እየጋለባቸው አለእድሜያቸው ከማጉብደድ
እንዲድኑና እንዲሁም ከእንቅርትና ከቢልሃ
ርዚያ እንዲጠበቁ በአቅራቢያቸው የተዘረጋ
የቧንቧ ውሃ ያስፈልጋቸዋል ። ልጆቻቸው
የከብት ጭራ ተከትሎ ከማደግ በስተቀር ሌላ
ነገር ሳያውቁ ደንቁረው እንዳይቀሩ ፣ አዳዲስ
ሙያ ፣ አዳዲስ አመለካከት እንዲኖራቸውና
ኑሯቸው እየተሻሻለ ከጊዜው ጋር እንዲራመዱ
በአቅራቢያቸው ትምህርት ቤት ያስፈልጋቸ
ዋል ። ጀንበር ባቆለቆለች ቁጥር በእንጦርጦር
ጨለማ ከመዋጥ ፣ ዘለአለም በእንጨትና
በኩበት ጭስ ታፍኖ ከመቸገር ለመውጣት ፣
የመብራት ሃይል አገልግሎት ያስፈልጋቸ
ዋል ። ለግማሽ ሰአት መንገድ ግማሽ ቀን
ሲዳክሩ ከመዋል ፣ የግብርና ውጤታቸውን
አገበያ ፣ የእንዱስትሪ ውጤቶችን እደጃ
ቸው ለማግኘት መገናኛ ያስፈልጋቸዋል ።
ሌሎችም — የመዝናኛ ፣ የመገበያያ ፣ የመ
ረዳጃ — አገልግሎቶች የሚሰጥባቸው ማእከሎች
የሚያስፈልግባቸው ምክንያቶችም አሉ ። ስለ
ሆነም እነዚህ ግልጋሎቶች በየጉባው ፣ በየ
ተራራው ፣ በየሸለቆው ተራርቆና ተበታትኖ
የትየለሌ ለሰፈረ ቤተሰብ ሁሉ ለየብቻው
ሊቀርቡ አይችሉም ፤ መሰባሰብን ይጠይቃሉ ።
የጤና ጣቢያን ፣ የትምህርት ቤትን ፣ የመገና



ኛን ፣ የውሃና የኮረንቲን እንዲሁም የሌሎ
ቹን አስፈላጊነት በመረዳት የዜግነት መብቶ
ቻቸው አድርገው እንዲሟሉላቸው መንግስ
ትን የሚጠይቁ ሁሉ ለመግቢያ ያህል በአንድ
አካባቢ የመሰብሰብና የመደራጀት ግዴታና
ሀላፊነት ያለባቸው መሆኑንም ማወቅ ይኖ
ርባቸዋል ። [21]

## (ሰ) ምክንያትና ውጤትን (ስለዚህ — እንዲህ) ማደርጀት

### አስረጅ ፲

" ... ቤተሰብ ሲፈርስ ፣ ልጆች ከእናት
ወይ ከአባት ጋር እንዲኖሩ ወይም እንደቁሳ
ቁስ በቁጥር ተለይተው ለእናትና ለአባት እኩል
እኩል እንዲደርሱ ይደረጋል ። የየድርሻቸ
ውን የተካፈሉም ሆኑ ሳይከፋፈሉ በአንዳቸው
ሀላፊነት ብቻ እንዲያድጉ የሚስማሙ እናትና
አባት አላማቸው የተመሳሰለ ነው ፤ በጊዜያዊ
መደለያ በማባባል የልጆቹን ፍቅር የየራሳ
ቸው የብቻ ድርሻ አድርገው ለመኖር መታ
ገል ። በእናት ስር የሚተዳደሩ ከሆነ ወደ አባት
ዘንድ ለጉብኝት ሲሄዱ ከተገቢው በላይ መስ
ተንግዶ ይቆያቸዋል ። በአባት ስር የሚተዳደ
ሩም ከሆነ ፣ እናት ዘንድ ሲሄዱ እንዲሁ የተ
ለየ መስተንግዶ ። እንዴ እናት ዘንድ እንዴ
አባት ዘንድ ፣ አባት ዘንድ እናት ዘንድ ፣ እናት
ዘንድ አባት ዘንድ ፣ ልጆች የሚውሉበትንና

[21] ከአዘጋጁው ።

የሚያመሹበትን ቦታ ሁኔታ መከታተል ያዳግታል ። የሚያደርጉትንና የተሰማሩበትን ተግባር ለማወቅ ይቅርና ። የት ነበራችሁ ሲባሉ "አባጋ" ወይም "እማዬጋ" ፣ ምን ስታደርጉ ቆያችሁ ሲባሉ፥ "ከአባዬ ጋር ስጫዎት" ፥ "እማዬን ስራ ስረዳ" — የማይሉት የማይፈጥሩት ምክንያት አይኖርም ። ለቁጥጥር አመችነታቸው ይዳከማል ፣ ቁጥጥር ይላል ። ከአጓጉል ጓደኞች ጋር መዋል በአጓጉል ቦታዎች መገኘት ይጀምራል ። በሆነ ባልሆነው ምክንያት አንዴ ከአባት አንዴ ከእናት ፥ ከዘመድ አዝማድ ገንዘብ እየተወሰደ ። ፍላጎት እያደገ ይሄዳል ፣ ገንዘብ እያጠረ ፣ የህይወት ትርጉሙ እየጠፋ ፣ መንፈስ እየተረበሸ ፣ አይሰሩ ስራ እየተሰራ — ሞራላቸውን እያላሸቀ ። እንዲያም ብሎ ይባስ ሲል ፥ ግዴለሽነትን ፥ ሲጠናዎት መዛዘንን ፥ ሲረጋጋ ወመኔነትን ፥ ሲለይለት ወፈፌነትን እያስከተለ . . . . የቤተሰብ መፍረስ ፥ የመንፈስ መረበሽና የሞራል ውድቀት ፥ የወመኔነትና የወሮበልነት ፥ ግፋም ሲል ፥ የወንጀለኝነት መንስኤ ነው ... "

ከላይ እንደ ተመለከትነው ፥ በ"ስለዚህ -እንዲህ " ወይም በ"እንዲህ - ስለዚህ" (ከድርጊት ተነስቶ አድራጊውን ለማግኘት ማስረጃ በማሰባሰብ) ወይም በ"እንዲህ - እንዲህ "(ድርጊትን ለተመሳሳይ ድርጊት መገኘት ማስረጃ በማድረግ) ፥ ምክንያታዊ ተዛምዶ ስልቶች እየተጠቀሙ አንቀፅን ለማበልፀግ ይቻላል ።



(ረ) <u>እንዳለ እና ለዋውጦ በመደጋገም</u>

«...ድሮ ያባ ዳኘው ግዛት ወሎን እንደ እግር ሽዋን እንደ እምብርት አደረገና ግራ ክንፉን ወደ ጨርጨር ፥ ቀኝ ክንፉን ወደ ወሊጋ ዘርግቶ እራሱን ወደጅማና ወደከፋ አቅንቶ ይሰፋ ይንሰራፋ ጀመረ ። ያባ ዳኘው ፈረስ ከዚህማ ወዲያ ፀሐይ አይጠመርረው ፥ በረሀ አያልበው ፥ ቁልቍለት አይደክመው ፥ አቀበት አይገታው ፥ እንዲአው ይረብ ፥ እንዲአው ይነጕድ ፥ መሬት አይብቃኝ ፥ ሜዳው ጠበበኝ ይል ያልፍ ፥ ይሄድ ጀመረ ...» 22

«...ከዚህ ወዲአ ዘበኛ እንደ ሌሊ አንገቱን ወደ ምድር ቀብሮ የነበረው እንገቱን ብቻ ቀና እያደረገ ተኩሱን ለቀቀው ። ከዚህማ ወዲያ ምን ይሆናላ... ያ ሁሉ ጀግና ፥ ያ ሁሉ ጐበዝ ፥ ያ ሁሉ መዘዞ ፥ ያ ሁሉ ተማች ፥ ያ ሁሉ ወዘላ ጐበዝ ፥ ያ ሁሉ ወጣት ሽልሚ ፥ እግር እግሩን ተሰንክሎ ተሰንክሎ በረዶና ወጀቦ ተጋግዞ ያበላሸው የገብስ ዝርዝር መሰለ ...» 23

«... የጎጃምን እናት ፥ የጎጃምን አባት የጎጃምን ሙሽራ ፊቱን አስነጩት ፥ ጠጕሩን አስቆረጡት ፥ ማቅ አስለበሱት ። በምባቦ ጦር ስንት ሙሽራ ባሏን አጣች ፥ እስንት እናት አባት ደገፋቸውን ፥ ጧሪአቸውን

22 አፈ ወርቅ ገ/ኢየሱስ ፥ 'ዳግማዊ ምኒልክ' ፥ (ሮማ 1901) ፥ ገፅ 29 ።
23 ከላይ ከተመለከተው ፥ ገፅ 35 ።

አጡት ፥ የስንቱ ጋሻ ተሰበረ ፥ እስንት ጎሻሜ ምሾ አወጣች ፥ እስንቲ ተፋጀ ፤ እስንቱ አለ ቀሰ ......... »[24]

«... ሰውን አትናቅ ፤ ሥራውንም አት ንቀፍ ... ገበሬውን አትንቀፍ ፤ ከነቀፍኸውም እህሉንና አትክልቱን ከእርሱ አትፈልግ ።

«ነጋዴውን አትንቀፍ ። ከነቀፍኸውም ሐሩን፥ ምንጣፉን ፥ ሌላውንም የንግድ ዕቃ ሁሉ ከእርሱ አትፈልግ ።

«ወታደሩን አትንቀፍ ፤ ከነቀፍኸውም አገ ርህን የሚያጠፋ ፥ ነፍስህን የሚገድል ጠላትህ ሲመጣ ተዋጋልኝ አትበለው ።

«ካህኑን አትንቀፍ ፤ ከነቀፍኸውም ፥ አስ ተምረኝ ፥ አጥምቀኝ አቁርበኝ አትበለው ...

«... ፋቂውን አትንቀፍ ፤ ከነቀፍኸውም በቁርበቱ አትተኛ ።

«ሸክላ ሠሪውን አትንቀፍ ፤ ከነቀፍኸውም የሸክላውን ዕቃ ሁሉ ከርሱ አትፈልግ ...

«... ሸማኔውን አትንቀፍ ፥ ከነቀፍኸውም ልብስ ሥራልኝ አትበለው ።

24 ከላይ ከተመለከተው ፤ ገፅ 36 ።



«ሌላውንም ይህንን የመሰለውን ሠራተኛ ሁሉ አትንቀፍ .........»[25]

«... ስንት ሰዎች የነበሩ ይመስልሃል ።

«የድኃ እንባ ሲፈስ የወንዝ ውኃ የሚፈስ የሚመስላቸው ፥ ስንት ሰዎች ነበሩ ።

«ድኃ ሲጮህ ውሻ የሚጮህ የሚመስ ላቸው ስንት ሰዎች ነበሩ ።

«ድኃ ታስሮ ወይም በሌላ ጭንቅ ነገር ተይዞ ሲሞት ግልገል የሚሞት የሚመስላቸው ስንት ሰዎች ነበሩ ።

«ጉልበት ካለን ብለው በደካች ሞላይ ያሰ ቡትን ሁሉ የሚሠሩ ስንት ሰዎች ነበሩ ።

«ሰውን ለማጥፋት እጅግ የሚጥሩ ፤ ሰው ንም ካላጠፉ እንቅልፍ የማይወስዳቸው ስንት ሰዎች ነበሩ ።

«ነገር ግን ከዚህ ቀደም የነበሩት ሁሉ መሬት ሆነዋል ። ከመሬት የተገኘ ሁሉ መሬት ስለሆነ ወደ መሬትም የማይመለስ ስለ ሌለ ፤ እኛም ነገ እንደነዚያው እንሆናለን... »[26]

«...ነገር ግን እኛን ቅር የሚለን ፥ እኛ የም ናዝነው ፥ እኛ የምንጨነቀው ፥ ዕድሜያችን የደ

25 ኅሩይ ወ/ሥላሴ ፥ 'ለልጅ ምክር ለአባት መታሰቢያ ።' (አ.አ.1963) ፥ ገፅ 99—100 ።
26 ከላይ ከተጠቀሰው ፤ ገፅ 104—105 ።

ረስ ፥ ልጣችን የተራሰ ፥ መቃብራችን የተማሰ ሆኖ በሚገኝበት ጊዜ ፥ እኛን እንደ መጦርና ፥ አስታሞ ፥ አጥቦ ፥ አጥኖ ፥ ገንዞ እንደ መቅበር ፥ ወደ ውጭ አገር ልሒድ ማለትህ ብቻ ነው አሉኝ…» [27]

"…ሌሎች አገሮች ምንም በተግባረ ዕድ ቢያ ምሩና ቢሽቀረቀሩ ፥ የእኔን አገር የመሰለ ሌላ መልካም አገር ፥ የኔን አገር የሚወዳደር ሌላ ደግና አገር ላይገኝ ምን ያታክተኛል ። ይሁን እንጂ የውጭ አገር ሰዎች ያሉበት አገር ፥ ምንም የተፈጥሮ ውበትና መልካምነት ባይኖረው ፥ በሰዎቹ ትጋት ፥ በሰዎቹ ብርታት ፥ በሰዎቹ መማር ፥ በሰዎቹ መጣጣር ፥ ለጭንጫው መሬት ያለውን የተሟላ የሥልጣኔ ልምላሜ አይቼ ይህ ብቻ በአገሬ በመጉደሉ ኀዘን ተሰማኝ …» [28]

"…ለመበዝበዛችንና ለመጨቆናችን መንስኤ የሆኑትን የኢኮኖሚ ፥ የፖለቲካና የማህበራዊ ሁኔታዎች በማያወላውል ሁኔታ መለወጣችን ለማንም በገሀድ የሚታይ ሀቅ ነው ።

"… ዛሬ የኢትዮጵያ ሰፊ ሕዝብ የሥራው ውጤት ባለቤት እንደመሆኑ በእሱ ላብ ሲንደ ላቀቁ የኖሩት ክፍሎች ወይም መደቦች ዘመን በእርግጥ አክትሟል ።

[27] ወ/ጊዮርጊስ ወ/ዮሐንስ ፥ 'እግዐዚ' ፥ ገፅ 30 ።
[28] ከላይ ከተመለከተው ፥ ገፅ 43 ።



«ዛሬ የኢትዮጵያ ሰፊ ሕዝብ በሀገሪቱ የፖለ ቲካ ፥ የኢኮኖሚና የማህበራዊ ህይወት ውስጥ ንቁ ተሳትፎ የሚያደርግ እንደመሆኑ በማናቸ ውም አቅጣጫ የሚቀየሱት የልማት መመሪ ያዎችና ፕሮግራሞች ሁሉ የእሱን ፍላጐት ለማርካትና ጐስቋላ ሕይወቱንም ለመለወጥ የሚታቀዱ ናቸው ።

"ዛሬ የኢትዮጵያ ሰፊ ሕዝብ ነፃነቱን ለማስ ከበር ከምን ጊዜውም ይልቅ ተደራጅቷል ፤ ታጥቋል ፤ ንቃተ ሀሊናውም እንዲሁ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየዳበረ መጥቷል ። ስለዚህ ከእንግ ዲህ የኢትዮጵያ ሰፊ ሕዝብ የተቀዳጃቸውን ድሎች የሚነጥቀው ምንም ዓይነት ኀይል አይኖርም ።

"ከግባችን ለመድረስ ፥ ማለትም ቁሳዊና መን ፈሳዊ ሕይወቱ የዳበረ ሶሻሊስት ህብረተሰብ ለመገንባት ወደፊት መጓዝ ያለብን ጐዳና ረዥም ቢሆንም በእስከ ዛሬው ትግላችን የተቀዳጀና ቸው ድሎች ከፍተኛ ግምት የሚሰጣቸው ናቸው …" [29]

"አገራችን ተለውጣለች ስንል በእኩል ነት ፥ በፍትህና በዲሞክራሲ ላይ የተመሠረተ ዕድገት ለማስገኘት የሚያስችሉ ቅድሚያ እርም ጃዎችን ሁሉ በቆራጥነት ወስደናል ማለታ ችን ነው ።

[29] ሠርቶአደር ፥ ቅጽ 3 ፥ ቁጥር 105 ፥ መስከረም 2 ቀን 1975 ።

"አገራችን ተለውጣለች ስንል ለተፋ ጠ ነና ለተመጣጠነ ዕድገት ማነቆ የነበሩትን ሁኔ ታዎች ሁሉ አስወግደናል ማለታችን ነው ።

ስለዚህ ፣ ከእንግዲህ የአገራችን ከኋላቀር ነት መላቀቅና ቁሳዊና መንፈሳዊ ሕይወቱ የተሟላ ህብረተሰብ መገንባታችን የሚወሰ ነው እያንዳንዳችን በተሠማራንበት የሥራ መስክ ሁሉ ለዚሁ ግብ መሳካት በምናደ ርገው ጥረት ነው ።

"ከእንግዲህ የኑሮአችን መሻሻል የሚወሰ ነው እያንዳንዳችን በተሠማራንበት የሥራ መስክ የምርት ውጤታችንን ለማሳደግ በም ናደርገው ጥረት ነው ።

"ከእንግዲህ ከድህነት ፣ ከበሽታና ከመሀይ ምነት ነፃ የሆነ ፣ የበለጸገና ዲሞክራሲያዊ የሆነ ህብረተሰብ መገንባታችን የሚወሰነው ራሳች ንንና አካባቢያችንን ለመለወጥ በምናደርገው ጥረት ነው ።

"ለዚህ አዲስ ሕይወት ግንባታ መታገል ፣ ለዚህ የላቀ ዕድገት ደረጃ መሥዋዕት መሆን የእያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ የዜግነት ኃላፊነት ነው ። " [30]

• 'አብያተ ክርስቲያናትንና ፋብሪካዎችን የም

---

[30] ከላይ ከተጠቀሰው ፣ (አረፍተ ነገሮቹ ሀዳግ እየለቀቁ ቢገቱም በአ ንድ አንቀፅነት መቆማቸውን አስተውል ።)



ንሠራ እኛ ሕዝቦች ነን ። ሠንመለቶችን እቆላ ልፈን የምንሠራና ብረት አፍስሰን መክሊት የምንቀጠቅጥ እኛ ሕዝቦች ነን ! ከዕለተ- ልደት እስከ ዕለተ-ሞት ላለው ጊዜ ሰውን ሁሉ የምንመግብና ሕያው አድርገንም የምናቆይ ሕያዋን ኃይሎች እኛ ነን !. . . ምንግዜም ፣ እና በየትኛውም ቦታ ቢሆን ሥራን ለመሥራት ሲሆን የመጀመሪያዎቹ የምንሆን ፤ ማናቸውንም ዓይነት የድኅማ ድጋፍ ለማግኘት ግን የመጨረ ሻዎቹ የምንሆን እኛ ነን ። ለመሆኑ ለእኛ ደንታ ያለው ማነው ? ቅንጣት ታህል በጎ ነገርን ለእኛ ያደረገልንስ ማነው ? የቀረው ቀርቶ ከሰው እንኳን የሚቆጥረን ይገኛልን ?. . . " [31]

• '. . . አሥር ዓመት ልጅ በነበርኩበት ጊዜ ፀሀይን በብርጭቆ ውስጥ አጥምጄ ለመያዝ እምችል መሰሎኝ . . . ብርጭቆየን ያዝኩኝና ተደብቄ የፀሀይ ጨረር ወዳለበት ቦታ ስሮጥ ከግድግዳ ጋር ተጋጭቼ ወደቅሁኝ ። የብርጭቆው ስብርባሪም እጄን ቆረጠኝ ። ከዚህም በስተ ቀር ከፉኛ ተደበደብኩኝ ። ከተደበደብኩኝ በኋላ ወደ አትክልት ቦታ ዞር ብዬ ሄድኩኝ ። እዚያም ሁኜ ውሀ ያዘለ ቦታ ላይ የፀሐይን መልክ ተንፀባርቆ አየሁኝ. . . ስረግጠው ውሀው ውስጥ በመንቦራጨቅ ልብሴ በጭቃና በውሀ

---

[31] ማክሲም ጎርኪይ ፣ 'እናት' ትርጉም ፣ በግዕዛን የማነ (ሞስኮ 1983 እ.ኤ.አ) ፣ ገፅ 128—129 ።

ወስ ፡፡ ወላጆቼ እንደገና ደበደቡኝ ፡፡ ስለዚህም ምላሴን ፀሐይዋ ላይ በስድብ አወጣሁና…"[32]

## (ሸ) በማወዳደር

**አስረጅ ፤**

'… ገበሬ አለበት ቦታ ላይ በእግሩ ተደላድሎ የሚቆም ነው ፡፡ ምንም እንኳን የቆመባት መሬት የርሱ ባትሆንም እላይዋ ላይ መቆሙ ይሰማዋል ! የመሬት ምንነት ለስሜቱ ይታወቀዋል ፡፡ የፋብሪካ ሠራተኛ ግን እንደ ወፍ ነው ፡፡ እኔ የበቀልኩበት ነው የሚለው የራሱ መሬት የለውም ፡፡ የራሱ ቤት የለውም ፡፡ ዛሬ እዚህ ቢገኝ ፣ ነገ ይኸንን የነበረበረትን የሥራ ቦታ ለቅቆ ይሄዳል ! ሴት እንኳን ከአንድ ቦታ ላይ ይዛ አታቆየውም ፡፡ አንድ ነገር ተዛብቶ ቢገኝ ያንን የነበረበትን ቦታ ሲለቅቅ እርሷንም ትቷት ይሄዳል ! የተሻለ ፍለጋ ከቦታ-ቦታ ይናውዛል ፡፡ ገበሬ ግን ከወዲያ ወዲህ ሳይባክን የኑሮ ሁኔታው የተሻሻለ እንዲሆንለት እዚያው ባለበት ረግቶ ይጥራል … "[33]

## (ቀ) ምርጫን በማጣበብ—አማራጮችን በማንጓለል

**አስረጅ ፤**

'…እናት እንዚህን ከመሳሰሉት መዝሙሮች

[32] ከላይ ከተጠቀሰው ፣ ገፅ 288—289 ፡፡
[33] ከላይ ከተጠቀሰው ፤ ገፅ 274—5 ፡፡



መካከል በአንዱ መዝሙር በተለይ ተመስጣለች ፡፡ ይህ መዝሙር በተጠራጣሪነትና ሙሉ በሙሉ እርግጠኛ ባለመሆን መንፈስ መውጫ መግቢያው ከማይታወቅ ቦታ የምትገኝ የተንሳቆለች ነፍስ የምታሰማውን ዓይነት ድምፅ የሚያሰማ ዜማ አልነበረም ፡፡ ወይንም ደግሞ በእጦት የተንሳቆሉ ፣ በፍርሃት አዘቅት የተዋጡ ፣ ማንነታቸውና ሰብዓዊ ክብራቸው የተረገጠባቸው ሰዎች የሚያቀርቡትን እሮሮ የሚያንጸባርቅ አልነበረም ፡፡ የጭፍን የዳሰሳ እየርን ለመጨበጥ በሃዘንና በትካዜ ሁኖ እህህ በሚል እንጉርጉሮ አንድ ኃይል እንደሚያሰማው ዜማ ዓይነትም አልነበረም ፡፡ አንዱን ከሌላው ብይ ለይ በበጎውም በክፉውም ጉዳይ ላይ ተወርዋሮ ጉብ ሲልበት የሚሻ የእግጉል ደፋርነት ምልክትም አልነበረም ፡፡ በቂም በቀል መንፈስ ተነሳስቶ ቀደም ካለ ጊዜ ጀምሮ የነበረውን ለማፈራረስ እንጂ ለመገንባት የማይቻለው መሆኑን የሚያሳይ ስሜት … አይገኝበትም … መዝሙሩ … ሰውን በሐሳብ ማዕበል የሚያጥለቀልቅ ፣ አንድ ስሜትን ቀስቃሽ የሆነ አንዳች ኃይል በውስጡ ይዞ … '[34]

'የመታመም ትርጉሙ ብዙ ነው ፤ ባልጋ ቁራኛ በደዌ ዳኛ ተይዞ መተኛት በሽታ ነው ፡፡ በጦርና በጎራዴ ፣ በጥይትና በቦምብ መመታትና መቁሰል በሽታ ነው ፡፡ ከዚህም ሌላ ሰው እንዲያው አይሞትምና በትንታና በህቅታ

[34] ከላይ ከተጠቀሰው ፣ ገጽ 79—80 ፡፡

ቃመው ተብሎ እግዚአብሄር ይማርህ ሳይባል ድንገታዊ ሞት በለሚያገኘው ለመጠሪያ ከተ ላከበት በሽታ ሊፈወስ አይችልም ። ነገር ግን ፣ ይህ አይነት አጠራር የተለምዶ ስለሆነ አፅመ ርስት ነውና ፍጡር ሊያስተባቃው አይገባም ። ክፉ በሽታ ግን ከአለበት አለ ፤ በራተኛ ለመ ምሰል ከመስሪያ ቤት ገብቶ መዉጣት መድ ሃኒት የሌለው በሽታ ነው ። ስራ ሰርተው ስማ ቸውን በአለም እንዳስጠሩትና ሀገራቸውን በከፍተኛ ክብር ላይ እንደ መሰረቱት እንደስመ ጥሩዎቹና እንደ ታሪክ መልካሞቹ ሰዎች ፣ ስራ እንዳይሰራ ስንፍና የልብ ውጋትና የራስ ምታት ሆኖበት በስራ ምድር ዞላ የሚውልና እንቅልፍ የሚገረዝዘው ፣ በነፍሱም በስጋውም የማይፈወስ በሽተኛ ነው . . . ክፉ በሆነ በወባ በሽታ የተ ነደፈ ፣ በሆዱ ወባ ያረግዘና ዘለአለም ሲንቀ ጠቀጥ ይኖራል ፤ እንዲሁም በስንፍና የተጠ መደ ፣ ስንፍና በሆዱ እንቁላሉን ስለሚጥል በት . . . ታሞ አይድንም . . . ”[35]

## (ለ) ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር

(1) መቼም ሶስተኛው ጌታዬ የሚያደርጉኝ ድርጊት አይጣል ነው ። ያም መጣ ያም መጣ መዋስ ነው ። ከኩሊ ኩሊ መተላለፍ ሆኖአል ስራዬ ። በቤንዚን መጠረጊ ቀርቶ በውሃ መን ጨፍጨፍ ሆኗል እድሌ ። ያውስ ከየት ተገ

35 ዳኛቸው ወርቁ ፣ 'የኪነ-ፅሁፍ ስልት መለማመጃ' — ያልታተመ ፣ (አ.አ. ዩኒቨርስቲ 1963. እ.ኢ.አ.) ፣ ገፅ 64 ።



ኘቶ ማን አስቦት ። ቀን ልብስ ነኝ ፣ ማታ ትራስ ነኝ ። የዱቄት ፣ የኖራ ፣ የጭቃና የምናምን መሸከሚያ መደላድል ነኝ ። እጄ የንፍጥና የላብ መጥረጊያ መሀረብ ሆኗል ። መልኬ ኑግ ከሚ መስል ጥቁርነቱ ወደ ቡላነት ተለውጧል ። ከስድስቱ የእጅ ቁልፎቼ ውስጥ በስተግራዬ ያለው አንዱ ብቻ ቀርቷል ። እሱም ያለው በአንድ ዘለላ ክር አማካይነት ብቻ ተንጠል ጥሎ ነው ። ክንዴ ተቀድዶ በጥቁር ካኪ እራፊ ተለጥፏል ። በኪሴ ዳር ዳር እንጀቴ ከመጉልጉሉም በላይ ፣ ቆሎ ለመዝገን አሁ ንም አሁንም በሚወጡትና በሚገቡት ልኬ ለሽ የኩሊ እጆች ምክንያት ከውስጥ በግራም በቀኝም ተሸንቁሬአለሁ ። የኮሊታዬማ አይ ወራ ፣ ጭቅቅቱ ተለድፎ በቡጥሜ የሚዛቅ ይመስላል ። ኑሮዬ በጣም ያሳዝናል ። የሰው ልጅ ተወልዶ አፉን ለመፍታት በማይችልበት በሁለት ዓመታት ጊዜ ውስዋ ከአዲስ ኮትነት አሮጌ ሆንኩ ። ኧረ ስንቱን ላውራው ? [36]

(አ. ሰይፉ ዘውዱ)

(2) «ለቦታው የውበት ፈርጥ ሆናዋለች ። አቋቋሟ ልዩ መልክ አለው ። ሰውነቷም ፍጹም መዝናናት ይታይበታል ። በቀኝ እጅዋ ያልተቀ ጠፈች ጽጌረዳ ይዛለች ፣ በዛፉም ከለላነት በረ ቂቅ ውበቷ ታደባለች ። ግራዋን እጅዋን ሀረጉ ሽንጧ ላይ አሳርፈዋለች ፤ በቀኝ እግርዋ መሬ

36_37 ከላይ ከተጠቀሰው ፣ ገፅ 69 ።

ቱን ጠበቅ አድርጋ ረግጣዋለች ፣ ግራ እግ ሯን አዝናንታዋለች ። ፊቷን በስያፍ መልሳ አንድ ነገር ትመለከታለች ፣ የሚታየውም ለእርሷው ብቻ ነው ። አስተያየትዋ ረቂቅ ጥልቅ ፣ ሩቅና ስሬ ነው ። ፈለጉን ለማግኘት በጣም ያስቸግራል ። » [37]

(ሸ. ብ.)

(ተ) <u>ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ</u>

<u>አስረጅ</u> ፤

(1) "ይጫወቱ እንጂ ጋሼ" ስትለኝ ከሀሳቤ በ ድንጋጤ ተመለስኩኝ ። እሷንም ማሽኮርመም ጀመርኩ ። ስትስቅ የጥርሶቿ አገላለጥ ፣ በግራ በኩል የአይኗ መርዘኛ አስተያየት ፣ ኮምጨጭ ስትል የግንባሯ አኮማታተር ፣ ለጥሪ ስትመ ልስ አይኗን ከብለል አድርጋ በለስላሳ ድምፅ "አቤት" ማለት ፣ በነገር ካልተስማማች የአንገ ቷን ማወዛወዝ፣ሰውነቷን ሲዳስሷት የከንፈሯን መምጠጥና የሰውነቷ መጋል ፣ ስትሄድ የሰው ነቷ መወዝወዝና መረግረግ ልክ የአመለወር ቅን ስለ አስታወሰኝ ልጅቷን ወደድኳት ። » [38]

(ተማሪ)

(2) «ፀዳል ሀብቷ የተፈጥሮ ውበቷ ብቻ ነው ። ጫማ የላትም እግሯ ግን እንሶስላ የሞቀች ይመ ስላል ፤ ተረከዟ ከሎሚ ያምራል ። ፀጉሯ ሽቶና

[38], [39] ከላይ ከተጠቀሰው ገፅ 70—71 ።



ዘይት አያውቅም ፤ በዕሙና ለመታጠብ እንኳ ዕድል አላገኘም ፤ ሆኖም እየተዘናፈለ ወር ዷል፤ የተከበረውን ትከሻዋን እጥለቅልቆታል። ጫፉም <u>ሀረጉን ሽንጧን</u> አልፎታል ፤ ዘለላ ዊንቱ መላልሶ ያጠፉት ይመስላል ። ዐይኖቿ ኩል አያውቁም ፤ ነገር ግን እንደ ንጋት ኮከብ ያበራሉ ። ጥርሶቿም ብርሃን ያስተጋ ባሉ ፤ የሚፋቁትም ዐልፎ ዐልፎ ነው ። ጥፍ ሮችዋ ቀለም አላዩም ፤ ሆኖም <u>ውበታቸው ዕፁብ ድንቅ ነው</u> ። ድህነትና ውበት በአንድ አካል ላይ እንደዚህ ያለ ፍፁም ህብረት ሲኖ ራቸው በፀዳል ላይ ብቻ ማየቴ ነው . . . » [39]

(ሽ. ብ.)

## 4.2.6 <u>የርዝማኔ ስልት</u>

የአንቀፅን ርዝማኔ ከዚህ አይነስ ፣ ከዚህ አይብዛ ብሎ መወሰን ያዳግታል ። አንዳንዱ ሀሳብ በጥቂት መስመሮች መቋጫ ያገኛል ። ሌላው አያሌ ማብራሪያና ማስረጃ ያስ ፈልገዋል ። ስለሆነም ለመንደርደሪያ ያህል አንዳንድ ነጥቦችን ማጤን ያስፈልጋል፤በጣም ረጃጅም ወይም በጣም አጫጭር በሆኑ አንቀፆች አለ መጠቀሙ ይበጃል ። በጣም ረጃጅም አንቀፆች የሀሳብ አንድነትና ዝምድና ያጣሉ ፤

('ሀረጉን ሽንጧን' የሚለው ሀረግ ምስል የማይከስት ተምሳሊት 'ውበ ታቸው ዕፁብ ድንቅ ነው' የሚለው ደግሞ የረቂቅ ባህሪያት መጠሪያዎች ሰብሰብ እንደሆን አስተውል ፤ ሁለቱም የአንቀፁን ግልፅነት ያዳክሙታል።)

በተለይ በጀማሪዎች ፅሁፍ ውስጥ — የተንጠለጠሉ ሀሳ
ቦችና ያልተዛዘሉ ሀረጎች የመሳሰሉት ይበዙባቸዋል ።
በስሜት ፈንጣቂነት ረገድም ረጃጅም አንቀፆች ታሪክን
ይጎትታሉ ፤ ስሜትን ያፍናሉ ፤ የፅሁፍን ይዘት ይደብ
ቃሉ — ለእነዚህ ተግባራት ታስበው እስካልዋሉ ድረስ
ጠቀሜታ የላቸውም ። በጣም አጫጭር በሆኑ አንቀፆችም
ረገድ የሚታየው ሁኔታ ከዚህ አይሻልም። በጣም አጫጭር
አንቀፆች ውስጥ የድርጊያ ፍጥነት ባይኖር ያለ ይመስ
ላል ። ሀሳብና ድርጊያ ይቆራረጣል ። ሊገለፅ የታሰበው
ስሜት የሚደብት አይነት ወይም ሌላ ርዝማኔን የሚጠይቅ
ሁኔታ ሊሆን ሲገባው የረፍትን ፣ የመዝናናትንና የተግታን
መንፈስ ያሳድራል — ለእነዚህ ተግባራት ተብለው እስ
ካልዋሉ ድረስ አጫጭር አንቀፆች ፋይዳ የላቸውም ።

አልፎ አልፎ ፣ በተለይ በጋዜጦችና በዲስኩሮች ውስጥ ፣
(ከገፅ 158—159 እና ገፅ 160—162 ተመልከት ።) የአንቀፅ ርዝማኔን
ስልት የሚሽሩ የሚመስሉ አቀራረቦች ይታያሉ ፤
በአንዳንድ አንቀፅ ሊሰባሰቡ የሚገባቸው አረፍተ ነገ
ሮች ሁዳግ እየተከፈተላቸው ለየብቻቸው ተበታትነው ።
ይኸን አይነቶች የየራሳቸው ምክንያት —(1) ፍሬ ነገር
ችን በጥድፊያ ለማሳየት (2) አቢይ ሀሳቦችን አጠናክሮ
ለማስገንዘብ (3) የአቀራረብ ተግታ ለመስጠት — ስለሚ
ኖራቸው ሊያደናግሩን አይገባም ። መሰረታዊ ዘዴዎቹን
መጠበቁ ይበጃል ።

ስለዚህ ፣ በተለይ ጀማሪ ፀሀፊዎች ፣ በጣም አጫጭር
(ከ4—5 መስመር) በሆኑና ፣ አንዳንድ አረፍተ ነገር በሆኑ
አንቀፆች (የጭውውት አንቀፆችን ሳይጨምር) እና በጣም
ረጃጅም በሆኑ (ግማሽ ገፅና ከዚያም በላይ) አንቀፆች ባይ
ጠቀሙ ይመረጣል ።



ምእራፍ አምስት

# የአደራረስ አይነቶች

## 5.1 መግለጫ

ለኪነ-ፅሁፍም ሆነ ለሳይንስና ፍልስፍና የሚሰራባቸው
አበይት የሀሳብና የተግባር ማሰባሰቢያ አይነቶች ፣ በቃልም
ሆነ በፅሁፍ ፣ አራት ሲሆኑ ፣ እነሱም ተራኪ ፣ ስእላዊ
(መስተዋታዊ) ገላጭ እና አመዛዛኝ ናቸው ፤ የጭውውት
ድርሰትን እንደ አምስተኛ ካልወሰድን በስተቀር ። እያን
ዳንዳቸው የሚያተኩሩበት የተለየ ጠቀሜታ ስላላቸው
የሚለያዩበትንና የሚዛመዱበትን በሚገባ ማስተዋል ያስ
ፈልጋል ። በተለይ ሰፊና ረጅም ፅሁፎችን ለመፃፍ ከመ
ጀመራችን በፊት እነዚህን ያደራረስ አይነቶች ባጭሩ
ፅሁፎች አማካይነት መለማመድ ይኖርብናል ። ልምዱን
ማግኘታችንን እርግጠኛ እስክንሆን ድረስ ።

ከዚህ በታች ማብራሪያና ማስረጃ እናቀርባለን ።

## 5.2 አጫጭር የድርሰት አይነቶች

### 5.2.1 አጭር ተራኪ ድርሰት

ስሙ እንደሚያመለክተው ፣ ተራኪ ድርሰት ሁናቴ
ንና ድርጊያን (ወይም ሰንሰላታዊ ሁነታዎችን) እንዲህ
እንዲህ ሆነ ወይም እንዲህ እንዲህ ተደረገ በማለት ማው
ጊያ ወይም መተረኪያ ነው ። ታሪክ'ራሱ አዉሪው ወይም

ተራኪው የደረሰበት ፣ በልምድ ያገኘው ፣ በሀሳቡ ያውጠነጠነው ወይም ከሌላ ሰምቶ የሚያስታውሰውን ያሀል አሳጥሮ ወይም አስፋፍቶ ለሌሎች የሚደግመው ፣ የሚያቀርበው ሊሆን ይችላል ።

እንደ ማንኛዎቹም ሌሎች የሀሳብ እና/ወይም ስሜት ማሰባሰቢያ ፅሁፎች ፣ የትረካ ፅሁፍም በትንሹ ጀምሮ ነው እያደገ የሚሄደው ፤ ቃላት ወደ ሀረግነት ፣ ሀረጐች ወደ አረፍተ ነገር ፣ አረፍተ ነገር ወደ አንቀፅ ፣ ከዚያም አንቀፆች እየተሰባሰቡ ልዩ ልዩ የድርሰት አይነቶችን በማስገኘት ። እንደ ማንኛዎቹም ሌሎች የሀሳብ እና/ወይም ስሜት ማሰባሰቢያ ፅሁፎች ስንል ደግሞ ፣ በተለይ ስእላዊ (መስተዋታዊ) ገላጭና አመዛዛኝ ፅሁፎችን ማለታችን ነው ።

እነዚህ አራት አበይት የፅሁፍ አቀራረቦች የሚለያዩት በአቀራረብ ብቻ ሳይሆን በግባቸውም ነው ። እያንዳንዳቸው (አንዳንዴ አንዱ የሌላዉን ወይም የሌሎቹን ግብ ደርቦ ቢገኝም) የየራሳቸው የሆነ አላማና ግብ አላቸው ። በዚህ ረገድ የትረካ ፅሁፍን ግብ እንመለከታለን ።

የተራኪ ፅሁፍ አላማ ምንድነው ?

የተራኪ ፅሁፍ አላማ በተከታታይ ድርጊያዎችና ገፀ ባህርያት አማካይነት ለሰዋዊ ልምድ ትርጉም ማስገኘት ነው ፤ (እንዲህ እንዲህ ተኖረ) ወይም (እየተኖረ ነው) በሚል አይነት አቀራረብ ፣ በተወሰነ የጊዜ ቅደም ተከተል ፣ በተወሰነ የድርጊያ ማቅረቢያ ፍጥነት ። የተራኪ ፅሁፍ አላማ የአንባቢን ወይም የትረካ አዳማጭን ፍላጐት በማነሳሳት ፣ አውቆትም ይሁን ሳያውቀው ፣ አስፈልጐት ለነበረው ሀሳብ እና /ወይም ስሜት ርካታ ማስገኘት ነው ፤ እየነካካ ፣ እየኮረኮረ ፣ እያሳሳቀ ፣ እያሳዘነ እና



የመሰከሩትን ስሜቶች እየቀሰቀሰ ። አንባቢዉ ወይም ትረካ አዳማጩ ከራሱ ውሱን ልምድ ውጪ የሌሎችን ሰዎች ልምድ ተካፋይ እንዲሆን ፣ ለጊዜውም ቢሆን እራሱን እረስቶ የሌሎችን ህይወት እንዲኖር እያደረገ ።

ተራኪ ፅሁፍ ሎቢቻው ቢሰራበትም ፣ በአብዛኛው ስእላዊን (መስተዋታዊ የሆነ አቀራረብን) ጨምሮና ተዛምዶ ይገኛል ። አይነቶቹም ሁለት ናቸው ፤ እውናዊ ተራኪና ልቦለዳዊ ተራኪ ።

(ሀ) <u>እውናዊ ተራኪ</u>

ተከታታይ ሁናቴንና ድርጊያን ወይም ተከታታይ ሁነታዎችን (ድርጊያዎችን) የሚዘረዝር ፣ በአብዛኛው እደራደሩ የተለመደ የጊዜን ቅደም ተከተል (ተከታታይ ሰአትን ፣ ቀንን ፣ ሳምንትን ፣ ወርን ፣ አመትን ወዘተርፈ...) የሚከተል የአፃፃፍ አይነት ነው ። አልፎ አልፎ በጋዜጣዎች የሚወጣው ስለ መኪና አደጋ ፣ ስለ ሀገር ጉብኝት ፣ ስለ በአል ቀን እና እንዲሁም ማንኛውም የህዝቦች ታሪክ እና የመሳሰለው ሁሉ የዚሁ ዘርፍ ነው ።

የዚህ አይነት ትረካ ስነ ፅሁፍነቱ ባይከድም ፣ አንባቢን እያባበለ ስቦ የሌሎችን ህይወት የማስኖር ሀይሉ ያነሰ ነው ። ተፈላጊነቱም እውቀትን ለማዳበር እንጂ ፣ ለጊዜውም ቢሆን የሌሎችን ልምድ ለማስኖር አይደለም ።

<u>አስረጅ ፤</u>

• "ዕለቱ ሰኞ፣ጊዜው ማለዳ ነበር ። ከተለመደው ሰላምታ በኋላ ፣ "ደጉ (እኔን መሆኑ ነው) ፣

ሐረር ደረሰው” በማለት መምህሬ ሲናገሩ የሰ
ማችው እማዬ ፥ ምንም አስተያየት ከመስጠት
ተቆጠበች ። እኔ ግን ደስ አለኝ ። የአዲስ አበባ
ዘማቾች ብዙዎቹ ወሎና ሐረር ይሄዳሉ የሚል
ወሬ አስቀድሜም ሰምቼ ስለ ነበር ጉዳዩ እን
ግዳ አልሆነብኝም ። እንዲያውም እመኘው
የነበረው ተፈፀመ ። አባቴ ወራሪ ጠላትን
ሊያጠቃ በተሰማራበት የሐረርጌ ክፍለ ሀገር
ምድር ፥ እኔም ሌላውን ጠላት ፥ ማይምነትን ፥
ለመውጋት ልሰማራበት ሆነ ። ያስደሰተኝም
ይኸው ነው ።

ባለፉት ብዙ ዘመናት ሊወሩን የመጡ ጠላቶ
ቻችንን በጦር በጉራዴ ያባረሩ የቀደምት አባ
ቶቻችንን ክንድ ሳይቀምስ የኖረ ጠላት ቢኖር
ማይምነት ነው ። ማይምነት ለሀገራችን ኋላ
ቀርነት አንዱ ምክንያት ነው ። ለዚህም ነው ፥
አብዮታችን በዚህ ጠላታችን ላይ ያተኮረበ
ትና ዘመቻም ያወጀበት ። እኔም በዚህ የሰፊው
ህዝብ ጠላት ላይ መዝመቴን ፥ ከአባቴ ታላቅ
ዘመቻ ነጥዬ አላየውም ። በዚህም የአባቴን
ፈለግ ተከተልኩ ፥ የሕዝብ ወገንነቴንም ለማ
ስመስከር ምቹ አጋጣሚ አገኘሁ በማለት
ተደሰትኩ ።

እናቴም ከማይምነት የተላቀቀችው በቅርቡ
በመሆኑ በማይምነት ያሳለፈችው መራራ ሕይ
ወት ትዝታው ከሕሊናዋ ገና አልጠፋም ።
ማይም ወገኖቻችንን ላስተምር ነው የምዘ
ምተው ፥ ይህም የዜግነት መብትና ግዴታዬ
ነው ስላት እራሷን በማነቃነቅ መስማማቷን



ገለፀችልኝ ። ከፊት ለፊት ካለው ሳጥን ላይ
ተቀምጣም ፥ 'እየሀ ልጄ' አለችኝ ። የናት
ምክሯን ልትሰጠኝ ፥ 'እየሀ ልጄ ፤ በዚህ ሦስት
ዓመት ውስጥ በመማሬ ብዙ ነገር ዐውቄያ
ለሁ ፤ ስታስተምር ተማሪዎችህን አክብር ፤
እነርሱንም መስለህ ቅረባቸው ፤ መልስ ሲሰ
ጡህ ቢሳሳቱ አትቆጣቸው ፤ ያጣመሙትን
አቃንተህ በመንገር ፥ (ጥሩ ነው ይበርቱ) ብለህ
አበረታታቸው ። እኛን ከሚያስተምሩት መካ
ከል ጥሩ የምንላቸው መምህራን እንደነዚህ
ዓይነቶችን ነው ። አንተም እንደነርሱ ሁን
ልጄ' አለችኝ ። እማዬ እውነትም የተማረችው
ፊደል ብቻ አይደለም አልኩኝ ። ምክሯንም
ተቀበልኩኝ ። 'አንድ መምህር ሲያስተምር ፥
በተማሪነት ጊዜው ካስተማሩት መምህራን
በጥሩነት የሚያደንቀውን መምህር መስሎ ለመ
ቅረብ ቢሞክር ይጠቅመዋል' ያለኝን የት
ምህርት ሙያተኛ አባባል አስታውሼ እማ
ዬን አደነቅኋት ።

በማግሥቱ ለዘጠነኛው ዙር ዘማቾች በተደረገ
ልን አሸኛኘት እማዬም እዚያው እስታዲየም
ነበረች ። ያለቻትን ገንዘብ በኪሴ ከተተችልኝ ።
የናት ሆድ ሆነና ነው እንጂ በዋዜማው ምሽት
ጭውውታችን ፥ የምንሄድለት ገበሬ እንዳለፈው
ሁሉ ፥ ለኛም ስለሚያደርግልን ከፍተኛ እንክብ
ካቤ ሁሉ ፥ ስገልፅላት አምሽቼ ነበር ።

እማዬን ተለየኋት ። የዘማች ሙሉ ልብሴን
ለብሼ እጄን በማውለብለብ እርሷንና ጉረቤቶ
ቻችንን እንዲሁም ሌላውን ሸኚ ተሰናበትኩ ።

'በደህና ተመለሱ' የሚለው ድምፅ ተሰብ ጋባ ። ጉዞ በአውቶቡስ ቀጀመረ ። የትም ህርትም ሆነ የእድሜ እኩዮቹ ከጐኔ አሉ ። ያለፈው ከናት ያለመለየት ፍላጐቴ በያዝኩት ከፍተኛ አላማ ተሸፈነ ። እኔም አድጌ የሚ ፈለግብኝን የናት ሀገር ውለታ ለመክፈል መብ ቃቴ እራሴን እንደ ትልቅ ሰው እንድመለ ከት አደረገኝ ።

አይቼው የማላውቀውን የሀገሬን ውበት እየ ቃኘሁና ከጓደኞቼ ጋር እየተጫወትኩ ፣ ርቀቱ ሳይታወቀኝ የወበራ አውራጃ ከተማ ወደ ሆነችው ደደር ደረስን ። ወደ ተዘጋጀልን የማ ረፊያ ቤትም ሄድን ። ተገቢው መስተንግዶ ተደረገልን ። ወደየአካባቢው ከተሰማራን በኋላ፣ ስለሚያጋጥሙኝ ሁኔታዎች በደብዳቤ ልገልፅ ላችሁ እሞክራለሁ ...» [1]

ዘማች ደጉ ታደሰ

. "አንድ አሑድ ከኳስ ሜዳ መልስ የተሳፈር ኩባት ታክሲ ፣ 'ሲጋራ ማጨስ አይፈቀድም' የሚለውን ማሳሰቢያ ለጥፋለች ። ታክሲዋን የሚያሽከረክረው ሹፌር ከጥቂት ጉዞ በኋላ ሲጋራ ማቀጣጠል ይጀምራል ። ከተሳፈ ርነውም መካከል አመል ያለበት ኑሮ ሲጋራ አውጥቶ ነጂውን እንዲለኩስለት ይጠይቀ ዋል ። ባለታክሲውም ሲጋራውን ሁለት ጊዜ ከሳበ በኋላ ጽሁፉን ተመልከተሃል የሚል ጥያቄ ያቀርባል ። ሁላችንም እርስ በርስ ተያየን፤

1 'ሠርቶአደር' ፣ ቅፅ 4 ቁ. 140 ፣ መጋቢት 29/75 ።



ሲጋራ እንዲለኩስለት የፈለገውም ተሳፋሪ ፣ 'ታዲያ ማሳሰቢያው አንተን አይመለከትም?' ቢለው ፣ ግዴታው 'የተሳፋሪዎች ብቻ ነው' የሚል መልስ ከሹፌሩ ይሰማል ። የአሽከር ካሪው አባባል ሰፈዝ የመሰለው ተሳፋሪም ፣ 'ለፈገግታ የሰነዘርካትን ቀልድ ተውና ሲጋ ራውን አቀጣጥልልኝ' ይለዋል ። መሪውን የጨበጠው ሹፌር ግራና ቀኙን ተመልክቶ ፣ 'የሲጋራ አመል ያለበት እንኳንስ አጠገቡ አጭሰውበት ቀርቶ ውል ሲለው እንዴት እንደሚያቅበዘብዘው አውቀዋለሁ ። ሱሰኞችም አለ መጨካከናቸውን የሚያውቁት የአዲስ ከተማ ልጆች ፣ 'የሲጋራ አጫሾችን ፍቅር ይስ ጥህ ይባባላሉ ፣ ሲተራረቡ' በማለት ያቀጣጠ ላትን ሲጋራ እንዲለኩስባት ሰጠው ።

ከተሳፈርነው መካከል ለተደረገው የቃል ልው ውጥ ለጊዜው ጣልቃ ባንገባም ፣ የዚች ፅሁፍ ባለቤት ግን ፣ ነጂውን 'የለጠፍከው ፅሁፍ ሲጋራ ማጨስ አይፈቅድም ። ማስገንዘቢያ ውን በቅድሚያ በስራ መተርጎም ያለበት ለጣፊው ነው ። ድርጊትህና ማሳሰቢያው ያል ተገናኙት ለምንድነው ?' በማለት ጠየኩት ። ሹፌሩ፣ 'ነገርን ነገር ያነሳዋልና ፣ ይህች ታክሲ የጓደኛዬ እንጂ የእኔ አይደለችም ። የኔዋ ታክሲ "ሲጋራ ማጨስ አይፈቀድም" የሚል ማሳሰ ቢያ የላትም ። ምክንያቱም ማሳሰቢያው ከእኔ የሲጋራ ሱስ ጋር አብሮ አይሄድም' በማለት ነገሩን ደመደመው ።' [2] (ሽፈራው ዘውዱ)

2 'ሠርቶአደር' ቅጽ 4 ቁ. 137 ፣ መጋቢት 15/75 ።

(ለ) <u>ልቦለዳዊ ትረካ</u>

በአብዛኛው ታሪኩ የሚካሄድበት የጊዜ ገደብ እንደ ትረካው ማሻቀቢያና መዓፊያ ፣ ማስባሰ ቢያና መቋጠሪያ ወይም እንደ ተፈለገው የትረካ ውጤት አይነት (የእያንዳንዱ ሁናቴ ወይም ድርጊያ መንተክተኪያና መስከኛ ቀለበት (ቅጥብ) እንደሚያስፈልገው የጊዜ ሂደት) በቅድሚያ ታስቦበት እየተመቻቸ የሚቀርብ ነው ። ሁነታዎች (ድርጊያዎች) የሚቀነባበሩትም ፣ እንዲሁ ትረካው ሊያስገኘው እንደ ተፈለገው ውጤት አይነት በኪናዊ አቅድና መመሪያ መሰረትነት ነው ።

<u>አስረጅ 1</u>

(1) <u>በነጠላ ሁናቴ ወይም ድርጊት ላይ የተመሰረተ</u>

<u>'አንድ ብቡ ፈሪ'</u>

- «አንድ ፈሪ ወታደር ትልቅ ጦርነት ሁኖ ባለ አብረውት የተሰለፉት ባልንጀሮቹ ደረታቸውን ባረር እየተሰነደቡ አንዱ ባንዱ ላይ እየተደራረቡ ሲወድቁና ሲሞቱ አየና ሆዱ ተሸበረበት ፣ ጉልበቱም ቁጠማ ሆነበት ። በዚአው ስፍራ ተሬሳ በቀር የሚአውቀው ሰው አልነበረም ። ጦርነቱ ግን ይልቁንም እሱ ባለበቱ በኩል እያደረ በጣም እየተፋፋመና እየተጋጋለ መጣ ። በዚህን ጊዜ መክቶም እንዳይችል እሩጦም እንዳያመልጥ ባየው ጊዜ ሌላም ነገር የሚአድነኝ የለ ከዚህ በቀር አለና ተሬሶቹ መካከል ፈነቃቅሎ ገብቶ አንዱን እሬሳ በላዩ ጭኖ ትንፋሹን አሳጥሮ ተቀመጠ ።



የወዲአኛውም የወዲህኛው በሾተል እየተጠማዘዘ በፎቁ እየተንመደ እያወካ እየተዋካ እየተተራመሰ በዚአው ከተሸሸገበት ቦታ በደረሰ ጊዜ የፈረሰ አንዳ ታሁን አሁን ያደባየኛል ሲል እግሩን በጣም ለመሸሸግ እጥፍ ሲአደርግ አንድ ፈረሰኛ አየውና ተፈረሱ ላይ እንደሆነ የዚህን ሳይቆስል የሞተ ሰው እግር በቀጭን ጦሩ ጠቆም ጠቆም እያደረገ ይሄስ የሞተም አይመስል አለ ። በዚህ ጊዜ ያ በውሸት የሞተ ፈሪ ፣ አይ ! አይ ! እያለና እግሩን እያፈራገጠ ፣ እሻ ተወኝ ሙቻለሁ ! ብሎ አፉን በጁ ተመተመ ። »*

(2) <u>በተከታታይ ሁናቴ ወይም ድርጊት ላይ የተመሰረተ</u>

(ሀ) <u>ስለ አንድ ሜማ ሰፊ</u>

«አንድ ሜማ ሰፊ ከጧት እስከ ማታ በእጁ ሜማ ሲሰፋ ባፉ ሲዘፍን ይውል ነበረ ። በጐረቤቱም አንድ ባለጠጋ ነበረና አንድ ቀን ወደ እርሱ መጥቶ ወዳጄ ሆይ ፤ እንዲህ ሌት ተቀን ስትደክም ባመት ምን ያህል ታተርፋለህ አለው ።

ሜማ ሰፊውም እየሳቀ መለሰ ። ጌታ ሆይ እኔ ያመት ትርፍን አላስብም ። ነገር ግን አሳቤ ሁሉ እጄ ወደ አፌ የሚያቀርበው የእለት ምግብ እንዳልቸገር ብቻ ነው አለው ።

ባንድ ቀን ምን ያህል ታተርፋለህ አለው ። ጌታዬ ሆይ አንድ ቀን ብዙ ፣ አንድ ቀን ጥቂት

* አፈወርቅ ገ/ኢየሱስ ፣ « የአማርኛ ቋንቋ ሰዋሰው » ( በኢጣሊያንኛ የተጻፈ )አ. አ. አ. 1905 ፣ ገጽ 267 ።

እሰራለሁ ፡ ትርፉ በምን ይታወቃል አለው ። ባለጠጋውም እንግዲህ እኔ ያለችግር እኖርሃለሁና ከኔ ዘንድ መቶ ምዝምዝ ወርቅ ውሰድና በጥንቃቄ ጠብቀህ እኑር ። በቸገረህም ጊዜ የሚበቃህን ያህል እንጂ በከንቱ አታባክን ብሎ ሰጠው ።

እርሱም ይህን ያህል ገንዘብ ባይኑ ስንኳ አይቶ አያውቅም ነበረና ደስ እያለው ተቀብሎ ወደ ቤት ሔደ ። ነገር ግን ይጠፋብኛል ብሎ ሲጨነቅ ሌሊቱን ሁሉ ካይኑ እንቅልፍ ሸሸ ። በሌሊትም የሰው ድምጽ በሰማ ጊዜ ገንዘቡን የሚቀማ ወምበዴ የመጣ ይመስለዋል ። ነፋስም ቤቱን ባንቃነቀው ጊዜ ገንዘቡን የሚሰርቅ ሌባ የመጣ እየመሰለው ይጨነቅ ጀመረ ። እንዲህም እየሆነ ብዙ ቀን ተቀመጠ ። ነገር ግን ልቡ የዚህን አሳብ የማይችለው ሆነ ። ከእለታት ባንድ ቀን እንዲህ ሲጨነቅ አደረና በማግሥቱ በማለዳ ተነሥቶ ወደዚያ ባለጠጋ ቤት እየሮጠ ሔዶ ለኔስ የቀድሞ ኑሮዬ እጅግ ይሻለኛል ። አሁንም የሰጠኸኝን መቶ ምዝምዝ ወርቅ ተቀበለኝ ። ቀን ሥሰራ እየዋለሁ ሌሊት እንቅልፍ ቢወስደኝ ለኔ እጅግ መልካም ነው ብሎ በትኖለት ሔደ ። »

(ለ) <u>ጀቡዴ</u>

«በአንዲት ቅንሽ መንደር አንድ በውሀ የሚሰራ ወፍጮ የነበረው ጀቡዴ የተባለ ሰው ነበረ ።

---

ኀሩይ ወ/ሥላሴ ፡ 'ስኳርና ወተት'(የልጆች ማሳደጊያ' አ.አ 1963) ገጽ 115።



በሉ ልክ በስታም እስከ ዛሬ አልተፈጠረም ። እገሌ ገንዘብ የተረፈው ጌታ ነው የተባለ እንደሆነ ፤ ውይ እሱን ነው እንዴ ፤ እሱንማ ከብዙ ጊዜ ጀምሮ የማውቀው የልብ ወዳጄ እኮ ነው ይላል ። ነገር ግን የአንድ ድሀ ሰው ስም ሲነሳ ፡ ሰውዬውን የሚያውቀው እንኳ ቢሆን ፡ ከዚያ በፊት ስሙን ያልሰማው መልኩን ያላየው ይመስላል ።

ጀቡዴ የጠገበ ጌታ ለመሆን በልቡ ይመኝ እንጂ ፡ ሀብታም ነበረ ለማለት አይቻልም ። እርግጥ ነው ፡ የዕለት እንጀራውን የሚያረጋግጥለት የወፍጮው ገቢ ነበረው ፤ ይህም ገቢው በምንም ምክንያት እንዲጐልበት እንዲጉላላበት አላደረገም ። ከመጠን በላይ ቆጣቢ ስለነበረ ፡ ከዚሁ መጠነኛ ገቢው ገንዘብ ማስቀመጥ ቻለ ። ፀልፎ ፀልፎ ሳጥኑን እየከፈተ ያከማቸውን በጥንቃቄ ከቆጠረ በኋላ በሀብቱ መደርጀት እየተደሰተ ፊቱን ፈካ አድርጎ ከንፈሮቹን በምላሱ ይዳስሳል ።

አንድ ቀን ከጐረቤቶቹ አንዱ ብዙ የተቀበረ ገንዘብ እንዳገኘ ሰማ ። ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ጀቡዴ እየከፋው ሔደ ። ይህን ያህል እየለፋ እሱ ያላገኘውን ሀብት ምንም ያልደከመ ያልለፋ ሰው ሲያገኘው ፤ ጌትነት ተከታትሎ ሲመጣለት ሰምቶ ነገሩ አልገባህ አለው ፤ ብስጭት አደረበት ፤ በወፍጮው ላይ ያውለው የነበረ የሥራ ትጋት እያነሰ ሔደ ፤ ይህም ቸልታው ሲጠራቀም የቆየውን ሀብቱን ይጐዳው ጀመር ።

በዚሁ በተከፋበት ሰሞን አንዲት ሌሊት ከወፍጮ ቤቱ መሠረት አጠገብ ከአንድ ትልቅ ጠፍጣፋ ድንጋይ ሥር እጅግ ብዙ ወርቅና አልማዝ እንደነበረ በህልሙ አየ ። ይህ አስደሳች ራእይ በልቡ ውስጥ ተስፋ አሳደረበት ። መከፋቱ ቀርቶ ወደ ቀድሞው ፈገግታው ተመለሰ ። ሕልሙ ሦስት ጊዜ ያህል ተደጋግሞ ከታየው በኋላማ ምንም ጥርጣሬ አላደረበትም ። ይህንን አጋጣሚ ዕድል ለማንም ሊገልጽ ስላልፈለገ ፣ የገዛ ሚስቱን እንኳን ተደብቆ ፣ አንድ ዶማና አካፋ ይዞ ወርቁንና አልማዙን በሕልሙ ካየበት ቦታ ደርሶ መቆፈር ጀመረ ። ከአንድ ግድግዳ ሥር ጀምሮ መሠረቱ ዘንድ ሲደርስ አንድ የማሰሮ ስባሪ ገል አገኘ ። በዚህ መልካም ምልክት ተበረታትቶ በኃይልና በፍጥነት እየቆፈረ እውነትም በሕልሙ እንዳየው አንድ ጠፍጣፋ ድንጋይ ካለበት ቦታ ደረሰ ። ድንጋዩን ለመፈንቀል ቢታገል አልሆንልህ አለው ። የሌላ ሰው ርዳታ ስላስፈለገው ያለውዴታው ሚስቱን ሊጠራ ሔደ ።

ምስጢሩን አውጥቶ በዘረገፈላት ጊዜ ሚስቱ በደስታ ተክለፈለፈች ። በአንገቱ ላይ ተጠምጥማ ሳመችውና ወድያው ወደ ቦታው ከነፉ ። ብዙ ከታገሉና ከደከሙ በኋላ ድንጋዩን ፈነቀሉት ። ነገር ግን ፣ እንኳንስ ወርቅ ሊገኝ የመተዳደሪያ ወፍጮአቸውን መሠረት አበላሽተው ከሚያሠጋ አደጋ ላይ ወደቁ ።

(ትርጉም—ሀ/ ማርያም ማርቆስ )



### 5.2.2 ስእላዊ (መስተዋታዊ)

የስእላዊ ፅሁፍ አላማ ፣ በስሜት ህዋሶቻችን ተደማጭነት ያላቸውን ፣ በማንኛውም ኪነ-ፅሁፍ ውስጥ ፣ በሙሉ በተዘረጉ ስሜት ጠቋሚ አውታሮች ውስጥ የሚንቀሳቀሱ ምስሎችን እና ለማንኛውም ፅሁፍ ደጀን የሚሆኑ ትርኢቶችን እያቀናበሩ ማቅረብ ነው ።

በደጀንነት የሚፈለጉ ትርኢቶች ፣ ታሪኩ የሚሆንበትን ክፍለ አለም ፣ የአውራጃውን ወይም የወረዳውን ፣ በይበልጥም ፣ የከተማውንና የቀበሌውን ገለፃ (በተለይ ልዩ በሚያደርገው ላይ በማተኮር) ፣ ባለታሪኮቹን ፣ ለመኖር የሚያከናውኑትን ስራ ፣ የእለት በእለት አኗኗራቸውን ፣ ባለታሪኮቹ የሚገኙበትን ታሪካዊ ዘመን እና የመሳሰሉትን ሁሉ ያጠቃልላሉ ።

በስሜት ህዋሶቻችን ተደማጭነት ያላቸው ደግሞ ፣ ለአይን ፣ ለጆሮ ፣ ለአፍንጫና ለሌሎችም አውታሮች ፈጣን ምስል የሚከስቱ ናቸው ። ቃላቱ ብቸኛና ተጨባጭ የተናጠል ስእል የሚኖራቸው (የቀለም ፣ የድምፅና የንቅናቄ ቃላት) ፣ ዝርዝር መግለጫዎቹም ከአንድ ከተወሰነ ግምባር ፣ አንድ የተወሰነ ግብን እንዲመቱ ሆነው በጥንቃቄ ስለሚመረጡ ስሜትን የመቀስቀስ ሀይል አላቸው ።

ስእላዊ ፅሁፍ ቴክኒካዊና ኪነ-ፅሁፋዊ የሆኑ መልኮች አሉት ። በቴክኒካዊ መልኩ የነገሮችን ፣ ሁኔታዎችንና ድርጊያዎችን መረጃና ጭብጥ ለአእምሯችን እንደሚያመቹ አድርጎ ያቀርባል (ለምሳሌ በደጀንነት የሚፈለጉ ትርኢቶችን)፤በኪነ-ፅሁፋዊ መልኩ ደግሞ ስሜት ከሳች ምስሎችን ያቀርባል (ለምሳሌ የስሜት ጠቋሚ አውታሮችን የሚቀሰቅሱትን) ።

## (ሀ) ቴክኒካዊ የሆነ ስእላዊ ፅሁፍ - ማስረጃና ማብራሪያ

'ሀብረተሰብአዊት ኢትዮጵያ በምሥራቅ አፍሪቃ የምትገኝ ሀገር ነች ። በሰሜንና በምዕራብ በኩል ከሱዳን ፣ በደቡብ ከኬንያ ፣ በምሥራቅ ከሱማሊያ ትዋሰናለች ። በሰሜን ምሥራቅ ቀይ ባህርን የሚያዋስን አንድ ሺህ አምስት ኪሎ ሜትር ጠረፍ አላት ። ጠቅላላ ስፋቷ 1,221,900 ካሬ ኪሎ ሜትር ሲሆን ፣ ትክክለኛው የሕዝብ ቆጠራ ባይደረግም ፣ 30 ሚሊዮን ሕዝብ እንደሚኖርባት ይገመታል . .

በአብዛኛው አፍሪቃ ውስጥ እንዳለው ሁሉ ኢትዮጵያ ክርሰ መሬት ውስጥ ያለው የመሠረት ድንጋይ ከ570 እስከ 4600 ሚሊዮን ዓመት ዕድሜ ያለው ነው ። ላይላዩም በእሳተ-ገሞራ ፍሳሽ በተደጋጋሚ ከመጥለቅለቁ የተነሳ ፣ በአንዳንድ ቦታ አያሌ ሺህ ሜትሮች ውፍረት ያለው ቢሆንም ፣ በአብዛኛው በመጠነኛ የኖራ ድንጋይና አሸዋ ድንጋይ የተሸፈነ ነው ። አሁንም ቢሆን የእሳተ-ገሞራው ተግባር መኖር በጥቂት ሕያው እሳተ-ገሞራዎችና በአያሌ ፍል ውሃዎች አማካይነት ይታያል ።

የአገሪቷን የመሬት ቅጥ ከሚለየው አንዱና ከፍተኛው ፣ የምሥራቅ አፍሪቃ ስምጥ ሸለቆ ሲሆን ፣ ይህም የመሬት



ግምሶት ከሰሜን ወደ ደቡብ በመዘርጋት ማእከላዊውን የኢትዮጵያን አዳጋ መሬት በምዕራብና በምሥራቅ በመክፈል ያቋርጣል ። በአየር ጠባይ ሁኔታዎች ፣ በአዝርእት ፣ በሰዎች መኖሪያና በውሃ ፍሳሽ ላይ ተጽእኖ የሚኖራቸው ዋናዎቹ ሦስት የሀገሪቱ የመሬት ቅጥ መልኮችም አንደኛ ፣ የምዕራብ ደጋ መሬቶች ፣ ሁለተኛ የምሥራቅ ደጋ መሬቶችና ሦስተኛ ስምጥ ሸለቆውና የምዕራብ ቆላ መሬቶች ናቸው. . .'

(አዲሱ የእንግሊዝኛ አውደ ጥበብ ገፅ — 996 ።)

ይህ ቴክኒካዊ የሆነ መስተዋታዊ ፅሁፍ ነው ፤ በጥቂቱም ቢሆን ፣ ስለ ኢትዮጵያ ጅኦግራፊ የቀረበ ። አላማውም አገሪቱ ያለችበትን ቦታ ፣ መሰረታዊ ተፈጥሮዋን ፣ በሰውና አዝርእት ላይ ተፅእኖ ያላቸውን የመሬት ቅጦች በመጠቆም ስርአት ያለው አጠቃላይ መረጃና መግለጫ ለማቅረብ ነው ። ከጅኦግራፊ ምሁር የቀረበ ነው እንበል ። በዚሁ አይነት ፣ በዚሁ ርእስ የተለያዩ ባለሙያዎች ከየልምዳቸው አኳያ አያሌ መስተዋታዊ የሆነ ቴክኒካዊ ፅሁፍ ሊያቀርቡበት ይችላሉ — ማለትም ገበሬዉ ለሰብል ዛመችነት አንፃር ፤ ባለፋብሪካው ጥሬ እቃ ከማግኘትና ከመገናኛ መስመሮች አንፃር ፤ የጦር መሪዉ ለውጊያ ስትራቴጂ ከሚኖረው ጠቀሜታና ወይም እነዚህን ከመሳሰሉ ሌሎች አንፃሮች በመመልከት ። ደራሲዉና ሰአሊዉም እንዲሁ ። ቴክኒካዊ ገለፃዎች የነገሮችን ፣ የሁነታዎችንና የድርጊያዎችን ምንነት ፣ ባህርያትና የአሰራር ሂደት በማስተዋወቅና በመግለፅ ያቀርባሉ ፤ መረጃዎቻቸውንና ጭብጣቸውን በስእላዊነት በመከሰት ለአእምሯችን እንዲገባ እያደረጉ ።

«... ያቀባበሉ ነገር በቃል ተናግሮ የሚጨርሱትና ጨርሶ በቃል የሚአስረዱት ነገር አይደለም ። ግሩም እጹብ ድንቅ ነበረ ። እስከ ረፋድ መንገድ ከሁለት እልፍ የበለጠ ጦር ተሰልፎ በጣልቂአ በጣልቂአው ባለ ሙዚካ ተሳክቶ ቁሞ ፤ መለኸቱ ፣ ነጋሪቱ ፣ እምቢልታው ሁሉ እየተነባበረ እየተመታ በመካከሉ ደጃች መኰንን እስከ ሰዎቻቸው በባለ ብር ጉብጉብ ሰረገላ ተቀምጠው ፤ በፊት በኋላ በቀኝ በግራ ባለወርቅ ባለወርቅ ኩፍታ በባለ ብር ጥሩር ሸልሚ ሰቀላ ሰቀላ በሚአካክል ፈረስ ተቀምጦ ተቀምጦ ፣ ደንገላሳ እየጋለበ ከንጉሡ አዳራሽ ደረሰ ። ያ ሁሉ የንጉሥ ሸልሚ ከናት ማኅፀን እንደ ሰው የወጣ አይመስልም ነበረ ። ብቻ በተለየ ሁለት ሁለቱን መዝዞ አንድነት እየ ጨፈለቁ ያበጁት ይመስልነበረ ። በግራ ክንዱ ጋሸ ፣ በቀኝ ክንዱ ዝሆን ለግቶ አላግቶ የሚጥል ይመሳሰል ነበረ ። ይሄው ሸልሚ የንጉሡ ዘበኛ ከንጉሡ ዙሪያ የማይለይ ምርጥ ሎሌ ነው ። ይሄው ምርጥ ዘበኛ ደረቱ በክንድ ቁመቱ በገመድ የሚሰፈር የመሳሰለ ሸልሚ ነበረ ። ከንጉሥ አዳራሽ ሲደረስ ከደጃፉ ላይ ግራና ቀኝ የየጁን በር በሬ የመሰለ ጅሀ ጁሁን ለብሶ ፣ ቅጹና ቅጡ ባበሻ ያልታወቀ ኩፍታውን አድርጎ ፣ የብር የብር ጐመዱን ይዞ ፣ አጋፋሪ ቁሞ ነበር . . . .

ካዳራሹ ጥልቅ ሲገባ ከበረዶ የነጣ የዕብነ በረድ ደረጃ ወለል ብሎ ይታይ ነበር ። በዚያ ወላላ ሰፊ ደረጃ ላይ በመካከሉ ተመልካም ከፋይ የለሰለሰ ወላንሳ ተነጥፎበት ነበረ ። ከደረጃው መካከል ብቅ ሲባል የሰማይ ስባሪ የመሳሰለ መስተዋት ዙሪአ ዙሪአውን እንቁጣጣሽ በመሰለ ወርቅ ተጣፍጦ ላይን ያስከር እራስ ያዞር ነበረ ። የቀረውን ፣ ታገራችን ታይቶ የማይታወቀውን ሕብር የሌለውን ሁሉ ፣ ላይን እንደሳት የሚፋጀውን ፣ እንደ



መራ የሚዋጋውን ደጃር ለማየት የሚቸግረውን በየገጹ ፣ በየስንቃው ፣ በየመስኮቱ ፣ በየወለሉ ፣ በየምኑም ሁሉ ያለውን ጌጥ ነገር ላየም ይግረመው ፣ ላላየም ይቍጨው ፣ ለሰማም ይጭንቀው እንጂ በስሙ ለማስረዳት ላገራችን አይታወቅም ... » *

ይኸኛው ደግሞ ጋዜጣዊ የሆነ ቴክኒካዊ መስተዋታዊ ፅሁፍ ነው ። አላማው (ከንነው አገላለፅ በመለስ) በጊዜው የነበረውን ተጨባጭ ትእይንት እንደ ነበረ አድርጎ ለማቅረብ ነው እንጂ ትእይንቱ የከሰተውን ስሜት ለመፍጠር አይደለም ። ከዚህም የተነሳ ከጅአግራፊያዊው ገለፃ እምብዛም አይለይም ።

## (ለ) ኪናዊ የሆነ ስእላዊ ፅሁፍ — ማብራሪያና ማስረጃ

ሌላው ደግሞ ኪነ-ፅሁፋዊ የሆነ ስእላዊ ድርሰት ነው ፤ ነገሮች ፣ ሁኔታዎችና ድርጊያዎች ለስሜት ህዋሶቻችን እንዲደርሱና ስሜት እንዲቀሰቅሱ ተደርገው የሚቀርቡበት ። አላማው ዝርዝር ባህሪዎችን ፣ መረጃዎችንና ጭብጦችን በእነሱነታቸው ለማቅረብ ሳይሆን ነገሮቹ ፣ ሁኔታዎቹና ድርጊያዎቹ በተከሰቱበት ወቅት ተራኪው ያደረበትን ስሜት አንባቢውም እንዲያድርበት ለማድረግ ነው ። ስለዚህ የተራኪው ጥረት ፣

- ስለ ነገሩ ፣ ሁኔታውና ድርጊያው ለመንገር ሳይሆን ፣ እንዳለ አቅርቦ ለማሳየት ነው ፤ አንባቢው በሚያነብበት ወቅት የሚታዩት አይነት ስሜት ለመፍጠር ፤

* አፈ ወርቅ ገብረኢየሱስ ፣ 'ዳግማዊ ምኒልክ' (ሮማ 1906) ፣ ገፅ 67—68 ።

አንባቢውን ፣ ምን ስሜት ወይም አዝማሚያ ሊኖረው እንደሚገባ ለማስገንዘብ ሳይሆን ፣ በተሳታፊነት አሰልፎ ፣ እነዚያን ስሜቶችና አዝማሚያዎች ራሱ እንዲደርስባቸው ለማድረግ ነው ።

እነዚህን አይነተኛ መለዮዎች እውን ለማድረግ የሚሰፉባቸው ዘዴዎች በቴክኒካዊ መስተዋቃዊ ድርሰት ከተመለከቱት ይለያሉ ። እርግጥ አሁንም ቢሆን ዝርዝር ጭብጦች አሉ ። ዝርዝር ጭብጦቹ ግን የሚመረጡት በመረጃ ይዘታቸው ብቻ ሳይሆን በይበልጥ የተፈለገውን ስሜት ለመከሰት በሚኖራቸው ሃይል መሰረትነት ነው ። ስለዚህም ቅድመ ዝግጅቶች ይጠይቃሉ ።

(1) በመጀመሪያ ፣ በሚመረጡት ጭብጦች አማካይነት እንዲቀስቀስ የታሰበው አቢይ ስሜት ተለይቶ መታወቅ አለበት ።

(2) ነገሩ ፣ ሁነታው ወይም ጉዳዩ ባንባቢው ላይ እንዲያሳድር የተፈለገው ስሜት ሲታወቅ ፣ መረጃ ዝርዝሮቹ ፣ የተባለውን ስሜት ለመፈንጠቅ ባላቸው ባህሪ መሰረት መመረጥ አለባቸው ።

(3) መረጃ ዝርዝሮቹን ግልፅና ቅርብ አድርገው ለማቅረብ የሚያመቹ ቃላትን ማዘጋጀት ያሻል፤ (ለምሳሌ ቅፅሎችን በመጠኑ አድርጎ ፣ ምስል የሚከስቱ ስሞችን ፣ ግሶችንና ተውሳከ ግሶችን እየመረጡ በመጠቀም ።)

(4) ፅሁፉ የሚቀርብበትን አኳያና አቅጣጫ መወሰን ያስፈልጋል ። (ገፅ 296—300 እና 147—150 ተመልከት ።)



## እንዲቀሰቀስ የታሰበው አቢይ ስሜት

ስለ አንድ ሰው በምንናገርበት ጊዜ ፣ ‘አይኗ ቀድሞ ያስርሃል’ ፤ ‘አፍንጫው ይጋረጥብሃል’ ፤ ‘ቀትረ ቀላል ነው’ ፤ ‘ሲያውት ያስደነግጣል’ እንላለን ። ሰውዬውን ወይም ሴትዮዋን በምናይበት ጊዜ የሚሰማንን አጠቃላይ መግለጫ መስጠታችን ነው ። ‘አይኗ ቀድሞ ያስርሃል’ ስንል ፣ ከሴትዮዋ አይኖች የሚመነጨው ውበትም ይሁን ሌላ ሀይል ይማርከሃል ፤ ሌላውን የአካሏን ክፍል የማየት እድል አይሰጥህም ማለታችን ይሆናል ። አይኗ ተለይታ የምትታወቅበት መሆኑ ነው ። ‘አፍንጫው ይጋረጥብሃል’ ስንልም እንዲሁ አፍንጫው የበላይነትን ፣ የትልቅነትን ስሜት ያሳድርብሃል ማለታችን ሊሆን ይችላል፣ከሰውዬው የአካል ክፍል ሁሉ ጎልቶ በመታየቱ ። በሌላ አነጋገር ፣ ‘አይንም’ ሆነ ‘አፍንጫ’ እንደ ዋነኛ መለያ በሚጠቀሙበት ወቅት ፣ እነዚህ ክፍሎች ሌላውን የአካል ክፍል ሁሉ በመጋረድ ሰውዬውን ወይም ሴትዮዋን የሚወክል የስሜት ከሳችነት ባህሪ ይኖራቸዋል ማለት ነው ። ‘ቀትረ ቀላል ነው’ ወይም ‘ሲያውት ያስደነግጣል’ ሲባል ግን በእርግጥ ምኑ እንደሚቀልል ወይም እንደሚያስደነግጥ ተለይቶ አይታወቅም ። ስለዚህ ገለፃው ያንን አል ያዘና አልጨበጥ ያለ የከባድነትና የአስደንጋጭነት ስሜት መከሰት ይኖርበታል ማለት ነው ። በሌላ በኩል ደግሞ እንዲከሰት የሚፈለገው ስእል በሰውዬው ላይ ሳይሆን ከሰውዬው ውጭ ለምሳሌ ተፅእኖ ያሳደረበት ብቸኛና ፍቅር የሌለበት ህይወቱ ሊሆን ይችላል ። (ገፅ 65—366 (ተ1) ተመልከት ።) እንዲያም ቢሆን ታዲያ ፣ የሚመረጡት ዝርዝሮች ከላይ በተመለከቱት አይነት ብቸኝነቱንና ፍቅር የሌለውን ህይወቱን የሚከስቱ መሆን ይኖርባቸዋል ፤ አንባቢውን እነዚህ ስሜቶች እንዲሰሙት የሚያደርጉ ።

አጠቃላይ የሆኑ አባባሎች — ሰውየው ብቸኝነት አጥቅቆታል፤ በህይወቱ አፍቅሮም ሆነ ተፈቅሮ አያውቅም — በኪነ-ፅሁፍ ምስል መከሰቻ ፅሁፍ ውስጥ ቦታ የላቸውም ። ስለዚህ እንዲቀሰቀስ የሚፈለገው አቢይ ስሜት ስንል ፣ በአንድ ነገር ፣ ሁኔታ ወይም ድርጊያ ፅሁፍ ውስጥ እንዲኖር የተፈለገው አይነተኛ ግንዛቤ ነው ። 'ሰውዬው ብቸኝነት አጥቅቆታል' ወዘተ . . . በሚለው ጠቅላላ አባባል የሚገለፀው አይነት ሳይሆን ፣ በብቸኝነት መጠቃቱ የተገለፀበት ዝርዝር ፅሁፍ የሚኖረው ባህሪ ። በሌላ አነጋገር ፣ በዝርዝሩ መስተዋታዊ ፅሁፍ ውስጥ የተሳለው ምስል የሚከስተው አይነተኛ ስሜት ነው ። የሚከተለውን ማስረጃ እንመልከት ፤

__አስረጅ ፤__

“. . . አዳራሹ በግማሽ በያይነቱ ምንጣፍ ተነጥፎበት ከወደ ግርጌው ግን ሣርና ኬሻ ተጥሎበት ነበር ። አልፎ አልፎ መሶቦች በቀይ ተሸፍነው ጉች ጉች ብለዋል ። ከታች ግን የመቃ ገበታ በተርታ ተደርድሮ ነጭ ጨርቅ ተሸፍኖ ይጠብቃል ። ከላይ ከምድር ከፍ ብሎ የተደለደለ ቦታ በረጅም መጋረጃ ተጋርዷል ። ባዳራሹ ግድግዳ አልፈው አልፈው ወጣት አሽከሮች ቆመዋል ። ድስትና እንጀራ የያዙ ገረዶችም በታላቅ ጥድፊያ ይተላለፋሉ ። አጋፋሪው አርአያን እየጠራ ወደ መጋረጃው አድርሶት አንድ ጊዜ ይቆዩኝ ብሎት እመጋረጃው ውስጥ ገባ ። ወዲያውም የሽማግሌውን ጉርናና ድምፅ ሰማ ። 'የታል እኮ አስገባው' እያሉ ሲናገሩ ሰውዬው ብቅ ብሎ አርአያን ፣ 'ጌታዬ ይምጡ' ብሎ መጋረጃውን ገለጥ አደረገለት ። እሱም ሲገባ በመጋረጃው ውስጥ ብዙ መኳንንትና ሴት ወይዘሮዎች ባራት ባምስት ሆነው መሶብ ከበው ሲበሉ አየ ። ባለቤቱም በሚያምር ሲጋጃ ምንጣፍ ላይ በትልቅ ፍራሽ ተቀምጠው በዙሪያው



ቀያይ መከዳዎች ተደግፈው ይበሉ ነበር ። ከጉናቸው አንድ ወፍራም ቀይ ሴት ወይዘሮ ቍጭ ብለዋል ። በግርጌያቸው ከመሶቡ ፊት ለፊት አንዲት ገረድ እጀቿን ወደ ፊት በመስቀልኛ አጣምራ ቆማለች ። ከእግሯ ሥር ዐሥር የሚሆኑ ድስትና ሳሕኖች ተደርድረዋል ። አንዳንድ ጊዜ ጐንበስ እያለች ወጥ እየጨለፈች ከመሶቡ ላይ በጌቶቿ ፊት ታወጣለች ። እንጀራውንም እፊቷ ካለው መሶብ እያነሣችና እየመረጠች እፊት እፊታቸው ታደርግላቸዋለች ። አንዳንድ ጊዜም እመቤቷ በቃል ሳይሆን በጥቅሻ እያዘዟት ወጥ ጨልፋ በጐድጓዳ ሳሕን ይዛ እዚያው አጠገባቸው አሉት መሶቦች ላይ እየተዘዋወረች ወጥ ታወጣለች ። አንድ ጠጕሩን ዙሪያውን ጋሜ የተላጨ ያሥር ዓመት ልጅ ረዥም ነጭ ጭራ ይዞ ከባለቤቱ ጐን ራቅ ብሎ ቆሞ ዝንብ ይከላከላል ። ደግሞ ሁለትና ሦስት ወጣት ልጆች ግድግዳውን ተደግፈው እንዳደገደጉ ቆመው ያስተውላሉ ። ሲበሉ ከሚሰማው የማላመጥ ድምፅና ከጭራው ሽውሽውታ እንዲሁም ጐርናና ከሆነው ከባለቤቱ ንግግር በቀር ሌላ ድምፅ አይሰማም ነበር . . .” [5]

በዚህ አንቀፅ ውስጥ የተደሩ ምስሎች

(1) __ቀለም*__

— በቀይ የተሸፈኑ መሶቦች
— ቀያይ መከዳዎች
— ቀይ ሴት
— በነጭ የተሸፈነ ገበታ
— ረዥም ነጭ ጭራ

[5] ግርማቸው ተክለ ሐዋርያት ፣ 'አርአያ' (አ.አ. 1963) ፣ ገፅ 113-4 ።

* የሚዋዋጡ ፣ የሚዋሃዱና የሚቃረኑ ቀለሞችን ጠንቅቆ ማወቅ ያስፈልጋል ፤ አለዚያ ያልታሰበ ውጤት ይሰጣል ።

— ድብቅና እንጀራ
— በያይነቱ ምንጣፍ (?)
— በሚያምር ስጋጃ (?)

(2) <u>ድምፅ</u>

— የአጋፋሪው ድምፅ (?)
— የሽማግሌው ጎርናና ድምፅ
— የማላመጥ ድምፅ
— የጭራው ሽውሽውታ

(3) <u>እንቅስቃሴ</u>

— በታላቅ ጥድፊያ የሚተላለፉ ገረዶች
— የአጋፋሪውና የአርአያ የቀስታ እንቅስቃሴ
— እየተዘዋወረች ወጥ የምታወጣ ገረድ

(4) <u>ክንውን</u>

— መኳንንትና ሴት ወይዘሮዎች (ዝም ብለው እልተቀመጡም) ይበላሉ ።
— ባለቤትየው ይባላሉ ።
— ገረዷቱ ጎንበስ እያለች ወጥ ትጨልፋለች ፤ እንጀራም እያነሳች እሬት እፊታቸው ታደርጋለች ፤
— ባለጋሜው ዝንብ ይከላከላል ።

በዚህ አይነት ፣ አዳራሹ ፣ በአረንጓዴና ብጫ መደብ ላይ ነጫጭ መስመሮችና አልፎ አልፎ ጥቁርና ቀይ ነጠብጣቦች ጣልጣል ባሉት መድረክ ላይ (በተለይ በአዳራሹ ግድግዳ እልፈው እልፈው ከቆሙት ወጣት አሽከሮችና አደግድገው



ከቆሙት ሁለትና ሶስት ወጣት ልጆች እንፃር ሲታይ) ዝቅተኛ እንቅስቃሴ ፣ ዝቅተኛ ክንውን የሚካሄድበት ፣ (በቃል ሳይሆን በጥቅሻ ትእዛዝ ከሚሰጡት ሴትዮ አንፃር ሲታይ) ከሽማግሌው ጎርናና ድምፅ ፣ ሲበሉ ከሚሰማው የማላመጥ ድምፅና ከጭራው ሽውሽውታ በስተቀር ድምፅ (በተለይ ሙዚቃ ባይኖርም ሳቅና ጨዋታ እንኳ) የሌለበት ዝግ ፣ ከባድና ሰዎቹን ሁሉ የሚደብት አየር የሰፈነበት ነው ።

ፅሁፉ የሽታም ሆነ የጣእም ምስል የሚከስቱ ክንውኖችን አያሳይም ። ደራሲው አውቀውም ይሁን ሳያውቁ የተዋቸው አላማቸውን አላሰናከሉባቸውም — በተለይ ስልጣን የሰፈነበት ፣ ህይወት የታፈነችበትና የሚደብት ሁናቴ ለመፍጠር ከሆነ ።

በአንቀፁ ውስጥ የሚገኙት ፣

— ‘በያይነቱ ምንጣፍ’
— ‘የሚያምር ስጋጃ
— ‘የአጋፋሪው ድምፅ’ አይነቶቹ ምንም አይነት ተጨማሪ ምስል ስለማይከስቱ ቢኖሩም ባይኖሩም ልዩነት አያመጡም ።

በዚህ አይነት የቀረቡትን ሌሎች ፅሁፎችም ፣ ከስእላዊ ፅሁፍ መለኪያዎችና ፅሁፉ እንዲያስገኝ ከተፈለገው ግብ አንፃር በመመልከት ፣ ደካማነታቸውንና ጠንካራነታቸውን ለመገምገም ይቻላል ።

«. . . ማየቴ ማየት እንዲሆንልህ እንዴት ብዬ ልንገርህ ። እንዴትስ አድርጌ ላስረዳህ ። የነፋሱ እነፋፈስና የባሕሩ እንቅስቃስ ደስታዎች በሰውነትህ እንዲንቀሳቀሱ

ያደርጋቸዋል ። የማዕበሉ አዘላለል ረድፍ ረድፍ እያበጀ ሲገነፍልና ፈረሰኛውን ፈረሰኛ እየተከታተለው ባሕሩን እየለቀቀ ፥ በተፈጥሮ ሳይሆን በገዛ ኃይሉ ባበቀለው ክንፍ አግድም ፥ ሲንቻረር ፥ «የእግዚአብሔር መንፈስ በውሃዎች ላይ ይሰፍ ነበር» የተባለው ቃለ አሪት ሲተረጐም ታየዋለህ። ማዕበሉ እንደ ሰገኖ እንገቱን አስግጐ በኋላ እግሩ ቀጥ ብሎ ቁሞ እንደገና በፊት እግሩ ደፋ ሲል በስግደት ላይ የሚገኝ ባሕታዊን ይመስላል ። ይህንም ይተወውና ሲያጋፍትና በዳሊጋው ልዩ ልዩ ጅምናስቲክ ሲሠራ ፥ በተፈጥሮው ፈጣሪውን የሚያስመሰግን ተግባር ይፈጽምበታል. . .

. . . . . ሌላ ፊትን ዘወር የማያሰኝና አሳብን የሚማርክ ነገር አይገኝም ። ከታች የዐይን ማረፊያ ዛፍ ከላይ የሕዋ መሸፈኛ አዕዋፍ ለበስማም ወልዴው አይታይም ። ውቅያኖሱ ለጥ ፥ ሰማዩ ቅልጥጥ ብሎ ሲታይ ዐይንን ምዕራፍ ያሳጣዋል ። ከቶውንም ሰማዩን ወደ ምድር ምን አወረደው ፥ ምድሩንስ ወደ ሰማይ ምን አወጣው ያሰኝሃል ። ፀሓዩና የባሕሩ ጽርየት ሲፎካከር ዐይኑ ወርቅ የሆኑ ብልጭልጭታዎችና የዕንቁ ጠቃጠቆ የመሳሰሉ ወራውርቶች እንደ ቢራቢሮ ሲፈናጠዙና እንደ ጅራታም ኮከብ ሲወረወሩ የዐይኖችህ ነጸብራቆች አብረው ይወነጨፉሉ . . . »[6]

## 5.2.3 ገላጭ ድርሰት

ገላጭ ድርሰት ፥ በአንድ ነገር ፥ ወይም ሀሳብ ወይም ጉዳይ ላይ የሚነገር ወይም የሚፃፍ ትችት ነው ። በአብዛኛው የሚሰራበት የድርሰት አይነት ስለሆነ ፥ ብዙ ጉዳዮችን ለማብራራትና ግልፅ ለማድረግ

[6] ወ/ጊዮርጊስ ፥ ወ/ዮሐንስ ፤ 'አግዐዚ' (እ.አ. 1961) ፥ ገፅ 7—8 ።



ይውላል — አንድ አውናዊም ሆነ ልቦለዳዊ ድርጊያ እንዲከሰት የሚገፋፉትን ቅድመ ሁኔታዎችና ድርጊቶች ለማዘጋጀት ፥ አንድን ታሪካዊ ሁኔታ ለመተርጎም ፥ የአካልን አወቃቀር (ቅጥንብርን) ፥ የመኪናን አሰራር ፥ የቃልን ትርጓሜ እና የመሳሰሉትን ሁሉ አቀናጅቶ ለማቅረብ ። ባጠቃላይ ፥ ገላጭ ድርሰት ስለ ነገሮች ፥ ሁነታዎችና ድርጊያዎች የተለያዩ ጥያቄዎችን ለመመለስ ይዋክራል ፤ ምን ማለት ነው ? ምንድነው ? እንዴት ነው የሚሰራው ? ከምን ከምን ነው የተዋደደው ? ምን ጠቀሜታ አለው ? ግሊጋሎቱ የቱን ያህል ነው ? እንዴት እንዲህ ሊሆን (ሊከሰት) ቻለ . . ? የጥያቄዎቹ አይነቶች ከተተኳሪው ርእስ እንደሚፈለገው መልስ አይነት ይለያያሉ ።

ገላጭ ድርሰት ለየብቻቸው ወይም አብሮ አብሮ የሚሰራባቸው የተለያዩ የማቅረቢያ ስልቶች አሉት ። (የትርጓሜ ውሳኔና ገደብ) ፥ የድልደላ ፥ የአብነት (ማስረጃ ፥ ምሳሌ) የማመሳሰልና የማነፃፀርና የትንተና ስልቶች ።

### (ሀ) ትርጓሜ (የውሳኔና ገደብ ስልት)

ውሳኔና ገደብ ፥ አንድ ነገር ፥ ሁነታ ወይም ቡድን የሚዛመደውን አጠቃላይ መደብ መጠቆምና ይኸው ነገር ፥ ሁነታ ፥ ወይም ቡድን ከአጠቃላዩ መደብ አባሎች የሚለይበትን ማመልከት ነው ።

በዚህ ዘዴ ነገሩ ፣ ሁኔታው ወይም ቡድኑ በአጠቃ ላይ መደቡ ውስጥ ያለውን ቦታና ዝምድና በማጤን ምንነቱን እናውቃለን ።

በመሰረቱ ትርጓሜ የሚያስፈልገው ቃል ነው እንጂ ቃሉ የቆመለት ነገር አይደለም ። ስንተረጉም ቃሉን በምን አይነት እንደምንጠቀምበት ነው የምናሳየው ። ስለሆነም ነገሩን ፣ ሁኔታውን ወይም ድርጊያውን ሳናውቅ ወካዩን ቃል ለመተርጎም ያዳግታል ። ስለዚህ ስለ ተወካዩም ማወቅ ይኖርብናል ። ቃልን ለመተርጎም የወካዩን (ቃሉን) እና የተወካዩን (ነገር ፣ ሀሳብና ሁኔታ) ምንነት ማወቁ ወሳኝነት አላቸው ።

## አስረጅ 1

"ባህል ሲባል በህብረተሰብ ታሪክ ሂደት ውስጥ መላውን የሰው ልጅ የፈጠራቸውን ቁሳዊና መንፈሳዊ ቅርሶችንና እንዲሁም እነዚህ ቁሳዊና መንፈሳዊ የባህል ግንኙነቶች የተፈጠሩበትን ፣ ግልጋሎት ላይ የሚውሉበትንና የሚተላለፉበትን ዘዴዎች ያጠቃልላል ። ቁሳዊ ባህል የሚባለው የሰው ልጅን ቁሳዊ ክንውንና ውጤቶችን የሚሸፍን መስክ ሲሆን ፣ ይህም የቴክኒክ መገልገያ መሳሪያዎችን ፣ የማምረት ልምድንና ሌሎችንም ቁሳዊ ሀብቶች በማጠቃለል ይይዛል ። መንፈሳዊ ባህል የሚባለው ደግሞ ሰዎች ቁሳዊ ምርትን በማምረት ሂደት የሚያመርቱት የመንፈሳዊ ምርት መስክ ሲሆን ፣ ይህም እንደ ሳይንስ ፣ ትምህርት ፣ ሥነጥበብ ፣ ፍልስፍና ወዘተ . . . የመሳሰሉትን ባህላዊ ቅርሶች ያጠቃልላል ። እነዚህ የቁሳዊና የመንፈሳዊ ባህል መስኮች የተነጣጠሉ ሳይሆን እርስ በርሳቸው የተያያዙ ናቸው ። በመካከላቸው ባለው ግንኙነት



ውስጥ መንፈሳዊው ባህል ከቁሳዊ ባህል የሚመነጭና በሱም የሚወሰን ይሁን እንጂ ፣ መንፈሳዊው በቁሳዊው ላይ ተመልሶ የራሱን ተፅዕኖ ያሳርፋል ። ይኸው የቁሳዊው ባህል እድገት ደግሞ ተመልሶ በተራው የመንፈሳዊውን ባህል ዕድገት ያዳብራል ።

«ከላይ ስለባህል ከቀረበው ሐሳብ ውስጥ የባህል ፅንሰ-ሐሳብ ሰፊና በውስጡም የህብረተሰቡን ቁሳዊና ቴክኒካዊ መሠረት እንደሚያጠቃልል በቀላሉ መገንዘብ ይቻላል ። ባጭሩ ባህል የሰው ልጅ ማኅበራዊ ተግባር እንቅስቃሴ ውጤት የሆነ ታሪካዊ ክስተት ነው ። ዕድገቱም የሚወሰነው በሶሲዮ-ኢኮኖሚ ቅንብሮች ተከታታይነት ነው ። የሶሲዮ-ኢኮኖሚ ቅንብሮች ተከታታይነት ደግሞ የማኅበራዊ አብዮት ውጤቶች ናቸው ። በተለይ በሶሻሊስት አብዮት የትኛውንም ዓይነት ጭቆናና ብዝበዛ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ በማስወገድ ነፃነትና እኩልነትን ለማስገኘት በዚህም ላይ በመመሥረት ከፍተኛ ባህላዊ ዕድገትን ለማስፈን የሚካሄድ በመሆኑ ካለፉት የሶሲዮ-ኢኮኖሚ ቅንብር ለውጦች ሁሉ የተለየ ጥልቀትና ይዘት ያለው ነው ። ስለዚህም በዚህ አብዮት ሂደት ውስጥ ከፍተኛ ባህላዊ ዕድገትን ለማስገኘት በህብረተሰቡ ቁሳዊና ቴክኒካዊ መስኮች ውስጥ ከሚካሄደው ሥር ነቀል ለውጥ ጋር በባህሉም መስክ ተመሳሳይ ለውጥ መካሄድ ይኖርበታል ።

«የባህል አብዮት እንቅስቃሴ የሶሻሊስት አብዮት አካል ሲሆን ይህም አዲሱን ሶሻሊስት ባህል ለመገንባት በመስኩ የሚካሄደውን አብዮታዊ እንቅስቃሴ የሚሸፍን ነው ። የአብዮቱም ዋነኛ ዓላማዎች መላውን የትምህርት ሥርዓት በአጭር ጊዜ ውስጥ እንደገና ማዋቀርና ባህላዊ ቅርሶች ለሰፊው ሕዝብ ግልጋሎት እንዲውሉ በማድረግ

ሰፊው ህዝብ ኢኮኖሚያዊ ፣ ባህላዊና ፖለቲካዊ ሕይወቱን
በማስተዳደር በኩል የሚኖረውን ቀጥተኛ ተሳትፎ ማረ
ጋገጥ ፣ ሶሻሊስት ምሁራንን በጥራትና በብዛት ማፍራትና
አዲስ ሶሻሊስት ባህል መገንባት ናቸው ። የሶሻሊዝም
ግንባታ እንደየአገሩ ታሪካዊና ተጨባጭ ሁኔታዎች መለ
ያየት የተነሣ የተለያዩ ባሕሪያት ሊኖሩት ቢችልም የእነ
ዚህ ከፍ ሲል የጠቀስናቸው የባህል አብዮት ዋነኛ ዓላማ
ዎች ተግባራዊ መሆን በግንባታው ሂደት ውስጥ ለየትኛ
ውም አገር ቢሆን አግባብነት ያላቸው ግዴታ ናቸው . . . »[7]

"ዲሲፕሊን ለኑሮ ፣ ለሥራ ፣ ለድርጅት ፣ ለትግል ፣
በአጠቃላይ ለማንኛውም አብዮታዊ ተግባር ስምረት
ፍቱንና ቁልፍ የሆነ መሣሪያ ነው ። በሌላ በኩል ደግሞ
ዲሲፕሊን የግለሰብንም ሆነ የድርጅትን መብትና ግዴታ
ለመቆጣጠር የሚያስችል ብሔራዊ የሞራል ህግ ነው ።

«በተለያዩ ሥርዓተ ማኅበሮች ውስጥ ዲሲፕሊን ያለ
ቢሆንም አጠቃቀሙ ግን እንደየሥርአቱ ባሕርይ የተለ
ያየ ነው ። በመደብ በተከፋፈለ ህብረተሰብ ውስጥ የሚ
ታየው ዲሲፕሊን ሰፊውን ሕዝብ በማዘዝና በመጨቆን
ላይ የተመሠረተ ነው ። በሌላ በኩል ደግሞ የሠራተኛው
መደብ የበላይነቱን ባረጋገጠበት ኅብረተሰብ ውስጥ የሚ
ሰፍነው አብዮታዊ ዲስፕሊን በጋራ ጥቅም ላይ የተመሠ
ረተ ፣ ሠራተኛው በመግባባትና በመፈቃቀር ፣ ዐውቆት
በፍላጐት የሚፈጽመው ነው ።

«የዲሲፕሊን ዓላማ በአንድ በኩል በልዩ ልዩ የሥራ
መስክ የተሰማሩ ሠርቶ አደሮችን በአንድ አቋም አዋህዶ
በዲሞክራሲያዊ ማዕከላዊነት መርህ ላይ በተመሠረተ

7 'መስከረም' ቅፅ 3 ቁጥር 12 ፣ ታኅሣሥ - መጋቢት 1975 ፣ ገጽ 50-51 ።



ማዕከላዊ አመራር ሥር እንዲሰለፉና ሥራቸው የተፈለገ
ውን ውጤት እንዲሰጥ ለማድረግ ሲሆን ፣ በሌላ በኩል
እያንዳንዱ የኅብረተሰብ አባል ራሱን ተቆጣጥሮ መሥራት
የሚገባውን በቅድሚያ አውቆ እንዲያከናውን ማስቻል
ነው ። ይህም በመሆኑ ዲሲፕሊን የነፍስ ወከፍና የወል
ወይም የጋራ ዲሲፕሊን በመባል በሁለት ተከፍሎ
ሊታይ ይቻላል ።

«የነፍስ ወከፍ ዲሲፕሊን የሚባለው እያንዳንዱ ግለ
ሰብ የሚፈለግበትን አውቆ የሚፈጽመው ነው ። ይኸውም
ግለሰብ ሠራተኛ የተሰጠውን የሥራ ድርሻ የበላይ ተቆ
ጣጣሪ አየኝ አላየኝ ሳይል ተግባሩን በተገቢው ሁኔታና
በወቅቱ ማከናወኑን የሚያመለክት ነው ። ይህንንም ለማ
ከናወን ሠራተኛው በቅድሚያ የተሰጠውን የሥራ ድርሻ ፣
ለሥራ መደቡ የወጡትን ደንቦችና መመሪያዎች ጠንቅቆ
ማወቅ ይጠበቅበታል ። የወል ዲሲፕሊን የሚባለው
ደግሞ እያንዳንዱ ግለሰብ በነፍስ ወከፍ የሚፈለግበትን
አውቆ ከሥራ ባልደረቦቹ ጋር በመግባባት ፣ በመረዳዳትና
በመፈቃቀር በጋራ ተግባሩን ማከናወኑ ነው ። በተለይም
በአብዮታዊ እንቅስቃሴ ውስጥ የሚገኝ ኅብረተሰብ ጥን
ካሬ ከሚለካባቸው መለኪያዎች መካከል የሕዝቡ የሞ
ራል አቋም ፣ ሥነ ሥርዓት ፣ በራሱ መመካት ፣ የሥራ ፍላ
ጐት ወዘተ . . . ጥቂቶቹ ሲሆኑ ፣ የነዚህ ሁሉ መሠረትና
መነሻው ደግሞ ፣ የነፍስ ወከፍና የጋራ ዲሲፕሊን ወይም
በአጠቃላይ የኅብረተሰቡ ዲሲፕሊን መሆኑ ግልጽ ነው ።

« በኅብረተሰቡ ውስጥ ዲሲፕሊን ከሌለ በቁጥጥር ብቻ
አዋጆችን ፣ ደንቦችንና መመሪያዎችን ማስፈጸም አይ
ቻልም ። ዲሲፕሊን በአጠቃላይ ይዘቱ በአመራር አካል
የሚቀየሱ ሕጐች ፣ ደንቦችና ሥነ ሥርዓቶች እንዲሁም ፣
በነዚሁ ላይ በመመርኮዝ አስተዳደራዊ አካሎችና በየደረ

ኛውም ያሉ የሥራ መሪዎች ለሥራ አፈጻጸም በሚበጅ ሁኔታ የሚያስተላልፏቸው መመሪያዎችና ትእዛዞች በሥራ ፈጻሚዎች መከበር እንዳለባቸው የሚያመለክት ነው ። እነዚህ ሥራ ፈጻሚዎች በተራማጅ ሥርዓት ውስጥ የሚጠበቅባቸውን ለማሟላት የሚጥሩ ከፍ ያለ ውጤት ለማስገኘት አመዛዝነውና ተጨባጭ ሁኔታው በሚፈቅደው መሠረት የፈጠራ ችሎታቸውንምጭምር አክለውበት ነው ።

«የሶሻሊስትን ሥርዓት ከሌሎች ሥርዓቶች የሚለየው ዓይነተኛ ባሕርይ ኤኮኖሚያዊና ማኅበራዊ እንቅስቃሴዎች ሁሉ በዲሞክራሲያዊ ማእከላዊነት መርህና አሠራር ላይ ተመሥርተው መመራታቸው ነው ። የዲሞክራሲያዊ ማዕከላዊነት መርህ በአንድ በኩል የሠራተኛውን የማይገሠሥ መብት፣ ማለትም በፖለቲካና በኤኮኖሚ አስተዳደር ውስጥ የሚያደርገውን ንቁ ተሳትፎ የሚያሳይ ሲሆን ፣ በሌላ በኩል ደግሞ የጥቂቱ ለብዙሀኑ ፣ የሁሉም ደግሞ ለአንድ ማዕከል ተገዥ መሆንንና እንደ ብረት የጠነከረ ዲሲፕሊን መከተልን የሚጠይቅ የማዕከላዊነት ውህደት ነው ። ለዲሞክራሲያዊ ማእከላዊነት ዋነኛው መሠረት በሥርዓቱ ውስጥ ሰፍኖ የሚገኘው ማኅበራዊ ይዞታ ነው ።

«በዲሞክራሲና በማዕከላዊነት መካከል ሚዛናዊ ግንኙነት ከሌለ የዲሞክራሲያዊ ማዕከላዊነት አሠራር ፍሬያማ ውጤት ሊያስገኝ አይችልም ። ሶሻሊስት ዲሞክራሲ ጠንካራ ድርጅትንና ዲሲፕሊንን ይጠይቃል ። ይህም ሕጎችንና የኅብረተሰብን የሞራል ግዴታዎች ማክበርን መጠበቅን ይጨምራል ። ዲሞክራሲ ያለ ዲሲፕሊንና ያለ ኃላፊነት ስሜት የሚመራ ከሆነ የሚያስከትለው ውጤት ሥርዓት አልበኝነት ነው ። የሶሻሊስት ዲሲፕሊን በንቃት ላይ የተመሠረተና ሰዎች በፈቃደኝነት የተቀበሉትና የሚፈጽሙት በመሆኑ ፣ በበዝባዥ መደቦች ዘንድ እንደሚ



ታየው በአሠሪና በታዛዥ መካከል ካለው ዲሲፕሊን ፍጹም የተለየ ነው ። ስለዚህ በሶሻሊስት ሥርዓት የሚኖረው ዲሲፕሊን ተፈጻሚነት በአንድ የተወሰነ አካል ብቻ ሳይሆን በአመራር ሰጪውና በተቀባዩ ላይም ነው ።

የተለያዩ የዲሲፕሊን ዓይነቶች መኖራቸው ባይካድም ዋነኛው ግን ከሰው የማምረት ተግባር ጋር በጥብቅ የተሳሰረው የሥራ ዲሲፕሊን ነው ። የሥራ ዲሲፕሊን መከበር የሥራ ውጤታማነትን ያዳብራል ፤ ምርታማነትን ያሳድጋል ብሎም የሠራተኛውን ሕዝብ የኑሮ ደረጃ ከፍ ያደርጋል ። ስለዚህ የሠርቶ አደሩን መንፈሳዊና ቁሳዊ ፍላጎት ለማሟላት ፣ ማኅበራዊ እኩልነትን ይበልጥ ለማረጋገጥና የጋራ ብልፅግና ለሰፈነበት አዲስ ህብረተሰብ ቁሳዊ መሠረት ለመጣል ሠርቶ አደሩ ለዲሲፕሊን ተገዥ መሆን ይኖርበታል ። ይህ ሊረጋገጥ የሚችለው ደግሞ ሠርቶ አደሩ ንቃቱን ከፍ ሲያደርግ ፣ በድርጅት ሲጠናከር ፣ የሥራ ክቡርነትን ተገንዝቦ መመሪያዎችንና ደንቦችን ጠንቅቆ በማወቅ በተግባር ሲተረጉም ነው ። ለዚህም በማርክሲዝም ሌኒኒዝም መመራት ይኖርበታል ። ...”[8]


(ለ) <u>የድልደላ ስልት</u>

ድልደላ በመደብ መለየት ማለት ነው ። በየመደቡ የሚደለደሉ ደግሞ ርባና ያለው የጋራ ባህርያት ያላቸው ነገሮች ፣ ሁነታዎችና ድርጊያዎች ናቸው ። እርባና ያለው ሆኖ ለመገኘት ደግሞ ከየፍላጎት አኳያ መታየት አለባቸው። ለምሳሌ የፖለቲካ ሰው ፣ ሰውን ከመደብ አንፃር — ከበርቴና ሰርቶአደር በማለት ይመድባል ። የቤተ ክህነት ሰው ደግሞ—ምእመናንና ናፋቂ (መናፈቅ) ፤ ወይም እርቶዶክስ፣

[8] ‘ሠርቶአደር’ ቅፅ 3 ፣ ቁጥር 90 ፣ ሰኔ 9/1974 ፣ ገጽ 3 ።

ካቶሊክ ፣ ፕሮቴስታንት ወዘተ . . . በማለት ይደለድላል ። እመዳደባቸው እየራሳቸውን ከሚመለከታቸው የፍላጎት አኳያ ነው ማለት ነው ።

ድልደላ ጠቃሚ እንዲሆን ፣ አንዳንድ አስፈላጊ መመሪያዎችን መከተል ይኖርበታል ። (1) በአንድ መደብ የተሰለፉ ሁሉ የሚመሳሰሉበት የጋራ ባህርያት እንዲኖራቸው ያሻል (2) ከሚመሳሰሉባቸው ባህርያት ውስጥ በየመደቡ የሚደለደሉበት በየተራ በየአንዳንዱ የጋራ ባህርይ ብቻ መሆን ይኖርበታል ። ለምሳሌ ከላይ የጀመርነውን ብንጨምርበት ፣




ከዚህ እንደምንመለከተው ፣ መደብ አንድ ፣ ከበርቴን በሁለት አይነት ይከፍለዋል ፣ አከፋፈሉ በአይነት ነው ። መደብ ሁለት ደግሞ ፣ የመሬት ከበርቴን እንደገና በሁለት ይከፍለዋል ፣ ይኸኛው ደግሞ በዜግነት ነው ። ማለትም ፣ በ(1) እና በ(2) ቁጥር የተመለከቱትን መመሪያ



ዎች ያሟላሉ ። ስለዚህም የድልደላ ስልት ጠቃሚ እንዲሆን የፍላጎት አኳያን ማወቅና መመሪያዎችን መከተል ያስፈልጋል ።

ታዲያ እንዲህ አይነቱ የድልደላ ስልት፣ለድርሰት አፃፃፍ ምን ይጠቅመናል ? የድልደላ ስልት የሚጠቅመን በአእምሯችን የሚገኘውን ስርአት የለሽ ፣ የምንፅፍበትን ድርሰት ርእስ ይዘት ስርአት ለመስጠት ነው ። የድልደላ ስልት አስተዋፅኦ (ንድፍ) እንደማውጣት ስለሆነ ። በትርጓሜ ስልት አቀናብረን የምናገኘው መግለጫ ተስፋፍቶ ድርሰት እንደሚወጣው ሁሉ በድልደላ ስልት ተከፋፍሎ የተገኘው ሲዛመድ አንድነት ያለውና የተዋሃደ ድርሰት ይወጣዋል ።

<u>አበረጅ ፤</u>

## ገ በ ሬ

ገበሬ አይነት አይነት አለው ፤ ምስጉን ገበሬ አለ ፣ ሰነፍ ገበሬ አለ ፣ ሌላም ሌላም አይነት ሊኖር ይችላል ፤ ከሁለቱ አከፋፈሎች እምብዛም ባይርቅም ። ከምስጉን ገበሬ ፣ የተሰጠውን ማሳ አቀላጥፎ በማረስ ተገቢውን ሰብል እንዲያስገኝ ከሚያደርገው እንስቶ ፣ ከማሳው ውጪ በተጨማሪ በማረስ ዞላ የዋለውን (ስራ የፈታውን) መሬት ምርታማ እስከሚያደርገው ድረስ ። ከሰነፉም እንዲሁ ለእጅ ወደ አፍ ለሆነው ኑሮው ያህል ብቻ ከሚጫጭረው እንስቶ ለዚህም ሳይበቃ ቀርቶ ቧገታ (ልመና) እስከሚሰማራው ድረስ ።

<u>ስለ ሰነፉ ገበሬ እምብዛም መናገር አያሻም ። ሆኖም የእርሻን ስራ ጨርሶ ከሚጠላው</u> እንስቶ <u>የአካባቢ ሁኔታዎችን እንደ ምክንያት በመውሰድ እስከሚሰንፈው ድረስ</u> የተለያዩ መልክ እንዳለው ማጤኑ ገበሬን ሰፋ

አድርጎ ለመመልከት ይረዳናል ። በአካባቢ ምክንያቶች ከሚሰንፈው ውስጥ ፣ ለምሳሌ በየቤተክርስቲያኑና በየመስጊዱ በማውደልደል ጠበል ጠዲቅ ወይም ምፅዋት ያለበትን በማነፍነፍ ጊዜ ስለሚያሳልፍ የሚሰንፍ አለ ። ከወር እስከ ወር ያሉትን ቀኖች አከባሪ ሆኖ ለመታየት በመሻት ዛሬ ማሪያም ፣ ነገ ሀዋሪያት ፣ ተነገወዲያ ጊዮርጊስ በማለት የሚሰንፍ አለ ። የሰፈር ሽማግሌ ፣ የገበሬ ማህበራት ተሳታፊ በመሆን ስብሰባዎችን ስራ ያስፈቱት በማስመሰል የሚሰንፍ አለ ። ግማሽ ጎኑ ነጋዴ ፣ ግማሽ ጎኑ ሽማኔ፣ ግማሽ ጎኑ ደብተራ ወይም ቄስ በመሆን የሚሰንፍ አለ ። የባላባትነት አጉል ኩራት ተከምሮበት የእርሻን ስራ ባለመፍቀድና፣ 'አፈር ገፊነት አይሆነኝም' እያለ በማጥላላት የሚሰንፍ አለ ። በእርጅና ፣ በበሽተኛነትና በአቅመ ደካማነት ምክንያቶችም የሚሰንፍ አለ ። በሌላ በኩል ደግሞ ፣ ከላይ እንደተመለከትነው የእርሻን ስራ ጨርሶ የሚጠላ አለ ። ሌላም ሌላም አይነት ሊኖር ይችላል ። ስለሆነም እንደነዚህ አይነቱ ገበሬ የሀገር ሸክም ፣ የገበሬ ማህበራት ነቀርሳ ስለሆነ የሚሻሻልበትን ካልሆነም የሚወገድበትን ከመሻት በስተቀር ደበሎ ሰቅለን ልንናገርለት አይገባም ። በሀገራችን መኖሩን መናገሩም እስነዋሪና አሳፋሪ ስለሚሆን ።

ሌላው አይነት — ማለትም ምስጉን ገበሬ ግን የሰርቶ አደሩ አለኝታ ፣ የሀገሩ መከታ በመሆኑ ስለሱ መናገር ብቻ ሳይሆን ልናመሰግነውና ልናወድሰው ይገባል ። እንደዚህ አይነቱ ገበሬ ለእርሻ ስራ ፍቅር ያለውና ያለ እርሻ ሌላ ስራ ያለ የማይመስለው ፣ ከመሬት ጋር የተቆራኘ ህይወት የሚኖር ነው ። ይኸም እንደላይኛው የተለያዩ አይነት አለው ። አንዳንዱ ራሱን ግብርናን ፣ ሌላው የገጠር ሰዎችን ፣ ሌላው ደግሞ የገጠር ኑሮን ከመውደዱ የተ



ነት ሊሆን ይችላል ፣ ገበሬ ሲሆን የበታው ። በመሆኑም እንደ ውዴታው አይነት ምስጉንነቱ ይለያያል ።

ራሱን ግብርናን የሚወደው የግብርናን ስራ አሟልቶ ከማወቁ የተነሳ በግብርና ልክ አውቆት የሚሰማራበት ሌላ ማደሮ ያለና የሚገኝ የማይመስለው ችሎታ ያለው ገበሬን ፣ ብርቱና ታታሪ ገበሬን እና ውጤት አልባ የሆነ ለፍቶም ቋቱ ጠብ የማይልለትን ጎድፋሪ ገበሬን ያጠቃልላል ።

ችሎታ ያለው ገበሬ መሬትን ለም — ለም ከጠፍ — ጠፍ ብሎ በመደልደል ከማወቁም ባሻገር የመሬትን ብልትና አገልግሎት ያውቃል ። ለእርሻና ለከብት ርቢ የሚሆነውን ፣ ውሃ የሚገኝበትን ፣ ሳር የሚያመችበትንና ሰብል የሚገማሽርበትን መሬት ለይቶ ይመርጣል ። እምራጭ ላይ ቢወድቅም ፣ በበረሃው የመስኖ ውሃ በማስገባት ፣ በየተራራውና በየተዳፋቱ እርከኖች እያበጀ አፈር እንዲታገድ ውሃ እንዲከተር በማድረግ ፣ በየረባዳው ረግረጉን መሬት በመጎደብና በማድረቅ በመሬት ማልሚያ ጥበብ ይጠቀማል ። ከዚያም መሬቱን በመመንጠር ፣ በመሰንጠቅ ፣ በማረስ ፣ ጓሉን በመከስከስ ፣ አፈሩን በማድቀቅና እንዳስፈላጊነቱም ፍግ እበትና የከብት ርጋጭ ወይም የእንዱስትሪ ውጤት ማዳበሪያ በመነስነስ ለዝሪት ያዘጋጃል ፣ ይዘራል ፣ ያርማል ፣ ይኮተኩታል ፣ በመጨረሻም ያመርታል ።

ችሎታ ያለው ገበሬ ፣ መሬት ለማረሻ ያለውን ጥናት ወይም ገርነት ፣ ለስላሳና ጥቁር መሬት ተጨፍልቆና ታርሶ ሲቆይ ፈጥኖ ዘር እንደሚቀበል ፣ መረሬ መሬት ውሃ እንደማይቋጥር እንደሚጠነክርና በደበልጥ ጉስላ እንደሚያስፈልገው ያውቃል ። መሬትን ማከር (ሰብልን እያፈራረቁ) መዝራት ያረጀ መሬትን ለማደስ አይነተኛ መን

ገድ መሆኑን በመረዳት ሰብሎቹን እያፈራረቀ ይዘራል ። ቅጠላቸው ፈጥኖ የሚሰፋፉ የሳር አይነቶችን(ማገጥና ባላ በባ ሳሮችን የመሳሰሉትን) በመዝራት ለምለም ማዳበሪያ በማድረግ ገልብጦ እያረሰ ወይም ለከብት መኖ እያዘጋጀ ይጠቀማል ።

ችሎታ ያለው ገበሬ የአየር ንብረትን ሁኔታ በቅርብ ይከታተላል ፣ ዳመና ፣ ጉም ፣ ውርጭና ዝናብ ፣ ሙቀትና ቅዝቃዜ ድርቅና ሙቂነት የሚያስከትሉትን ጥቅምና ጉዳት በመረዳት ምን ጊዜም ለየሁኔታው መቋቋሚያ ይሆናሉ ብሎ የሚገምታቸውን ዘዴዎች በቅድሚያ በማዘጋጀት ይጠብቃል ።

ችሎታ ያለው ገበሬ የዘር አመራረጥ በቂ ልምምድ ያለው ነው ። ምን አይነት የብርእ እህል ፣ ያበባ እህል ወይም ያገዳ እህል በምን አይነት ቦታና የአየር ንብረት ተዘርቶ ምን እንደሚያስገኝ ፣ ምን አይነት የጓሮ አትክልት በእንዴት ያለ ቦታ መተከል እንዳለበት ፤ የጭረት ፣ የቅባት ፣ የቀለም ፣ የቅመምና መአዛ የሚሰጡ በቀልቶች ፣ እንዲሁም የከብት መኖ የሚሆን አዝርእት በየትኛው አየር ንብረትና በየትኛው ቦታ ላይ ይበልጥ እንደሚናችና እንደሚስማማው በልምድ ወይም በትምህርት የደረሰበት መሆኑን በተግባር ያስመሰክራል ..................

ሌላው ብርቱና ታታሪው ገበሬ ..........................................[9]

(መ) <u>የአብነት (ምሳሌ) ስልት</u>

የአብነት ስልት ፣ ከትርጓሜ ስልትና ከድልደላ ስልት ጋር ይመሳሰላል ። በትርጓሜ ስልት አንድ ጉዳይ (ግለነገር) ወይም ቡድን ካጠቃላይ መደቡ ጋር ያለውን ዝምድናና የሚለይበትን ብቸኛ ባህሪ ስንገልፅ ፣ በድልደላ ስልት በተመሳሳይ ባህርይ መሰረት በየአጠቃላይ መደቡ የሚሰባሰቡትን ወላጅና ተዋላጆች ( ግለነገር ወይም ቡድን) እንደረድራለን ። በአብነት ስልት ደግሞ አንድ ነገር አጠቃላዩን መደብ እንዲያብራራልን እናደርጋለን ። በማስረጃው እንዲብራራ የሚፈለገው ሰው ፣ ግለነገር ፣ የአሰራር መንገድ ፣ ሁኔታ ፣ ድርጊያና የመሳሰለው ሊሆን ይችላል ። ማስረጃው ፣ የራሱ የሆነ በአንባቢው ወይም በሰሚው ዘንድ እሱነቱን ለይቶ የሚያሳውቅ ግለኛ ባህሪ ሊኖረው ሲገባ ፣ በሌላ በኩል ደግሞ የመደቡን ተፈላጊ አበይት ባህሪያት መወከል አለበት ።

<u>አስረጅ ፤</u>

. «ማንኛውም ግለሰብ ፣ ማኅበራዊ ቡድን ወይም መደብ በዘመኑ ኅብረተሰብ ኑሮ ላይ የሚያደርገው ተጽእኖ ይኖረዋል ፤ ተጽእኖው አፍራሽም ገንቢም ሊሆን ይችላል ። በአፍራሽነቱ የሚጫወተው ሚና በኅብረተሰቡ ዘንድ ውጉዝ ስለሚያሰኘው ከያዝነው ርእስ ጋር ካለመዛመዱም በላይ ተቃራኒ ነው ። እንዲያውም ለኅብረተሰቡ ደህንነት የሚቆሙት ክፍሎች አንዱ ሚና በአፍራሽነት የተሠለፉትን ኃይሎች መዋጋት ነው ። ስለሆነም አንድ ተግባር የመሥዋእትነት ሚና የሚኖረው የኅብረተሰቡን ኑሮ ወደፊት በማራመድ ረገድ በሚያደርገው አስተዋጽኦ ነው ። ለዚህ አስተዋጽኦ የሚቆም ግለሰብም ሆነ መደብ ባለበት ዘመን ይብዛም ይነስ ላካባቢው ፣ ለመደቡ ፣ ላገሩ ፣ ብሎም ለዓለም ኅብረተሰብ ዕድገት የሚከፍለው መሥዋዕትነት አለ ማለት ይቻላል ። መሥዋዕትነትን የሚከፍለው ክፍል ተግባር እንደየዘመኑና እንደየኅብረተሰቡ የዕድገት ደረጃ ሊለያይ ይችላል ። በአንድ ወቅት አገሩን ከውጭ ወራሪ ኃይል ለመከላከል ፣ በሌላ ወቅት በአገሩ ውስጥ የሚነሡትን የመከፋፈል ፣ የረሃብና በጠቅላላውም

[9] ከአዘጋጁ

የኋላቀርነት ችግሮችን ለማስወገድ ወይም እነዚህን ሁሉ ች
ግሮች የተወጣ ኅብረተሰብ ከሆነማ ለላቀ የዕድገት ደረጃ
የሚከፍለው መሥዋዕትነት አንድን ኅብረተሰብ ካለበት
ችግር ለማላቀቅ አለዚያም ከፍተኛ ዕድገት እንዲጐናጸፍ
ለማድረግ ይሆናል ፡፡ ችግሮቹን ለማስወገድም ሆነ ተፈላጊ
ውን የዕድገት ደረጃ ለመድረስ ህብረተሰቡ የሚገኝበትን
የዕድገት ደረጃ መገምገምና መረዳት ከመሥዋዕትነቱ የሚ
ቀድም ተግባር ይሆናል ፡፡

«መሥዋዕትነት የተለያዩ ደረጃዎች ሊኖሩት ይችላል፡
በተለያዩ አገሮች ወይም መደቦች መካከል በሚደረገው
ጦርነት ውስጥ በቀጥታ በመሳተፍ ለጦሩ ስንቅና ትጥቅ
በማቀበል ፣ ደም በመለገስ ፣ የዘማቹን ቤተሰብ በመንከ
ባከብ ተሳትፎ ማድረግ ከጦርነቱ ጋር የተያያዘ መሥዋዕ
ትነት ነው ፡፡ የኅብረተሰቡን ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ
እርምጃዎች ለማሳደግ በተለያዩ ሕዝባዊና የሙያ ማኅ
በራት ውስጥ በፈቃደኝነት ያለ ክፍያ በመሥራት የሚ
ደረገው አብዮታዊ አስተዋፅኦ የመሥዋዕትነት አንዱ
ገጽታ ነው ፡፡ መሥዋዕትነት በአንድ አገር ክልል ብቻ
የተወሰነ ላይሆን ይችላል ፡፡ ሰፊው ሕዝብ በአገሩ አድ
ኃርያን ላይ የሚያገኘው ድል የአድኃርያን ኃይል በመ
ናዱና የጭቁኖችን የበላይነት በማጠናከሩ ከዚያ አገር
ድንበር ውጭ ላሉ ጭቁን ሕዝቦችም አስተዋፅኦ ያደር
ጋል ፡፡ ሶቪዬት ኅብረት በሁለተኛው የኢምፔሪያሊስቶች
ጦርነት ያጣችው የሀያ ሚሊዮን ሕዝቧ ሕይወት አገሯን
ብቻ ሳይሆን ጠቅላላውን ያለም ሕዝብ ከፋሺስቶች ነፃ ለማ
ውጣት የከፈለችው የመሥዋዕትነት ዓለማቀፋዊ መልኩ
ነው ፡፡ በዓለም አቀፋዊነት መርህ በመመራት ከኢትዮ
ጵያውያን ጐን በመሰለፍ ደማቸውን ያፈሰሱት የኩባና
የዴሞክራቲክ የመን አብዮተኞች መሥዋእትነት የኢትዮ



ጵያን አብዮት ለማራመድ ነው ፡፡ ዛሬ እጅ አዙር ቅኝ
አገዛዝን ፣ ጽዮናዊነትን ፣ አፓርታይድን ፣ ፋሺስታዊ
አስተዳደሮችንና የኢምፔሪያሊስቶች የጦርነት ትንኮሳን
የሚቃወሙ ኃይሎች ካገራቸው ጥቅም ጋር በቀጥታ
የተያያዙ ጉዳዮች ስለሆኑ ሳይሆን ለዓለም አቀፋዊነት
የሚያደርጉት አስተዋፅኦ ነው ፡፡

«የኢትዮጵያ ሕዝብ ፣ በተለያዩ ዘመናት ከውጭ ተስፋ
ፊዎች ፣ ቅኝ ገዥዎችና ፋሽስቶች ጋር ባደረጋቸው ትግ
ሎች በከፈለው መሥዋዕትነት ያገሪቱ ነፃነትና አንድነት
እስከዛሬ ድረስ ተጠብቆ ቆይቷል ፤ ይህም ባብዛኛው
ያለፉት ትውልዶች ታሪካዊ ተግባር ነበር ፡፡ ያገሪቱን ነፃ
ነት የመጠበቅ ጥያቄ ገና ወዝአደሩ ባልተፈጠረበት
ዘመን ባብዛኛው በአርሶ አደሩ ትከሻ ላይ የወደቀ ኃላፊ
ነት ነበር ፡፡ አርሶ አደሩ ይህንን ሚና ሊጫወት የቻለው
በዘር ፤ በሃይማኖት ወይም በሌላ ሳይከፋፈል ፤ ለዓላማው
መሳካት ባንድነት በመቆሙ ሲሆን በዚህም የመሥዋእ
ትነቱን ፍሬ ለማየትና ለዛሬውም ትውልድ ለማስተላለፍ
በቅቷል ፡፡

«ይህ ቀደምት አበው የተሰውለት የሕዝቡ አንድነትና
ነፃነት ጥያቄ አገሪቱ በሥርነቀል አብዮት ውስጥ በመሆኗ
ካለፈው ይበልጥ የተወሳሰበ መልክ ይዞ ተከስቷል ፡፡
ስለሆነም አዲሱ ትውልድ በዘመኑ ካጋጠሙት ችግሮች
በተጨማሪ ያባቶቹን አርማ እንዲያነግብ የአድኃርያን
ግፊት አስገድዶታል ፡፡ በመሆኑም ጓድ ሊቀ መንበር
እንዳሉት ‘. . . ዛሬም አብዮታዊ ሠራዊታችን በየ
ግንባሩ ለዚህ አብዮት ደህንነትና ለሀገሪቱ ህልውና
ይህንን አድርጐልኝ ፤ ይህ ጐደለኝ ፤ ሰለቸኝ ፤ ሳይል የሰ
ፊውን ሕዝብ አርማ አንግቦ ከአብዮቱና ከሕዝቡ ፀሮች
ጋር እየተዋደቀ ነው ፡፡’ ይህ የህይወትን አሳልፎ የመስ

ጠት ፈቃደኝነት አንድ ዜጋ ለኅብረተሰቡ ከሚከፍለው
ዋጋ ሁሉ የላቀ ፤ እበው 'መብራት ራሱ ነዶ ለሌላው
ያበራል' የሚሉት አባባል በተግባር የሚገለጥበት ፤ ገሀድ
መስዋዕትነት ነው ። ስለዚህ ዛሬ ለኢትዮጵያ ጭቁን
ሕዝቦች ከቆመ መደብ ለዚህ ትግል መሳካት የበኩሉን
መሥዋእትነት እንዲከፍል ይጠበቅበታል ። የዚህ ትግል
ውጤት ባብዛኛው ለዛሬው ሳይሆን ለሚቀጥለው ትውልድ
ነው ። ይህ ደግሞ ከግለኝነት ፍጹም ነፃ ከሆነ ወገን ብቻ
የሚገኝ ተግባር በመሆኑና የተግባርም ፍሬ ከአገሩ ድን
በር አልፎ ለሌሎች ኅብረተሰቦችም ስለሚተርፍ መስዋ
ዕትነቱ ዓለምአቀፋዊ ያሰኘዋል ። መሥዋዕትነትንም የሚ
ከፍለው ክፍል ተግባሩን ከተለመው ዓላማ ጋር በማወዳ
ደር ሲመዝነው ይከራበታል ...» [10]

«... ማኅበራዊ ጠንቆችን ለመከላከልና ለማስወገድ
የሚወሰደው እርምጃ ከኤኮኖሚው አጠቃላይ እድገት
ተነጥሎ የሚታይ ባይሆንም ለጊዜውና በአጭር ጊዜ
ዕቅድ ምን መደረግ አለበት ለሚለው ልዩ ልዩ ዘዴዎችን
በመቀየስ ችግሩን ለመቀነስ ጥረት መደረግ እንደሚኖ
ርበት ሁኔታዎች ያመለክታሉ ። በተለይም ዝሙት አዳ
ሪነትን ፣ ቦዘኔነትንና ወንጀለኝነትን የመሳሰሉትን ማኅ
በራዊ ጠንቆች ለማስወገድ ከቻሉት ሶሻሊስት አገሮች
የሥራ ልምድ በመቅሰምና አስፈላጊውን ጥናት በማድ
ረግ ጠንቆቹን ደረጃ በደረጃ ለመከላከል ከፍተኛ ትግል
መደረግ ያለበት መሆኑን ጥናቶች ይጠቁማሉ ።

«ለምሳሌም ያህል ኩባ ፣ ከአብዮቱ ማግስት ጀምሮ
እርሻና ኢንዱስትሪን በሶሻሊስት መስመር ለመገንባት
ያደረገችው ጥረትና ለማኅበራዊ አገልግሎቶች መስፋፋት

[10] 'ሠርቶአደር' ቅጽ 4 ፣ 108 ፣ 'መስከረም' 20/1975 ፣ ገጽ 3 ።



የሰጠችው ትኩረት ብዙ የሥራ መስኮችን ለመክፈትና
የሥራ አጥነትንም ችግር ደረጃ በደረጃ ለማስወገድ አስ
ችሏታል ። በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ በተለይ የሙያ ዕውቀት
የሯቸው ሥራ ግን የሌላቸውን በትምህርት ፣ በጤናና በሌ
ሎች የማኅበራዊ መስጫ ተቋሞች ውስጥ ገብተው እን
ዲሠሩ መደረጉ ለችግሩ ዘላቂ መፍትሄ ሊያስገኝ ችሏል ።
በተጨማሪም አዳዲስ ትምህርት ቤቶች መከፈታቸውና
ከውጭ አገሮች የተገኘውን የነፃ ትምህርት እድል አገሪቷ
በሚገባ ለመጠቀም መቻሏ ለብዙ ሥራ አጦች የትምህርት
እድል አስገኝቷል ።

«የቬየትናም ሕዝባዊት ሪፐብሊክም ተመሳሳይ የሆነ
ሊጠቀስ የሚገባው ታሪክ አላት ። ደቡብ ቬየትናም ከአሜ
ሪካን ኢምፔሪያሊዝም መዳፍ ተላቃ ስትወጣና ለሁለት
እንድትከፈል ተደርጋ የነበረችው ቬየትናም አንድ ስት
ሆን በሳይጎን ከተማ ከግማሽ ሚሊዮን የሚበልጡ ሴትኛ
አዳሪዎችና በሚሊዮን የሚቆጠሩ ሥራ አጦች ይገኙ
ነበር ። የቬየትናም መንግስትና ሕዝብ በወሰደው ቆራጥ
እርምጃ በተለይ በሴትኛ አዳሪነት ዝቃጭ ኑሮ ይኖሩ
ለነበሩት የተሀድሶ ፕሮግራም በማዘጋጀት ፣ የልማት
ሥራዎችን ፣ ፋብሪካዎችን ፣ እርሻዎችንና አነስተኛ የእደ
ጥበብ ተቋሞችን በማስፋፋት በሥራ ላይ እንዲሰማሩ
አድርጉአል ።

«ወደ ሶሻሊስት ኅብረተሰብ በሚደረገው ግስጋሴ
እንደ ሥራ አጥነትና ሴትኛ አዳሪነት የመሳሰሉት ማኅበ
ራዊ ችግሮችና ጠንቆች ደረጃ በደረጃ እየተወገዱ የሚሄዱ
እንጂ በአንድ ጊዜ የሚጠፉ አይደሉም ። ስለሆነም እነ
ዚህ ችግሮች ዛሬም በአገራችን ጐልተው የሚታዩ ዐቢይና
አሳሳቢ ሁኔታዎች መሆናቸውን መገንዘብ ያስፈልጋል ።
ጓድ ሊቀ መንበር መንግሥቱ ኃይለማርያም ለኢሠፓአኮ

ማዕከላዊ ኮሚቴ 2ኛ መደበኛ ስብሰባ ባቀረቡት ሪፖርት ላይ 'ማኅበራዊ ችግሮቻችን በምርት ኃይሎች ዕድገት እየተወገዱ የሚሄዱ ቢሆንም እጅግ አሳሳቢ የሆኑት በተቻለ መጠን የሚቃለሉበትን ሁኔታ መሻት ቸል ሊባል የማይገባው ነው ። ማይምነትን የማስወገዱን ዘመቻ ማጠናከር ፣ በተላላፊ በሽታዎች ላይ መዝመት ፣ ሥራ አጥነትን ለማቃለል ተገቢ ትኩረት መስጠትና የማንባታው ትግላችን ፀር የሆኑትን ለሕዝብና ለመንግሥት ንብረት እንክብካቤ አለማድረግን ፣ ጉቦና ስርቆትን መዋጋት ፣ በአጸንሩም ቁጠባና ምርታማነት እንዲዳብር ማድረግ በማኅበራዊ ረገድ ከፍተኛ ትኩረት ሊሰጣቸው የሚገባ አበይት ጉዳዮች ናቸው' ብለዋል ። የመደብ ጠላቶቻችን ግን እንዲህ ያሉትን ችግሮች ሊፈቱ የማይችሉና በሕዝብ ላይ ሆን ተብሰው የተጫኑ አድርገው ለማቅረብ ይሞክራሉ ። ሐቁ ግን ይህ እንዳልሆነ ከሚከናወኑት ተግባራት ማየት ይቻላል . . . »[11]

(ሰ) <u>የማመሳሰልና የማነፃፀር ስልት</u>

ማመሳሰልና ማነፃፀር ወደ አንድ የተቋጨ አላማ ማምራት አለበት ። ዳመናው እንበሳ ይመስላል ብንል የማመሳሰሉ ተግባር ስለ ዳመናውም ሆነ ስለ አንበሳው የሚያስተምረን ነገር የለም ። የዚህ ስልት ዶግሞ አቢይ አላማው የሚያውቁትን ከማያውቁት ጋር በማመሳሰልና በማነፃፀር የማያውቁትን እንዲያውቁ ለማድረግ ነው ።

(1) ማንኛውም ነገር ከተለያዩ አቅጣጫዎች እየታሰበ የተለያዩ ፍላጎትን እንዲያሟላ ሆኖ ሊቀርብ ይችላል ። ስለሆነም ያንን መመልከቻ አኳያ መወሰን ያስፈልጋል ።

[11] 'መስከረም' ቅጽ 3፣ ቁጥር 12፣ ታኅሣሥ - መጋቢት 1975 ፣ 102 - 3 ።



ለምሳሌ ከገበሬ አኳያ ከሆነ ፣ በገበሬው ልምድ እንፃር መታየት ይኖርበታል — ገበሬው አንድን መሬት ለም ፣ ለም ከጠፍ ፣ ጠፍ ብሎ በመመደብ ፣ ለሙን መሬት ከዚያ በፊት ከሚያውቀው ለም ወይም ለም ከጠፍ ወይም ጠፍ ጋር በማወዳደር ፣ ሊያስገኝ የሚችለውን ሰብል ወይም ለማቅናት የሚፈጀውን ማዳበሪያ ፣ ወይም እነዚህን የመሰሉ ሌሎች ጉዳዮችን ሊገመግም በሚችልበት አይነት ። ወይም ይኸንኑ መሬት ለኢንዱስትሪ ከማቋቋሚያነት አኳያ ለማየት ይቻላል ። በዚህ ረገድ የሚገመግምም ሰው ቢሆን የሚመለከተው ያው ከባለኢንዱስትሪው ልምድ አኳያ ነው መሆን የሚኖርበት — ከዚያ በፊት የሚያውቀውን የኢንዱስትሪ ስፍራ ከአሁኑ ጋር በሚያመሳስልና በሚያነፃፅር አይነት ። ለማንኛውም ፣ ስልቱ እንዲሰምር ከተፈለገ ፣ አኳያው ግልፅ እንዲሆን ያሻል ።

(2) ማመሳሰሉና ማነፃፀሩ ለምን እንዳስፈለገ መታወቅ ይኖርበታል ። (ሀ) የማይታወቀውን ከሚታወቀው ጋር በማነፃፀር የማይታወቀውን ለማወቅ ። (ለ) ካጠቃላይና ከታወቁ ባህርያት በመነሳት ፣ ያልታወቁት ግለነገሮች ባህርያት በታወቁት አጠቃላይ ባህርያት ውስጥ ይካተቱ አይካተቱ እንደሆነ ለመገምገም ። (መ) ግለነገሮችን እየተነተኑ አቅርቦ ያላቸውን አጠቃላይ የጋራ ባህሪ (ሀሳብ) ለማግኘት ።

እኳያን የመወሰንና የአኳያውን ግብ የማወቅ ዘዴዎች በማመሳሰልና በማነፃፀር ስልት ለሚቀርቡ ፅሁፎች ወሳኝነት አላቸው ።

## አስረጅ ፤

. «...'ማናቸውም አይነት ደንብ ለዘወትር የሕዝብ ጥቅም አይሆንም ። የሚጠቅምበት ጊዜ አለው ። አንዱንም ሕዝብ የሚጠቅም ደንብ የሌላውንም ሕዝብ ሁሉ ሳይ ጠቅም አይቀርም አያሰኝም ። ስለዚህ ቀጥሎ የተፃፈውን ቃል ለመናገር ይቻለናል ፤ ደንብ ሁሉ ምንም ቢጠቅም በተለየ ጊዜያት ውስጥና ለተለየ ህዝብ ብቻ ነው ።'

«... ከላይ ካሰፈርነው አባባላቸው ማየት እንደ ምንችለው ፣ ነጋድራስ በሌላ አገር የሆነው ሁሉ በኛም አገር መሆን አለበት የሚሉ ጭፍን ተሟጋች አይደሉም ። ነገሮችን ከጊዜና ከቦታ አንጻር የሚያዩ ናቸው ። ይህም ችሎታቸው ነው ከፍተኛ የአስተሳሰብ ተጽእኖ ካሳደሩ ባቸው ከእንደነዴቪድ ሪካርዶና ከመሳሰሉት ምሁራን «ነጻ »የውጪ ንግድ ፖሊሲ ይልቅ የንግድ መከላከል ፖሊሲን በመምረጥ እንዲያፈነግጡ ያደረጋቸው ። ደግ ሞስ የሁሉንስ ኢኮኖሚ አስተሳሰብ የሚወስነው የሚ ወክሉት መደብ ወይንም ወገን ጥቅም አይደለምን ። አሜሪካዊው ቤንጃሚን ፍራንክሊን አሜሪካ ውስጥ ለወ ረቀት ገንዘብ ብርን ተክቶ መሥራት የተሟገተው ወደ እንግሊዝ አገር ይጐርፍ የነበረውን ወርቅና ብር ለማስ ቀረት አይደለምን ? ፈረንሣዊው ቡስገርልበርት ብርና ወርቅን ረግሞ እንደ ገንዘብነታቸው የሚሰጡትን አገል ግሎት መኪድ ደረጃ የደረሰው በሉዊ 14ኛ አካባቢ የተኰ ለኮሉት መሳፍንት ለብርና ወርቅ ያደርጉ የነበረው መስገ ብገብ እንገሽግሾት አይደለምን? እነ ዴቪድ ሪካርዶስ



ቢሆኑ ለነፃ የውጪ ንግድ ፖሊሲ ሽንጣቸውን ገትረው የተሟገቱት በወቅቱ እንግሊዝ በኢንዱስትሪ ከሌሎች አገሮች በሙሉ በተሻለ ደረጃ....... ላይ መገኘቷ በሚ ደረገው ልውውጥ ለእንግሊዝ ይጠቅማታል በሚል እም ነት አይደለምን? እንዲያው ለምሳሌ ያህል ጠቃቀስናቸው እንጂ የየትኛውም የታወቀ ምሁር ጥናት ከዚህ እውነታ ውጪ አይደለም ። ነጋድራስም እንደዚሁ ። ነጋድራስ በተለያየ እድገት ደረጃ ላይ በሚገኙ አገሮች መካከል ያለው የኢኮኖሚ ግንኙነት በተለይም በንግዱ መስክ ያለው ምን እንደሚመስል ከማሳየታቸው በፊት ስለል ውውጥ አጠቃላይ አስተያየት ይሰጣሉ ። እንጠቅሳለን ፤

'መለዋወጥም የሰው የተፈጥሮ ባህሪ መሆኑ ከሰው ኑሮ ውስጥ ማናቸውንም አንዳች ነገር አስተውለን ብን መለከት እንረዳለን ። ባልና ሚስት ከዳጅና ከቤት ሆነው ሠርተው የሠሩትን ሥራ ይለዋወጣሉ ። አባትና እናትም ልጆቻቸውን መግበው ስላሳደጉ ልጆቹ ሲያድጉ በሥራ ይረዳሉ ።........ ብረት ሠሪውም ማረሻ አብጅቶ ጤፍ ይቀበላል ። አራሹም ጤፍ ሰጥቶ የተሻለ ማረሻ ያገኛል ። ዕውቀት ባለው ሕዝብ መካከል ግን በከንቱ የሚሰጥ የለም ። በከንቱም የሚበላ ሰው የለም ። የሁሉም ትዳሩ ተለዋውጦ ነውና እንካ ሥራ አምጣ ሥራ ይባላል ። ይህ ሳይሆን ቀርቶ በላተኛው ከሠራተኛው ሲበዛ በማናቸውም ቤት ሀብት ሊገባ አይችልም ...'

«እንግዲህ አባባላቸውን በሰፊው መጥቀሳችን ያለ ምክንያት አይደለም ። ልውውጥን በሚመለከት ያላቸውን አስተሳሰብ በተጠቃለለ መንገድ ለማየት እንድንችል ነው ። በቅድሚያ መለዋወጥ የተፈጥሮ ባሕሪ ነው ያሉት ትክክል መሆን አለመሆኑን እንመልከት ። መለዋወጥ ባንድ በተወሰነ የኅብረተሰብ እድገት ደረጃ የተከሰት

ታሪካዊ ፈረጅ እንጂ ከሰው ተፈጥሮ ባሕሪ ጋር ተያይዞ የሚቀርብ ዘለዓለማዊ ፈርጅ አይደለም ። በጥንታዊ የጋርዮሽ ሥርዓት ማህበር የምርት ኃይሎች እጅግ ዝቅተኛ እድገት ደረጃ ላይ የሚገኙ በመሆናቸው ጥንታዊው ሰው ኑሮውን ለማሸነፍ ከተፈጥሮ ጋር በሚያደርገው ትንቅንቅ ጉልበቱን እንዲያስተባብር ይገደዳል ። ይህ የጋራ ሥራ ደግሞ በምርት ማከናወኛ መሣሪያዎች ላይ የጋራ ባለቤትነት እንዲሰፍን ያደርጋል ። ምክንያቱም ማንም አንድ ግለሰብ ለብቻው የማምረት ተግባር ሊያከናውን ስለማይችል ነው ። በአደንም ሆነ በፍራፍሬ ለቀማ ላይ የሚሠማሩት ሌላው ቢቀር የዱር አራዊቶች የሚያደርሱባቸውን ጥቃት እንኳን ለመከላከል ኃይላቸውን እንዲያቀናጁ ይገደዳሉ ። በዚህ የኅብረተሰብ የእድገት ደረጃ የሚኖረው የሥራ ክፍፍል በተፈጥሮ ላይ የተመሠረተ ነው ። በዚህ አኳኋን በአደኑም ሆነ በፍራፍሬና ሥራ ስር ለቀማ ላይ የተሰማሩት በጋራ ያፈሩትን ምርት የኮሚዩኒቲው አባላት ይሰጣጣሉ ወይንም በጋራ ይከፋፈላሉ እንጂ እያንዳንዱ በግል ያመረተው ኖሮት ተመጣጣኝ ለውጥ የሚጠይቅበት መሸቃቀጥ የሚካሄድበት ደረጃ አይደለም ። ለውውጥ እንዲኖር ካርል ማርክስ እንዳስቀመጠው ፤

‘1ኛ ፣ ምንም ዓይነት ለውውጥ የታሪካዊ ሂደት ውጤትም ሆነ ወቅቱን ጠብቆ የመጣ ከስራ ክፍፍል ውጪ ሊኖር አይችልም ። 2ኛ ፣ ግላዊ ለውውጥ የግላዊ ሥራ መኖርን ይጠይቃል ። 3ኛ ፣ የአንድ ለውውጥ ደረጃ ስፋቱና ባሕርይው የሚወሰነው ባጠቃላይ በምርቱ እድገትና አቋም ጭምር ነው ።’

እንግዲህ በግል መለዋወጥ እንዲኖር የሥራ ክፍፍል መኖሩ ብቻ ሳይሆን ሥራም ግላዊ ጠባይ መውሰዱም እንዲሁ የግድ ነው ማለት ነው ። ይህ ደግሞ መሆን



የሚችለው የምርት መሣሪያዎች በመሻሻላቸው የተነሳና የእያንዳንዱ ሰው የማምረት ችሎታም ከፍ በማለቱ ምንም እንኳን ሥራ በመሠረቱ ማኅበራዊ ቢሆንም በግል በማምረት ተግባር ማከናወን ሲቻል ነው ። ለክላሲካል ፖለቲካል ኢኮኖሚ ምሁራን ግን ነገሩ የተገላቢጦሽ ነው ። ለውውጥ በማምረት ሂደት ውስጥ በተወሰነ ወቅት በተወሰነ ሁኔታ ሥር የሚከሰት ማኅበራዊ ተግባር ከመሆን ይልቅ የሰው ልጅ በተፈጥሮ የመለዋወጥ ባሕርይ ስላለው ራሱን በተለያዩ የሥራ መስኮች እንደሚያሰማራ በማድረግ ፣ ምክንያቱን ውጤት ፣ ውጤቱን ምክንያት አድርገው ያቀርባሉ ። ኤሪክ ሮል የተባለው ጸሐፊ ‘የኢኮኖሚ አስተሳሰብ ታሪክ’ በተሰኘው መጽሐፉ ላይ አዳም ስሚዝ ስለዚህ ያስተጋባውን መልእክት በማስመልከት ሲጽፍ ፤

« ለአዳም ስሚዝ የሥራ ክፍፍል የሥራ ምርታማነት ማደግ ዋነኛ ምክንያት ነው ። ስለዚህ ነጥብ የታወቁ ማስረጃዎቹንም ከሰጠ በኋላ የዚህ መንስኤ ምን እንደሆነ ወደ መጠየቁ ያመራል ። እዚህም ላይ ነው ፤ በሥራ ክፍፍል መሠረት ለመለዋወጥ ባለው ውስጣዊ ዝንባሌ ላይ እንደ ተመረኮዘ አድርጎ የሚያቀርበው ። እንደርሱ ግምት ይህ የሰው ልጅ ባሕሪዩ መሠረታዊ ዓላማ ነው ።» ሲል አስፍሯል ። እንግዲህ ነጋድራስም ስለ ለውውጥ የሰው ልጅ የተፈጥሮ ባሕሪዩ መሆን ሲያወሱ የክላሲካል ፖለቲካል ኤኮኖሚ ምሁራንን የተሳሳተ ኢኮኖሚያዊ አስተሳሰብ ማስተጋባታቸው እንደሆነ ግልጽ ነው ። ታዲያ ! ይህ በእንዲህ እንዳለም ቀደም ሲል ከጠቀስነው የነጋድራስ አባባል ውስጥ ግን አንድ ጠቃሚ ነጥብ ይታያል ። ይኸውም «ዕውቀት ባለው ሕዝብ» መካከል «የሁሉም ትጸና ተለዋውጦ ነውና እንካ ሥራ እምጣ ሥራ ይባባላል» ያሉት ነው ። ይህ አባባላቸው ምንም እንኳን ቀደም ሲል

እንዳየነው ልውውጥን በሚመለከት ያላቸው ግምት የተ
ሳሳተ ቢሆንም በካፒታሊስት ኅብረተሰብ ውስጥ ልውውጥ
ያለውን ቦታ ለማጤን የቻሉ መሆኑን ያሳያል ። ልውውጥ
የሸቀጥ ልውውጥን መልክ የወሰደው ገና በጥንታዊ የጋ
ርዮሽ ሥርአተ ማኅበር ማክተሚያ ላይ ቢሆንም ፥ በባ
ሪያ አሳዳሪውም ሆነ በፊውዳሉ ሥርአተ ማኅበር ውስጥ
የነበረ ቢሆንም ፥ በካፒታሊዝም ውስጥ ግን ከሸቀጥ ምርት
ዋነኛ የምርት መልክ መሆን ጋር ከፍተኛ ደረጃ ላይ የደ
ረሰ በመሆኑ ነው ። ነጋድራስ ከላይ ከጠቀስነው መንደር
ደረያ ሀሳብ በመነሳት ቀጥለው የሚያወሱት 'ዕውቀት
በሌላቸውና' 'ዕውቀት ባላቸው' ህዝቦች መካከል ስላ
ለው የልውውጥ ሁኔታ ነው ። ይህንንም ነጋድራስ እን
ደሚከተለው ያቀርባሉ ።

'ዕውቀት የሌላቸው ሕዝቦች ዕውቀታቸው ከፍ
ካለ ሕዝቦች ጋር የሠሩትን ነገር ሲለዋወጡ ዕውቀት
የሌላቸው ሕዝቦች የሚያገኙት ጉዳት ትልቅ ነው ። የዚ
ህንም ጉዳት ልክ ፈጽመን እንድንረዳው ቀጥሎ የተጻ
ፈውን ምሳሌ እንመልከት ፤ ወደ ኤሮፓ አገር ከጥር
1904 ዓ.ም. ድረስ የሄደው ቆዳ 241,499 ፈረሱላ ነው ።
ያንዳንዱንም ፈረሱላ ቆዳ ዋጋ ባዲስ አበባ ገበያ 13 ብር
ነበር ። እዚያ የሄደው ቆዳ የዋጋው ድምር ብናሰበው
3,139,487 ብር ይሆናል ። በፈረንጅ አገር ተበጅቶ የሚ
መጣው ቆዳ ግን ባዲስ አበባ በፈረሱላ ብናሰበው እስከ
200 ብር አወጣ ። እንግዲህ አንዱ ፈረሱላ ቆዳ ከፈረንጅ
አገር ተሠርቶ እስኪመለስ ድረስ በፈረሱላው 89 ብር
ፈጀ ማለት ነው ። የኢትዮጵያ መንግሥት 241,499
ፈረሱላ ቆዳ ከዚሁ ካገሩ ማበጀቱን ትቶ ወደኤሮፓ ቢሰድ
ኪሳራው 21,493,411 ብር ይሆናል ። የኢትዮጵያ ሕዝብ
ስምንት ቀን ሲሠራ ቢያንስ ቢያንስ ሰባት ቀን ለኤሮፓ
ሰዎች ሠርቶ አንድ ቀን ለራሱ ነው ።'



«ነጋድራስ ይህንን ነቁጥ በመውሰድ ያስተጋቡት
መልእክት ጉልህነት የነበረውን ያልተመጣጠነ ልውውጥ
በማሳየታቸው ብቻ የተወሰነ ሳይሆን ፥ ዛሬ ኋላቀር አገሮች
የሚሰቃዩበትን የኢኮኖሚ ነቀርሳ ማለትም በአለም
አቀፍ የካፒታሊስት የስራ ክፍፍል ክልል ውስጥ ኋላቀር
አገሮች ያላቸውን የጥሬ ዕቃ አቅራቢነት የንግድ ድርሻም
ጭምር በሚያስገርም አስተዋይነት ማየት መቻላቸውም
ነው ። ዛሬ የኋላቀር አገሮችን የኢኮኖሚ ባሕርይ ስንመ
ለከት የውጭ ንግድ በኢኮኖሚያቸው ሕይወት ውስጥ
ተገቢ ያልሆነ ከፍተኛ ሚና እንዲጫወት ከመደረጉም
በላይ ይኸው የውጪ ንግዳቸው በአንድ ወይም ሁለት
ጥሬ እቃዎች ንግድ ላይ የተመረኮዘ በመሆኑ ለኢምፔሪ
ያሊስቶች ብዝበዛ የተጋለጡና በተለያዩ መልኮቹ የኢም
ፔሪያሊስቶች ጥገኞች እንዲሆኑ እንደተደረጉ እንመለከ
ታለን ። ይህ ደግሞ በአስርና ሀያ ዓመት ጊዜ ውስጥ የተ
ከናወነ ድርጊት ሳይሆን ከዓለም አቀፍ የካፒታሊስት
ኢኮኖሚ መመሥረት ጋር የተቆራኘ የረዥም ጊዜ የተ
ዛባ ግንኙነት ውጤት ሆኖ እናገኘዋለን ። ታዲያ! ነጋድ
ራስ ከዛሬ ስድሳ ዓመት በፊት ይህንን የተዛባ ኢኮኖሚ
ያዊ አቋም እንዲኖረን የሚያደርገውን የንግድ ዝንባሌ
ማሸተታቸው ለአስተዋይነታቸው በቂ ማስረጃ ነው ።
ይህንንም በማየታቸው ነው 'ዕውቀት የሌለው ሕዝብ
ሁሉ ለብቻው መንግሥት ቢኖረውም ባይኖረውም ዕው
ቀት ያላቸው ሕዝቦች ይገዙታል' ሲሉ እቅጩን የተና
ገሩት ። ነጋድራስ ያኔ ይህንን ያሀል ተቆጭተው የተና
ገሩት ሁኔታ ዛሬ በሳይንስና ቴክኖሎጂ መዳበርና አርተ
ፊሺያል ጥሬ ዕቃዎችን ማምረት በመቻሉ የኋላቀር አገ
ሮች 80 በመቶ የሚሆነው የውጪ ንግድ ገቢያቸው ለተ
መሠረተበት ጥሬ ዕቃ በዓለም ገበያ ያላቸው ድርሻ 20

በመቶ ብቻ በመሆኑ የኢምፔሪያሊስት አገሮች የሚያደርጉባቸውን የዋጋ መጫን ቢያዩ ምንኛ ባዘኑ . . . »[12]

«ተፈጥሮ እራሷ የደረጃዎች ዋሻ በመሆኗ የተፈጥሮ ውበት ምንጭ ደረጃዎች ናቸው ። በተፈጥሮ ክልል ውስጥ በዐይን ታይቶ ፣ በእጅ ተዳስሶ ፣ በጆሮ የሚሰማው ሁሉ ከሥርዓት የወጣ አይደለም ። ምድር አብቅላ የምታፈራው የዕፀዋት ዘር ፣ በሰማይ በራሪ አእዋፍ ፣ በየብስና በባሕር የሚኖሩ እንስሳት ፣ እንዳው በጠቅላላው የፍጡር ዘር ሁሉ የተወሰነ መልክ ፣ ቅርፅና ባሕርይ ተገዥዎች ናቸው ።

«ፕላኔቶች ሥርዓትን ጠብቀው በምህዋራቸው ይዞራሉ ። የክረምትና የበጋ የቀንና የሌሊት መፈራረቅ ፤ አሁንም የቀን ፣ የሳምንት ፣ የወራትና የዓመታት መለዋወጥም እንዲሁ በተፈጥሮ ሥርዓት ውስጥ የተቀየሰ ነው ። ሰው ራሱ በደረጃ የተፈጠረ በመሆኑ ከእርግዝና እስከ ልደቱ ፣ በቁም አካሉ ፣ በባሕርዩና በእንቅስቃሴው በመጨረሻም ዕድገቱን አፍጅቶ እስከ ሞቱ ያለው ሂደት አሁንም በደረጃ ነው ።

'ደረጃ' ነባር ፣ አንቀፁ 'ደረጀ' ነው ። ደስታ ተክለ ወልድ 'ዐዲስ ያማርኛ መዝገበ ቃላት' በተሰኘው የቃላት ስብስባቸው ውስጥ ፣ 'ደረጀ' የሚለውን ነባር አንቀጽ 'ተደላደለ ፣ ተመቻቸ ፣ በሀብት ላይ ሀብት ጨመረ ፣ ወገን አበዛ ፣ ሥር ሰደደ . . .' ብለው ይተረጉሙና ፣ 'ደረጃ' የሚለውን ቃል 'ዕርከን ፣ መውጫና መውረጃ' ወይንም ደግሞ 'የማዕረግ ስም' ብለው ይደመድማሉ ። ተሰማ ሀብተ ሚካኤል

[12] አየለ ዘውገ ፣ 'የነጋድራስ ገ/ሀይወት ባይከዳኝ ፤ የፖለቲካዊ ኢኮኖሚ አስተሳሰብ ' (ክፍል 2) ፣ 'መስከረም' ቅፅ 1 ቁጥር 5 ፣ ሰኔ 1973 ፣ ገፅ 38 - 42 ። በይበልጥ ለመረዳት በተጠቀሰው ርዕስ በአየለ ዘውገ ተዘጋጅቶ በ'መስከረም' ቅፅ 1 ቁጥር 4 እና 5 የወጣውን ተመልከት ።



ግጽው በበኩላቸው ፣ 'ከሣቴ ብርሃን ተሰማ' በተሰኘው የአማርኛ መዝገበ ቃላት በሰጡት ትርጉም ፣ 'ደረጀ' ማለት 'ሥራን በመልክ በመልኩ ሠራ ፣ አደራጀ ፣ ደለደለ ፣ አስተካከለ ፣ አከናወነ ፣ አቀነባበረ ፣ አበጀ ፣ አስማማ' ይሉና 'ደረጃ'ን ደግሞ ፣ 'ከታች ወደ ላይ መውጫና ወደ ታች መውረጃ ፣ የእግር መቀባበያ ፣ መረጋገጫ ያለው ዕርከን ፣ 'ማዕረግና ከፍተኛ ሹመት' ይሉታል ።

«ከላይ የጠቀስናቸው ሁለቱ የዘመናችን የአማርኛ ቃላት ትርጉም ተጠሪዎች 'ደረጀ' በሚለው ነባር አንቀፅ ትርጉማቸው 'ማደላደልን' ፤ 'ማመቻቸትንና' 'ሥራን በመልክ በመልኩ መሥራትን' መጥቀሳቸው ለዚህ ፅሁፍ አላማችን ቢያቀርባቸውም ለ'ደረጃ' በሰጡት ትርጉም ግን ከማእረግ ፣ ከሹመት ፣ ዝቅ ብሎም ከእግር መቀባበያ መውጫና መውረጃ ፈቀቅ ባለማለታቸው በአላማ እንሊያያለን ።

«በዚህ ፅሁፍ 'ደረጃ' የሚለውን ቃል የምንተረጉመው ፣ ደስታ ተክለ ወልድም ሆኑ ተሰማ ሀብተ ሚካኤል የጠቀሱትን የእግር መወጣጫ ድንጋይም ሆነ ሌላ ከጥሬ ስረቱ አንስቶ ከጅምር እስከ ጭርሱ ያለውን መጠኑን ፣ ቁጥሩን ፣ ከብደቱን አሰላለፉን ወዘተርፈና ባጠቃላይ አነጋገር አሰራሩን ደንግጎ የሚዘረዝረውን በባለሙያ ተጠንቶ በስራ ላይ የሚለውን 'ደንብ' ማለታችን ይሆናል ። በማእረግና በሹመት ከፍታና ዝቅታም ቢሆን አንድ የተወሰነ የስራ መስክ የሚጠይቀው ማእረግ ፣ ወይም ሹመት በአንፃሩ የሚፈለገውን የትምህርት ፤ የአገልግሎት ፣ የእድሜ ፣ አግባብ ያለው የስራ ልምድ ለማለት እንጂ እንዳው ደረቁን አይደለም ።

«ምናልባት 'ደረጀ' ለሚለው ነባር አንቀፅ ደስታ ተክለ ወልድ የሰጧቸው ፣ 'የተደላደለ' ፣ 'የተመቻቸ' የሚ

ሉትግና ተሰማ ሀብቱ ሚካኤል ደግሞ ፣ ‘አስተካከለ’ ‘ሥራን በመልክ በመልኩ ሠራ’ ‘አደራጀ’ ‘አቀነባበረ’ የሚሏቸውን ትርጓሜዎች ስንመረምር ለደረጃ ምደባ ስራ አላማዎች የቀረቡ አንድን ነገር ለማስተካከል ፣ ለማመቻቸት ፣ ለማደራጀትና ለማቀነባበር የተወሰነ ‘ስርዓት’ ፣ ‘ደንብ’ መከተል እንደሚያስፈልግ የሚጠቀሙ በመሆናቸው ይህ ስርአትና ደንብ ወይም ደረጃ ከሰው ልጅ ተፈጥሮአዊና አለታዊ እንቅስቃሴ ጀምሮ ያለውን ሂደት እንመለከታለን ።

«ከአካል ተፈጥሮአችን ጀምሮ ከአንደበታችን የሚወጡት ቃላት ፣ እረማመዳችን ፣ ሰላምታ አለዋወጣችን ፣ አቀማመጥና አቋቋማችን የተወሰነ ስርአት ተገዥ ነው ። በአንድ በተወሰነ ታሪካዊ ወቅት የሚኖር ማህበረሰብ በልደት ፣ በሰርግና በቀብር ላይ የሚያከናውናቸው ድርጊቶች ሁሉ የደንብና የስራአት ተገዥዎች ናቸው ። ከጋርዮሽ ህብረተሰብ ጀምረን እስከ መደብ አልባው ህብረሰተብ ያሉትን የእድገት ሂደቶች ስንመረምር እያንዳንዱ ስርአት የራሱ የሆነ ታህታዊና ላእላዊ መዋቅር እንዳለው እንገነዘባለን ፤ መጭውን ከቀረው የሚለየው ማለት ነው ። በዚሁ በህብረተሰብ ታሪካዊ ሂደት ውስጥ በየደረጃው ማህበረሰብ በአመጋገብ ፣ በአለባበስ ፣ በአመለካከትና ባጠቃላይ በስነ-ልቦና ባህርያት የሚታይ ልዩ ከስተት-ደረጃ አለው ። ይህ አባባል እንኳንስ በህብረተሰብ ደረጃ በግለሰብ ደረጃም ቢሆን እከሌ እንዲህ ነው ፤ እከሊት እንዲህ ናት ብለን ግለሰቦችን በደረጃ የምንገመግምበትንም ይመለከታል ።

«ይህ ብቻ አይደለም ፤ ለመሰረታዊ ፍጆታ የምንገዛው ፣ ግዝተን የምንከፍለው ሁሉ በደረጃ የተተመነ ነው ። ከእግር መጫሚያችን ጀምሮ እስከ አንገት መከረቢያችን



ከፍ ብሎም ለአይናችን የሚሆነው መነፅርና የራስ ባርኔጣችን እንደ ቅጥነትና ውፍረታችን ፣ እንደማጠርና መርዘማችን በልክ ፣ በደረጃ የተመጠነ ነው ። ጢም ላጭው ፣ ፀጉር ከርካሚው ፤ ጣቃ ቀዶ በሜትር ለክቶ የሚሰፋው ሆነ ቆዳ ቀዶ የሚጨማው ለአሰራራቸው እንዲሁ ልክና ስርዓት አላቸው ፣ ደረጃ ። ከየመደብሩ ፣ ከየኪዮስኩ ፣ ከየጉልቱ ተሰፍሮ ፣ ተመዝኖ ፣ ተቀድቶና ተለክቶ የሚገዛው እንዲሁ ለተተመነለት የዋጋ መጠን በደረጃ የሚወሰን ነው ።

«ከማእድ ቤት በተለያዩ ደረጃዎች የሚበስሉ የምግብ አይነቶች በሰሀን ወይም በሌላ ቀርበው በሹካ ወይም በማንኪያ ወይም ደግሞ በጉርሻ ተመጥነው ታኝከውና ተውጠው ባዮሎጂያዊ ሂደታቸውን እስከ መጨረሻው ደረጃ የሚያከናውኑት በስርአት ነው ፣ በደረጃ ። የምንኖርባቸውም ሆኑ የሌሎች ቤቶች ምሰሶዎች ቁጥራቸው ፣ ውፍረታቸውና ቁመታቸው በባለሙያ ተመጥኖ የቆሙናቸው ። በሩ ፣ መስኮቱ ሌላውም ሁሉ እንዲሁ ፤ በደረጃ ።

« ብርድልብስ እንጥፈን እንሶላ ደርበን እንተኛም ፤ ጠረጴዛ ላይ ቁጭ ብለን ወንበር ላይ አንፅፍም ። ክራባት አስረን ሸሚዝ እንለብስም ። ጫማ አድርገን ካልሲ እና ጠልቅም ወዘተ . . . ሁሉም ስርአት ፣ ሁሉም ቅደም ተከተል አለው ለማለት ነው ፤ ደረጃ ።

«ከዱር መጥቶ ለሸማ የሚውለው ጥጥ ተፈልቅቆ ፣ ተዳምጦ ፣ ተባዝቶ ፣ ተለቅቆ ፣ ተዳውሮና ተሸምኖ ነው ልብስ የሚሆን ፤ በደረጃ ። ሌላው ሁሉ እንዲሁ ። ከቤት ወጥተን ወደ ጎዳና ስንገባ ተሽከርካሪዎች ቀኝ መንገዳቸውን ይዘው ሲጓዙ ፣ ‘ቀይ’ ሲበራ ሲቆሙ ‘እረንጓዴ’ ሲበራ ጉዟቸውን ሲቀጥሉ እንመለከታለን ፤ ደንብ ስርአት

ስለሆነ ፥ ደረጃ ። ተሽከርካሪው መኪናና አሽከርካሪው ደግሞ የሚግባቡበት ዘዴ ፥ ደንብ አላቸው ። ፍሪስዩን ረግጦ ማርሽ አስገብቶ ቤንዚን ሰጥቶ ለመሄድ ፥ በደረጃ ። አንድ አሽከርካሪና ሌላው የሚግባቡባቸው ደንቦች ፥ ስርአቶች አሉ ፥ ለመቆም ፥ ለመጠምዘዝና ሂድ ልሂድ ለመባባል ። እንዲሁም የአይሮፕላኑ አብራሪ ሲነሳ ፥ ሲበርና ሲያርፍ የሚከተላቸው ደንቦች አሉ ፥ ደረጃዎች ።

«ዛሬ በብሄራዊም ሆነ በአለም አቀፍ ደረጃ የምናውቃቸውን የስፖርት አይነቶች ስናስብ ፥ የሜዳዎቹና የመዋኛዎቹ ርዝመት ፥ ወርድና ስፋት በልክ የተመጠነ ነው ። ለልዩ ልዩ የስፖርት አይነቶች የሚውሉት መሳሪያዎችም እንዲሁ ፥ በደረጃ ። ስንቱ ይዘረዘራል? እንዳው ባጠቃላይ በሰው ልጅ ታሪክ ውስጥ ደረጃ (ስርአት) አልባ የሆነ ነገር የለም ። የደረጃ ስራ አላማ ባጭሩ ህይወትን ለተዘበራረቀ ፥ ለተመሰቃቀለና አደገኛ ለሆነ ኑሮ ሊዳርጉ ከሚችሉ አጋጣሚዎች ሁሉ ለመከላከልና ኑሮን የተመቻቸ ፥ የተደላደለና ስጋት የሌለበት ለማድረግ የሚረዳ ፍቱንና የሰው ልጅ ከተፈጥሮ የወረሰው ፥ በስራ ያዳበረውና ለዛሬው ግስጋሴ የተጠቀመበት ፍቱን መሳሪያ ነው ።» [13]

### (ረ) የትንተና ስልት

ላይ ላዩን ሲታይ ፥ የትንተና ስልት ከድልደላ ስልት እምብዛም የሚለይ አይመስልም ። ሆኖም መሰረታዊ ልዩነት አላቸው ። በድልደላ ውስጥ ክፍልፍሎቹን የሚያገናኛቸው ፥ የጋራ የሆነ ባህርይ ተካፋይነታቸው ነው እንጂ

[13] "የደረጃዎች ዜና" ፥ ቅፅ 6 ቁጥር 6 ህዳር/1974 ።



የአንዱ መኖር ለሌላው ወሳኝነት አይኖረውም ። በትንተና ስልት ግን አባሎቹ አንዱ ሌላውን እንዲደግፉ ሆነው ነው የሚዋቀሩት ፤ ማለትም አንዱ አባል ለሌላው አባል መኖር ወሳኝነት አለው — ለምሳሌ ሰውን ብንወስድ ፥ ከአካላቱ ወሳኝ አባሉን — ልቡን — ብንቆርጥ ሰውዬው ሊኖር አይችልም ። የአንዱ አባል መለየት በሌሎቹ አባላት መኖር ላይ ወሳኝነት አለው ማለት ነው ፤ በትንተናም ውስጥ እንዲሁ ። በትንተና ውስጥ ሁሉም አባሎች የተዋደዱ ስለሆኑ እንዳሻ እየቆራረጡ የሚያወጡለት ቅርፅ አይደለም ፤ አንዳች አባል ከተቆረጠ ትንተናው ርባና አይኖረውም ። ስለዚህ በትንተና ስልት ውስጥ ዋናው ዘዴ ርባና የሚኖራቸውን አባላት እርባና ከማይኖራቸው አባላት ለይቶ በመምረጥ አማዋቀሩ ላይ ነው ። ይህን ለማድረግ ደግሞ ስለሚተነትነው ርእስ በቂ እውቀት እንዲኖር ያሻል ። አለዚያ እርባና አለው ተብሎ የተመረጠው አባል ሲቆረጥ ለትንተናው ልዩነት ስለማያመጣ አላዋቂነትንም ጭምር ያጋልጣል ።

አስረጅ ፥

የዕውቀት መገኛ

«ዕውቀት የሚገኘው የማይደረስበትን ትልልቁን ነገር በማሰብ እየመሰላቸው አሳባቸውን ወደላይ የሚያንጠራሩ ሰዎች ትልቅ ስህተት ያደርጋሉ ። እውቀት የሚገኘው ትልልቅ ነገር በማሰብ ብቻ አይደለም ። በተራው ሕይወታችን የምንመለከተውን ነገር ሁሉ ለማወቅ በመፈለግና በመጣጣር ፥ በመመራመር ነው እንጂ ። ማናቸውም ተራ ሰው ፀሐይ ስትወጣ ፥ ነፋስ ሲነፍስ ፥ ዝናም ሲዘንም ፥ ዕፀዋትም ሲለመልሙ ባይኑ ሲያይ ፥ በጆሮው ሲሰማ፥በእጁ ሲዳስስ ፥ የሚያስደንቅ ወይም የሚከነክን ነገር አያገኝበትም ። ይህ ሁሉ የሚሆነው በተለምዶ መስሎ

ስለሚታየው እንዳላየ አይቶ ፣ እንዳልሰማ ሰምቶ ያልፈዋል ። ይህ ነገር እንዲህ የሆነበት ምክንያት ምን ይሆን ብሎ ምስጢሩን አይመረምርም ። እንደዚህ ያለ የመመራመር አሳብ ከቶ በፍጹም በልቡ ውስጥ አይፀነስበትም ። ይህን የመሰለ ሰው አንዳንድ እንደማናቸውም ዕቃ በመሬት ወድቃ የምትገኝ እንጂ ተመርምራና ማሰብ በሚባለው መሳሪያ ተደክሞባት የምትገኝ አይመስለውም ። ይህን የመሰለም ሰው ፣ እገሌ እንዲህ ያለ ጥበብ ፈለሰፈ ሲሉት ፣ ያ ሰው ብልሀቱ ድንገት ተገልጦለት ያለ ድካም ጥበቡን ያገኘ መስሎ ይታይዋል እንጂ ፣ ጥሮ ግሮ ነው ብሎ አይጠረጥርም ። ጥበብ የምትገኘው እንደዚሁ ድንገት ባጋጣሚ ነገር ስለሚመስለው ፣ እሱም እንዲሁ ዕድል በጥቶት ድንገት አገኛታለሁ እያለ ዕድሜውን ሙሉ ሲጓጓ ይኖራል ። እስኪ ጥበብን ልፈልግ ብሎ አይደክምም ፤ አይጣጣርም . . . » [14]

« . . . ባህል ሰፋ ብሎ ሲታይ ዲያሌክቲካዊ ግንኙነት ያላቸው ቁሳዊ ፣ ቴክኒካዊና መንፈሳዊ ይዘቶች አሉት ። ይህም ዘርዘር ብሎ ሲተነተን ባህል የኅብረተሰብ ሕይወታዊ እንቅስቃሴዎችን — ማለትም ሳይንሳዊና ቴክኖሎጂያዊ የማመንጨት ፣ የፈጠራ ፣ የማግኘትና የዲዛይን ማውጣት ችሎታዎችን ፣ የኪነ ጥበባት የዕድገት ደረጃዎችን ፣ የሥራ ምርታማነትንና የአመራረት ዘዴዎች ቅልጥፍናን ፣ የምርት ውጤቶችና የተፈጥሮ ሀብቶች ክፍፍል ፣ ስርጭትና ልውውጥ ሥርዓቶችን ይይዛል ። ከዚህም አልፎ ባህል የፖለቲካ ፣ የአስተዳደርና የአኗኗር መዋቅሮች የጊዜ አጠቃቀም ሥርዓትን ፣ ምኞቶችን ፣ ተስፋዎችንና የመሳሰሉትን የኑሮ ውጤቶችን የያዘ ሕይወት ያለው ስብስብ ነው ። ሲጠቃለል ባህል የሰዎች የስራ ውጤትና ሰዎች ከሌሎች እንሰሶች የሚለዩበት መደበኛና ዓይነተኛ ምልክታቸው ፣ የየወቅቱ አኗኗራቸው ነፀብራቅ ፣ ድምራዊ የይዘት ክምችት ያለው ክስተት ነው ።

«ባህል ከሚንፀባረቅባቸው ድርጅቶች መካከል ትምህርት ፣ የጤና አጠባበቅ ፣ የሕዝቦች አሠፋፈር ፣ የከተሞች አቀራቀርና መስፋፋት ፣ የፖለቲካ መዋቅሮች ፣ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ፣ ኢንዱስትሪና እርሻ ፣ የትራንስፖርትና መገናኛ ዘዴዎች ፣ ኪነጥበባት ፣ የምርት ክፍፍል ፣ ስርጭትና ልውውጥ የመሳሰሉት ይገኙበታል ። የነዚህን ድርጅቶች የዕድገት ሂደትና ደረጃ ማጥናት የተጠቃሚዎቻቸውንና የገንቢዎቻቸውን ሕዝቦች የባህል ሁኔታ ማወቅ ያስችላል ። ይህም ማለት የትምህርት ሥርዓት ተፈጥሮን በቁጥጥር ሥር ለማዋልና ለመጠቀም የሚያስችል ዓላማ ፣ ይዘት ፣ መዋቅርና የአፈጻጸም ዘዴዎች መያዙን መገምገም ያስፈልጋል ። በጤና በኩል ኅብረተሰቡ በሽታን ለመከላከል ፣ ከተያዘም ለመዳን ያለውን የሰው ኃይል ፣ የድርጅትና የቁሳቁስ መሟላት ሁኔታን ማጥናት ይገባል ። ጊዜን ለሥራና ለዕረፍት ለመጠቀም የሚያስችል ሥርዓትና ልምድ መኖሩን መመልከት ያሻል ። ለኪነ ጥበባት ፣ ለቴክኒክና ለሙያ ዕድገቶች አስፈላጊ መዋቅሮች መኖራቸውን ማጤን ይገባል ። የልዩ ልዩ የአገልግሎት ድርጅቶችን ደረጃ መመልከት ያስፈልጋል ። ለልዩ ልዩ የምርት ተቋሞች ተገቢ የአመራረት ዘዴዎች ፤ የምርት መሣሪያዎችና ቁሳቁሶች ፣ ድርጅቶችና የሰው ኃይል መገኘቱ መጠናት አለበት ። በአጠቃላይ የኅብረተሰቡ የግንዛቤ ፣ የአስተሳሰብ ፣ የአመለካከትና የተግባራዊ ችሎታ ደረጃ መገምገም ይኖርበታል . . . » [15]

[14] አዲስ ዘመን ፣ ሰኔ 6/34 ።

[15] ‘መስከረም’ ፣ ቅጽ 3 ፣ ቁጥር 12 ፣ መጋቢት ፣ 1975 ገጽ 55 ።

ገላጭ ድርሰት ከሌሎች ፅሁፎች ፣ ማለትም ፣ ከሂስ ፅሁፍ ፣ ከአመዛዛኝ ፅሁፍ ፣ የአንድን ሀሳብ ወይም ነገር እድገትና ውጤት ከሚገልፅ ፅፍሁ (ሳይንሳዊ ውጤት ወይም ንድፈ ሃሳብ) ውጪ ያለውን ማንኛውንም ባህርይ ከአንድ ከተወሰነ ግምባር የሚያቀርብ ማፍታቻ ፣ ማሳወቂያ ፣ መግባቢያና ማስተማሪያ ፅሁፍን ሁሉ ያጠቃልላል ።

ገላጭ ድርሰት ፣ በስእላዊ (መስተዋታዊ) አፃፃፍ ስልትና እንዲሁም አብነት (ምሳሌ) በሚያስፈልገው ክፍል፣ በትረካ የአፃፃፍ ስልት ይጠቀማል ።

በኪነ ፅሁፍ ውስጥ ፣ በአብዛኛው ፣ የአንድን ፅሁፍ ስሜታዊ አቀራረብ ዘይቤ (ለማሳዘን ፣ ለማሳቅ ፣ ለመቀለድ ፣ ለማሾፍ ፣ ለምፀት ፣ ለአሽሙር ወዘተርፈ . . . ያለውን አዝማሚያ) ለመፍጠር ፣ ትረካው የሚካሄድበትን ቦታና ባለ ታሪኮቹን አመቻችቶ ለማቅረብ ፣ የታሪኩን ባህርያት ለማስተዋወቅና ለሌሎችም በታሪኩ ውስጥ አብነት ፣ ማመሳሰልና ማነፃፀር እና መተንተን ለሚያስፈልጋቸው ጭብጦች ሁሉ ያገለግላል ።

### 5.2.4 አመዛዛኝ (አደራዳሪ) ድርሰት

አመዛዛኝ ድርሰት ከገላጭ ድርሰት ጋር ይመሳሰላል ። የሚለይበት ነገር ቢኖር በአላማው ነው ። ገላጭ ፅሁፍ ማብራሪያን በመስጠት ብቻ ሲበቃው ፣ አመዛዛኝ ፅሁፍ አንባቢውን ወይም ሰሚውን የአንድን ጉዳይ እውነትነት ወይም ውሸትነት ለማሳመን ይጥራል ። ስለዚህም ገላጭ ፅሁፍ የአመዛዛኝ ፅሁፍ ረዳትና አካል ነው ።



አከራካሪ ስለሆኑ ጉዳዮች የሚፃፍ እንደ መሆኑ ፣ ፀሀፊው ለአንድ ግምባር ቆሞ አንድን ጉዳይ በአንድ መልኩ ብቻ በመቃወም ወይም በመደገፍ ሊፅፍ ይችላል ፤ ለማስረጃ ያህል፣ «ትዳር ለጤነኛ ህብረተሰብ ወሳኝ ነው » የሚለውን ርእስ ከወሳኝነቱ አኳያ ብቻ ደግፎ ለማሳመን በመሞከር ፤ ወይም ለሁለቱም ግምባር የቆመ በመምሰል ፤ ጉዳዩን በመደገፍና በመቃወም አቅርቦ ፣ በመከያው ማስረጃው ያደላበትን አጠናክሮ በመተቸት ፤ ለምሳሌ ፣ ከላይ የጠቀስነውን ርእስ በመውሰድ ፣ ትዳር ለጤነኛ ህብረተሰብ ወሳኝ ስለመሆኑና ስላለመሆኑ አስረድቶ ፣ በመጨረሻ ፣ አንደኛውን ወገን በማጠናከር ። ስለሆነም በማንኛውም መልኩ ቢሆን ተከራካሪው የጉዳዮችን መሄጃ አስቀድሞ በመገምገም በተቃውሞው ሊሰነዘሩ ይችላሉ ለሚላቸው ነጥቦች ቅድሚያ ዝግጅት ማድረግ ይኖርበታል ።

አመዛዛኝ ፅሁፍ አንዳንዴ አእምሮን የሚቀሰቅስና የሚያሳስብ ፣ አንዳንዴ ስሜትን የሚቀሰቅስና የሚነድ ፣ አንዳንዴም ሁለቱንም ስለሚሆን ለብዙ ጉዳዮች ማቅረቢያነት ያገለግላል ።

ምሳሌ ፤

— ብሄራዊ ጉዳዮችን ፣

(ስለ ብሄረሰቦች ፣ ስለ ቦዘኔነት ፣ ስለ አካባቢ ፅዳት፣ ስለ መሰረተ ትምህርት እና ስለ መሳሰለው ፤)

— ርእዮተ አለማዊ ጉዳዮችን ፣

(ስለ ህይወት ፣ ስለ ተፈጥሮ አመለካከት ፣ ስለ ሶሻሊስታዊ ወይም ካፒታሊስታዊ ርእዮትና ስለ መሳሰለው፤)

— ፖለቲካዊ ጉዳዮችን ፣

(ስለ ዱታንት ፣ ስለ ውጪ ፖሊሲ ፣ ስለ ቅኝ አገዛዝና ስለ መሳሰለው ፤)

— የሞራል ጉዳዮችን ፤

(ስለ ቤተኛ አዳሪነት ፣ ትዳር ስለ ማፍረስ ፣ ስለ ስነ ስርአትና ዲስፕሊን ወዘተ . . .)

<u>አመዛዛኝ ድርሰት ለመፃፍ ትኩረት የሚሰጥባቸው አበይት ነጥቦች</u>

(ሀ) ለጉዳዩ መካተቻ የሚሆን <u>መንደርደሪያ አረፍተ ነገር ማውጣት</u>

መንደርደሪያው ሀሳብ ጉዳዩን አሟልቶ የያዘና በአንድ አረፍተ ነገር ሊገለፅ የሚችል መሆን አለበት ። መንደርደሪያው ፣ ጉዳዩ የሚቋጠርበት አቢይ ነጥብ በመሆኑም ምን ለማሳየት ወይም ለማስገንዘብ እንደ ተፈለገ የሚጠቁም ግልፅና ቀጥተኛ አባባል ሊሆን ይገባዋል ።

<u>አስረጅ ፤</u>

«ለቀበሌ ሊቀ መንበር ምረጡ ። »
«ብርቱካን መብላት ለጤንነት»
«የሀገር ፍቅር ከህብረተሰባዊነት ተነጥሎ መታየት የለበትም ። »

(ለ) ለጉዳዩ የሚቀርቡትን ማስረጃዎች እንደየአይነታቸው ማገናዘብ ፤

(1) ሰንሰለታዊ ማስረጃዎች

ሰንሰለታዊ ማስረጃዎች ተወላላጆች ስለሆኑ ፣ አንዱ ከሌላው የሚወጣ ነው ። በአብዛኛው ምክንያቶች



ውጤትን ፣ ውጤቶችም እንዲሁ ሌሎች ምክንያቶችን ወይም ውጤቶችን እየሆኑ የሚበራከቱበት ስልት ነው ።

<u>አስረጅ ፣</u>

«የቤተሰብ መፍረስ የልጆችን መበተን ፣ የልጆች መበተን የመንፈስ መረበሽንና የሞራል ውድቀትን ፣ የሞራል ውድቀት ወመኔነትንና ወሮበልነትን ፣ ወሮበልነት ወንጀለኛነትን ይጋብዛሉ » የሚል መንደርደሪያ ቢኖር ፣ እያንዳንዳቸውን ምክንያታዊ ተወላላጆች በተለያዩ አንቀፆች አሳድጎ ለማቅረብ ይቻላል ።

(2) <u>እየብቻቸው በሆኑ በተለያዩ ማስረጃዎች</u>

እነዚህ እያንዳንዳቸውን ሆነው የሚቀርቡ ምክንያቶች ፣ በያሉበት ማጥገብ አለማጥገባቸው መመዘን አለበት ። አንዳንዶቹ ያለ ምንም ተጨማሪ ማብራሪያ ተቀባይነት ሲኖራቸው ፣ ሌሎቹ ደግሞ ፣ ለመንደርደሪያው ማበልፀጊያነት ከመቅረባቸው በፊት እየራሳቸው በበቂና በማያጠራጥር መንገድ እንዲታመኑ የሚያደርግ መግለጫና ማስረጃ ያስፈልጋቸዋል ። ስለዚህ ፣

(ሀ) <u>አጢያያቂ የማይሆኑትንና ተቀባይነት ያላቸውን ለይቶ ማውጣት</u>

(ለ) <u>አጠያያቂ ለሆኑት አስፈላጊ ምክንያቶችን አቀናብሮ ማቅረብ ያስፈልጋል ።</u>

ምክንያቶቹ አንዳንዴ በግል እውቀትና ልምድ ላይ ፥ አንዳንዴ በአካባቢ የወል ልምድ ላይ ፥ አንዳንዴ ደግሞ በሳይንስና በዘመናዊ ምርምር ላይ ሊመሰረቱ ይችላሉ ። በወል ልምድ ላይ የተመሰረቱትን ለማስታወስ ያህል ከመጠቆም በስተቀር ማብራሪያ አያሻቸውም ። በግል ልምድና እውቀት ላይ የተመሰረቱት ግን ፥ ከተገኙበት ምንጭ ጭምር መጠቀስ ይኖርባቸዋል ፤ ጥርጣሬን ለማስወገድ ።

ለምሳሌ ያህል ፥ «ለቀበሌ ሊቀ መንበር ምረጡ» ከሚለው መንደርደሪያ ፥ በመምረጥ ወይም በአለመምረጡ ላይ ክርክር ከመነሳቱ በፊት ፥ በቅድሚያ በቀበሌ አስፈላጊነት ላይ ልንስማማ ያስፈልጋል ። የማንስማማ ከመሰለው ደራሲው ይኸንኑ በቅድሚያ አውቆ ማስረጃዎቹን መደርደር ይኖርበታል ።

(መ) <u>ተቃውሞን አውቆ በቅድሚያ ስለ ማፍረስ (ማክሸፍ)</u>

> ክርክሩ የሚያዘምባቸውን ነጥቦች አስቀድሞ በመጠርጠር መዘጋጀት ያስፈልጋል ። ይህም ሁኔታ ራስ የቆሙለትን ግምባር ብቻ ሳይሆን ሌሎች የሚቆሙላቸውን የተለያዩ ግምባሮች ጭምር መገመትና ማጤንን ይጠይቃል ። ማጤንም ብቻ አይደለም ከራስ ለተለዩት ግምባሮች ማስተባበያና መቃወሚያም ማዘጋጀት ያስፈልጋል ።

<u>አስረጅ ፤</u>

<u>«ተስፋፊነትና ጠባብነት……… ዓይነተኛ ገጽታ</u>

«...ልዩ ልዩ ቅጽሎችን ያስከተሉ የሶሻሊዝም ዓይነቶች ቦግ ድርግም ብቅ ጥልቅ ማለታቸውን ባያቋርጡም ወደ እውነተኛውና ሳይንሳዊ ሶሻሊዝም የሚደረገው ጉዞ



ጠናክር ወደኋላ አላለም ። በሶሻሊዝም ፥ ለዚያውም በሳይንሳዊ ሶሻሊዝም ስም ለመነገድና ለማጭበርበር በየጊዜው መድረክ ላይ ወጥተው ተግባራቸውንና ድርጊታቸውን አጋልጦ ከተፋቸው ውስጥ ፥ በጠባብ ብሔረተኝነትና በተስፋፊነት የተወጠሩት የሱማሌ የገዥ መደቦች ፥ ዛሬ ከውርደትና ከውድቀት ጉዞአቸው ከመጨረሻው የሐፍረት አዘቅት ውስጥ በመግባት የኢምፔሪያሊዝም ቡችልነታቸውን ለዓለም ሕዝብ በማያጠራጥርና በማያወላውል አኳኋን እያስመሰከሩ ነው...

«...ዚያድ ባሬ በሶማሊያ ስለሚመሠረተው የሶሻሊስት ስርዓት በሐሰኔ የፖለቲካ ትምህርት ሲከታተሉ ለቆዩት የሶማሊያ ወጣቶች ገለጻ ሲያደርግ ፥ በተለይም የሶማሊያን ሶሻያሊዝም ምንነት ሲገልጽ እንደሚከተለው አስቀምጦታል ።

> የኛ ሶሺያሊዝም የሶማሊያ ሶሺያሊዝም ፤ አፍሪካዊ ሶሺያሊዝም ወይም የእስላም ሶሺያሊዝም አይደለም ፤ ይልቁንም በሰው ልጅ ልምድና እውቀት የዳበረው የመጀመሪያው ዓይነት ሶሻያሊዝም ነው ። የኛ ሶሺያሊዝም በራሱ ተጨባጭ ሁኔታ የሚመራ ሶሺያሊዝም ነው ።

« ይህ መቼም ከሞላ ጐደል ጤናማ አስተሳሰብ ነው እንበል ። ይሁን እንጂ ፥ እውነተኛው የዚያድ አቋም ይህ አይደለም ። የዚያድ ባሬ (ሶሺያሊዝም) ምንጩ ምንድር ነው ? መሠረቱ ሃሳቡስ በርግጥ እርሱ እንዳለው (የመጀመሪያው ዓይነት) ሶሺያሊዝም ነው ? ለዚህ ጥያቄ ራሱ ዚያድ ባሬ መልሱን ሲሰጥ እንዲህ ይላል ፤

> ሶሺያሊዝም የተጀመረው የት ነው ? ያፈለቀውስ ማን ነው? ይህንን ጥያቄ በሚመለከት አያሌ ሰዎች በውዥምብር ውስጥ ወድቀዋል ። እኛ እንደሚ መስለን የሶሺያሊዝም ምንጭ የእስላም ሕዝብ ነው ፤ መሠረተ ሃሳቡም የመነጨው ከእስላም ሃይማኖት ነው ።

« በዚያድ አመለካከት በዓለማችን የሶሺያሊስት ስር ዓት ግምባታ የተጀመረው ከእስልምና ሃይማኖት አመ ጣጥ ጋር ከሆነና የሶሺያሊዝምም መሠረት የእስላም ህዝብ ከሆነ ፣ 1ኛ/ የሶሺያሊስት ስርዓት በዓለም ላይ መስ ፈን የጀመረው ከታላቁ የጥቅምት የሩስያ አብዮት በፊት በሰባተኛው ምዕተ ዓመት ከክርስቶስ ልደት በኋላ መሆኑ ነው ፤ ምክንያቱም የእስልምና ሃይማኖት መስፋፋት የጀ መረው ከላይ በተጠቀሰው ዘመን በመሆኑ ነው ።

« በሌላ በኩል ደግሞ ፣ የእስላም ሃይማኖት የሶሺያሊ ዝም መሠረት ከሆነ ፣ የእስልምናን ሃይማኖት የተቀበለ ሁሉ በዚህ ብቻ ሶሺያሊስት ሊሆን ይችላል ማለት ይሆን ? ፊት ካቀረብነው ትንተና እንደምንረዳው በሶማሊያ የሚ መሠረተው ሶሺያሊዝም (የሶማሊያ ሶሺያሊዝም ፤ አፍ ሪካዊ ሶሺያሊዝም ወይንም የእስላም ሶሺያሊዝም) ሳይ ሆን የመጀመሪያው ዓይነት ሶሺያሊዝም ነው ከተባለ ፣ ይህ የሶማሊያው ሶሺያሊዝም ከየት ተነስቶ የት ሊያርፍ ነው።

«ዚያድ ባሬ ባንድ በኩል የእስልምና ሃይማኖት የሶሺያ ሊዝም መሠረት መሆኑን በግልጽ ሲያስረዳ ፣ በሌላ በኩል ደግሞ ይህንን ቃሉን በሚያስገርም ሁኔታ ሲያጥፈው እናያለን ። ዚያድ በሶሺያሊዝምና በእስልምና ሃይማኖት መካከል ያለውን ግንኙነት ሲያስረዳ እንዲህ ይላል ፤

> ሶሺያሊዝም እንደ እስልምና ሃይማኖት ከሰማይ የወረደ መልዕክት አይደለም ። ይልቁንም ሰዎች



> በምርት መገልገያዎች ሲጠቀሙ የሚፈጥሩትን ግንኙነት ስርዓት ባለው መንገድ የሚያቀነባብር ነው ።

« እንግዲህ ሶሺያሊዝም እንደ እስልምና ሃይማኖት ከሰማይ የወረደ መለኮታዊ ቃል ካልሆነ ፣ የእስልምና ሃይ ማኖት የሶሺያሊስት ንድፈ-ሀሳብ ምንጭ ሊሆን የቻለው በምን ተአምር ነው? የዚያድ የንድፈ ሀሳብ ችግር ይህ ብቻ አይደለም ። አንዳንዴም ያመልጠውና ትክክለኛውን ነገር ተናግሮ በአደባባይ የለፈፈውን ሀሳቡን ሲያፈርስ እንዲህ ይላል ።

> ... ከኛ ቀደም ብለው ሶሺያሊዝምን በተግባር ያዋሉ ሀገሮች ሶሺያሊዝምና ሃይማኖት አብረው አይሄዱም ብለዋል ፣

በማለት እራሱ ተወናብዶ ሌላውንም ያወናብዳል ። ዚያድ ባሬ ስለ ሶሺያሊዝም ያለው የተወናገረገረ አስተሳ ሰብ በዚህ ብቻ የሚወሰን አይደለም ። ዚያድ ስለ ሶማሊያ ሶሺያሊስቶች ዓላማ ሲያብራራ ፤

> እግዚአብሔር ሰውን ሲፈጥር ደጉንና ክፉውን ለመለየት እንዲችል አእምሮ ሰጥቶታል ። ስለሆ ነም... ሰው በሰው ከሚበዘበዝበት ስርዓት ይልቅ እኩልነት የሰፈነበትን ኅብረተሰብ ለመፍጠር ተነሳስተናል ።

ይላል ። እንደ ዚያድ አመለካከት የሶሺያሊስት ስርዓት ምሥረታ ፕላን በፈጣሪ ተረቆና ጸድቆ በሰዎች አእምሮ በኩል ተፈፃሚነት ያገኛል ለማለት ካልሆነ በስተቀር የሶሺያሊዝም መሠረቱ ሰብዓዊ ስነ ምግባር ሳይሆን የሰ ብዓዊነት ባህርዩ የሶሺያሊዝም አንድ ገጽታ ብቻ ነው ። ይህም ብቻ አይደለም ። ዚያድ ስለ ሶሺያሊዝም መሠረት አጣርቶ አለማወቁን የሚያስገነዝበን ስለ መደቦችና የመ

ደብ ትግል ያለው አሳዛኝ ሀሳብ ነው ። ዚያድ ባሬ በሶማሊያ ስለ መደቦች አሰላለፍ ሁኔታ ሲናገር ፣

> በማርክሲስቶች አስተሳሰብ ከሄድን በሶማሊያ ኅብረተሰብ ውስጥ መደቦች የሉም ፤ እኛ ዘላኖች ገበሬዎች አነስተኛ አሰሪዎችና ወታደሮች ነን ።

በማለት የራሱን አስተያየት ሰንዝሯል ። በዚያድ ባሬ የመደብ ትንተና መሠረት ዘላኖች፤ገበሬዎች አነስተኛ አሰሪዎችና ወታደሮች ከመደቦችና ከመደብ ትግል ውጪ ናቸው ። እዚህ ላይ ‘በማርክሲስቶች አስተሳሰብ’ ማለቱ የሚገርም ቢሆንም የሰጠው ማጠቃለያ ደግሞ እጅግ የሚያስገርም ነው . . . የእውነተኛ ማርክሲስቶችና የሳይንሳዊ ሶሺያሊዝም አቋም ግን ጨርሶ ከዚህ የተለየ ነው ።

« እዚህ ላይ የቬትናም ኮሚንስት ፓርቲ ዋና ፀሐፊ የሆኑት ፣ ጓድ ሌዳዋን የተናገሩትን መጥቀስ በቂ ይመስለናል ። ጓድ ሌዳዋን መደቦችንና የመደብ ትግልን በሚመለከት በአጠቃላይም የማርክሲስቶች ተግባር ምን መሆን እንዳለበት ሲያስገነዝቡ ፣

> በማርክሲስት አመለካከት አኳያ ኮሚዩኒስቶች የትግላቸውን እስትራቴጂና ታክቲክ ሲቀይሱ ለሠራተኛው መደብ ጥቅም ቅድሚያ በመስጠት በኅብረተሰብ መደቦች መካከል የሚኖሩትን ግንኙነቶችና ልዩነቶች አጣርተው ማወቅ ይኖርባቸዋል። አብዮታዊ ስሜታቸውንና ሳይንሳዊ ዕውቀትን በማቀናጀት ማርክሳዊውን የመደብ ትግል መርህ ጠንቅቀው ማወቅ ይኖርባቸዋል ።

በማለት ማርክሲስቶች ለመደቦችና ለመደብ ትግል ንድፈ-ሀሳብ ተገቢውንና አስፈላጊውን ትኩረት መስጠት እንዳለባቸው ተናግረዋል ። የዚያድ ባሬ ቅጥፈት ይበልጥ



ቁልጭ ብሎ የሚታየው ስለ ሶሻያሊዝም አቋሙን በሚገልጽበት ጊዜ ነው ። ይህንንም በሚመለከት ዚያድ ሲናገር ፤

> ሶሺያሊዝም የማይጠቅመን ሆኖ ሲገኝ አሽቀንጥረን እንጥለዋለን ፤ በዚህ ፋንታም ሌላ መንገድ እንሻለን ፤ መርሁ ጠቃሚ ሆኖ ከተገኘ ግን እንቀበለዋለን ።

ይለናል ። የዚያድ ባሬ የፖለቲካ አቋም ከውጭ ሲያዩት እጅግ የተምታታ ቢሆንም ፣ ከቃላትና በየጊዜው ከሚለዋውጣቸው ሽፋኖች በስተጀርባ ግን በጠባብነትና ተስፋፊነት ላይ የተመሰረተ የከረረ ብሔርተኝነት ሆኖ ይገኛል ። (ሶሺያሊዝም የማይጠቅመን ከሆነ አሽቀንጥረን እንጥለዋለን) ያለውን ሀሳብ ዛሬ በተግባር ተርጉሞ ከቀንደኛ የኢምፔሪያሊስት ኃይሎች ጋር በማበር በአፍሪካ ቀንድ ለሰላምና ለዕድገት የቆሙ ሀገሮች የሚያደርጉትን ጥረት ለማደናቀፍ ሲጣጣር በገሀድ እያየነው ነው ። የበግ ለምድ መልበስ የተኩላን ተኩላነት አይለውጠውም ። ዚያድ ባሬ ስለ ሳይንሳዊ ሶሺያሊዝም በነበረው የተጭበረበረ አስተሳሰብ ውስጥ ወድቆ ሲጮህ የራሱ ድምጽ በፈጠረው የገደል ማሚቶ ተደናግጦ ይታያል ።

« በመሠረቱ አብዮታዊ ተግባር ቀላል ጉዳይ አይደለም ። ይህንን እውነታ ጃክ ዎዲስ « New theories of Revolution » በተባለው መጽሐፍ ውስጥ በዚህ መልክ አስቀምጦታል ።

> ‘አብዮት ከፍተኛ ጥንቃቄ የሚጠይቅ ጉዳይ ነው ። የሰዎች ሕሊናዊ ፍላጐት ወይንም በድፍረት የተሞላ የአብዮታዊ መፈክሮች ድርድር አይደለም ። አብዮታውያን የሕዝቡን፣ ማለትም፣ የሠራተኛውን፣ የገበሬውን ፣ የተማሪውን ፣ የምሁራኑን ፣ ስሜት ጠን

ትቶው ማወቅ ይኖርባቸዋል ። የሕዝብ መሪዎች የሚሠሩት ስህተት በቀጥታ በሕዝቡ ጫንቃ ላይ የሚወድቅ በመሆኑ ፤ በዚህ ረገድ ከፍተኛ ጥንቃቄ መደረግ አለበት ።

ዚያድ ባሬ እንደሚለው ሳይሆን ፣ 'ማርክሲዝም (ሳይንሳዊ ሶሻሊዝም) ተጨባጩን ሁኔታ በትክክል የሚ ተንትን በመሆኑ ከሌሎች ሶሺያሊስት ንድፈ፣ሐሳቦች ለየት ያለ ነው ። የአብዮትን ነባራዊ የዕድገት ሂደት በማጤን ሰፊው ሕዝብ የአብዮት ኃይልና የፈጠራ ችሎታም ምንጭ በመሆኑ በትግል ወቅት የወሳኝነት ሚና እንዳለው ያስተ ምረናል ። ይኸውም ትንታኔ በማርክሳዊ የታሪክ አቀራ ረብ ላይ የተመሠረተ እንደ መሆኑ በያንዳንዱ የአብዮት ወቅት ስለሚፈጸሙት ዐቢይ ጉዳዮች ሰፊና በሥርዓት የተቀነባበረ ትምህርት ይሰጣል ።'

'የሶማሊያን ጉራማይሌ ሶሺያሊዝም የዛሬ ወዳጆቹ እንኳ ሳይቀሩ የተቹት ጉዳይ ነው ። ከአራት ዓመት በፊት (1977) ለሥራ ጉዳይ ወደ ግብጽ ፣ ሱዳን ፣ ኢትዮጵያና ሶማሊያ ሄደው የነበሩ የአሜሪካ ኮንግሬስ አባሎችም በሶማሊያ ስላዩት ነገር ይህንን ሪፖርት ጽፈው ነበር ።

> የሶማሊያ አብዮታዊ ምክር ቤት ሳይንሳዊ ሶሺ ያሊዝምን እከተላለሁ ይላል ። እኛ እንዳየነው ከሆነ ግን በአገሪቷ ውስጥ ካፒታሊዝም እያቆ ጠቆጠ ነው......... የሶማሊያ መሪዎች ብዙውን ጊዜያቸውን ያጠፉት የራሳቸውን......... ሶሺያ ሊስታዊ......... የኤኮኖሚ ዕድገት ከማፋጠን ይልቅ ለአጋዴት ጦርነት ዝግጅት በማድረግ ነው ።

«ስለ ሶማሊያ 'አብዮት' አይዲዮሎጂካዊ መሠረት ሰፋ ያለ አመለካከት ሊኖረን የሚችለው በማንኛውም ሶሺያሊስት አብዮት ውስጥ ተፈፃሚነት የሚያገኙ ሕጎች



ምን ምን እንደሆኑ በመመልከት በዚህ አንፃር በሶማ ሊያ ውስጥ ያለው ሁኔታ ምን እንደሚመስል ለመገ ምገም ስንችል ብቻ ነው ። ዛሬ ሶሺያሊዝምን ለመገንባት በማንኛውም አገር የሚደረገው ጥረት የሚመራው በግ ምባር ቀደሙ ማርክሳዊ ሌኒናዊ ፓርቲ መሪነት ሲሆን የዚሁ ግምባር ቀደም ድርጅት ሳይንሳዊ አመራር ወሳኝ ነው ። በሌላ በኩል ደግሞ ፣ ለሶሺያሊዝም ግምባታ መሠ ረት ለመጣል የሠራተኛውና የገበሬው መደብ ተግባራዊ አንድነትና ኅብረት ወሳኝ ነው ። በተለይም የውጭ ፖሊ ሲን በሚመለከት ወዘደራዊ ዓለም አቀፋዊነትን በመር ህና በተግባር ደረጃ መቀበልና በሥራ መተርጐም እጅግ አስፈላጊ ነው ። በተለይም እንደ ሶማሊያ ባሉ ኋላ ቀር አገሮች ሶሺያሊዝምን ለመገንባት ከተፈለገ ይህ ፈጽሞ ሊዘለል የማይቻል መሠረታዊ መርህ ነው ።

«በዚህ ጽሁፍ ውስጥ ከላይ ለማብራራት እንደ ተሞ ከረው የማንኛውም አብዮት ጥንካሬ በአብዮቱ የንድፈ ሀሳብ ጥራት ላይ የተሠመረተ እንደመሆኑ መጠን አብ ዮታዊ አይዲዮሎጂ ከሰፊው ሕዝብ ማኅበራዊ ስነ ልቡ ናና ማኅበራዊ ንቃተ ሕሊና ጋር የሚጣጣም በመሆኑ ለኅብረተሰቡ ንቃተ ሕሊና መዳበር መሠረታዊ ነው ። ለሶሺያሊዝም የሚደረገውም ትግል ከዚህ መሠረተ ሐሳብ የሚነሣ መሆን ይኖርበታል ። ...»

## 5.2.5. የጭውውት ድርሰት

ጭውውት ፣ ትረካ በድርጊያ የሚገለፅበት አይነተኛ መንገድ ነው ። ጭውውት ፣ ራሳቸው ባለታሪኮቹ እርስበር ሳቸው የሚያካሂዱት የሀሳብ እና/ወይም የስሜት መገናኛ

16 ሰሎሞን ዲባባ ፣ ተስፋፊነትና ጠባብነት ፣ የሱማሌ ገዥ መደብ ገጽታ ፣ 'መስከረም' ቅፅ ፤ 2 ቁጥር 7 ፣ ታህሳስ 1974 ፣ ገጽ 50 - 57 ።

ነው ። ስልትነት የሌለውን ሀሳብ ማቅረቢያ አይደለም— ወይም ማናቸውንም በቀጥታ በተራኪው ሊቀርብ የሚችልን ነገር በጥቅስ በመክበብ ማዥጐርጐሪያ ። በአብዛኛው ፣ ጭውውት የትረካውን ሂደት የሚያራምዱ ነጥቦችን መያዝ አለበት ።

የጭውውት አባባል የአንድን ህዝብ ወግ ፣ ልምድ ፣ አኗኗር ፣ አስተያየት (ስልት ፣ ፈሊጥ ፣ ዘዬ ፣ ፈዝ ፣ ዘይቤ ፣ ልግጫ ፣ ቀልድ ወዘተ...) እና ባጠቃላይም የዚያን ህዝብ ውለኛ ባህሪዎች ማወቅን ይጠይቃል ። እያንዳንዱ ግለሰብም ከልምዱና ከሰው ጋር አብሮ በመኖር የተማረው ስነልቦናዊ አመለካከት ያሻዋል ፤ በህብረተሰቡ ውስጥ የሚገኘው ሰው የነገሮች አባባል ባህሪው ፣ እንደየሁኔታው የሚኖረውን ለውጥ ለማጤንና እንደየለውጡም ራሱን ለማመቻቸት ። በባህል በተራራቁ ሰዎች መካከል የሚደረግ ጭውውት አለመግባባትን ያስከትላል ።

ጭውውት ፣ በተለይ በዘመናዊ ፅሁፍ ውስጥ ፣ የተራኪ አስተያየት አይታከልበትም ። ከባለታሪኮቹ ጋር ሆነን ነው እዚያው በዚያው ፣ ወዲያው ወዲያው የምናዳምጠው ። ቢሆንም አእምሯችን ከሁለት አኳያ ነው ማጤን የሚኖርበት ፣ (1) ባለታሪኮቹ ምን እየተባባሉ እንዳሉ እና ጭውውቱ ከነሱ አንፃር ምን ማለት እንደሆነ (2) ካጠቃላይ ትረካው አንፃር ተራኪው በጭውውቱ ምን ሊያሳውቅ እንደፈለገ ። በጭውውቱ ውስጥ ባለታሪኮቹ ገና ያልደረሱበት ተራኪውና አንባቢው ግን ቀስ በቀስ እየተገነዘቡት ያደገ የአባባል ሂደት ሊኖር ይችላል ። ባጠቃላይ በትረካ ስልት ከቀረበ ፅሁፍ ውስጥ ይልቅ በጭውውት ውስጥ አንባቢው ወይም አዳማጩ እያሌ ሁነቶችንና ድርጊያዎችን ከራሱ ልምድና እውቀት አኳያ እያሚላና የራሱን ብያኔ ወይም መደምደሚያ እየሰጠ ማለፍ ይኖርበታል።



(ሀ) <u>የጭውውት ስልቶች</u>

እንደየባህሉ እድገትና እንደየቋንቋው ብልፀጋ እያሌ የጭውውት ስልቶች ይኖራሉ ። ለዚህ ፅሁፍ ያህል ግን ጥቂቶቹን ብቻ እንመለከታለን ።

(1) <u>ለውይይት</u>

የዚህ አይነቱ ጭውውት አላማ በተወሰነ ሀሳብ እና/ ወይም ጉዳይ ላይ ልዩ ልዩ ተዛማጅና ተቃራኒ መልኮቹን እያነሱ በመነጋገር ፣ ለሀሳቡ ወይም ለጉዳዩ መፍትሄና መቋጫ መሻት ነው ። አዳዲስ አስተሳሰብንና አመለካከትን በሚያሳምን መንገድ ለማቅረብ ይሰራበታል ፤ በተለይ ርእዮተአለማዊ አመለካከትን ።

(ሀ) <u>ለእውነት ከሳችነት</u>

<u>አጅ ፣</u>

<u>እምሜ</u> ስማ ስማ አባክህ!........ ጥቅም አይደልለኝም ........ ከባላጋሮቼ ጋር በመመሳጠር ጥብቅና የቆምኩለትን ሰው ጉዳይ አላጣምም..........
እንዴታ! ጠበቃ ቢሉህ ጠበቃኮ አይደለሁም ...

<u>ትርፌ</u> እኔምኮ አላልኩም ።

<u>እምሜ</u> ትርፌ ልንገርህ ፣ በሁሉ ነገር ስወድህ አንደበትህ አይጥመኝም ።

<u>ትርፌ</u> አንደበት አይበላ ፣ ምን መጣም ያስፈልገዋል?

<u>እምሜ</u> ኧረ በእነዋሪዋ! «አንደበት አይበላ» የማለት አማርኛ! ይኸንኮ ነው የምለው ፤ የነገርን መሄጃ፣ የነገርን አቃቂር ማወቅ የነገርን አረቄ ማውጣት አይደለም ! ተሳስተሃል ! የለም የለም ትርፌ

የጐድን የሚሄድ አነጋገር አለሀ ። እንጃ ! በእን ግሊዙ እንዲያ እንደሁ አላውቅም ። ባማርኛው ቢሆን አይገቡ ገብቷል ።

ትርፌ ምናልባት ልዩ ስጦታ ሊሆን ይችላል ፤ እግዚ አብሄር ለኔ ብቻ የሰጠኝ………

አምሜ አይ እንግዲያው አጉል ነገር ሰጥቶሃል ፤ አጉል ነገር የሰያፍ የሚያስኬድ……… አዎ ፥ ሌላው ቢቀር ላንተ የሚሆን አዳማጭ መጨመር ነበ ረበት…ደግሞም አበቃቀል ለየቅል ሆነ እንጂ… አንተን ብሆን ስጦታ አልለውም ፤ ፀሎት የሚ ያዝለት በሽታ ነው……… ልንገርህ ……… ፀሎት የሚያዝለት ፤ እንዲህ ያለ የለዛ ድርቀት!

ትርፌ የለዛ ወዘና አይሁን ብቻ ![17]

## (ለ) ድርጊያ ጠቋሚነት

(በድርግ ወሳኝነት ፥ በባህሪ ጠቋሚነት እና በድርጊያ ወሳኝነት ፥ ገፅ 336 ፥ ከ 337-338 እና ከ 399-340 ተመልከት ።)

## (2) ለክንክና ወግ

ጭውውቱ እንደነገሩ ጊዜ ለማሳለፍ የሚደረግና ምንም ያህል የተጨበጠ የሀሳብ እድገት የማይታይበት የሚመስል ነው ። በአእምሮ የሚጉላላና የሚከነክንን ሀሳብም ሆነ ጉዳይ በቀጥታ ሳይጠቅሱ ዳርዳሩን እየነካኩ የማለፍ ፈሊጥ ነው ፤ ልብ ያስበውን የሚሸፋፍኑ አባባ ሎች ይበዙበታል ።

[17] ዳኛቸው ወርቁ ፥ 'ትበልጥ' ፥ (አ.አ 1962) ገፅ 89 ።



አጅ ፥

ናደው እንጃልህ ብቻ ፥ ሊገባኝ ያልቻለው……… የት ላይ እንደ ተሳሳትሁ………እንዲህ እንኳ እንደ ዱሮ አባት አላንጓለልኳቸው ፤ ገበታ እንኳ ከኔው ጋር ቀርበው ነበር የሚበሉት ………

አምሜ አስተምረሃቸዋል ደሞ ።

ናደው አስተምሬያቸዋለሁ ።

አምሜ የሚበሉት የሚጠጡት አልጐደላቸው ።

ናደው ስነግርህ!……… አልጐደላቸው !

አምሜ አልታረዙ !

ናደው አልታረዙ !

አምሜ የኪስ ገንዘብ አላጡ !

ናደው የኪስ ገንዘብ አላጡ !

አምሜ እንዲያውም በከተማው የሚታዩት እነሱ ነበሩ ።

ናደው እንዴታ ! ያያቸውና የሚያውቀኝ ሁሉ ብሎ ብሎ ታከቶታል ።

አምሜ ታክቱ ያላቸው……… [18]

## (3) ለጉንያ ወግ

ይህን አይነቱ የባለታሪክ ንግግር እምብዛም ጭው ውት ነው ሊባል አይችልም ። ተናጋሪው የተሰማውን ፥ ያብላላውን ፥ ያውጠነጠነውን ይናገራል እንጂ መልስ አይጠብቅም ። ራሱ አነጋገሩም ቢሆን መልስ የሚጠብቅ

[18] ከላይ ከተጠቀሰው ፤ ገፅ 5—6 ።

አይነት አይደለም ። ጉንፃ ጭውውት በይበልጥ የማዘዝን ፣ የማነሳሳትን ፣ የማጓጓትንና የስልጣንን ፣ የመበየንን ፣ የመሸወድን እና የመሳሰሉትን አባባሎች ያጠቃልላል ። የተያያዘ የሀሳብ ልውውጥ አይኖረውም ።

አጅ ፣

የትም ወርቅ (ገልመጥ በማረግ) ዛሬ ልጂ እግዜሩ ቅርብ ነው ። የናት ያባትሽ ልቅሶ መስማት አይገ ሬምሽ......... እዎ ፣ አገርሽ ለመመለስ በመ ቁረጥሽ ይበጅ አርገሻል ......... ቢሆንም ታዲያ.........

ቢሆንም ታዲያ......... ቢሆንም ታዲያ......... ...ነገርን ነገር ይወልደዋል እቴ ፣ አንድ የሩቅ ዘመዴ ነበረች ......... ታዲያ አስራ ሶስት ልጆች ነበሯት......... መቼም አገሬው ሲወዳት......... ምንድነው ኧረ ፣ ስም ነበ ራት ፣ እዎ ፣ 'አድባር ! አድባር' ይሏት ነበር......... ምን ያረጋል ፣ የኋላ ኋላ እን ዲሁ ሳይሞላላት ፣ እንደ ባከነች...... አንዱን ሳቲዘው አረፈችው ......... እዎ ፣ ቁጫጭ ሲበዛም ጥሩ አይደለም......... ከሰው በታች ያረጋል ......... ድህነት ያመጣል ፤ ድህነት የሚሉት በሽታ ......... የኋላ ኋላ አጥንት እንደ ዋሽንት ሲጮህ የሚያዋጣው ያው ገን ዘብ ነው ..........[19]

19 ከላይ ከተጠቀሰው ፣ ገፅ 74 ።



(4) ለእየራስ ወግ

የጋራ በሆነ ጉዳይ ላይ ይጀመርና ተናጋሪዎቹ የየራሳቸውን ፍላጎት ለማራመድ ከሚኖራቸው ግፊት ሳይሰማሙ የሚያካሂዱት ጭውውት ነው ።

አጅ ፣

«ይገርምሃል ! እላዬ ላይ ወጥታብኝ ነበርኮ አበርሀ ላይ !»
«እኔ ደሞ ምን ትመጣ ብዬ !»
«እንዴት መሰለህ የገላመጠችኝኮ ደሞ !»
«ዱብዳ ነውኮ የሆንከብኝ !»
«ምናርግ ነው ደሞ አንተን የምትልህ ?»
«ይገርማል !»
«የቧን ነገር እንዳታነሳብኝ ብያለሁ.........»
«ስብሰባው ተሰረዘ !»
«በጭራሽ !»
«ምን ትመጣ ብዬ!» [20]

(ለ) የጭውውት አቀራረብ

(1) የእያንዳንዱ ተናጋሪ ሀሳብ በአዳዲስ መስመር በትምእርት ጥቅስ እየተለየ መቅረብ አለበት ። አንዱ ተናጋሪ እገፅ ህዳጉ ሳይደርስ በተወው በዚያው መስመር ላይ የሌላው ተናጋሪ ሀሳብ ለጥቆ አይፃፍበትም ።

(2) እያንዳንዱ ተናጋሪ ተለይቶ መታወቅ አለበት ፤ ተለይቶ ካልታወቀ የንግግሩን ሂደት ለመረዳት ያዳግታል ፤ ማን ለምን እንደ ቆመ ለመገንዘብ ።

20 ከላይ ከተጠቀሰው ።

# ክፍል ሶስት

## ትረካ

## ጥንታዊ

## ዘመናዊ

## ምእራፍ ስድስት

## ጥንታዊ ታሪክ

በሰለጠኑም ሆነ በመሰልጠን ላይ በሚገኙ ህዝቦች ባህል ውስጥ፣ ታሪክን ፈጥሮ ማውራት ከጥንት ጀምሮ ያለ ልማድ ነው ። እህ ፣ ከዚያስ ምን ሆነ?......... ከዚያስ .........ከዚያስ እያሰኘ የሚያጓጓን ታሪክ ።

ለአብነት ያህል የሚከተለውን ታሪክ እንመልከት፡-

«አንድ ታሪክ ላጫውታችሁ ልጆቼ» አሉ ሽማግሌው፤

«በዱሮ ዘመናት ፣ በአንድ መንደር ውስጥ ፣ ከአንድ አባት ፣ ከአንድ እናት የተወለዱ እህትና ወንድም ፣ ባን ድነት እየተጋገዙ ይኖሩ ነበር ። ከጊዜ በኋላ እህቲቱ ባል አገባች ። ወንድምዬው ብቻውን መኖር አቃተው ። እህቱ ዘንድ ሄዶ ደባል ሆነ ። አንድ ሁለት ዓመታት አለፉ ፤ ወንድምዬው የግል ስራውን እየሰራ ፣ እህቲቱ ባሏንና ወንድሟን እያገለገለች ። በመኪያው ፣ ሴት ልጅ ወለደች ። ወንድምዬውም የሙያ ስራውን እየሰራ የሚያገኘውን አንዳንድ አሞሌ እህቱ ዘንድ በማስቀመጥ ብዙ እንደሆን አወቀ ። በወለድ ሊያበድረው መፈለጉንም ለእህቱ ነገ ራት ። ምናለ መቼስ የሰው ልቡ አይታወቅ .........ምን ይሆንላችኋል ታዲያ ፤ ወንድምዬው አንድ ቀን ጧት ይነሳና አሞሌው ወደ ነበረበት ጐታ ሄዶ ቢመለከት በቦ ታው ድንጋይ ተሞልቶበት ማግኘት ። ተደናግጦ ይሄ ድና እህቱ ዘንድ አሞሌው ወደ ድንጋይ ተለውጦ አገኘ

ሁት ብሎ መንገር ። ምኝ ነሀና ፣ አሞሌ ብዙ ጊዜ ሲቆይ ወደ ድንጋይነት መለወጡን አታውቅም ብላ ትመልስለታለች እሷም ። ያዝናል ፤ ይተክዛል ፤ ጥርጣሬ ይገባዋል ። በር ግጥ ወደ ድንጋይ መለወጡንም ለማረጋገጥ ይፈልጋል ።

ጥቂት ቀናት ካወጣው ካወረደው በኋላ ፤ ወደ ሜካ ሄዶ ዝንጀሮ ይገድላል ። ከዚያም እቤት አምጥቶ የዝን ጀሮውን ሬሳ የእህቱ ልጅ ተኝታበት እነበረው መደብ ላይ አስተኝቶ ፣ ልጅቷን እሩቅ ቦታ ወስዶ ይደብቃታል ። እናቲቱ ፣ ልጄ ካሁን አሁን ትነሳለች እያለች ብትጠባ በቅ ምንም አይነት እንቅስቃሴ ይጠፋል ። ወደ መደቡ ጠጋ ትላለች ። ገለጥ አድርጋም ብትመለከታት ወደ ዝንጀሮነት ተለውጣ ታገኛታለች ። ከመጠን በላይ ትደነ ግጣለች ። አይኖቿንም ልታምን ያቅታታል ። የጐረቤት ርዳታ ልትሻ ሮጣ ትወጣለች ። ካንዲት ጓደኛዋ ጋር ትመ ለሳለች ። ጓደኛዋ ግን የሆነውን ባየች ጊዜ የበለጠ ትደነ ግጣለች ። ውርጅብኝ ነው ትላታለች ፤ መላ ካልተበጀ ለት እስከ መጨረሻው ስም የሚበክል ። ሰው ሳይሰማ ሞተች ብሎ መቅበሩ የሚሻል መሆኑንም ታማክራታ ለች ። እንደ መከረቻትም ፣ ደህና አድርጋ በጨርቅ ጠቅላ ቁቁ በማለት ፣ ላካባቢው ጐረቤት ጭንቅና ድንጋጤዋን ታሰማለች ። ጐረቤት ይሰበሰባል ። ልቅሶ ይጀመራል ። እልፎ እልፎም የሀዘን ግጥም መወራወር —

እህት— ወይ ዘንድሮ ! ወይ ዘንድሮ !
ልጅቷ ሆነች ዝንጀሮ !

ወንድም— እወይ ጉባይ ! እወይ ጉባይ !
እሞሌዉ ሆነ ድንጋይ !

እህት— እሞሌው እለ ባዲስ ጉታ ፣
የልጄን ነገር እንዴታ ?



ወንድም— እሞሌዉ ካለ ባዲስ ጉታ ፣
ልጅቷም አለች ካጉቷ !

የየራሳቸውን ተንኮል ያወጡታል ። እሷም ልጅዋን እሱም እሞሌዉን ያገኛሉ……… እና ብልጥ ለብልጥ አይን ፍጥጥ የተባለውም ከዚህ የተነሳ ነው……እላችኋለሁ።»[1]

ይህ እንግዲህ በቃል ሲነገር የኖረ ታሪክ ነው ። «በዱሮ ዘመናት» በማለት የጊዜን ፤ «ባንድ መንደር ውስጥ» በማለት ፣ የቦታን ፣ «ወንድምና እህት» በማለት የባለታሪክን (የገፀ-ባህሪን) ፣ «ሽማግሌ» በማለት የተራኪን ፣ « ልጆች » በማለት የአዳመጭን ፣ «ብልጥ ለብልጥ አይን ፍጥጥ» በማለት የሀሳብ መንደርደሪያን አስፈላጊ ነት ፣ ጥንታውያኑ ተረድተውት እንዴት ሲጠቀሙበት እንደኖሩ የሚያሳዩን ። ባሁኑ ዘመንም ቢሆን ፣ በአብዛ ኛው ፣ የቃል ተራኪው በፀሀፊ ፣ አድማጩ ባንባቢ የተ ለወጡ ይምሰሉ እንጂ የቀሩት ፣ ጥንታዊ ቦታቸውን እን ደያዙ ናቸው ። እነዚህም ሁለቱ ቢሆኑ ጨርሶ ቀርተዋል ለማለት አይቻልም ።

ታሪኩ አስገራሚነትና ልብ አንጠልጣልነትም አለው። ወንድምዬው ፣ እሞሌውን ወደ ድንጋይ ተለውጦ ሲያ ገኘው ፣ እህትዬዋ ፣ ልጅዋን ወደ ዝንጀሮነት ተለውጣ ስታ ገኛት መገረማቸው ያለ ነው ። አስገራሚነቱ ለባለታ ሪኮቹ ብቻ ቢመስልም እኛሳ አድማጮቹ ፣ ምን ያደርጉ ይሆን ብለን መጠየቃችንና ለማወቅ መፈለጋችን ይቀ ራል? አይቀርም ። በተለይማ ልጅቷ ተደብቃ ፣ ዝንጀሮው ለቀብር ተዘጋጅቶ ስንመለከት ፣ የማወቅ ፍላጐታችን እያ ደገና ፣ እጓጊነት እየፈጠረብን ነው የሚሄደው ። አስገራ ሚነትና አስደንጋጭነትም ቢሆን ፣ አዳማጮችንም የሚ

[1] ከአዘጋጁ ።

ጨምር አልታጣም ። ባንዳንድ ጥንታዊ ታሪኮች ውስጥ እንደሚገኘው አይነት አንዳንዱ ያላሰብነውን አጋጣሚ ነገር በማምጣት ፣ አንዳንዱ የእግዚአብሔርን ፣ የመላእክትን የሰይጣንን ጣልቃ ገብነት በማሳየት ፣ አንዳንዱም ደግሞ ምስጢሩን ከኛ ካድማጮች እስከ መጨረሻ በመደበቅ የሚጠቀሙበትን ስንመለከት ።

ባጭሩ እንግዲህ ፣ ጥንታውያኑ ፣ ልማድ ያስተማራ ቸውን የህይወት ባህሪ ሳይለቁ (የጊዜን ተከታታይነት በመከተል ማከለኛ ከለኛ ፤ ሞት ከልደት በኋላ እንደ ሚመጣ አይነት) የሰው ልጅ ስለሚገጥሙት ስለደግነቱ ፣ ስለክፋቱ ፣ ስለፍቅሩ ፣ ስለጥላቻው ወዘተ ሁኔታዎች ሲተርኩ ኖረዋል ማለት ነው ። በዘመኑ ትክክል መስሎ በታያቸው መንገድ ።

ታሪክን በፅሁፍ ማስፈር እየተስፋፋ በሄደበት ጊዜ ደግሞ፣ከበፊቱ የነበረው ያተራረክ ዘዴ ለወጥ ማለት ጀመረ። ለዚህም አብነት «ጦቢያ» ከአፈ ወርቅ ገብረ ኢየሱስ የተ ደረሰውን ልቦለድ ታሪክ መመልከቱ ይበጃል ።

«አሪት ተሽሮ ወንጌል መሰበክ በተጀመረ ዘመን አረ መኔው ክፍ ብሎ ክርስቲያኑ ዝቅ ይል ነበር........(አረማ ውያኑ (ክርስቲያን የተባለውን ሁሉ የገደሉትን ገድለው የማረኩትን እንደባሪያ ይሸጡት ወይም ከቤታቸው ጥኑ ጥኑ ሥራ ያሰሩት ነበረ........ እንደዚሁ ሁሉ አንድ ጊዜ አረመኔዉ እንደ ልማዱ የክርስቲያኑን አገር ሊዘርፍ...... መጣ በተባለ ጊዜ የክርስቲያኑ ንጉሥ ........ ባራት ደጃዝማቾች እግር አሳዝዞ ሄድ ተዋጋ ብሎ ሰደደ........ ነገር ግን ... የክርስቲያኑ...... ድል ሆነ ። ከነዚያ ከሄዱት ......ሦስቱ ከውጊአው ላይ ሞቱ ። አንደኛው ግን ተያዘ... »[2]

[2] አፈ ወርቅ ገ/የሱስ ፣ 'ጦቢያ' ፣ (እ.አ 1958) ገፅ 1 ።



በዚህ በመጀመሪያው አንቀፅ «አሪት ተሽሮ ወንጌል መሰበክ በተጀመረ ዘመን» ሲሉ ፣ የጊዜ አወሳሰናቸው ጥን ታዊውን የታሪክ አቀራረብ ዘዴ የተከተለ ይመስላል ። ሆኖም እንደ ጥንቱም የተጠቃለለ አይደለም ። ታሪኩን እተወሰነ ዘመን ያውለዋል ። ወደ አራተኛዉ መቶ ክፍለ ዘመን ማለት ነው ። እዚህ ላይ ፣ «ከዕለታት አንድ ቀን» ወይም «በጥንት ዘመን» ከሚለው አጀማመር መለየቱን መገንዘብ ይጠቅማል ።

ታሪኩ የአራት መቶኛዉ ክፍለ ዘመን ከሆነ ደግሞ ድርጊቱ የተፈፀመው በጐንደር አካባቢ መሆን ይኖርበ ታል ። ስለዚህ ፣ ምንም እንኳ ቦታው ተለይቶ ባይጠቀስም፣ በምናነብበት ጊዜ ፣ የጐንደር አካባቢን በአእምሯችን መያዝ ይኖርብናል ። ይኸም አቀራረብ «ባንድ ቦታ» ወይም «ባንድ መንደር» ከሚለው ጥንታዊ መግቢያ የተለየ ነው ።

ከዚያ ቀጥሎ ደግሞ ፣ ከሶስቱ ደጃዝማቾች «አንዱ (ግን) ተያዘ» በማለት ታሪኩ የሚመለከተውን ሰው ጠቅ ሰውልናል ። ነገር ግን ይኸ ጃዝማች ዋናው ባለ ታሪክ ቢሆን ኖሮ በስም መታወቅ ነበረበት ፤ ተለይቶ የመታዬት መልክ እንዲኖረው ። ደራሲው ግን በስም ስላልለዩት ፣ ዋናው ባለ ታሪክ ወደፊት እንደሚመጣ ተስፋ በማድረግ ማንበብ እንቀጥላለን ።

እዚህ ላይ ስለ ባለ ታሪኮቹ ሰዎች ስም አወጣጥና አወሳሰን ጥቂት ልናውቃቸው የሚያስፈልጉ ዘዴዎች አሉ ።

በማንኛውም ኪነ-ፅሁፍ ውስጥ የሚገኙ ባለ ታሪኮች በሁለት ክፍል ይከፈላሉ ።

እንደኛዎቹ ዋናዎቹ ናቸው ።

(1) በተፀውኦ ስም ተለይተው ይጠራሉ ።
(2) ይኸው መለያቸው በፅሁፍ ውስጥ ተደጋግሞ ይጠቀሳል ።
(3) ጠቅላላ ባህርያቸውም ፣ በሚያሳዩት እንቅስቃሴ ፣ በሚሰሩት ስራ ፣ በሚያደርጉት ንግግር ፣ በሚውሉበት አካባቢ ይገለፃል ።

ሁለተኛዎቹ ተከታዮቹ ናቸው ።

(1) በወል ስም ወይም በግብር ስም ፣ አንዳንዴም በተፀውኦ ስም ይጠራሉ ።
(2) የመደጋገም እድል እምብዛም አይኖራቸውም ።
(3) አገልግሎታቸው በደጀንነት ነው ።

ከ «ጦቢያ » ከመጀመሪያው ገፅ የተጠቀሰው አንቀፅ እንግዲህ ጠቅላላ የሆነ ጥንታዊ የትረት አቀራረብን ዘዴ ተከትሏል ማለት ነው ። ቦታዉ ፣ ሰዉ ፣ ጊዜዉ ሳይወሰን በመቅረቡ ።

የጦቢያን ታሪክ እንቀጥል ።

የተያዘው ደጃዝማች ቤተሰብ ሞቷል ብለው ተስፋ ቆርጠው ሳሉ መሸጡን ሰሙ ። የተሸጠበትንም ከፍለው ለማስለቀቅ ቁርጥ አሳብ አደረጉ ።

«... በመጨረሻው... ወንዱ ልጅዋ ዋህድ የጌታ አድሮ ደመወዙን እያመጣ ሊአጠራቅም ፣ ቤቲቱ ጦቢያ ግን እን ጨት ለቅማ ውሀ ቀድታ የሚበሉትን እያሰናዳች ልታ ቀርብ ፣ ቤተሰቡን ፣ ሎሌውን ፣ ገረዱን የሚሰጡት ገንዘብ የለምና ሊአሰናብቱ አሰቡና ተማከሩ ...» [3]

[3] ከላይ ከተጠቀሰው ፣ ገፅ 4 ።



ዋህድ አባቱን ከግዞት ማስለቀቂያ የሚሆን ገንዘብ ለማጠራቀም በሚጥርበት ወቅት ፣ እንዳጋጣሚ ጉረዶ ማንነት የሚቀጥረው ሀብታም ነጋዴ ያገኛል ። ለነጋዴው ቤተሰቡ የገጠመውን ችግር ያዋየዋል ። ነጋዴውም የዋ ህድን የሰውነት ምርቃነት በመመልከት አዝኖ ይዞት የነበረውን ገንዘብ እስተከረጢቱ ይሰጠዋል ። ያጋጣሚ ነገር ። በተጨማሪም ፣ ያባቱን ስምና የገዛውን አረመኔ ስሙን እስከ ምልክቱ ለነጋዴው ነግሮት ይለያያሉ (በነ ገራችን ላይ አድራሻውን እንዴት እንዳወቀው አስቀድሞ አልተነገረንም) ።

አንድ ቀን ማታ ...... ቤተሰቡ እንደ ልማዳቸው «እኒሄ ገንዘብ መቼ ተጠራቅሞልን ፣ እስተመቼ ገንዘቡን ሰደን ፣ መቼ ተፈትቶ ታባታችን ጋር ዓይን ላይን ፤ እንተያይ ይሆን...» [4] እያሉ የቅጠላ ቅጠል ራታቸውን ሲበሉ አባታ ቸው ድንገት ከተፍ ይላል ። ከመጠያየቅም የተነሳ ነጋ ዴው ያስለቀቀው መሆኑን ይረዳሉ ፣ ያጋጣሚ ነገር ።

እዚህ ላይ እንደገና ወደ ጥንታዊው የታሪክ አቀራ ረብ ዘዴ ተመልሰዋል ። ዋህድ አሽከርነት መቀጠር ቢፈ ልግ ባጋጣሚ በነፃ ገንዘብ የሚሰጠው ሀብታም ነጋዴ ያገኛል ። ከዚያም ሀብታሙ በሰጠው ገንዘብ ላይ ለመ ጨመርና አባቱን ለማስፈታት ሲታገል ባጋጣሚ ነጋ ዴው አስፈትቶት ኖሮ አባትዬው እቤቱ ከተፍ ይላል ።

ባጋጣሚ ሁኔታ ላይ የሚመሰረት ፅሁፍን ጨርሶ ለማስወገድ አይቻል ይሆናል ። የሚቻል መስሉ ከታያቸ ውም ውስጥ እንኳ የተሳካላቸው ብዙ አይደሉም ። ቢሆ ንም የግድ መጠቀም ካስፈለገ ፣ ቢያንስ ፣ ቢያንስ አን ባቢ የሚደናገርበትን ሁኔታ መምረጥ ያስፈልጋል ፤ አጋ

[4] ከላይ ከተጠቀሰው ገፅ 8 ።

ጣሚ መሆኑን ሳያጤን የሚያልፍበትን ።

(1) በእለታዊ ኑሮው አልፎ አልፎ ሲደረጉ ወይም ሲደ
ርሱ ስለሚያይ እንደ እንግዳ ነገር የማይሆንበትን
እንዲያም ሆኖ በጥንቃቄ ። በኑሮው ውስጥ የሚ
ገጥሙት ነገሮች ፥ በተወሰነ ፅሁፍ ውስጥ ሲሰፍሩ
ታማኝነት እንዳያጡ በማድረግ ።

(2) በፅሁፉ ውስጥ እደናግረው የሚያልፉበትን ቦታ
በመምረጥ — በመሰረታዊና በማጠቃለያ ምእራፎች
ውስጥ ሳይሆን ወደየመካከሉ በመሸንቀር ። እንደ
ዚህ ካልሆነ ላንባቢ በጉልህ ስለሚታዩ ፅሁፉን
ያደክሙታል ።

እፅሁፍ መጨረሻ ገደማ ስለሚመጣ አጋጣሚ «ፍቅር
እስከ መቃብር»ን ማንበቡ ይጠቅማል ።

ሰብለ ወንጌል (አባ አለም ለምኔ) ጫካ ለጫካ ስት
ጓዝ ትደክማለች ። ሾህና ጋሬጣ እግሯን ያቆስለዋል ።
ይመሽባታል ። አውሬዎች ይመጡባታል ። አንድ የወ
ርካ ዛፍ ወጥታ ታድርና ታነጋለች ። በማግስቱ ከዛፉ
መውረድ ያቅታታል ። ያጋጣሚ ነገር ቀፎ አውራጅ ባላ
ገሮች ይመጡና ያወርዷታል ። እንደገና ትንሽ ትሄድና
ትደክማለች ። እንደገና ሊመሽባት ይሆናል ። ያጋጣሚ
ነገር አንዲት ከባለቤቷ የነጠቀች በቅሎ አጠገቧ መጥታ
ትቆማለች ። የበቅሎዋ ጌታም ተከትሏት ኖሮ ይመጣና
ሰብለን እመንደር ድረስ ይወስዳታል ። ያስተናግዳታል ።
ከዚያ በዛብህን ፍለጋ አዲስ አበባ ትመጣለች ። ታጣዋ
ለች። ወዳገሯ ስትመለስ ያጋጣሚ ነገር በዛብህ ታሞ እተኛ
በት ቤት አሳድሩኝ ብላ ትሄዳለች ። በዛብህን ታገኘዋለች ።
በዛብህ ይሞታል ። ከጥቂት አመታት በኋላ ያጋጣሚ ነገር
ጉዱ ካሳ በዚያው በኩል ይመጣል ። ያገኛታል.........



የ«ጦቢያ» ን ታሪክ እንቀጥል ።

ዋህድ ፥ ነጋዴው ለዋለላቸው ውለታ ምስጋና ለማ
ቅረብ ነጋዴውን ፍለጋ ከቤቱ ይወጣል ። ብዙ ችግርም
ይደርስበታል ። አንድ ቀን በሩቁ ትልቅ የነጋዴ ሰፈር
ያያል ። እሰፈሩ ለመድረስ ወንዛወንዝ የበዛበት ሜዳ
ነበርና ቢለው ቢለው እርቀቱ ያው ይሆንበታል ።

«በመሀል ቤት ጀንበር ጠለቀችና ድንግዝግዝ አለ
...... በወፎች ጫጫታ ስፍራ የፈንጣው ድምጥና የጓ
ጉንቸሩ ፥ በያረንቋው ፥ በየረግረጉ ያለው ጉርጥ ዋየታ
ተቶካበት...... ባንድ ወገን ተዝሳው ፥ ባንድ ወገን
ቀበሮው ሲጯጯሁ ሳለ ፥ ባንድ ወገን ጅቡ እሙኝ ይል ፥
ነብሩ ያጉርር ፥ አንበሳው ይገስል ጀመር...... ጨለ
ማው እያደር ባሰ... መንገዱም ጠፋው ፤ ልቡም መባባት
ጀመረ ። በቀኝም በግራም በፊትም በኋላም ቢአይ ሁሉም
ጅብ ሁሉም ነብር ፥ ሁሉም አንበሳ መሰለው .........
በጨለማው እሻግሮ አንድ ቁጥቋጦ መሳይ አየና አራት
እግር ያለው የውነተኛው አንበሳ መሰለውና ነፍስና ሥጋው
ተለያየበት ......... የሚንቀሳቀስ ፥ ዘሎም ሊይዘው ልቡል
ልተው የሚል መሰለው......... ለዚያ አንበሳ ብዙ ሰው
የመጣበት እንዲመስለው ብሎ ድምጡን ባስር ባስራም
ስት ዓይነት እያደረገ አንድ ጊዜ ቃሉን ከፍ ፥ አንድ ጊዜ
ዝቅ አንድ ጊዜ ቀጭን ፥ አንድ ጊዜ ጉርናና እያደረገ ፥ እንዳ
ንድ መንጋ ሰው...... ይጯጯህ ገባ... ያው በገዛ ፍርሃቱ
የፈጠረው የቁጥቋጦ አንበሳ የሚከተለው መሰለው.........
መብረክረኩ ባሰ......... ቀጭን ሳብ መጣና በገላውም
በፊቱም ተሰራጨበት......... ኋላ ግን ድምጡም ሰለለበት፤
ጉረሮውም ይብሰውን ተዘጋበት......... ያው የውሸት
አንበሳ ንቆት ዝም ያለው መሰለው ። ዋህድ መጠራጠር
ጀመረ......... በጉልበቱ ተንበረከከና ትክ ብሎ... ሲመለ

ከት ጥቂት ጥቂት የሚንቀሳቀስ መሰለው…….ትክር ብሎ ባስተዋለ ጊዜ ይልቁንም ተመንቀሳቀሱ ወደሱ መራመድ የጀመረ መሰለው……. ባባና ተተንበረከ ከበት ጠጠር አፍሶ ወደ ፊቱ ብትን አደረገ…… አንድ ድርጭት ተተሸሸግሁበት ተገለጥሁ ብላም እንደሆነ አይ ታወቅ እግር ቅጠሉን በክንፍዋ እስሸብራ ተነሥታ በረ ረች ። ዋሀድም ያው እውሬ ደርሶ አነቀኝ መስሎት ትንፋሹን አቋርጦ እንደ ሞተ ታለበት ተዘረጋና መንቀ ሳቀሱም ቀረ…….» [5]

ይህ በሰፊው የተጠቀሰ አንቀፅ መስተዋታዊ ያቀ ራረብ ዘዴ ነው ። ዋሀድ ደነገጠ ፤ ፈራ ፤ ተንቀጠቀጠ በማለት ብቻ ሳይወሰን ፥ ፍራቱን ጥሩ አድርጐ በጉልሀ የሚገልፅ ። በታሪኩ ውስጥ ጥቅሙም የድርጊያውን ውጤት ለማወቅ ልብን ማንጠልጠል ነው ። እርግጥ ትንሽ ተጋኗል ። ባጭር ጊዜ ውስጥ የቀበሮ ፥ የተ ኩላ ፥ የጅብ ፥ የነብር ፥ የአንበሳ ድምፅ ሰማ ብለን ለማመን ያዳግተናል ። ሆኖም ንባቡን በምንቀጥልበት ቁጥር ልዩ ልዩዎቹ ሁነቶች በድንጋጤ ምክንያት በዋ ሀድ ሀሊና ውስጥ የተፈጠሩ መሆናቸውን እንገነዘ ባለን ። ስለዚህ የአውሬዎቹንም ድምፅ የሰማ መስሎት ይሆናል በማለት ከስህተት ሳንቆጥርበት እናልፈዋለን ። ፅሁፉም እንደገና የመታመን ደረጃውን ይይዛል ።

እዚህ ላይ አንድ ልናጤነው የሚገባ ነገር አለ ። ሊታመን የቻለው በህሊና ውስጥ የተፈጠረ ስለሆነ ብቻ አይደለም ። ቦታው ብጣም የተጠቃለለ ስለሆነም ጭምር ነው ። በተለይ ስላውሬዎቹ የተገለፀው በቦታ የተወሰነ ቢሆን ኖሮ የሚከተሉት አይነት ጥያቄዎች በአእምሯችን ይፈጠሩ ነበር ።

[5] አፈ ወርቅ ገ/የሱስ ፥ 'ጠቢያው' ፤ ገፅ 17—19 ።



(1) በሀገራችን ተኩላና ነብር አሉ ወይ ?

(2) በጐንደር አካባቢ አንበሳ ይኖራሉይ ?

(3) በዚህስ አካባቢ ባንድ ሌሊት ተኩላ ፥ ጅብ ፥ አንበሳና ነብር ሊገጥሙት ይችላሉ ወይ ?

(4) የተጠቀሱት አውሬዎች መኖራቸው ቢረጋገ ጥም እንኳ ፥ ተአማኒነታቸው ሳይደመሰስ በኪነ-ፅሁፍ ልንጠቀምባቸው እንችላለኖይ ?

ስለ እንስሳት የሚያጠኑ ሊቃውንት እንደሚሉት ፥ በሀገራችን ነብርና ተኩላ አይገኙም ። የሚገኙት የድመት ዘር የሆነው ጢቃጠቋግ (በእንግሊዝኛ leopard የሚሉት) አውሬና ቀበሮ ናቸው ። አንበሳ ግን በኢትዮጵያ ይገኛል ። ቢሆንም በጐንደር አካባቢ መኖሩ የተረጋገጠ አይደለም።

የሆነው ሆኖ ዋናው ነገር የአውሬዎቹን መኖር አለ መኖር መጠየቁ ወይም ማረጋገጡ አይደለም ። መኖራ ቸውን ጠይቀን ብናረጋግጥም ፥ እነዚህን እውነቶች እን ዳሉ ወስደን በኪነ-ፅሁፍ ውስጥ ልንጠቀምባቸው እን ችላለኖይ ነው ።

በዛሬው ዘመን ፥ በኪነ ጥበብ አለም አስቸጋሪ መስሎ የተገኘው ተአማኒነትን የመፍጠሩ ጉዳይ ነው ። በህይ ወት የሚገጥሙንና የምናያቸው ነገሮች ከልብ ወለድ ስራዎች ይበልጥ የማይታመኑ እየሆኑ በመሄድ ላይ ናቸው ። ያንዳንድ ሰዎችን የህይወት ታሪክ የተመለከትን እንደሆነ በርግጥ እንዲህ ያሉ ሰዎች ኖረዋል ወይም በመ ኖር ላይ ናቸው ብለን ማመን ያዳግተናል ። አብረን እየ ኖርን እያወቅናቸው እንኳ እነሱነታቸውን እንጠራጠራለን። ከሰውነት በላይ ሰውነት ያላቸው እየሆኑብን ። አንዳንዴ በኪነ ጥበባት ስራዎች ልንይዛቸው እንሞክራለን።የያ ዝናቸውም ይመስለናል ። ብዙ ጊዜ ግን ያመልጡናል።

ፅሁፋችሁ ፥ ስእላችሁ ምነው ተአማኒነት አጣ ብለን ከያንያኑን ስንጠይቃቸው ፥ ምነው እከሌን አታውቁትም ፤ እንዲህ ያለውን ቦታ አላያችሁትም ፤ ሄዳችሁ ልታረጋግጡ ትችላላችሁ ይሉናል ። እንሄዳለን ። እናረጋግጣለን። የፃፉት ፅሁፍ ወይም የሳሉት ስእል በርግጥ እውነታን የተከተለ ሆኖ እናገኘዋለን ። ነገር ግን ፥ ፅሁፋቸውን ወይም ስእላቸውን እንድንቀበለው አያደርገንም ።

ፅሁፍ ወይም ስእል ራሱን የቻለ አለም ነው ። በህይወት እውነት የሆነን በፅሁፍ እውነት ለማስመሰል ዘዴ ይጠይቃል ። የህይወት እውነተኝነት የሚለካው በህይወት ነው ። የኪነ-ፅሁፍም እውነተኝነት በዚያው እኪነ ፅሁፉ ውስጥ በቀረበው ። እባ አለም ለምኔን በህይወት ሳሉ እንደዚያ አይነት እውሬዎች ከበዋቸው ይሆናል ። ነገር ግን ፥ በፅሁፍ ውስጥ እንደዚያ አይነት ሁኔታ ሆኗል ብሎ ማሳመን ልዩ ጥበብ ነው ። ያስቸግራል ።

በኪነ-ፅሁፍ ውስጥ እውነት ተብሎ የሰፈረው ከፅሁፍ ውጪ የሚገኝ አለማዊ ምስክር አይሻም ፤ እዚያው እውስጡ ከሚገኘው እንጂ ። እንዲሁም በህይወት የምናዩው ሁነት ከዚያው ከህይወት — በኪነ-ፅሁፍ ውስጥ የሚገኝ ምስክርነት ሳይሆን ።

እንግዲህ ከውጪው አለም ምስክር የሚሻ ፅሁፍ ደግሞ ፥ ውጪውን አለም ብዙ ሰው እንደሚያውቀውና እንደተረዳው አድርጐ በመውሰድ ፥ በፅሁፍ ውስጥ ደሞ የሚታመንበትን ዘዴ መፈለግ ይኖርበታል ። በኪነ-ፅሁፍ ውስጥ አስፈላጊው ፥ አፍአዊውን ኑሮ እንዳለ መገልበጡ ሳይሆን የተገለበጠውን ሊሆን የሚችል ድርጊት ነው ብሎ አንባቢ እንዲቀበለው እማድረጉ ላይ ነው ።



ወደ 'ጠቢያ' ታሪክ እንመለስ ።

ዋህድ በዚያ ሌሊት ቁልቁለቱን እየተተማተመ ሲጉተት ተወራጅ ወንዝ ይደርሳል ። ውሃ ጠምቶት ነበርና ይጠጣል ። እዚያው እንደ ወደቀ አንዲት ውሃ የጠማት የነጋዴዎች በቅሎ ችካሏን ነቅላ አምልጣ ኖሮ ከወንዙ ትደርሳለች ። ዋህድ እንደ ምንም ብሎ ይይዛትና እንዳወቅሽ ወደ ሰፈርሽ ውሰጅኝ ብሎ ይቀመጥባታል ። ከሰፈሩ ሊደርስ ጥቂት ሲቀራቸው ጕረደማኖች ዱካ ሰምተው ሲሮጡ ይደርሱበታል ። ከበቅሎዋ ወርዶ ይሸሸጋል ። ሊያመልጥ አልቻለም ይያዛል ። የሰውነቱ መጐሳቆልና መደማማት ያሳጣዋል ። ርዳታን በማግኘት ፥ እንዲያዝኑለት በማድረግ ፈንታ ለሌብነቱ ምስክር ይሆንበታል ። ሲደበድቡትም ያድሩና በማግስቱ የሞተ መስሏቸው ጥለውት ይሄዳሉ ። ኩበት ለቃሚ ሴት ታገኘውና ርዳታ ታደርግለታለች ። የቧም ልጅ ባረመኔዎች ተይዞ መሸጡን ታጫውተዋለች ። የልጃቸውን ስምና ያገሩን ስም ትነግረዋለች ።

ይህ እንግዲህ ለታሪኩ አስፈላጊ የሆኑ ስድስት ጭብጦችን እንደያዘ መመልከት ይኖርብናል ፤

(1) ከመንገዱ አስቸጋሪነት የተነሳ የዋህድ ሰውነት መቆሳሰል ፥
(2) እንደዚያ ውሃ ጠምቶት ከወንዝ መድረሱ ፥
(3) እንደ ዚያ ደክሞት እርዳታ ሲፈልግ ፥ በቅሎዋ ውሃ ልትጠጣ እሱ ወደነበረበት ቦታ መምጣቷ ፥
(4) የጉረደማኖቹ ዱካ ሰምቶ መምጣት ፥ የዋህድ መደብደብና መጣል ፥
(5) የኩበት ለቃሚዋ መምጣትና ርዳታ ማድረግ ፥
(6) የኩበት ለቃሚዋ ልጅ ባረመኔዎች መሸጥ ፤

ምን ማለት ነው እንግዲህ ይኸ ?

በአንደኛው ቁጥር የተጠቀሰውን እንመልከት ፣ በዚያ ክበሬው በጠቅስነው ስእላዊ እንቀፅ ፣ ፍራትን ገዝፎ እንዲታይ አድርገውታል ብለናል ። ታዲያ ድካማቸው ለዚሁ ብቻ ነው ? አይደለም ።

(ሀ) ከዚያ ሁሉ መከራው በኋላ ምን ይውጠው ይሆን ብለን እንድናስብና የማወቅ ፍላጐታችን ተኮርኩሮ ጉጉት እንዲፈጥርብን ተጠቅመውበታል ።

(ለ) ሰውነቱን በማጕሳቆልና በማቆሳሰል ፣ ድብደባ የለመደ ወሮበላ ስላስመሰሉት ፣ ከነጋዴዎቹ ለሚደርስበት ዱላ ፣ በነጋዴዎቹ እንዳንፈርድ ፣ አዘጋጅተውበታል ።

(መ) ከቁልቁለቱ ወደ ወንዙ ፣ ከወንዙ ወደ በቅሎው ፣ ከዚያም ወደ ጕረደማኖቹ መሸጋገሪያ ድልድይ አድርገውታል ።

ሁለተኛውን ቁጥር እንመልከት ፣

(ሀ) የሚጓዝበትን ሀገር "ወንዛወንዝ የበዛበት ሜዳ" ነው ብለው አስቀድመው በመጥቀስ ፣ ውሃ ማግኘቱ አጋጣሚ አለመሆኑንና የወንዙ መጠቀስ ያለምክንያት ያለመሆኑን አስገንዝበውበታል ። (በኪነ-ፅሁፍ ውስጥ አንድ ሰው ሽጉጥ መያዙ ከተነገረን ሲሰራበት መታየት አለበት ። አለዚያ ጌጥነቱ ብቻ በቂ አይደለም ።)

(ለ) ከዚያ ሁሉ ድካሙ በኋላ ፣ ውሃ እንዲጠጣ በማድረግ ፣ ተግታን ሰጥተውበታል ። አንድ ሌሊት ሙሉ በጕረደማኖቹ ለሚወርድበት ዱላ ቻይነት እንዲኖረው ። "ምነው አልበዛም !" ብለን ሰሚዎች ወይም አንባቢዎች የታሪኩን ታማኝነት እንዳንጠራጠርባቸው ማለት ነው ።

ሶስተኛውን ቁጥር እንመልከት ፣

(ሀ) የነጋዴዎቹን መንደር ከመምሸቱ በፊት ከሩቅ



ተመልክቶ ወደዚያው ይጣደፍ ስለነበረ ፣ የበቅሎዋ ወደ ወንዙ መምጣት ፣ እስፈሩ ለመድረሱ ምልክት ይሆነዋል ።

(ለ) ተስፋና ብርታት ይሰጠዋል ።

አራተኛውን ቁጥር እንመልከት ፣

(ሀ) በቅሎዋን እንደ ተቀመጠ እሰፈር ቢደርስ ኖሮ ፣ ሰውነቱ የተጕሳቆለበት እውነተኛው ምክንያት ታውቆ ፣ ሌባ ከመባል ይድን ስለነበረ ፣ በጕረደማኖቹ መያዙ ፣ ለታሪኩ ሀረግ ሌላ ቅርንጫፍ ይሰጣል ።

(ለ) አስቀድሞ የነጋዴ እጣ ክፍል እንደ ነበረው ስለምናውቅ ደግ ደጉን እንድንመኝ በማድረግ ፣ ያልታሰበው ውርጅብኝ ድንገተኛ ጥፊ እንደ መታው አይነት እንዲሰማን ያደርጋል ።

(መ) ሲደበድቡት አድረው ጥለውት ሲሄዱ ስናይ ደግሞ — እንደገና አሁንም "ምን ይውጠው ይሆን ?" ብለን በመጠየቅ ለማወቅ በመፈለግ ማንበብ እንቀጥላለን ።

አምስተኛና ስድስተኛ ላይ መልሳችንን እናፃፍለን ፣

(ሀ) ኩበት ለቃሚዋ ከሞት ታድነዋለች ።

(ለ) የኩበት ለቃሚዋ ልጅ ለመጀመሪያ ጊዜ በታሪኩ ውስጥ ይገባል ።

(መ) የልጅዋ መሸጥ ፣ አስቀድሞ የተነሳንበትን ፣ የዋህድን አባት መሸጥ በማስታወስ ታሪኩን የክብነት መልክ ይሰጠዋል ።

ታሪኩ በዚህ አይነት መንገድ እየተደጋገመ ይፈፀማል ። እሀይቅ ውስጥ የተወረወረ ድንጋይ ፣ ትንሽ ክብ ፣ ትልቅ ክብ ፣ ትልልቅ ክብ እየፈጠረ ፣ ተዘራዝሮ ከውሃው ጋር እንደሚዋሃድ አይነት ታሪኩም ከህይወታችን ጋር ተዋህዶ።

እንግዲህ ታዲያ ታሪክን ለመፃፍ ወይም ለመተረክ ምን ምን ያስፈልጉናል ማለት ነው ?

<u>ከተራኪው በኩል የሚፈለገው</u>

(1) በክፉውም ሆነ በደጉ ፍርድ ለመስጠት የማይቸኩልና በግብረ ገብ አስተያየቱ ሆደ ሰፊ የሆነ ፤

(2) ስለሚናገረውም ሆነ ስለሚፅፈው ሁኔታ ወይም ድርጊት ምርምር ያደረገና ጥርት አድርጎ አውቆ ከሰውነቱ በማዋሀድ ፤ ሰብእናን (ሰውነትን) በሚያሳይ መንገድ የተዋሀደውን የማቅረብ ችሎታ ፤

(3) በታሪኩ በሙሉ የተዋጠ የሚያስመስል ያየ ፃፍ አየር (ተራኪው ግዴለሽነት ከታየበት አንባቢ-አድማጭምአይከተለውም) ፤

(4) በቃላት ስእሊነቱ ፤ ቦታንም ሆነ ድርጊትን ፤ ቁልጭ አድርጎ የማሳየት ችሎታ ፤

<u>ከታሪኩ የሚጠበቀው</u>

(1) ቁልጭ ብሎ የሚታይ የጊዜ አቀነባበር ፤ የቦታ አሳሳልና ፤ ግልፅ ያለ የባለ ታሪክ አቀራረብ ፤

(2) በጊዜ የተከታተለ ድርጊት — "ሲጓዝ ተመሸበት ሲአድር ፤ ሲሄድ ሲሄድ ተመሸበት ሲአድር" እያለ ማደግ — (ጦቢያ) ገፅ 29 ። *

(3) በተከታታይነታቸው ብቻ ሳይሆን ፤ ህብረተሰቡ በሚሰጣቸው ዋጋና አክብሮት የተመረጡ ጥዩቆችን (ፋይዳዎችን) የያዙ ድርጊቶች (አንድ ሰአት ከገበሬው

*ሌሎቹን የጊዜ ማከታተያዎች ገፅ 267-277 ተመልከት ።



ጋር ቁጭ ብዬ አወራሁ ። ባራት አመት ዩንቨርስቲ መፃህፍት ንባብ ካገኘሁት የበለጠ ጥቅም አተረፍኩ እንዲያሰኝ ሆኖ ፤ ማለት የተገኘው ጥቅም ከጊዜና ከድካም በላይ ዋጋ ያለው ሆኖ እንዲገመት በማድረግ ) ፤

(4) ከእንግዲህስ ምን ይውጠው ይሆን ብሎ የሚያሳስብ ጉጉትን የሚፈጥር ድርጊት ፤

(5) ባንድ መልኩ ብቻ እያታለለ ሲስበን የነበረን ሁኔታ ሌላ መልኩን ድንገት እንዲያሳይ የሚያደርግ ሀተታ ፤

(6) ባድማጩ ወይም ባንባቢው <u>እሙንነትና ተቀባይነት</u> ማግኘት ።

ጥንታዊ የትረካ አቀራረብ እንግዲህ ፤ ከዘመናዊ ልቦለድ አንፃር ሲታይ ገና ጮርቃ የነበረ ቢመስልም ፤ ለዘመናዊ ልቦለድ አስፈላጊ ናቸው የምንላቸውን ዋና ዋና ክፍሎች (ማለትም ፤ ታሪክ ፤ ሴማ በታሪኩ አማካይነት እንዲታወቅ የተፈለገው ሀሳብ ወይም ጉዳይ) ፤ ባለታሪክ ፤ ተራኪ (ታሪኩን አቅራቢ) ፤ አካባቢ (ደጀን) ፤ ትልም (የታሪኩ አቀራረብ) ፤ ፎርም (የታሪኩ ማቅረቢያ ቅርፅ) እና (ማቅረቢያ ቋንቋዉ) የያዘ እንደነበረ ማጤን ያስፈልገናል ።

# ምዕራፍ ሰባት

# ዘመናዊ ትረካ

ስሙ እንደሚያመለክተው ተራኪ ፅሁፍ ፣ በጊዜ ገደብ ትልም እየተሳሳበ፣ በነባር መዳረጊያዎች አማካይነት ድርጊያንና ተደራጊን (ወይም ስንሰለታዊ ሁነታዎችን) ማውጊያ ወይም መተረኪያ ነው ።

## 7.1. ትልም

"ትልም ፣ በድርጎች ፣ ሁነታዎችና መዳረጊያዎች አመራረጥ ጥበብ ላይ የተመሰረተ ፣ እንደሚከተለው የጊዜ ገደብ የተለያዩ ውጤት የሚኖረው ፣ በቅድሚያ ታስቦበት የሚታቀድ የትረካ (የነባር መዳረጊያዎችና ሁነቶች) ዝምድና ስልት ነው ።

### 7.1.1 የጊዜ ገደብ

ትልም በተወሰነ ጊዜ ገደብ ውስጥ የሚሳሳብ እንደ መሆኑ ፣

(ሀ) በጊዜ ቅደም ተከተል ተያይዞ ፣

(ሀ ሁ ሂ ሃ. . .)

(ለ) መነሻውን ዘሎና ሲያስፈልግ ወደኋላ ተመላልሶ ፣

(. . . ሁ ሀ ሂ . . .)

(መ) ወሳኝ ከሆነው የታሪኩ ክፍል ጀምሮ ፥ ፊትና ኋላ ሳይል ያንኑ አጉልቶ በማሳየት ፥
(ሂ ሃ ሄ ሀ....)

ይቀርባል ። በ(ሀ) በተመለከተው ፥ በተከታታይ የጊዜ ገደብ (ሰኞ ፥ ማክሰኞ ፥ ረቡእ . . . መስከረም ፥ ጥቅምት ፥ ህዳር . . . 71 —72 —73 ዓ/ም ወዘተ ... እያለ) ፥ በ (ለ) ፥ ከታሪኩ መካከል ጀምሮ እልፎ አልፎ ወደኋላ በመመለስ ፥ በ(መ) ፥ ወሳኝ የሆነውን የትረካ ክፍል ብቻ በጭቆ አውጥቶ በመተረክ ፥ ይካሄዳል ማለት ነው ። በእያንዳንዳቸው ገደቦች መሰረትም የተለያዩ ትልሞች ይኖሩናል ።

### 7.1.2 ነባር መዳረጊያዎችና ሁነቶች

#### (ሀ) ነባር መዳረጊያዎች

ነባር መዳረጊያዎች ፥ በአብዛኛው ገፀ - ባህርያትን (ባለታሪኮችን) ፥ የታሪኩን ሜዳ ፥ የታሪኩን ዘመንና ወቅት፥ የኑዋሪዎችን የእለት እለት ተግባርና የመሳሰሉትን የሚያጠቃልሉ የታሪኩ ደጀንና የታሪኩ ባለቤቶች ናቸው ።

(1) ገፀ - ባህሪያት

ገፀ - ባህርያት የታሪኩ ባለቤት ወይም ታሪክ ፈጣሪዎቹ (ባለታርኮቹ) ናቸው ፤ ሰውን ፥ እንስሳን እና ግኡዝ ነገሮችን ያጠቃልላሉ ።

እስረጅ ፥

ከሰው — አስፋው ፥ ፋጡማና የመሳሰሉት ...
ከእንስሳ — አንበሳ ፥ ጠጣ ፥ ፈረስ እና የመሳሰሉት ...
ከግኡዝ ነገሮች— መሬት ፥ ወንበር ፥ ጨረቃ እና የመሳሰሉት ...

( በተጨማሪ ከገፅ 331—344 ተመልከት ። )



(2) የታሪኩ ሜዳ

የታሪኩ ሜዳ በታሪክ ደጀንነት የሚያገለግሉት ሁሉ ናቸው ።

እስረጅ ፥

- ስነ-መሬቱ ፥ የቦታው አቀማመጥ ፥ ትእይንቱ ፥ አዝርእቱና የመሳሰሉት ፥
- የገፀ-ባህርያቱ ስራ አይነትና የእለት በእለት የአኗኗር ጠባያቸው ፥

  ግብርና ፥ እናጢነት ፥ የፋብሪካ ሙያ (በተጨማሪም ደስታቸውን ፥ ሀዘናቸውን የሚገልፁባቸው ሁኔታዎችና የእረፍት ጊዜያቸውን ማሳለፊያቸው) እና የመሳሰሉት ፥
- ታሪኩ የተከናወነበት ዘመንና ወቅት (ታሪካዊ ዘመኑ ፥ አራቱ የአመት ክፍሎች እና የመሳሰሉት) ፥
- የገፀ-ባህርያቱ አጠቃላይ አካባቢ— ባለታሪኮቹ የሚንቀሳቀሱበት የኢኮኖሚ ፥ የርእዮተ-አለም፥ የእውቀት ፥ የማህበራዊ እድገት ፥ የሞራል ፥ የእምነትና የአጠቃላይ ቀስቃሽ ስሜት ይዞታ።

  (በተጨማሪ ከገፅ 344—350 ተመልከት ።)

ባጠቃላይ በዚህ በ(2) ቁጥር ውስጥ የሚጠቃለሉት 'የእንዲህ እንዲህ ነው' አባባሎች ናቸው ። በሌላ አነጋገር አባባሎቹ የሚገልፁት ፥

— የነዋር መዳረጊያዎችን ማንነት ነው ።

አስረጅ ፡

‘ታምራት ወታደር ነው ።’
‘አዲስ አበባ ዋና ከተማ ነው ።’
‘ጉራጊኛ የሴም ቋንቋዎች አባል ነው ።’

እና/ወይም

— የነባር መዳረጊያዎችን አባላት ባህርያትና መከተቻ ስሜቶችን ነው ።

አስረጅ ፡

‘ታምራት ሳቂታና ተጨዋች ነው።’
‘አዲስ አበባ ከአንድ ሚሊዮን በላይ ህዝብ ይኖርበታል ።’
‘ከተራራው ደረት ላይ ቀጭን መንገድ አለ ።’

ከላይ የተመለከቱት አባባሎች ከተራኪው አስተያየትና ፍርድ ጋርም ይቀርባሉ ።

አስረጅ ፡

‘ታምራት ኮምጫጫ ወታደር ነው።’
‘ታምራት ሳቂታና ተጫዋች ሲሆን ሲከፋው ደግሞ አያድርስ ።’

(ለ) ሁነታዎች

ሁነታዎች ሂደት ፡ ለውጥና እድገት የሚታይባቸው ድርጊያዎች እና/ወይም ተደራጊዎች ናቸው ።



(1) ድርጊያዎች

ድርጊያዎች ፡ ገፀ-ባህርያቱ በታሪኩ ውስጥ የሚያከናውኗቸው ፡

‘እንዲህ አደረገ እና እንዲህ እንዲህ ሆኑ አባባሎች’ ናቸው ። አበይት ሁነቶችና ድርጊያዎች የሚከተሉትን ይይዛሉ ።

(ሀ) በአካል እንቅስቃሴ የሚገለፁ

አስረጅ ፡

“ወደ ቤቱ ገባ ።”
“እጁን አነሳ ።”

(ለ) ሀሳቦች

ባእምሮ ውስጥ በቋንቋ ቢገለፁም በንግግርም ሆነ በአካል እንቅስቃሴ የማይከሰቱ ፡

አስረጅ ፡

“እሱ ደስ ብሎኛል” አለ ።
“እሱ መጨረስ አለብኝ ብሎ” አሰበ ።

(መ) ስሜቶች

ገፀ-ባህርያቱ በቃላትም ሆነ በአካል እንቅስቃሴዎች እሚልተው የማይገልጿቸው ፤ በተራኪው የሚሚሉ ፡

አስረጅ ፡

“እንቅልፍ እንቅልፍ አለው ።”
“እንደ መደናገጥ አለ ።”
“ቅዝቃዜ (ሙቀት ፡ ሽካሬነት እና የመሳሰለው) ተሰማው ።”

(ሰ) ጢኖቶች (ትኩረቶች)

በገፀ-ባህርያቱ አይን ተጢነው በአእምሯቸው የሚከሰቱ ሁኔታዎችና ነገሮች ፤ በተራኪው የሚሟሉ ፡

አስረጅ ፡

"አንድ ነገር የተቅመዘመዘ መሰለው ።"

"እውሬው በጭለማው ውስጥ ሲላወስ ታየው ።"

(ረ) እምብዛም ያልተጠቆሙ ስሜቶች

በግልፅ ታውቀው እንዲህ ናቸው የማይባሉ ደብዛዛ ስሜቶች — እንድ ሰው ሲቀመጥ ሲል ድንገት ወንበር ከስሩ ሲነሳ የሚሰማውን አይነት -በተራኪው የሚሟሉ ፡

አስረጅ ፡

— አይኗ ሟ አለባት ።
— ልቡ እየናረ አስቸገረው ።

በዚህ ውስጥ ቃላት እምብዛም የማይገልፅዋቸው አእምሯዊና ልባዊ ስሜቶች ሁሉ ይጠቃለላሉ (የደስታ ፥ የህመም ፥ የቅናት ፥ የትልቅነት እና የመሳሰሉት) ።

(ሸ) ከዚህ በላይ የተጠቀሱት አምስቱ ወይም ሌሎች ድርጊያዎች ያሉባቸው ጭውውቶች ፡

አስረጅ ፡

'ደስ ብሎኛል' አለ ።
'መጨረስ አለብኝ' ብሎ አሰበ ።



)2) ተደራጊዎች

የታሪኩ ገፀ-ባህሪ ወይንም ማንኛውም ሌላ ባለታሪክ (እንሰሳ ወይም ግኡዝ ነገር) የድርጊት ተቀባይ ሆኖ የሚገለፀው ሀሳብ ነው ።

አስረጅ ፡

'እንደ ቀጭን አየር ከሁለንተናው እየናኘ የሚሽረሽረው ነገር አይኑን እንባ ሲያስቋጥረው ተሰማው ።'

በዚህ አረፍተ ነገር ፥ በግልፅ በስም ያልተጠቀ ሰው ገፀ - ባህሪ ተደራጊ እንጂ አድራጊ አይደለም ። ባጢቃላይ በ(2) ውስጥ የሚጠቃለሉት ፥ 'እንዲህ እንዲህ ተደረገ' የሚሉ አባባሎች ሁሉ ናቸው ።

የሁኔታ አባባሎች ማቅረቢያ

የሁኔታ አባባሎች ሁለት የማቅረቢያ ዘዴዎች አሏቸው ፤ እነሱም የታሪኩን ሂደት የማሳየት እና የመንገር ናቸው ።

አስረጅ ፡

'ምሳዬን በላሁ' አለ ታደሰ ። በአብዛኛው ፥ የታሪክ ሂደትን የማሳየት ተግባር ፥ ጭውውታዊ ነው ። እና

«ታደሰ ምሳዬን በላሁ አለ» — የመንገር (የመተረክ) አቀራረብ ፤

በዚህ አይነት እያንዳንዱ ሁነታዎች የየራሳቸው የሆነ መከሰቻ አላቸው ማለት ነው ፤ ራሳቸውን ችለውና ለየብቻቸው ተለይተው የሚቀርቡበት ።

(መ) አጉራ (አቢይ) እና አሟፋሪ (ንኡስ) መዳረጊያና ሁነታን መምረጫ ስልት

(1) እንደገና ለመመልከት ያህል ፣

• የመሆንና የመኖር አባባሎች ፣

አጅ ፣

• ታደሰ ሰው ነው ።
• ታደሰ በ1973 ዓ/ም ተወለደ ።
• ታደሰ ሰፊ ቤተሰብ ነበረው ።

• የማድረግ (የድርጊያ) እና የመደረግ (ተደራጊነት) አባባል በመሆናቸው ፣

አጅ ፣

• ታደሰ ውሻውን ገደለ ።
• ታደሰ ወደ ቤቱ ገባ ።
• ውሽንፍሩ አቅጣጫውን አሳተው ።
• አፍንጫን በመስቀል ፣ በመነክነክና በመነቅነቅ ፣ ቀስ እያለም በማንኮርኮር ፣ በመሳሳቅ ፣ በመዘባበት ፣ ላንቃን በመለቆድ ፣ በማስጮህ ፣ ቀስ እያለም በማጉረምረም ፣ በማንኩራፋት የጀመረው ውክወካና ውካታ ሳይታሰብ ደርሶ የተናጋሪውን ድምፅ ዋጠው ።

(2) የመምረጫ ስልት

• የመዳራረጊያና የሁነታ አባባሎች

ለየብቻቸው ፣ ራሳቸውን የቻሉ አባባሎች መሆናቸው ብቻ አይደለም ፣ መጠን ያለበት ። የተለያየ ጠቃሚነትና



ክብደት ያላቸው መሆኑም ጭምር ነው ። በውስጣቸው ፣ አሸጋጋሪና አቀባባይ የሆኑ አበይት ሁነታዎችና አሟፋሪ የሆኑ ንኡሳን ሁነታዎች አሉ ። አበይት ሁነታዎቹ የታሪኩ አጉራዎች ናቸው ። ባጋጣሚ አንዳቸው ቢወጡ የሌሎቹ ትርጉም ይናዳል ። ታሪኩን እስከ መጨረሻ የሚያራምዱ የሀሳብ ሰንሰለቶች ናቸው ። ንኡሳን ሁነታዎቹ ደግሞ ሳጋዎችና ማሟያዎች ናቸው ፤ ገላጭ ፣ ምስሉ ከሳችና አብራሪ በመሆን ፣ የሚያገለግሉ ።

(ከ142—169 ገፅ ተመልከት ።)

አስረጅ ፣

(1) የቤተ ርስት ሹም ነበር ።
(2) ቆንጆ ሚስት አገባ ።
(3) ጉቦ አምጡ ሆነ ስራው ።
(4) በየቦታው ቅምጦች ያዘ ።
(5) ሚስቱ ጥላው ሄደች ።

ከዚህ በላይ ከ(1) እስከ (5) የተመለከቱትን ሁነታዎች እያንዳንዳቸውን ባሉበት ሁኔታም ሆነ ወይም እያንዳንዳቸውን በየአንዳንድ አንቀፅ ወይም አንቀፆች ፣ በየአንዳንድ ምእራፍ ወይም ምእራፎች ተብራርተው ሊተረኩ እንደሚችሉ አይነት አድርገን ብንወስዳቸው ፣ ቁጥር (1) እና (3) አሟፋሪ ሁነታዎች ፤ ቁጥር (2) ፣ (4) እና (5) አበይት ሁነታዎች ናቸው ። ይኸም ማለት በ (1) እና በ(3) ቁጥሮች ከተመለከቱት በስተቀር የቀሩት ሶስቱ የጊዜ ሰንሰለት ሳይለቁ ታሪኩን የሚያራምዱ የታሪኩ አጉራዎች ናቸው ማለት ነው ።

እዚህ ላይ የጊዜ ሰንሰለት ስንል ፣ ታሪኩ የተከናወነበትን ተፈጥሯዊ የጊዜ ቅደም ተከተል እንጂ ደራሲው ታሪኩን ያቀረበበትን ቅደም ተከተል አይደለም — ለምሳሌ

መወለድ ፣ ሚስት ማግባት ፣ መሞት — የተፈጥሮ ህግጋትን ተከትለው የቀረቡ ሲሆን ፣ በደራሲው አቀራረብ ረገድ ግን ሚስት ካገባበት ጊዜ ጀምሮ አልፎ አልፎ ወደ ኋላ በመመለስ ስለ ልደቱ በማቅረብ ታሪኩ የተከናወነበትን ቅደም ተከተል እንዳስፈላጊነቱ ሊለዋውጠው ይችላል ። (ከገፅ 267-278 ተመልከት ።) ሆኖም ታሪኩን የሚሰማው ወይም የሚያነበው ፣ የታሪኩን ተፈጥሯዊ ቅደም ተከተል በሀሳቡ ውስጥ አዟዙሮ ለማጤን እንዳይቸገር ሆኖ መቅረብ ይኖርበታል ።

ስለሆነም ፣ ንኡሳን ሁነታዎች ጉድለት በታየበት ሁሉ በዘፈቀደ የሚገቡ አይነት መስለው እንዳይታዩ ያስፈልጋል ። አቢይ ሁነታዎች በጊዜ ቅደም ተከተል እንደሚቀናበሩ ሁሉ ንኡስ ሁነታዎችም ፅሁፉ ሊያስገነዝብ በሚፈልገው ሁኔታ መሰረት ነው መግባት ያለባቸው ።

ለምሳሌ ፣

(ሀ)

(1) የቤተ ርስት ሹም ነበር ።
(2) ቆንጆ ሚስት አገባ ።
(3) ጉቦ አምጡ ሆነ ስራው ።
(4) በየቦታው ቅምጦች ያዘ ።
(5) ሚስቱ ጥላው ጠፋች ።

ማለት

'የቤተ ርስት ሹም ስለነበረ ቆንጆ ሚስት ቢያገባም ፣ ቅምጦች ስለያዘ ጥላው ጠፋች ፤' ወይንም ፣
'የቆንጆ ሚስት ፍላጎቱን ለማርካት ሲል ጉቦ መቀበል ቢጀምርም ፣ ጉቦው ስላዘናናው



ቅምጦች ስለያዘ ፣ ሚስቱ ጥላው ሄደች ' የሚሉና ሌሎችንም እነዚህን መሰል ትርጉሞች ይሰጣል ።

(ለ) ሌላ ምሳሌ ደግሞ እንውሰድ ፤

(1) ቆንጆ ሚስት አገባ ።
(2) ሚስቱ ጥላው ጠፋች ።
(3) በየቦታው ቅምጦች ያዘ ።
(4) ጉቦ አምጡ ሆነ ስራው ።
(5) የቤተ ርስት ሹም ነበር ።

እዚህ ላይ ደግሞ የሚያሳየው ሚስቱ ጥላው መጥፋቷን ፣ ስለዚህም እሱ ቅምጦች መያዙን ፣ ቅምጦችንም መያዝ ገንዘብ ስለሚያሻው ጉቦ መቀበሉን ሲሆን ፣ የቤተ ርስት ሹም ስለ መሆኑ የተጠቀሰው ማንነቱን ለማመልከት ነው ።

በዚህ አይነት ንኡሳን ሁነታዎች ቦታ በለዋወጡ ቁጥር የተለያዩ ትርጉምና ስሜት ስለሚሰጡ አገባባቸው በጥንቃቄና በፅሁፉ አላማ መሰረት እንዲሆን ያስፈልጋል ።

(ሰ) የመዳረጊያና የሁነታ አባባሎች ጥቆማ ስልት

ሁነታዎችና ነባር መዳረጊያዎች እንደ ሁኔታው ፣ በቅርብ ከሚኖራቸው ትርጉም ውጪ የተለያዩ እንደ ርዳሪ ሁኔታዎችና ድርጊቶች ይጠቁማሉ ። ስለዚህም አባባሎቻቸው በጥንቃቄ መቅረብ ይኖርበታል ።

(1) የሁነታ አባባሎች ነባር መዳርጊያዎችን ወይም የነባር መዳረጊያ አባባሎች ሁነታዎችን ይጠቁማሉ ፤

ለምሳሌ፡

“ሜልቱ ወልዴን መታችው’ ቢል፣ የነባር መዳረጊያ አባባሎች የሆኑትን “ሜልቱ የምትባል ገፀ-ባህሪ አለች”ን እና፣ “ሜልቱ ተማች ናት”ን ይጠቁማል ።

በሌላ በኩል ደግሞ፣

“ ወልዴ አጥፊ ነው ” ቢል፣ የትረካ ሂደት አባባል አመልካች የሆነውን፣ “ወልዴ ብዙ ጊዜ ያጠፋ ነው ፤ ወደፊትም ማጥፋቱን ይቀጥላል ” ማለትን ይጠቁማል ።

(2) አንድ ሁኔታ ሌላ ሁኔታን ፣ አንድ ነባር መዳረጊያ ሌላ ነባር መዳረጊያን ይጠቁማል ፤

ለምሳሌ፡

“እዜብ እስቴርን ሰረቀቻት” የሚለው አባባል “ከሰረቀች በኋላ እዜብ ተያዘች” ወይም “ከሰረቀች ጀምሮ እስከዛሬ አልተያዘችም” የሚሉትን ሌሎች የትረካ ሂደት አባባሎች ይጠቁማል ።

በሌላ በኩል ደግሞ፣

“እዜብ ሌባ ናት” ቢል፣ “እዜብ ጥሩ ምግባር የላትም” የሚለውን ሌላ ነባር መዳረጊያ ይጠቁማል።

ሆኖም፣ ትረካ፣ ራሳቸውን ችለው የቆሙ የተለያዩ የአበይትና የንኡሳን ሁኔታዎችና የጥቆማቸው ጥርቃሚ ነው ማለት አይደለም ። ከዚህ በፊት ከገፅ 123 እስከ ገፅ 140 ስለ አንቀፅ አንድነትና ዝምድና፣ እና ከገፅ 142 እስከ 169 ስለ አንቀፅ ማሳደጊያ ዘዴዎች እንደ ተመለከትነው ፣



ትረካ፡

(ሀ) እያንዳንዱ ሁኔታና ነባር መዳረጊያ እንዳጋጠመ አብሮ አብሮ በመሆን የተከማቸበት ሳይሆን፣ አንዱ ከሌላው ጋር ተሳስሮ የተዛመደበት ነው ፤ በአንድ መንደርደሪያ (ግልፅም ሆነ ውስጠ ታዋቂ) ሀሳብ ወይም ጉዳይ ዙሪያ ፤ በሌላ አነጋገር፣ በጠጅ ቤት ውስጥ በተወሰነ ወቅት እንደሚሰሙት ልዩ ልዩ ወሬዎች፣ በተለያየ ጊዜና በተለያዩ ሰዎች ላይ ደርሰዋል ተብለው እንደሚወሩት አይነት ፣ ሁኔታዎቹና ነባር መዳረጊያዎቹ ያልተዋሃዱበት አይደለም — በግልፅ የሚታዩ የተለያዩና ልዩ ልዩ ቀለም ያላቸው ክሮች ተሰበጣጥረውና ተቀናባብረው በሁብረቀለማት የሸጉኑና ልዩ ልዩ የአጣላለፍ ቅርፅ ያለው ቡጋቿ እንደሚያስገኙት አይነት ነው እንጂ ።

(ለ) እያንዳንዱ አባባል ፣ ከአጠቃላይ ግቡ አንፃር እየታየ፣ በቅድሚያ በታሰበበት የአቀራረብ ተራና ግልፅ በሆነ ያቀነባበር ስርአት የተዘጋጀበት ነው ።

( ከገፅ 123 እስከ 169 ተመልከት ።)

ባጭሩ በ(ሀ) የተመለከተው በትረካው ውስጥ (ምን ሆነ ? በማለት) ምን ምን የተዛመዱ ሁኔታዎች እንደ ተካሄዱና ምን እንደ ተከሰተ አውቀን የምናሳውቅበት (የጽሁፉ ታሪክ) ሲሆን፣ በ(ለ) የተመለከተው ደግሞ (እንዴት ሆነ ? ብለን) የታሪኩን ሁኔታዎች አቀራረብ በቅደም ተከተል የምናቀርብበት ነው — አንባቢውም ሁኔታዎቹ እንዴት እንደሆኑ — የሚገነዘብበት ።

7.1.3 የድርጎች፣ የሁኔታዎችና የመዳረጊያዎች አመራረጥ

(ሀ) አመራረጥ

በአንድ ገፀ-ባህሪ አእምሮ ውስጥ እንኳ በአንድ ወር ወይም በአንድ አመት ውስጥ የሚመላለሱትን

ሁነታዎች ፣ ሀሳቦች እና ድርጎች ሁሉ መፃፍ በቀላሉ የሚገመት አይደለም ። በእያንዳንዱ ድርግ (ለምሳሌ በአንድ የዳንስ ምሽት ወይም በአንድ የሰርግ ቀን ወይም በግማሽ ቀን የእግር ጉዞ እና በመሳሰሉት የአንዱ ክንውኖች) ውስጥ የሚኖሩት ሁነታዎችና ሀሳቦች ከታሰቡማ ምዝገባው ፣ የትየለሌ ነው የሚሆነው ። በሁለትና በሶስት ገፀ-ባህርያት አእምሮ ውስጥ የሚመላለሱትን መመዝገቡስ ? በአንዱ ገፀ-ባህሪ ከተረዳነው መገንዘብ አያዳግትም ።

በዚህ አይነት ከተሄደም አንድ የተዛመደ ታሪክ ለመፃፍ እንደሚያስቸግር አያጠራጥርም ፤ ታሪኩ ዝምድና በማይኖራቸው ድርጎች ፣ ሁነታዎችና ሀሳቦች ተውጦ ስለሚቀር ። ስለዚህ ደራሲው ተጨናንቀው ከሚገኙት ድርጎች ፣ ሁነታዎችና ሀሳቦች ሁሉ አንድ አይነት ዝምድና ያላቸውንና ለአንድ አላማ በህብረት የሚሰለፉትን ብቻ መምረጥ ይኖርበታል ፤ ማለትም ፣

አንደኛ ፣ ከአስራ ሁለት ያህል (ከደስታ ፣ ከሀዘን ፣ ከፍርሃት ፣ ከፍቅር ፣ ከጥላቻ ፣ ከቅናት ፣ ከምቀኝነትና ከመሳሰሉት) ስሜቶች ውስጥ አንዱን ወይም ሁለቱን ብቻ መርጦ ማቅረብ ይኖርበታል ። ለዚያውም ቢሆን በሚገባ ተወስነው ። ለምሳሌ ፣ ሁለቱንም እንተወውና አንዱን እንኳ ብንወስድ “ ፍቅር ” ን — ብዙ የተለያዩ የፍቅር አይነቶች እንዳሉ መገንዘብ ይኖርበታል ፤ ፍቅር እንደ ስጋዊ ፍትወት (እንደ መጨማጨም) ፣ ፍቅር እንደ መዝናኛ ፣ ፍቅር ችግርና እጦትን እንደ ማስረሻ ፣ ፍቅር እንደ እንክብካቤ ፣ ፍቅር የራስ እንደ ማድረግ ስሜት ፣ ፍቅር ለማንኛውም ፍጡር እንደ መቆርቆር ፣ ፍቅር እንደ እናት ኩራት ፣ ፍቅር እንደ ባልና ሚስትነት እና እንዲሁም እንደ ሀገር



ፍቅር ፣ የገንዘብ ፍቅርና የመሳሰሉትን ያቅፋል ። ስለዚህም ደራሲው ስለ የትኛው አይነት ፍቅር እንደሚፅፍ አስቀድሞ መወሰን ይኖርበታል ።

ሁለተኛ ፣ ከመቶ በላይ ከሚቆጠሩት አካላዊና መንፈሳዊ ቅራኔዎች ውስጥ አንዱን ወይም ሁለቱን መምረጥ ይኖርበታል ። ለምሳሌ ፣ ሰው ከሰው ጋር ፣ ሰው ከተፈጥሮ ጋር ስላለው ቅራኔ ፣ ወይም በራሱ በሰው ውስጥ ስለሚኖረው የፍላጐትና የተግባር ቅራኔ ። እነዚህም ስለ ፍቅር እንዳሳየነው ሁሉ እየብቻ የሆኑ ለሚቃረኑ አባሎች (ለምሳሌ ፣ ሰው ከድንቁርና ፣ ሰው ከበሽታ ፣ ሰው ከድህነትና ከመሳሰሉት) ስላሏቸው ፣ ደራሲው መፃፍ ከመጀመሩ በፊት መወሰን ይኖርበታል ።

ሶስተኛ ፣ ከሺ በላይ ከሚቆጠሩ ገፀ-ባህርያት ውስጥ ሁለቱን ወይም ሶስቱን ፣ ከሚሊዮን በላይ ከሚቆጠሩ ድርጐች ውስጥ ሰባት ወይም ስምንቱን መምረጥ አለበት።

እዚህ ላይ አንድ ማስተሳሰሪያ ሀሳብ እንዳለ መገንዘብ ይበጃል ፤ ማንኛውም አይነት ምርጫ ሲካሄድ ፣ አመራረጡ ለገፀ-ባህርይው እንደሚስማማና ለተግባር እንደሚያመቻቸው ተደርጐ መሆኑ ። የሰመሩ ሁነታዎች ሁሉ ከባህርይው ተፈጥሮ የመነጩ የሚመስሉ ፣ የሰመሩ ቅራኔዎችም እነዚህን ገፀ-ባህርያት በሚገባ የሚያሳትፉ ሲሆኑ አገንፋይ ስሜቶቹም ከገፀ-ባህርያቱ ውስጥ በመመንጨት ባህርያቱ ሊኖሯቸው ወይም ሊገልጿቸው የተገቡ ናቸው የሚባሉ አይነት መሆን አለባቸው ።

በሌላ አገነጋገር ፣

የድርጐች ፣ የሁነቶችና የሀሳቦች ምርጦች ፤

(1) በቅድሚያና በእቅድ የተዘጋጁ ናቸው ። ለአንድ አላማ ተመርጠው የተቀናበሩ ናቸው እንጂ ከህይወት እንዳሉ በቀጥታ የተወሰዱ አይደሉም።

(2) ሰንሰለታዊና ተባባቢ ድርጊቶች ናቸው ። ምንም አይነት ማራኪ ቢሆን የአንድ የዳንስ ምሽት ድርግ ብቻውን አይበቃም ፤ አንዳቸው ከሌላው ላይ በመመዘዝ የሚያድጉ ፣ ቢያንስ መግቢያ ፣ መበልፀጊያ እና መደምደሚያ ያላቸው ሶስት ድርጎች ወይም ከተቻለ አያሌ ድርጎች ያስፈልጋሉ ።

(3) የአካላዊ እና / ወይም የመንፈሳዊ ቅራኔዎች ውጤት ናቸው ። አንዱን ድርግ ከሌላው የሚያዛምደውና ትግሉን የሚያሳድገው አንዱ ሀይል ከሌላው ሀይል ጋር ያለው ተፃራሪነት ነው ። (የመቅደሙን (ለ) እና ገፅ 284 ተመልከት ።)

## (ለ) <u>የአመራረጥ ዝርዝር ስልቶች</u>

መታተት ያለባቸውንና በውስጠ ታዋቂነት (ተዳብሰው) መታለፍ ያለባቸውን ሁነታዎችና መዳረጊያዎች (መደራረጊያዎች) ምረጥ ። በተለይ እንባቢው ባለው እውቀትና ልምድ መሰረት ማሟላት የሚችላቸውን ዝርዝር ሁነታዎች ሁሉ አታስገባ ፤

<u>ምሳሌ ፣</u>

(1) "የወልዴ ሚስት ሌሊት ምጥ ያዛት ።"
(2) "ወልዴ ከእንቅልፉ ነቅቶ ልብሱን ለበሰ ።"
(3) "ለሚስቱ የሚሆን ልብስ መርጦ አለበሳት ።"
(4) "አምቡላንስ እንዲመጣለት ስልክ ደወለ ።"
(5) "ሚስቱን ደግፎ ከመኝታ ቤት ወደ ሳሎን ወጣ ።"
(6) "አምቡላንስ እስኪመጣ እሳሎን ቆየ ።"



(7) "አምቡላንስ መጣ ።"
(8) "ሚስቱን ደግፎ የሳሎኑን በር ከፍቶ ወጣ ።"
(9) "በሩን ከፍቶ አምቡላንሱ ውስጥ ገባ ።"
(10) "ሚስቱን ደግፎ አጎኗ ተቀመጠ ።"
(11) "ምጡ እየጠናባት ሄደ ።"
(12) "ሆስፒታል ደረሱ ።"
(13) "ሚስቱን ጥግ አሲዞ አስቀመጠ ።"
(14) "መታከሚያ ካርድ ሊያወጣ ሄደ ።"
(15) "ካርድ አውጥቶ ሲመለስ ሚስቱን አጣት ።"
እና የመሳሰሉት…

ከነዚህ 15 አባባሎች ውስጥ ዋና ዋና ድርጊያዎቹ (1) ፣ (4) ፣ (11) ፣ (12) እና (15) ናቸው ። የቀሩት አስፈላጊዎች አይደሉም ።

ሳይጠቀሱ በመቅረታቸው አንባቢው የታሪኩን ይዘት አይስተውም ። ምንም እንኳ እያሟላ ማን በቡን ባያጤነውም ፣ ራሱ ኑሮ ያስተማረውን ያህል በሚያነብበት ወቅት ሁሉ ተደርገዋል የሚላቸውን ያህል እያሟላ መገንዘቡ አይቀርም ፤ ሚስቱን ልብስ ከማልበሱ በፊት የእንቅልፍ ልብስ እንደ መሆኑ ከእንቅልፉ መንቃት የነበረበት መሆኑን ፣ አምቡላንስ ከመግባቱ በፊት ከቤቱ መውጣቱንም ሆነ የአምቡላንስ በር ከፍቶ መግባቱንና የመሳሰሉትን የሚጠቁሙት አባባሎች ግልፅና በውስጠ ታዋቂነት መታለፍ ያለባቸው ናቸው ። ትረካ በጥንቃቄ ተመርጠው የተቀናጁ የተወሰኑ አባባሎችና እንዲያም ብሎ የተወሰኑ ድርጊቶች ውጤት ነው ። ስለሆነም እንደ ፎቶግራፍ ጨርሶ

“ሙሉ” ሆኖ እንዲቀርብ አያስፈልግም ፤ በአንባቢው ወይም በአዳማጩ በየድርጊቱ ውስጥም ሆነ በየድርጊቶቹ መካከል ሊገቡ የሚችሉት ሁነታዎችና ገፀ-ባህርያት ስፍር-ቁጥር ስለሌላቸው ።

### 7.1.4 ትልምና ሂደቱ

ትልም ፣ ሁነታዎችንና ድርጊቶችን በጊዜ ገደብ አመቻችቶ ማቅረቢያ ስልት መሆኑን ተመልክተናል ። እንደ ትረካው አላማም በትልሙ ውስጥ የሚጎነጎኑት ቅራኔዎች ፣ ባንድ ፊት ሰውን በሌላ ፊት ሌሎች « ነገሮችን » እንደሚይዙ ተረድተናል — ማለትም ቅራኔዎቹ ፣

- በሰውና በተፈጥሮ ሀይሎች መካከል
- በሰውና በሰው መካከል
- በሰውና በህብረተሰብ መካከል
- በሰው ውስጥ በሚነሱ ሁለት ሀይላት መካከል (ልስራ አልስራ ፣ ልግደል አልግደል ፣ ልተኛ ልነሳ ፣ ልሂድ ልቅር ወዘተ ...) እንደሆኑ ።

ቢሆንም ፣ በፅሁፍ ውስጥ አንድ ሰው ከሌላ ሰው ወይም «ነገር» ጋር የሚኖረው ትግል ብቻ ለድርሰት መጎንጎኛነት አይበቃም። ቅራኔው የሰመረ እንዲሆን ቅራኔውን የሚቀሰቅስ ሀይል ያስፈልጋል ። ወይም አንድ መድረስ ያለበት ግብ ። ቅራኔውን ያነሳሳው ሀይል ወይም የቅራኔው ግብ በግልፅ እስካልታወቀ ድረስ ቅራኔው ፋይዳ የለውም ። ባለታሪኩ ለአንድ ነገር ያለው ምርጫ ወይም ከአንድ «ነገር» የሚያደርገው ሽሽት በግልፅ መታየት አለበት ፤ በንግግርም ሆነ በድርጊያ ።



#### (ሀ) ነጠላና ውስብስብ ትልም

ትልምን ነጠላ ወይም ውስብስብ የሚያሰኘው የሚጠቀምበት የቅራኔ ማነስና መብዛት ነው ። ፅሁፉ አንድ ሰው አንድን ተራራ ለመውጣት ያደረገውን ትግል (በሰውዬው አልሸነፍ ባይነትና በተራራው አስቸጋሪነት መካከል ያለውን ቅራኔ) ብቻ የሚያሳይ ፅሁፍ ከሆነ ትልሙ ነጠላ ይባላል ። በሌላ በኩል ደግሞ ፣ በዚሁ ሰውዬና አደጋ ገጥሞት ልጆቹን ያለአባት እንዳያስቀር በምትሰጋው ሚስቱ መካከል ሌላ ቅራኔ ፣ እና በራሱም በሰውዬው ውስጥ ተራራውን ልውጣ አልውጣ ሶስተኛ ቅራኔ ካለ ትልሙ ውስብስብ ይባላል ። ስለሆነም በአንድ ግጭት ላይ ብቻ የሚያተኩር ትልም እምብዛም አይገኝም ።

#### (ለ) የሰንሰለታዊ ተዛምዶ ወይም የትእይንት ትልም

ትልም በውስጣዊ ቅንጅት ፣ በምክንያት-ውጤት-ምክንያት-ውጤት ሂደት ሲዛመድ በሰንሰለታዊ ተዛምዶ የተቀናበረ ይባላል ። በውስጣዊ ቅንጅት አማካይነት ሳይሆን፣ የማይመሳሰሉና የማይሳሳቡ ሁነታዎችና ድርጊያዎች ባያሉበት (ለየብቻ) እንደሚነሸጡ ወይም ስሜት እንደሚፈነጥቁ ሆ ነው ሲዘጋጅ ደግሞ የትእይንት ትልም ይባላል ። በትእይንታዊ ትልም በሚቀናበር ትረካ ውስጥ ሁነታዎች (ድርጊያዎችና ተዋራጊዎች) በተውኔት ውስጥ እንደሚታየው አይነት በየትእይንቶቹ ብቃት ብቻ ይቀርባሉ ። ባተራኪው የሚደረግ ገለፃ እምብዛም አይኖርም ። ተራኪው (የታሪኩን መዳረጊያ) ደጅኑን ፣ ባለታሪኩ ያለበትን ውስጣዊና ውጫዊ ሁኔታ በዝርዝር ያቀርባል ። ከዚያም ሁነታዎቹን ፣ ትርካውን በማሳደጊያ ልዩ ልዩ ትእይንቶች እና ፋታ በመስጫ ትእይንቶች ፣ በጭውውት ትእይንቶች ፣

በመደምደሚያ ትእይንትና በመሳሰሉት ከፋፍሎ ዘለቅና ስፋ ባለ ዝርዝር መስተዋታዊ ገለፃ ያቀርባል ። እንዲሁም እያለ ቀስ በቀስ ገንብቶ መዳፈያው ላይ ድንገት ቀጥ ይላል ። ከቀረቡት ትእይንቶች የትረካው ውላዊ ስሜትና መልእክት ይከሰታሉ በሚል ግምት ።

በሰንሰለታዊ ተዛምዶ የሚቀናበር ትልም በምክንያት ውጤት ተዛምዶ ነው የሚጐነጐነው ብለናል ። ይህም ማለት ፣ አንድ ምክንያት (ምክንያቶች) ድርጊያን ያመጣል ፤ ድርጊያው ደግሞ ሌላ ምክንያት ይፈጥራል ፤ እንዲሁ ደግሞ ሌላ ድርጊያ ይከተላል ፤ እስካበቃ ። ለዚህ ጥሩ ማስረጃ ሂፖሊተስ በሚል ተውኔቱ ውስጥ ዩሪፒደስ የተጠቀመበትን ትልም እንመልከት ። ፈድራ የምትባል ንግስት በእንጀራ ልጅዋ በሂፖሊተስ የሚያቃጥል ፍቅር ትጠመዳለች (የትረካው መቀስቀሻ ሀይል) ። ከመጠመዷም የተነሳ የሚያስጨንቅ የፍቅር ስቃይ ያድርባታል። ፍቅሯን ለመወጣት ወይም ስቃይዋን ለማብረድ ትፈልጋለች (ግብ) ። እርምጃ ትወስዳለች (ድርጊያ)። ሂፖሊተስን ለግብረ ስጋ ግንኙነት ትጠይቀዋለች ። ጥየቃው በሂፖሊተስ ውስጥ ጭንቅና ጥበት ( ጥያቄዋን የመፈፀምና ወይም ያለመፈፀም ምርጫ ይገጥመዋል ፣ ) ይፈጥራል ። ( ምክንያት) ። ጭንቅና ጥበቱን የሚገልፅ ድርጊያ ይፈፅማል — አገሩን የአባቱን ቤተ መንግስት ጥሎ ይጠፋል ። (የመረጠውን እርምጃ ይወስዳል ። ) የሂፖሊተስ መጥፋት በፈድራ ውስጥ ጭንቅና ጥበት ይፈጥራል (ምክንያት) ። (የሚሻል የመሰላትን ምርጫ ታደርጋለች ።)ጭንቅና ጥበቷን የሚያጠፋ የመሰላትን ድርጊያ ትፈፅማለች — ንፁሁን ሂፖሊተስን ፣ በግብረ ስጋ ሊደፍራት እንደ ነበረ አድርጋ በአባቱ በዜሳዎስ ላይ ትወነጅለዋለች ። በልጁ ላይ የተሰ ነዘረው ውንጀላ በዜሳዎስ ውስጥ ጭንቅና ጥበት (ለድርጊያ የሚቀሰቅስ ሀይል) ይፈጥራል (ምክንያት) ። ጭንቅና ጥበቱንም ያበረደ ይመስለውና ሊመርቀው ይገባ የነበረውን ልጁን የሚያስፈራ ርግማን (ድርጊያ) ያወርድበታል ። ይህ ሀያል እርግማን ለሂፖሊተስ መሞት ምክንያት ይሆናል ። ሂፖሊተስ አሰቃቂ ሞት ይሞታል (ድርጊያ) ። የሂፖሊተስ ሞት በፈድራ ውስጥ መጨነቅና መጠበብ (ለድርጊያ የሚቀሰቅስ ሀይል) ይፈጥራል (ምክንያት) ። ይህም ጭንቅና ጥበት ራሷን በራሷ እንጠልጥላ እንድትገድል ያደርጋታል—(የሀጢአት ዋጋ ሞት እንዲሉ ዋጋዋን ታገኛለች ።)

በማንኛውም አይነት ትልም ውስጥ ዋናዉ ተፈላጊ ነገር ፣ (በትእይንቶችም ሆነ ተዛምዶ ባላቸው አበይት ሁነታዎች መቅረቡ ብቻ ሳይሆን) ፣ እያንዳንዱ ሁነታ የትረካውን እድገት በማስመልከት የሚኖረው ጥያቄን የመጠየቅና መልስ የማስገኘት ፣ እንዲያም ብሎ ትልሙን አንድ እርምጃ ወደፊት የማራመድ ችሎታ ነው ። አለዚያ ትልሙ ደካማ ይሆናል ።

## 7.1.5 ትልም ከባለታሪኮች ጋር ያለው ዝምድና

ነጠላም ሆነ ውስብስብ ትልም የሚከሰተው በሁነታዎችና ድርጎች ሂደት ነው ። ሂደቱን የሚያራምደው ደግሞ ባለታሪኮች በድርጊያዎቹ ውስጥ የሚኖራቸው ተሳትፎ ነው ። ሂደቱን የሚያራምድ ተሳትፎ ደግሞ ፣ ማንኛውም ተሳትፎ ሳይሆን ፣ አድራጐታቸው ከውለኛ ባህርያቸው የሚመነጭ መሆኑ የሚታይበት ሁነታ ( ገፅ 270-274 ፣ 334-335 ) እና ድርግ ( ገፅ 335-338 ) ነው ። ስነ-ልቦናዊ ባህርይና ውጫዊ ሁነታዎች ተጣምረው ከሚገኙበት ፤ ይህን አይነት ውለኛ ባህርይ

ያለው ባለታሪክ ፣ ይህን እርምጃ መውሰዱ የማያጠራጥር ነው የሚያስብል የሚያሳምንና የሚገፋፋ እውነታ የተከሰተበት ። የባለታሪኩ ውለኛ ባህርይ እንዲያ እስከሆነ ድረስ እንዲያ ማድረጉ ያለ ነው የሚያሰኝ ። እንደ ሮሚዎና ዡሊየት ፍቅር ወይም እንደ ኦቴሎ ቅናት ያለ ውለኛ ባህርይ ገፀ-ባህርያት የሚወስዱትን እርምጃ የሚያሳምን ። ስለዚህ ፣ ትልም የሁነታዎችና የድርጊቶች ሂደት በመሆኑ የባለታሪክን ተሳትፎ (በሚቀርቡት ቀራኒዎችም ሆነ ሌሎች ሁነታዎች አማካይነት) የሚጠይቅ እስከሆነ ፤ ተሳትፎ ደግሞ የሚያረካ እንዲሆን ከባለታሪኩ ተፈጥሮ የመነጨ መምሰል እስካለበትና በዚህም ሳቢያ ትልሙ የሚያራምደው ስሜት አመርቂነት እንዲኖረው ከባለታሪኩ ውለኛ ባህሪ መመንጨት ካለበት ፤ ባጠቃላይም የትልም አላማ ባለታሪክን ለድርጊያ ማመቻቸትና መከሰት እስከሆነ ፤ ትልምና ባለታሪክ ፣ እንደየሁኔታው ፣ ነጠላ ወይም ውስብስብ ዝምድና እንደሚኖራቸው መገንዘብ ያሻል ።

### 7.1.6 የትልም ጥድፊያና ዘገምታ

የትልም እንቅስቃሴ እንደ ሁነታዎቹና ድርጊቶቹ አይ
ነት ጠንካራ ወይም ደካማ ፣ ፈጣን ወይም ዘገምተኛ ይ
ናል ። የሚከተሉትን ትረካዎች እንመልከት ፤

«በሁለት ሪፑብሊኮች መካከል ጦርነት ተነሳ ።
በዚህን ጊዜ አንደኛው ሪፑብሊክ ከአንድ ንጉስ ጋር የጦ
ቃልኪዳን ስምምነት ተፈራረመ ። ሌላው ሪፑብሊክ ስም
ምነቱን ሲሰማ ፣ ሁለቱን ለመነጣጠል በማሰብ ፣ የአዛዥ
ጀነራሉን ልጅ በሚስትነት ይሰጠዋል ። በዚህም ቃ
ኪዳኑን እንዲያፈርስ ያደርገዋል ። ጦርነቱ ተፋፍሞ ሁለ
ሪፑብሊኮች በሚዋጉበት ጊዜ ፣ የንጉሱን አማችነ



ያተረፈው ሪፑብሊክ ድል ይሆናል ። ንጉሱም ይማረካል ። ከድል አድራጊው ሪፑብሊክ ጉን ተሰልፎ የነበረ ሌላ ንጉስ ድል እሆነው ንጉስ ከተማ ሲገባ ፣ ንግስቲቱ (የተማረከው ንጉስ ሚስት) ለድል አድራጊው ሪፑብሊክ አሳልፎ እንዳይሰጣት ትለምነዋለች ። የለመነችውን ለማድረግ ቃል ይገባል ። በይበልጥ ጉዳዩን ለማመቻቸትም በሚስትነት ያገባታል ። ከሰርጉ በኋላ ፣ ከድል አድራጊው አዛዥ ጀነራል መልእክተኛ ይመጣል ፤ ንግስቲቱን ለመውሰድ ። ንጉሱ ግን አሳልፎ ሊሰጣት ስላልወደደ ፣ በምርኮኛነት ወደ ሪፑብሊኩ ሊልካት ወደሚፈልገው ጀነራል ዘንድ አቤቱታ ይሄዳል ። አቤቱታው አይሳካለትም ። ከዚያም ቃሉን ለማስከበር ባለመቻሉ አዝኖ ለንግስቲቱ መርዝ ይልክላታል ፤ መርዙን በመውሰድ በጠላቶቿ እጅ ከመውደቅ እንደምትድን ገልፃ ንግስቲቱ መርዙን ትቀበላለች ። ትጠጣዋለች ። ትሞታለች» ። (ትሪሲኖ ከፃፈው ፣ «ሶፎኒስባ» ከተባለ ትረካ ።)

ይህ እንግዲህ ልዩ ልዩ ድርጊያዎች ያሉበት ጠንካራ ትልም ነው ። ፈጣን እንዲሆን ደግሞ ትልሙን የሚያበለፅጉት መዳረጊያዎች (ሌሎች ባለታሪኮች ፣ ደጀኖች ፣ መግለጫዎች ፣ ጭውውቶች እና የመሳሰሉት ሁሉ) ለትልሙ እንደሚያመቹ ብቻ ተመጥነው ነው መዘጋጀት ያለባቸው ። ስለሆነም አሁን ባለበት ፎርሙ የትረካ አስተዋፅኦ ነው እንጅ ትረካ አይደለም ።

ሌላ ደግሞ እንመልከት ፤

«አንድ ባለጠጋ አንድ ዳውላ እህል ከቤቱ ተሰረቀበትና ወደ ዳኛ ሔዶ ነገሩን ሁሉ ነገረ ። ዳኛውም የቤትህን ሰዎች ሁሉንም ሰብስበህ አምጣልኝ አለው ። እርሱም ሰብስቦ አቀረበ ፤ ዳኛውም ብዙ በትር አስመጥቶ ሁሉንም በትክክል አስ

ቆረጠው ። ከዚያም በኋላ ለዚያ ሰው ቤተ ሰዎች ለሁሉም አንዳንድ በትር ሰጣቸው ፤ ሲሰጣቸውም ነገ በዚህ ጊዜ ተመልሳችሁ ኑ ፤ ነገር ግን የጌታውን እህል የሰረቀ ሰው በትሩ አንድ ጋት በልጦ ያድራል እያለ ሰጣቸው ። ያየጌታውን እህል የሰረቀ ሰው ይህን በሰማ ጊዜ ማታ ከበትሩ አንድ ጋት ቆረጠለት ።

በማግሥቱ በዚያው በታዘዙበት ሰአት ሁሉም ተሰብስበው ወደ ዳኛው ቤት ሔዱ ። ዳኛውም ሁላችሁም የሰጧችሁን በትር አምጡ ብሎ ባንድነት ቢያቆመው ፥ የሌባው በትር አጥሮ ተገኘ ፤ ከዚህ በኋላ እጁ ተይዞ ቢመረመር መስረቁን አምኖ ቅጣት ተፈረደበት… »
(ከነሩይ ወ.ሥ. "ሱካርና ወተት . . . ፥ 16ኛ ተረት ።)

ይኸኛውም እንደበፊቱ ራሱን የቻለ ትልም ነው ፤ ተከታታይ ድርጊያዎች ባሉበት በአንድ ሁነታ ላይ በመመሰረት አንድነትና መልእክት ያለው ። ተንትነን እንመልከተው ፤

(1) አንድ ባለጠጋ ነበረ ።
(2) አንድ ዳውላ እህል ከቤቱ ተሰረቀበት ።
(3) ወደ ዳኛ ሄዶ አመለከተ ።
(4/ ዳኛው የባለጠጋውን ሰው ቤተ ሰዎች እንዲሰበሰቡ አደረገ ።
(5) እኩል ቁመት እንዲኖራቸው ሆነው የተቆረጡ አንዳንድ በትሮች ለያንዳንዳቸው ሰጣቸው ። (የጌታውን እህል የሰረቀው ሰው በትር አንድ ጋት በልጦ እንደሚያድር በመንገር ። )
(6) ሌባው ፥ ማታ ከበትሩ አንድ ጋት ቆረጠለት ።
(7) በማግስቱ ሲመረመር የሌባው በትር አጥሮ ተገኘ ።
(8) ቅጣት ተፈረደበት ።



ከዚህ በላይ ከ(1) እስከ(8) የተዘረዘሩት ድርጊያዎች በጊዜ ገደብ የተመለከቱ ሰንሰለታዊ አበይት መሸጋገሪያዎች ናቸው ። በተጨማሪ ደግሞ ፥ ንኡሳን ድርጊያዎችን የሚመስሉ (ማለትም ለአበይት ድርጊያዎቹ አጫፋሪ የሚመስሉ ) ፥

(1) (ባለጠጋው) ሰብስቦ አመጣለት ።
(2) ዳኛው ብዙ በትር አስመጥቶ ሁሉንም በትክክል አስቆረጠው ።
(3) ነገ በዚህ ጊዜ ተመልሳችሁ ኑ (አላቸው ) ።
(4) ያ የጌታውን እህል የሰረቀ ሰው ይህን ሰማ ።
(5) በማግስቱ በዚያው በታዘዙት ሰአት ሁሉም ተሰብስበው ወደዳኛው ሄዱ ።
(6) ዳኛው ሁላችሁም የሰጧችሁን በትር አምጡ አላቸው ።
(7) በትሮቹን በአንድነት አቆማቸው ።
(8) ተያዘ ሌባው ።
(9) ቢመረመር መስረቁን አመነ ።

አባባሎች አሉበት ። እነዚህ አባባሎች ግን ትልሙን አያሳድጉም ፤ በአንባቢው ወይም በአዳማጩ ፥ በልምዱና በእውቀቱ አማካይነት ከሀሳቡ የሚሟሉ ናቸው ። (ገፅ 282 እስከ 284 ተመልከት ) ስለዚህ ይኸኛው ትረካ እምብዛም ደጀን የማያስፈልገው በቃላት ብቻ ሳይሆን ያለድምፅ በሚንቀሳቀስ ስእልም ሆነ በውዝዋዜ ሊተረክ የሚችል ፈጣን ትልም ነው ፤ እንደ በቂ ትረካም ይወሰዳል ።

ይኸው በአንድ ድርግ ላይ የተመሰረተ ትልም ፥ እምብዛም ለትረካው ፋይዳ በሌላቸው ክርክሮች (በባለፀጋውና በዳኛው ፥ በዳኛውና በቤተሰቦቹ ፥ በባለፀጋውና

በሌባው ወዘተ… ) ቢጨናነቅ ግን ትልሙም ይደክማል ፤ ትረካውም ከመቼ ባለቀ የሚል ስሜት ይፈጥራል — ዘገምተኛ ይሆናል ።

## 7.1.7 ትልም ለስሜት ፍንጢቃ ፣ ትልም ለሰበካ ፤ ትልም ለፕሮፓጋንዳ ፣ ትልም ለስሜትና ለመልእክት

ትረካ አንድን ህይወት በሙሉነቱ (እንደ ተኖረ በማስመሰል) እንዲሰማን እያደረገ ማቅረቢያ ዘዴ ነው ። ይኽንንም በሚያደርግበት ጊዜ ፣ አንዳንዴ ስሜቶቻችንን በመደባበስና በመጠቋቆም ይኽ ነው የማንለው ፣ የማይጨበጥ አይነት ልምድ ይሰጠናል፤ ( ገፅ 340-344 ። ) አንዳንዴ፤ ይኽም ሊሆን ያም ሊሆን ይችላል የሚያሰኝ አሻሚ ስሜት ውስጥ ይከተናል ፤ ( ገፅ 365-374 ቊጥር 40 ድረስ ። ) አንዳንዴ ደግሞ ትረካው የታለመበትን ግብ ቁጭ ቁልጭ አድርጎ ያቀርብልናል ፤ ( ገፅ 365-374 ቊጥር 41 ድረስ ። ) ለማንኛዎቹም ቢሆን መሰረታቸው ያው ትልሙ ነው። እንደ ትልሙ አተላለም ነው የየትረካው ግብ የሚለዋወጠው ። ስለዚህም ትለማ ጥንቃቄን ይጠይቃል ። በተለይ የመጨረሻው መልእክት አብሳሪ አይነቱ ወደ ሰበካና እልም ወዳለ ፕሮፓጋንዳና ቅስቀሳ ውስጥ በመግባት የስሜት ቀስቃሽነቱንም ሆነ የመልእክት አስተላለፊነት ሀይሉን እንዳያጣ ያስፈልጋል ። በዚህ ረገድ ከጥንቶቹ ፣ የኀሩይ ወልደ ሥላሴን «የልብ ሀሳብ» እና የመኮንን እንዳልካቸውን «ጣይቱ ብጡል» እና «መልካም ቤተሰቦችህን መመልከቱ ይበቃል ። ትልም የስሜት ፈንጣቂነትንና የመልእክት አስተላላፊነትን ሚዛናዊነት መጠበቅ ይኖርበታል ።



## 7.1.8 የልባንጠልጥልነት (የልብ አንጠልጣል) እና የግርምታ ስልቶች

በትረካ ስልት ውስጥ ፣ እንደየትልሙ አይነት ፣ አቢይና ንኡስ ሁነታዎች እንዳሉ ( በገፅ 274 እስከ 277 ) እና ሁነታዎቹንም ለድርጊያ የሚቀሰቅሳቸው ሀይል እና ወይም ግብ ( ከገፅ 284 እስከ 287 ) እንደሚኖራቸው ተመልክተናል ። ከዚህ ለጥቀን ደግሞ የሁነታዎቹን ሀይልና ግብ አጓጊነት የሚያበስሩትን አንዳንድ ስልቶች እናመለክታለን ።

አጓጊነትን የሚያበስሩ ስልቶች በአብዛኛው በልባንጠልጥልና ግርምታ ስልቶች ይጠቃለላሉ ።

### (ሀ) የልባንጠልጥል ስልት

የልባንጠልጥል ስልት ጭንቀትና ጥበትን ከደስደስ ስሜት ጋር እያዋዋደ የሚያቀርብ ልብን የሚሰቅል የሀሳብና የድርጊያ ድብቅነት ነው ። ውጤቱ በቅድሚያ በታወቀ (ባለታሪኩ እንደሚገደል ወይም እንደሚሞት ወይም ያፈቀራትን እንደሚያገኝ ወይም እንደማያገኝ ወዘተ… በቅድሚያ በታወቀ) ወይም ባልታወቀ ትልም* ውስጥ ይሰራበታል ። ውጤቱ በማይታወቅ ትልም ውስጥ ሲሰራበት ፣ ተከታታይ ሁነታዎቹ እንዳስፈላጊነቱ ፣ ለተለያዩ ጥያቄዎች መልሶችን ማስገኘት ይኖርባቸዋል— ማን፣ ምን፣ እንዴት፣ ለሚሉት ጥያቄዎች ። ውጤቱ በታወቀ ትልም

* ውጤቱ የታወቀ ትልም ሲባል ፣ የትረካው አጠቃላይ ሂደትና ባለታሪኮቹ የሚደርስባቸውም ሆነ የሚያደርሱት ነገር በቅድሚያ የታወቀበት ትልም ሲሆን ፣ ውጤቱ የማይታወቀው ደግሞ ባለታሪኮቹ የሚያደርሱትም ሆነ የሚደርስባቸው ነገር በቅድሚያ የማይታወቅበትና ቀስ በቀስ የሚገለፅበት ነው ።

ውስጥ ሲሰራበት ደግሞ ፣ ትልሙ የሚመልሰው ጥያቄ በአብዛኛው መቼ? የሚለውን ጥያቄ ይሆናል ።

ልባንጠልጥል ስልት ፣ ልብን የሚሰቅለውና ጭንቀትና ጥበት የሚፈጥረው ፣ በባለ ታሪኮቹ ላይ የሚደርሰውን ወይም ባለታሪኮቹ የሚያደርሱትን ካለማወቅና ርግጠኛ ካለመሆን ሳይሆን ፣ አንባቢው ወይም አዳማጩ በባለታሪኮቹ ላይ ጭንቀትና ጥበት የሚያስከትሉትን ሁኔታዎች አስቀድሞ ቢያውቅም ፣ ባለታሪኮቹን ለማስጠንቀቅ እማይችልበት ሁኔታ ላይ በመገኘቱ ነው ። ስለሆነም አንዳንዴ ከቅድመ ጥቆማ ጋር አንዳንዴ ደግሞ ከአሳዛኝ ምፀት ጋር ይዛመዳል ።

ቅድመ ጥቆማ ፣ በትልሙ ውስጥ እልፍ እልፍ በሚሰራጩ ቃላትና ሀረግ አማካይነት ወደሚፈለገው ግብ የሚመራ እንጥብጥብ ነው ። እንዲህም በመሆኑ ጥቆማው ልብ አንጠልጥልነት የሚኖረው ፣ ባለታሪኮቹን የሚያሰጋና አንባቢን የሚሰግጥና የሚሰገጥጥ ድርጊያ በትልሙ ውስጥ ሲኖርበት ነው ። አለዚያ ፣ ቅድመ ጥቆማው፥ የአቢይ (የአጉራ) ሁኔታዎች አካል በመሆን ትረካውን ማራመድ ብቻ ይሆናል ተግባሩ ። በዚህ አይነት የቅድመ ጥቆማ አቀራረብ ስልት የልብ አንጠልጥል ስልት አካል የሚሆነው በከፊል መሆኑን መገንዘብ አያዳግትም። ቅድመ ጥቆማ ያለበት አፃፃፍ ሁሉ ልባንጠልጥልነት ስለማይኖረው ። ልባንጠልጥልነት የሚኖረውም ሁልጊዜ ቅድመ ጠቋሚዎች ያሉበት ባለመሆኑ ፣ ውጤቱ በታወቀ ትልም ውስጥ እንደሚገኘው አይነት ።

ሌላው ጉዳይ ፣ ልባንጠልጥል ስልት ከአሳዛኝ ምፀት ጋር ያለው ዝምድና ነው ። በዚህም ስልት ቢሆን ፣ ልባንጠልጥልነቱ ያለው የትልሙ ሂደት መቼ? የሚለውን



ጥያቄ በመመለሱ ረገድ ነው ። ከዚህ በስተቀር አንባቢው ፣ በአብዛኛው የትልሙን ሂደት ያውቃል ። ባለታሪኩ በማያውቀው ፣ አንባቢው ግን በሚያውቀው አይነት ፣ ባለታሪኩ ቀስ በቀስ ወደ ውድቀቱ ሲያመራ ያያል ፤ ራሱ ባለታሪኩ የሚናገረውና የሚያደርገው ጭምር ውድቀቱን ሲያመለክትበት ። መቼ? የሚለው ጥያቄ ሲመለስም ትልሙ በመቋጨቱ የአንባቢው ወይም የአድማጩ ልብ ሲረጋ ፣ ባላሰበው መንገድ የፈፀመው ድርጊያ ደግሞ በባለታሪኩ ላይ ግርምታን ሊፈጥርበት ይችላል (ለመገረም ካበቃው) ።

(ለ) <u>የግርምታ ስልት</u>

ግርምታ የልባንጠልጥል ሌላው መልኩ ነው ። ግርምታ የሚመነጨው ድንገተኛና አጋጣሚ የሆነው አስገራሚ ድርጊያ እስኪከሰት ድረስ ነው ። ከተከሰተ በኋላ አስገራሚነቱ ያከትማል ። ከዚህም የተነሳ በግርምታ ላይ የተመሰረቱ ትልሞች እምብዛም ደጋግሞ የመሰማትና የመነበብ እድል አይገጥማቸውም ። ሆኖም ፣ ብዙ ትልሞች በብዙ ግርምታዎች እየተገነቡ በማደግ የልባንጠልጥልነት ባህርይ እንዲኖራቸው ለማድረግና በልባንጠልጥልነት የተተለሙትን ደግሞ በግርምታ እንዲያበቁ ለማድረግ ይቻላል ።

## 7.2 <u>ተራኪ</u>

ተራኪዉ ታሪኩን የሚያቀርበው ነው ። በአብዛኛው ተራኪዉ ደራሲዉ አይደለም ። ደራሲውንም ሆኖ መታየት የለበትም ።

አንድ ደራሲ ለሚደርሰው እያንዳንዱ ድርሰት የተለያዩ ወካይ ተራኪዎች ሊኖሩት ይችላል ። ራሱ ደራሲዉ

ግን በተለይ ከተራኪዎቹ አንዳቸውን ወይም ሁሉንም ነው ለማለት አይቻልም ። ተራኪዉ ፣ ደራሲዉ ሊያስተላልፈው የፈለገውን አገናዝቦ የሚያቀርብ ፣ አንባቢዉ ሁሉ ከልዩ ልዩ ድርሰቶቹ ውስጥ አቀንባብሮ ይህን አይነት ነው ወይም ይመስላል ብሎ የሚያውቀው ወካይ ደራሲ ሲሆን ፣ ደራሲዉ ግን ተራኪዉን ጭምር የፈጠረው የድርሰቱ ራስ ነው — ባጠቃላይ በሙሉ የድርሰቱ አቀራረብ ለማለት የሚፈልገውን ድርሰቱ እንዲልለት የሚያደርግ ።

### 7.2.1 የተራኪ አኳያዎች

ወካይ ተራኪዉ ፣ በድርሰቱ ውስጥ የሚቀርቡ ሁነታዎችን ፣ ድርጊያዎችንና ነገሮችን የሚያይበት ወይም የሚያጤንበት የተለያዩ ሶስት አኳያዎች (ግንባሮች) አሉት ፤

#### (ሀ) በአይን ከማየት አኳያ

(1) ራሱ ተራኪዉ ፣ እንደ ወካይ ተራኪ ሆኖ በአይኖቹ የሚመለከታቸውን አስፈላጊዎች በማስፈር፣

አጅ ፡

"እቆምኩበት እንጦጦ ተራራ ላይ ሆኜ አዲስ አበባን ቁልቁል ስመለከተው ፣ አልፎ አልፎ የተቆረጠ ጫካ መሰለኝ" ——

በተራኪ ገፀ-ባህርይ አይን ፣ በአንደኛ መደብ ግምባር የቀረበ ።

(2) ወካይ ተራኪዉ ፣ አንድ ገፀ-ባህሪ በአይኖቹ የሚመለከታቸውን በመስፈር — ማለትም ተራኪዉ ሁነታዎችንና ነገሮችን በገፀ-ባህርይዉ አይን እያየ ሲያሰፍር ፣



አጅ ፡

"ዝናሽ ፣ እመኖሪያዋ ፎቅ በረንዳ ላይ ቆማ የምትመለከታቸው ሰዎች ሁሉ ድንኮች ሆኑባት" — ተራኪዉ እዳር ቆሞ ሁነታዎች በዋናዉ ገፀ-ባህርይ እየታዩ የቀረበ ፣ ወይም

"ከዝናሽ ግምባር ፣ አዲስ አበባ ፣ አይሮፕላን ውስጥ ሆኖ ሲያውት ፣ እልም ያለው ጫካ ነበር።" ከአንስተኛ ገፀ-ባህርይ አንፃር የቀረበ ።

(3) ተራኪ፣ አንድ ገፀ-ባህርይ ሌላ ገፀ-ባህርይ በሚያይበት አይን እያየለት ሲያሰፍር ፣

አጅ ፡

"አስቴር ፣ ታደገ አስፋን ድንገት ሳያስበው ሲመረግተው አየች ።"

#### (ለ) ከአእምሮ ልምድ አኳያ

ተራኪም ሆነ ገፀ-ባህርይ ነገርን (ሁነታዎችንና ነገሮችን) ከአስተዳደጉ ፣ ከእውቀቱ ፣ ከአስተሳሰቡ ፣ ከእምነቱ ፣ ከልምዱና በጠቅላላው ከህይወቱ ፍልስፍና አንፃር እንዲያይ ሆኖ ሲሰፍር ነው ።

አጅ ፡

" ማንኛውም ለስራ የበቃ ሰራተኛ ሁሉ በአገሪቱ እድገትና ልማት በመሳተፍና ድርሻውን በማበርከት አዲሱን ህብረተሰብ መገንባት ይኖርበታል" አሉ መምህሩ ፣ "አለዚያማ የመብላት የመጠጣትና የመኖር መብት አይገባውም ። "

እዚህ ላይ የተለያዩ አመለካከቶች አሉ ፤

(1) ‘ማንኛውም ለስራ የበቃ ሰራተኛ ሁሉ በአገሪቱ እድገትና ልማት በመሳተፍ ድርሻውን ማበርከት አለበት ።’

(2) ‘ተሳትፎው አዲሱን ህብረተሰብ ለመገንባት መሆን ይኖርበታል ።’

(3) ‘ካልተሳተፈ የመብላት ፣ የመጠጣትና የመኖር መብት አይገባውም ።’

በልቦለድ አለም ውስጥ ያሉ ገፀ - ባህርያትም ሆኑ ፣ በእውናዊዉ አለም ያሉ ሰዎች ፣ በአባባሎቹ በቁጥር (1) ቢስማሙ በቁጥር (2) እና (3) ላይስማሙ ፣ ወይም በቁጥር (1) እና (2) ተስማምተው ፣ በቁጥር (3) ላይስማሙ ፣ ወይም ጭራሹንም ከቁጥር (1) እስከ (3) ባሉት አባባሎች ላይስማሙ ይችላሉ ። ስለዚህም አባባሉ ከማን ርእዮተ አለም አንፃር እንደ ተሰነዘረ ማወቁ እጅግ አስፈላጊ ይሆናል ።

(መ) <u>ከፍላጎት ሂደት አኳያ</u>

ሁኔታዎችና ነገሮች ከየገፀ-ባህርያቱ አይኖች አኳያና ከየአእምሯቸው ልምድ አኳያ ከተጤኑ ፣ እያንዳንዱ ገፀ-ባህርያት በፅሁፍ ውስጥ የሚሜወቱት ሚናና ሊደርሱበት የሚፈልጉት ግብ ወይም ፍላጎት ይታወቃል ። ከዚህም የተነሳ ሁኔታዎችና ነገሮች የገፀ-ባህርይውን ግብ ወይም ፍላጎት በመልካምም ሆነ በአጉል ሁኔታ ሲደግፉት ወይም ሲያጩናግፉት ይታያል ። በአብዛኛው ፣ ገፀ-ባህርያት እነዚህን ሁኔታዎችና ነገሮች ላያውቋቸውም ላያጤኗቸው ይችላሉ ። ከተራኪዉና ከአንባቢዉ ግን የተሰወሩ ስለማይሆኑ ፣ ማናቸውንም ሁኔታዎች



የሚተረጉሙት ለገፀ-ባህርያቱ ደስታ፣ ሀዘን፣ እድገት፣ እኗኗርና ግብ ካላቸው ተፅእኖ አኳያ ነው ። ማለትም ከየገፀ-ባህርያቱ የፍላጎት ሂደት አኳያ እያጤኑ ። በድርሰቱ ውስጥ የገፀ-ባህርይነት ሚና የሌለው ተራኪ ማለትም አቢይ (ዋና) ፣ ንኡስ (አነስተኛ) ገፀ-ባህርይ ወይም ታሪኩ በሆነበት ጊዜ የነበረ ገፀ-ባህርይ ካልሆነ ፣ የፍላጎት አኳያ አይኖረውም ። የፍላጎት አኳያ እንዲኖረው ገፀ-ባህርይም መሆን ይኖርበታል ። እንዲያ ሲሆን ነው ትረካውን ለትችት ፣ ለማብራራት ፣ ቅዋሜን ለመቋቋምና ለመገተር ፣ ለፍላጎት ማበራቻ ምክንያቶችን ለመደርደር ፣ ለማጋለጥም ሆነ ለመጋለጥና ለመሳሰሉት መጠቀሚያ ለማድረግ የሚቻለው ።

ይህ የፍላጎት አኳያ የሚያመለክተው ፣ በፅሁፉ ውስጥ የተገለፀውን የህይወት ፍላጎት ስለሆነ ፣ ተአማኒነቱም እዚያው ውስጥ በቀረበው የኑሮ መሰረትነትና መለኪያነት መሆን ይኖርበታል ።

<u>አጅ ፣</u>

“ለጊዜው ሞቅ ብሎት ስለነበር ባያጤነውም ፣ አነጋገሩ ደርዝ ይዞ ስለነበር ፣ በቀላሉ የማይፋቅ ቂም ነው ያተረፈው ፣ ከሱ አንፃር ሲታይ —” የፍላጎት አኳያው ሞቅ ብሎት የነበረው ገፀ-ባህርይ መሆኑ ነው ።

ባጠቃላይ እንግዲህ ፣ አኳያዎች አንድን ሁኔታ ወይም ድርጊያ ከቦታ ፣ ከርእዮተ-አለም ወይም ከእለት በእለት ኑሮ አንፃር መመልከቻ የሆኑ ፣ ተራኪዉም ሆነ ገፀ-ባህርይዉ ፣

የት ሆኖ በማን አይን አየው ?

ወይም

ይሆን ለማለት ያስቻለው እምነቱ ፣ አስተሳሰቡ ፣ የሞራል መለኪያው ፣ በጠቅላላው አለምን መመልከቻው እንዴት ቢሆን ነው ?

ወይም

ካለበት የእለት በእለት ተግባራዊ ህይወቱ አንፃር ሲታይስ እንዴት እያደረገው ወዴትስ እየመራው ነው ?

የሚሉትን ጥያቄዎች ለመመለስ የሚያስችሉን ናቸው ።

### 7.2.2 የተራኪ አይነቶች

እዚህ ላይ የወካይ ተራኪዉን ሚናና አኳያ ከገፀ-ባህርያቱ ሚናና አኳያ ለይቶ ማጤን ያስፈልጋል ። በቅድሚያ እንደጠቆምነው ወካይ ተራኪዉ ገፀ-ባህርይ ሊሆን ቢችልም፣በአብዛኛው ከታሪኩ ውጪ ሆኖ ታሪኩን የሚተርክ ነው ። እንደየሁኔታውም ፣

(ሀ) በጊዜ ፣ በቦታ በገፀ-ባህርይ ሳይወሰን እንዳሻው በመንቀሳቀስ ከራሱና ከገፀ-ባህርያቱ አንፃር እየተመለከተ ይተርካል ። ማለትም — ማንኛውም በታሪኩ ተሳታፊ የሆነ ተራኪ-ገፀ-ባህርይ ሊያደርገው የማይችለውን አጠቃላይ ትእይንትን ወይም ማንም ገፀ-ባህርይ የሌለበትን ትርኢት ወይም ገፀ-ባህርይው አጢኖ ያልተመለከተውን ፣ ወይም ጭራሹንም ያላየውን ውስጣዊና ውጫዊ ክስተት እያየ ይተርካል ። የዚህ አይነቱ ሁለገብ ሁሉን አዋቂ ተራኪም 'አዋቂ-ኩሉ' ተራኪ ይባላል ።

( ከገፅ 178-182 ተመልከት ። )



(ለ) ሁነታዎችን፣ነገሮችንና ድርጊያዎችን አንድ አቢይ፣ አንድ ንኡስ ወይም አንድ በወቅቱ የነበረ ምስክር (ማን ይመስክር የነበረ እንዲሉ) ገፀ-ባህርይ ካየው፣ ከሰማው፣ ካሰበው እና ስሜቱ ከተቀሰቀሰበት አንፃር ያቀርባል ። የዚህ አይነቱም <u>ውሱን (ስውር) ተራኪ</u> ይባላል ፤ ሁነታዎችን በአንዱ ገፀ-ባህርይ አይን እየተመለከተ ስለሚተርክ ። እንዲህ አይነቱ ገለልተኛ ተራኪ ታሪኩን በሚተርክበት ወቅት የራሱ የሆነ አጠቃላይ ትእይንትን ፣ ገፀ-ባህርያት የሌሉበትን ትርኢትና ገፀ-ባህርያቱ ያላጤኑትንና ያላዩትን ከመተረኩ ውጪና ታሪኩን ለመተረክ ካለው ፍላጎት በስተቀር ባህርያቱ በድርሰቱ አለም ውስጥ ሊኖራቸው የሚችለውን ፍላጎት አይነት አይኖረውም ።

(መ) ሁነታዎችን ፣ ነገሮችንና ድርጊያዎችን ራሱ አቢዩ ወይም ንኡሱ ፣ ወይም በወቅቱ የነበረ ምስክር ገፀ-ባህርይ እንዳየው ፣ እንደሰማው ፣ እንደገባው እና በልምዱ እንደደረሰበት አድርጎ ያቀርባል ። የዚህን አይነቱ አንደኛ መደብ ተራኪ ይባላል ። አንዳንዴ የሚተርከው ታሪክ ይዘት በህይወት ውስጥ የሚኖረውን ወሳኝነት ሳያጤን ሲቀር ፣ ሞኛሞኝ አንደኛ መደብ ተራኪ በመባል ይታወቃል ።

(ከገፅ 166-167 (በ) (1) ፣ በ168 (ተ) (1) እና ከገፅ 173-177 ተመልከት ። )

### 7.2.3 የተራኪ ተግባራት

ከላይ በጥቂቱ እንደ ተጠቀሰው የተራኪ ተግባራት እንደ ተራኪው አይነት ይለያያሉ ።

(ሀ) <u>ተራኪው ገለልተኛ ሲሆን ፥</u>

(1) እያንዳንዱ ትእይንት የሚይዘው ራሱን የቻለ ድርጊያ ይሆናል ።

(2) በእያንዳንዱ ትእይንት መካከል የሚያልፈው ጊዜ ማብራሪያ ሳይሰጥበት ይታለፋል — አንባቢው ከሀሳቡ እንዲሞላው እየተተወ ።

(3) ሁነታዎች በእውኑ አለም የሚወስዱት ጊዜና ስለ እነሱ ለመተረክ የሚወስደው ጊዜ የተመጣጠነ ይሆናል ።

(4) ታሪኩ የሆነበት ቦታና የተከናወነበት ጊዜ የታወቀ መሆን ይኖርበታል ።

(5) አጠቃላይ ትእይንቶች ፥ ከራሱ ከተራኪዉ ወይም ከአንድ ገፀ-ባህርይ አንፃር ፥ አስተያየትና ትችት ሳይጨመርባቸው ይቀርባሉ ።

(ለ) <u>'አዋቄ - ኩሉ' ተራኪ ሲሆን ፥</u>

(1) ትረካው ልዩ ልዩ ትእይንቶችና ባጭሩ የተወጣጡ (እጥርጥር) ሀተታዎች (ወይም አስተያየቶች) ይፈራረቁበታል ፤ ትእይንት — እጥርጥር ፤ ትእይንት — እጥርጥር ፥ ወዘተ ...

(2) ባጭሩ የተውጣጣው ሀተታ ፥ የጊዜ ፥ የቦታ ፥ የሁነታዎችና የመዳረጊያዎች እጥርጥር እና በየትእይንቶች ውስጥ የሚገኙ የአዝማሚያዎች ፥ የድርጊያዎችና የመሳሰሉት ፍሬ ነገሮች እጥርጥር ሊሆን ይችላል ።



(3) ትረካዉ ፥ ተገን የሚሆኑ ትእይንቶች ምስል ፥ ገፀ-ባህርይ የሌሉበት ትርኢትና ገፀ-ባህርያቱ ያላጡኑትና ያላደረጉት ሁነታና ድርጊያ ሀተታ ይኖርበታል።

(4) ተራኪዉ እገፀ - ባህርያቱ አስተሳሰብ ውስጥ ብቅ ጥልቅ እያለ የሚመዘግበው ሁነታ ሰንሰለታዊ ድርጊያዎችን ወደሚቀጥለው የትረካ ደረጃ የሚያሸጋግርና ወደ ታሪኩ መደምደሚያ የሚያዳርስ መሆን ይኖርበታል ፥ ገፀ - ባህርያቱ የሚያስቡትን ለማሳወቅ ብቻ ሳይሆን የታሪኩን ሂደት ለማራመድ መዋል አለበት።

(5) ሁነታዎቹ በእውኑ አለም የሚወስዱት ጊዜና ስለ እነሱ ለመተረክ የሚወስደው ጊዜ የተመጣጣን አይደለም ፥ በየትእይንቶቹ መካከልም ሆነ በየትእይንቶች ውስጥ የሚኖሩት ሀተታዎችና ትርጓሜዎች ባጭሩ ተውጣጥተው ስለሚቀርቡ ።

(6) አልፎ አልፎ ታሪኩ በጊዜና ቦታ ሳይወሰን ሊቀርብ ይችላል ፤ ለምሳሌ በገፀ - ባህርይ ሀሳብ ውስጥ የሚመላለስ ትዝታ ሲመዘገብ ።

(7) በአብዛኛው የሚቀርቡት ትእይንቶችና ገፀ-ባህርያት በእውናዊዉ አለም ከሚታወቁት የተለዩ አይሆኑም ። ስለዚህም በፅሁፉ ውስጥ የተሰነዘሩ አንዳንድ አባባሎች ተአማኒነት የማይኖራቸው መስለው ሲታዩ በእውናዊው አለም የሚሰራባቸው ፍልስፍናዊና ሳይንሳዊ አመለካከቶችና ታሪካዊ ሀቆች በአጠቃላይ ማስረጃነት ሲቀርቡ ይታያል ።

(መ) <u>ተራኪዉ አንደኛ መደብ ሲሆን ፥</u>

(1) እያንዳንዱ ትእይንት የሚይዘው ራሱ አቢዩ ወይም ንኡሱ ገፀ-ባህርይ እና ወይም በወቅቱ የነበረ

ምስክር ገፀ-ባህርይ ካየው፣ ከሰማው፣ ከገባውና በልምዱ ከደረሰበት አንፃር ይሆናል ።

(2) በእያንዳንዱ ትእይንት መካከል የሚያልፈው ጊዜ በአንደኛ መደቡ ተራኪ ልምድ መሰረት አስተያየት ይሰጥበታል ።

(3) ሁነታዎች በእውኑ አለም የሚወስዱት ጊዜና ስለ እነሱ በመተረክ የሚወስደው ጊዜ አይመጣጠንም ።

(4) አጠቃላይ ትእይንቶች ከአንደኛ መደብ ተራኪው አንፃር አስተያየትና ትችት ይሰጥባቸዋል ።

(5) ታሪኩ የሆነበት ቦታና የተከናወነበት ጊዜ የታወቀ ይሆናል ።

(6) ተራኪዉ በተለይ ስለ ተቃራኒ ገፀ-ባህርያት ሲተርክ ከፍተኛ ጥንቃቄ ማድረግ ይኖርበታል ፣ ታማኝነት እንዲኖረው ።

### 7.2.4 ተራኪ ሀተታና ትርጓሜ ማቅረቢያ ዘዴዎች

ተራኪዉ የማህበረሰቡን ፣ የየአንዳንዱን ሰውና የስርአቱን መንፈስ አቀራረቡ ሊያራምደው ወይም ሊያስተላልፈውና ሊያስተምረው በሚፈልገው ርእዮተ-አለማዊ አመለካከቱ ተአማኒነት ላይ የተመሰረተ ነው ። ሀተታና ትርጓሜውም ፣ ተራኪዉ ይገንዘበውም አይገንዘበው ፣ በዚሁ አመለካከቱ እየተበረዘ ነው የሚቀርበው ። እነዚህ አመለካከቶች ፣ በአብዛኛው ፣ ከአትኩሮትና ከፍተሻ የተገኙ አጠቃላይ ሳይንሳዊና ፍልስፍናዊ መመሪያዎችንና የሰው ተፈጥሮ ህግጋትን ፣ ሁለንታዊ ወይም መጠናዊ ህቆችን ፣



ሎጂካዊ እውነታዎችን ፣ የቃላት ያካባቢ ትርጓሜዎችን እና በተለምዶ እንደ ትክክል ተቆጥረው ተቀባይነት ያገኙ ግምቶችን ያጠቃልላሉ ። አመለካከቶቹም ሀተታና ትርጓሜ እንዲሰጥባቸው የሚያስፈልገው ፣ በተለይ በአንድ አገር ውስጥ አብዮታዊ ለውጥ ከመደረጉ የተነሳ፣ በአብዛኛው ሰው ታማኝነት የነበራቸው አመለካከቶች ስለሚናጉና ተቀባይነታቸው ከማጠራጠሩ የተነሳ፣ በልቦለዱ ውስጥ ለተመለከቱ ሁነታዎች እንደ ማስረጃ ሲቀርቡ ታሪኩን ጭምር ተአማኒነት ስለሚያሳጡት ነው ። ስለሆነም ከዚህ ቀጥለን ለሀተታና ለትርጓሜ የሚሰራባቸውን መፍቻ፣ መበየኛ (አስተያየትና ግምት መስጫ) ማጠቃለያ ዘዴዎች እናብራራለን ።

(ሀ) ፍቺ

ደራሲዉ ሁነታዎችንና መዳረጊያዎችን በሚያቀናጅበት በማንኛውም ጊዜ፣ እውናዊዉን አለም ከልቦለዳዊዉ አለም ለይቶ ማጤን ይኖርበታል ። በእውናዊዉ አለም ተአማኒነት ያላቸው ሁነታዎችና መዳረጊያዎች ሁሉ እንዳሉ ወደ ልቦለዳዊዉ አለም ቢወሰዱ ታማኝነት አይኖራቸውም ። እንዲሁም በተወሰኑ ልቦለዳዊ ገፆች ውስጥ የተገለፁ ሁነታዎችና መዳረጊያዎች እንዳሉ ወደ እውናዊዉ አለም ቢወሰዱ ታማኝነት አይኖራቸውም ። እውናዊዉ አለም እንደ ልቦለዳዊዉ አለም ሁሉ ነገሮቹ ክርክም ብለው በስርአት የተዘጋጁበት አይደለም ፤ ዝርክርክነትና አጋጣሚ ይበዛበታል ። በልቦለድ አለም ውስጥ ለሚታዩ ሁነታዎችና መዳረጊያዎች በዚህ አይነት ሊሆኑ ወይም ሊደረጉ ይችላሉ የሚያሰኝ የራሳቸው የሆነ ማገናዘቢያ ፣ ማሳመኛና የራሳቸው አይነት ፋይዳ ያሻቸዋል ። በውናዊዉ አለም የበጀው ማሳመኛና ፋይዳ በልቦለዳዊዉ አለም ላይበጅ ይችላል ።

ከዚህም የተነሳ ብዙ ጊዜ የድርሰት ተራኪ የሆነ ሁሉ በልቦለዱ ውስጥ ለሚከናወኑት ሁነታዎችና ድርጊያዎች በተለይ አንባቢዉ የሚጠራጠራቸው ወይም የተለየ አስተያየት ወይም ትርጉም የሚሰጣቸውና ወደ አልታሰበ ሀሳብ የሚያንደረድሩት መስሎ ከታየው ፣ በዚያው በልቦለዱ ውስጥ ከሚካሄደው ህይወት እንዳይወጣና ትክክለኛውን ፈር እንዲይዝ ለማድረግ ፣ እንዳስፈላጊነቱ በማብራሪያ ፣ በገለጣ ፣ በትርጓሜና በመሳሰሉት በመደገፍ የልቦለዳዊዉን አለም ህይወት ታማኝነት ለማብሰር ይጣጣራል ። በዚህ አይነትም ፣ በልቦለዱ ውስጥ ለሚታዩት ፣

- አድራጐቶች ፣ ጠባዮች ፣ ጉዳዮች ፣ የነገር ሂደቶችና ለመሳሰሉት ፤
- ባህርያቱ በአእምሮ ካለመብሰል ፣ ከመጃጀት ፣ ንግግር ካለማወቅ ፣ ወግን ፣ ባህልን ፣ ልምድን ካለመገንዘብ ለሚያሳይዋቸው ድክመቶችና ከነዚህም የተነሳ ለሚኖሩ ፀያፎችን ካለማጤን ለሚፈጠሩ ጉዳዮች ፤
- ባንባቢ በኩል ይነሳሉ ተብለው ለሚገመቱ ተቃውሞዎች (ማለትም ፣ ይህንን ሲያነቡ እንዲህ ብለው ቢያስቡስ ፣ ለዚህኛው ይሄኛው አይነት ሀሳብ ቢመጣባቸውስ ለሚሉት ፣ መደናቀፎቹን በቅድሚያ በማሰብ ፣ መቋቋሚያዎቹን መልሶች እፅሁፉ ውስጥ እንዲኖሩ ለማድረግ)

አስፈላጊ የሆኑ ማፍታቻዎችን ፣ ገለጣዎችን ፣ ትንታኔዎችንና ማብራሪያዎችን እና የመሳሰሉትን ያቀርባል ።



አጅ ፣

(1) ጭውውትን በመተርጎምና በማቃናት

«...‘እስካለ ምን ማለትሽ ነው ፣ እኔና አንቺ በወንድምነት ብንተያይም ሰው ሊጠራጠር ይችላል’ አላት ። ዳኘው በማለት ፈንታ ሰው ብሎ ።

‘ሰው የማያስበውን ማሰብ ፣ ወይም እንዲህ ይባል ይሆናል ማለት የጀግና ፣ የጎበዝ ጠባይ አይደለም’ አለችው ።

ትንሽ ዝም ብለው እንደቆዩም ፣ ‘ለመሆኑ ዳኘውን ምን አርገህ ትገምተዋለህ ?’ አለችው ። ዳኘው እንዳልበደለው ስለምታውቅ የዳኘው ጠላቶች በውሸት የሚያስወሩበትን አምኑዋል ብላ ጠርጥራለች ።

‘ እውሬ ነው የሚመስለኝ ’ አለ ፣ ንገሪኝ ካልሽኝ እውነቱን ልንገርሽ ለማለት ትክሻውን ወደ ላይ ገፋ አድርጎ።

‘ ለምንድነው አውሬ አድርገህ የምትገምተው ?’ አለችው አስካለ ፣ በመገረምም በቅሬታም ።

‘አርበኞች መልካቸው አውሬ ከመምሰሉም ሌላ ጨካኞች ናቸው ’ አለ በጋሻው ፣ ከአስካለ ፊት ላይ ቅሬታ በማየቱ በግል ዳኘውን መጥላቱ እንዳልሆነ ለማሳየት አስተያየቱን ስለ አጠቃላይ አርበኞች አድርጎ ።

‘ ጠላትን ጠላት አድርገህ ካልወሰድከው እንዴት ትዋጋለህ ? ጭካኔ ይህ ነው ?’ አለችው ። ከጥያቄ ይልቅ ትዝብት ነበር ።

‘ እኔ ምን አውቄ ፣ ተዋጊ አይደለሁም’ አለ ። ይህን ነገር ተከራክሮ የሚረታበት እንዳልሆነ ያውቀዋል ...» [6]

[6] ጥላሁን ግስው ፣ ‘አዳባይ ’ ፣ (አ.አ. 1975) ፣ ገጽ 13 ።

### (2) በትንታኔ

'...የልጅነት ዘመን ግን አንድ ደረጃ ላይ ያልፋል ። ያንን ቀን በቅድሚያ የሚያውቀው የለም ። ብቻ በሥጋም በመንፈስም መለወጥ ይመጣል ። አስካለ አስራሁለት ዓመት ሲሆናት እንደድሮው ከበጋሻው ጋር ስትጫወት እስከዚያ ያላስተዋለችውን አስተዋለች ። ከአይኑም ከፊቱም ትልቅ ፍራቻ የሚፈጥርባት ነገር አነበበች ። እሱም ለመጀመሪያ ጊዜ ስታፍር ተመልክቱዋት ልቡን ደስ አለው ። እሱዋ በልጅነት ስሜቱን ለማስተዋል አለመቻልዋ ገደቡ ሲሆን መመልከት መጀመርዋ ግን እሱዋም የልጅነት ዘመኑዋን እንደ ጨረሰች ማረጋገጫ ነበር ። ከድምጹ ቅላፄ ሁሉ ከወንድምነት ሌላ ፍላጎት እንዳለው አነበበች ። ጥርጣሬውን ለማስወገድ ደግሞ የመንደሩ የቤቱ ሰው አለ ። እሱም እራሱ ጥርጣሬዋን አስወገደው ። ወንድሟ አለመሆኑን ተገነዘበች ። ይህ የሽግግር ወቅት ግን የሁለቱንም ሕይወት ለወጠው...'[7]

### (3) በገለጣዎች

'...ወታደሮቹ የሚጉዋዙት እንደአካባቢው ፣ እንደ መንገዱ አመቺነትና ሁኔታ ነው ። አንዳንድ ጊዜ በአቡዋራው ምክንያት ካሚዮኖቹ ተከታትለው መጉዋዝ ሲያቅታቸውና ሌላው አካባቢ ምቹ ሲሆን በመሃላቸው መጠነኛ ክፍት ቦታ በመተው ግራና ቀኝ ጎን ለጎን ይሽከረከራሉ። አንዳንዴ ደግሞ ፣ መንገዳቸው አጠራጣሪና ጫካ ሲሆን ወታደሮቹ በሙሉ ከካሚዩኖቹ ላይ ይወርዱና ግራና ቀኝ አካባቢውን እያሰሱ ወይም እየፈተሹ በእግራቸው ሲጓዙ ካሚዩኖቹ መንገዱን ይዘው በዝግታ ያልፋሉ ።

[7] ከላይ ከተጠቀሰው ፣ ገፅ 53 ።



"በአካባቢው ጠላት ካጋጠመ ተኩስ ይከፈትና በጥይት ተጠዛጥዞ ፣ በሳንጃ ተዘናጥሎ ፣ በቦምብ ተሰናጥሮ ማለፍ ነው ። የሞተው እሬሳው ተቀብሮ ፣ ቁስለኛው ተጭኖ ጉዞው ይቀጥላል ። ቀደም ብሎ ሰርጎ ገቦቹ አደጋ ጥለው ከመሸሽ በስተቀር ፊት ለፊት ገጥመው ስለማይቆዩ የዚህ ዓይነቱ ሁኔታ አዘውትሮ አይገጥምም ነበር..."[8]

### (4) በማብራሪያ

'... በሪሁን ጉዋደኞቹ ሃዘን እንዳይከብዳቸውና ተስፋ እንዳይቆርጡ በማለት ኮስተር ፣ ፈገግ ይበል እንጂ ውስጡ አርዋል ፤ በሃዘን ነፍርዋል ፣ በድካም ዝልዋል ... ታማኝ ጉዋደኛ ፣ ለአንድ ዓላማ አብሮ የቆመ ጉዋደኛ ሲሞት እጅግ ያሳዝናል ፤ ያስደነግጣል ። የብቸኛነትና የተስፋ መቁረጥ ስሜት ያመጣል ። እነዚህ ሁሉ ስሜቶች በሪሁንን ተሰምተውታል ። ግን እውስጡ ቀበራቸው ፤ ዋጣቸው ፤ ማንም እንዲያውቅበት አልፈለገም ። እንዲያውም እነዚህ ስሜቶች ለቆራጥ ዓላማ መሰናከሎች መሆናቸውን አውቆ በሌሎች ጉዋደኞቹ ዘንድ እንዳይኖሩ ተከላከለ ...'[9]

### (ለ) ብዩና አስተያየትና ግምት

ተራኪው ፣ በትረካው ውስጥ ስለሚገጥሙት ባህርያትና ሁነታዎች ማፍታቻና ማጤቃለያ በመስጠት ሳይወሰን ፣ የልቦለዱን ፋይዳ ፣ ርባና ፣ እምነት ፣ የኑሮ ዘይቤና የመሳሰሉትን ፣ በእውናዊው አለም ከሚኖራቸዉ አጠቃላይና ተግባራዊ ትርጓሜ አንፃር እያገናዘበ የራሱ የሆነ አስተያየትና ግምቱን ይሰጣል — አሰራሩ የልቦለዳዊውን

[8], [9] ገበየሁ አየለ ፣ 'ማዎራ ጦር ፣' (አ.አ. 1975) ገፅ 7 ፣ ገፅ 290—91 ።

ፅሁፍ ብቸኛ አመለካከትና የአኗኗር ዘይቤ፣ የሰው ልጅ በአውናዊዉ አለም ከሚከተለው የታመነበት ርእዮተአለምና የአኗኗር ዘይቤ አንፃር በማመሳከር የራሱ የሆነ ብየናን እንደ ማቅረብ ያለ ነው ።

ይህን አይነት የትራኪ ሚና በተለይ ለታዳጊ አገሮች የሚያስፈልግና የሚደገፍም ነው ። ትራኪዉ በዚህ ሚናዉ ነው አጉል ልምድ ፣ አጉል እምልኮት ፣ አጉል አስተሳሰብና በጠቅላላው ኀታቾችና ከጊዜው ጋር የማያራምድ ርእዮተአለምን ለማስቀረት የሚጥረው ። በሌላ በኩል ደግሞ ፣ በዚሁ ሚናው ነው አዲስ ፋይዳ ፣ አዲስ እምነት ፣ አዲስ ያኗኗር ዘይቤና ተራማጅ ርእዮተአለም በህዝብ መንፈስ እየሰረፀ የተግባር መመሪያ እንዲሆን የሚያረገው ። *

ከታሪኩ ሂደት ጋር አብሮ የሚራመደው የዚህን አይነት ግምት አሰጣጥ አንዳንዴ በገላጮች ፣ ቅፅልን በመሳሰሉት ቃላት ፣ ሌላ ጊዜ በስእላዊ ሀረግ ፣ ሌላ ጊዜ ደግሞ ፣ ሰፋ ባለ ፅሁፍ (በአመዛዛኝና በገላጭ ፅሁፍ ውስጥ የተመለከትናቸውን ቴክኒኮች በመጠቀም) ይገለፃል ። የአቀራረቡም ስልት እንዲሁ ሊለያይ ይችላል — በቀልድ ፣ በአሽሙር ፣ በምፀት ፣ ባዜኔታ ፣ በማጋነን ፣ ከፍ ከፍ በማድረግ ፣ በማኪያኪያስ እና በመሳሰሉት ሁሉ ።

<u>አጅ ፤</u>

በዚህ አይነት የሚቀርብ አስተያየትና ግምት ፣ በተለይ በአማርኛ ስነፅሁፍ ውስጥ እንደ ምእራፍ ርእስና እንደ አንቀፅ መንደርደሪያ አረፍተ ነገር ጭምር ሲሰራበት ቆይቷል ።

* ስለ ስነፅሁፍ መልእክት ፣ በተጨማሪ ገፅ 249 ተመልከት ።



(1) እንደ ምዕራፍ ርእስ

<u>ከ ‘ እንደ ወጣች ቀረች ’ [10]</u>

‘መልካም ቤተሰብ’
‘ያልታደለ ጋብቻ’
‘ጊዜ ወዳጅ’
‘የከፋት ዕድሜ’
‘የውሸት ጉልበት’
‘ፍቅር ምኝ’
እና የመሳሰሉት …

ከዚህ በላይ እንደ ተመለከተው ተራኪዉ ፣ ‘መልካም ፣ ያልታደለ ፣ ወዳጅ ፣ የከፋት ፣ የውሸት ፣ ምኝ’ በሚሉት ቅፅሎችና ቅፅል መሰሎች ግምቱንና ብይኑን ሰጥቷል ማለት ነው ።

<u>ከ‘ፍቅር እስከ መቃብር’ [11]</u>

‘የሚታይ እንጂ የማይበላ ፍሬ’
‘የወላድ መካኖች’
‘የቅኔ ማእበል’
‘የጋራ ድል’
‘እፍ ዝም ቢል ሌላው ይናገራል’
‘የብራ መብረቅ’

[10] አሰፋ ገ/ማርያም ፣ ‘እንደወጣች ቀረች’፣ (አ.አ. 1957)፣ ገፆች ፣ 1፣14 54 ፣ 60 ፣ 69 እና 96።

[11] ሀዲስ ዓለማየሁ ፣ ‘ፍቅር እስከ መቃብር’ ፣ (አ.አ. 1973) ፣ ገፆች 39 ፣ 47 ፣ 71 ፣ 172 ፣ 323 እና 373 ።

ፅሁፍ ብቸኛ አመለካከትና የአኗኗር ዘይቤ፣ የሰው ልጅ በእውናዊዉ አለም ከሚከተለው የታመነበት ርእዮተአለምና የአኗኗር ዘይቤ አንፃር በማመሳከር የራሱ የሆነ ብየናን እንደ ማቅረብ ያለ ነው ።

ይህን አይነት የተራኪ ሚና በተለይ ለታዳጊ አገሮች የሚያስፈልግና የሚደገፍም ነው ። ተራኪዉ በዚህ ሚናዉ ነው አጉል ልምድ ፥ አጉል እምልኮት ፥ አጉል አስተሳሰብና በጠቅላላው ኋታችና ከጊዜው ጋር የማያራምድ ርእዮተአለምን ለማስቀረት የሚጥረው ። በሌላ በኩል ደግሞ ፥ በዚሁ ሚናው ነው አዲስ ፋይዳ ፥ አዲስ እምነት ፥ አዲስ ያኗኗር ዘይቤና ተራማጅ ርእዮተአለም በህዝብ መንፈስ እየሰረፀ የተግባር መመሪያ እንዲሆን የሚያረገው ። *

ከታሪኩ ሂደት ጋር አብሮ የሚራመደው የዚህን አይነት ግምት አሰጣጥ አንዳንዴ በገላጮች ፥ ቅፅልን በመሳሰሉት ቃላት ፥ ሌላ ጊዜ በስእላዊ ሀረግ ፥ ሌላ ጊዜ ደግሞ ፥ ሰፋ ባለ ፅሁፍ (በአመዛዛኝና በገላጭ ፅሁፍ ውስጥ የተመለከትናቸውን ቴክኒኮች በመጠቀም) ይገለፃል ። የአቀራረቡም ስልት እንዲሁ ሊለያይ ይችላል — በቀልድ ፥ በአሽሙር ፥ በምፀት ፥ ባዘኔታ ፥ በማጋነን ፥ ከፍ ከፍ በማድረግ ፥ በማኪያኪያስ እና በመሳሰሉት ሁሉ ።

አጅ ፥

በዚህ አይነት የሚቀርብ አስተያየትና ግምት ፥ በተለይ በአማርኛ ስነ-ፅሁፍ ውስጥ እንደ ምእራፍ ርእስና እንደ አንቀፅ መንደርደሪያ አረፍተ ነገር ጭምር ሲሰራበት ቆይቷል ።

* ስለ ስነ-ፅሁፍ መልእክት ፥ በተጨማሪ ገፅ 249 ተመልከት ።



(1) እንደ ምዕራፍ ርእስ

ከ‘እንደ ወጣች ቀረች’ [10]

‘መልካም ቤተሰብ’
‘ያልታደለ ጋብቻ’
‘ጊዜ ወዳጅ’
‘የክፋት ዕድሜ’
‘የውሸት ጉልበት’
‘ፍቅር ሞኙ’
እና የመሳሰሉት …

ከዚህ በላይ እንደ ተመለከተው ተራኪዉ ፥ ‘መልካም ፥ ያልታደለ ፥ ወዳጅ ፥ የክፋት ፥ የውሸት ፥ ሞኙ’ በሚሉት ቅፅሎችና ቅፅል መሰሎች ግምቱንና ብይኑን ሰጥቷል ማለት ነው ።

ከ‘ፍቅር እስከ መቃብር’ [11]

- ‘የሚታይ እንጂ የማይበላ ፍሬ’
  ‘የወላድ መካኖች’
  ‘የቅኔ ማእበል’
  ‘የጋራ ድል’
  ‘እፍ ዝም ቢል ሌላው ይናገራል’
  ‘የብራ መብረቅ’

[10] አሰፋ ገ/ማርያም ፥ ‘እንደወጣች ቀረች’፥ (አ.አ. 1957)፥ ገፆች ፥ 1፥14 54 ፥ 60 ፥ 69 እና 96።

[11] ሀዲስ ዓለማየሁ ፥ ‘ፍቅር እስከ መቃብር’ ፥ (አ.አ. 1973 ) ፥ ገፆች 39 ፥ 47 ፥ 71 ፥ 172 ፥ 323 እና 373 ።

ከ'አዳባይ'[12]

'ማንም ሰው ከህሊናውና ከባሕሉ ሸሽቶ አያመልጥም…'

'ሩህሩህ እናትም እጅዋን የምታነሣበት ጊዜ አለ…' …'ይደርስ እንደሁ እስቲ እጃችሁን ወደ ሰማይ ዘርጉት…' ፡ 'ለራሴና ለቤተሰቤ የማደርገውን ለአገሬ እንዳደረግኩት አልቆጥረውም…'
'ሁለት ባቄላዎች…'

'የምትፈራውን ነገር እንዳያነሱብህ ከፈለግህ ሲመሻሽ ሄደህ ነገ እመጣለሁ ብለህ ተመለስ…'

በሶስቱም መጻህፍት ውስጥ ተራኪዎቹ ርእሶቹን የተጠቀሙባቸው በየምእራፎቹ ውስጥ ለሚያሰፍሯቸው ጉዳዮች መንደርደሪያና ማሰባሰቢያ በማድረግ ጭምርም መሆኑን ማጤኑ ይበጃል ። ( ስለ መንደርደሪያ ከገፅ 123 እስከ 126 ተመልከት ።)

(2) በየአንቀፆቹ ውስጥ-በሁነታዎች ላይ እንደ መበየኛ

ከ'እንደ ወጣች ቀረች'[13]

— '… የሃይማኖት ምቀኝነት የሌላት የወንድማማቾች አገር…'
— '… ሰላማዊዎች ሕዝቦች…'
— '… በድካማቸው ወዝ በሚያገኙት … ተደስተው
— '… ለከንቱ ስም ወይም ለትልቅ ድሎት… ድምበር አልፈው የሰውን ለመውሰድ የማይፈልጉ ህዝቦች…'
— '… የራሳቸውን ለሰው በመለገስ እንግዳን በመቀበልና በመሸኘት … . በስምና በምግባር ደጎች …'
— የወዳ ያ ሰው … በቅንአት ዐይን ተመለከተ
— '… በዚች በተቀደሰች አገር አንድ የተቀደሰ ቤተሰብ . . .'
— '… ጨዋዎች ባላገሮች…'
— '…ባሕሪያቸው እንደመልካቸው እያማረና…'
— 'ታላቅ ምሳሌነትና ሞገስ እየተሰጣቸው ሄደ…'
— '…ሕይወት ካለ ማደግ አይቀርምና …'

'እናት'[14]

'… ወጣቶቹ… የብልግና ዘፈኖችን ወደሚዘፍኑበት . . . አስጸያፊ የሆኑ የብልግና ንግግሮች ወደሚለዋወጡበት … ይሄዳሉ…'

'… አድካሚ በሆነ ሥራ ውልቅልቃቸው የወጣ በመሆኑ…' ፡ 'በረባ-ባልረባው ነገር ሁሉ ፀብ በማንሳት…' ፡ 'ሰብአዊ ግንኙነታቸው የተመሠረተው በክፉ አሳቢነት መንፈስ … ነው…'

[12] ጥላሁን ግሰው ፡ 'አዳባይ' (አ.አ 1975) ፡ ገፆች 55 ፡ 67 ፡ 91 ፡ 109፡ 129 እና 139 ።
[13] አሰፋ ገ/ማርያም ፡ 'እንደ ወጣች ቀረች' ፡ (አ/አ 1957 ) ገፅ ፡1-4 ።
[14] ማክሲም ጎርኪይ ፡ 'እናት' ፡ (ሞስኮ 1981) ከገፅ 21—22 ።

'... ይኸንን ዓላማ-ቢስ የሆነ የጭካኔ ተግባራቸውን ...' '...የሰከሩና የሚያሳዝኑ ገደቢሶችና አሳፋሪዎች ናቸው...'

እነዚህ በቃላት ፣ በሀረግ ፣ አንዳንዴም በሰፊ ፅሁፍ የሚገለፁ አስተያየትና ፍርዶች ፣ በምፀት (ፌዝ) ፣ በቃላት አካባቢ ትርጉም ፣ በሙሉ-በከፊል እና በመሳሰሉትም ይቀርባሉ ።

በምፀት (ፌዝ)

አጅ ፦

'ጥምጥማቸውን የተራራ ስባሪ አሳክለው ቅዳሴ ቆመው ያያቸው መስቀላቸውን ሳይሳለም አያልፍም ፤ ማታ ማታ ጋቢያቸውን ተጐናንበው የንስሐ ልጆቻቸውን መጠየቅ ያዘወትራሉ ።'

(ስለ አካባቢ (ዘመድ አዝማድ) ትርጉም ፣ ሙሉውን በከፊልና ስለ መሳሰሉት ከገፅ 49—54 ተመልከት ።)

## (መ) ማጠቃለያ

በመሸጋገሪያ ዘመን፣በተለይ አብዮት በማካሄድ ላይ በሚገኙ ህዝቦች ውስጥ ከአብዮት በፊት ታማኝነት የነበራቸው ብዙ ሀሳቦች ፣ እምነቶችና አባባሎች መናድ ይጀምራሉ ። አንዳንዶቹ እንኳንስ ለሌሎች አባባሎች መነሻና መሰረት ሊሆኑ ሲያስተላልፉት የቆዩት ፋይዳ መስሎ ይወሰድ የነበረው ቁም ነገር ሁሉ ርባና ያጣል ። በኛ አገርም የሚታየው ሁኔታ ከዚህ የተለየ አይደለም ፤ ለምሳሌ ያህል ስለተሿሚዎችና ስለሴቶች ሲነገሩ የነበሩ አባባሎች (በተለይ ምሳሌና ፈሊጦች) በአብዛኛው ተሽረዋል — 'ሲሾም ያላወቀ ሲሻር ይቆጨዋል' ፤ 'ለንጉሱ አጐ



ንብሱ' ፣ 'የቤት ጠጪ የግመል ፈንጭ የለውም' ፣ 'ልጅ ይሰማል እንጅ አይናገርም' እና የመሳሰሉት ።

ይህ በአንዳንድ መንደርደሪያ ሀሳቦች ረገድ ሲሆን ፣ እምነትን በሚመለከትም ቢሆን ብዙዎቹ እንደማሾፈያ እየተወሰዱ ነው ፤ ለምሳሌ ለታቦት ስለት መሳልና በየታቦቱ ስም መማልን የመሳሰለው ፤ ለታቦት ተስዬ ስለቴ ይሰማልኛል ፣ በታቦት ወይም በእግዚአብሄር ምዬ መሀላው ይደርስብኛል የሚለው እምነት እየተቀነሰ ነው ። እውነትንና ውሸትን ፣ ክፋትንና ደግነትን ፣ መስራትንና አለመስራትን ፣ መውደድንና መጥላትን ስለመሰሉት እንዲሁም ስለአንዳንድ ተቋሞች (ቤተክርስቲያን ፣ መስጊድ ፣ ቤተሰብ ፣ እስር ቤት ፣ ትምህርት ቤት ወዘተ...) የነበረን አስተሳሰብ እየተለወጠ ነው ።

እነዚህ በቀጥታ የእለት በእለት ኑሯችንን የሚመለከቱት አይነቶች ሲሆኑ በርእዮተአለማዊ አመለካከታችንም የሚታየው ለውጥ ከነዚህ የተለየ አይደለም ፤ ሶሻሊስታዊ ርእዮተአለማችን ብዙ የህይወት መለኪያዎቻችንን እያለወጣቸው ነው ።

በዚህ አይነት በልቦለዳዊዉ አለም ውስጥ የምንጠቀምባቸውን አባባሎች በከፍተኛ ጥንቃቄ መምረጥ ይኖርብናል ማለት ነው ። እለዚያ ለአባባሎቹ አጠቃላይ የሆኑና በሚገባ የሚያቅፏቸው ሳይንሳዊና ፍልስፍናዊ እውነትነታቸው የማይጠረጠር ድጋፍ መስጠት ይኖርብናል ።

ድጋፍ መስጠት ይኖርብናል ስንል ደግሞ ፣ ለማያስተማምኑ አባባሎቻችን ሁሉ አጠቃላይና እውነት የያዘ ሳይንሳዊ ወይም ፍልስፍናዊ አባባል እንደማጠቃለያ እናክልበት ማለታችን አይደለም ። በእዉኑ አለም የሚታመንበት (ሳይንሳዊው እውነት ለውጥ ባይኖረውም)

ፍልስፍናዊ እውነት የሚለካው በልቦለዱ ውስጥ በተመለከተው ሁነታ እንፃርም እውነት ሲሆን ነው ።

ለምሳሌ ፣ 'ሰው የሆነ ሁሉ ምንጊዜም እውነቱን መናገር አለበት' የሚል ተቀባይነት ያለው አጠቃላይ የህይወት መመሪያ ቢኖር ፣ የአባባሉን ተአማኒነት የምንረዳው ከተጠቀምንበት ሁኔታ ጋር ሲዋሃድ የሚኖረውን ዝምድና ካጤን በኋላ ነው ፤ ምናልባትም ፣ እውነት መናገር አጉል ውጤት እስካላስከተለ ድረስ ።

ለምሳሌ በሚከተለው ሁነታ አንፃር ፣

አንዲት ብዙ የወለደች ሴት ባሏን ከሌላ ሴት ጠርጥራ ልጆቿን በትና ልትሄድ ስትነሳ አስታራቂ ሆኖ የሚቀርብ ሰው ፣ ምንም እንኳ የባልዬውን ብልግና ቢያውቅም ፣ ሚስትዬዋ ባሏን በአጉል የጠረጠረችው መሆኑን አሳምኖ ቤተሰቡን ከመፍረስ ቢያድን 'ከምንጊዜውም እውነት' 'አንዳንዴ ውሸት' የበለጠ ታማኝነት ይኖረዋል ፤ አያጠያይቅም ።

ስለዚህ ፣ ውነት መታየት ያለበት ፣ በአጠቃላይ እውነትነቱ ሳይሆን ፣ በእውናዊዉም ሆነ በልቦለዳዊዉ አለም ከሚያጋጥመው ብቸኛ ሁኔታ ጋር ከመመቻቸቱ ወይም ተስማምቶ ከመገኘቱ አኳያ ነው ። ቁም ነገሩ ከብቸኛ ሁነታው አንፃር ሲታይ የሚኖረው ተአማኒነት ነው ።

እጅ ፣

"አንድ የመንግስት ባለስልጣን በየጊዜው እየመጣ ስራ የሚያስፈታውና በመጣ ቁጥር ስለራሱ በስተቀር የማያወራ ጓደኛ ነበረው ። ፊለፊት ቢነግረው ይቀየማል ብሎ ስላሰበ እንስቶብት አያውቅም ። ጓደኛው ግን እየባሰበት እንጂ እየተሻሻለ አልሄድ



ብሏል ። እንዲያውም ከመርሳቱ የተነሳ ነገሮችን መደጋገም ጀምሯል ።

"አንድ ቀን ባለስልጣኑ ለአስቸኳይ ስራ ጉዳይ ሊያነጋግሩት የሚፈልጉ ባለጉዳዮች እፀሀፊው ዘንድ ተራ በመጠበቅ ሳሉ ቀደም ብሎ እቢሮው ገብቶ የነበረው ያው የትምህርት ቤት ጓደኛው እንደተለመደው ማብቂያ የሌለውን ስለራሱ ማውራት ጀምሮ ቢሮውን አልለቅ ይለዋል።ፀሀፊቱ አልፎ አልፋ እንግዶቹ እየጠበቁ መሆናቸውን ለመነገር ትደውልለታለች ። በመጨረሻ ለፊርማ የተዘጋጁ አያሌ ፋይሎች ተሸክማ ትገባና የሚጠብቁት ሰዎች ጉዳይ አስቸኳይነቱን ትናገራለች ። ፀሀፊቱ ወጣ እንዳለች ፣ 'አይ እንግዲህ እኔም ጊዜህን አልወስድብህም' እያለ ቢጃራውን በማያያዝ 'እና ይኸውልህ ከዚያ እቤቷ ስደርስ . . ."
<u>አዘውትሮ ስለ ራሱ የሚያወራ ሰው ምንኛ ይሰለቻል ?</u>

ይህ በስረዝ የተመለከተው በተራኪዉ የተሰነዘረ አስተያየት እንግዲህ ለዚህ ድርግ ነው እንጂ ምቹነቱ ስለራሱ አዘውትሮ የሚያወራ ሰው በማንኛውም ሌላ ጊዜ ሁሉ አሰልቺ ነው ማለት አይደለም ።

በሌላ በኩል ደግሞ ፣ አጠቃላይ እውነት የታሪኩ ሂደት አካል እንጂ እንደ ግንጥል ጌጥ ለብቻው ያፈጠጠ ወይም የተደረተ መስሎ መታየት የለበትም ። ፍቺው አጉጦ በመታየቱ ፣ አንባቢዎችን ወደራሱ ስለሚስብ ሊደብቀው የተፈለገው እንዲጋለጥና እንዲጤን ይጋብዛል ። በዚህም አባባሉ ተአማኒነቱን እንዳያጣ ለማድረግ የተደረገው ሙከራ ሁሉ ከንቱ ይቀራል ።

ለምሳሌ ፣ እያንዳንዱን አንቀፅ ወይም ምእራፍ ባስፈላጊዎቹ ሁነታዎችና መዳረጊያዎች እያመቻቸ በሚተርክበት ወቅት ሀሳቡን ያጠናከረና መንደርደሪያ ያገኘ እየ

መሰለው ፣ በየአንቀፁ 'ለሰው ደግ መዋል ለራስ ደግ መዋል ነው ።, የቶሎ ቶሎ ቤት ግድግዳው ሰንበሌጥ ' ፣ ' በአውር ይጠቃቀሷል ፣ በደንቆሮ ይንሾካሾኳል' እያለ ቢጠቃቅስ በታሪኩ ውስጥ ላሉት አባባሎች የገቡ ግንጥል ጌጦች ወይም ድጋሚና ለሁነታዎቹ ማጠቃለያ የገቡ አጫጭር አባባሎች ስለሚመስሉ መደረታቸው በግልፅ ይታያል ።

ከዚህ በታች ከልቦለዶች የተወሰዱ ማስረጃዎችን እናመለክታለን ፤

<u>ከእንደ ወጣች ቀረች</u> [15]

. '...ከፋት የደግነት አፍራሽ ነው ፤ የደግነትንም ዋጋ ያላወቀ የከፋትን ዋጋ ሊያውቅ አይችልም ።'

. '...የመልካሞች ሰዎች መልካም ምኞት ውሎም ቢያድር ደግ ፍጻሜ አያጣምና . . .'

. '...በትምህርት ማደግ ለሰው ልጅ የነውሩ መስተዋት ነውና...'

<u>ከፍቅር እስከ መቃብር</u> [16]

(1) '...ወደታች እያዩ የሚያዙት ካለ ከላይ የሚያዝ ቢኖር ምንም ያክል አይከብድም ...'

(2) '...ከፍና ዝቅ አርጎ እይቶ የሚቆጡትና የሚመቱት በታች ካለ ከላይ የሚቆጣና የሚመ ታቢኖር እያ ምም...'

(3) '...የሚያሸንፉት በታች ካለ ከላይ የሚያሸንፍ ቢኖር ግድየለም...'

[16] እሰፉ ገ/ማርያም ፣ 'እንደ ወጣች ቀረች' ፣ (እ.እ 1957) ፣ ገፅ 1 3 ።
[15] ሀዲስ ዓለማየሁ ፣ 'ፍቅር እስከ መቃብር ፣' (እ. እ. 1973) ፣ ከገፅ 19—21 ።



(4) '...ያልተለመደ እንግዳ ችግር ቆዳ ያሳሳል ፣ ሆድ ባሻ ያደርጋል...'

(5) '... ይግባኝ የሌለባቸው ቆራጭ ፈላጭዋ እሳቸው ብቻ ነበሩ...'

(6) '...ከችግር ጋር ሲታገሉ ፣ ሲጥሉት ሲጥላቸው አብ ረው የኖሩ ቆዳቸው ጠንክሮ ስድብ ይሁን ቁጣ የማይዘልቀው ነበሩ...'

(7) '...የሚገጥማቸውን ችግር ሁሉ በጸጥታና በትእግ ስት የሚቀበሉ...'

(8) '...ለማሸነፍ የሚሞክሩ እንጂ ቶሎ ሆድ የሚ ብሳቸውና ተስፋ የሚቆርጡ አልነበሩም...'

(9) '... ችግር ሲለምዱት ጥሩ ነው...'

(10) '... ችግር ሲለምዱት ጉዋደኛ ሲያደርጉት ከሱ ጋር እየታገሉ እየወደቁ እየተነሱ ሲኖሩ ጥሩ ነው...'

(11) '...ከችግር ጋር ሲታገል የኖረ ቆዳው ይወፍራል ፤ ጅማቱ ይጠነክራል ፤ ጡንቻው ይደነድናል ፤ የተ ጣለበትን ሁሉ ሸክም መሸከም ይችላል ፤ የገጠ መውን ሁሉ ያሸንፋል...'

(12) '... ስለዚህ እድሜ ላሳደጊያቸው ፣ እድሜ ላስተማሪ ያቸው ፣ እድሜ ለችግር ፣ በጋለ መብራቱን ቆዳ ቸውን አወፍሮ ጅማታቸውን አጠንክሮ ትግል እያስተማረ የስድብና የቁጣ የንቀትና የግልምጫ ውሽንፍር እንዳይገባቸው አድርጎ ፣ ሁሉን እንዳ መሉ እንዲችሉ አድርጎ ሳነጻቸው ፣ ለቀረጻቸው እድሜ ለችግር . . .'

(13) '...አቶ በጋለ ሁሉንቻይ ነበሩ...'

(14) ‘…ያቶ ቢጋለ መቻል ፣ ትእግስታቸውና መሽነፍን እንደ ውርደት አለመቁጠራቸው…’

(15) ‘…ብቻ እንዲህ ያለው ግጭትና ኩርፊያ የባልና ምሽት ፍቅር ትንሽ እንደ መደነዝ ሲል ለመሞረድና ለመሳል የሚያስፈልግ በሚዋደዱ ባልና ምሽቶች ሁሉ የሚደርስ ግጭት ነበር…’

(16) ‘…ምርር ብለው ያለቀሱበትን ቶሎ የሚረሱ…’

ከ «እናት»[17]

- ‘…እንቅልፋቸውን ገና ጠግበው ያልጨረሱ…’
- ‘…ቀዝቃዛ አቀባባል ወደሚያደርግላቸው ወደ ፋብሪካው…’
- ‘…እየሩን በባለጌ ፀያፍ ስድቦች እንዲወረር ያደርጉታል…’
- ‘…ማሽኖች የሠርቶ አደሮችን ጉልበት… እንደ ሎሚ ከመጠጡ በኋላ…’
- ‘…ቆሽት የሚቀቅለውን ቮድካ በብዛት ይጠጣሉ…’

ማጠቃለያ፣ እጅግ አስፈላጊ በሆነበት ቦታ ከሆነና ከታሪኩ ሂደት ጋር እስከ ተዋሃደ ድረስ የልቦለድ ታሪኩን ሁኔታና መዳረጊያዎች ከእውናዊዉ አለም ፋይዳዎች ፣ የሞራል መመሪያዎች ፣ ርእዮተአለማዊና ሳይንሳዊ አመለካከቶች ጋር በማዛመድ ተአማኒነትን ይፈጥራል ። የአባባሎችን አግባብ ፣ ወቅታዊ ግልጋሎትና ፍሬ ነገር ይጠ

17 ማክሲም ጎርኪይ፣ ‘እናት’፣ ትርጉም በግዕዝ የማነ(ሞስኮ 1981)፣ ከገፅ 19—21 ።



ቁማል ። ስለሆነም አጠቃቀሙ ጥንቃቄን ይጠይቃል ። ከዚህ በላይ በቁጥር ከተመለከቱት ውስጥ፣ ከቁጥሮች 1—4 እና ከ9—12 የተጠቀሱትን አባባሎች በእውናዊዉም አለም ሆነ በልቦለዳዊዉ አለም ለማሳመን ያስቸግራል ። ተአማኒነት የማያገኙ ከሆነ ደግሞ ልቦለዱንም ተአማኒነት ያሳጡታል ።

## 7.2.5 የተራኪ ድምፅ

የትረካ ግምባር ፣ ተራኪም ሆነ ባለታሪክ ከቦታ ፣ ከርእዮተ አለምና ከእለት በእለት ኑሮ አንፃር ህይወትን የሚመለከቱበት ነው ብለናል ፤ መባያዉ ወይም ቋንቋዉ ሳይሆን ፣ መባያዉ የሚታይበት አኳያ ። የትረካ ድምፅ ግን መባያዉ — ቋንቋና አገባቡ — ነው ፤ ሁነቶችና መዳረጊያዎች ለአንባቢዉ ወይም ለሰሚዉ የሚተላለፉበት ።

ድምፅም እንደ ግምባር ፣ አንዳንዴ የተራኪዉ አንዳንዴ ደግሞ የባለታሪኩ ይሆናል ። ስለሆነም የባለታሪኩም ሆነ የተራኪው ድምፅ በመስማቱ ግምባሩም የየራሳቸው ነው ለማለት አይቻልም ። አንዳንዴ ድምፁ የተራኪዉ ሲሆን የሚየያው ወይም የሚያጤነው (ባለግምባሩ) ግን ባለታሪኩ ይሆናል ። አንዳንዴ ደግሞ ድምፁም ግምባሩም የተራኪዉ ይሆናል ።

እጅ ፣

(ሀ) ድምፁም ግምባሩም የተራኪዉ ሲሆን ፣

‘…አዳባይ በክረምት ይደፈርሳል ፤ ቀይ አፈር ይመስላል ። ጥቁር ፣ ትልቅ ሰፊ ሆኖ ፍጥነቱ እየጨመረ እንደ ገደል ናዳ እየተወረወረ የበጋውን ቀጭን ጅረት ኩል መሳይ ውሃውን እያለበሰ ፣ ደረቅ በነበረበት ቦታዎች ሁሉ

እየተሹለከለከና ድንጋዮችን እየናደ ፥ ዛፍ እየነቀለ ፥ እያ ጓሩ ገስግሶ ደረቅ የነበረውን ቦታ ሁሉ ያለብሰዋል ። ክረምቱ ሲያልፍ ወተት ይመስላል ። ቆይቶ ኩል መስሎ ይጠራል ። በአንድ ወቅት የነበረውን ለማስታወስ እድል አይሰጥም ። በየትኛውም መልኩ ውብ ስለሆነ ያለፈውን የመናፈቅ ትዝታ አያመጣም...'[18]

(ለ) ድምፁ የተራኪው ፥ ግምባሩ የባለታሪኩ ሲሆን

'...ደርቤ ኪሱ ውስጥ ያለውን አምባር በልዩ ስሜት እየዳበሰ ወደ ቤት ገባ ። ገረዱዋ አዲስ ስለ ነበረች አላወቀችውም ። ወይዘሮ እምሳለ ሲያነጋግሩት አይታ ስለ ነበረ በአክብሮት እጅ ነስታው ወደ ሳሎን አስገባችው ። እጀ ሰባራ ያደርጉት የነበሩት አሮጌ ሶፋዎች የሉም ። እንግዳ ቤቱ በአዳዲስ የቤት ዕቃዎችና ምንጣፍ ከመጠን በላይ አጊጦ አል ። በእሜቴ ሹል ታኮ ጫማ ፥ ፈንጣጣ እንደ በላው ፊት የተጠቀጠቀው ጣውላ መልኩን አል ለወጠም ። እንደ በፊቱ ነበር ። ጉልበቴን የበላ ጣውላ የሚል አሳብ መጣበት...'[19]

## 7.2.6 የተራኪ መልእክት *

በኪነ-ፅሁፍ አለም መልእክት የሚባለው ፥ በባለታ ሪኮቹ ፥ በሁነቶቹ ፥ በድርጊቶቹና በምስሎች አማካይነት አካል የሚያገኘው ሀሳብ ነው ፤ ስጋዊና መንፈሳዊ አስተ ያየትን የያዘው ።

[18] ጥላሁን ጣሰው ፥ 'አዳባይ' ፥ (አ.አ. 1957) ፥ ገፅ 27—28 ።
[19] በዓሉ ግርማ ፥ 'የቀይ ኮከብ ጥሪ' ፥(አ.አ. 1972 ፥) ገፅ 66 ።
* (ስለ ስነ ፅሁፍ መልእክት በተጨማሪ ገፅ 294 ተመልከት ።)



ለምሳሌ ያህል ከ'ጦቢያ'[20] እንውሰድ ፥

(ሀ) <u>በባለታሪኮች</u>

(1) ደግና ቸር በነበረው የዋህድ አባት

(2) የዋህድን አባት ባስፈታው ሀብታም ነጋዴ

(3) ዋህድን ተደብድቦ ከወደቀበት ባነሳችው ኩበት ለቃሚ ሴት

(ለ) <u>በሁነቶችና በድርጊቶች</u>

(1) ያረመኔው ንጉስ ፥ ጦቢያን ከናባቷ አተራራው ላይ በማረካቸው ጊዜ በሚሆነው ሁኔታ.

(2) ጦቢያን ፥ ባላደረገችው ድርጊት ፥ ድንኩ ባሳ ጣት ጊዜ ፥ የንጉሱ እህት እንዳትጋለጥ ባሳየ ችው ተጋድሎ

(መ) <u>በምሳሌዎችና በገላጮች</u>

(1) "ደግ አድራጊ አበደረ
ክፉ አድራጊ ተገደረ...
ሎጋስ ቢለግስ አበደረ እንጂ አልሰጠም..."

(2) "...የሰው ውለታ እንዲህ ክፉም ቢሆን በጎ በወዲያኛው ዓለም ብቻም አይደል አንዳንድ ጊዜ በዚህም ዓለም ወይ ፍዳው ወይ ካሳው ላድራጊው ይደርሳል..."

[20] አፈ ወርቅ ገ/የሱስ ፥ "ልብ ወለድ ታሪክ ፥" (አስመራ) 1958 ፤ ገፅ 50 ፥ 74 ፥ 1 እና 84 ።

(3) "...ባንድ ኑጋዴ ሰበብ ሁሉ ዳነ። ባንድ አሌት ምክንያት ሁሉ አመነ። ባንድ ንጉሥ ቃል ኢትዮጵያ ቆመ..."

በልቦለድ ስራ ዋናው ቁም ነገር (ታሪኩ ፣ መልእክቱ ፣ ሴማው) እና (እውን መስለው የሚታዩ ገፀ-ባህርያቱ ሳይሆኑ) ከጠቅላላው ቅንብር የሚገኘው ህያው የሆነ ልምድ መሆኑን አስተውል ።

## 7.3. ባለታሪኮች (ገፀ-ባህርያት)

### 7.3.1 መግለጫ

ባለታሪኮች የታሪኩ ባለቤት እንደ መሆናቸው በአብዛኛው ሰዎች ሲሆኑ እንሰሳንና ግኡዝ ነገሮችን እንደሚጨምሩ ጠቁመናል ። ባለታሪኮች ፣ የአንባቢን ፍላጎት እንዲማርኩ ፣ አንባቢዉን በእውናዊዉ አለም የገጠሙት ወይም ሊገጥሙት ይችላሉ ተብለው የተገመቱ ፣ በየመፃህፍቱ ፣ ሲኒማውና በሌሎችም ኪነጥበባት ውስጥ የተለማመዳቸው ሰዎች አይነት ሊሆኑ ይገባል ። -

የባለታሪኩ ሞዴል ደራሲዉ የሚያውቀው አንድ ሰው ሊሆን ይችላል ፤ ወይም አያሌ ሰዎች — እና ከሚያውቃቸው አያሌ ሰዎች ነው አውጣጥቶ የሚቀርፀው ። ስለዚህም አንባቢዎቹም እንደዬ ይሆን ፣ ሴላ ጊዜ ያን ይመስላል በማለት የየራሳቸውን ግምት ፣ ፍላጎት ፣ አውቂያ ፣ አስተያየት እየጨመሩ ፣ በለመዱትና እውናዊ ሰው ነው በሚያሰኝ መለኪያቸው እየገመገሙ ታሪኩን ይከታተላሉ ። ስለሆነም የልቦለዳዊ አለም ባለታሪክ የዚያው አለም አካል መሆኑ መዘንጋት የለበትም ።

በልቦለድ አለም ውስጥ ሁለት አይነት አበይት ባለታሪኮች አሉ ፤ ነጠላና ውስብስብ ባለታሪኮች በመባል ይታወቃሉ ። ዋናው መለዮአቸውም እንዲህ ነው ወይም እንዲህ ነች በመባል ለመታወቅ ወይም ላለመታወቅ ያላቸው አካላዊና ባህርያዊ አቀራረብ ነው ።



### .2 የባለታሪክ አይነቶች

#### (ሀ) ነጠላ ባለታሪክ

በእውናዊዉም ሆነ በልቦለዱ አለም አንዳንዱ ባለታሪክ የአንድ ውሳኔ ባህሪ ተገዥ ሲሆን ይታያል ። ይህም እንደ ሁኔታው ይለያያል ። አንዳንዱ አንድ ድምፅ ሰማሁ ብሎ ፣ ሌላው የማይፈልገው ቃል ተጠራ ብሎ በየመንገዱ ቅጡ ሲጠፋው ይታያል — ለምሳሌ — ሳጥ የሚል ድምፅ ሰማሁ ብሎ ወይም 'አይጥ' ፣ 'አባብ' የተባሉት ቃላት ተጠሩ ብኝ እና አስደነገጡኝ በማለት ሳቢያ ሊደባደብ የሚፎክረውን አይነት ። እንዲህ ያለው ባህርይ ፣ ድርጊያውን እንደ ቀልድ ወይም የምር ይጀምርና የማይነቀልና ውለኛ ባህርይ ሆኖበት ይቀራል— ማለትም ያ ድምፅ ቡተሰማ ጊዜ ወይም ያ ቃል በተነገረ ወቅት ፣ ያ ሰው ወይምባለታሪክ ፣ 'እንዲያ' ያለ ባህርይ እንደሚያሳይ እውቅ ነው ማለት ነው። ይህም ብቻ አይደለም ፤ ከጊዜ በኋላ ሌሎች ባህርያቱ ሁሉ እየተሸፈኑ ያው አንዱ ብቻ ይገንና መታወቂያው እስከ መሆን ይደርሳል ። ከዚህ አይነቱ እምብዛም የማይለዩ ሌሎችም ነጠላ-ውሳዊ-ባህርያት አሉ ። እነዚህ ረቂቅ ሀሳቦችን የሚገልፁ የግብር ስሞች ሲሆኑ ፣ ባለታሪኮቹ የሚወክሉት ያኑን የግብር ስሙን ሀሳብ ነው ። ለምሳሌ ትእግስት ፣ ደግነት ፣ ክፋት ፣ እውቀት እና የመሳሰሉት — በነዚህ ስሞች የሚጠሩ ባለታሪኮች በስሞቹ የተወከሉትን ሀሳቦች በተግባር ማሳየት ይኖርባቸዋል ማለት ነው ። ምንም ያድርጉ ፣ ምንም ይድረስባቸው ወይም ይድረስላቸው መደምደሚ

ያው በስማቸው የተጠቀሰው ባህርይ ይሆናል፤ሌላው ሌላው ሰዋዊ ባህርያቸው ይዋጥና (ከብላቴን ጌታ ኅሩይ ወ/ሥላሴ ፥ 'ወዳጄ ልቤ' ውስጥ ያሉትን ባለታሪኮች ተመልከት)፤ከዚህም የተነሳ ስማቸው እንደ ተጠራ ወዲያው በታሪኩ ውስጥ የሚኖራቸው ተሳትፎ ስለሚታወቅ አጓጊነትና አስገራሚነት ይጎድላቸዋል ። ስለሆነም ከእንደዚህ አይነቶቹ ውስጥ አንድ ሳይሆን ከአንድ በላይ ውለኛ ባህርያት የሚኖራቸው አንዳንዶቹ ገፀ-ባህያት ጠባብ እንቅስቃሴአቸውን አልፈው በመውጣት የውስብስብነት ጠባያት ያላቸው ስለሚመስሉ በተለይ በአጫጭር ልቦለዶች ውስጥ አቢይ ባለታሪክ እየሆኑ በብዛት ይሰራባቸዋል ።

ለማንኛውም ፥ ነጠላ ባህርያት ፥ ከዚህ በፊት እንደ ጠቀስነው ፥ በወል ስም ፥ በግብር ስም አንዳንዴም በተፀውኦ ስም ቢጠሩም ፥ በየምእራፉ የሚያስገኙ ተሳትፎ ስለማይኖራቸው አገልግሎታቸው በይበልጥ በአዳራጊነት/ተገንነት ፥ በአጋላጭነት ፥ የዋናውን ባህሪ ትውስታ ተጨባጭ በማድረግ ወዘተ.... ይሆናል ። በዚህም ተግባራቸው የሚከተሉት አገልግሎቶች ይኖሯቸዋል ፤

(1) የዋናዎቹን ባለታሪኮች ባህርይ ለማጉላት (ስለ ዋናዉ ባለታሪክ ከሌሎች ባለታሪኮች ጋር በማውራት ወይም ለየብቻቸው በማሰላሰል ፥ ወይም አብረው ሆነው በሚያሳዩት ድርጊት) ፥

(2) በምስጢር ተካፋይነት — ችግሩን ፥ ብሶቱን ፥ ብስጭቱን ፤ ጉድለቱን ፥ ድርጊቱን ወዘተ... ስለሚያጫውታቸው ፥ በቀጥታ ከዋናዉ ባለታሪክ ልናገኘው የማንችለውን ሁኔታ በማቅረብ ፥



(3) ዋናዉ ባለታሪክ ለሚጉድለው የአካል ወይም የባህርይ ጉድለት አነፃፃሪ በመሆን (ደካማ እንደሆነ ኅበዝ ፥ ክፉና ግልፍተኛ እንደሆነ ደግና ታጋሽ ሆኖ በመገኘት እና በመሳሰለው ) ፥

(4) ራሳቸውን ችለው ፥ ለአንድ ለታወቀ ሙያ በመቆም፥ በዚያ ሙያ ለታወቁ ባለታሪኮች መስተዋት በመሆን (ሰርቶ አደርን ፥ ገበሬን ወዘተ.... በመወከል) ፥

(5) የተወሰነ ባለታሪክን በመወከል — (አቶ ትእግስት ፥ አቶ ትህትና ወዘተ... ) ፥

(6) ባጠቃላይ የታሪኩ ደጀን በመሆን ፥

(ከታሪኩ ጋር ቀጥታ ግንኙነት ሳይኖራቸው የአጠቃላይ አካባቢውን ሁኔታ ለመፍጠር—በፊልም ውስጥ ዋናው ባለታሪክ የሚገኝበት ድርጊት ሲከናወን ሲያልፉ ሲያገድሙ እንደሚታዩት ሰዎች ።)

እዚህ ላይ ከላይ በተጠቀሱት አቀራረቦች ረገድ የሚነሱ አንዳንድ ችግሮችን ማጤን ያስፈልጋል ።

(ሀ) <u>በፅሁፉ ረገድ</u>

(1) አንዳንዴ የፅሁፉን ዋና ዋና ባለታሪኮች በግብር ስም እንጠራቸዋለን ። ይህንንም ስናደርግ ፥ የሚታዩ ፥ የሚጨበጡ የሚያደርጋቸው ጉልህነት ይቀራል ። ሰው መሆናቸው-ቀርቶ ሀሳብ ይሆናሉ ። መፅሀፉም የሰው ልጅ በሙሉ ስብእናው የሚታይበት ልቦለድ መሆኑ ይቀርና የሀሳብ ፥ የሃይማኖት ፥ የፍልስፍና ስነ ፅሁፍ ይሆናል ። ይህን አይነቱ አቀራረብ በቦታው ፥ ለምሳሌ በ'ወዳጄ ልቤ' ውስጥ እንደምናየው አይነት ፥ ሊጠቅም ይችላል ።

(2) ብዙ ጊዜ የዋና ዋናዎቹንም ሆነ የነጠላዎቹን ባለታሪኮች ቁጥር አንወስንም ። ከዚህም የተነሳ በየምእራፉም ሆነ አልፎ አልፎ አዳዲስ ባለታሪኮች ስለምንጨምር ፅሁፉ ደብዛዛ ይሆናል ፤ ማእከል ያጣል ። በዘፈቀደ በየቦታው የሚጨመሩ ብዙ ባለታሪኮችን ቀርቶ አንድን ባለታሪክ እንኳ ቢሆን በሙሉ ሰብእናው በሚጨበጥ መንገድ ፣ ባንድ ጥራዝ ውስጥ መግለፅ አስቸጋሪ ተግባር ነው ።

(ለ) በአንባቢ ረገድ

(1) በልቦለዱ ውስጥ ለነጠላ ባለታሪኮች የተፀውኦ ስም እንሰጣለን ። በዋናው ባለታሪክ ትውስታ ውስጥ በሆነ ባልከፋም ፣ ያውም አንዴ ወይም ሁለቴ ። ከዚያ ውጪ ከሆኑ ግን የታሪኩን ሀረግ የሚከታተለውን አንባቢ ፣ ስማቸውን ማጤን ስለሚኖርበት ከብዛታቸው የተነሳ ያደናግሩታል ።

(2) በሌላ በኩል ደግሞ ፣ ባንዴ ሁለቴ ብቻ ተቀጭተው ስለሚቀሩ (በከንቱ ተስፋ ፣ ካሁን አሁን ቀጥለው የሚለውን አንባቢ) ሀሳብ ይበትናሉ ።

(3) ለዋናዎቹ ባለታሪኮች አንባቢው ሊኖረው ይገባ የነበረው አትኩሮት በነጠላ ባለታሪኮቹ ይዋጣል ።

(መ) ውስብስብ ባለታሪክ

በእውናዊዉም ሆነ በልቦለዳዊዉ አለም ውስብስብ ባለታሪኩ ፣ በነጠላው ባለታሪክ ውስጥ እንደ ተመለከተው ፣ የአንድ ወይም የሁለት ውለኛ ባህርያት ተገዥ አይደለም ። አያሌ ውለኛ ባህርያት አሉት ፤ አንዳንዶቹ ይጋጫሉ ፤ ሌሎቹ ይቃ



ረናሉ ፤ ጠባዩ እንዲህ ነው ብሎ መወሰን ያዳግታል። ለምሳሌ ውለኛ ባህርይው ጭካኔ የሆነ ባለታሪክ፣ አልፎ አልፎ ሩህሩህና ደግ ሲሆን ይታያል ። እንዲያም ሆኖ በዚህ ሁኔታ ሩህሩህና ደግ በዚያ ሁኔታ ጨካኝ ይሆናል በመባል ሊታወቅ አይችልም ፤ እምብዛም በቅድሚያ አይተነበይም ።

ውለኛ ባህርይ

ውለኛ ባህርይ እንግዲህ አባዜ ቢያዝ ቁጥር የማይለወጥ የየአንዳንዱ ሰው መሰረታዊ ፣ አብሮ የሚኖርና አንዱን ከሌላው መለያ የሆነ ባህርይ ነው ። ጊዜያዊና አላፊ የሆኑ የተወሰኑ ሁኔታዎች ከሚፈጥሩት ድንገተኛ የባህሪ ክስተት ተለይቶ መታወቅ አለበት ። ለምሳሌ ባንድ ሁነት ወቅት አንዱ ባለታሪክ ፍርሃት ይዞት ይሆናል ። በሌላ ወቅት ግን ያው ሁነት ቢደገምም ሆነ ሌላ ተመሳሳይ ሁነት ቢፈጠር ባለታሪኩ ይፈራል ማለት አይደለም ፤ ሊፈራም ላይፈራም ይችላል ፤ ፍርሃቱ በድፍረት ሊለወጥ ይችላል ፤ ምንም አይነት ስሜት ላይፈጥርበትም ይችላል ። የዚህ አይነቱ ጊዜያዊ ስሜት ፣ ሀሳብ ፣ አዝማሚያ እና የደስታ ፣ የሀዘን ፣ የኩርፊያ እና የመሳሰሉት መጣ-መለስ የሚል አባዜ ውለኛነት የለውም ። ስለሆነም ከውልኛ ባህርያት ጋር አብሮ ሊከሰትም ላይከሰትም ይችላል—እንደ ሁናቴው ፤ ማለትም በአብዛኛው ደልዳላ ባህሪ ያለውና ታጋሽ የሆነ ሰው መውጫ ሲያጣ ቱግ እንደሚል አይነት ፤ ወይም፣ በመሰረቱ ህግ አክባሪ የሆነ ሰው ፣ ህጉን ራሳቸው ህግ አውጪዎቹ ሲሽሩት ሲያይ ህግ እንደሚጥስ አይነት ። ወይም ፣ በአ

ንድ በተወሰነ ሁነታ ጊዜ በአንድ ባለታሪክ አእምሮ ውስጥ ፣ በባህሪነቱ ዘላቂነት ኖሮት ሳይ ሆን ፣ ለሁነቱና ለወቅቱ እንደሚያመችና እንደ ሚስማማ ሆኖ ፣ እንደሚከሰተው ተገቢ እሳቤና ብሎም ድርጊያ አይነት ። ይህንን መሳዩ ብልጭ ድርግም የሚል የሀሳብ፣የስሜት፣የጊዜያዊ ፍላጐትና የሁነታዊ አባዜ ብልጭታ ራሱን የቻለ የሁለንታዊ፣ የአጠቃላይና የአካባቢ እውነት ወለለት (ከአጠቃ ላይ እውነታዎች በማስተጋባት የሚፈጠር) እና የጊዜያዊ ክስተት ግንዛቤ ውጤት ነው እንጂ ዘላ ቂነት ያለው ውለኛ ባህርይ አይደለም ። ከመጀመ ሪያው እንደ ጠቆምነው፣ውለኛ ባህርይ መሰረታዊና መለዮ ባህርይ ነው። መለዮ ባህሪ በቁጥር እየጨመ ረና እልፎ አልፎም አንዱ ሌላውን እየተጫነውና አንዳንዴም እየተካው የሚከሰት ባህርይ ነው — ማለትም አንድ ባለታሪክ እስከ ተወሰነ የወጣት ነት ዘመኑ (20 ዓመት) ፈሪና ወላዋይ ሆኖ ኖሮ እንደሁ ፣ ከ20 ዓመቱ በኋላ ደፋርና ቆራጥ በመሆን ሊለወጥ ይችላል ። ወይም ድፍረት ሳያጣ ዳተኛነት የሚያጠቃው ሆኖ የኖረው ፣ ደፋርና ፈጣን ሊወ ጣው ይችላል ። የባለታሪክ ድርጊያ ሁሉ ተአ ማኒነቱ የሚለካው ፣ ድርጊያው ከውለኛ ባህሪው የመነጨ ወይም ያልመነጨ ከመሆኑ አኳያ እየታየ ነው ። ውስብስብ ባለታሪክ የሚባለውም ፣ በእውና ዊው አለም ውስጥ እንደሚገጥመን ወዳጃችንም ሆነ ጠላታችን አይነት ፣ በእርግጥ እንዲህ ነው ብለን ማ ወቅ ስለሚያዳግተን ነው—ከውለኛ ባህርያቱ ውስብ ስብነት የተነሳ። ብዙውን ጊዜ በየሁነታው አዲስ መ ስሎ ስለሚታይና የማስገረም ችሎታ ስለሚኖረው ።

(ለውለኛ ባህርይ ምሳሌ ከገፅ 340-344 ተመልከት ።)



## 3. በለታሪክ የማቅረቢያ ዘዴዎች

### (ሀ) ቀጥታ በሆነ በተራኪ መግለጫ የሚቀርብ

የዚህ አይነቱ ዘዴ ፣ ባለታሪኩን በሙሉ በፅሁፉ መግቢያ ላይ በማስፈር ወይም በድርጊያ እየደገፈ በፅሁፉ ውስጥ እልፎ እልፎ በማስገባት ያቀርባል ። በመግቢያው ገደማ ፣ የባለታሪኩን ምንነት ባንድ ነት የማቅረቡና የማስተዋወቁ ዘዴ በአሁኑ ዘመን እምብዛም ባይሰራበትም፣ በብዙ ልቦለዶች ውስጥ ሲያገለግል ቆይቷል። ከዚህ የማቅረቢያ ዘዴ ውስጥ፣ በአሁኑ ዘመንም በብዛት የሚሰራበት በመግቢያው ገደማም ቢሆን፣ በየቦታው በማደላደል የሚቀርበው በተከታታይ ብልጭ ድርግምታዎች ፣ በተለያዩ ድርጊያዎችና ትርከቶች አማካይነት የሚገለፀው ነው ። አጠቃላይ ዘዴው ለአንደኛ መደብ ወይም 'ለአዋቂ-ኩሉ' ተራኪ ነው የሚያገለግለው። (ከገፅ 302 እስከ 304 ተመልከት ።)

**አስረጅ ፣**

**(1) አካላዊ አቀራረብ**

"...አቶ ጉልላትም እንደ ባለቤታቸው እንደ ወይ ዘሮ እምላለ እንቅልፍ አጥተው በመቸገር ፣ ስንደዶ የመሰለ አፍንጫቸውን ከአንሶላው ብቅ አድርገው ፣ ወርዝቶ የሚታየውን መላጣቸውን እያብለጨለጩ፣ እንደ ጉድጓድ ውሀ ወደ ውስጥ የራቁትን አይኖቻ ቸውን ብልጭ ድርግም ያደርጋሉ ፤ ወፍራም ሰው ነታቸው አባይ ይዞት እንደሚሄድ ግንድ ከአልጋው ውስጥ ይገላበጣል..."[21]

---

[21] በዓሉ ግርማ ፣ 'የቀይ ኮከብ ጥሪ'፣ (አ.አ. 1972) ፣ ገፅ 5 ።

"...እወንትም መቢያው እጅግ የተዋበች ፥ እጅግ የተደነቀች ፥ ላያት ሁሉ የምታነሆልልና የምታዘ ነጋ ነበረች ። ዓይንዋ አስቀድሞ የብር አሎሎ መስሎ ከአጥቢያው ኮከብ የተፎካከረ ነበር ። በዚህ ላይ ደግሞ ሽፋሽፍቷ እንደ በልግ ሣር ተጨብጦ የሚታጨድ ይመስል ነበር ። አፍንጫዋ ቀጥ ያለ ፥ ከንፈሯ መፈንዳት የጀመረ የማለዳ ጽጌ ረዳ ይመስል ነበር። እንደወንድ የተቆረጠችው ጠጉርዋ እንደ ሰኔ ቡቃያ ወይም እንዳዲስ መሬት ጤፍ እየጋሸበ የሐር ነዶ መስለ ። በፀሐይና በውርጭ የተንሳቀለውና የጠቆረው ፊቷ እያሸለተ ሀሜ በረዶ ተመስለው ጥርሷ ጋር ገና ከሩቁ እየጠቀሰ ከተሸሸገችበት ቤት ነቷን ያሳጣበት ጀመር። አጠረች፥ ረዘመች ፥ ወፈረች ቀጠነች የማይሉትን ያካላቷን ነገር መናገር በከንቱ ነው ። እሞ ብርሌ የመሰለው አንገቷ እንደ ደከመው እያረፈ የወጣ ነው ። አለፀጥንት የተሠራው የእጅ ጣቷ እጅ ሥራ ከበዛበት አመልማሎ ይፎካከራል ። እንደ ፈረስ ለኮ ሳብረገብ ያለው ዐጥንት የሌለበት ወገቧ ከንብ አውራው ጋር ይለካካል ። ባቷ፥ ተረከዟ፥ ይቆጡኛል ያለ የተሠራ የተቆጣ ነው ። ስትፈራ ስትቸር የምትገልጠው ጥርስና ከንፍሯ ከዚያ አት ያይ ጋር ብርቱውን ያዝላል፥ሰነፉን ይገድላል. . ."[22]

(2) <u>ድብልቅ አካላዊና ባህርያዊ አቀራረብ</u>

'...መላ ሰውነቱን ፀጉር የወረረው ፥ አመለካከቱ ጭፍግግ ያለ በመሆኑ የቀፈፈው ፥ በተጠራጣሪነት የሚመለከቱ ትናንሽ ዐይኖች ያሉት እና የቅንድብ

[22] አፈ ወርቅ ገ/የሱስ ፥ 'ጦቢያ' (አ.አ 1958) ፥ ገጽ 47 ።



ቹን ሽፋሽፍቶችም በአጓጉል አመለካከት ከፍ-ዝቅ የሚያደርጋቸው ሚካኤል ቭላሶቭ የተሰኘው ሜካኒክ ይኸንን የመሰለ አኗኗር ይኖራል ። ፋብሪካው ውስጥ ከሚሠሩት ሁሉ በችሎታው እጅግ የተደነቀ ሜካኒክ ሲሆን ፥ በሚኖርበቱ አካባቢም እጅግ ጠንካራ የሆነ ጉልበታማ ሰው እርሱ ነው ። ከበላይ አለቆቹ ጋር ግን የማይስማማ በመሆኑ ምክንያት የደሞዝ ዐበሉ ዝቅተኛ ነው ። በማንኛውም የበዓል ቀን ፥ ከአንዱ ካገኘው ሰው ጋር በመጣላት ያንን የተጣላውን ሰው አፈር-መሬት አስግጦ ስለሚለቀው ሰው ሁሉ የጠላውና የፈራው ነው . . . በፀጉር የተወረሩት እጆቹ እና ፊቱ ፥ ከዐይኖቹ አንሥቶ እስከ አንገቱ ድረስ ተንዠርግጎ የወረደው ጥቁር ጢሙ ማንንም የሚያስበረግግ ነው ። ሰዎች ግን በተለይ የሚፈሩት ዐይኖቹን ነው — ዐይኖቹ ትናንሾች ናቸው ። ነገር ግን በጥልቀት አተኩረው የሚመለከቱ ስለሆኑ ፥ በሌላው ሰው አእምሮ ውስጥ ጠልቀው የሚገቡ ይመስላሉ ። እነዚሁኑ ዐይኖቹን የተመለከተ ማንም ሰው ቢሆን ፥ በሃሳቡ የሚያሰላስለው ፥ እንዳችም ፍርሀት የሌለበት እና ይቅርታ-ቢስ ከሆነ አጥቂ አውሬ ፊት የቆመ መስሎት ነው...'[23]

[23] ማክሲም ጎርኪይ ፥ 'እናት' ፥(ሶቪየት ሀብረት ፥ 1981) ፥ ገፅ 25-6 ።

## (3) ባህርያዊ አቀራረብ

### በጭውውት ፥ በድርጊያዎችና በትርክቶች የሚቀርብ ፥ ከተራኪ አስተያየት ጋር

#### በድርጎች — ትርክቶች

«...'እናንት የውሾች ልጆች ! ድራሻችሁ ይጥፋና ፥ አትጠፉም ከዚህ ! በማለት በጢም ከተከበቡት ከናፍሮቹ ውስጥ በልዘው ቢጫ የሆኑ ፍልጥ-ፍልጥ የሚያካክሉ ጥርሶቹን ግጥጥ በማድረግ ጎርናና በሆነ ድምፅ ይናገራል... ሰዎች ተነስተው በመሄድ ላይ ሳሉ የፈሩ ስድባቸውን ፈራ-ተባ እያሉ ይጣጥላሉ ።

«...'የውሾች ልጆች !' ይላቸዋል ፤ ዐይኖቹን ከጉድጓዶቹ እንደ ወስፈ አሹሎ በማውጣት እና በንቀት አመለካከትም በመመልከት እየተከተላቸው . . . ጭንቅላቱን ከፍ በማድረግም . . .

«...'ታዲያስ ፥ ማነው መሞት የሚፈልግ ?'

«ቭላሶቭ ብዙ አይናገርም ። 'የውሻ ልጅ' የሚለው ስድቡ ግን ... ፖሊሶችን ፥ ባለሥልጣኖችን ፥ የፋብሪካውን አለቆች ለመስደብ የሚጠቀምበት . . . . ነው ። ሁልጊዜም ሚስቱን ይጠራት የነበረው — 'አንቺ ውሻ' በማለት ነበር ።

'አንቺ ውሻ ፥ አታዩም እንዴ እዚህ ፥ ሱሪዬ እኮ ተቀድዷል ... !'...» [24]

[24] ከላይ ከተጠቀሰው ፥ ገፅ 26 ።



#### በድርጊያዎች (በተግባር በሚከሰቱ እንቅስቃሴዎች)

'...እንደርሱው ትልቅ እና ፀጉራም የሆነ ውሻ አለው ። ሁልጊዜ ጧት በማለዳ እስከ ፋብሪካው ድረስ ተከትሎት የሚሄድ ሲሆን ፥ በምሽት ላይ ደግሞ ፥ ከፋብሪካው ደጃፍ ላይ ቆሞ ይጠብቀዋል ። ቭላሶቭ የበዓላት ቀኖችን የሚያሳልፈው ከአንዱ መሸታ ቤት ወደ ሌላ መሸታ ቤት በመዞር ነው . . . ውሻውም ፀጉርማ ጭራውን እየቆላ ቀኑን ሙሉ ጌታውን በመከተል . . . ይውላል ። ቭላሶቭ ሰክሮ ወደ ቤቱ በመመለስ ለእራት ወደ ገበታ ሲቀርብ ውሻውንም ራሱ በሚመገብበት ሳሕን ያበላዋል ። አንድም ጊዜ ቢሆን ውሻውን ሰድቦትም ሆነ ወይንም መትቶ አያውቅም ። ይሁን እንጂ ደግሞ ፥ አንድም ጊዜ ቢሆን የጨዋታ ንግግር አሰምቶት ... አያውቅም ። ከእራት በኋላ ሚስቱ የማዕዱን ሳሕኖች ከማንሳት ዘግየት ካለች ፥ ሳሕኖቹን መሬት ላይ ይወረውራቸዋል ። ከዚያም ከፊት-ለፊቱ አንድ ጠርሙስ ቮድካ ያስቀምጥና ጀርባውን ለግድግዳው ሰጥቶ ዐይኖቹን በመጨፈን . . . በተሳሰረ አፉ ዘፈን ለመዝፈን ያላዝናል. . .'[25]

#### በጭውውት (ባህርይን ለማሳየት የቀረበ ድርግ)

"...ልጁን ፖቬልን የዐሥራ አራት ዓመት ልጅ ሆኖ ሳለ ፥ የጭንቅላቱን ፀጉር ጨምድዶ በመያዝ ፥ ሊያንጠለጥለው ፈለገ ። ፖቬል አንድ ትልቅ መዶሻ አፈፍ በማድረግ እነሣና. . .

"'እንዳትነካኝ !' አለው ።

[25] ከላይ ከተጠቀሰው ፥ ገፅ 27—28 ።

ዘ…'ምን አልክ ?' አለ አባትዬው ፣ ደመና ከሰማይ ሁኖ እንድን ትልቅ ነጭ ዛፍ ወደታች እያንዣበበ እንደሚ ንጎባለል ሁሉ ፣ ረዥሙን እና ሸንቃጣውን ልጁን ወደ ታች እየተመለከተ ።

'የሚበቃኝን ያህል ከዚህ በፊት ተደብድቤአለሁ ። ከእንግዲህ ወዲያ አልደበደብም' አለ ፖቤል ። እናም መደሻውን ከወዲያ-ወዲህ ያወዛውዝ ጀመር ።

አባትየው ልጁን ገልመጥ ብሎ እያየ በፀጉር የተወ ረሩ እጆቹን ወደ ጀርባው በማድረግ ፣

'እሺ ይሁን . . .' አለ ፈገግ እንደ ማለት ብሎ ። ከዚ ያም በረዥሙ ተነፈሰ እና የሚከተለውን ተናገረ ፣ ' ቆይ ግዴለም አንተ ! ውሻ . . .'

"ከዚያም ጥቂት ቆየት ብሎ ወደ ሚስቱ ዞር አለና 'ከእንግዲህ . . . ለቤት ወጪ. . . እንዳትጠይቂኝ ። ከአ ሁን በኋላ የሚቀልብሽ ፖቤል ነው ።'

'አንተ ደግሞ የምትቀበለውን ደሞዝ በሙሉ ልትጠ ጣበት ነዋ ?' በማለት ሚስቱ ስትፈራ-ስትቸር በቀስታ መለሰችለት ።

'ይኼ አንቺን የሚያገባሽ. . . አይደለም ! አንቺ ውሻ ! ከፈለገኝ በላይሽ ላይ ውሽማ መወሸምም እችላለሁኝ'አላት።

"ውሽማ አልወሸመም ። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ እስከ ሞተ እስከ ሁለት ዓመት ጊዜ ድረስ ግን ልጁ የትደረሰ ብሎ እንኳን ዞር ብሎም ያላየው ከመሆኑም በስተቀር ፈጽሞ አላነጋገረውምም ነበር…"[26]

ከዚህ በሰፊው ከተጠቀሰ ፅሁፍ እንደምንረዳው የባለታሪኩ ውለኛ ባህርያት ፣ ስራ ወዳድነት ፣ ሀይለኝነት ፣ ቂመኝነት እምብዛም የማያቀርብ ሩህሩህነትና አስፈላጊ ሆኖ

[26] ከላይ ከተጠቀሰው ፣ ገፅ 27 ።



ራስን የመቆጣጠርና የመግታት ባህሪ ናቸው ። እነ እንግዲህ እንደ ሁኔታው እየተሻሻሉ ወይም እየተበላሹ አንዳንዴም በሌሎች እየተተኩ ይቀርባሉ ማለት ነው — በልቦለድ ውስጥ ። ለምሳሌ ግልፍተኝነቱ ፣ (ሳህኖቹን በመወርወር የሚገለፀው ጊዜያዊ አባዜ) ልጁ መዶሻ ሲያነሳ ወይም በሚስቱ ላይ ውሽማ እይዛለሁ የማለት ፉከራውን ሲያስብበት እንደ ገታ ሁሉ ፣ እየቀረ የሚሄድ ጊዜያዊ ጠባይ ሊሆን ይችላል ። እንደ የማላዘን ዜማው ወይም ግልፍተ ኛነቱ በሌሎች ሁነታዎችም ጊዜ በመከሰት ውለኛ ባህርይ እየሆነ ሊያድግም ይችላል ።

**በድርጊያዎች የሚቀርብ — የተራኪ ድብቅ አስተያ የት በጥቂቱ ያለበት ወይም ጭራሹንም የሌለበት**

በዚህ አቀራረብ ፣ ተራኪዉ ስለ ድርጊያዉ በሰ ዋራ መንገድ ትችት እና ወይም ማጠቃለያ በጥ ቂቱ ያቀርባል ወይም ጭራሹንም አያቀርብም ፤ አንባቢዉ ከድርጊያዉ የባለታሪኩን ውለኛ ባህ ርያት ይቃርማል ብሎ ይገምታል ። የዚህን አይነት የባለታሪኮች አቀራረብ በይበልጥ የተውኔት ተዋ ንያን አቀራረብ ሲሆን ፣ ዘመናዊ የልቦለድ ድርሰትም ሌሎቹን ዘዴዎች በመተው በዚህኛው መጠቀምን አዘውትሯል ። ዘዴው በይበልጥ ለስውር ተራኪ ነው የሚያገለግለው ።

እስረጅ ፣
'ክፍቅረሃት ነበር?'
'አዎ ፣ በመጠኑ ፣ ደህና ነገር ነች ።'
'ሌላዋስ ?'
'ሌላዋ ፓሪስ ሄዳ ነበር. . . በነገራችን ላይ ፣ ወዳጅህ ምንም ሳታደርግህ ለማቋረጥ ትችላለህ. . . እምልህ ፣

እንተ ሲበቃሁ...'

'እዎ እችለላሁ ፡ በሚገባ ።'
'እንዴት ታደርጋለህ?'
'እተዋታለሁ!'
'እኮ እንዴት?'
'እላያትማ በቃ!'
'እቧ ልታይህስ የመጣች እንደሁ?'
'ቤት የለሁም ።'
'እንደገና ብትመጣስ?'
'እሞኛል እላታለሁ ።'
'ላስታምህ ብትልስ?'
'አንድ አጉል ነገር አድርጋታለሁ ።'
'ችላው ብትቀመጥስ?'
'እቧ እኔጋ በምትመጣበት ቀን ጠብቆ እንዲይዛት
ለባሏ ደብዳቤ እፅፍባታለሁ — በድብቅ ።'[27]

## 7.3.4 ባለታሪክና አቋሙ

በልቦለድ ውስጥ የሚቀርቡ ባለታሪኮች ሁለት
አቋም አላቸው ። አቋማቸውም ልውጤና አይለ
ወጤ በመባል ይታወቃል ። አይለወጤ ባለ
ታሪክ የሚባለው በትረካው ሂደት ወቅት ምንም
አይነት ለውጥ የማያሳየው ባለታሪክ ነው ፤
ነገሮች ይደርሱበታል ፤ ሁነቶች ይካሄዱበታል ፤
ራሱም ያካሂዳል ፤ በራሱ ውስጥ ግን ምንም አይ
ነት ለውጥ አያሳይም ። እስከ መጨረሻው እንደ
ነበረ የሚቆይ፣እንዳስቀመጡት የሚገኝ ነው ። የድ
ርጊያው ሂደት ያው መጀመሪያ ላይ የነበረውን

[27] ጊ. ዶ. ሞፓሳ ፡ 'ጣምራ መርፌ' (አሜሪካ ፡ 1957) ፡ ገፅ 416 ።



አቋሙን ቀስበቀስ ላንባቢው ለመከሰት ነው እንጂ ፡
በድርጊያው አማካይነት የሚኖረውን ለውጥ ለማ
ሳየት አይደለም ። አንዳንዴ አንባቢው ስለ አይለ
ወጤ ባለታሪክ አቋም ቀስ በቀስ እየተገለፀለት
በሚሄድበት ወቅት ፡ ስለ ባለታሪኩ የሚኖረው አስ
ተሳሰብ እየተለወጠ በመሄዱ ራሱ ባለታሪኩም
የተለወጠ ሊመስለው ይችላል ።

ልውጤ ባለታሪክ የሚባለው ደግሞ በትረካው
ወቅት በነገሮችና በሁነቶች ሂደት ምክንያት ውስ
ጣዊ ለውጥና ብሎም የአቋም ለውጥ የሚያሳየው
ባለታሪክ ነው ። የዚህ አይነቱ አቀራረብ ዋና አላ
ማም ድርጊያዎች በባለታሪኩ ላይ የሚያመጡትን
ለውጥ ማሳየት ነው ። እውቅ ልቦለዶችና ተውኔቶች
ልውጤ ባለታሪኮች ያሏቸው ሲሆን አጫጭር ልቦ
ለዶች ግን በአብዛኛው በአይለወጤ ባለታሪኮች
ነው የሚጠቀሙት ።

## 5 የባለታሪክ ጥምርነት

ባለታሪክ ፡ የአንድ የብቸኛ ሰው ወይም የብዙ
ብቸኛ ሰዎች ባህርያት የተሰባሰቡበት እንደ መሆኑ
በስም ተወስኖ በመቅረቡ እውቅና ብቸኛ ባለታሪክ
ሲሆን ፡ ከዚያም ከዚያም የተሰባሰቡ ባህርያትን ያቀ
ፈ በመሆኑ ደግሞ ፡ ያንንም ያን የመምሰል ባህሪ ስለ
ሚያገኝ ሁለንታዊነት አለው። ከዚህም የተነሳ አን
ድ ባለታሪክ ከአካባቢውና ከራሱ ባህል ውጪ
ታዊነትና ተወዳጅነት እንዲኖረው የብዙ ባህል
ውጤት የሆኑ ሰዎችን የሚያገናኝ ባህሪ ሊኖረው
ያሻል — ማለትም የብቸኛነትና የሁለንታዊነት
ጥምር መሆን ይኖርበታል ።

## 7.3.6 አጠቃላይ ማስረጃዎች

### ለልውጤነት የተመቻቹ ባለታሪኮች

"ለብ ያለ ሙቀት እየናን ሞልቶታል ። ለምለም ነፋስ አደይ አበባዎችን እያበሰ አልፎ አልፎ ይነፍሳል ። እንዲት ኩራት የያዛት ወጣት ባለመከደኛ የፊት መስተዋቷን ከፊት አድርጋ ፊቷን እየተመለካከተች አልጋዋ ላይ ቁጭ ብላለች ። በፊትለፊቷ መስኮት የሚገባውን አየር አልፎ አልፎ እየማገች ። አመተ ምህረቱ 1975 ፣ ወሩ መስከረም ፣ እለተ ቀኑ የመስቀል ማግስት ፣ ወደ ምሽቱ ገደማ ነው ።

"ወጣቷ ሮማን ትባላለች። ኩራት የያዛት በራሷ ሰውነት ነው ። አይኗ ያምራታል ። ሽፋሏ ያምራታል ። አፍንጫዋ ያምራታል ። ቀለሟ ያምራታል... እንዲያ እንዲያም እያለ እረፍት የሚነሳና የሚነሰነስ ነገር በሰውነቷ እየናኘ ልቧን ናድ ናድ ያደርገዋል ፤ እያረፈ ፣ እያረፈ ። ምን ሊያስከትል ይሆን እንዲያ ያረጋት ? ውቃቢዋን እንዲያ እንዲያ ያሰኘው ?

"ስሟ ሮማን ነው... ሮማን ፣ ሮማን አዎ ፣ ስሟም ያምራታል ። አንዳንዴ ትኩስ ፍሬ የሆነ ስሜት ፣ አንዳንዴ ፈረንጅ የሆነ ስሜት ያመጣባታል ፣ ከንፋሱ ጋር እያዋዋደ ። ሮማን ሮማን . . . ሮሚን ጨርቆሴ ግን እስከዚህ አያምራትም ። ያባቷ ስም የሚጨንፍ ስሜት ነው የሚነዛባት ፤ የታፈነ ፣ የታመቀ ስሜት — ሲጠሩት አይጥማትም ። ባለመከደኛ መስተዋቷን እየተመለካከተች ተቀምጣለች ሮማን ። የፊቷን ቀለም በይበልጥ የሚያደምቀውን ምቹ ብርሃን በመስተዋቷ ለመጥለፍ እየሞከከረች ። ምንኛ የታደለ ፣ ፈጣሪው የባረከው ይሆን እሷን የሚደገኘው ? ኩራት ይዟታል. . .

'እኔ ለራሴ ኩራት ይዘኛል

ሞሀመድ አሊ ልከውብኛል. . .' እያሰኘ ።

"ማንባሯን ሰብስብ ፊታ ፣ ሽፋሽፍቿን ከፍ ዝቅ ፣ ከንፈሯን ያዝ ለቀቅ ፣ ፊቷን ፈገግ ኮርተም ፣ ጨንቆር ገርመም እያደረገች ተመለካከተችው ፣ ቡሬ ፊቷን — በየሲኒማው እንዳየችው ። የዋዛ ሰው አይደለችም ፤ ወንድን ለማጥመድ ያላትን ያራዳ አይነት ውበት አደነቀች ። የማር ወለላ ወተት ከሚመስለው የፊቷ ቀለም ወጥጥ — ብቅ ጥልቅ ሲል ሲብረቀረቅ ፣ ጊዜውን ሲጠብቅ እየተመለከተች — በአስራ ስምንት አመቷ ። የመሸተኛው ቻቻታ ፣ የሙዚቃውና ያዝማሪው ድንፋታ ፣ ሳቁ ፣ ስድቡ ፣ ጩኸቱ . . . ሁሉም በመስኮቷ መጉረፍ ጀምሯል — የመናጠጥ አይነት ስሜት በሁለንተናዋ እየነዛ — የአርብ ምሽት ውካታ ። መስተዋቱን ገርምማው በመነሳት ወደ መስኮቱ ተጠጋች ። ውጭ ውጭውን እያየች ብዙ ታገለች ፣ ልሂድ ልቅር እያለች — እንደኛዋ "ፓርቲ" ምን ይጠብቃት ይሆን ? ?

"እንቅልፏን ጠግባ የተነሳች አይነት ፊቷን ታባብሳለች ፣ እንደ ቡሬ ድመት ። በፊቱ ውስጥ የሚንቀለቀለው የደረሰ ስሜት ሲፈራ ሲቸር ይታያል ፤ አልፎ አልፎ ብርቅ ፍንጥቅ እያለ የዝንኪላ ፍሬ ቀለም በገቡት አይኖቿ እያለፈ ሲውገነገን ። የቀይ ዳማ ገፅታዋን ሲያበራው ሲያጠፋው ። ከንፈሮቿ ደረጃ ደረጃ የወጣለት ደማቅ ጥቁር ተቀብተዋል ፤ ልክ በጊዜው ፋሽን ። ሽፋሽፍቶቿ ተነቅለው በቀጭኑ ተረስሰዋል ፤ በጊዜው ፋሽን ። እንደዚሁም በጊ

ዜው ፋሽን ዘመናዊ ቅንድቦች ስክታለች ፤ የቂንዳቸው
ሙራ ያይናቿን ውጋጋን እንዲናኝ አይነት ። በማያዊ
ከፊይ ጉርድ ለብሳለች በሁለት ጉብታዎች ላይ ክተናደ
ነጭ የሀር ሸሚዝ ጋር ፤ ወገቧን በቀይ ቀበቶ ሸብ አድርጋ ።
በመዘዞ አንገቷ ላይ ፥ አጕጠጕጤ መሳይ ትልቅ ዛጉል
በወርቅ ሀብል ተሸብቧል ። ረጅምና ጥቁር ፀጉሯ በቀጭን
በቀጭን ተጉንጉና ጫፍጫፉ በትናንሽ ዛጉል ተቆልፏል ።
ስትንቀሳቀስ ፊቷን ዙሪያውን እያበሰ እዋት እዋት እያለ
ድብብቅ እያጫወተ ። ታዲያ ፀጉሯም ያኮራታል ፤ ሆን
ብላ የምታደርገው አይነት ወደ ቀኝ ወደ ግራ በዞረች ቁጥር
አብሮአብሮ እየሆነ ሲያወካ እየሰማች ።

"በዚህ ሁሉ ማህል ሴት ሆና መፈጠሯም ሳያኮራት
አልቀረም ፥ ስሜቱ ይኸ መሆኑን ባታጤነውም ። 'እንዳ
ንዴ ምንም ሳላገኝ የሚያስፈነጥዝ ስሜት በሁለመናዬ
ይሞላል ፥ አይሰሩ ስራ ያሰራኛል ፥ ነካ ሲያረገኝ ነው መሰ
ለኝ' ትላታለች ለጓደኛዋ ፥ በቅርቡ ። በየእለቱ በጧት
ተነስታ ቂጣ ጠፍጥፋ ፥ በሰሊጥ ወቅጣ ቁርስ ማዘጋጀቱ ፥
ታናናሾቿን ቀስቅሳ ፥ የሴቶቹን ፀጉር ካበጃጀች በኋላ
ቁርሳቸውን ማብላቱ ፥ እቃቸውን ማበጃጀቱ ፥ ወደ ትም
ህርት ቤቱ መሮጡ . . . አንድ የተለየ የደስታ ስሜት ይሰ
ጣታል ፥ የእንቅስቃሴ ፥ የመስፈፍ ፥ የመክነፍ . . . የመ
ጦፍ ። ምንም ሁኔታ የሚያስጐነብሳት አይመስላትም ።
ምን ቢሆን ይሆን እንዲያ ያረጋት ? እንዲያ እሚሰማት ?
'ኦ ምንም አይደል' ብላታለች ጓደኛዋም በሀሳብ በተዋጠ
አንደበት ፥ 'እንዲያው ስላላየሽው ነው ማንኛውንም ።'

"ያርብ ማታ ሙዚቃ ከመቸውም የበለጠ ያሽቃብ
ጣል ፤ ልቧም በዚያው ልክ መምታት ጀምሯል ። አሁንም
አልወሰነችም — 'ልሂድ ልቅር' ትታገላለች ። ራቁቱን
የነበረውን ክንዷን በአንድ ጣቷ ረጅም ጥፍር አከክ



አከክ እያደረገች ፥ ልብ ብለው በማያደርጉት አይነት ያደባ
ብስ እንቅስቃሴ. . . ታስባለች ፥ ታስባለች ፤ ያ የመስከረም
ምሽት ብርዝ አየር የፍልውሃ ባኞ ስሜት በሁለመናዋ
እየቀሰቀሰ..."

"የያዘው አባዜ ያልታወቀለት ነበር ተፈራ ፥ በልጅ
ነቱ ። የጅላጅልነትና የእንፉዝነት አዝማሚያም ታይቶ
በታል ፥ አስራሁለት አመት እስኪሆነው ። ልጆች ሲሰ
ድቡትና ሲያሾፉበት እንኳ እሱን ያሾፉብትና የሰደቡት
መሆኑ የሚገባው ቆይታ ቆይቶ ነበር ። ያም ቢሆን የሚታወ
ቀው አፊቱ ላይ ቦግ ይልና ለብዙ ጊዜ ተለጥፎ በሚቆይ
ፈገግታው ነበር ። በዚያ ላይ በጥፊም ሆነ በርግጫ ፥ በግ
ፊያም ሆነ በጡጫ ለሚቀምሰው አፀፋውን ለመመለስ
የሚሞክረው እንዲሁ ቆይቶ ቆይቶ ነበር ፤ በጊዜው ያልተሰ
ማው አይነት ። በትምህርቱም ቢሆን ፊደል ተራራዉ ሆኖ
ቆይቷል ፤ አምስት አመትም እንደሁ ነበር የፈጀበት ፊደል
ለመቁጠር ። 'ያምስት አመት አርበኛ' ይሉት ነበር ልጆቹ
ከዚሁ የተነሳ ። በቁመናውም እንደ እድሜው አልነበረም
አስተዳደጉ ፥ የአስር አመት ልጅ ቁመና አልነበረውም ፥
በአስራ ሁለት ። ከዚያ በድስተኛ ክፍል እንደደረሰ ፥ አስራ
ሶስት አመቱ ላይ ድንገት ማደግ ጀመረ ፤ አይሰሩ ስራ የሚ
ያሰራው ፥ ያበጠው ይፈንዳ የሚል አይነት ሆነ ፥ የያዘውም
አባዜ ። አንድ ጊዜ የማርያምን ፅዋ ይዘው የሚሄዱ ሴቶች
አጋጥመውት ፥ እንደሚሳለም ሰው መስቀወርቅ ወደ ተሸከ
መቸው ልጃገረድ ጠጋ ብሎ ኮቱን ከነጠላዋ ጋር ከቋጠረ
በኋላ ፥ አልፈታም ብሎ እቤታቸው ድረስ በመከተል ፥
የቡራኬውን ጉርማጅ ይዞ ሲወጣ የታየው ተፈራ ነው ፤
ስለት አለብኝ በማለት ብቻ ። አንድ ቀንም እንዲሁ እሱና
ጓደኞቹ ሽምብራ እሸት ተሸክሞ ከሚሄድ ነጋዴ ትንሽ
ትንሽ ሲቦጫጩቁ ፖሊስ ደርሶ ሲያባርራቸው ተፈራ ነው

እየየውን በረጅሙ እያቀለጠ ፥ እጁን እያማታና እያወራጨ ሰይጣን የሰፈረበት አይነት ሲሮጥ መንገደኛውን ሁሉ ሲያትራምስ የታየው ። በሱ ቤት ፖሊስ በለቀቀባቸው ድንጋጤ ማሸፉ ነው ። በሱቤት ለፖሊስ እንዴት ይሮጣል ለማለት መቀለዱ ነው ። እንዲህ እንዲህ ያለው አድራጐቱ ታዲያ ለማን ይግባ ? አንድ ቀን ደግሞስ ፥ እሰው መኪና አጠገብ ሳንቲም ወድቆበት ሲፈላልግ ፥ በየጊዜው የመኪናው እቃ እየተሰረቀ የተበሳጨና ሞቅታ የተጫጫነው የመኪና ባለቤት ድንገት ደርሶ አፈር ባስጋጠው ጊዜ ፥ ደም በደም ሆኖ እጉድባ ውስጥ ተዘርሮ ሲገኝ ፥ ምን አገኘህ ሲባል የመለሰው 'አሳንባሬ ተፍቶኝ ነው' እና ምን ይበሉ ሰዎቹስ ፥ በእርግጥ ትንሽ ለየት ያለ ነገር ነበረበት ። እብደትም ባይሉት ። አለ አይደለም ፥ ተፈራ እንደ ተራ ሰው ባንዴ ታይቶ የሚታለፍ አልነበረም ፤ እንዲህ ነው ተብሎ የሚተው ወይም የሚረሳ አይነት ። ማለት ከማን አለብኝነቱና ከወመኔነቱ በስተቀር — ከፈሱ የተጣላ ነገር ፥ ደሞኮ ደስታ ባገኘበት . . . አንዳንዴ የሚዘጋው ነገር ያዝበታል ። ፊቱን ምርጊት አስመስሎ ለብዙ ቀናት ይቆያል ፤ ፈገግታ የሚባል ሳይታይበት ። እዎ ፥ እጅግ አስቸጋሪ ነበር እስራ ስምንት አመት እስኪሆነው…”

## 7.4 የትረካ ሜዳ (ዳጀን)

የትረካ ሜዳ ስነ መሬቱን ፥ የባለታሪኮቹን ስራ አይነትና የእለት በእለት አኗኗር ጠባያቸውን ፥ ትረካው የተከናወነበትን ዘመንና ወቅት ፥ አጠቃላይ ርእዮተአለማዊ አካባቢያቸውን እና የመሳሰሉትን ፥ ( ገፅ 269 ተመልከት ። )እንደሚይዝ እና ለታሪኩ ማጠናከሪያና ማጉሊያነት እንደሚውል ጠቁመናል ።



### 7.4.1 የዳጀን አጠቃቀም

የፅሁፍ ዳጀን በሚመረጥበት ወቅት ፥ በዝርዝር አመራረጡ ረገድ ከፍተኛ ጥንቃቄ ያስፈልጋል ፤ ተራኪዉ ማቅረብ ያለበትን አንባቢዉ ከልምዱ ከሚሞላው በመለየት ። ለምሳሌ ፥ በማንኛውም ዳጀን በሚያስፈልግበት ትረካ እንደ መንገደኞች ፥ መኪናዎች ፥ ተክሎች ፥ መንገዶች ፥ ሱቆች ፥ ገበያዎች እና የመሳሰሉትን አንባቢዉ ከሀሳቡ እየሞላ ሊያነብ ይችላል ፤ እየሞላሁ ሳነብ ብሎ ሳይሆን ፥ እንደ ልማድ ሆኖበት — ማለትም ሳይታወቀው አእምሮው እየሞላለት ። ሌሎችን ግን ፥ ማለትም ከትረካው ሂደት ጋር ቀጥታ ግንኙነት ያላቸውንና ታሪኩን ለማጉላት፥ ለማኳሰስ ወይንም ስሜት ለመፈንጠቅ የሚውሉትን ተራኪዉ ለሚፈልገው ግብ እንደሚያመቹ እያደረገ ማዘጋጀትና ማቅረብ ይኖርበታል ። ከዚህ ቀጥሎ ዋናዎቹን የዳጀን ማቅረቢያ ስልቶች ከአገልግሎታቸው አንፃር እንመለከታለን ።

### 7.4.2 የዳጀን ማቅረቢያ ስልቶች

#### (ሀ) አዳራሽ (የሚያዳርስ) ዳጀን

አዳራሽ ዳጀን ፥ በትረካው ውስጥ አልፎ አልፎ በመገኘት የታሪኩ ሀረግ እስኪቀጥል ፋታ መስጫ ዳጀን ነው ። ከታሪኩ ሁነትና ድርጊያ ጋር ግንኙነት የለውም ። ዳጀኑ ኖረም አልኖረ ልዩነት አያመጣም ። የባለታሪኮቹን ድርጊያ ፥ በተግባርም ሆነ በስሜት አያጫፍርም ። ተራኪዉም ቢሆን የታሪኩን ሂደት ለመተቸት ፥ ለመተርጐምም ሆነ ለማጠቃለል አይጠቀምበትም ። ባጠቃላይ የዚህን

አይነት ደጀን ራሱ ደጀኑ ለሚኖረው ስነ ዕሁፋዊ ውበት ካልሆነ በስተቀር ለልቦለዱ ፋይዳ የለውም ። እንዲያውም በግልፅ ያፈጠጠ ደጀን መሰናክልነቱ ስለሚታይ አንባቢዉ እንዲዘለው ይገደዳል ። ሆኖም ፣ አልፎ አልፎ አንዳንድ ደራሲያን ፣ (1) በልቦለዱ ውስጥ ያለውን የታሪክ ጊዜ በማራዘም አንባቢዉ በንባብ የሚወስድበትን ጊዜ ፣ በታሪኩ ጊዜ እንዳለፈ ረጅም ዘመን መስሎ እንዲታየው ለማድረጊያ ይጠቀሙበታል። (2) አስቃቂ ወይም አሳዛኝ ለሆነ ትርኢት ተግታ መስጫ በማድረግ ይጠቀሙበታል — አንባቢው የተቀሰቀሰበት ስሜት እየበረደለት እንዲሄድና የመንፈስ እርጋታውም እንዲመለስለት ለማድረጊያ ። ለማንኛውም ለራሱ መስተዋታዊ ወይም ገላጭ ይዘት ተብሎ ብቻ የሚቀርብ ደጀን በዛሬው ዘመን እየቀረ ሄዷል ።

(ማስረጃዎችን ገፅ 148 እና ከ186-187 ተመልከት ።)

## (ለ) መነሻ ደጀን

የዚህ አይነቱ ደጀን ፣ ለታሪኩ መነሻ ፣ ለድርጊያው አስፈላጊ የሆኑ መሰረታዊ ነገሮችንና ፍላጎቶችን የሚያሟላና በአጠቃላይ ስሜት ፈንጣቂነት የሌለው መግለጫ ነው። የዚህ አይነቱ ደጀን፣ እጥር ምጥን ባለ መንገድ ባለታሪኩን ፣ ትረካው የሚካሄድበትን ስፍራ ፣ የትረካውን ዘመንና ወቅት ፣ ለትረካው የሚያስፈልጉ መሳሪያዎችን ፣ አለባበሶችን እና የመሳሰሉትን ይጠቁማል። በዘመናዊ ልቦለድ ውስጥ በተለይ ስውር ተራኪ ይጠቀምበታል ።

(ከገፅ 128-130 ፣ 147 ፣ 149 እና 151 ተመልከት ።)



## (መ) ስሜት ፈንጣቂ ደጀን

ስሜት ፈንጣቂ ደጀን ሊገለፅ ለተፈለገው ሁነት ወይም ድርጊያ የሚስማማ ደጀን ነው ። ለምሳሌ የመረረ ጠብ ለሚካሄድበት ድርጊያ ፣ መብረቅና ዶፍ የከፋበት ዝናብ በደጀንነት ይቀርባል ። ሁለት ፍቅረኞች ፍቅራቸውን በሚገላለፁበት ቦታ ፣ የአታክልት ስፍራና ወፎች የሚያፏጩበት፣ ኩልል ያለ ውሃ የሚፈስበት አካባቢ በደጀንነት ይመረጣል ። ሰው ማለቂንና ውድማነትን ለማሳየት፣ ሀይለኛ ነፋስ ስራስሩን እያንገዋለለ የሚነዳበት አቧራማ ደጀን ይመረጣል። ሆኖም ማንኛውም ምርጥ ስሜት ፈንጣቂ ደጀን ቢሆን፣ ከሁለት አኳያ መታየት ይኖርበታል። (1) ከባለታሪኩ አኳያ (2) ከአንባቢዎቹ አኳያ ።

### (1) ከባለታሪኩ አኳያ

በዚህ ረገድ፣ ተራኪዉ ደጀኑን ከባለታሪኩ ግምባር ሊመለከተው ይገባል ። ከባለታሪኩ ግምባር ከተመለከተው ፣ ባለታሪኩ ደጀኑ የሚፈነጥቀው ስሜት ተሰምቷቸዋል ማለት ነው። እለዚያ ስሜታማ ሁኔታን በስሜታማ ደጀን ውስጥ ማቅረቡ አንባቢዉ ደጀኑ የሚፈጥርበትን ስሜት የባለታሪኩ አድርጎ እንዲቀበል መከጀል ነው — ማለትም ስሜቱ የመነጨው ከእውናዊዉ አለም ከራሱ ነው እንጂ ከድርሰቱ ስለማይሆን የድርሰቱን ረብ ይቀንሰዋል ።

### (2) ከአንባቢዎች አኳያ

ከአንባቢዎች አኳያ የሚቀርብ ደጀን ፣ ማለትም ደጀኑ ከትረካው ጋር የተዛመደው ለአንባቢዉ ተመሳሳይ (ትይዩ) ስሜት የሚፈጥር ሁኔታ ከመሆኑ ላይ

ብቻ የሆነና ለባለታሪኮቹ ኖረም አልኖረ ልዩነት የማያመጣ ከሆነ ደግሞ ፣ ስሜት ፈንጠቀም አልፈ ንጠቀ በአንድ ቁጥር ከተመለከተው ደጀን ተለይቶ የሚታይ ስላልሆነ ፣ በዚያ የተገለፀው ውሳኔ ለዚህም ይፀናል ። የልቦለዱን አለም በእውናዊዉ አለም ልምዱና እውቀቱ የሚገነዘበው አንባቢ ፣ በህይወት ያለፈበት የባህል ተፅእኖ የቀሰቀሰበት ስሜት ቢኖር ለቀረበው ደጀን ይኖረዋል ተብሎ ከተመገተው ስሜት ውጪ ሊሆንም ስለሚችል ፣ ቅስቀሳው ለትረካው ጭራሹንም የማይስማማ ይሆናል ። ለምሳሌ ፣ ዝናብ የልምላሜ ፣ ያዲስ ህይወት ፣ የደስታ ወኪይ ነው በማለት ተቀብሎ የኖረን አንባቢ ሁለት ፍቅረኞች ለመጣላታቸው መተንበያ ወይም አጫፋሪ አድርጎ ማቅረብ (ከአንባቢው አኳያ) ትርጉም የለውም ። የቀረበው ከባለታሪኮቹ አኳያ ከሆነ ግን ፣ ይኸው አንባቢ እምብዛም ሳያስበው በፀሳቡ 'የፈጠራ ሰዎች ነገር' በማለት ብቻ ሊያልፈው ይችላል — የልቦለድ አለም ቅእይንት መሆኑን በማጤን ። በተጨማሪም በልቦለድ አለም ፋይዳ ያላቸው የሚመስሉ ደጀኖች በእውናዊዉ አለም ሳይጤኑ የሚታለፉ አይነት ሊሆኑ እንደሚችሉም ማስታወስ ይበጃል ።

## ሰ) ፌዛዊ (ልግጫዊ) ደጀን

ፌዛዊ ደጀን ፣ በባለታሪኮቹ ስሜት ፣ ሀሳብና ድርጊያ ላይ ለማሾፍ ፣ ለመቀለድ ፣ ለማሳቅ ፣ ለማስደንገጥ ፣ እይታን ለማቃወስ ፣ አዝማሚያን ለመግታትና ለመሳሰለው የሚቀርብ ነው ። አንዳንዴ ተፈጥሮ በታሪክ ስታሾፍ ፣ ታሪክ በማህበራዊ እኗኗር ሲያስቅና ሲያሳዝን ፣ ማህበራዊ ኑሮ በተፈጥሮ ሲያፌዝ ፣ ተፈጥሮ ወይም ታሪክ ወይም ማህበረሰብ ወይም ሁሉም በሰው ሰውነት ሲሳለቁ ይገለፅበታል ። አቀራረቡ ፣ በአብዛኛው ከተራኪዉ አኳያ አንባቢዉ እንዲያጤነው ሆኖ ሲሆን ፣ ባለታሪኮቹ ሊገነዘቡትም ሳይገነዘቡትም ይችላሉ — ለምሳሌ የኢትዮጵያን ማህበራዊ ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ጉስቁልና ተቀን አድርጎ ፣ ሀይለ ስላሴ ውሾቻቸውን ሲያንቆሻብሉ ፣ የሻምፓኝ ብርጭቆቸውን ሲያጋጩ ፣ የሶስት ሺ ዘመን የኢትዮጵያን ስልጣኔ ለአለም ህዝብ ለማስተዋወቅ ሲንሸረሸሩ ፣ እንደ ማሳየት ያለ ነው ። ወይም የ66 አመቱ ምህረቱን ታሪካዊና አብዮታዊ ሀብት ለሰፊው፣መሬት ላራሹ እንቅስቃሴ ተገን አድርጎ ፣ አንድ መስፍን ፣ ከበርቴ ወይም የባላባት ቤተሰብ ሳይሰራ ያገኘውን፣ ሲያርስ ያካበተውን ሀብት ለማሸሽ የመጨረሻ ሞት ሽረቱን ሲታገል እንደ መግለፅ ነው ። ወይም፣ አዲስ ህይወት ለመጀመር በፍቅር ተገናኝተው በመዝናኛ አደባባይ ውስጥ በሚናፈሱ ፍቅረኞች ደጀንነት፣ ትዳር አስጠልቶት የሚወናጨፍንና የወጣትም ድካም መጨረሻው የሱኑ አይነት እንደሚሆን አጨልሞ የሚያይን አዛውንት እንደ መሳል ነው ።

## (ረ) አእምሯዊና ልቦናዊ ደጀን

የባለታሪኮችን ውስጣዊ የአስተዳደግ ፣ የእውቀት ፣ የልምድ ፣ የሞራል ፣ የርእዮተአለማዊ አመለካከትና አቋም ለውጫዊ ድርጊያቸው ፣ ንግግራቸውና የሁነቶች ሂደት ተገን አድርጎ ማቅረብ ነው ። በትዝታና በትውስታ መልክ ነው አቀራረቡ። ትዝታን የጊዜ ገደብ ስለማይወስነው ብዙ አመታትን በትንሽ ገፆች ለማጠቃለል ይቻላል ።

## (ሸ) እውነታ ፈንጣቂ ደጀን

የዚህ አይነቱ ደጀን በተለይ የሚሰራበት ፣ ባለታሪኩቹ ሀሳባዊነት በሚያጠቃው ህይወትን መተርጎሚያ ሲዘፈቁና እውናዊዉን አለም እየለቀቁ መሄዳቸው ሲታይ ነው ። የደጀኑን መኖርና አለመኖር ባለታሪኩቹ ላያጤኑት ይችላሉ ። ለአንባቢው ግን የባለታሪኩቹን ሀሳብም ሆነ ድርጊያ መጠቆሚያ ነው ። ደጀን ሆኖ የሚቀርበው ከታሪኩ ጋር የተገናኘ ትርጉም ይኖረዋል ማለትም አይደለም ፤ ብዙ ጊዜ ተጨባጭ ነገሮችን በመዘርዘር 'እረ እባክህ በሀሳብ ብቻ ከምትንደረደርበት አለም ተመለስ' ለማለት ብቻ የሚቆም ነው ። ለምሳሌ ፣ አለገዳዲ ወንዝ አጠገብ እግሩን ታጥቦ ጋደም ያለ ባለታሪክ ፣ በሀሳቡ 'ውትድርና ተቀጥሬ ፣ ትምህርት ቤት ገብቼ ፣ በብዙ ጦርነቶች ድል አድርጌ ፣ በጥቂት አመታት ውስጥ የአፍሪካ ታዋቂ ጀግና በመሆን አፍሪካን ባጠቃላይ እንድመራ ሲጠይቁኝ. . .' እያለ ሲያስብ ፣ ተራኪው 'ሁለት የሸራ ጫማዎች ፣ ታጥቦ የተሰጣ የተቀዳደደ ካልሲ ፣ በእግሩ ላይ መንቀሳቀስ የጀመረ ትል' በማለት አጠገቡ ያለውን ይዘረዝርልናል ። ይህ ዝርዝር ምናልባት ፈዛዛም ሊመስል ይቻላል ። ነገር ግን 'ወንዝ ፣ ድንጋይ ፣ ባህርዛፍ ፣ ገላውን የሚታጠብ ሰው' በሚሉትም ሊተካ ይችላል — ጨርሶ ከታሪኩ ጋር ምንም አይነት ግንኙነት በሌላቸው ነገሮች ። የተራኪዉ ፍላጎት ደጀኑ ከባለታሪኩም ሆነ ከራሱ አዲያ ትርጉም እንዲኖረው ሳይሆን ፣ ባለታሪኩ ከእውነታ አለም እየወጣ መሆኑን ለአንባቢው ለመጠቆም ነው ።



## 7.5 ቅርፅ

ቅርፅ የማንኛውም አይነት ክየና መባያና ተባይ መቀናበርና መዋደድ ነው ። ቅርፅ ፣ መባያው ለተባዩ ስምሙ ሆኖ መገኘት ነው ። ቅርፅ ፣ የጥበቡ አካል አባሎች ተመጣጥነውና ተዋውደው ከመገኘታቸው የተነሳ ፣ 'እዚህ ላይ ቢጨመር ፣ እዚህ ላይ ቢቀነስ' ያለማሰኘታቸው ነው ። ቅርፅ የማይነጣጠል ውህደት ነው ፤ የትልም ፣ የሀሳብ እና/ወይም ስሜት እና የምጠና ። ቅርፁ የተዋጣ ክየና ሁሉ በሀሳብ ያንደረድራል ፤ ስሜትን ይቀሰቅሳል ፤ አይንን ይማርካል ፣ '. . .በትንሽ ክብ ፊት ረጅም አፍንጫ ፤ በሞላላ ፊት የሾላ ግንባር ፤ በቀጭን እግር ላይ ክብደቱ የሚመነዝል የስጋ ሸክም. . .' ያለበት አይነት አካል ስለማይመስል ። ቅርፅ የመጣኝነት ውጤት ነው ።

ቅርፅ የሚዘይደው ከቃላት ጀምሮ ሲመጠን ነው ። ስለሆነም በመጠኑም ቢሆን ስለ ቃላትና ስለ አረፍተ ነገር ሁብረትና ውህደት ከዚህ በፊት አብራርተናል ፤ ስለ ልዩ ልዩ አንቀፆችም እንዲሁ ። ስለዚህ ምጠናን (ሜካኒካዊ በሆነ መንገድ) ለማሳየት ያህል አንድ አንቀፅ ብቻ ጠቅሰን ወደ አጠቃላይ የቅርፅ አወጣጥ ማብራሪያ እንሸጋገራለን ።

'...ጣሊያኑ ሞተሩን ዘወረ ፤ እና ታዲያ ፣ እያንዳንዱ እነዚህ ትንንሽ ግለሰቦች እንዞ! ባንዴ ነፍስ ዘሩ — ጫማ ሰፊው ጫማ ቅጥቀጣ ፣ ብረት ሠሪው ብረት ልምሸቃ ፣ ወታደሩ ሻምላ ውዝወዛ ፣ ወይዘሮዋ ማራገቢያ ንስነሳ ፣ አሳላፊው ጠርሙስ ክምበላ ፣ ምሁሩ መጽሐፍ ንብነባ ፣ ገረዲቱ ወተት ምዥረጋ ፣ ንፉጉ ብር ቆጠራ — ተያያዙት ሥራቸውን — ባንዴት ሞተር ዝወራ ። አዎ ፣ አፍቃሪዉም በዚሁ ግፊት የፍቅሩን ከንፈሮች ተሳለመ! ማን ያውቃል ፣

በዚህ ያቸንጉሊት ትእይንት አንድ ቀላጅ — ተጠፍጣሪ — አንጀቱ እሮ እየማቀ — እኛ የሰው ልጆች ፣ ሥራችን ምንም ይሁን ወይም መደቡቻችን ፣ የቱን ያህልም ከባድ የቱን ያህልም ቀላል — ሁላችንም በአንድ ሙዚቃ የምንጨፍር መሆኑን እና በመከያውም ምንም ጿቱ ጠብ እንደ ማይ ልልን ሊያሳስበን ፈልጎ እንደሁ ፤ ሩጫ ሩጫ ሩጫ ! ጥድፊያ ፤ ሙዚቃው እስኪያቆም ፤ ሁሉም በያለበት እርጭ እስኪሉ ። እም ሙዚቃው አቆመ ፤ ውትወታው አከተማ ! — ታዲያ ንንሳ! የጫማ ሰፊው ጫማ ተሰፍቶ አላለቀም ፤ የብረት ቀጥቃጩ ብረት ተለምሽቆ ። የጠርሙስ ከምባዩ ብራንዲ አንድ ጨብታ አልጎደለም ፤ በአላቢዋም ባልዲ አንድ ጠብታ አልተጨመረም ። የገብጋባው ገንዘብ አንድ ሳን ቲም አላደገም ፤ የምሁሩም ጥናት ያንኑ ገፅ አላለፈም ። ሁሉም እዚያው ፣ ራሳቸውን በስራ ጥድፊያው ፣ በደስታው ፣ በማካበቱ ፣ በማወቁ ከመብከንከናቸው በፊት ፣ በነበሩት ሁናቴ ላይ ነበሩ ። እጅግ የሚያሳዝነው ደግሞ አፍቃሪው በተለገሰው ከንፈር ደስታው ጨምሮ አልተገኘም …"

ይህ ፅሁፍ ፣ አንቀፅን ሚዛናዊ ባልሆነ ድግግሞሽ የማመጣጠን ስልት ነው ። ደራሲው ፣ በመጀመሪያው ክፍል ተጠቃሾቹን አንድ ባንድ ይዘረዝራል ፤ በመጨረ ሻው ክፍል ግን ሁለቱን ይተዋቸዋል ፤ ወታደሩንና ወይ ዘሮዋን ። ፅሁፉ ስምሙ ሆኖ እንዲታይ እያንዳንዱን ዝርዝር በጫማ ሰፊው ጀምሮ በአፍቃሪው ይጨርሳል ። በዝርዝሩ ውስጥ ያሉትን ሌሎቹን ግን በሌላ እቅድ መሰ ረት ያሰልፋቸዋል ፤ ማለትም 1—2—5—6—7—8 የነበ ሩትን 1—2—5—7—8—6 በማድረግ ። ከዚያም እንደገና 'በመልፋት ፣ በመደሰት ፣ በማካበት ፣ በማወቅ' በማለት ያጠቃልላቸዋል ።

---

* ፒ· ሎሬንስ ፣ 'የሶርን የስድ ፅሁፍ አቀራረብ'(1945 እ.ኤ.አ.)ገፅ ፣ 180 ።



እንደምንመለከተው ተመጣጣኝነት እንዲኖር ማን ኛውም ሁነት ፣ ጉዳይ ወይም ነገር በነበረበት ሁኔታ ሁል ጊዜ እንዳለ መደጋገም ወይም እኩል በኩል ተመዛዝኖ መገኘት የለበትም — ማለትም እንደ ሰው አካል — ግራና ቀኝ አይኖች የሚመሳሰሉ ፤ ግራና ቀኝ ጆሮች የሚመሳ ሰሉ ወዘተ… ስለዚህም ነው ደራሲው እየለዋወጠ 1—2—3—4—5—6—7—8 የነበረውን 1—2—5—6—7—8 ፤ 1—2—5—7—8—6 እና በመጨረሻም እንደገና በሌላ መንገድ በማሰለፍ የተጠቀመው። ( ገፅ 17 (መ) የተጠቀሰውንም ግስረጃ ተመልከት ። ) ይህ እንግዲህ ከቅርፅ መመጠኛው ስልቶች ውስጥ የሚዛናዊነት ስልት ነው ። ሌሎቹ ደግሞ ፣ የትልም ስልት (ከገፅ 267 እስከ 295 ተመልከት ።) ፣ የሀሳብ እድገት ስልት (ከገፅ 363 እስከ 389 ተመልከት ።) የምስል ፣ ስልት በመባል ይታወቃሉ ። አንድ ኪነ - ፅሁፍ የሰመረ ቅርፅ እንዲኖረው በሁሉም መጠቀም ይኖርበታል ።

## 7.5.1 <u>አጠቃላይ መርህ</u>

በኪነ - ፅሁፍ ዝግጅት ውስጥ ሁለት አይነት የቅርፅ አወጣጥ ይታያል ። አንደኛው ፣ ሊባል የተ ፈለገው ይዘት በአጥጋቢ ሁኔታ እንዲባል ፣ ራሱ ይዘቱ የሚኖረው ውስጣዊ ቅርፅ ሲሆን ፣ ሌላው ደግሞ ፣ በአዲሱ ቅርፅ የተሰነዘረው ሀሳብ ተሰሚነት እንዲኖረው በተለመዱ ነባር የቅርፅ አይነቶች — ማለትም በውጫዊ ቅርፅ የመጠቀም ስልት ነው ።

## 7.5.2 <u>ውጫዊና ውስጣዊ ቅርፅ</u>

### (ሀ) <u>ውጫዊ ቅርፅ</u>

በውጫዊው ቅርፅ ረገድ ሁላችንም የምናውቃ ቸው ፣ ምንበዛም የማይለወጡ ቅርፆች አሉ ፤ ሲያ

ያዝ የመጣውን ልምድ በመከተል የሚሰራባቸው —ባለ ሶስት ፥ ባለ አምስት እና ባለ ሰባት ክፍል ቅርፆች እና የመሳሰሉት ። ለሚጭር ፅሁፍ ከተራ ድርሰት ጀምሮ የሚሰራበት ባለሶስት ክፍል ቅርፅ (መግቢያ-ማበልፀጊያ-መደምደሚያ) ሲሆን ፥ ለረጃ ጅም ደግሞ ባለ አምስትና ባለ ሶስት ክፍል ቅርፅ ነው ። ባለ-ሁለት ፥ ባለ አራት ፥ ባለ ስድስት ወዘተ... ግን እምብዛም አይሰራባቸውም ፥ ቢሰራባቸውም ፤ ካለማመቻታቸው የተነሳ ታዋቂ ፅሁፍ አላተረፉም ።

## (ለ) ውስጣዊ ቅርፅ

በውስጣዊ ቅርፅ ረገድ ፥ በነበረው ላይ አንዳንድ ጭማሪ ወይም ቅናሽ ከማድረግ በስተቀር ገጨርሶ አዲስ የሆነ ቅርፅ ማምጣቱ ያዳግታል ። የቃላት አገባብን ፥ የአረፍተ ነገር አወቃቀርን ፥ የአንቀፅ አቀራረፅን የመሳሰሉት ፥ እንደ ባህሉና እንደየቋንቋው እድገት የተለያዩ ቢመስልም ፥ እምብዛም ለውጥ አያሳዩም ። እልፎ አልፎ እንደሚታየው 'አለ ቢባል' ፥ ምናልባት በዋናዎች የማቅረቢያ ስልቶች ላይ ነው ፤ ለምሳሌ ፥ በኪነ-ፅሁፍ ውስጥ ፥ በሁተታና በጭውውት አቀራረብ ረገድ ፥ በባለታሪክና በደጀን አቀራረብ ረገድ ፥ በተራኪና በፅሁፍ ግምባር አቀራረብ ረገድና በመሳሰሉት ። በጠቃላይ ግን፥እነዚህን ሁሉ ጨርሶ ደምስሶ አዲስ ውስጣዊ ለውጥ ያመጣ የለም—አዲስ ስሜት አመንጭ ውስጣዊ ቅርፆችን መፍጠሩ ሳይሆን፥ማለማመዱ ጊዜ በመፍጀቱ ምክንያት ይሆን ? አዲሶቹን ቅርፆች የተፈጥሯችን አባላት እድርገን ለመቀበል ጊዜ አመጣሽ መሆናቸውን መርሳት ስለሚኖርብን?



## 7.5.3 የአጭርና የረጅም ኪነ-ፅሁፍ ንድፋዊ ማስረጃ ፤

### አጭር ንድፋዊ ማስረጃ

ይህ ንድፋዊ ማስረጃ ሰባት ክፍሎች ይኖሩታል፤ በቅርፅ አገነባብ ስልትም ፥ ክፍሎቹን ፥ 1—2—3—4—5 — 6 — 7 ብለን በአሀዝ ብናመለክታቸው ፥ በጎደሎ ቁጥር የተመለከቱት 1 — 3 —5 — 7 በቅርፁ አቢይ ክፍልነታቸው ፥ የፅሁፉ ታሪክ ተከታታይነት የሚገኝባቸው ናቸው ፤ በሙሉ ቁጥር የተመለከቱት ደግሞ ፥ 2—4—6 በንኡስ ክፍልነታቸው ፥ የታሪኩ ሂደት የሚቋረጥባቸው ፥ መዳረጊያዎችን አመቻችዎች ይሆናሉ ማለት ነው ። ይህንን በአሀዝ የተጠቀሰውን በቃላት እንመልከተው ፤

1ኛ ክፍል ፤ በዚህ ክፍል የታሪኩን ሜዳ ያዘጋጃል ፤ ባለታሪኮችን ከማስተዋወቅ ጭምር (መግቢያ) ።

**አጅ ፥**

'የሀብታም ልጅ የሆነ ኤፍሬም የሚባል የሀያ አመት ወጣት ከሀረር አዲስ አበባ ለትምህርት መጥቶ ማራቶን ሆስቴል ውስጥ አንድ ክፍል ተከራይቶ ይገባል ። እሆስቴሉ አጠገብ በሚገኝ ቪላ ግቢ አንዲት ውብ ልጅ ያያል ፤ ውበቷም ይስበዋል...'

2ኛ ክፍል ፤ በዚህ ክፍል ለታሪኩ ደጋፊ የሚሆኑ መዳረጊያዎች (ንኡስ ድርጊያዎች ፥ ባለታሪኮችና ደጀኖች ጭምር) ይብራራሉ ። የታሪኩ ሂደት ድርጊያ ያቆማል ፤

**እጅ ፥**

‘ኤፍሬም ሀረር እስተማረው የነበረውን መምህር አዳፍሬን ለመጠየቅ ይሄዳል ። እዚያም በጭውውታቸው ወቅት ማራቶን ሆስቴል ማረፉን ይገልፅለታል ። አዳፍሬ እሆስቴሉ ስር በሺላ ውስጥ ስለሚኖረው ሰው ያጫውተዋል ፤ ሱስ የሚያሲዙ እፆች ከገጠር እያስመጣ ወጣቶችን እንደሚበክልና የወለዳት ልጁንም ለዚሁ አላማ እንደሚጠቀምባት በአዳፍሬና በሰውዬው መካከል በዚሁ የተነሳ ቂም በቀል እንዳለ በትንሹ ይገለፃል ።’

3ኛ ክፍል ፤ በዚህ ክፍል የታሪኩ ሀረግ እንደገና ይመዘዛል (አቢይ ድርጊያ) ፤

**እጅ ፥**

‘ኤፍሬም ልጅቷን (ስሟ ብርቱካን ይባላል) በአጥር ላይ ያነጋግራታል ፤ ይተዋወቃሉ ፤ ይጨዋወታሉ ፤ በሌላ ጊዜ እቤቷ ትጋብዘዋለች ። ኤፍሬም ብርቱካንን እየወደዳት ይሄዳል ፤ ሊዳብሳት ፥ የራሱ ሊያረጋት ይሻል ።’

4ኛ ክፍል ፤ በዚህ ክፍል ታሪኩ እንደገና ያቆማል ፤ (መጸረጊያና ንኡስ ድርጊያ)

**እጅ ፥**

‘መምህር አዳፍሬ ፥ ኤፍሬም ሆስቴል ይመጣል።ኤፍሬም ከብርቱካን ጋር የተያያዘው ጎዳና አደገኛነቱን ፥ ሰውዬው በእርግጥ እፅ እንደሚያሰራጭ እንደሚያውቅና በየጊዜው ገጠር የሚሄደውም እፁን ለማምጣት መሆኑን ፤ ከፖሊስም ጋር በመተባበር እጅ ከፍንጅ ሰውዬውን የሚያሲዙበት ጊዜ ሩቅ እንደማይሆን ይገልፅለታል ።’



5ኛ ክፍል ፤ የታሪኩ ሀረግ እንደገና ይሳባል (አቢይ ድርጊያ) ፤

**እጅ ፥**

‘ኤፍሬም እብርቱካን ቤት ይሄዳል።ስለ ራሷ፥ ስለ ቤተሰቧ ታጫውተዋለች ፤ ፍላጎቷን ፥ ህልሟን ትገልፅለታለች ። እዚያው ውሎ ያመሻሻል ። በመጨረሻ አብረው እፁን በማጨስ አዲስ የህልም አለም ያያሉ ። ኤፍሬም ፥ በእርግጥ ፍቅር የያዘው ይመስለዋል ።’

6ኛ ክፍል ፤ ለስስተኛ ጊዜ የታሪኩ ሂደት ይገታል (መጻረጊያና ንኡስ ድርጊያ) ።

**እጅ ፥**

‘ኤፍሬም እመምህር አዳፍሬ ቤት ይሄዳል ። ሁኔታውን ያጫውተዋል ። እፁን በሚመለከት ግን አንዳችም ነገር እንዳላየ ይነግረዋል ። ለማንኛውም መምህሩ ስለ እፁ አደገኛነትና እንዲያጨስ እንኳ ቢጠየቅ ወደ ሳምባው እንዳይስበው ይመክረዋል ፤ በከንፈሩ ላይ አዳዲስ ለውጦችን ስለ ተመለከተ ። ልጅቷንም ቢተዋት እንደሚሻልና ህይወቱን እንደምታበላሽበት ፥ እንደማትሆነውም ይገልፅለታል ።’

7ኛ ክፍል ፤ ለመጨረሻ ጊዜ የታሪኩ ሀረግ መቋጠሪያውን ያገኛል (አቢይ ድርጊያ — መደምደሚያ) ፤

**እጅ ፥**

‘አንድ ቀን መምህር አዳፍሬ ፥ ኤፍሬምን እኖብር

ቱካን ቤት ሲገባ ያየዋል ፤ የብርቱካን አባት በቅ ርቡ እገጠር ሄዶ መጥቷል ። ከፖሊሶች ጋር በመ ተባበር ቤቱን እንዲከበብ ያደርጋል ። ባለቤትዬው ቤቱ እንደ ተከበበ ያያል ። ኤፍሬምን በስርቆሽ በር ሲያስወጣው ፖሊሶች ያያሉ ። ኤፍሬም እን ዲቆም ሲጠየቅ ይሸሻል ። በሚሮጥበት ጊዜ ጥይት ይተኮሳል ። ልጅቷ ትሰማና ትከተላለች ፤ ድንገት ሯጭ መኪና ያገኛትና ገጭቶ ይገድላታል ።

ይህ እንግዲህ ሰባት ክፍል ያለው የታሪክ ቅርፅ ነው ። በአቢይ ክፍሎቹ የኤፍሬምንና የብርቱካንን ፍቅር ደረጃ በደረጃ ይተርካል ፤ አንድ ነጠላ ትልም መሆኑ ነው ። በንኡስ ክፍሎቹ ደግሞ የኤፍሬም ንና የመምህሩን ግንኙነት ይገልፃል ። በተጨማሪም ፤ ቀስ በቀስ ሰውዬውን ታሪኩ ውስጥ ያስገባዋል ፤ በመግባቱም የልጅቷ ሞት ምክንያት ይሆናል ፤ ቂም በቀሉ ይሰካለታል ። ይኸኛዉ ደግሞ ፤ ሌላው ነጠላ ትልም ነው።ውስብስብ እንዲሆን ቢያስፈልግ ሁለቱ ትልሞች ለአንድ አላማ መቋጨት አለባቸው ።

## ረጅም ንድፋዊ ማስረጃ

ይህንኑ ባለሰባት ክፍል ቅርፅ ለረጅም ልቦ ለድም ለማዋል ይቻላል ። ለምሳሌ እንደሚከተለው በመከፋፈል ፤



1ኛ ክፍል

(ሀ) (ለ) (መ) — ሶስት ክፍል መግቢያ

2ኛ ክፍል

(ሀ) (ለ) (መ) (ሰ) (ረ) — አምስት ክፍል መዳረጊያዎችና ንኡሳን ድርጊያዎች

3ኛ ክፍል

(ሀ) (ለ) (መ) — ሶስት ክፍል አበይት ድርጊያዎች

4ኛ ክፍል

(ሀ) (ለ) — ሁለት ክፍል መዳረጊያዎችና ንኡሳን ድርጊያዎች

5ኛ ክፍል

(ሀ) (ለ) (መ) — ሶስት ክፍል አበይት ድርጊያዎች

6ኛ ክፍል

(ሀ) (ለ) (መ) (ሰ) (ረ) — አምስት ክፍል መዳረጊያዎችና ንኡሳን ድርጊያዎች

7ኛ ክፍል

(ሀ) (ለ) (መ) — ሶስት ክፍል መደምደሚያ

ሚዛን — 3 ፡ 5 ፡ 3/2/3 ፡ 5 ፡ 3

ለረጅምም ሆነ ለአጭር ልቦለድ በአብዛኛው የሚ ሰራበት አምስት ክፍሎች ያለው ቅርፅ ነው ።

እዚህ ላይ ልናጤነው የሚገባ መሰረታዊ ነጥብ አለ ። ቅርፅን ፣ መግቢያው በዚህን ያህል አንቀፅ ፣ ማበልፀጊያው በዚህን ያህል ፣ መደምደሚያውን ደግሞ በዚህ ማበልፀግ ትችላለህ የሚል ህግ ሊወጣ እንደማይችል መገንዘብ ያሻል ። የሚወስነው እያንዳንዱ የድርሰት ይዘት ነው ። ስለዚህ በሶስት ፣ በአምስት ወይም በሰባት የተከፈለ ቅርፅ በምንመርጥበት ወቅት መንደርደሪያዎቹ ጥያ ዎች የሚከተለውን አይነት ሊሆኑ ይገባል ፤

— መግቢያው ለትረካው መንደርደሪያ የሚያመቹ ብቁ ነጥቦችን ሁሉ ይሰጣል አይሰጥም ? በማያስፈልጉና ሀሳብን ባልሆነ መንገድ በሚያዘምቱ ነጥቦች ተጨናንቋል ፣ አልተጨናነቀም ?

— የትረካው አቢይ ጉንጉን የድርጊያውን እድገት አስፈላጊ ደረጃዎች ያቀርባል ፣ አያቀርብም ? ወይስ አቢዩ ጉንጉን እድገት በማይጨምሩ ነጥቦች በማጨናነቅ አንባቢን ያደናግራል ?

— መደምደሚያውስ ? የትረካውን መልእክት ግልፅ የሚያደርጉ (በውስጠ ታዋቂነትም ሆነ በግልፅ) በቂ ነጥቦችን ይዟል ፣ አልያዘም ? መልእክቱን አጨልሞታል ፣ የማያስፈልጉ ነጥቦችን በመጨመር ?

ባጠቃላይ ቅርፁ ለትረካው እንዲያመች ሆኖ መዘጋጀት ይኖርበታል ።

## 7.6 የአፃፃፍ ዘዬ

በዚህ ፅሁፍ ውስጥ ዘዬ ሲባል ፣ የሀሳብ ፣ የሁነታና የድርጊያ አባባል ስልት ማለት ነው ። ዘዬ ፣ ይዘትን ማስ ባሰቢያና ትርጉም መስጫ ቅርፅ ነው ፣ የሚባለውና አባ



ባሉ የሚጥይቁበት ነው ዘዬ ፣ እንደየራስ ግግር ሁሉ ይለያያል ። ከራስነት ጋር የተዋሀደ፣የራስ የሆነ አነጋገር እንዳለ ሁሉ ፣ የራስ የሆነ አፃፃፍም አለ ። በራስ የቃላት አመራረጥና የአረፍተ ነገር አሰካክ የቀረበ ሀሳብ ፣ በሌላ የቃላት አመራረጥና የአረፍተ ነገር አሰካክ ሲተካ መልእክቱ ያው አይሆንም ። አዳማጩ ወይም አንባቢው ከአባባሉ የሚረዳው የተባለውን ሀሳብ ብቻ ሳይሆን አባባሉ የተባለበት መንገድ የሚኖሩትን ተዛማጅና ዘማች ትርጉችም ጭምር ነው ። ዘዬው የይዘቱ አካል ነው ።

ዘዬ እንደ ፀሀፊው ግብና ዘዬው ለይዘቱ እንደሚኖረው አስፈላጊነት ይለያያል ። ስሜት የመፍጠር ፣ ስእልን የመከሰት ፣ ውይይትን አካሂዶ የማሳመን ግብ አለ ። ሀሳብን ወይም ጭብጥን በቀጥታ በማቅረብ የሚደረግ የማብራራት ፣ የመተንተን ፣ የመግለፅ ሳይንሳዊና ፍልስፍናዊ ግብ አለ ። በመጀመሪያዉ በተመለከተው የኪነ ፅሁፍ ግብ ውስጥ ዘዬና ይዘት እኩል አግባብና ዋጋ አላቸው ። እንዲያውም አንዳንዴ ፣ በአብዛኛው ፣ በዘዬው ብቻ ታውቆ የሚኖር ኪነ-ፅሁፍ ይታያል ። እንዲህ አይነቱ ፅሁፍ ፣ ታዋሽነቱን ከሚያበስሩት ውስጥ በዚህ መመሪያ ውስጥ እንደ ተመለከቱት አይነት ፣ በተለያዩ የአቀራረብ ቴክኒኮች ይጠቀማል ። ከቀጥታ አገላለፅም አሻሚና ግራ የሚያጋባ አይነቱን ይመርጣል ። ፅሁፉ የሚዘጋጀው ፍሬነገርን ለማስተላለፍ ብቻ ሳይሆን ፣ አንባቢዉ በሚኖረው አስተዳደግ ፣ ትምህርትና ልምድ መሰረት በሀሳብ እየተንደረደረና ከሀሳቡ የጐደለውን እየሞላ እንዲያነበውም ጭምር ስለሆነ፣ በአብዛኛው ደጋግመው ሲያነቡት አዳዲስ ስሜቶችን ይሰጣል ፤ ያልታዩ ሁኔታዎችን ይከስታል ። በሁለተኛዉ በተመለከተው የሳይንስ ፅሁፍ ግን ፣ ከመባያው ዘዬ ይልቅ ተባዩ (ይዘቱ)

የበለጠ አግባብና ዋጋ አለው ። አሻሚና ግራ የሚያጋባ አይነት አገላለፅ ፣ እንደ ጉድለት ስለሚቆጠር አቀራረቡ ቀጥታና ግልፅ ነው ። አንባቢ በሀሳብ እየተንደረደረ ለሚያደራው ሀሳብ እምብዛም ቦታ የለውም ። በአንዳንድ የኪነ-ፅሁፍ ቴክኒኮች ቢጠቀምም ፣ ፅሁፉ ለስሜት ከሳች ነት የተዘጋጀ ስላልሆነ ፣ ከፍሬ ነገሩ በስተቀር ፣ ታዋሽ ነት የለውም ። ሀሳቡም ተጨቃሎ ለመቅረብ የሚችል በመሆኑም ፍሬነገሩ እስከ ታወቀ ድረስ ደጋግሞ ማን በብ አያስፈልገውም ። ባጠቃላይ ግልፀት ያለው የሳይ ንስ ፅሁፍም ሆነ አንጊ ፣ አሳማኝና ታዋሽ ኪነ-ፅሁፍ የየራሳቸው የሆነ የአፃፃፍ ዘዬ አላቸው ።

በዚህ መመሪያ ውስጥ እንደ ተመለከቱት አይነት ልዩ ልዩ የኪነ-ፁሁፍ ቴክኒኮችን በማመልከት የአፃፃፍን ዘዬ ወደ ተመሳሰለ አቅጣጫ ለመምራት አይቻልም ፤ ከአንዱ ቴክኒክ ይኸንና ይኸን ያህል ፣ ከሌላው ደግሞ ፣ ያንና ያንን ያህል ለክተህ በመውሰድ አቀናብር በማለት ። እያንዳንዱንም የተለያየ ዘዬ እንዲህ እንዲህ መሆን አለ በት ብሎ መወሰን አይቻልም ፤ በመሰረቱ ዘዬው ከይዘቱ ጋር ስለሚገኝ ። ስለዚህ ፣ ዘዬ ይዘትን ጥርት አድርጎ ማወ ቅን ይጠይቃል ። ይዘት በግልፅ ከታወቀ ፣ ዘዬው በቀላሉ ይከሰታል ።



## መ ው ጫ

ዋና ዋና ብለን የገመትናቸውን የፅሁፍ ጥበብ ስል ቶች ከነመግለጫቸው ፣ ማብራሪያቸውና ማስረጃቸው ጋር ለማቅረብ ሞክረናል ። ለወደፊቱ በትረካ ሂደት ሞተርነት በሚያገለግሉት — ንፅፅር ፣ ድግምግምታ ፣ ሚዛናዊነት ፣ ጠቋሚነት ፣ ውጥረት መፈንጠቂያ ዘዴዎች እናቀርባለን ። ለጊዜው ከዚህ የፅሁፍ መመሪያ ውስጥ የተመለከቱትን ነጥ ቦች ያሰባስባል ብለን በመገመት ፣ የሚከተለውን መውጫ* አቅርበንላችኋል ፤ ለመግቢያዉ ሚዛናዊነትን በመስጠት ።

ማጠቃለያ ትረካ ከነመግለጫው

«እንዳርጌ ፣ አስራ ሁለት አመት የሆነው ድሃ ልጅ ፣ ከቡችላነቱ ጀምሮ ያሳደገውንና የሚወደውን ሶለግ ውሻ ውን ለመሸጥ ተገደደ ፣ በሁለት ምክንያቶች የተነሳ ።አን ደኛ ፣ እንዲህ አይነቱን ግዙፍ ውሻ መቀለብ ባለመቻሉ ። ሁለተኛ ፣ እጎረቤቱ የሚኖረውን ሀብታም ሰው ልጅ ካስ ደነገጠበት በኋላ አንድ ቀን አንዱ በመርዝ ይገድልብኛል የሚል ስጋት ስለ አደረበት ።»

ይህ ፅሁፍ የድርጊያ አንቀፅ ነው ፤ ልጁ ውሻውን የመሸጡ ። ፅሁፉ ያተኮረውም እድርጊያው ያደረሱትን ሁነቶች በጊዜ ገደብ እየተረኩ(አንባቢው ጉዳዩን ፣ ሁና ቴዎቹ በተፈፀሙበት ቅደም ተከተል እየኖረው እንዲ ሄድ በማድረግ) በማሳየት ላይ ሳይሆን ፣ የድርጊያውን መነ ሾዎች (ውሻውን እንዲሸጥ ያደረጉትን ምክንያቶች) እና

* በተለይ የትረካው ትልም (በከፊል) እና የትረካው መልእክት መግለጫ ዎች ፣ ከሌንስ ብሩክስ እና ሮበርት ዋረን ከፃፉት፣ 'ዘመናዊ አመርቂ ጽንጽ' ነው ዮርክ 1961 ( እ.ኤ.አ. ) ፣ ከገፅ 190—197 የተወጣጣ ነው ። ውርስ ትርጉም — በዳኛቸው ወርቁ ።

በድርጊያው ምን ለማድረግ እንደ ተሞከረ በመግለፅ ላይ ነው ። ፅሁፉን ለወጥ አድርገን በመፃፍ ደግሞ እንመልከተው ፡

«እንዳርጌ ፡ ከቡችላነቱ ጀምሮ ያሳደገው ቦለግ ውሻ ነበረው ። በጣም ይወደው ነበር ። ነገር ግን ከስራው ስለ ተባረረ ለውሻው ተገቢውን ምግብ ሊገዛለት አልቻለም ። ከዚያ ደግሞ ፡ ይባስ ብሎ ፡ ውሻው የአንድ ጎረቤቱ የሆነ ሀብታም ሰው ልጅ አስደነገጠበት ፡ የዳቦ ጉርሻጅ ሲበላ አግኝቶ ። እንዴ በመርዝ ይገድልብኛል ብሎ ሰጋ ፡ እንዳርጌ... እና ውሻውን ሸጠው ። »

በዚህም እንደ በፊቱ የድርጊያው መነሾዎች ተሰጥተዋል ። ግን አሁን በተለየ ሁኔታ በድርጊያው እንቅስቃሴ ውስጥ ታቅፈዋል ። በመጀመሪያ ላይ እንዳርጌ በሁለት ምክንያቶች የተነሳ ውሻውን ሸጠ ብለን በፃፍንበት ወቅት የትረካን አተራረክ የሚወስነውን ጠባይ — ትረካን በጊዜ ገደብ ማንቀሳቀስን — ጥሰናል ፤ ራሱን ተከታታይ ድርጊያውን ሳይሆን የድርጊያውን መነሾዎች እንደ ዋና የፅሁፉ ጉዳዮች አድርገን በመውሰዳችን ። የመጀመሪያው ፅሁፍ ድርጊያዉን ባስከተሉት ምክንያቶች ላይ በማተኮሩ በአብዛኛው ገላጭ ነው ፤ እንዳርጌ ለምን ውሻውን እንደ ሸጠ ይገልፃል ። ሁለተኛዉ ደግሞ ፡ የጊዜን ሂደት ተከትሎ ሁነቶችን እንዳመጣጣቸው በማቅረብ ስለተቀናበረ በአብዛኛው ተራኪ ነው ፤ በጊዜ ገደብ ወስጥ ምን ምን እንደ ተደረገ ይነግረናል ። ስለ ታሪኩ አይደለም የሚነግረን ፤ ታሪኩን ራሱን ነው ። ትረካ ፡ አሁን እየተከናወነ ያለ አይነት ስሜት ነው መፍጠር ያለበት ፤ እፊታችን እየተደረገ እያየነው ፡ እኛም በመንፈስ እየተካፈልንበትነፍላጎታችንን እንዲያም ሲል ድጋፋችንን እያከልንበት የምናጤነው አይነት ።



ሆኖም ፡ ከላይ የጠቀስነው ትረካ አጥጋቢ አይደለም ፤ ተራና ያልተሟላ ትረካ ነው ። በመጀመሪያ ፡ ራሱን የቻለ ሁነታና መዳረሻ ይዟል ለማለት አይቻልም ። ሁነታና መዳረሻ ተቀናጅተው አሁን እየተከናወነ ያለ እንዲመስለን የሚያደርግ ባህሪ የለውም። ምብዛም በሀሳብ የሚያንደረድሩ ጥቃቅን ዝርዝሮች የሉበትም ። በሌላ በኩል ደግሞ ፡ በትረካው ምን ለማለት እንደ ተፈለገ አናውቅም ። ነጥቡ አይታይም ።

<u>ትረካውን እንደገና እንፃፈው ፤</u>

1. «እንዳርጌ እከሌን የማይሉት ትንሽ ልጅ ነበር ፤ እመርካቶ አሜሪካን ሰፈር ከሚኖሩት ሌሎች ልጆች እምብዛም የማይለይ ። ፊቱ ልድፍ አይነት ፡ ምንም አይነት መልያ የሌለው ፤ አይኖቹ ጥቁርም የማይባሉ ፡ ቡናማም የማይባሉ ፡ ደብዛዛ አይነት አፈርቻ ፤ ሌላው ቀርቶ ፀጉሩ ሳይቀር ከርዳዳና ኩርንችት አይነት የነበረ ። ልብሶቹም ፡ መጨቅጨቂያ የሚመስሉ ውራጆችና የተጣጣፉ ነበሩ ፤ የሰፈሩ ልጆች ከሚለብሷቸው የማይለዩ ። መኖሪያውም እንዲሁ ከሌሎች የማይለይ ፡ በዝርግ በርሜል የተከደኑ ፡ ጣሪያቸውና ግድግዳዎቻቸው በቦንዳ የተማገሩ ፡ የዘይት ቆርቆር ቅጥልጥሎች በታጀቡበትና መተላለፊያቸው በቁሻሻ በተኮለኮለ ሰፈር ፤ ጭራሽ የተሰፋ ውጋጋን አልነበረውም ህይወቱ ። በዚያ ላይ አባቱ ነዝናዛ፤ አቅመ ደካማና ጠበኛ የነበረ ፤ እናቱ የስቃይ ኑሮዋን አሜን ብላ የተቀበለች ምስኪን ፤ ወንድሙ ምን ጊዜም የማይፀዳው ፡ የተንኮል ሳቅ የማይለየው ፡ ከሰፈሩ ወመኔዎች ጋር አሰሳ በማይወጣበት ጊዜ እንዳርጌን በማሰቃየት የሚደሰት ፤ መቆፈሪያ በሚመስል የጣቱ ቋር በማጋጨት ። ሆኖም ይህ እኗኗሩ አልነበረም ታዲያ ፡ እንዳርጌን ከሌሎቹ ልጆች የተለየ ያደረገው ። ይኸ ህይወቱ እንደ ማንኛዎቹም አብዛኛዎቹ

ልጆች ነበር ። አንዳርጌን የተለየ ያደረገው ስለማ ውሻው ነበር ።

2. « በአንድ ወቅት ፣ ከሁለት አመት በፊት — አስር አመቱን ባከበረበት በክረምት ውስጥ — አንድ ውሻ አገኘ ። ውሻዉ በጊዜው ገና ቡችላ ስለ ነበር ፣ ጥውልግልግ ያለና ችጋር የያዘው ፣ ያለ አቅሙ የተሸከማቸው የእግሮቹ መዳፎች የሚመነዝሉት አይነት ሲሆን ፣ በጊዜው እየቦታው እተቆለለው እቆሻሻ ክምር ውስጥ እያነፈነፈ ይቆፋፍር ነበር ።

3. « በዚያን ጊዜ ማንም ሰው እንደዚህ ሸንጣምና ጉልበታም ሆኖ ያድጋል ብሎ ያሰበ አልነበረም ፤ እንዲህ አሁን አንበሳ ሊያክል ።

4. « አንዳርጌ እቤቱ አመጣው ። ቤተሰቡ በውሻዉ ላይ የሚያሳየውን ቅዋሜ ፣ ፌዝና ልግጫ ፣ አልፎ አልፎም እርግጫ ተቋቁመለት ፣ 'እኔ ራሴ እመግበዋለሁ' በማለት፤'እኔ ራሴ ለፍቼ በማመጣው ገንዘብ ከምገዛለት ምግብ ውጪ የእናንተን ምግብ ጭራሽ አይቀምስም' እንዳለውም ቃሉን ጠበቀ ። እንጨት መሰንጠቂያ ቤት ስራ ያዘ ። ደከመኝ፣ ታከተኝ ብሎ የማይሰራው ስራ አልነበረም ለውሻው ሲል። ትልቁ ተስፋው ሲመሽ ወደ ቤቱ ተመልሶ ከሸቀጥ መጠረቂያ ጣውላዎች አገጣጥሞ በሰራለት የውሻ ቤት አጠገብ ተቀምጦ ፣ መስሎ የኔ መስሎ እያለ ባወጣለት ስም በማንቆሻበል ያመጣለትን ስጋ ሲበላ ማየቱ ነበር ... »

ለምሳሌ ትረካውን በዚህ አይነት ብንጀምር ፣ መጀመሪያ በቀረበው ላይ ብዙ ዝርዝሮች ጨምረናል ። አሁን ፣ ውሻዉ ለአንዳርጌ ለምን እጅግ አስፈላጊ እንደ ሆነ አውቀናል ። እርግጥ በዚህ ነጥብ ላይ ቀጥታ የተገፈ አስተሳሰብ የለም ። ቢሆንም ፣ አንዳርጌ ብቸኛና ፍቅር የሌለበት ህይወት ስለሚኖር ፣ ውሻዉ ፣ ልጁ በተፈጥሮው የሚ



ሰማውን ጓደኝነትና ፍቅር ለማግኘት ያለውን ፍላጎት የሚያሟላለት መሆኑን ማየት አያዳግተንም ። በዚህም አንዳርጌ ለውሻው ለሚያደርገው ድካም ሁሉ ምክንያት እንደ ነበረው እናያለን ፤ የህይወቱ ማእከል በመሆኑ ። በሌላ አነጋገር ፣ በሀሳብ በመንደርደር አንዳርጌ የነበረበትን የአእምሮ ሁኔታ እንገነዘባለን ። በዚህኛው ፅሁፍ ፣ አንዳርጌ ለውሻው የነበረው ቅርበትና ምክንያቱ አሁን እንደ ገለፅ ነው ፣ በአስረጅነት ፣ እንደ ገላጭ ሆኖ ነው የቀረበው ። ሆኖም ይህ ገላጭ አካል ፣ በራሱ በትረካው ውስጥ በተጉነኑት ሁነታዎችና መዳረጊያዎች ውስጥ ተውጢል ፤ ለብቻው አላፈጠጠም ። በተመሳሳይ ሁኔታም ፣ በትረካው ውስጥ የተሸረቡት ትናንሽ ምስል መከሰቻዎች የቀረቡት ትእይንቱንና አንዳርጌን በግልፅ እንድናያቸው በመረዳት ተፈላጊው ስሜት እንዲቀሰቀስብን ለማድረግ ጭምር ነው እንጂ በመስተዋታዊ አንቀፅነት ስእል እንዲስሉ ብቻ አይደለም ።

እዚህ ላይ በግልፅ መታወቅ ያለበት ፣ ትረካ የአንድን ህይወት ሂደት ሙሉነት እንዲሰማን ለማድረግ የሚቀርብ መሆኑ ነው ፤ እንድናይ ፣ እንድንሰማ ፣ ስሜታችን እንዲቀሰቀስ እና ሁነታውና መዳረጊያው የሚቋጩበትን እንዲገባን ለማድረግ ። መስተዋታዊ ፅሁፍ ብቻውን የሁነታውን ጥቂት ገፅታዎች እንድናይ ወይም እንድንሰማ ሊያደርግ ይችላል ። ገላጭ ፅሁፍ ደግሞ የሁነታውንና የመዳረጊያውን ትርጉም ፣ መነሻና ውጤት እንዲገባን ያደርጋል ። ይሁን እንጂ ፣ ትረካ ሙሉ በሙሉ እጥጋቢ እንዲሆን ፣ ሁነታዎችና መዳረጊያዎች በመስተዋታዊና በገላጭ ፅሁፍ አቀራረብ ዘዴዎች ተዋውደው የተገኙበትና፣ በትረካው የሚገለፀውን ህይወት በመኖር ላይ እንዳለን ሆነ እንዲሰማን ለማድረግ የሚያስችል መሆን አለበት ።

ትረካውን እንቀጥል ።

5. «ሁለቱ አመታት ሌሎችም ለውጦች ታይቶባቸዋል ፤ በስራው ረገድ ከሳጋቱራ ሰብሳቢነት ወደ ሳጋቱራ ቋጣሪነት ፣ ከሳጋቱራ ቋጣሪነት ወደ ሳጋቱራ አከፋፋይነት ደረጃ ለመድረስ በቅቷል፣ እንዳርጌ። በተለይ ሳጋቱራ በየጀንያው በሚቋጥርበት ጊዜ ፣ የየደንበኞቹን ቅጥልጥልና ድሪቶ የሆኑ ጆንያዎች ይይዛሉ ተብሎ በሚገመተው ሳጋቱራ መጠን እየለዩ መደልደሉ ፣ ለግማሽ አመት ያህልም ቢሆን ፣ የእንዳርጌ የስራ ድርሻ ስለ ነበር ፣ ደንበኞቹ እንደሚሰጡት ጉርሻና እንደ ወዳጅነታቸው እያየ የሚገለገልበት የገቢ ምንጭ ሆኖለታል ። ደሞወዙም ከአስራ አምስት ብር ወደ አርባ አምስት ብር አድጎለታል ፣ በዚሁ ወቅት ። እንዲያውም ባንድ ዘመን ፣ እንደ ማንኛውም ሌላ ሰው ፣ ከድርጅቱ - ሳጋቱራ በጅምላ እየገዛ በሚኖርበት አካባቢ መቸርቸር ጀምሮ ስለነበር ፣ የወር ገቢው እስከ ስድሳና ሰባ ብር ደርሶ ነበር ። መስሎም ታዲያ ፣ እነዚህ አጋጣሚዎች ሊያስገኙ በቻሉት ድጋፍ ጭምር ነበር እንዲያ እያደገና እያማረበት የተመዘዘው ። እንዳርጌ ከሚያገኘው የገንዘብ ጉርሻ ሌላ ፣ በተለይ ሆቴል ቤት ካላቸው አንዳንድ የሳጋቱራ ደንበኞች የሚገኘው የምግብ ትርፍራፊ ድጋፍ በቀላሉ የሚገመት አልነበረም ።

6. « እና ፣ ይብዛም ይነስ ስራው የሚፈልገውን ጥቅም ስላስገኘለት ፤ በትጋት ነበር የተያያዘው ፣ እንዳርጌ ። ብዙ እንጨት ሲገኝ ብዙ ሳጋቱራ ይኖራል ። ብዙ ሳጋቱራ ሲኖር በየጆንያው የመሙላቱ ስራ ይኖራል ። ብዙ እንጨት ከሌለ ደግሞ ፣ ብዙ ሳጋቱራም አይኖርም ። ብዙ ሳጋቱራ ከሌለም ብዙ ስራ አይኖርም ። ሆኖም ቀኖች እየነጎዱ ነው ፤ ቢሰራም ባይሰራም ።

7. « እንዳርጌ በአኗኗሩ እምብዛም ለውጥ አላሳየም ፤ የእለት በእለት ድርጊቱም ያው እንደ ሰፈሩ ልጆች ነበር ፤ አለባበሱም ጭምር ። ምናልባት አዘወትሮ በሚለብሰው ጥቁር ቆዳ መሳይ ጃኬት ካልሆነ በስተቀር ። እሱም ቢሆን ገጣባ የሚያጠቃው ያህያ ጀርባ መስሏል ፤ በየቦታው ተገጣጥቦ ። እና ደግሞ በፊቱ ፣ እንደ ሌሎቹ ልጆች አፈርማና ሻካራ ቢመስልም ፣ ገራምነቱ ፣ ለሳሳ ብርሃን እሚፈነጥቁ ደንቤ አይኖቹ ውስጥ መታየቱ ።

8. « … 'አዎ ፣ እንደምታየው የስራ እንቅስቃሴው እየቀነሰ እየቀነሰ ነው የሄደው … እንጨቱ ሲገኝ ማድረቂያ ማጣት፣ ማድረቂያ ሲገኝ የእንጨቱ መጥፋት ፤ እንጨቱም ማድረቂያውም ሲገኝ ገበያው መዳፈን . . .' እያለ ችግሩን አስቀድሞ በመደርደር ነበር ፣ ከስራ መሰናበቱን የገለፀልኝ አሰሪው ።

9. « በጣውላ ግድግዳና በሸንሸን ቆርቆሮ ጣራ ተለይቶ ፣ እግቢው ሲገቡ ፤ በስተቀኝ ጥግ ላይ ከተሸጎጠ ኪዎስክ ውስጥ ተቀምጦ ፣ እንደ ተለመደው አይኖቹን እመሬት ውስጥ ተክሏል ፤ የመሰንጠቂያ ቤቱን ባለቤት እግሮች አሳልፎ ። ሰውን ሲያዳምጥ ፣ ሰውየውን ሳይሆን የሰውየውን ግርጌ የማዳመጥ አይነት ባህሪ ይታይበታል ። ወይም አንዳንዴ ፣ የሰውዬውን ራስጌ — አየሩ ወይም መሬቱ የሚያነጋግሩት አይነት ።

10. ' ታዲያ ምን ይሻለኛል ? ' ለራሱ የሚናገር አይነት ነው የተነፈሰው ።

11. ' እንዴት?.. '

12. ' የውሻዬ ነገር ፣ ምን ላበላው ነው ? . . '

«ባለቤቱ ነገሩ አልገባውም ። ራሱን ብድግ ፣ ሽፋሉን ዘቅዘቅ በማድረግ እየተመለከተው ፣

13. ‘ ስራው ይገኝ እንጂ ግዴለህም .....
እስትትራብ ዝም አንልም፣እድልህ ቀንቶ መንግስት ንጨ ቱን ከለቀቀ መልሰን እንቀጥርሃለን ....’

14. ‘ እንዲያው እዚያውም ድረስ ፣ ምናልባት’
የሌሊት ዘበኝነትም ቢሆን ይገኝ እንደሁ ...’

15. ‘ አሄ ፣ አሁን . . . . ’

16. ‘ በግማሽ ደምወዜም ቢሆን ...’

17. ‘ አሁን አንችልም ፤ የለም. . . .አንችልም ።’

18. «...እንዳርጌ ሌላ ቦታ ስራ ለማግኘት ብዙ ጥረት አደ ረገ ። ያላዳረሰው የእንጨት መሰንጠቂያ ፣ የአናጢ ቤት የንዳጅ እንጨት መቸርቸሪያ አልነበረም ። ሆቴል ቤቶች ውስጥም ስራ ለማግኘት ሞክሯል ። አልተሳካለትም ። አልፎ አልፎ የሳጋቱራ ደንበኞቹ በነበሩት ሆቴሎች አካ ባቢ እየተላላከ እንደ በፊቱም ባይሆን ትንሽ ትንሽ የምግብ ትርፍራፊ ከሚሰጡት በስተቀር፣ያገኘው ተስፋ አልነበረ ውም ። እንዲያም ሆኖ የተቻለውን ያህል ከመስሎ አጠ ገብ አልተለየም ። ያገኘውን ያህል ያመጣለታል ፤ ይመግ በዋል ፣ ያሻሽዋል ፣ ይላፋዋል ። መስሎም ፀጉር የመጣልና የመክሳት ሁኔታ ቢታይበትም እምብዛም አላሳጣም ።

19. « ሳምንታትና ወራት አለፉ ፤ እንዳርጌ ምንም አይነት ቋሚ ስራ ለማግኘት አልቻለም ። ያለ ስራ ብዙ ጊዜ መቀ መጥ ያቅበጠብጣል ። መቅበጥበጥ ደግሞ አይመች ምኞት ያስመኛል ። አይጓደኙት ጓደኛ ያጎዳኛል ። አይሰሩ ስራ ያሰራል። እንዳርጌ ከምርካቶ ወመኔዎች ጋር መዋል ጀመረ፤ የነሱም ምግባር ቀስ በቀስ እየተጋባበት ሄደ ። በየቦታው መንከራተት ፣ በኩሊነት መዋተት ፣ እየባስቴው ቤት መጎ ለት ፣በሆነባልሆነው መጣላት፣መሰዳደብ፣መደባደብ እለታዊ



የኑሮ መልኩ ሆነ ። ቀስ በቀስም፣ በተለይ ጉልበታማዎቹ እያጠቁት ሲሄዱ ፣ ለወንድሙም የሚበቀልልኝ መስሎት ባሜወተው ቁጥር የተንኮል ሳቁን እየሳቀ፣ ’እንዴት እን ዴት ነው የመታህ ?.... እንዲህ ?..’ እያለ የባሰ በማጋጨት ስለሚጨምርለትና ስለሚያላግጥበት ፣ ኑሮ እያስቸገረውና ድብድቡ እያየለበት ስለ ሄደ መስሎን እያስከተለ መዞር ጀመረ .....

20. «...‘ጃስ ልለው ነው ኋላ !’ ይላቸዋል ፣ አይነውሃቸው ሳያምረው ሲቀር ። መስሎ ወዲያው ነው ስለታም ጥርሶቹን የሚያሳየው ፤ ምንጭሩን ሳብ ረገብ ፤ ያዝ ለቀቅ እያደረገ ፤ እያሳሳበ ።

21. « ሆኖም ፣ ይኸም ቢሆን ተስፋ የሚጣልበት ሆኖ አላ ገኘውም ። መስሎ ቀስ በቀስ የሰው እጅ ለመደ ። ቀድሞ የማያስጠጋቸውን ወመኔዎች ዛሬ ያስጠጋቸዋል ። አልፎ አልፎም ከእጃቸው ይበላል ። ዛሬ ዳቦ ኑፈነፈ ቁጥር ጭ ራውን ውንውን ማድረግ ጀምሯል ።

22. « አንድ ቀን እንዳርጌና መስሎ እደጃቸው ሲጫወቱ መስሎን ዳቦ ይሸተዋል ። መስሎ ዙሪያውን ያነፈንፋል ። አንዳንዴ መሬቱ ላይ ፣ አንዳንዴ አየሩ ላይ አፍንጫውን እየተከለ ዘወር ይላል የቤቱን አጠገብ ኩርባ ። ወዲያው አየ ሩን የሚበሳ የድንጋጤ ጩኸት ይሰማል ።

23. « እንዳርጌ ይደርሳል ። አንድ ሰውዬና አንዲት ሴትዮ ከቤታቸው ሮጠው ይወጣሉ ። ሀብታም ጎረቤቶቹ ጋር ይፋጠጣል እንዳርጌ ። መስሎ ጭራውን ሰቅሎ ግራና ቀኝ ይዘልላል ፤ በአንድ የዳቦ ጉርማጅ ዙሪያ ። ልጁ ስቅስቅ ብሎ ያለቅሳል ። ሰውዬው ወደ ቤቱ ሮጦ ይመለስና የባህር ዛፍ ፍልጥ ይዞ ይወጣል ።

24. ‘ መስሎ ! ’ ብሎ ይጣራል አንዳርጌ በድንጋጤ ድምፅ ፤ እንዳይመታበት ሮጦ በፊለፊቱ በመቆም ። መስሎ ሸብረክ ብሎ ለሽ እንደ ማለት ይልና አፊት እግሮቹ ላይ አገጩን ተክሎ ይመለከታል — አንዴ ፍልጡን ፣ አንዴ እሚዳ ላይ ወድቆ የሚታየውን ጉርማጅ — ጥፋቱን የተረዳ አይነት ።

25. ‘ የቁልቤው ገብርኤል አይለመነኝ ! እዚሁ ባላስቀረው ፣ ሁለተኛ እደጇ ባገኘው ! » ብሎ ፍልጡን አምዘግዝጎ እድንጋይ ላይ በመጠለዝ ይናገራል ሰውዬው ፤ ፍንጥርጣሪው በየቦታው እስኪበተን ።

26. « መስሉ የተጠለዘ አይነት በድረግ ብሎ ጅራቱን ሸጉቦ ይፈተለካል ።

27. « ይንቀጠቀጣል ፣ ይንቀጠቀጣል በንዴት ፣ ሰውዬው። ሴትዮዋ ልጇን ታባብሳለች ፣ ትደባብሳለች ፣ ታሻሻለች ።

28. ‘ «ዳ.....ቦ.....ዳቦ.....ል...ሰጠው ብዬ.....ዳቦ.....ልሰ.....ጠው ብዬ , ይላል ልጁ ትንፋሹ ቁርጥ ቁርጥ እያለ ።

29. ‘ ለጅብ ይሰጠውና ደሞ ለሱ.....’ ትናገራለች ሴትዮዋ ። ‘ ነብር እየኝ ይበል.....’

30. ‘ አንዳርጌ አንገቱን ሸጉቦ መሬት መሬቱን ያያል ።

31. ‘ ዳቦ ል.....ል...ሰጠው ብዬ.....’ ይላል ልጁ ።

32. ‘ ለጅብ ይሰጠውና ደሞ ለሱ.....’ ትመልሳለች ፣ ሴትዮዋ ፤ ዳቦውን ከተሸቀነጠረበት ቦታ እያነሳች ። ዳቦውን እንድትሰጠው እጁን ይዘረጋል ፣ ልጁ ።

33. « ከዚህ ቀን ጀምሮ አንዳርጌ ከፍተኛ ስጋት አደረበት ። ስለ መሰሎ ባሰበ ቁጥር የሚሰማው ያ የልጅ ጩኸት ፣ የሚታየው ያ በድንጋይ ላይ የተወቃ እንጩት ሆነ ። መስሎ ዳቦውን ለመቀማት እንዳልሞከረ ልቡ ያውቃል ። ልጁ ዳቦውን ሊሰጠው እጁን ሲዘረጋ በጨዋታ አይነት ዘሎ ለመ



ቀበል ሲሞክር እንዳስደነገጠውም ገብቶታል ። ግን ማን ይሰማዋል ቢናገር ፤ ማንስ ያምነዋል ። መስሎን አስሮ ለመቀለብ እስካልቻለ ድረስ የመስሉ ህይወት በአስጊ ሁኔታ ላይ እንዳለ ታየው ። ቀጥቅጠው ይገድሉብኛል ፤ ይመርዙብኛል የሚል ፍራቻው እየጨመረ ሄደ ። መስሉ ያለ ስጋት የሚኖርበትን ዘዴ ያሰላስል ገባ ።

34. « አንዳርጌ መስሉን በአንድ ከፍተኛ ቦታ ላይ በተሰራ በትልቅ ቪላ ውስጥ ለሚኖር፣ዘውዴ ለሚባል ልጅ ሸጠው። የዘውዴ አባት ሀብታም ነበር ። ዘውዴ መስሉን መመገብ ይችላል ። ዘውዴ መስሉን በሚገባ ሊንከባከበው ይችላል ፤ የነዘውዴን ውሻ ማንም ሊመታው አይችልም ። እነዘውዴ ቤት ማንም መስሉን ሊመርዘው አይችልም ፣ ያንን ሰማይ ጠቀስ አጥር ዘልሎ ። አንዳርጌ እንዲህ እያሰላሰለ ራሱን ያፅናናል ።

35. « ሆኖም አንዳንዴ እነዚህ አስተሳሰቦች ተገቢውን ያህል አያፅናኑትም ። እና ፣ መስሉን ከማግኘቱ በፊት ዱሮ የነበረበት ብቸኝነትና ባዶነት ይሰማዋል ። ታዲያ አሁን ትልቅ ልጅ እየሆነ ነው ፤ ትልቅና ጠንካራ ። ስለዚህም እንዲህ ያሉትን ስሜቶች የተቻለውን ያህል ለመርሳት ይታገላል ። አሁን አዘውትሮ አይሰራም ። ከሰፈሩ ወመኔዎች ጋር እየተቀላቀለ እዚያው እሰፈሩ ውስጥ ሲንገላወድ ይውላል ። መስሉንም ወደ መርሳቱ ተቃርቧል ።

36. « አንድ ቀን ፣ የተለመደ ዙረቱን ቀጥሎ ሳለ ፣ አትልቁ መስጊድ አጠገብ ዘውዴንና ውሻውን አገኛቸው — ትልቅ ጠንካራና ሸንጣም ውሻ ወጥቶት ስለ ነበር ወዲያው አላወቀውም ። ወደ ውሻው ቀረበ ፤ ‘ መስሎ መስሎ! እንዴት ነህ!’ የውሻውን ጆሮ መጎተትና ራሱን ማካከክ ጀመረ ። ከሁለት አመት በፊት ማታ ማታ በሸቀጥ መጠረቂያ ጣውላው ቤት ውስጥ ይኖር በነበረበት ወቅት ያደርገው እንደ ነበረ አይ

ነት ፤ መስሎ ራቱን ከበላ በኋላ ። ውሻዉ በአፍንጫው አሽ ታትተው ፤ እጆቹንም ላላሳቸው ። አንዳርጌ ዘውዴን እየተ መለከተ ፣ 'ሆው ! ትመለከትልኛለህ ! ተመልከት እባክህ ! አይገርምህም ? ያስታውሰኛል ማለት ነው !'

37. « ዘውዴ ምንም ቃል ሳይወጣው ለትንሽ ጊዜ ታገሰው ፤ ከዚያም ፣ «እጅህን ከውሻው ላይ አንሳ ፤ የኔ ውሻ ነው አሁን ' አለው ።

38 .« አንዳርጌ ወደ ኋላው አፈገፈገ ።

39. «መብረቁ ! ቶሎ እዚህ! ' በማለት አዘዘው ዘውዴ ውሻ ውን ፤ ውሻዉም ወደርሱ ሄደ ። የውሻዉን እራስ አሻሸው ። ውሻዉም የዘውዴን እጆች ይላልስ ጀመረ ...

40. « ዘውዴ ፊቱን አዞረ እና መንገዱን ቀጠለ .....

41. « በማግስቱ መኪኖን ጀመረ አንዳርጌ ፣ ስራ ፍለጋ ። ዱሮ ይሰራበት እነበረበት እንጨት መሰንጠቂያ ግቢ ስራ አገኘ — ዱሮ ፣ መስሎ ቡችላ በነበረበት ጊዜ እሰራበት ። እንደ ዱሮውም አዘውትሮና ሳያቋርጥ መስራት ጀመረ ፤ ዱሮ 'ስራዬን ቶሎ ጨርሼ እቤቴ ከመቼ ደርሼ ውሻዬን መግቤ' እያለ በጥድፊያና በጉጉት ምሽቱን ሲጠባበቅ በነበረበት አይነት መንፈስ ። ሆኖም አሁን ለውሻዉ የነበረው ፍቅር አብቅቷል ፤ ያ ጊዜ አከትሟል ። መስሎ ጌታ ለውጦ ታልና ። »

አሁን ትረካው እስከ መደምደሚያው ቀርቧል ። ኢያሉ ሁኔታዎችን ስላቀፈ ዘርዘር አድርገን እንመልከተው ።

1. ቃላትና አገባባቸው

1.1 በታሪኩ ውስጥ የተመለከቱ ወሳኝ ስሞች

1.1.1 የየቅል ፣ ብቸኛ እና/ወይም ከቻርጌ ስሞች



| | |
|---|---|
| አንዳርጌ | ኩርንችት |
| ትልቁ መስጊድ | መርከቶ |
| አሜሪካን ሰፈር | ሶለግ |

1.1.2 ጥቅል እና /ወይም ብቸኛ ስሞች ፤ ነባር*

| | | |
|---|---|---|
| እከሌ | ጣሪያ | እባት |
| ልጅ | ቦንዳ | እናት |
| ጎረቤት | ዘይት | ወንድም |
| ፊት | ቆርቆሮ | ወመኔ |
| አይን | ሀብታም | ጣት |
| ፀጉር | ቤት | ቋር |
| በርሜል | ሰው | ውሻ |

1.1.3 ጥቅል እና/ወይም ብቸኛ ስሞች ፤ ዘር**

| | | | |
|---|---|---|---|
| ልድፍ | ሰፈር | ቆሻሻ | አሰሳ |
| መሊያ | መኖሪያ | መተሳለፊያ | መቆፈሪያ |
| ልብስ | ዝርግ | ክምር | ቅጥልጥ |
| መጨጨቂያ | ግድግዳ | ሳቅ | ዙረት |
| ጭራጅ | | | |

1.2 ረቂቅ ስሞች

| | |
|---|---|
| ተስፋ | ተንኮል |
| ውጋጋን | ኑሮ |
| ህይወት | |
| ስቃይ | |

1.3 አጉልማሾች (ቅፅልና ተወሳከ ግሶች)

| | | | |
|---|---|---|---|
| ትንሽ | አፈርቻ ቀርቶ | ጠበኛ ቀርቶ | የታጀቡበት (ቆርቆሮ) /ሌላው/ |

* ነባር — ግስ የሌለው ከግስ ያልተወለደ
** ዘር — ግስ ያለው ከግስ የተወለደ

ልድፍ ክርዳዳ የማይሉት /ልጅ/ የተኮለኮለ (ሰፈር)

የተጣጣፉ (ልብሶች)

ጥቁር ዝርግ የሚኖር /ልጅ/ የማይወጣበት

ጭራሽ /የሳይታይበት/ /ጊዜ/

ቡናማ ነዝናዛ የሚመስል /ልብስ/ /የተለየ/

በማጋጨት /የሚደሰት/ /ያደረገው/

ደብዛዛ አቅመደካማ የሚለብሳቸው /ልጆች/ አብዛ

አጠገብ ም /የማይለይ/

## 1.4 ማሰሪያ አንቀፅና መስሎቼ

ነበር የነበረ /ነበር/ የተቀበለች /ነበረች/

አኗኗር /አልነበረም/

የማይለይ /ነበር/ የተጣጣፉ /ነበሩ/ የማይፀዳው /ነበር/

ይፋጠጣል

የሌለው /ነበር/ የተከደነ /ነበር/ የሚደሰት /ነበር/ የማይባሉ /ነበሩ/ የተማገረ /ነበር/ ብላ (የተቀበለች /ነበረ/

ከዚህ በላይ በዝርዝር እንደምንመለከተው ፣ አንቀፁ ከተገነባባቸው ቃላት ፣ 40 % ጥቅልና * ብቸኛ መጠሪያዎች ፣ 20 % ስምንና ግስን አጎላማሾች (ወሳኞች) ሲሆኑ ፣ 6 % ረቂቅ

---

* ጥቅል መጠሪያዎች አንፃራዊ በለሆኑ ፣(ገፅ 34-39 ተመልከት) ፣ ከብቸኛ መጠሪያዎች እኩል እንዳንዴም ሰፋ አድርጎ በመጠቆም ሀይላቸው ይበልጥ እንደሚያገለግሉ መዘንጋት የለብንም ።

የከመቶ (%) አገላለፅ የተጠቀምንበት ፣ የተለያዩ ቃላት እንደየፅሁፉ ውስጥ አይነት የሚኖራቸውን ሚና አጠናክረን ለማቅረብ ፣ ስለሆነ በየፅሁፉ ውስጥ ሁሉ ቃላቱ በዚህ አይነት የከመቶ (%) አገላለፅ ተዋረድ መገኘት አለባቸው ማለታችን አለመሆኑ እንዲታወቅ ያስፈልጋል ።



መጠሪያዎች እና 20 % ማሰሪያ አንቀጾና መስሎቼ ፣ 14 % መስተዋድድ ፣ መስተፃምሮችና የስም ምትኮች ናቸው ። በኪነ ፅሁፍ ውስጥ፣ ብቸኛ ከቻርጌ እና ጥቅል መጠሪያዎች ከአጎላማሾቻቸው ጋር አይለው መገኘታቸው ያለና መሆንም ያለበት ነው።አለዚያ ፅሁፉ ምስል የመከሰትና ብሎም ስሜት የመቀስቀስ ሀይል አይኖረውም ። ሆኖም ይህ አስተሳሰብ ፣ ረቂቅ መጠሪያዎችን ያንጓልላል ማለት አይደለም ። እንደ ሁኔታው ረቂቅ መጠሪያዎችም (ከሳይንሳዊና ፍልስፍናዊ ቦታቸው ሌላ) በኪነ-ፅሁፍ ውስጥም መለዮ ቦታ እንዳላቸው መገንዘብ ይኖርብናል ። ለምሳሌ ፣ «አባቱ ጠበኛ የነበረ፣እናቱ የስቃይ ኑሮዋን አሜን ብላ የተቀበለች» የሚለውን ሀረግ እንውሰድ ። በውስጡ በሰረዝ የተመለከቱት ጠበኛና የስቃይ ኑሮ ረቂቅ መጠሪያዎች ናቸው ። በጥቅልና ብቸኛ መጠሪያዎች ለውጠን ፣ «አባቱ እንደ ተኮሳተረ የሚኖር ፣ እትንኩኝ ባይ ፣ ምን ቃዋኛለህ ብሎ አፍንጫውን የሚነፋ ፣ ጠጥቶ ሞቅ ሲለው ነገር የሚፈልግ ፣ በሆነ ባልሆነው ልደባደብ የሚል የነበረ ፣ እናቱ የምትለብሰው የምትበላው ያረረባት ፣ የባሏን ስድብና ድብደባ ችላ የምትኖር ፣ ለመናገር ስሜቷን ለመግለፅ የማይፈቀድላት ሰውን ቀና ባላ ለማየት ፍራትፍራት የሚላት ፣ በዚያ ላይ በሽታ የሚያጠቃት እና በዚህ አይነት ኑሮ ጠባ የሚደርስባትን አሜን ብላ የተቀበለች» ብለን ብንፅፈው ጠበኛነትና የስቃይ ኑሮ የሚኖራቸውን ሰፊና እያሌ ተጠራሪ ሀሳቦችና ድርጊቶች አያቅፍልንም ። ረቂቅ መጠሪያዎች በአግባቡ ሲሰራባቸው ምትክ የለሾች ናቸው ።

በስነ-ፅሁፍ ውስጥ ስሞች ምስል ይከስታሉ ሲባል ፣ ምን ማለት ነው ? በስነ ፅሁፍ ውስጥ ስሞች ምስል ይከስታሉ ሲባል ፣ ስሞች እንድም በትምህርትና በልምድ ለአወቅ ነው ነገር ፣ ሰው ፣ ሀሳብና ስሜት መጠሪያ በመሆን ያ ነገር ሰው ወይም ሀሳብ በቀጥታ በአእምሯችን እንዲታየን ያደርጋሉ — ነገሩን ፣ ሰዉን፣ሀሳቡን እና ስሜቱን ያመለክታሉ፣ ይጠቁማሉ ማለት ሲሆን (አንዳርጌ ፣ መርካቶ ፣ ኩርንችት ፣ ውሻ ወዘተ...) ፣ አንድም የማናውቀውን ነገር ፣ ሰው ፣ ሀሳብ እና ስሜት ከምናውቀው ጋር በማመሳሰልና በማነፃፀር ያልታየንን እንዲታየን ያደርጋሉ ማለት ነው ። (ፀጉሩ <u>ኩርንችት አይነት ፣ ልብሱ መጨቅጨቂያ የሚመስል ፣</u> <u>መቆፈሪያ የሚመስል ጣት</u> ወዘተ...)

ብቸኛ እና /ወይም ከቻርጌ ቃላት ስሞች ብቻ አይደሉም ፤ ግሶች (በተለይ ውስን ግሶች) ተውሳከ ግሶች * እና ከግስ የተገኙ ስሞች (አጅ፣ ጨቀጨቀ — መጨቅጨቂያ/ መጨጨቂያ ፤ ቆፈረ — መቆፈሪያ ወዘተ...) እና ቅፅሎችም (አጅ፣ ለደፈ — ልድፍ ፤ ጠቆረ — ጥቁር ወዘተ...) ጭምር ናቸው። በተለይ ውስን ግሶች * ብቸኛ ግሶች ናቸው ፤ መደባቸውንና ቁጥራቸውን ወዘተ... በግልፅ ስለሚያመለክቱ ። ሌሎቹ ግን ፣ ማለትም አርእስት (አጅ ፣መጨቅጨቅ) ፣ ባቢዘር (አጅ ፣ አጨቃጨቅ) ፣ ቦዝ (አጅ ፣ ጨቅጭቆ) ፣ ወሰን የለሽ ግሶች — በመደብ ፣ በፆታ ፣ በቁጥርም ሆነ በጊዜ የማይ

---

* ለተወሳከ ግስ ወሳኝነት ምሳሌ ገፅ 382 ተመልከት ።

* ውስን ግስ የሚባለው በየመደቡ (1ኛ ፣ 2ኛ ፣ 3ኛ መደብ) እየተዘረዘረ ባለቤን ፆታውን፣ ጊዜውን፣ ቁጥሩ ... ንወዘተ የሚያመለክት ግስ ነው። (አጅቱ ጨቀጨቀ –3ኛ መደብ ፣ ተባእታይ ፣ ሀላፊ ፣ ነጠላ መሆኑን።)



ለዩ ስለሆኑ ፣ (አጅ፣ መጨቅጨቅ የሚለው አርእስት ለማንኛውም መደብ ነጠላና ብዙ ፣ ለማንኛውም ፆታ ፣ ለማንኛውም ጊዜ ስለሚያገለግል) ፣ ብቸኝነት የሚኖራቸው ፣ ግሶቹ የተወሰኑ ድርጊቶቹን አመልካች ሲሆኑ ከመቻላቸው አኳያ ብቻ ነው ።

<u>አጅ</u> ፣

መጨቅጨቅ (መጨጨቅ) ማለት መጠቅጠቅ ፣ መወተፍ ፣ መሸጎጥ ፣ መሸፈን ፣ መድፈን እና የመሳሰሉትን ማለት ነው ። ሆኖም እያንዳንዳቸው ተመሳሳይ ቃላት በማናቸውም ቦታ አንዱን ባንዱ ሊያስተካ የሚያስችል ተመሳሳይነት የላቸውም ።

ተመሳሳዩ ቃላት ብቸኛ ለእል ከመስጠት አንፃር የሚኖራቸውን የመወሰንና የማጠቃለል ትርጉሞች ፣ <u>ዐዲስ የማሪኛ መዝገበ ቃላት</u> ባቀረባቸው መሰረት እንመልከት ፤

*ጨቀጨቀ — ጠቀጠቀ ፣ ደፈነ ።

<u>ሌሎች ትርጉሞች</u>

(1) ነዘነዘ ፣ አተረከ ፣ ነተረከ ።
(2) ... አጨቀየ ።
(3) ርጥብ ጌሾ ወቀጠ ።

- ወተፈ — <u>ጣርን</u> ፣ ጭድን ፣ ቅጠልን ፣ ጨርቅን ፤ ሸጎጠ ፤ ከደነ ።
- ሸጎጠ...— አገባ <u>፣ ወተፈ</u> ፤ በቅርብ ደበቀ፣ ሸሸገ ።
- ደፈነ — ቀበረ፣ <u>መረገ</u> ፣ <u>መላ</u> ፣ <u>ጠቀጠቀ</u>፣ሸፈነ፣ <u>ወተፈ</u> ፣ ዘጋ ፣ ጨፈነ ፣ አለበሰ ፤ የውሃ ፣ የገንዘብ ፣ የነገር ..፤ የጕሮ ፣ የዐይን ።
- ጠቀጠቀ — <u>ደፈነ</u> ፣ <u>ደበቀ</u> ፣ ሸሸገ ፣ ሰወረ ፣ <u>ዘጋ</u> ፣ ሸፈነ፣ ጨፈነ ፤ ጕሮን ፣ ምስጢርን ፣ ምድርን ።

## ሌሎች ትርጉሞች

(1) አጠጋጋ ፣ አቀራረበ ፤ ወንፊትን ፣ ሸማን ።

(2) አበዛ፣ በግድ ጨመረ ፣ አገባ ፣ በላ ፣ ወጠቀ፤ ... ምግብን ፣ ሆድን ።

(3) ረገጠ ፣ ረመረመ ፤ መሬትን ።

ሸፈነ ...— አለበሰ፣ እንዳይታይ አደረገ ፣ ጋረደ ፣ ከለለ ጨፈነ ከደነ ።

ከዚህ በላይ እንደምንመለከተው ፣ የጨቀጨቀ ዘሮች ከማንኛቸውም ሌሎች ግሶች የበለጠ ውሱንነት እንዳላቸው ግልፅ ነው ። ስለዚህም መጨቅጨቂያ የሚለው አርእስት ፣ መሸፈን ከሚለው አርአስት የተሻለ ብቸኛ ምስል የመከሰት ሀይል አለው ። ህዝቡ እንደሚለውም መጩጨቂያ ወይም መጨቅጨቂት ቢል ደግሞ ፣ እንዲያውም የበለጠ ይሆናል ፤ በምጣድና ባከንባሎ መካከል የሚኖረውን ቀዳዳ ለመድፈን በተደጋጋሚ የሚጠቀሙበት የጨርቅ ትልታይ መሆኑንና ፣ ከጭሱ ብዛት የተነሳ መቆሸሹንና መጥቆሩን ስለሚያሳይ ።

በዚህ አይነት መታ የሚለውን ግስና ተመሳሳዮቹን እንመልከት ፤

| | | | |
|---|---|---|---|
| መታ | ቀጠቀጠ | አጣፈረ | ጠረቀመበት |
| ደበደበ | ዘረረ | ጠፈጠፈ | ከካ |
| መረገተ | ወገረ | ገረፈ | ፈለጠ |
| ቀሸመደ | ረገጠ | ኮረኮመ | ሸነቆጠ |
| ወቃ | አዘረጠ | አሎለ | |
| መደወተ | ጠለዘ | አደባየ | |



እዚህ ውስጥም እንደምንመለከተው ቢሆን ፣ ከመታ ይልቅ መረገተ፣ ኮረኮመ፣ ሸነቆጠና የመሳሰሉት የበለጠ ብቸኛ መሆናቸው ግልፅ ነው ። ሆኖም ፣ ከእንደነዚህ አይነት ብቸኞች ደግሞ በማመሳሰል ፣ በማነፃፀርና በፈሊጦች አማካይነት የሚደረገው ምዕል የመከሰት ሀይል የበለጠ እንደሚሆን መገንዘብ ያስፈልጋል ፤

**እጅ ፣**

እፈር አስጋጠው ።
አይነስቡን አበረረው ።
ጀርባውን ሞሸለቀው ።
መንገጭሌውን አወለቀው ።
(በጡጫ) ጠበሰቀው ።
(በክርን) ደቆሰው ።
(በቡጢ) ነፋው ።
(በጥፊ) አቃጠለው ።
እግንባሩ ላይ አፈላበት ።
እሆዱ( አንገቱ) ላይ ቆመበት ።
እና በመሳሰሉት አይነት ።

የግሶች* ምስል የመከሰት ሀይል በዚህ ብቻ አያበቃም ። ብዙ ጊዜ ፣ የግሱን ባለቤት ተፈጥሮና ወዲያውም የድርጊቱን ተፈጥሮ ጭምር የመሳል ባህሪ አላቸው ።«እንዳርጌ ፣ መስሎን ከቡችላነቱ ጀምሮ እሳደገው» ቢል ፣ እንዳርጌ ለመንከባከብና ጠብቆ ለማሳደግ ያለውን ተፈጥሮና እራሱን የመንከባከቡንና የማሳደጉን ድርጊያ ምስል ጭምር ነው በአእምሯችን የሚከስተው ፤ እንደየልምዳችን (የሚከሰተው ያሳዳጊ ምስል ለልምዳችንና ለስሜታችን እንደሚቀርበን ያሳዳጊ አይነት — የአባት ፣ የእናት ፣ የገበሬ ፣ የከብት እርቢ ወዘተ... በመሆን) ሊለያይ እንደሚችል ሁሉ ፣ የድር

ጊያውም ተፈጥሮ እንስሳት፣ አእዋፍ፣ ሰው፣ ግንብ፣ ሀሳብ የማሳደግ እየሆነ ሊለያይ ይችላል ።

በዚህ አይነት አጠቃቀም ፣ ባጠቃላይ ፣ ማነጻመኛ ከስከተለ ግስና ከግስ መሰሎች ይልቅ ነጠላውን የቆመ ግስ ይመረጣል ።

ቅፅሎች ስሞችን በይበልጥ ብቸኛና ከቻርጊ ለማድረግ ይሰራባቸዋል ። ሆኖም በስም ላይ የምንደርተው እያንዳንዱ ቅፅል የዚያን የስም ምስል ጉልቶ እንዲታይ ለማድረግ መቻል አለበት ። አለዚያ ቅፅሎቹ ከመብዛታቸው የተነሳ ምስሉ ደብዛዛና ጨርሶ የማይታይ ሊሆን ይችላል ።

<u>ምሳሌ ፣</u>

- የአሜሪካን ሰፈር
- ትልቁ መስጊድ
- ልድፍ ፊት
- ደብዛዛ ፣ አፈርቻ አይን
- ከርዳዳ ኩርንችት ፀጉር
- የተጣጣፈ ፣ መጨጨቂያ የመሰለ ልብስ
- በዝርግ በርሜል የተከደነ ፣ ጣሪያና ግድግዳው በበንዳ የተማገረ፣ የዘይት ቆርቆሮ ቅጥልጥል መኖሪያ
- በቆሻሻ ክምር በተከበበ መተላለፊያ
- ነዝናዛ ፣ አቅመ ደካማና ጠበኛ አባት
- የማይፀዳው ፣ የተንኮል ሳቅ የማይለየው ፣ ከሰፈሩ ወመኔዎች ጋር አሰሳ ሳይወጣ አንዳርጌን በማስቃየት የሚደሰት ወንድም

ከዚህ በላይ የተመለከቱት አነላማሾች የሚታዩንን ምስሎች የሚያጨልም ዝርዝር አይታይባቸውም ። ነገር ግን ፣ «ልድፍ ፊት ፣ ሹል ግንባር ፣ በወረንጦ የማይለ



ቀም አይን ፣ ሚዳ ሙሉ አፍንጫ ፣ እንጥልጥል ከን ፈር..» በማለት ቅብራክቶ ቢሆንስ ?

የሁኔታና የተዛምዶ ተወካዮችም (ተ/ግስ፣ መስተዋድድ፣ መስተፃምር) ቢሆኑ ፣ ብቸኛ ምስል የመፍጠር ሀይል አላቸው ። ተውሳከ ግሶች፣ ግስን፣ ሌላ ተውሳከ ግስንና ቅፅልን በማጎላመስ ብቸኛ ምስል ይፈጥራሉ ። መስተዋድዶች፣ በስሞችና በስም መሰሎች ላይ በመጫን ፣ ከተጫኗቸው ቃላት ጋር በመሆንና ለየብቻቸውም (በተለይ አቅጣጫና ቦታን ሲያመለክቱ) ለሚያጎላምሱት ቃል ብቸኛ ምስል ያስገኛሉ ። መስተፃምሮች፣ በግስ ላይ ሲወድቁ ስሞችንና ስም መሰሎችን በማጎላመስ ብቸኛ ምስል ይከሰታሉ ።

<u>ተውሳከ ግስ</u>

- ግስን ብቸኛ ሲያደርግ ፤
  <u>እጅ ፣</u> ተንደርድሮ መታው ፤
- ተ/ግስን ብቸኛ ሲያደርግ ፤
  <u>እጅ ፣</u> ተንደርድሮ በሀይል መታው ።
- ቅፅልን ብቸኛ ሲያደርግ ፤

  <u>እጅ ፣</u>

  አሜሪካን ሰፈር የሚኖር ልጅ ፤

<u>መስተዋድድ ፣</u>

- ከስምና ከስም መሰሎች ጋር ሆኖ ምስል ሲከስት ፤

  <u>እጅ</u>

  <u>በዝርግ በርሜል</u> የተከደነ።(ስምን ብቸኛ ሲያደርግ፤)

በፀንዳ የተማገረ ፤ (ቅፅልን ብቸኛ ሲያደርግ ፤)
እቤቱ አመጣው ፤ (ግስን ብቸኛ ሲያደርግ ፤)
ወደ ቤቱ ተመልሶ ፤ (በዝን ብቸኛ ሲያደርግ ፤)

- በራሱ ቆሞ ምስል ሲከሰት ፤

አጅ ፤

«በውሻው ቤት አጠገብ »
«በውሻው ቤት ፊት ለፊት »
«በውሻው ቤት ጎን »
«በውሻው ቤት ጀርባ »
«በውሻው ቤት ውስጥ »

እያንዳንዳቸው የተሰመረባቸው መስተዋድዶች ብቸኛ ምስል ይከስታሉ ።

- መስተፃምሮች
  - በግስ ላይ ሲወድቁ ፤

  አጅ ፤

  «በቆሻሻ የተቦለከለ ሰፈር »
  «የማይፀዳው ወንድም »

2. ...በታሪኩ ውስጥ የሚታዩ የአንቀፅ ሂደቶች ፤

2.1 አንቀፅ 1 እና 2

በዝርዝር ነጥቦች የተቀናበረ ፤ የብቸኝነትንና አለኝታ የሌለው የመሆንን ምስልና ብሎም ስሜትን እንዲፈጥር ሆኖ ።

2.2 አንቀፅ 2—7

በጊዜ ቅደም ተከተል የተጠቃለለ ትረካ ፤ አንቀፅ 6 እና 7 ሳጋቱራ የሚለውን ቃል በመደጋገምና በንፅፅር (ገጣባ የሚያጠቃው ያህያ



ጀርባ እና ደንቤ እይኖች ወዘተ ...)
የአንዳርጌን ባህርይና የስራውን ጠባይ ለማጉላት የተሞከረበት ።

2.3 አንቀፅ 8—17

በጭውውት የተቀናበሩ አንቀፆች ፤ ሶስተኛውን አቢይ ድርጊያ (አንዳርጌ ከስራ መባረሩን) ስለሚስሉ ፤ ትልሙን ወደፊት ያራምዳሉ ።

2.4 አንቀፅ 18—35

በጊዜ ቅደም ተከተል የተጠቃለሉ የትረካ አንቀፆች ፤ አንቀፅ 19 በተለይ ፤ ለየብቻቸው ሆነው በተደረደሩ አረፍተ ነገሮች (የተሰረዘባቸውን አ/ ነገሮች ተመልከት ) ተያይዘው ፤ በተዛዘሉ ሀረጎች (በሰረዛሰረዝ የተለዩትን ተመልከት) እና በመጠይቅ አ/ ነገሮች አማካይነት ፤ ድርጊያዎች በባህሪ ላይ የሚያስከትሉትን ለውጥ ለመጠቆም የተሞከረበት ።

2.5 አንቀጽ 36—40

የጭውውት አንቀፆች ፤ ስድስተኛውን አቢይ ድርጊያ (የአንዳርጌ ባህሪ መለወጡንና አዲስ የህይወት መመሪያ መከተል ያለበት መሆኑን መገንዘቡን) ስለሚስሉ ፤ ትልሙን ወደፊት ያራምዳሉ።

3. የጊዜ ገደብ

3.1 የታሪኩ አንቀፆች አኳኋን

አንቀፅ 1— ታሪኩ የተጀመረበት ወቅት (ሀላፊ ጊዜ)

እንቀፅ 2—ታሪኩ ከመጀመሩ በፊት ስለ ነበረው ሁኔታ (የሀላፊ - ሀላፊ ጊዜ)

እንቀፅ 3—ከሀላፊ - ሀላፊው ጊዜ እንደገና ታሪኩ ወደ ተጀመረበት በመምጣት (መሸጋገሪያ እንቀፅ)

እንቀፅ 4—6 —እንደገና በጊዜ ሂደት ወደ ኋላ በመመለስ

እንቀፅ 7—40 —እንደገና ደግሞ ወደፊት በመምጣት

ባጠቃላይ፣በንኡስ ቁጥር 7.1.1(ለ) እንደ ተመለከተው ታሪኩን ከወደ መካከሉ በመጀመርና ከዚያም ወደ ኋላ ተመልሶ እንደገና ወደ ጀመረበት ጊዜ ወደፊት በመምጣት የተተረከ ፅሁፍ ነው (ሁ ሀ ሂ . . .)

## 3.2 የኋሊት መተረኪያ ዘዴዎች

በዚህ አይነት ታሪኩ ከመጀመሩ በፊት የነበሩትን ሁነታዎች ወደ ኋላ ተመልሶ ለማሟላት፣ በቀጥታ ከተራኪው ግምባር የሚደረገው የማጠቃለል ገለፃ አንደኛዉና በብዛት የሚሰራበት ዘዴ ነው ። ሌሎቹ ዘዴዎች ደግሞ፣ ቅድመ-ድርጊያዎችን

(ሀ) ሁለት ወይም ሶስት ገፀ-ባህርያት እንዲወያዩባቸው ማድረግ፣ ወይም

(ለ) ጉዳዩ በቀጥታ የሚመለከተው ገፀ-ባህሪ በትውስታ ወይም በትዝታ አይነት እንዲታወሰው ማድረግና ከሱ ግምባር መመዝገብ፣ ወይም



(መ) ከታሪክ ማህደር፣ ከማስታወሻ ደብተር ከጋዜጣና ከመሳሰለው ያገኙት አስመስሎ ማቅረብ ፣ ወይም

(ሰ) በጊዜው ከተፃፉ ደብዳቤዎች እና ከመሳሰሉት መጥቀስ ናቸው ።

ታሪኩ ከተጀመረ በኋላ የኋሊት ተመልሶ የሚደረግ ማንኛውም ማሟያ ትረካ፣ ሁነታዎች በእውኑ አለም በተግባር ከፈጀባቸው የጊዜ መጠን እጅግ በጣም ባነሰ የጊዜ ገደብ አጠቃሎ ባጭሩ ለማቅረብ ስለሚያስችል ፍቱን የሆነ የታሪክን ሂደት ማፋጠኛ ዘዴ ነው ።

## 4. የታሪኩ ትልም

4.1 ትልሙ ውስብስብ ነው ።

- በአንዳርጌና በቤተሰቡ መካከል ፤
- በአንዳርጌና በህብረተሰቡ (አሰሪውና አካባቢው) ፤
- በአንዳርጌ ውስጥ በተነሱ ሁለት ሀይላት መካከል (መስሎን ልሽጠው አልሽጠው) ፤

4.2 ቅራኔውን የሚቀሰቅስ ሀይል አለው ።

አንዳርጌ የሚወደውን ውሻ ለማቆየት ያለው ፍላጐት፤

4.3 ትልሙ በሰንሰለታዊ ተዛምዶ የተጎነጎነ ነው ።

4.3.1 እያንዳንዱ ሁነታና ድርጊያ ትልሙን አንድ እርምጃ ያራምደዋል ። (አንዳርጌ ውሻ አገኘ ፤ ውሻው ከቤተሰቡ ጋር ቅራኔ ፈጠረበት ፤ ስራ ያዘ ፤ ስራ አጣ፤

ውሻውን የሚያበላው አጣ፤ ውሻው ልጅ አስደነገጠ፤ አንዳርጌ ውሻውን ይጣድሉብኛል ብሎ ፈራ ፤ ውሻውን ሸጠ ፤ ወዘተ...)

4.3.2 ማንኛውም የትልም ሂደት የሚያራምዳቸው የገፀ-ባህሪ ድርጊያዎች ፣ ከገፀ-ባህሪው ውለኛ ባህሪ የሚመነጩ መሆን ስላለባቸውና በዚህ ታሪክ ውስጥ የተገለፁት እርምጃዎችም የተወሰዱት አንዳርጌ ከሚያራምደው ውለኛ ባህሪ (ብቸኛነቱንና አለኝታ የለሽነቱን ከሚቋቋምበት ለውሻው ካለው ፍቅር) አንፃር በመሆኑ፣ ታሪኩ ተአማኒነት አለው ።

## 4.4 የትልሙ ጥድፊያና ዘገምታ

አንዳርጌ ከስራ ከወጣበት አንስቶ ውሻው ልጁን እስካስደነገጠበት ጊዜ ያለው ሁኔታ ዘገምተኛ ነው፤እምብዛም እንቅስቃሴ ስላልነበረበት ። በዚህ ወቅት የተመለከቱት አንዳንድ ንኡሳን ድርጊያዎች (አጅ ፣ ስራ ለማግኘት ያደረጋቸው ዝርዝር ጥረቶች) ቢወጡም አበይት መሸጋገሪያዎቹን ስለማይነኩ ጉዳት አያመጡም ።

## 4.5 ትልሙ ልባንጠልጥልነት አለው

- አንዳርጌ ውሻውን ለመመገብ የሚያስችለው ስራ ያገኛል/አያገኝም ?
- መስሎ አሳዳጊውን ፈልጎ ይመጣል/አይመጣም ? አንዳርጌ ተስፋ ይቆርጣል/ተስፋ ይገዛል ? (መስሎን ሳዲሱ ጌታውም ከሚያሳየው ፍቅር አንፃር ሲገመግመው) ...ወዘተ...



## 5 የታሪኩ ነባር መዳረጊያዎችና ሁነቶች

### 5.1 ነባር መዳረጊያዎች

ነባር መዳረጊያዎች በታሪኩ ውስጥ የሚሳተፉት ገፀ - ባህርያት ማንነትና ታሪኩ የሚሰራበት (የታሪክ ሜዳ) ምንነት የተገለፀባቸው ናቸው ፤ በዚህ ታሪክ ውስጥ እንደምንመለከተው።

#### 5.1.1 ገፀ - ባህርያቱ

አንድ ሰውና አንድ እንሰሳ (አንዳርጌና መስሎ) እና

#### 5.1.2 የታሪኩ ሜዳ

- መርካቶና የአሜሪካ ሰፈር
- የእንጨት መሰንጠቂያ ቤት

ናቸው ። ገለፃዎቹ የቀረቡት ስለ ገፀ-ባህርያቱ እና ስለ ታሪኩ ሜዳ በመንገር ሳይሆን ገፀ-ባህርያቱንና የታሪኩን ሜዳ በማሳየት ነው ። የሚፈጠሩትንም ስሜቶች ቢሆን እኛው እንድንደርስባቸው ነው የተፈለገው ፤ እንዲህ እንዲህ ያሉ ስሜቶች ሊፈጥሩ ይገባል የሚል ማዘዣ አልተሳለፈም ። (ማለትም አንዳርጌ ፣ ፍቅር የለሽ ፣ አለኝታየለሽ ፣ አስከፊ ኑሮ የሚኖር ነው ወይም የመርካቶ ጀንጎል ፣ ቀፋፊ ፣ የሚያስጠላ ፣ የጭቁኖች መኖሪያ ነው የሚል አጠቃላይ ትረካ የለበትም ።) አጠቃሎ ከማቅረብ ዘርዝሮ የማቅረብ ፣ ዘርዝሮ ከማቅረብ የጉድን በመነካካት የመጠቋቆም ስልቶች ፣ አንባቢዎችን ፣ ገፀ-ባህርያቱ የሚኖሯቸውንና የታሪኩ ሜዳ የሚያሳ

ድኅትን አዝማሚያና ስሜቶች በይበልጥ እንዲረዷቸውና እንዲሰሟቸው ለማድረግ ያስችላሉ።

### 5.1.3 መከተቻ (ውላዊ) ስሜት

መዳረጊያዎች ፣ በገፀ-ባህርይነትና በታሪክ ሚዳነት ላሏቸው ባህርያትና ፋይዳ ብቻ አይገለፁም ። የታሪኩን ሂደት ስሜት በማቀፋቸውም ጭምር እንጂ ። በታሪኩ ውስጥ እንደምንመለከተው በመዳረጊያዎቹ ውስጥ እንዲከተቱ የታሰቡት ስሜቶች ፣

- የብቸኝነት ፣ የአለኝታቢስነትና የተስፋቢስነት ስሜት ፣
- የፍቅር ስሜት እና
- የቁራጥነት ስሜት ናቸው ።

በመጀመሪያዉ ስእላዊ አንቀፅ እንደምንመለከተው ፣ ሁኔታዎች ተሰባስበው (ሰካራምና ተደባዳቢ አባት ፣ አቅመቢስ እናት ፣ ርህራሄ የሌለው ታላቅ ወንድም ፣ የተስፋ ጭላንጭል የማይታይበት ሰፈር ... ወዘተ ...) ገፀ-ባህሪውን (እንዳርጌን) እርምጃ እንዲወስድ (ሰዋዊ ፍላጐቱን የሚገልፅበት መንገድ እንዲፈልግ ፣ ሌላ ቢያጣ ውሻ እስከማሳደግ እንዲደርስ) ያደርጉታል ። የወሰደው እርምጃ በሱና በውሻው መካከል ጠንካራ ፍቅር ያሳድራል ። ጠንካራ ፍቅር መመስረቱ ከታመነበት ጀምሮ ደግሞ ፣ ታሪኩ የሚራመደውና አንድነትና ታማኝነት የሚኖረው እንዳርጌ ለውሻው ባለው ጠንካራ ፍቅር (ከዚህም የተነሳ በሚኖረው ፍላጎትና በሚቀሰቀሰው



ደራሽ (ድንገተኛ) ሀይል ምክንያት ይሆናል ። በመጀመሪያዉ አንቀፅ ፣ ሁኔታዎች እንዳርጌን የሆነ እርምጃ እንዲወስድ እንዳስገደዱት ሁሉ ፣ እንዳርጌ ውስጥ ያደረቀው ፍቅር ደግሞ ሌሎች እርምጃዎችን እንዲወስድ ያደርገዋል ።

## 5.2 ሁነታዎች

ሁነታዎች ሁለት አይነቶች (የማድረግ ሁነታዎችና የመደረግ ሁነታዎች — ገፀ-ባህሪና የታሪክ ሚዳ አንድ ነገር ሲያደርጉ ወይም ሲሆንባቸው) እንደሆኑና በአብዛኛው አካላዊ ፣ ንግግራዊና ሀሳባዊ ድርጊያዎችን ፣ በተጨማሪም በቃላት ለመግለፅ የሚያዳግቱ የስሜት ፣ የስማት (sensation) እና የጢነት (perception) ድርጊያዎችን (ገፅ 272 እስከ 273 ተመልከት) እንደሚገፉ ተመልክተናል ። ከዚህ በታች ደግሞ በተግባር እንመረምራቸዋለን ።

### 5.2.1 እያንዳንዱ ሁነታ መጀመሪያና መጨረሻ አለው ፤

አጅ ፣ "እንዳርጌ . . . . አንድ ውሻ አገኘ" የሚለውን አባባል ብንወስድ ፣ እንዳርጌ አውቆም ሆኖ ሳያውቅ ውሻ ለማግኘት ፈልጎ ፣ ፍላጎቱ እንደ ተሳካለት ነው የሚያሳየን ። ፍላጎቱ ተነሳበት ፤ ፍላጎቱ ተፈፀመለት ።

### 5.2.2 እያንዳንዱ ሁነታ ከጠቅላላው ትረካ አንፃር መጀመሪያና መጨረሻ አለው ።

"እንዳርጌ . . . . . አንድ ውሻ አገኘ" የሚለው አባባል "እንዳርጌ ውሻውን ያገኘበት ቦታ ትቶት ሄደ" ወይም "እንዳርጌ ውሻውን

እቤቱ ወሰደው" ወይም "እንዳርጌ ውሻውን ሊወስድ ሲል ባለቤቶቹ ደረሱበት" ... ወዘተ... የሚሉትን ሌሎች የሁነት ሂደቶች በመጠቀም ያበቃል ። በዚህ አይነት እያንዳንዱ ሁነት የራሱ የሆነ ግብና ትርጉም እና የአጠቃላይ ትረካው ግብና ትርጉም ይኖረዋል ማለት ነው ።

5.2.3 አንድ ሁነት ከሌላ ሁነት ጋር እየተዛመደ ከፍ ያለ ትርጉም እንዲያስገኝ ሆኖ ሲገነባ ደግሞ ፣ (እያንዳንዳቸው የተሟላ ሁነት እንደሆኑ ሁሉ) ጉንጉኑ የራሱ የሆነ መጀመሪያና ማከተሚያ ፣ የራሱ የሆነ አንድነትና የራሱ የሆነ ሙሉነት አለው — የተወሰነ ግብና ትርጉም እንዲያስገኝ ሆኖ ስለ ተቀናጀ ፣ የአንድ ድርጊያ ሂደት ተጀምሮ ስለ ተጨረሰበት ።

የታሪኩን ሁነቶች በዝርዝር እንመልከታቸው ።

5.2.4 <u>የታሪኩ ዝርዝር ሁነቶች</u>

(እንዲህ አደረገ ፣ እንዲህ ተደረገ ፣ እንዲህ ሆነ)

<u>ክፍል 1</u>

(ሀ) <u>እንዲህ ሆነ</u>
- እንዳርጌ ውሻ አገኘ ።

(ለ) <u>እንዲህ አደረገ</u>
- ውሻውን እቤቱ ወሰደው ።

(መ) <u>እንዲህ ተደረገ</u>
- ከቤተሰቡ ቅዋሜ ደረሰበት ።



<u>ክፍል 2</u>

(ሀ) <u>እንዲህ አደረገ</u>
- እንዳርጌ ስራ ያዘ ።

(ለ) <u>እንዲህ ሆነ</u>
- ታታሪ ሰራተኛ ሆነ ።
- ለውሻው የሚያበላው አገኘ ።

(መ) <u>እንዲህ ተደረገ</u>
- ከሁለት አመት በኋላ ከስራ ተባረረ ።

<u>ክፍል 3</u>

(ሀ) <u>እንዲህ ሆነ</u>
- ሌላ ስራ ማግኘት አቃተው ።
- መስሎን የሚያበላው አጣ ።

(ለ) <u>እንዲህ አደረገ</u>
- እንዳርጌና መስሎ ከሰፈሩ ወመኔዎች ጋር ተደባለቁ ።

<u>ክፍል 4</u>

(ሀ) <u>እንዲህ ሆነ</u>
- እንዳርጌ ወመኔ ሆነ ።
- መስሎ ሌሎች ሰዎች መልመድ ጀመረ ።

(ለ) <u>እንዲህ አደረገ</u>
- መስሎ የሀብታም ጎረቤት ልጅ አስደነገጠ ።
- እንዳርጌ ለመስሎ ህይወት ተቋቋመ ።

### ክፍል 5

(ሀ) <u>እንዲህ ሆነ</u>

- እንዳርጌ መስሉን ይገድሉታል ብሎ ፈራ ።

(ለ) <u>እንዲህ አደረገ</u>

- መስሉ በህይወት የሚኖርበትን መንገድ ፈለገ ።
- መስሉን ለሀብታም ልጅ ሸጠ ።

### ክፍል 6

(ሀ) <u>እንዲህ ሆነ</u>

- እንዳርጌ ወመኔነቱን ቀጠለ ።
- መስሉን መርሳት ጀመረ ።
- ከብዙ ወራት በኋላ መስሉን ከአዲሱ ጌታው ጋር አገኘው ።

(ለ) <u>እንዲህ አደረገ</u>

- መስሉን በስሙ ጠራው ።

(መ) <u>እንዲህ ሆነ</u>

- መስሉ አሳዳጊውን አወቀው ።
- መስሉ ያሳዳጊውን እጅ ላሰው ።

(ሰ) <u>እንዲህ ተደረገ</u>

- ውሻውን እንዳይነካ ፣ ውሻው የሱ እንዳል ሆነ ተነገረው ፣ ባዲሱ ባለቤት ።
- አዲሱ ጌታው መስሉን ባዲሱ ስሙ ጠራው ።



(ረ) <u>እንዲህ ሆነ</u>

- ውሻው ወዳዲሱ ጌታው ሮጠ ።
- የአዲሱን ጌታውን እጅ መላላስ ጀመረ ።

(ሸ) <u>እንዲህ አደረገ</u>

- እንዳርጌ ፊቱን አዞረ ።
- እመንገዱ ገባ ።

### ክፍል 7

(ሀ) <u>እንዲህ ሆነ</u>

- እንዳርጌ አዲስ እውነታ ተገለፀለት ።
- እንዳርጌ ስራ ፍለጋ ጀመረ ።
- እዱሮ ቦታው ስራ አገኘ ።

(ለ) <u>እንዲህ አደረገ</u>

- ለተገለፀለት እውነታ ከዱሮው በበለጠ ታታሪነት መስራት ጀመረ ።

5.2.5 ከላይ በዝርዝር እንደ ተመለከትነው ፣ ብዙ ጊዜ ሁነታዎች በቀላሉ <u>በእንዲህ ሆነና</u> <u>በእንዲህ ተደረገ</u> ይጀምሩና የሚፈፀሙት በድርጊያ ነው ። ሆኖም፣ <u>በሆነና</u> <u>በተደረገ</u> በቀላሉ ይጀምራሉ ሲባል እንዳፈቀደ — ማለትም አንድ አይነት አዝማሚያ ላይ በማይደርሱ ሁነታዎች ሁሉ ይገነባሉ — ማለት አይደለም ። እያንዳንዳቸው ሙሉና ትርጉም ያላቸው ተጎናኝ ሁነታዎች የሚጀምሩት ፣ ነገሮች ሲዋልሉና ወደ አንድ በኩል በማጋደል ሲታኑ እማይችሉበት ደረጃ ላይ መድረሳቸው ሲታይና ሲታወቅ ነው — አንድ አይነት ዝመት ላይ ሲደርሱ ።

ለምሳሌ ፣ እንዳርጌ በአስር አመት እድሜው ፣ የተስፋ ጭላንጭል በማይታይበት ሰፈር ውስጥ ፣ ከስካራምና ተደባዳቢ አባት ፣ አቅመቢስ እናት ፣ ተንኮለኛና ርህራሄ የሌለው ታላቅ ወንድም ጋር ፣ ፍቅርና አለኝታ በሌለበት አካባቢ መኖሩ ፣ ዘላቂነት እንደማይኖረው ከአገላለፁ እንረዳለን ። ዝመቱ ለአንድ አይነት ለውጥ ዝግጁ እንደሆነ እናጤናለን።

በዚህ አይነት የሁኔታዎች አመጣጥ የተገነባው ትረካ ደግሞ ፣ የሚቋጨው (በየደረጃውም ቢሆን) ሲዋልሉ የነበሩት ሁኔታዎች፣ ለጊዜውም ቢሆን(በተራቸው መዋለላቸው ስለማይቀር) የሚረጉበት መቋጫ ያገኙ መሆናቸው ሲታወቅ ነው ።(ለምሳሌ ፣ እንዳርጌ ውሻውን በማግኘቱ እንደተቋጨው አይነት።) ስለዚህም፣ የውሻው መገኘት ወቅታዊና እንዳርጌም ሰዋዊ ፍላጎቱን ለማሟላት መፈለጉ ተገቢ በመሆኑ ፣ የዋለለውን ያረጋዋል ብለን በማመን እንቀበለዋለን።

## 6. የታሪኩ መልእክት

ታሪኩ ውሻው ሲሸጥ ቢያቆም ኖሮ አንባቢው ፣ ትረካው ሊያስገነዝብ የሚፈልገውን ትክክለኛ ትርጉም ሊያጤነው ይችላል ። ግፋ ቢል ለልጁ ያዝን ይሆናል ። ምናልባት ልጁ ውሻውን ያጣው ከድህነቱ የተነሳ ነው የማለት ግንዛቤ ያሳድር ይሆናል ። እንደዚህ አይነቶቹ ስሜቶችም የትረካው መልእክት ናቸው ተብለው ይወሰዱ ይሆናል ። ዳሩ ግን ፣ ማንኛቸውም ቢሆኑ ጥርት ብለው እንዲታዩ አልሆኑም ። አንባቢው በፅሁፉ በትክክል ምን ሊባል እንደታሰበ እርግጠኛ ሊሆን አይችልም ። በትረካው ያልተሟላ አይነት ስሜት ነው የሚያድርበት ።

የእንዳርጌንና የዘውዴን መገናኘት የሚተርከው ክፍል ሲጨመርበት ግን፣ ፅሁፉ እንዲኖረው የታሰበውን አቅጣጫ አንባቢው በይበልጥ ሊያጤነው ይችላል ፤ የፅሁፉን ረብ



ሊገነዘበው ይችላል ማለት ነው ። በዘውዴ ፣ በውሻው ባለቤትና ፣ በእንዳርጌ ፣ ውሻዉን እንዲሁ በሚያፈቅረው አሳዳጊው መካከል የሚታየው ንፅፅር ፣ ምንም አስተያየት ሳይጨመርበት ፣ ግልፅ የሆነ መልእክት እንዳለው እንረዳለን ።

በሁለቱ ልጆች መካከል የተከሰተውም ሁኔታ ፣ በንፅፅር ከተጠቆመው በላይ ረብ ሊኖረው እንደሚችልም እንገነዘባለን ። ውሻዉ የዘውዴንም እጆች ሲላልስ አይተናል ። ይህ ታዲያ ቀደም ብለን ከጠቀስነው ጋር እንዴት ይቋጫል ። ድርጊያዉ እንዳርጌ ለውሻዉ ያለውን ፍቅር ያጎደለበትና ያጎደፈበት አይነት መስሎ ነው የሚታየው ። ሌላው ጥያቄ ደግሞ እንዳርጌ ፊቱን አዙሮ አመንገዱ ሲገባ ምን ይሆን የሚሰማው ? ምናልባት ውሻው በከዳው ጊዜ ልጁ የሚሰማውን ቅሬታ ወይም ቅያሜ ወይም ጥላቻ እንባቢዉ ያጤንለታል ። ፀሀፊዉ ግን ከዚህ የበለጠ ውጤት እንዲያስገኝለት ይሆናል የፈለገው ። ተጨባጭ ውጤት ። ምናልባት ይኸን ሁኔታ በእንዳርጌ እድገት ውስጥ ወሳኝ አይነት አደብ መግዣ ነጥብ እንዲሆን ይሆናል ያቀደው ፤ ተራ ነገር የሚመስል ፣ ነገር ግን እስከ መጨረሻዉ የህይወቱ ሂደት የሚለውጥ አይነት ። ስለዚህም “በማግስቱ መኪናን . . . ስራ ፍለጋ” በማለት ይጀምርና ፣

ሁኔታው በእንዳርጌ ላይ ያሳደረውን ውጤት ይገልፅልናል ፤ በወቅቱ የተሰማውን የቅሬታ ፣ የቅያሜና የእንጀት መቆረጥ ጊዜያዊ ስሜት ብቻ ሳይሆን ፣ ልምዱ በተፈጥሮው ውስጥ የተወውን ማህተምና ከዚህም የተነሳ የተከሰተውን ለብዙ ዘመን ለህይወቱ አቅጣጫ የሰጠውን ዘላቂና መለያ ባህሪውን ። አንባቢውም ሆነ ፀሀፊው ፣ እንዳርጌ ከልምዱ የተማረውን እውነት ነው ብለው ላይስማሙ ይችላሉ ፤ ገንዘብ የልብ ስር ነው ፤ የፍቅር ፣ የታማኝነትና የርህራሄ

መሠረት ነው ብለው ። ቢሆንም አንዳርጌ ከልምዱ የተማረው ለራሱ 'እውነቱ' ነው — ህይወቱን የሚመራበት ፣ መኖሩን የሚያውቅበትና ለመኖርም የሚፈልግበት መመሪያውና ደንቡ ሆኗል ።

ዋናዉ ነገር — አንባቢዉ ተቀበለውም አልተቀበለው — ዋናዉ ነገር ፣ መልእክቱ ቁልጭ ብሎ መተላለፉ ነው። ትረካው ሙሉ ነው ። እንዲያም ሲባል ሙሉነቱ በተራኪዉ ማጠቃለያ ወይም መደምደሚያ ስለ ተሰጠበት አይደለም። በእርግጥ መልእክቱ ፣ በአንዳርጌ ነባሪ ሁኔታ ከሚገኝ ከግንኛውም ሰው ድርጊያዎች እየተጎነጎነ በእንዲህ አይነቱ ውጤት ሊቋጭ ይችላል የሚያሰብል ታማኝነት ባይኖረው ኖሮ፣ መደምደሚያዉ መኖሩ ትረካዉን ሙሉ አያደርገውም።

በአብዛኛው ፣ ትረካዎች መልእክታቸውን በውስጠ ታዋቂነት ይተውታል እንጂ በግልፅ አይናገሩትም ። ስለ ሆነም ሙሉ ትረካ ከተከታታይ ሁነታዎቹ የሚፈለቀቅ ረብ ያለው ነጥብ ወይም ትርጉም ሊኖረው እንደሚገባ ማጤን ያሻል ።

እዚህ ላይ ፣ ሌላ ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል ። በእርግጥ ትረካዉ ሙሉ ነው ብለናል ። ይኸን ስንል ግን ፣ አንዳርጌ ልምዱ ያስገኘውን የህይወት ትርጉም አቋሙን አይለውጥም ማለት አይደለም ። ምናልባትም ትረካዉ የአጭር ታሪክ ወይም የረጅም ልቦለድ አካል ሊሆን ይችላል ። በመሆኑም ፣ አንዳርጌ ለብዙ ዘመናት ፣ ልምዱ ባስተማረው ለገንዘብ የመሞት ጠባዩ ሀብታም ፣ ከበርቴና ተፈሪ እመሆን ደረጃ ላይ ደርሶ ፣ በገንዘቡ የሚያደርገው ጠፍቶት ቅጡን በሚያጣበት ወቅት ፣ ሁሉን ነገር በገንዘብ ለማድረግ አለመቻሉን በመገንዘብ ፣ 'እውነት' ብሎ ሲመራበት የኖረው ህግ ከፍተኛ ስህተት መሆኑን እንዲ



ረዳና አዲስ 'እውነት' መግር ያለበት መሆኑን እንዲገነዘብ ሆኖ ሊቀርብ ይችላል ፤ በመኪያውም አዲሱን እውነት ሊግር ።

እንግዲህ ፣ ትረካ ሙሉና የተዋጣ ነው ሲባል ፣ ውስጠ ታዋቂም ሆነ በግልፅ የተነገረ ፣ ትረካው የሰንሰለታዊ ሁነታዎችን ትርጓሜ ይጠይቃል ። ትርጓሜው እትረካው ውስጥ በሚገኝ ባለታሪክ ፣ ለምሳሌ በአቀረብነው ታሪክ ውስጥ በአንዳርጌ አይነት ፣ ወይም በቀረቡት ሁነታዎችና መዳረጊያዎች እማካይነት በአንባቢው ፣ ወይም በተራኪው በራሱ ሊከናወን ይችላል ። በማንኛዎቹም ሁነታዎች ግን የተሟላ ትረካ እንዲኖር ትርጓሜ ይኖራል ። ይህም እስተ ባለባችን አንባቢን በድርጊያዎቹ አቀራረብ እንዲሳብና እንዲግረክ ለማድረግ ከሚበጁት መንገዶች ውስጥ አንደኛው ፣ ድርጊያው ወደ ተቋጨ መልእክት ማምራቱ ፣ መሆኑን ይጠቁምልናል ።

## 7. የታሪኩ ቅርፅ

ትረካዉ በሰባት የተከፈለ ቅርፅ አለው ።

በመጀመሪያዉ ፣ ባለታሪኩን ፣ ታሪኩ የተከናወነበትን ቦታና በተለይም ትረካዉን የሚያንቀሳቅሰውን ሁነታ ፣ የአንዳርጌን የስቃይና የፍቅር የለሽ ኑሮ እንገነዘባለን ፤ ቡችላውን እስኪያገኝ ድረስ — ይህ እንግዲህ ታሪኩን ማድሪያው መሆኑ ነው ።

ከሁለተኛዉ እስከ ስድስተኛዉ በጊዜ ቅደም ተከተል የተሰለፉ ሰንሰለታዊ ሁነታዎችን እናገኛለን — ለአንድ ግብ የተቀናበሩ ሁነታዎችንና የሚያስከትሉትን ድርጊያ — ማለትም ፣

በሁለተኛው ፤

— እንዳርጌ ውሻውን ለመመገብ የሚያስችለው ስራ ያገኛል ።

(ውሻው የህይወቱ ማእከል ይሆናል)

በሶስተኛው ፤

— ስራውን ያጣል ።

(ከሰፈሩ ወመኔዎች ጋር ይደባለቃል ።)

በአራተኛው ፤

— ውሻው የሰው ልጅ ያስደነግጣል ።

(እንዳርጌ መስሎን ይገድሉታል ብሎ ይፈራል ።)

በአምስተኛው ፤

— ውሻውን ይሸጠዋል ።

(እንዳርጌ ወመኔነቱን ይቀጥላል ፤ መስሎን ወደ መርሳት ይቃረባል ።)

በስድስተኛው ፤

— እንዳርጌ መስሎን ያገኘዋል — ከጌታው ጋር ።
(መስሎ አዲስ ስም ወጥቶለታል) ።

በሰባተኛው ፤

— እንዳርጌ እንደገና ስራ ይይዛል ።

(ትረካው ወደ አንድ ግብ ይሰባሰባል ። ህጋዊ ባለቤት በመሆንና የፍቅር ባለቤት በመሆን መካከል የነበረው የመጨረሻ ግጭት አዲስ እውነታ ይከስታል ።)



# ቃ ላ ት

## ሀ

| | |
|---|---|
| ሀሳብ | idea |
| ሀተታና ትርጓሜ | commentary |
| ሁለንታዊ | universal |
| ሁለንታዊ አዛማጅ ትርጉም | universal connotation |
| ሁነት (ኹነት) | event |
| ሁኔታ | situation |
| ህዋስ | sense |

## ለ

| | |
|---|---|
| ልምድ | experience |
| ልቅ አረፍተ ነገር | loose sentence |
| ልባንጠልጣይነት | suspense |
| ለዋጭ ባለታሪክ | dynamic character |
| ልዉኛ አረፍተ ነገር | effective sentence |

## መ

| | |
|---|---|
| መልእክት | message |
| መመፃደቅ | moralizing |
| መተርጎምና ማቃናት | interpret and justify |
| መነሻ ደጀን | utilitarian setting |
| መጠሪያ (ስያሜ) | term |
| ረቂቅ-መጠሪያ | abstract term |
| ብቸኛ መጠሪያ | specific term |
| ከቋርጌ መጠሪያ | concrete term |
| የተናጠል (እየቅል) መጠሪያ | particular term |
| ጥቅል (ወል) መጠሪያ | general term |
| ሙሉ-በከፊል | synecdoche |
| ማጠቃለያ | generalization |

| | |
|---|---|
| ምሳሌ (አስረጂ ፣ አብነት) | example |
| ምስል | image |
| ምክንያታዊ ተዛምዶ | generalization |
| ምጥን አረፍተ ነገር | balanced sentence |
| ምፀት | irony |
| አሳዛኝ ምፀት | tragic irony |
| **ሰ** | |
| ሰበካ | preaching |
| ሰዋዊ ቅርበት ያላቸው (የቃላት) | words charged with heightened human content |
| ሰውኛ | personification |
| ሰፊ አቀማጅ ትርጉም | common connotation |
| ሴማ | theme |
| ስልት | system |
| የድልደላ (ምደባ) ስልት | classification |
| የምሳሌ ስልት | illustration |
| ስሜት | feeling, emotion |
| ስሜት ቀስቃሽ (ኮርኳሪ) | emotive |
| የስሜት አውታሮች (ህዋሶች) | sense organs |
| ስሜት ፈንጣቂ ደጀን | symbolic setting |
| ስብስብ | collection |
| የአወዳዳሪ፣ የአነፃፃሪ፣ የአዳዳኝ ፈሊጦችና የመሳሰሉት ስብስብ | collection of rhetorical cliches and florid language and the like |
| ስነ-ፅሁፍ | literature |
| ስያሜ (መጠሪያ) | term |
| ስለዚህ እንዲህ (ምክንያትና ውጤት) | cause and effect |



| | |
|---|---|
| **ረ** | |
| ረቂቅ መጠሪያ | abstract term |
| ረብ (ፋይዳ) | value |
| ርእሰ ነገር | subject |
| **ቀ** | |
| ቃላትና ውክልናቸው | words and their functions |
| ቅርፅ | structure |
| በሰዋስው ቅርፃቸው | by grammatical structure |
| በኪነ-ፅሁፍ ቅርፃቸው | by rhetorical form |
| ቅድመ-ጥቆማ | foreshadowing |
| ቅጥንብር (ቅጥ ተሁብር) | form |
| **በ** | |
| ባህርይ | characteristic |
| ዋነኛ ባህርይ | dominant characteristic |
| ባለታሪክ (ገፀ-ባህሪ) | character |
| ነጠላ ባለታሪክ | flat character (one dimensional) |
| ውስብስብ ባለታሪክ | round character (two dimensional) |
| ብቸኛ መጠሪያ | specific term |
| **ተ** | |
| ተምሳሌት | metaphor |
| የተምሳሌት ግነት (የተጋነነ) | inflated metaphor |
| ተራኪ | narrator |
| የተራኪ አኳያ | narrator's point of view |
| ተነፃፃሪ | contrast |
| የጋነ ተነፃፃሪ | inflated contrast |

| | |
|---|---|
| ተደራጊ | happening |
| ታሪክ | story |
| የታሪክ ግዛ | setting |
| ትልም | plot |
| ትረካ | narrating |
| የትረካ ድምፅ | narrator's voice |
| ትርክት | episode |
| ትርጉም የለሽ ፀጉር ሰንጠቃ | nonsensical hair splitting |
| ትርጓሜ | definition |
| ሀተታና ትርጓሜ | commentary |
| ትኩረት (ጠንቅ) | perception |

## አ

| | |
|---|---|
| አስረጅ (አብነት ፣ ምሳሌ) | example |
| አስተያየትና ግምት | judgement |
| አረፍተ ነገር | sentence |
| ልቅ አረፍተ ነገር | loose sentence |
| ልጡኛ | effective sentence |
| ነጠላ አረፍተ ነገር | simple sentence |
| ድርብ አረፍተ ነገር | compound sentence |
| ድብልቅ ,, ,, | complex sentence |
| ድርብ ድብልቅ አረፍተ ነገር | compound-complex sentence |
| ዝግ አረፍተ ነገር | periodic sentence |
| አብነት (አስረጅ) | example |
| አትኩሮት | concentration |
| አነፃፃሪ ፈሊጦች | figures of contrast |
| አንበቶ መጣል | overstatement |
| አንቀፅ | paragraph |
| አንፃር | simile |
| አእምሯዊና ልቦናዊ ደጀን | inner setting |
| አገልግሎት | function |



| | |
|---|---|
| በአገልግሎት | by function |
| አወዳዳሪ ፈሊጦች | figures of comparison |
| አዋቂ ኩሉ ተራኪ | omniscient narrator |
| አውደ ጥበብ | encyclopedia |
| አዛማጅ (ተጠሪሪ) ትርጉም | connotation |
| ሁለንታዊ አዛማጅ ትርጉም | universal connotation |
| ሰሬ አዛማጅ ትርጉም | common connotation |
| ውሱን አዛማጅ ትርጉም | unique connotation |
| አይለወጤ ባለታሪክ | static character |
| አጓዳኝ ፈሊጦች | figures of association |
| አኳያ ( ግምባር ) | point of view |
| የተራኪ አኳያ | narrator's point of view |
| ከአይን የማየት አኳያ | perceptual point of view |
| የአእምሮ ልምድ አኳያ | conceptual point of view |
| የፍላጎት ሂደት አኳያ | interest point of view |
| አሳቤ | concept |
| እውነታ | reality |
| አጥርጥር | summary |
| እንዲህ - ስለዚህ | effect to cause |
| እንጥብጥብ | |
| ከእንዲህ - እንዲህ | effect to effect |

## ከ

| | |
|---|---|
| ክቻርኔ መጠሪያ | concrete term |
| ከያኒ | artist |
| ኪነ-ፅሁፍ | creative writing |
| ክፋል-በሙሉ | synecdoche |
| ኪናዊ | artistic |
| ክሊሼ | cliches |
| የሰለቸ ክሊሼ | worn-out cliches |
| የወሸነኔ ክሊሼ | romantic cliches |

ኸ

ኹነት — event

ወ

ወለለት — echo
ወካይ — symbol
  ተወካይ — referent (individual object)
ዋነኛ ባህሪ — dominant characteristic
ዋናዊ (መከተቻ) ስሜት — dominant emotion
ውሱን አዛማጅ ትርጉም — unique connotation
ውሱን አዋቂ-ኩሉ ተራኪ — limited omniscient narrator
ውስብስብ ባለታሪክ — round character (three dimensional)

ዘ

ዘመድ አዛማጅ ትርጉም — figurative meaning
ዘማች — metonymy
ዘዬ (የአፃፃፍ) — style
ዝግ አረፍተ ነገር — periodic sentence

የ

የተንዛዛ — long-winded
የአፃፃፍ ዘዬ — style

ደ

ድረታ — redundancy
ድርጊያ — action
ድርግ — act



ገ

ግነት (የግነ ምስል) — hyperbolic image
ግላዊ ትርጉም — denotation
  ግላዊ ነጠላ ትርጉም — single denotation
  ግላዊ ድርብርብ ትርጉም — multiple denotation
ግምባር (አኳያ) — point of view
ግርምታ — surprise

ጠ

ጥቁ ማንሳት — understatement
ጥምርነት — fusion
ጥቅል (ወል) መጠሪያ — general term
ጥቅልና ረቂቅ ፅሁፍ — abstraction
ጥቅም — value

ፈ

ፋይዳ — value
ፌዛዊ ድባብ — ironic setting
ፍቺ — interpretation